<u>መናፍቃን</u>

Yisak Gese

ማንቀላፋቱ ይበቃል! !

የቅዱስ ሲኖዶስ አስደሳች ውሳኔ

1/ቃለ አዋዲ እና ታዖሎንስ በቤተ ክርስቲያን ስም እንዳይነገዱ በቅዱስ ሲኖዶስ ተወስኖባቸዋል ከዛ ባሻገር ቤተ ክትስቲያን የራሷ የሆነ 24 **ሰዓት አገልግሎት የሚሰጥ የቴሌቭን ስርጭት እንደምትጀምር በቅዱስ ሲኖዶስ ተገልጿል ማንኛውም ተቋም በቤተ ክርስቲያን ስም በየአዳራሹ መሰብሰብ እንደማይችል ተወስኗል እግዚአብሄር ፍጻሜውን ያሳምርልን**

ፀረ ሀራ ጥቃ

በፀረ ሀራጥቃ (መናፍቃን) ዙሪያ የተጀመረው እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሁሉም ህዝበ ክርስቲያን ቁጭት እየሆነ በመምጣቱ ውጤት ማስገኘት ጀምሯል ጥቂቶች የፕሮቴስታንቱ ተልእኮ እና ጥፋት የገባቸው መጨህ ከጀመሩ ሰንብተዋል ነገር ግን ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ብዙኃኑ ተኝቶ የነበረ ቢሆንም ጊዜውን ጠብቆ የፕሮቴስታንት ተሀድሶ መናፍቃን የለቀቁት ግልጽ የሆነ ቤተ ክትስቲያንን የማጥፋት ዘመቻና ውድ በሆኑ በተዋህዶ የቁርጥ ቀን ልጆች ያላሰለሰ ጥረት ጉዳዩ የሆሉም በመሆኑና ተቃውሞው በመበርታቱ አስከ ላይ ቅዱስ ሲኖዶስ ድረስ ትኩረት እንዲያገኝና መስመር እንዲይዝ ሆኗል

ጮኸን እንዳልጮህን አልተቆጠርንም

የክርስቶስ ቤተሰቦች ውድ የተዋህዶ ልጆች ከሃይማኖታችን የሚበልጥ

አንዳች ነገር የለምና የጀመርነውን ቤተ ክትስቲያናችንን የመጠበቅ ድርሻ በብቃትና በንቃት ሆነን ከጸሎት ጋር ልንቀጥል ይገባል በተለይ ባለማወቅ የአጥፊው ቡድን በመደገፍ እየጠፉ ያሉ የተዋህዶ ልጆችን በማስተማር መመለስ ያስፈልጋል ጥቂት መናፍቃን ኦርቶዶክስ በመምሰል በየ ግሩፑና በየ ፌስቡኩ አጥፊዎችን በመደገፍ እውነተኞች እንደ ሆኑ ከንቱ ልፍለፋን በማሰማት እንደሚያወናብዱ ይታወቃል ስለዚህ የሰይጣንን ተንኮል ተረድተን ቅድስት ቤተ ከወርስቲያናችንን ከምን ጊዜውም በላይ እንጠብቃት በፀረ ፕሮቴስታንት ተሀድሶ ጥምረት በየሳምንቱ ማክሰኞ የምእመናንን ግንዛቤ ለማስፋት እየተዘጋጀ የሚቀርበውን ሰፋ ያለ በመረጃ የተደገፈ ትምህርት በዩቱብ (ሀራ ጥቃ 001- 004) ድረስ የተለቀቀውን ጥናታዊ ጽሁፍና ትምህርት በመከታተል እራሳችንን በመንፈሳዊ እውቀት በመሙላት ከሚመጣብን የሰይጣን ፈተናና የሀራ ጥቃ (መናፍቃን) ጥቃት እንጠብቅ እግዚአብሄር ለሀገራችን ሰላም ይስጥልን ሀገርን በጸሎቷ ዘውትር የምትጠብቀውን ሃይማኖታችንን ከከሀድያን ስውር ደባና ጥፋት ይጠብቅልን እመቤታችን በረድኤት አትለየን በምልጃዋ ትጠብቀን አሜን

ዲ/ን ይስሐቅ ዓለሙ

2/ ተሀድሶ ክፍል ፭

በቀሲስ ደጀኔ ሽፈራው..

ካለፈው የቀጠለ

የጽድቅና የሕይወት አገልግሎት፤

የአዲስ ኪዳን አገልግሎት የጽድቅና የሕይወት አገልግሎት ነው።ምክንያቱም፦ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ፈሳሽነት ሁሉን ነገር አዲስ አድርጐታልና ነው። “ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፤” ያለው ለዚህ ነው። ማቴ፡፳፮፥፳፰። በዚህም፦ የአዲስ ሕግ የወንጌል፥የአዲስ ርስት የመንግሥተ ሰማያት መጽኛ ፥ በመስቀል ላይ የሚፈሰው የእርሱ ደም መሆኑን፥ዓርብ ሊሰቀል ሐሙስ ማታ ተናግሮአል። ሞትን እና ኩነኔን ያመጣብንን የአዳምን ኃጢአት በመስቀል ላይ በፈጸመው ቤዛነት በመደምሰሱ (በማስወገዱ)፥ ጽድቃችን፦ የሞት አገልግሎት፣ የመርገም ጨርቅ መባሉ ቀርቶልናል። በመሆኑም፦ ስንዴ ዘርቶ እሾህ ማጨድ፥ደክሞ መና መቅረት፥ ወደ ሲኦልም መንጐድ፥ ያለፈ ታሪክ ሆኗል። ጌታችን በወንጌል፦ “ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ሐሴትም አድርጉ፤ . . . የሰው ልጅ(በተዋህዶ ሰው የሆነ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ) ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር (ከባህርይ አባቱ ከአብ ጋር እኩል በሆነ ጌትነቱ) ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤” በማለት የነገረን ለዚህ ነው። ማቴ፡፭፥፲፪፣፲፮፥፳፯። ዋጋችን ደመወዛችን በሰማይ እንደሚቆየን በአማናዊ ቃሉ ሲያስተምረንም፦ “እናንተን (ቅዱሳንን) የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥እኔንም የሚቀበል የላከኝን (አብን መንፈስ ቅዱስን) ይቀበላል። ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር (በቅዱሳን) ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም።

. . . እውነት እላችኋለሁ፥ እናንተስ የተከተላችሁኝ፥በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ(በተዋህዶ ሰው የሆነ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ) በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት (በጌትነቱ በሚገለጥበት) ጊዜ፥እናንተ ደግሞ (በተዋህዶ ሰው የሆንኩ የባህርይ አምላክ መሆኔን ያመናችሁ) በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ (በእስራኤል ዘሥጋ በአይሁድ፥ በእስራኤል ዘነፍስ በክርስቲያኖች ላይ) ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ። ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ (ፍጹም ዋጋ) ይቀበላል፥የዘለዓለምን ሕይወት ይወርሳል።"ብሎናል። ማቴ፡ ፲፱፣፲፱፥፳፰።ቃሉ እንዲህ ቢልም አንዱን እንኳ ትተን ልንከተለው አልቻልንም፥ ቅዱሳን ግን ሁሉን ትተው በመከተል ባለ ዋጋ ሆነዋል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ደማቸውን እስከ ማፍሰስ ድረስ የጸኑት ሁሉ፥ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ወደ ሲኦል ቢወርዱም በረድኤተ እግዚአብሔር ተጠብቀዋል። በዚያን ዘመን በሃይማኖት ምክንያት ስለፈሰሰ የቅዱሳን ደም፥ጌታችን በወንጌል፡- ጻፎችንና ፈሪሳውያንን ሲወቅስ፥ "ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችሁ (ይፈርድ ባችሁ) ዘንድ።"ብሏል። ማቴ፡፳፫፥፴፭። በአዲስ ኪዳን ዘመን ደግሞ እንኳን የሰማዕትነት ደም፥ በቅዱሳን ስም የተዘከረ ቀዝቃዛ ውኃ እንኳ የማይጠፋ ዋጋ እንደ አለው ነግሮናል። ቆርሶ ማጉረስ፥ ቀድዶ ማልበስ፥ቀድቶ ማጠጣት፥የታመመ መጠየቅ፥የታሰረ መጐብኘት፥በጌታ ቀኝ የሚያቆም፥"እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ዓለም ሳይፈጠር

የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ትወርሱ ዘንድ ኑ።" የሚለውን ቃለ ሕይወት የሚያሰማ ሆኗል።ማቴ፡ ፳፭÷፴፬።ቅዱሳን ይህችን ሀገር በሃይማኖት ፊት ለፊት እያዩ በማገልገላቸው÷"ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ÷በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘለዓለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለ እናውቃለን። . . . ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃል እንጠብቃለን። . . . አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርንም አየሁ÷ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና ÷ባሕርም ወደ ፊት የለም።ቅድስቲቱም ከተማ አዲስቱ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ÷ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።"ብለዋል።ፎኖ፡ቆሮ፡፭÷፭፣ ፎኖ፡ጴጥ፡ ፫÷፲፫፣ራዕ፡፳፩÷፭።ከነቢያት እነ ኢሳይያስም ፡-"እነሆ÷አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁና፤(ፈጥሬ አዘጋጅቼ አለሁና፤) የቀደሙትም አይታሰቡም÷ወደ ልብም አይገቡም።ነገር ግን በፈጠር ሁት(ፈጥሬ ባዘጋጀሁላችሁ) ደስ ይበላችሁ÷ለዘለዓለምም ሐሤት አድርጉ።"የሚለውን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሲያስተጋቡ ኖረዋል። ኢሳ፡፷፭÷፲፯።

በብሉይ ኪዳን ዘመን መሥዋዕቱ እና መሥዋዕት አቅራቢው ሙታን ሲሆኑ÷መሥዋዕት ተቀባዩ እግዚአብሔር ብቻ ሕያው ነበር።በአዲስ ኪዳን ዘመን ግን÷ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥስቱንም ሆኖ ተገኘ።ሕያው መሥዋዕት÷ሕያው መሥዋዕት አቅራቢ÷ ሕያው መሥዋዕት ተቀባይ እርሱ ሆነ።ሕያው መሥዋዕት በመሆኑ÷"ሥጋዬን የሚ በላ÷ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤" አለ።ዮሐ፡ ፮÷፶፫።በመሆኑም የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ማታ ÷ሥርዓተ ቍርባንን ለደቀ

መዛሙርቱ ባስተማራቸው ጊዜ÷ጎብስቱን ለውጦ ሥጋ መለኮት÷ ወይኑንም ለውጦ ደመ መለኮት ካደረገው በኋላ አቀርቧቸዋል። ፈጽሞ መለወጡንም ሲነግራቸው፡-“ጎብስቱን አንሥቶ ባረከ÷ቈርሶም ለደቀ መዝሙርቱ ሰጠና፡- እንካችሁ÷ብሉ፤ይህ ሥጋዬ ነው አለ።ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው÷ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ስለ ብዙዎች ለኃጢ አት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው÷አላቸው፤” ይላል።ማቴ፡ ፳፮÷፳፮። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፡-“ስለዚህ ሳይገባው (ንስሐ ሳይገባ ወይም ሳያምን) ይህን ጎብስት የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን (ሰውነቱን በካህን አስመርምሮ ንስሐ ይግባ)÷ እንዲሁም ከጎብስቱ ይብላ÷ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና።” ብሏል። ፩ኛ፡ቆሮ፤፲፩÷፳፯። በመሆኑም አንድ ጊዜ ተሠውቶ÷ሕያውና ዘለዓለማዊ የሆነ መሥዋዕት ሥጋውንና ደሙን ስለሰጠን÷ዕለት ዕለት የምንቆርበው ቅዱስ ቊርባን አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም እንደሆነ እናምናለን።

ሕያው መሥዋዕት አቅራቢ በመሆኑም÷“ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለ ሁና÷ስለ ዚህ አብ ይወደኛል።እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም።ለኖራት ሥልጣን አለኝ÷ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ፤” ብሏል። ዮሐ ፡፲÷፲፯።በዮሐንስ ራዕይም ላይ÷“ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ÷ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ሕያው ነኝ÷የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ።” ሲል እናገኘዋለን።ራዕ፡፩÷፲፰

።በመስቀል ላይ፥በሞተ ሥጋ ነፍሱ ከሥጋው ብትለይም፥ በተዋህዶ የነበረ ሕያው መለኰት ከሥጋም ከነፍስም አልተለየም።በመሆኑም ከሥጋ ጋር ወደ መቃብር፥ ከነፍስም ጋር ወደ ሲዖል ወርዷል።ይኸንንም፥- ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፥“ክርስቶስም ስለ ሰው ኃጢአት አንድ ጊዜ ሞቶአልና፤ጻድቅ እርሱ እኛን ወደ እግዚአብሔር (ወደ አብ፥ወደ ራሱና ወደ መንፈስ ቅዱስ) ያቀርበን ዘንድ ስለ እኛ ስለ ኃጢአታችን በሥጋ ሞተ፥ በመንፈስ (በመለኰት) ግን ሕያው ሆነ።በእርሱም በወኅኒ (በሲ ዖል) ወደ አሉ ነፍሳት ሄዶ ነግነትን ሰበከላቸው።“በማለት አስረድቷል።ጀኛ፡ጴጥ፡፫፥ ፲፰።ወልድ ዋህድ ብለው በእርሱ ያመኑ ቅዱሳንም በእርሱ ሕያዋን ናቸው።ይኸንንም፥-“ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፥ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም” በማለት ለእኅተ አልዓዛር ነግሮአታል።ዮሐ፤፲፩፥፳፭።

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ራሱን ሕያው መሥዋዕት አድርጐ ያቀረበ ሕያው ሊቀ ካህናት ነው።ይኸንንም ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ፥“ቅዱስና ያለ ተንኰል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል፤እርሱም እንደነዚያ (እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን) ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ (በየዕለቱ መከራ ሊቀ በልና ሊሞት)አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና። ሕጉ ድካም ያላቸውን (በአዳም ኃጢአት የተያዙትን አንድም ድካመ ሥጋ ያለባቸውን) ሰዎች ሊቀ ካህናት አድርጎ

ይሾማልና፤ከሕግ በኋላ የመጣ የመሐላው ቃል ግን ለዘለዓለም ፍጹም የሆነውን (የማይ ለወጠውን)ልጅ(ወልድን)ይሾማል።(ሾመልን።)"በማለት ነግሮናል።ዕብ፡፯፥፳፯።በተጨማ ሪም፥- "ሊቀ ካህናት ሁሉ ስለ ኃጢአት መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ከሰው ተመርጦ ለእግዚአሔር በሆነው ነገር ሁሉ ስለ ሰው ይሾማልና፤እርሱ ራሱም ደግሞ ድካምን ስለሚለብስ፥ላልተማሩ ትና ለሚስቱት ሊራራላቸው ይችላልና፤በዚህም ምክንያት ስለ ሕዝብ እንደሚያቀርብ እንዲሁ ስለ ራሱ ደግሞ መሥዋዕትን ስለ ኃጢአት ሊያቀርብ ይገባዋል።እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም።እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ ሊቀ ካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረምና፤ነገር ግን፥-አንተ ልጄ ነህ፥አኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ያለው እርሱ (የባህርይ አባቱ አብ) ነውና፤እንደዚሁም በሌላ ስፍራ ደግሞ፥-አንተ እንደ መልከ ጼደቅ ሹመት (ክህነት) ለዘለ ዓለም ካህን ነህ፥ይላል።"ብሎናል።በዚህም፥-በብሉይ ኪዳን ዘመን ወደ ሥልጣነ ክህነት የመጡ ትን ሰዎች የጠራ፥ክብሩንም የሰጣቸው፥ እግዚአብሔር እንደነበረ ነግሮናል።

እንግዲህ በዚህ ሁሉ ምክንያት፥አገልግሎቱን የሞትና የኩነኔ አገልግሎት ያሰኙት ነገሮች ሁሉ በመሻራቸው፥በታቦቱ ፊት የምናገለግለው አገልግሎት የጽድቅና የሕይወት አገልግሎት ነው ነው።በጽላቱ ላይ የተቀረጹት ቃሎቹና ቅዱስ ስሙም ዘመን የማይሽራቸው ሕያውና ዘለዓለማዊ ናቸው።እርሱ ራሱ፥"ሰማይና ምድር ያልፋል፥ቃሌ ግን አያልፍም፤" ብሎናል። ማቴ፡ ፭፥፲፰። ለጽላቱ ስንሰግድ፥ የምንሰግደው ለቅዱስ ቃሉ እና ለቅዱስ ስሙ ነው።አንድም ለቃሉ ባለቤት ነው። "ስለዚህም እግዚአብሔር እጅግ ከፍ

ከፍ አደረገው።(የተዋህደውን ሰውነት አምላክ አደረገው)።ከስም ሁሉ የሚበልጥ ስምን ሰጠው። (ሰውነት በተዋህዶ አምላክ በመሆኑ በመለኰታዊ ስም ተጠራ)።ይህም በሰማይና በምድር በቀላያትና ከምድር በታች ያለ ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይሰግድ ዘንድ ነው።"ይላል። ፊል፡ ፪፥፱።

በብሉይ ኪዳን ዘመን÷እግዚአብሔር ሙሴን፡-"ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ይዘረ ጋሉ÷የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ÷ፊታቸውም እርስ በርሱ ይተያያል፤ የኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ ስርየት መክደኛው ይመለከታሉ።የስርየት መክደኛውንም በታቦቱ ላይ ታደርገዋለህ፤ እኔም የምሰጥህን ምስክር በታቦቱ ውስጥ ታኖረዋለህ። በዚያም ከአንተ ጋር እገናኝለሁ።"ብሎታል።ዘጸ፡፳፭÷፳።ይልቁንም የአዲስ ኪዳን ዘመን÷የኃጢአት መጋረጃ ተቀድዶ ሰውና እግዚአብሔር ፊት ለፊት የተያዩበት ዘመን በመሆኑ÷ሥጋውና ደሙ በሚፈተትበት መንበረ ታቦት አጠገብ ያገኘናል÷ እናገኘዋለን፤ ያነጋግረናል÷እናነግረዋለን።ሕገ ኦሪትን ያከበሩ ሰዎች÷ከላይ በዝርዝር ባየናቸው ምክንያቶች ወደ ሲዖል ወርደዋል÷ ሕገ ወንጌልን ያከበሩ እና የሚያከብሩ ሰዎች ግን ወደ ገነት ወደ መንግሥተ ሰማያት ይጓዛሉ።በቀኙ ተሰቅሎ የነበረ ወንበዴ እንኳ÷በመጨረ ሻዋ ሰዓት አምኖ ንስሐ በመግባቱ÷በውንብድና ውስጥም ሆኖ ከሠላሳ ዓመት በፊት ሠርቶት የነበረውንም ጽድቅ ቆጥሮለት÷"ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ፤" ብሎታል።ሉቃ፡፳፫÷፵፫ ።በመ ሆኑም ከክብረ ኦሪት ክብረ ወንጌል ይበልጣል።ኦሪት ለወንጌል አምሳልና መርገፍ ነች።እኛ የታነጽነው በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ነው÷የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ

ነው ፤በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤በእርሱም እኛ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብረን እንሠራለን ።ኤፌ፡፪÷፳።

ሕገ ልቡና- ምሳሌ ኦሪት - ትንቢተ ነቢያት፤

ሕግ ሳይሠራ በፊት በሕገ ልቡና ዘመን÷እግዚአብሔር፡- ወዳጆቹን እንደመረጠና ከወዳጆቹም ጋር እንደነበረ የታወቀ ነው።ሄኖክን ከዓይነ ሞት ሰውሮ ወስዶታል።ዘፍ፡፭÷፳፬።ኖኅን ጽድቁን ከመሰከረለት በኋላ ከጥፋት ውኃ ሰውሮታል።ዘፍ፡፯÷፩።ይኸንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡-“ኖኅም ስለማይታየው ነገር የነገሩትን ባመነ ጊዜ ፈራ፤ቤተሰቡንም ያድን ዘንድ ክፍል ያላት መርከብን ሠራ፤በዚህም ዓለምን አስፈረደበት፤በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ። ” ብሏል።ዕብ፡ ፲፩÷፯።አብርሃምን÷ይስሐቅን እና ያዕቆብን የመረጠ÷የእነርሱም አምላክ እኔ ነኝ÷ያለ እግዚአብሔር ነው።ዘጸ፡፫÷፮።በአዲስ ኪዳንም ሕያዋን ብሎአቸውል።፸፪÷፴፪፣ዕብ፡፲፩ ÷፲።ሐዋ ርያው ቅዱስ ያዕቆብ ይኸንን ይዞ÷“አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ወደ መሠዊ ያው ባቀረ በው ጊዜ÷በሥራው የጸደቀ አይደለምን? እምነት ለሥራ ትረዳው እንደ ነበር÷ በሥ ራውም እምነቱ እንደመላችና ፍጽምት እንደሆነችም ታያለህን? መጽሐፍ፡-አብርሃም በእግዚአብ ሔር አመነ፤ ጽድቅ ሆኖም ተቆጠረለት የሚለው ተፈጸመ፤የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ፤”ብሏል። ያዕ፡፪÷ ፳፫።አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ለሞት አሳልፎ በመስጠቱ÷ተቀዳሚና ተከታይ የሌለ ውን አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመስቀል ሞት አሳልፎ ለሰጠ ለእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖአል።ዮሐ ፡፫÷፲፮።ይስሐቅም ለመታረድ

በመታዘዙ፥ ለባህርይ አባቱ ለአብ፥ለመስቀል ሞት ለታዘዘ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ለመሆን በቅቶአል።ፊል፡፪፥፰።

እግዚአብሔር፡-ሕገ ኦሪትን እስከ አምልኮ ሥርዓቱ ሠርቶ የሰጠው ለሙሴ ነው። ሙሴም ፡-እግዚአብሔር የነገረውን እና ያሳየውን ሁሉ፥ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ኦሪት ዘዳግም ድረስ በአምስት መጻሕፍት ጽፎ አስተምሯል።በሥራው ሁሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር።ዘጸ፡፫፥፲፪ ።ፊት ለፊትም ይነጋገረው ነበር።ዘኁ፡፲፪፥፰።ስለ ሕዝቡ ኃጢአት በሚማልድበ ትም ጊዜ፥ እግዚአብሔር፡-"እንደ ቃልህ (የምልኛ ቃልህን ተቀብዬ) ይቅር አልሁ፤"ይለው ነበር ። ዘኁ፡፲፬፥ ፳፩።ጌታ ችን ክብረ መንግሥቱን፥ምሥጢረ መለኮቱን በደብረ ታቦር በገለጠ ጊዜ፥ ሙሴን ከመቃብር አስነ ሥቶ በአጠገቡ አቁሞታል።ማቴ፡፲፯፥፫።ይህም የሆነው፥"ሙሴ የእግዚአብሔርን ክብር ያያል፤" ብሎ አስቀድሞ ስለ ተናገረለት ነው።ዘኁ፡፲፪፥፰።በደብረ ሲና ፊቱ የበራ ሙሴ፥በደብረ ታቦር ፊቱ እንደ ፀሐይ ለበራ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው።በሌላ በኩል ደግሞ፡- ሙሴ ግብጻዊውን ገድሎ እስራኤላዊውን ማዳኑ፥ኢየሱስ ክርስቶስ የዲያብሎስን ሥራ ገድሎ አዳምን ለማዳኑ ምሳሌ ነው። ዘጸ፡፪፥፲፪።በበትሩ ባሕረ ኤርትራን ለሁለት ከፍሎ ሕዝቡን ማሻገሩ ደግሞ፥ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ባሕረ እሳትን ከፍሎ ነፍሳትን ለማሻገሩ ምሳሌ ነው ።ዘጸ፡ ፲፭፥፳፭። በዚህን ብቻ ሳይሆን በብዙ ነገር፥ለምሳሌ፡- በመሪነቱ፣በዳኝነቱ ለክርስቶስ ምሳሌ ነው።ዘዳ፡፲፰፥፲፭፣የሐዋ፡፫፥፳፪፣ዕብ፡፫፥፭፤፰፤፱፤የሐዋ፡ ፯፥ ፴፭።ጌታችን በወንጌል፥ስለ ሙሴ ሲመሰክር፥"እኔ በአብ ዘንድ የምከሰሳችሁ አይምሰላችሁ፤የሚከሰሳችሁስ አለ፤እርሱም እናንተ ተስፋ

የምታደርጉት ሙሴ ነው። ሙሴንስ አምናችሁት ቢሆን እኔንም ባመናችሁኝ ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና።ሙሴ የጻፈውን ካላመናችሁ ግን የእኔን ቃል እንዴት ታምናላችሁ?" ብሎአል። ዮሐ፡፭÷፵፭፣ዘጸ፡፵፬÷፳፪-፵፭።ከትንሣኤውም በኋላ በኤማሁስ ጕዳና ላገኛቸው ለሉቃስና ለቀለዮጳ÷ ከሙሴና ከነቢያት÷ ከመጻሕፍትም ሁሉ ስለ እርሱ የተነገረውን ተርጕሞላቸዋል።ሉቃ፡፳፬÷ ፳፯።

ለቅዱሳን ነቢያት ለዓበይቱም ለደቂቃኑም ሀብተ ትንቢትን የሰጠ እርሱ ነው፤በመሆ ኑም የራቀውን አቅርቦ÷የረቀቀውንም አጉልቶ ስለገለጠላቸው፡- የሚያልፈውንም የሚመጣውንም በእ ርግጠኝነት ተናግረዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ÷"ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጕም አልተፈቀደምና፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ÷ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተና ገሩ።"ያለው ለዚህ ነው።፪ኛ፡ጴጥ፡፩÷፳።ለምሳሌ፡-ነቢዩ ኢሳይያስ÷"እነሆ ድንግል ትፀንሳለች÷ ወንድ ልጅም (ወልድን) ትወልዳለች÷ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች። . . . ሕፃን ተወልዶልና÷ወንድ ልጅም (ወልድም) ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ስሙም ድንቅ መካር÷ኃያል አምላክ÷የዘላለም አባት÷የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።" በማለት÷ትርጓሜ የማያስፈልገው ደረቅ ትንቢት የተናገረው ለዚህ ነው።ኢሳ፡፯÷፲፬፣፱÷፮፣ማቴ፡፩÷፳፪።ስለዚህ ኦሪቱም ነቢያቱም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገሩ እናስተውላለን።ይኸውም ይታወቅ ዘንድ÷ፊልጶስ ናትናኤልን፡-"ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል።" ብሎታል ።ዮሐ፡

ኧ፥ፗኗ።

Like . Menkem Tekea

ሮሞ ምዕራፍ 3

1 እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው።

2 አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው። ታዲያ ምንድር ነው?

3 የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን?

4 እንዲህ አይሁን፤ በቃልህ ትጸድቅ ዘንድ ወደ ፍርድ በገባህም ጊዜ ትረታ ዘንድ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን።

5 ነገር ግን ዓመፃችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያስረዳ ከሆነ ምን እንላለን? ቍጣን የሚያመጣ እግዚአብሔር ዓመፀኛ ነውን? እንደ ሰው ልማድ እላለሁ።

6 እንዲህ አይሁን፤ እንዲህ ቢሆን እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈርዳል?

7 በእኔ ውሸት ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከላቀ ስለምን በእኔ ደግሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርድብኛል?

8 ስለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም? እንዲሁ ይሰድቡናልና አንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገራሉና። የእነርሱም ፍርድ ቅን ነው።

9 እንግዲህ ምን ይሁን? ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም ሁሉ ከኃጢአት በታች እንደ ሆኑ አስቀድመን

ከሰናቸዋልና፤

10 እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ።

11 ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥

12 በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም።

13 ጕሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው፥ በመላሳቸውም ሸንግለዋል፤ የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ፤

14 አፋቸውም እርግማንና መራርነት ሞልቶበታል፤

15 እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው፤

16 ጥፋትና ጕስቁልና በመንገዳቸው ይገኛል፥

17-

18 የሰላምንም መንገድ አያውቁም። በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም።

19 አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤

20 ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።

21 አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥

22 እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን

የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤

23 ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤

24 በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።

25 እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተሰሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ኾሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፥

26 ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው።

27 ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፥ በእምነት ሕግ ነው እንጂ።

28 ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና።

29-

30 ወይስ እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻ አምላክ ነውን? የአሕዛብስ ደግሞ አምላክ አይደለምን? አዎን፥ የተገረዘን ስለ እምነት ያልተገረዘንም በእምነት የሚያጸድቅ አምላክ አንድ ስለ ሆነ የአሕዛብ ደግሞ አምላክ ነው።

31 እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ።

ተሀድሶን <<ለጥፋት የተመሰረተ የወንበዴዎች ህብረት>> ብለው ከእነዚህ ወንበዴዎች እንዴት እራሳችንን መጠበቅ እንዳለብን አሳስበውናል። በተለይ እነዚህ አካላት ባለፈው

3/ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ከዘመነ አርዮስ መናፍቃን ጋር እንዳመሳስለው ሁሉ ዲያቆን ያረጋልም ተሀድሶዎችን በብዙ መልኩ ከዘመነ አርዮስ እስከ ዘመነ ሉተር የነበረውን የፀረ ክርስቶስ አመለካከት የተላበሱና በወንጌል ላይ በመጨረሻው ዘመን የበግ ለምድ ለብሰውና እውነተኛ እረኛ መስለው መንጋውን ያስታሉ ተብሎ ትንቢት የተነገላቸው ነጣቂ ተኩላዎች ናቸው ብለዋቸዋል።

※ "መድሎተ ፅድቅ" (የፅድቅ ሚዛን) በሚለውና በቅርብ ለንባብ ካበቁት መፅሀፋቸው በመነሳት የተሀድሶዎችን ምንነት፣ ማንነት እና ስህተት አብራርተው ለዚህም መፅሀፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያለው ማስረጃ አቅርበዋል። የሀዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን መልዕክቶች በማንሳት በቂ ምላሽ የሰጡት ዲያቆን ያረጋል በተለይ ተሀድሶዎች በቅርቡ ይዘው ከመጡት አዲስ የመዳን አስተምዕሮን ሙሉ ለሙሉ ክህደት ያለበት ብለውታል። እነዚህ አካላት መዳንን በቅስፈት እንጂ በሂደት አይፈፀምም ይላሉ። ነገር ግን ቅዱስ ጳውሌስ ለፊጵስዩስ ሰዎች በፃፈው መልዕክቱ ላይ መዳን በቅስፈት ሳይሆን በሂደት እስከ መጨረሻው እንደሚፈፀም ገልፆልናል። ይሉናል። ፊሊጲሲዮስ (2፥12)

"ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ሁልጊዜ እንደ ታዘዛችሁ፥ በእናንተ ዘንድ በመኖሬ ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ስርቅ፣ ፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን

መዳን ፈጽሙ! ይላል።

※ እነርሱ በአንድ የመፅሀፍ ቅዱስን ጥቅስ በመምዘዝ ሰው አንዴ ከአመነ ኩነኔ የለበትም ይላሉ፣ አዎ ልክ ነው። በክርስቶስ ያመነ የእምነት ኩነኔ የለበትም እኛም እንላለን ነገር ግን የስጋ ኩነኔ ግን ወደ ሰማያዊቷ ከነዐን እንደማታደርስ ሁላችንም ልናውቅ ያስፈልጋል። የስጋ ኩነኔአቸው ለነፍሳቸው የተረፈባቸው እስራኤል ዘስጋ ምድራዊቷን ከነዐንን ከሀጢያታቸው ብዛት አላተመለከቷትምና። እግዚአብሔርን አመንን ያሉት እስራኤል ዘስጋ በማመናቸው ብቻ ለምን መንግስቱን አላዩትም? በአንፃሩ ግን አምነው የፀኑት፣ ህብረታቸውንም ከእግዚአብሔር ያደረጉት ካሌብ እና እያሱ ግን ከነዐኒቷን ምድር አዩ ብሎ መፅሀፍ ይነግረናል። ይህ በብሉይ ዘመን የነበረው ምሳሌ ሙሉ ለሙሉ የአዲስ ኪዳን (እስራኤል ዘነፍስ) ምሳሌ ወይንም ጥላ ነው። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ በ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 1 እስከ 11 ድረስ በዝርዝር የብሉይ ኪዳንን እስራኤልን ምሳሌ ያስቀመጠው።

※ መምህሩ ሲቀጥሉም እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ የማዳንን ስራ አንዴ ፈፅሟል ነገር ግን ሰው አመንኩ ካለ በኋላ ግን መዳኑን መፈፀም አለበት። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ (በዕብራውያን 12፥ 1) ላይ እምነታችንን በትዕግስት ሮጠን የምንጨርሳት መሆኑን የነገረን፣ ለዚህም እርሱ እራሱ ለሰማዕትነት ክብር ሲዘጋጅ 2ተኛ ጢሞቲዮስ 4፥ 7 ላይ "ሩጫዬን ጨርሻለው ያለው።"

ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያት ስራ 14፥21-22 ላይ እምነታችን በመከራና በስራ ይፈተንና በእግዚአብሔር ዘንድም ይታይ ዘንድ " ወደ እግዚአብሔር

መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ፥ ወደ ልስጥራን ወደ ኢቆንዮንም ወደ አንጾኪያም ተመለሱ። ይለናል። በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ የሚለው ለመዳን መከራ ያስፈልጋል ማለት ሳይሆን ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን እምነትን በተጋድሎና በትሩፋት ያስተባብር ዘንድ ሲያጠይቅ ነው።

ጌታችን በሉቃስ ወንጌል ላይ በምዕራፍ 13 ፥ 24 ላይ "ብዙዎች ሊድኑ ይፈልጋሉ ግን አይችሉም ያለው እኛንም ይሆን?" ታላቁ ሀዋርያ ቅዱስ ያዕቆብስ በመልዕክቱ ላይ በምዕራፍ ሁለት ምን አለን? አምኛለው ብሎ ነገር ግን ያለ ስራ በእምነት ብቻ ድኛለው ለሚሉት ሰዎች ይህ አይነቱን እምነት ሰይጣናዊ እምነት ብሎ ይጠራዋል። ምክንያቱም አጋንንቶችም እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ ያምናሉና። በወንጌል ላይ የኢየሱስን ክርስቶስን ያለጊዜያችን አታጥፋን ብለው እንደለመኑትም እናያለን። ስለዚህ ኢየሱስ በመለኮት ሀይል ማጥፋት እንደሚችል ያምናሉ ማለት ነው። መለኮታዊ እንደሆነ ያምናሉ ማለት ግን ግን ለምን አልዳኑም? ለዚህም ነው ያዕቆብ በመልክቱ በምዕራፍ ሁለት ቁጥር 19 ላይ

" እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።"

※ እናም ሰው አምኛለው ብሎ ስራ ከሌለው ግን ይህ አይነቱ አጋንንታዊ እምነት ነው። ምክንቱተም አጋንንት ከሰው የሚለዩት ለአምላካቸው በስራ የሚገልጡት መስዋት ስለሌላቸው ነው። ለዚህም ነው ቅዱስ ያዕቆብ በመልክቱ ላይ

(የያዕቆብ መልእክት 2:24)

" ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ።"

" እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን?"

" ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።" ብሎ የነገረን። ስለዚህ የተሀድሶ አሰራር እዚጋ ዋጋ ያጣል ማለት ነው እንደ መምህሩ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ገለፃ።

ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ እስከ መጨረሻ የፀና እርሱ ይድናል ካለ በኋላ ለፍርድ ሲመጣ በፊቱ የምንሰበሰብ እኛን ምን ያህል አምናችኋል ሳይሆን እምነታችሁ በምን ስራችሁ ተገልጧል ነው የሚለን። ለዚህም ፃድቃን የሚላቸውን ስንመለከት በስራ፣ በተጋድሎ እንጂ በቅስፈት ድናችኋል አይላቸውም። ማቴዎስ 25 ከቁጥር 33 ጀምሮ ማንበብ ይቻላል።

※ እንግዲህ ስለ እምነት መዳን የእኛን እና የተሀድሶዎችን ልዩነት አንስተን ይህን ያህል ካወራን መምህራችን ዲያቆን ያረጋል ተሀድሶዎች የሚለዩበት አንደኛው መንገድ ብለው ይህን እንደሚከተለው አሳስበውናል፦ ቤተክርስቲያን ፊፅሞ ያላስተማረችውን ትምህርት እንዳስተማረች በማስመሰል ቤተክርስቲያንን ጥፋተኛ አስመስሎ መስበክ፣ በአንፃሩ ደግሞ የምታስተምረውን ትምህርት እንደማታስተምርና በዘመነ ኦሪት ያለች ኋላቀር አስመስሎ መናገር። በተለይ በመላዕክታት ድርሳን ላይና በአንዳንድ የፃድቃን ገድላት ላይ ያልተፃፈን ታሪክ እንደተፃፈ በማስመሰልና ትርጓሜውን በማጣመም የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን የእውነት ሳይሆን የተረት ተረት ቤተክርስቲያን አስመስሎ ማስተማር።

❊ በመጨረሻም መምህር ያረጋል ይህን መልዕክት በአፅዕኖት አስተላልፈዋል፦ እያንዳንዱ ምዕመን ጥንቃቄ እንዲያደርግና ማንም የለሰለሰ አንደበትን ተጠቅሞ ቢመጣ እንድንጠነቀቅ የሰይጣንን በእባብ አድሮ መገለጥ ጠቁመዋል። የእባብን ለስላሳ ቆዳ፣ ቅልስልስ አንደበት ሄዋንን ለማታለል የተጠቀመበት አማራጭ ነበር ብለዋል። የእባብ ቆዳ እና መቅለስለስ የውሥጧን መርዝ ላልተገነዘበ ሰው በጣም ታምራለች፣ ትስባለችም! እኛ ግን ዛሬ የእባብን የውስጥ መርዝ አውቀን እንስሳዋን እንደምንጠነቀቃት ሁሉ በእምነት ደካማ የሆነው እኛን በእባብ አምሳያ ተቅለስልሰው እና ቆዳቸውን አብረቅርቀው ነገር ግን የውስጣቸውን መርዝ ቀብረው የመጡ በርካቶች አሉና፤ ዛሬም ሰባኪ መስለው ቀሚሳቸው ከሚያብረቀርቅ፣ የጌታን ቃል ነጋሪዎች መስለው አንደበታቸው ከሚቅለሰለስ ነገር ግን በውስጣቸው መርዛማ ከሆኑ አሳሳቾች ተጠበቁ ብለዋል።

ቴድ ሉቃስ

10/27/2015

4/ የድረሱልን ጥሪ ከስልጤ ክርስቲያኖች

በስልጤ ዞን ውስጥ በተለያየ ወረዳ የሚኖሩ ጥቂት የተዋህዶ በጎች አሉ:: በየዘመኑ እጅግ ብዙ ግፍና መከራ እየተቀበሉ አንዳንዶቹ ሳይታወቅላቸው ይችን ዓለም በሰማዕትነት ተሰናብተዋል::

የሚገርመው ይህ ችግር መኖሩን በመንግሥት እና በቤተክህነት እየታወቀ ጆሮ ዳባ ልበስ መባሉ ነው:: ማንም በወቅቱ ምላሽ ባለማግኘታቸው ተስፋ በመቁረጥ ካህናት ከቦታው በመሠደድ ምዕመናኑ ማዕተባቸውን በመበጠስ የሌላ እምነት ወደመከተል አንዳንዶቹ በፍርሃት ውስጥ ሆነው

እግዚአብሔርን የሚጠብቁ ሆነዋል።

በክልሉ በየቀኑ የሚደርሰው ህዝበ ክርስቲያኑን የማሸማቀቅ እና ብሎም በስንት መከራ የተሠራውን ቤተክርስቲያኗን እስከማቃጠል (አምና የሰማዕቷን የቅድስት አርሴማ ልብ ይሏል)።ተደርሷል እኛም ጥቂት ሆነን ቅዳሜ ጥቅምት ፮ ህዝበ ክርስቲያኑን ለማፅናናት ከ አ፡አ የ 2:40 መንገድ ነው በሄድንበት ወቅት አባቶች በመሪር ሀዘን ህዝበ ክርስቲያኑ እንዲደርስላቸው የሚከተለውን ነግረውናል።

የመጀመሪያዉ ከዞኑ የመንግስት ባለስልጣናት በልማት ስም ከማስተር ፕላኑ ጋር የማይጣጣም ከጀርባው ሌላ ድብቅ ዓላማ ያለው የቤተክርስቲያኗን ይዞታ ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ለቢዝነስ እና ለመንገድ በሚል ቦታውን ለመንጠቅ እየተሯሯጡ እንደሚገኙ ይህንንም ለፊደራል ጉዳዮች እና ለቤተክህነት ሰዎች በደብዳቤ ቢያሳውቁም ችግሩ ስር ከመስደድ ውጪ ምላሽ አለማግኘታቸውን በምሬት ገልፀዋል ከዚህ በጎላ እኛ ናቡቴ እነሱም አክአብን እንሆናለን ወይ ያጠፉናል አልያም እናጠፋቸዋለን ብለው እልህ እና ቁጭት በተሞላበት ሁኔታ ሲናገሩ ምን ያህል በችግሩ ውስጥ መሆናቸውን ያስገነዝባል። በቅርብ ቀን መሃንዲሶች በድፍረትና በማን አለብኝነት ቤተክርስቲያን ቅጽር ገብተው ሲለኩ የተመለከቱት አንድ አባት እገላለሁ ብለው በሰዎች ገላጋይነት ነገሩ ሊበርድ ችሏል። ከዚህ በፊትም በዞኑ ውስጥ በሚገኘው መድኀኔዓለም ቤተክርስቲያንን ለማፍረስ መንገድ በዚሁ ቦታ ስለሚወጣ መፍረስ አለበት በማለት ቢገልጹም በቤተክርስቲያኗ የቁርጥ ቀን ልጆች ከኢትዮጵያ መንገድ ባለስልጣን ሰራተኞች ጋር በመነጋገር ፕላኑ ሆን ብለው ቤተክርስቲያኗን ለመጉዳት እንደሆነ

በመገንዘባቸው ማስተር ፕላኑ እንዲስተካከል ተደርጓል።

ሌለው በዚህ ዞን ልዩ ስሙ ዳሎቻ በሚባለው አካባቢ የእመቤታችና የደብረ ሳህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የነበረ የጠጠር ማምረቻ ከነቦታው ተወስዶባቸዋል።

የምዕመናኑ ስቃይ በዚህ አያበቃም ከዩኒቨርሲቲ በጥሩ ውጤት ተመርቀው በደቡብ ክልል መንግስት ከተመደቡ ቢቆዩም ሁሉንም ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ እስካሁን ድረስ እየተጉላሉ ይገኛሉ። ወደ ሌላ ስፍራ በመሄድ ስራ ማግኘት እንደ ሚችሉ ቢያውቁም ቤተክርስቲያ ጥለው መሄድ የማይታሠብ እንደሆነ እና ስለ ቤተክርስቲያን ቢራቡ እንደሚመርጡ ገልፀዋል።

ካህናቱ እና ምዕመኑ እስከ ፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ድረስ ቢሄዱም ምላሽ ማጣታቸውን ይገልፃሉ። ከአሁን ቀደም ብዙ ባለስልጣናት ተወልደውበታል በሚባለው ወረዳ ላይ ቤተክርስቲያን ለማሠራት የሞከሩ 16 የሚሆኑ ከተለያየ ቦታ ለስራ የመጡ ክርሰቲያኖች ከ 6-10 ዓመት እስር ዓመት ተፈርዶባቸው የነበረ ቢሆንም ወደ 15 የሚጠጉት በእግዚአብሔር እርዳታ ሲወጡ ግን አንዱ እስካሁን በማረሚያ ቤት እንደሚገኝ ገልጸዋል። እግዚአብሔር ህዝበ ክርስቲያኑን ይጠብቅልን።

መልዕክቱን ሼር በማድረግ ሰው እንዲያውቀው ይደረግላቸው!!!!!!

Endale Arega

እግዚአብሔር ቀን አለው ክርስቶስ ዝም አይልም ታጋሽ ነው ግን ቀኑ ሲደርስ ምድርን ያንቀጠቅጣል በተዋህዶ ላይ መከራ ቢበዛም ሊያጠፉን አይቻላቸውም በጭራሽ የ እግዚአብሔር ክንድ ከኛ ጋር ነውና አባት ሆይ

አንተ ድረስልን

Like · Nikisti Yetewahedo

አይግረመንም አይድንቅንም አግራችን በስማይ ነው። እይትግድልንም እንኳን እነብዝለን ክረስተና በድም ይትመስረትች ናት እግዚአብሔር ይድረስላች ውግኖች

Like · Lidya Ye Maryam Lige

ጌታ ሆይ ቤትህን ከ እምያፈርሱስ እነ እርሱ ይፍረሱ . ለተጨነቁ ግን ድረስላቸው።

Like . Tariku Fekadu

ምነዉ በአዬ ካሌብ ዘመን በተፈጠርኩ ምን ይደረግ ሰዉ የለማ ግድ የለም እግዚአብሄር ጊዜ አለዉ

Like · Lovely AB

ወይ እማማ ኢትዮጵያ የተዋህዶ ደሴት

እንዳልነበርሺ ሁሉ ! አሁን አሁን ምድርሽና ቤተ- መቅደስሽ በመናፍቃን ይወረስ !

አቤቱ ፈጣሪ ሆይ እርዳታህን እንሻለን።

Like · Samson Solomon

ዛሬ ሁላችንም ዞር ብለን በርብርብ ታሪክ የምንሰራበት አባቶቻችን የምንመስልበት ቦታ መሆኑን አለበት

Like . Emebet Tsome

እኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤታችን በሰማይ ነው ሁሉም ለበጎ ነው

Like · Wube Mekuria

በአለት ላይ የተመሰርተቺ ማንም ሊናዉጣት አይቸለም መሰርታአ ደም ነዉ ክርስትና በአፍቺን የምናወራዉ አይደለም ከልብ የምንሞትላት ናት ትዋህድ ሀይማኖቴ 0 ላት እዉነትኛ ሀይማኖት

Like · Yene Sinshow

ለሁሉምን ጊዜ አለው በእግዚአብሔር ቀን አለው ስለኔ የሚሰቃዩ ብጽሀን ናቸው ብላል እግ ያጽናችሁ

Like · Kib Kibret

ፈሪዎች ናቸው ፣ ቀድማቹ በጥፊ ማለት ብቻ ነው ደግሞ ለሌባ ፊት መስጠት ፣ የመንግሥት ፣ ቸልተኝነት ፣ የፈጠራቸው ፣ ጥቂት ውሾች ፣አሉ አንድ የሚታይ ነገር እስከሚያደርጉ ነው የሚጠበቀው ! ወደነበሩበት ይመለሳሉ ።

ቅድስት አርሴማ ደጓ እናቴ

5/ የመናፍቃንን መዝሙር መስማት..... ዲያቆን ህብረት የሺጥላ

እባክዋን ካነበቡ በዋላ ሼር አድርጉ

• ዘፈን መስማት ኃጢአት ነው የመናፍቃንን «መዝሙር›› መስማት ግን ዓመፅና

ክህደት ነው። ኃጢአት የምግባር ሕፀፅ ሲሆን ዓመፅ ደግሞ የሃይማኖት ሕፀፅ

ነው። የቱ የሚከፋ ይመስልሃል?

- «የመናፍቃንን መጽሐፍ ከመመልከት ተከልከል››ማር ይስሐቅ ::
- «ዑቅ ከመኢትቅረብ ኀቤሃ - ወደ እርሷ ከመቅረብና ገልጾ ከማየት እንኳን
ተጠንቀቅ›› ይላል። ምክንያቱንም ሲያስረዳ መንፈሰ ጽርፈት / የስድብ መንፈስ/ እንዳያድርብህ ነው ይላል። በእርግጥ ይህ ቃል የተነገረው የመናፍቃንን መጽሐፍ ስለማንበብ ነው። ማር ይሥሐቅ ከላይ እንዳስጠነቀቀን
የመናፍቃንን መጽሐፍ ማንበብ ክፉ ነገር ነው። መጽሐፋቸውን ከማንበብ በላይ
በዘፈን ዜማ የወዛ «መዝሙራቸውን መስማት›› እጅግ አይከፋምን? ስለዚህ
እንደ መጽሐፋቸው ሁሉ «መዝሙራቸውንም›› መስማት ይከለክለናል።
- እነርሱ «የምስጋና መዝሙር›› ቢሏቸውም አስተውሎ ለሰማቸው ፉከራና
ሽለላዎች ናቸው።
- የመዝሙሮቻቸው የጌታችንና የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስሙን
ሲያነሡ ልክ ባልጀራቸውን እንደሚጠሩ ያህል በድፍረት መሆኑ ደግሞ እጅግ
ያሳዝናል። ታዲያ አንተ መዝሙራቸውን እየሰማህ ከእነርሱ ጋር «ኢየሱስ ጓደ›› ለማለት ልብህ ይከጅላልን?

‹‹ይህ ነው ምስጋናቸው›› ይመልከቱት

ዘፈን መስማትና ዘፋኝነት ለመናፍቃን መዝሙር ሊያጋልጥ ይችላል።

ምክንያቱም የመናፍቃን መዝሙር ከሚያስጨፍር ዘፈን አይለይምና።

እንዲያውም አንዳንድ ኦርቶዶክሳዊያን ወጣቶች ለመናፍቃን መዝሙር የቀረበ

አመለካከት እንዲኖራቸው ያደረገው በውስጣቸው ያለው የዘፈን እርሾ ነው። ብዙ

ዘፋኞች ወደ መናፍቅነት እንዲሄዱና በዚያም «ዘማሪ›› እስከመባል መድረሳቸው

በዚህ ውጤት ነው።

የተዘረዘሩትን ጉዳቶች ጨምሮ ለከፍተኛ ጉዳት ያጋልጣል። ብዙ እጥፍ ይከፋል።

ዘፈን መስማት ኃጢአት ነው የመናፍቃንን «መዝሙር›› መስማት ግን ዓመፅና

ክህደት ነው። ኃጢአት የምግባር ሕፀፅ ሲሆን ዓመፅ ደግሞ የሃይማኖት ሕፀፅ

ነው። የቱ የሚከፋ ይመስልሃል?

ከባሕር ማዶ ያሉ በርካታ ዘፋኞች ታሪክ ሲጠናና ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው

የሚናገሩት «የቤተ ክርስቲያን ዘማሪ›› እንደነበሩ ነው። አብዛኞቹ ለዘፋኝነታቸው

መነሻ የሆናቸው «መዝሙር›› እንደሆነ አበክረው ይገልጻሉ።

የእነዚህ ዘፋኞች ገለጻ የሚያመለክተው የ«መዝሙር›› ተብዬው ዜማና መሣሪያቸው ከዘፈን ዜማና መሣሪያ ጋር ምንም ልዩነት ስለሌለው ወደ ዘፈን
እንደተሳቡ ነው። ሰይጣን ሰዎችን በለመዱት መሳብ ሥራው ነውና። የሰው ልብ
ማረፊያ ይሻል። የሰው ልብ ሌላ ለመያዝ ካለሆነ በቀር የያዘውን ለቆ በባዶ መቀመጥ አይሆንለትም። ይህን የሚያውቅ ሰይጣን መዝሙርን ሲያስለቅቅ ዘፈንን ያስጨብጣል።
ለፈጣሪ ክብር ምሰጋና ይግባውና እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ባሕር ማዶ ሰዎች
የመዝሙርና የዘፈን ልዩነት ጠፍቶን ግራ እንድንገባ የሚያደረግ ችግር የለብንም። ምክንያቱም የመዝሙራችን ዜማ ከዘፈንም ሆነ ከመናፍቃን መዝሙር ዜማ የተለየ ሲሆን የመዝሙር መሣሪያችን ደግሞ ከዘፈንና ከመናፍቃን የመዝሙር መሣሪያ በእጅጉ ይለያልና።
ሆኖም እንደ ባሕር ማዶ ዘፋኞች ሁሉ በኛ አገርም ያሉ በርካታ አዝማሪዎችና
ዘፋኞች «ዘማሪ ነበርኩ፣ መነሻዬ የቤተክርስቲያን መዝሙር ነው።›› ሲሉ ይደመጣል። በእርግጥ ከዘማሪነት እስከ ድቁናና ምርግትና/መሪጌትነት/ ማዕረግ የደረሱ በርካታ ሰዎች ወደ ዘፋኝነት ያዘነበሉና የሄዱ እንዳሉ ይታመናል።
ጥቂቶች ግን ዘፈኖቻቸውን ከሚያዳምጡላቸው ሰዎች መካከል
አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ናቸው ብለው ስለሚያምኑ ተቀባይነትን

እንደሚያገኙ አስበው «ዘማሪ ነበርኩ›› እያሉ ይዋሻሉ።

ቤተክርስቲያን የመናፍቃንን «መዝሙር›› እንዳይሰሙ ልጆቿን የምታስተምረው

የዜማ ዕቃዎቿ ከመናፍቃን የመዝሙር መሣሪያዎች ልዩ ስለሆኑ ብቻ አይደለም። ይህ አንዱ ቢሆንም ዋናው ግን መናፍቃን የሚምሩትና የሚሠውት

ለአጋንንት ስለሆነ ነው።

ለዛሬ ይቆየን ይቀጥላል

ወስብአት ለእግዚአብሔር

ወለ ወላዲተ ድንግል

ወለ መስቀለ

Elsa Getanh

Like. Dawit Tiruneh

biblical aydelem ...this is yours idea...if you can some evidence in a bible?

Like · Dawit Tiruneh

" ስሙን በዘፈንያመስግኑ፥ በከበሮና በመሰንቆም ይዘምሩለት።" (መዝሙረ ዳዊት 149:3)

Like · Yonas Henok

እግዚአብሔር ይቅር ባይ ስለሆነ አንተንም ይቅር ይበልህ ዲያቆን ። ስለእዉነት ከሆነ ኦርቶዶክስ ተኝታለች ወንጌልን አስቀድማ እንደመቀበሏ ወደማጀት አስቀመጠችዉ አልተጠቀመችበትም ።በገድልና ተረት ተረት

ከመንፈስ ቅዱስ ዉጭ በሆነ ታሪክ ተጠምዳለች ከነዛም ሰወች መካከል አንተ አንዱ ነህ የቅዱስ ወንጌል ፀር ነህ ።ግን ክርስቶስ እንደ ሊዲያ ያለን ልብ እንዲሰጥህ እፀልያለሁ ለማንኛዉም ገድለ ገደል ከምታነብ መፅሀፍ ቅዱስን አንብብ እግዚአብሔር ይረዳህል።

Like · Meseret Mesela

ምንም ክርክር አያስፈልገውም እ�ኛ ኦርቶዶክስ የሆንን ያሬዳዊ ዜማ አለን መንፈስ የሚያድስ የምያረጋጋ የውስጥ ሰላም የሚሰጥ ።

መጸሀፍ ቅዱስ በምያዘን መስረት እግዝያብሄርን እናመሰግን ።

Like · Tarekegne Endalew

ምነው ምድረ ግሪሳ ተንጫጫ ከዘፈንም አልፎ አይን አስጨፍኖ አንገት አስደፍቶ የሚስጭህ የሰይጣን መንፈስ መሳቢያ ዘፈን ነው ። ለማንኛውም አምላከ ቅዱሳን ማስተዋል የይስጣቹህ

Like · Sena Oromo

እኔ ደሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ እያጣቀሰ መስሎኝ ሰፍ አልኩበት:: ወንድሜ ዲያቆን የሺጥላ ስላለ ሣይሆን ክፉንና ደጉን ማወቅ የምንችለው አንብበን እንጂ የሺ ጥላን ጠይቀን አይደለም

Like · Mesfine Demelash

ዳያቆን የሺጥላ ስላለ አይደለም እውነቱን ክርስቶስ ይግለፅልን የማንንም መዝሙር ዘፈን ማለት አንችልም ከመፍረድ ይሰውረን አሜን

Like · Tourist Dilla

ተከድኖ ይብሰል የመናፍቃን የአዳራሽ ውስጥ ጩኸት መንፈስ ቅዱስ ከሆነ ኩነኔ በኔ ይሁን እንደዚህ ያለ መንፈስ ቅዱስ አልፈልግም::

መንፈስ ርኩስም አደለም መንፈስ ቅዱስም አደለም ሳይኮሎጅካል ጨዋታ ነው::መንፈስ ቅዱስ የራሰሱ ሐይል አለው::መጽሐፍ ቅዱስን በሰከነ ስብከት እንደ ኦርቶዶክስ ቢሰብኩ ማንም ተነስቶ አይጮህም አይዘልም::የነሱን አሰባበክ ሲስተም ሳይኮሎጅስቶች አምሮ ጭንቀት ያለባቸውን ለማዳን ሚጠቀሙበት ሲስተም ነው::ይህን መንገድ ተጠቅሞ ማንም ሰው እንኳን በእግዚአብሄር ስም ይቅርና ያባቶቻችን መንፈስ ብሎ ታምር ሊሰራበት ይችላል::

ዋናው ሲስተም በኢየሱስ ስም እያሉ እጮኹ እዘለሉ ኡኡኡ እያሉ የጆሮ ታምቡር በሚነቅል ሞንታርቦ አዳራሽ የሞላውን ህዝብ ማስደንገጥ ነው::ሲደነግጥ በመንፈስ ጭንቀት ካቅሙ በላይ ሆኖ ሲወድቅ መንፈስ ቅዱስ ይሉታል::

የመናፍቃን መንፈስ ቅዱስ ሳይኮሎጂ እንጅ ሰይጣንም መ.ቅዱስም አደለም::ሳይኮሎጅስቶች እንደሚፈጠሱበት እነሱም ይፈውሱበታል::

ሳይኮሎጅ ነው ያልኩት ከመሬት ተነስቶ ስም ለማጥፋት አይደለም;;

ማንም ፕሮቴስታንት የሆናችው ራሳችው ሞክሩት::

የውነት መንፈስቅዱስ ከሆነ ሞንታርቦ በሌለበት ጩኸት በሌለበተ በጸጥታ ድምጽ ጸልዮ መንፈስ ቅዱስ በራሱ ሲሰራ ካገኛችው ውሸተምነቴን ስም አጥፊነቴን ትነግሩኛላቸው::

ለመሆኑ በጩኸት እያዘለለ ላብ ጥምቅ እስኪለን ዘለን ካልመጣን ቸርች የሄድን ይመስለናል?በፍጹም

Like · Melese Habte

ይህን ጽፈህ የለቀቅከው ሠው እርግጠኛ ነኝ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ

አይደለህም የትኛውም እምነትና አስተምህሮት ተሳደቡ ብሎ አይልም ቅራቅንቦ ለቃቅመህከምትናገር የእውነት አምድ መሠረትየሆነው ወንጌል ለአህዛብ ብትሰብክ ዋጋህ በሰማይ ታላቅ ነበር የሚያሳዝነው ዲያብሎስ ሰድብን ይሰጣል አንተም ከሰጪው ሰድብን ተቀበልክ እግዚአብሔር ማስተዋልና መመለስን ይስጥህ

ሚካኤል ዘየካ and 48 others .

ይህ ዜና ያልደረሳችሁ የተዋሕዶ ልጆች ካላችሁ:

ሰበር ዜና እነሆ ብለናችኋል!

6/ ዜና ውግዘት ዘ ሐራጥቃ ተሐድሶ በምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት!

የሐራጥቃ ተሐድሶ ኑፋቄ አራማጆችና ምንደኞች በውግዘት እየተጠቀነሱ ነው።

አርአያነት ባላቸው በብፁዕ አቡነ ስምዖን (በምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ) እና የቤተ ክህነት አገልጋዮች ኮርተናል።

ይህን አርአያነት ያለው ተግባር በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጪ ያሉ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ አገልጋዮችና አማኞች ሊያከብሩና ሊከተሉት ይገባል።

እኒህ አገልጋዮች ይቅርታ ጠይቀን ወደ አገልግሎታችን እንመለስ የሚል ሃሳብ እያነሱ ሲሆን ቤተክህነቱ በጥልቀት ሊያየው የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ አስቀድመን ልንጠቁም እንወዳለን!!

የአርዮስን "ተጸጽቻለሁ!" ብሎ መምጣት አይቶ ከውግዘቱ የፈታውና ለባሰ

ምንፍቅና በር የከፈተውን *አኪላስ* ተቀስፎ መሞቱን ማስታወስ ይጠበቅብናል።

በነቀምቴ ከተማና በየወረዳው በመዘዋወር የሐራጥቃ/ የፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ/ ትምህርት በማስተማርና በመቀስቀስ፣ በተለይም በጽዋ ማኅበራትና የዋህ ምዕመናንን እውነተኛ የቅድስት ቤተክርስቲያን አገልጋይ በመምሰል የኑፋቄ ትምህርታቸውን እንዲሁም በቅድስት ቤተክርስቲያን ዐውደ ምህረትና ለተልእኮአቸው በተመቻቸላቸው ቦታዎች ሁሉ፣ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አስተምህሮ ውጪና ከቅዱሳን መጻሕፍትና ከአዋልድ መጽሐፍት ጋር የሚጣረሱ፣ ከቅዱሳን አባቶች እና ከመምህራነ ወንጌል ያልተገኙ እውነት የሚመስሉ ውሸቶች በምዕመናን ልቦና በመዝራትና አጠራጣሪ ትምህርት በመስጠት ምእመኑ ለሚወዳትና ለሚሞትላት ርትዕይት ሃይማኖት ጥርጣሬ እንዲኖረውና አባቶች በዘሩት መልካም የወንጌል ንፁህ ዘር ላይ እንክርዳድ ለመዝራት ደፋ ቀና ቢሉም፣ ክፉ ሃሳባቸው በሥላሴ ቸርነት በድንግል ምልጃ በብፁእ አባታችን አቡነ ስምዖን መልካም ፈቃድ እንዲሁም በካህናት ጉባኤና በእውነተኛ ምእመናን ጥረት ክፉ ሴራቸውና የውሸት ትምህርታቸው ቢጸ ሐሳዊነታቸው ተረጋግጦ በማንኛውም የቅድስት ቤተክርስቲያን አገልግሎት ላይ እንዳይሳተፉ፣ ክህነት ያላቸውም ክህነታቸው እንዲያዝ በመደረጉ እኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን በእጅጉ ደስተኛ ሆነናል።

በአገልግሎት ሕፀፅ ምክንያት መረጃ የተገኘባቸውን የ 8 ቱን ስም ዝርዝርና የአገልግሎት ቦታቸውንና የውግዘት ደብዳቤያቸውን ከዚህ በታች አቅርበናል። ይህም ደብዳቤ ለሚመለከታቸው የቤተክርስቲያን አካላትና የመንግስት አካላት በምሥራቅ ወለጋና የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

በአባ ስምኦን ቲተር እና በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የምሥራቅ ወለጋ ሀ/ስብከት ጽ/ቤት የራስጌ ማሕተም በቀን 14/01/2008 ዓ.ም. እኒህ ደብዳቤዎች ተበትነዋል።

ተ.ቁ ስም የአገልግሎት ቦታ

1 => አባ ሳሙኤል ታከለ ዋማ ገሎ ወረዳ ቤ/ክ ኃላፊ

2 => ቄስ ሙሴ ዘሪሁን ነቀምቴ ምስራቀ ጸሐይ ኪ/ም ቤ/ክ

3 => መ/ር ስዩም ስንታየሁ ቄ/ወለጋ ደ/ዶሎ

4 => ዲ/ን ታረቀኝ ፍቃዱ ነቀምት ዋቻ ደ/ሣ/ቅ/ሚካኤል ቤ/ክ

5 => ዲን/አለማየሁ አየልኝ ነቀምት ደርጌ ፊ/ህ/አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤ/ክ

6 => ዲ/ን ቶላ በየነ ሲቡ ሲሬ ወረዳ ደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ቤ/ክ

7 => ለወጣት ኢታና ዲንቂሳ ነቀምት ዋቻ ደ/ሣ/ቅ/ሚካኤል ቤ/ክ

8 => ወጣት ነቢዩ ጀምበሬ አርጆ ጉደቱ ባአታ ማርያም ቤ/ክ

በማናቸውም የቅ/ቤተ/ክ አገልግሎት ላይ እንዳይሳተፉና ምዕመናንንም ነቅተው በመጠንቀቅ ሥርዓተ አምልኮታቸውን እንዲፈጽሙ ይህ ደብዳቤ በሁሉ የነቀምት ከተማ አድባራትና በምሰካበ ቅዱሳን ቅዱስ ዑራኤል ወሳሙኤል ገዳም የተነበበና ለምዕመናንም የተገለጸ ሲሆን፣ በዚሁ እለት መስከረም 16 ቀን በመስቀል አደባባይ ደመራው ከመለኮሱ በፊት ጉዳዩን በመግለፅ ሰፊ ትምህርት ተሰጥቶበት ምዕመናን ሁሉን ተረድተው ሥርሆተ ህዝብ ሆኗል።

የምዕመናን ጩኸት በርትቷል የእውነተኛ አገልጋዮች አንድነት ከገደማት

እስከ አድባራት ከሃገር ውስጥ እስከ ውጪው ዓለም በእጅጉን አንሰራርቷል። ለዚህም ነው ባለፈው ወር በጥምቀት ተመላሾች..... በ1 ሳምንት ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ100,000 በላይ ፊርማ የተሰበሰበው፤

የተከበራችሁ ብጹአን አባቶቻችን የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት:

ልዑል እግዚአብሔር በሰጣችሁ ስልጣን ሃይማኖታችንንና ምዕመናንን ከነጣቂ ተኩላ /ከሐራጥቃ/ትጠብቋት ዘንድ ልጅ አባቱን ማንኛውንም ጥያቄ በሚጠይቅበት የአባትና የልጅ መንፈስ በታላቅ ትህትና እንጠይቃለን። ያጠፋን መምከር፣ መገሰፅ፣ ቀኖና መስጠት በተለይም "መወገዝ ያለበትን ማውገዝ" የእናንተ ሥልጣን ነውና። ከቅዱሳን መላእክት ወገን የነበረው ሣጥናኤል በሥራው ተወግዛል። ስሙም ተቀይሮ ሰይጣን ተብሏል። ከቅዱሳን ሐዋርያትም የአስቆሮቱ ይሁዳ ተለይቷል፤ ከሊቃውንትም አርዮስ ፣መቅዳንዮስ ....ተወግዘዋል። ‹‹ማውገዝ የነበረ ያለ ወደፊትም የሚኖር ነው።››

"ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወደው፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያና በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከእመቤታችን መወለዱን የማያምን ሰው ቢኖር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው የተለየ የወገዘ ይሁን።" እንደሚል ሥርዓተ ቅዳሴ!

አለዚያ አነዚህ ሐራጥቃዎች ዓይናችን እያየ እንደ ሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ርስታችንን ለመካፈል (ለመውረስ) የማይዳዳቸው ምንም አይነት ምክንያት የለም።

ስለዚህም አባቶቻችን ብጹአን ሊቃነ ጳጳሳት

"አሁንም በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔር ቤ/ክ ትጠብቁ ዘንድ

መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ!!"

/ሐዋ ሥራ 20፤28/

ምንጭ => ማኅበረ ቅድስት ልደታ ዘነቀምቴ ደብረ-ፅዮን

ጥቅምት 11/2008 ዓ.ም.

ይቆየን!

ኦርቶዶክስ መልስ አላት/Orthodox Have An Answer

7/ "ተሐድሶ የለም" ማለት የተሐድሶነት ማረጋገጫ

ዲ/ን አባይነህ ካሴ

አንዳንድ ጊዜ የሰጣቸው ቅሎች መድረክ ቢሰጣቸውም ቅሉ የሚተነፍሱትን እንኳ ለመቆጣጠር አልቻሉም። ሰሞኑን ደቡብ ምዕራብ በተካሄደ "ጉባኤ ከለባት" ላይ በተሰጣቸው መድረክ በአገኙት አጋጣሚ ተጠቅመው ከስድብ ናዳ በስተቀር ኦርቶዶክሳዊ ለዛ ባጣው አሳዛኝ ሕዝበ ክርስቲያኑን የማወክ ተልእኮ "ተሐድሶ የለም" በማለት አቋማቸውን የገለጡ ሰዎች እንዳሉ ስሰማ ውስጤ በጎዘን ደማ።

በተለይም እንደ አውራ መስሎ ለመታየት የሚሞክረው አንዱ "እኔም ኢየሱስ የሚለውን ስም በመጥራቴ ተሐድሶ እየተባልኩ ነው። አስኪ መልክኣ ኢየሱስን ተመልከቱ እንዴት ኢየሱስ ማለት ተሐድሶ ያስብላል?" በማለት ስለ ተሐድሶ ጥብቅና ለመቆም ሙከራ አድርጓል። እንዲህ በማለት

መናገሩ ብቻውን አላዋቂነቱን፣ በውስጡ ምንም ዓይነት ግብረ ክርስትና እንደሌለ ያሳብቅበታል።

--> ተሐድሶ የለም?

ተሐድሶን ያወገዘ እኮ ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ሲያወግዝም የቀረበለትን ማስረጃ በሚገባ አገላብጦ ሊቃውንትን መድቦ እና መርምሮ እንጂ በግብታዊነት አልወሠነም። በዚኽም ለመመከር እና ለመመለስ አሻፈረኝ ያሉቱ ተወግዘው ተለይተዋል። ራሳቸው የፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ አቀንቃኞች ያልተከረከሩለትን አቋም አዲሱ ተከራካሪ ከወዴት አገኘው?

አንድ ነገር አለ ወይም የለም የሚባለው መቼ ነው? ይኽስ ሊባል የሚገባው በማን ነው? አንድ ነገር አለ ወይም የለም ለማለት ጥልቅ ጥናት ያስፈልጋል። ከሁለቱም ዓይነት መደምደሚያዎች በፊት ማስረጃዎች ይቀድማሉ። ማስረጃዎቹም በብቁ ባለሙያ ይመረመራሉ። የምርመራው ስሌት አለ ወይም የለም ወደሚል መደምደሚያ ያደርሳል። ስለዚህ "ተሀድሶ የለም" ወደሚል መደምደሚያ የደረሰ ማንኛውም አካል ከአዋጁ በፊት ይኽንን ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል።

ለመኾኑ ሰውየው ምን መረጃ ለማን አቅርቦ ያውቃል? "ተሐድሶ የለም" ብሎ ከመናገር መቅደም ያለበት ያሰባበሰበውን መረጃ ይዞ ሥልጣኑ ላለው አካል ማቅረብ ይጠበቅበታል። የቤተ ክርስቲያን ልጅ ነኝ ካለ ለቅዱስ ሲኖዶስ እንዲቀርብ ማድረግ ነበረበት። ግን ምን ያደርጋል ብቻውን ጅምሮ ብቻውን ጨረሰው። ራሱ ይፈጫል፣ ራሱ ያቦካል፣ ራሱ ይጋግራል፣ ራሱ ይበላል። እንዲህ ዓይነት ብቻን የመቆም ፍለጎት ተጠናውቶታል።

ጎበዝ ተከራካሪ ማስረጃውን አጠናቅሮ በሚገባው ዐውደ ፍትሕ ተገኝቶ

ይከራከራል። ግን ነገረ ጅራፍ ብቻ ኾነ። ራሱ ገርፎ ራሱ መጮኽ። ቅዱስ ሲኖዶስ አለ እያለ እርሱ የለም የሚል ከኾነ ሰልፉ ከእነማን ወገን ነው? ከአሥራ ዘጠኝ ሰማንያዎቹ መጨረሻ ጀምሮ በተከታታይ ቅዱስ ሲኖዶስ ሲያወግዘው የኖረውን ይኽንን የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ አንድ ጎረምሳ ተነሥቶ የለም ካለ ሰውየው ከእነማን ወገን ነው? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ያስነሣል።

አባቱን የማይሰማ ለአባቱ የማይታዘዝ ልጅነቱ ሊካድ ሊደመሰስ ይችላል። አባቶቻችንን መስማት አንዱ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን መዋቅራዊ ግዴታ ነው። ልጅነትን ለመስጠት ሥልጣኑ የእነርሱ ነው። ልጅነትን የመከልከል ሥልጣኑም የእነርሱ ነው። ቅዱስ ሲኖዶስ በዚኽ አሠራር የተገነባ መንፈሳዊ መዋቅር ነው። ይኽንን ጥሶ ገንፍሎ ወጥቶ የመንደር ተልእኮ ለማሳካት መሞከር መልእክቱ ሌላ ነው። እነ ተዐቀቡኬን የመሳሰሉ መጻሕፍት አሳትሞ ያሠራጨውን የቅዱስ ሲኖዶስ ውሣኔ በአንድ መድረክ ለመሻር ማን መብቱን ሰጠው? በሕግ፣ በሥርዓት አለመመራት አንዱ የተሐድሶነት መገለጫ ነው።

እውን ተሐድሶነት ኢየሱስ ብሎ መጥራት ነውን?

ኢየሱስ ኢየሱስ ማለትማ አይደለም ተሐድሶው መልማዮቹም ፕሮቴስታንቶቹ ሲጮኹት የሚውሉት ነው። ምናልባትም በዘወርዋራ ለእነርሱ ጥብቅና ሊቆምላቸው ፈልጎ ካልኾነ በስተቀር። እንዲህ ብሎ የጌታን ስም መጥራት የንጹሕ ክርስቲያንነት መገለጫ ሊኾን እንደማይችል ገና በማለዳ ራሱ የስሙ ባለቤት ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲኽ ብሎ ነገሮናል።

"በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል።የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችኋም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።" ማቴ ፯፥፳፪።

እነዚህስ ቢያንስ በስሙ ያደረጉት የሚመስል ምትሐታዊ ተአምር አድርገዋል፣ እርሱ ግን ከምኑም የለበት። የሚድኑ አሉ፣ ከኤች አይቪ ቫይረስ በጸሎቴ አድኛለሁ እያለ ከማምታት በስተቀር ምንም የሌለበት ባዶ ክህደት። እምነት አይሉት ክህደት ወንገርጋራ ሕይወት። በጸሎቴ ድነውልኛል ያላቸውም ቢኾኑ በራሱ መዝገብ ብቻ ያሉ እንጂ ምስክርነት ሲሰጡ አልታዩም። ብቻ ምን አለፋችሁ በአንዳንድ የቴሌቪዥን ጣብያዎች እንደምናያቸው በአየር ላይ እንፈውሳለን እንጸልይላችሁ ከሚሉት በምንም በማያንስ ሁኔታ እየተውረገረገ ቤተ ክርስቲያንን ማተራመስ ብቻ። ችሎታው ካለ በራሱም በቤቱም ያለውን ቃልቻዊ ጠባይ ምነው አላጠፋው?

በመጨኽ ደረጃ ከኾነ ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ኢየሱስ የሚለውን ስም ደጋግሞ በመጥራት ይጮኻል። እኛም ጠባችን ኢየሱስን በሚገባ ልክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደምትጠራው አድርጋችሁ እስካልጠራችሁ ድረስ የቤተ ክርስቲያን አይደላችሁም ብለን ነው።

እኛ፦

☞ ኢየሱስ ስንል አምላክ አማልእክት - የአማልክት አምላክ

☞ ኢየሱስ ስንል እግዚእ ወአጋእዝት - የጌቶች ጌታ

☞ ኢየሱስ ስንል ንጉሠ ነገሥት - የነገሥታት ንጉሥ

☞ ኢየሱስ ስንል አልፋ ወ ኦ - መጀመሪያው እና መጨረሻው፣ ፊተኛውና ኋለኛው

☞ ኢየሱስ ስንል ንጉሠ ሰማይ ወምድር - የሰማይና የምድር ንጉሥ

☞ ኢየሱስ ስንል ኤልሻዳይ - ኹሉን ቻይ

☞ ኢየሱስ ስንል አዶናይ - መድኃኔዓለም

☞ ኢየሱስ ስንል ወልደ አብ ወልደ ማርያም - የአብ ልጅ የማርያም ልጅ በተዋሕዶ ልደት የከበረ

☞ ኢየሱስ ስንል ፈጣሬ ኩሉ - ኹሉን የፈጠረ

☞ ኢየሱስ ስንል እግዚአብሔር ማለታችን ነው።

ስሙን ስንጠራ ይኽ ሁሉ በልባችን ሰሌዳ ታስቦ ነው። በድፍረት አንጠራውም፣ በፍርሃት በረዐድ በመንቀጥቀጥም እንጂ። እነዚያን አላውቃችሁም ያላቸው በድፍረት የሚጠሩቱን ነው። ሳያምኑ፣ ሳያውቁት በስሙ ብቻ ቁማር የሚጫወቱትን ነው። እነጸም ፋሲካውም ሳያምኑ ሲጠሩት እንቃወማቸዋለን። ክርስቶስ እነዚያን አላውቃችሁም እንዳላቸው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም አላውቃችሁም ትላቸዋለች።

ከነቢያት አንዱ ብለው የሚያምኑት እና የሚከተሉት እኮ ሞልተዋል። ስሙንም በነጋ በጠባ ይጠሩታል። እነርሱ ግን ስሑታን ናቸው። ምእመናንም አይደሉም። የእነ ቅዱስ ጴጥሮስ ዘገባ እኮ ያመለከተው ይኽንን እውነት ነበረ። ከነቢያት አንዱ አይደለም ጌታችን። እርሱ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ኢየሱስ ማለት ብቻ ዋስትና አይደለም ማለት ነው። እንዲች እንዲች እያሉ የውብድና ሥራ ለመሥራት በር መክፈት ለስርቆት ማመቻቸት ከተነቃባችሁ ቆይቷል። ይልቁንስ በቶሎ

ንስሐ ግቡ!

ቤተ ክርስቲያን ቅድስቲቱ ዐውደ ምሕረት የዘፈን የዳንኪራ ቤት እስክትኾን መሥራት ስለኾነ ተልእኮው ይኸው ዘፈናችሁባት። እንደ ሲኒማ ቤት ዘለላችሁባት። ዳንኪራ ረገጣችሁ። እናንተማ ሥራችሁ ነውና አደረጋችሁ። ግን ሌሎቻችንስ ምነው ዝምታችን! አባቶችስ እዚያው በመድረኩ የነበራችሁ እንዴት አስቻላችሁ? ልጆቻችን በሰው ሀገር በአረመኔዎች ፊት ሃይማኖታቸውን መሰከሩ እኛ ግን በቤታችን ዝም አልን። እንዴት ነው ነገሩ?

ማጠቃለያ

የምን ምስክር ምን እንዲሉ "ተሐድሶ የለም" ማለት የራስን ማንነት ማጋለጥ ነው። ዐይንን በጨው ታጥቦ የእደባባዩን እውነታ መካድ ሌላ ከሃዲነት ነው። አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀውን እውነታ ሸምጥጦ መካድ ያው ከሃዲነት ነው። እናም "ተሐድሶ የለም" ማለት ራሱ ተሐድሶነት ነው።

1/ ቃለ አዋዲ እና ታዖሎጎስ በቤተ ክርስቲያን ስም እንዳይነገዱ

2/ ተሀድሶ ክፍል ፭

3/ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ከዘመነ አርዮስ መናፍቃን ጋር እንዳመሳስለው

4/ የድረሱልን ጥሪ ከስልጤ ክርስቲያኖች

5/ የመናፍቃንን መዝሙር መስማት

6/ ዜና ውግዘት ዘ ሐራጥቃ ተሐድሶ በምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት!

7/ "ተሐድሶ የለም" ማለት የተሐድሶነት ማረጋገጫ

8/ "እመኑኝ! አደገኛ ችግር የሚፈጠረው "ፕሮቴስታንቱ" የመነኩሴ ልብስ ለብሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ዕለት ነው

Deacon Henok Haile

8/ "እመኑኝ! አደገኛ ችግር የሚፈጠረው "ፕሮቴስታንቱ" የመነኩሴ ልብስ ለብሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ዕለት ነው። አንድ ፕሮቴስታንት ያማረ ሙሉ ልብስ ለብሶ ወደ እናንተ ሲመጣ ላትቀበሉት ትችሉ ይሆናል። የመነኩሴ ልብስ ከለበሰ ግን የምታዩት እንደ አባት ነው።

በዚህ ዘመን እየገጠመን ያለው አሳሳቢ ችግርም ይኸው ነው። ሰዎች የኦርቶዶክሰረ ያልሆነ ትምህርትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያስፋፉ ነው። የእኛ ያልሆኑ ትምህርቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰርገው ሲገቡ ልታገኙ ትችላላችሁ። ከዚያስ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

አንዱ ተነሥቶ ጉባኤ ሲያዘጋጅላቸው "ፕሮቴስታንቶቹ"ም ግልብጥ ብለው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ። በጉባኤው መካከልም ያለማቋረጥ (አሜን ፣ ሃሌሉያ እያሉ) መጮህ ይጀምራሉ። ኦርቶዶክሳዊ የሆነ ትምህርት መሠጠት ሲጀመር ግን ጥለው ይሔዳሉ። ጉባኤውም ይዳከማል።

ይህን የሰጡን ሁኔታ በማመካኘት ሰዎችን ለመሳብ በሚል አንዳንዶች የፕሮቴስታንት ዓይነት ትምህርት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያስተምራሉ። ኦርቶዶክስ መሆን ማለት ግን ኦርቶዶክሳዊውን ትምህርት ብቻ ማስተማር ነው። (ኦርቶዶክስነት ኦርቶዶክስነት ነው)

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

ሚያዝያ 24 1999 እ ኤ አ የተናገሩት

(ምንጭ Return to Orthodoxy https://

Like · Meseret Kibret

ከቻልሽ ይህችን ተጭነሽ አድምጭ ።

ብዙ .....ማድመጥ ይጠቅማል ቆንጅትዬ.

Like . Ephrem Ebhrem

ለሜንኛውም የኛ አምላክ ሳይተኛ ሳያንቀላፎ ጠብቆናል እየጠበቀን ነው እስከእዘላለም ይጠብቀናል እደነ በጋሻውው አይነት ተኩላ ደግሞ እያንቀላፉ እደሚጠብቀን ምእመናን እያወናበደ በገዛ ቤታችን አውደምህረት

ላይ ቆሞ ሲያጭበረብረን አይተናል

ታዲያ ይሄ ሰው ደግሞ ወደ አውደምህረት እዲመጣ የፈቀደለት መነው ? አባቶችስ ቢሆኑ የኦርቶዳክስ የነሱ መኖር ይመስላቸዋል ? እኛ የሚጠብቁን አባቶች አሉ ብለን ለነሱ በበላይነት ሰተን እደዚ የበግ ለምድ ለለ

በሱ ተኩላዎች አሳልፈው ሲሰጡን ከነሱ

ውጪ ለመናፍቃን ፓስተሮች ልንናገር ይፈልጋሉን ? አሁንም ግዜው አረፈደም ልጁን እደሚጠብቅ አባት እልቅናው የተሰጣቸው ሰለሆነ እነዚን ተኩላዎች ከቤታችን አስወጥተው በጎቹን የመጠበቅ ግዴታ ስላለባቸው በራቸውን

የማጠናከር ግደታ እዳለባቸው መዘጋት

ያአለባቸው አይመስለኝም ውርደት ከመጣ መጀመሪያ የሚያጠቃው አባን ነው ልጅ የሚጎዳው ከዛ በኋላ ንው መቃት ለራስ ነው

Like · Samson H Galato

እንደነዚህ ያሉትን ማለታቸው ነው። እኛ ተኝተናል ቤታችንን ሰይጣን በእባብ እንደገባ እና ሄዋንን እንደጣላት እኚህም እንደምትመለከቱቱ

እያደረጉ ይገኛሉ። ትውልድ ንቃ።

Like . Yoanasab Gebreab

እኔምለው ከኦርቶዶክስ ኃይማኖት የተማራችሁት ሰው መጥላትን ነው እንዴ???

Like . Andargachew Gezahegne

በአሁኑ ሰዓት አገራችን እንደነዚህ አይነት ወይም እደገ፡ቀደሙት አባቶቻችን አይነት ነው ያጣችው ከእምነት ይልቅ ፖለቲካ እና አለማዊ ጥቅም ጠፍሮ ይዟቸው እምነታችንን በእነሱ ፍቅር ማጣትትና ፈረሀ እግዚአብሔር መጉደል ምክኛት ቤተክርስቲያን ለሁለት ተከፍላ የዉጭና የዉሰጥ ሰኖዲወሰ እየተባለ በሙሰና የቤተክርስቲያኗ ንብረቶችና ታሪካዊ አመጣጧን ሂሉ በሚንድ ሁኔታ ከአባታዊ ባህሪ ውጭ ብዙ ጥፋቶች እየፈፀሙ ይገኛሉ ህዝበ ክርስቲያንኑ ግን በእግዚአብሔር ቸርነት እሰካሁን አለ ወደፊትም በእግዚአብሔር ቸርነት ኦርቶዶክሳዊነቱን እንደጠበቀ ይቀጥላል! እነዚህ በኑዋይ እና በሰልጣን ምድራዊው የመንግሥት ከለላ በማድረግ እምነታችንን የሚያዳክሙ አባቶችን አምላክ ልቦና ሰጧቸው እምነታችን እንደ ቀደመው በእምነት መሪዎቹ እምነትና ክብር ኑሮት ከአምላካችን ጋር በሙሉ ፍቅር ለመገናኘት ያብቃን ፤ አሚን

ናቡቴ የተዋሕዶ ድምጽ

9/ ነገረ ተሐድሶ፦

እነዚህ ራሳቸውን “ተሐድሶ” ብለው የሚጠሩ አካላት ለራሳቸው ከማመን አልፈው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ያልሆነ መልክ በመስጠት ፕሮቴስታንታዊ የሆነውን የራሳቸውን አዲስ ትምህርት በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ በግድ ለመጫን እየተንቀሳቀሱ ነው። የእነዚህ አካላት ዋና ዋና ስልታቸው ሦስት ናቸው። እነሱም፦

1፤ አንደኛው ስልት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና አስተምሮ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊውና ከቀደምት ቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርት የተለየ እና የራቀ አስመስሎ ለማሳየት መሞከር ነው። ይህም የቅድስት ቤተ ክርስቲያንናችንን አስተምህሮዋንና እምነቷን፣ ምስጢራቷንና ሥርዓቷን፣ ይትበሃሏንና ትውፊቷን፤ በአጠቃላይ ሁለንተናዊ ሕወቷን በሙሉ ከጥንቱ ከጌታችንና ከሐዋርያት እንዲሁም ከሊቃውንት ትምህርት የራቀና የሚቃረን አስመስሎ ማሳየት ነው። ይህም ለቤተ ክርስቲያኒቱ መልኳ ያልሆነውን ሌላ መልክ በመስጠት ሰዎች ከልቦናቸው ውስጥ እንዲያወጧትና እንዲጠሏት ለማድረግ የረዳናል በሚል ነው። ለዚህ ዓላማቸውም ቤተ ክርስቲያኒቷ የምታምነውን እንደማታምን፣ የማታምነው ደግሞ እንደምታምን፣ የምትለውን ደግሞ እንደማትል፣ የማትለውን ደግሞ እንደምትል እያስመሰሉ ያለ ይሉኝታና ያለ ኃፍረት ደጋግመው ጽፈዋል።

ተሐድሶዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐዋርያዊ እና ኦርቶዶክሳዊ የሆነውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን አስተምህሮ ጥላሸት ለመቀባት ይረዳናል ያሉትን ነገር ሁሉ እንዳችም ሳያስቀሩ አሟጠው ለመጠቀም ሞክረዋል። ጽሑፋቸው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን በመንቀፍና

በማጥላላት ላይ ያተኮረና ያመዘነ ነው። ለዚህም እነርሱ ሌሎችም የሚነቅፉበትን ነገር ሳይቀር ለራሳቸው ሲሆን ደግሞ በአዎንታ ተቀብለው ተጠቅመውበታል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆኑ ብዙ ምንጮችንና ነገሮችን ከመጠቀማቸውም ባሻገር ባለቤትነታቸው ከሚታወቁት ሆነ ከማይታወቁ ተረቶችና ወጎችን እንኳ ሳይቀር ቤተ ክርስቲያኒቱ ለመንቀፍ የሚጠቅም መስሎ እስከታያቸው ድረስ ለመጠቀም ሞክረዋል። አንድን ነገር ደግመው ደጋግመው በመመላለስና ስድቡና ነቀፋውም ቢሆን መልኩን ከመለወጥ በስተቀር ያለቀባቸው መሆኑን አፍ አውጥቶ እስኪናገር ድረስ ያንኑ ነገር በየመጣጥፎቻቸውና በየገጹ ያቀርባሉ።

ተቀባይነታቸውን ለማስፋት ሲሉም "ኦርቶዶክስ" የሚለውን ከሁለት በመክፈል ራሳቸውን "የጥንቱ ኦርቶዶክስ" ብለው ሲመድቡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምታምነውና የምታደርገውን ደግሞ ከጥንቱ የተለየ ነው ለማለት "የአሁኑ ኦርቶዶክስ" የሚል ታርጋ ሊለጥፉላት የሞከሩም አሉ። ይህም ራሳቸውን ፕሮቴስታንት አይደለንም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነን ለማለት ነው። ይህን መጠቀም የሚፈልጉትም ቤተ ክርስቲያኒቷን ከውስጥ ሆነው ሙሉ በሙሉ ቀስ በቀስ በሂደት በመሸርሸር ኦርቶዶክሳዊ ማንነቷን በማሳጣት ፕሮቴስታንት የማድረግ ስውር ዓላማቸውን ከዳር ለማድረስ እንዲረዳቸው ነው።

ሁሉተኛ፦ ተሐድሶዎች ራሳቸውን በየመጣጥፎቻቸውና በየገጹ፣ በንግግራቸው ሁሉ "የጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን" እንደሆኑ ለማሳየት እንዴት እንደሚዳክሩ "መድሎተ ጽድቅ" (የእውነት ሚዛን ቅጽ ፭) በሠፊው ያትታል። ወዘተ. . .

ሦስተኛ፦ ስልታቸው ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእምነት አስተምህሮ ላይ ያቀረቡት ነቀፋና ማሳጣት እውነት ለማስመሰል ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርቶች መካከል ለሃሳባቸው ድጋፍ ይሆናል ያሏቸውን የተወሰኑ ነገሮች ለመጠቃቀስ መሞከር ነው። ወዘተ. . .

ምንጭ፦ “መድሎተ ጽድቅ” (የእውነት ሚዛን ቅጽ ፭)

(የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ስውር ደባቸውንና ማንነታቸውን፣ አጠቃላይ ስራቸውን ፍንትው አድርጎ የሚያስቃኝና ሊነበብ የሚገባ እጹብ ድንቅ ምላሽ! እናም ሌሎች እጅግ ምጡቅ፣ በጥልቀትና በምርመራ፣ በመረጃና በማስረጃ የደገፈና የተጻፈ ልዩ መጽሐፍ ነው፤ “መድሎተ ጽድቅ” የእውነት ሚዛን! አንብቡ፣ ለሌሎችም ያስነብቡ!።)

October 18 at 1:05am ·

Friends of Friends

More

6 people like this.

Kidistarega Ayele

ኑ እዩት። ጉባኤው 4 ኪሎ በሚገኘው ቱሪስት በፊት ለፊት ባለው አዛውንቶች አዳራሽ እራሳችሁትዘግቡታላችሁ አዳራሽ ለምን ተከለከለ

ወደፊት እናይዋለን

Report · Oct 18

Aschalew Gerbaw

ህዝባችን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እየሄደ ስለሆነ ጥሩ መረጃ ነው እግዚአብሄር ጥንካሬውን ይስጥልን : :

Report · Oct 18

Kidistarega Ayele

የዛሬው በጉባኤ በምድራዊ ሰዎችቢታገድም ሰልፉን የእግዚአብሔር ነው የተዋህዶ ልጅ። በርታ ንቃ በሀይማኖት ጽና በጉባኤው በአባቶቹ በጸሎተ ወንጌል። ተከፍቶ በዘማርያንልዩ ጣእመ ዝማሬን ካስሙ በጐዋላ በእማሆይ ገጥሞ ተነቦ በቀሲስ ምንዳዬ ብርሀኑ 2 ዝማሬ ከቀረበ በሑዋላ በፖሊስ ሀይል። በጸሎት። ተዘጋ ለኛ እግዚአብሔር። ረድቶናል ምግቡን በመያዝ መቄዶንያ ሄደን ደስ ብሎናል እግዚአብሄር ቢፈቅድ በቅርቡ ጉባኤው። ይደገማል ከርስቲያን በትህትና ነው በአመጽ። አያገለግልም መናፍቅ ይማር እኛ ን ከመንግስት አጋጭተው ሁኡከት ለማስነሳት እኛከ በክርስቲያኖች ነን ከጥንቶቹ አባቶቻችን ትእቢት አልተማርንም ዲ/ተስፋዬ ሞሲሳና የድሬትዩብ ጋዜጠኛ ለ 3 ሰአታት ቢታሰሩ የጳውሎስና ይሲላስን በረከት አገኙይህ ለመናፍቃ እፍረት ነው ከቤታችሁ ወጡ ከሚሉን ቤታችንን ይልቀቁልን

Yared Gebremedhin

10/ አውሮፓን ጅብ ያስበላ የሉተር ስብከት

በተዋሕዶ መድረክ

ከሀገር ቤት ከወጣሁ አሥረኛ ዓመቴን እየያዝኩ ነው።በዚያን ጊዜ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ መናፍቃን በቡድን በመደራጀት እንቅስቃሴ ጀምረው ነበር።እኛ ያልዘመርንበት ሰርግ ምኑን ሰርግ ሆነ።እኛ ያልተገኘንበት ጉባኤ እንዴት ጉባኤ ሊባል ይችላል በሚል የሌላውን አገልግሎት ሁሉ ባዶ አድርገው እራሳቸውን ሲያስቀድሙ አስታውሳለሁ።በወቅቱ ከጥቅም አንጻር ብቻ የሚደራጁ የመሰላቸው ጥቂቶች አልነበሩም።አካሄዱ ግን ከጥቅም ባለፈ ሌላ የተለየ ዓላማ ከጀርባው እንደነበረበት ያስታውቃል።ያን ጊዜ በተደጋጋሚ ሲናገሩት የሚሰማ ትልቁ አጀንዳቸው “ጌታ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አልተሰበከምና እርሱን መግለጥ አለብን” የሚል ነው።ይሄ አጀንዳ ደግሞ ምንጩ ማን እንደሆነ እናውቀዋለን።እነዚህ ቀሚሳችንን ለብሰው በድፍረት የሚውረገረጉ ውሉደ መርገም የተሐድሶ ማናፍቃን ተላላኪዎች ናቸው።እንዲህ የሚሯሯጡት የተሰጣቸውን ተናግረው የእለት ጉርስ ለማግኘት ነው።ዋነኞቹ እና በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ይህ መልእክት እንዲተላለፍ የሚፈልጉት ግን በምዕራቡ ዓለም የዘሩት የሉተር እምነት የጠወለገባቸው ፕሮቴስታንቶቹ ናቸው።ፕሮቴስታንቶቹ የሉተር እምነት በምድር አውሮፓ ጠውልጎና ደርቆ ሲመለከቱ ለጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን “ጌታን ሊገልጡ” ሚሴዎናውያንን ላኩ ሚሴዎናያኑ ደግሞ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አራማጆችን ልከው ሕዝቡን ማደናቀር ያዙ።ለቀባሪ ማርዳት ይሉሃል ይሄ ነው።

በአውሮፓ ተዘርቶ ያልበቀለ፣ሕዝቡን ለእስልምና እና እግዚአብሔር የለም ለሚል ፍልስፍና አሳልፎ የሰጠ ከንቱ እምነት፣ሉተር የመሠረተው የፕሮቴስታንት እምነት እኛ ሃገር ለመዝራት መሞከር ተሳልቆ ወይም ምቀኝነት እንጂ ሌላ ምን ይሉታል።በምድረ አውሮፓ ወደ ሉተራውያን"ቤተ ክርስቲያን"የሚሄድ ሕዝብ ጠፍቷል።ከዚህ ይልቅ ሕዝቡ እግዚአብሔር የለም በሚል ፍልስፍና ኢአማኒ ወደ መሆን ተሸጋግሯል።በሚሺነሪ ታሪክ የምትታወቀው አፍሪካን በፕሮቴስታን እምነት ለማጥለቅለቅ ሌት ተቀን የምትሰራው ስዊድን እንኳን ከሕዝቧ ቁጥር 34 ፐርሰንቱ እግዚአብሔር የለም ብሎ እንደሚያምን ጥናቶች ይጠቁማሉ።የእግዚአብሔር መኖር የሚያምነው ደግሞ 27 ፐርሰንት የሚሆነው ብቻ ነው።በፈረንሳይም 40 ፐርሰንት የሚሆን ሕዝብ የእግዚአብሔርን ሕልውና የማይቀበል ሰሆን የእግዚአብሔር መኖር አምኖ የሚቀበለው ደግሞ 18 ፐርሰንት ብቻ ነው። በመካከል የለም አለ ሳይል የሚኖር ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ እንዳለም ልብ ይበሉ(1)።

ሌላው በ2011 እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው በታላቋ ብሪቴን ክርስቲያን ነን ብሎ የሚያምነው 72 ፐርሰንት ሲሆን "ቤተ ክርስቲያን" የሚሄደው ህዝብ ግን 1.4 ፐርሰንቱ ብቻ ነው።ሉተር በተፈጠረባት ሀገር በጀርመን 72 ፐርሰንቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ክርስቲያን ነኝ ብሎ የሚያምን ሲሆን "ቤተ ክርስቲያን" የሚሄደው 1,2 ፐርሰንቱ ብቻ ነው(2)።ከዚህ አንጻር ሁለት ፐርሰንት የሚሞላ ሕዝብ "ቤተ ክርስቲያን"የማሔድባቸው ሃገሮች(እንግሊዝ፣ጀርመንን የመሳሰሉ ሀገሮች)“ዓይናችሁን በወንጌል እናብራ አዲስ ጌታ

እንስበካቸሁ"በሚል መነሳታቸው ብቻ ሳይሆን ማሰባቸው በራሱ እጅግ እጅግ የሚያስገርም ነው።ነገሩ የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስላለች ይመስላል።

ጥንታውያኑ አብያተ ክርስቲያናት ከጌታችን እና ከሐዋርያት የተቀበሉትን ክርስትና ይዘው በብዙ ፈተና ሳይፈቱ ዘመናትን ስለመሻገራቸው ዓለም በሙሉ የሚያውቀው እውነታ ነው።ሶሪያ፣ግብፅ፣አርመ

ን፣ኢትዮጵያ ሕንድ፣ኤርትራ ..... ለዚህ ሕያው ምስክሮች ናቸው። ከገጠማቸው ፈተና ከድህነታቸው አንጻር እግዚአብሔር የለም ለማለት የሚቀርቡት እነርሱ ነበሩ።ነገር ግን የያዙት እምነት (ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) በዓለት ላይ የተመሠረተች በመሆና ልጆቿ ችግር ሳይፈታቸው በመከራ ውስጥም እየጸኑ ወልድ ዋሕድ ሲሉ ይኖራሉ።አንዳንድ ጌዜ ሰይጣን ኃይል እና ጉልበት በመጠቀም የእነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ልጆች ሲያርድ እና ሲገድል የምናየውም ለዚህ ነው።አሁን አሁን ዶግማ፣ቀኖና፣ትውፊት ምን እንደሆነ ለማወቅ ዓለሙ ወደ እነዚህ አብያተ ክርስትያናት መገስገስ ጀምሯል።የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለመረዳት ዓለሙ ወደ ጥንታውያኑ አብያተ ክርስቲያናት እየቀረበ ነው።በነገረ ክርስቶስ ላይ የሚያስተምሩትም ትምህርት ይህ ይጨመርበት ይህ ይጎድለዋል የሚባል አይደለም።

ታዲያ የጥንካሬ ተምሳሌት ለሆኑ፣የጠራ ትምህርተ ሃይማኖት ላላቸው ለእነዚህ አብያተ ክርስተያናት አዲስ ወንጌል መላክ ምን ይሉታል ? እንዴትስ ያለ ድፍረት ነው ? ክርስቶስን አማላጅ የሚል የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ሌሎች ቅዱሳንን ክብር የሚያቃልል አዲስ ወንጌል፣ጾም ጸሎት አያስፈልግም የሚል አዲስ፣ወንጌል ለተዋሕዶ ልጆች

ለምን አስፈለገን ? ይህ አዲስ ትምህርት በሉተራውያን ሻንጣ ወደ ሃገር ቤት ገብቶ ውሉደ መርገም በሆኑ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ እምነት አራማጆች በኩል በተዋሕዶ አደባባይ ካልተዘራ የሚል ትንቅንቅ ተይዟል። ተዋሕዶ ስዊድን እና ጀርመንን እንድትታደግ ድረሺልን የሚል ጥሪ መስማት ሲገባት ሕዝባቸውን አምላክ የለሽ ባደረጉ ፕሮቴስታንቶች ደጃፎቿ እየተንኳኳ ነው።ለማንኛውም እኛ የክርስቶስ ወንጌል ሳይበረዝ እና ሳይከለስ የደረሰን ነን፣የድንግል ማርያም የቃል ኪዳን ልጆች ነን።ስለዚህ አውሮፓን ጅብ ያስበላ የሉተር ስብከታችሁን ይዛችሁ ከመድረካችን ውረዱ።

ቀሲስ ያሬድ ገብረ መድኅን (ኮለምበስ ኦሀዮ)

ናቡቴ የተዋሕዶ ድምጽ

11/ ተሐድሶ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተጀመረ ሰማንያ ዐመታትን አስቆጥሯል። በእነ አልፍሬድ ባክስተንና ዳቪድ እስክስ ተዘርቶ፣ በእነ መሠረት ስብሐት ለአብ ውኃ አጠጭነት አድጎ፣ በፕሮቴስታንቶች የገንዘብ ድጋፍ፣ በብዙ የልማት ደርጅቶች እርዳታ ከዚህ ደረሰና በእነ በጋሻውና አሰግድ አቅራቢነት ዕለት ዕለት እንድንሰማው ተገደድን። ግን እነ እገሌ ተሐድሶ ናቸው ብለን ከማውራት ያለፈ ለሥራ እና ለዓላማ መረጃ የምንፈልግ ሰዎች ስንቶች ነን? ብዙዎቻችን መረጃ የምንፈልገው ማን ምን እንደሆነ ለማወቅ እና ለማውራት እንጂ የተሐድሶዎችን ስልትና አካሔድ ተረድተን ቤተ ክርስቲያንን ከከፋ አደጋ ለመታደግ አይደለም። በግለሰብ ፎቶ ላይ ስንት አስተያየት የምንሰጥ ሰዎች በተሐድሶ ጉዳይ የመወያያ ርእሰ ጉዳይ

ስንጠየቅ ምንም አለማለታችን ያሳዝናል። ይህን ጊዜ ፖስት የተደረገው “ከወንድና ከሴት ማን ይሻላል” ዐይነት ወሬ ቢሆን ኖሮ 1000... ላይክ፣ 9000 ኮሜንት፣ 100000 ሼር እናይ ነበር። ደግሜ እላለሁ ከፊዝ ቡክ እንውጣ ወደ ፊስ ቡክ እንግባ። ለቤተ ክርስቲያን አሁን ካለችበት በላይ አስጨናቂ ጊዜ የለም። ቢያንስ አሳብ ለማዋጣት አንድከም።

Like . Gashaw Tarekegn

ህዝቡ ሀሳብ የማያዋጣው ለምን መሰለክ እምነቱን በጽኑ መሰረት ልቡ ላይ አላስቀመጠም እርግጠኛ ነኝ የኦርቶዶክስ አማኝ በልምድ በባህል የወረስነው ሀይማኖት መስሎ ሚታየን ብዙዎቻችን ነን ከልጅነቱ ጅምሮ ለገብርኤል ለሚካዔል ለድንግል ማርያም .....ለፆድቃን ስእላት ድፍት ብሎ ሲሰግድ ዝም ብሎ የታለፈ ነገር ዛሬ ላይ ችግር ፈጠረ ስንቶቻችን የፀጋና የእምልኮ ስግደት የተምታታብን ስዎች እኮ ነን እነዚህንና ሌሎች መሰረታዊ ጉዳዩችን ጠንቅቆ የማያውቅ ምእመን ተይዞ ሁሉ ነገር ይከብዳል በዚህ ክፍተቶቻችን ስንቶች ጴንጤ ሆኑ አሁንም መሰራት ያለበት ብዙ ነገር አለ ከላይ ጀምሮ:::::

Like . Kidist Shifarew

አብዛኛዎቻችን እንዴት እና በምን መንገድ። ነው እኛ ለቤተክርስቲያናችን መቆም የምንችለው ማለትም አብዛኛዎቻን ውስጣችን ቢታይ ድክመታችን ይበዛ ሆኖም ግን ሁላችንም በምንችለው ሁሉ ከቤተክርስቲያናችን ጎን። እንቆማለን በሁሉም።እግዚአብሔር ይቅደም

Like . Alemneh Befrdu Tesema

.....engedi men enelalen egziabher

yabetkrestiyanen tensae yasayen tegu xebaqi yeseten yegn cuhet waga iyaxanew eko .....sele tahedeso xebaqiwochu zem aluu !!!

Like . Lij Redeat Gorbi

We can't tolerate them. Here we are on side of Our Mother Church

Like . Bisrat Terefe

Egziabher sow fetro sow ayatam,yetekedemn bimeslachewum manim aykedmenim,lemin kefitlefit mimeran yeEgziabher hayl newuna, egziabher birtatun yisten.

Like . Frhewot Tesfaye

ናቡቴ የተዋሕዶ ድምጽ

12/ “ክቡር መጋቤ ሐዲስ” በጋሻው ግን እንደ አባ ሰላማ ድረ ገጽ ማኅበረ ቅዱሳንን ካልተሳደብ መስበክ አይችልም እንዴ? በአንድ ወቅት ኢቢኤስ ላይ ቀርቦ “እንደተቋም ኢትዮጵያ ውስጥ ተሐድሶ አለ ብየ አላምንም፣ ካለ ቦታውንና ቢሮውን ቢነግሩን” ብሎ ነበር። እንደተቋም የምትለዋን ግን አስምሩልኝ። እንደ ተቋም ማለቱ በግለሰብ ደረጃ ተሐድሶ

እንዳለ ያውቃል ወይም ቢያንስ ራሱ ተሐድሶ መሆኑን ያምናል ማለት ይሆን። ለእናንተ ትቼዋለሁ። ይህንን ባለበት አፋ ግን ቦንጋ ሒዶ ስለ ተሐድሶ በስውር የሰጠው ሥልጠና ይህን መስል ነበር፦

• ተሐድሶ የሚለው ቃል ፖዘቲቭ ነው ... ይህንን ቃል ይዘው በዋነኛነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ ተነሥተዋል የሚል የመድረክ ወሬ በማውራት በወንድሞቻቸው ላይ የሐሰት ክስ ከፍተው በይፋ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች፣ ወይም ደግሞ ማኅበረ ቅዱሳን የሚባለው ቡድን ነው። (2 ኛው ደቂቃ ጀምሮ)

• ሁላችንም የተጠለልንባት፣ ትልቋ፣ ጨዋዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት። ሌላው ደግሞ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን አሁን ከ 1984 ... ጀምሮ በውስጧ እንደ ፈለግ እየኮበኮበ ነው። እንደ ፈለግ ሞቷ ላይ የሚያኮበኩበው ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን የሚባለው ቤተ ክርስቲያን ነው። (5 ኛው ደቂቃ ጀምሮ)

• ይህ ማኅበር ራሱን ማኅበረ ቅዱሳን ብሎ ለራሱ ይህን ስም ሰጥቶ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ራሱን ያበቀለ ማኅበር ነው። (7 ኛው ደቂቃ ጀምሮ)

• 1984 ላይ መንግሥት ዐዋጅ ዐወጀ .... በዚያ ጊዜ በብላቴን የተደራጁት የትናንትናዎቹ አንጃዎች የዛሬዎቹ ማኅበረ ቅዱሳን ወይም ቤተ ክርስቲያንን እንጠብቃለን የሚሉት ሰዎች በየዩኒቨርሲቲው ገቡ። ዩኒቨርሲቲ ገብተው ትምህርት እንደጀማመሩ ቀጥታ ይህን መንግሥት በብረት አይደለም በብዕር እናወጣዋለን የሚል ስውር ስብሰባ ነበር። እንዴት ነው የምንዋጋው ብለው ሲያስቡ ትልቋን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጠጋት

ነው። (10 ኛውና 11 ኛው ደቂቃ)

• መጀመሪያ ማኅበረ ቅዱሳን እንደ ማኅበር ራሱን ገናና አድርጎ ለማቆም ጠጠር የወረወረበት ማኅበር ሃይማኖተ አበው የሚባል ማኅበር ነው። ... ይህን ማኅበረ ለማፍረስ ማኅበረ ቅዱሳን የተጠቀመው ቀላልና አጭር መንገድ ይህች ዛሬ ተሐድሶ የሚላት ናት። ለምሳሌ፦ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኦርጋን፣ በኪቦርድ ትጠቀም ነበር። (16 ኛው ደቂቃ ጀምሮ)

• በ 1990 ዓ.ም ላይ እነ ጽጌ ሥጦታው ወንጀል ባይሠሩም፣ ጥፋት ሠረተናል ባይሉም የቀኖና ጊዜ ነው ተብሎ ደብረ ሊባኖስ የሐዱት ሲኖዶሱ ትንሽ የጸሎት ጊዜ ይኑራቸው ተብሎ ነው፣ ቀኖና አይደለም። ሲሐዱ ግን እነዚህ ከአዲስ አበባ ደውለው መናፍቃን መጥተዋልና በአሉበት ቦታ ቀጥቅጣችሁ ግደሉ ሊያጠፉት ነው ደብረ ሊባኖስን ይሏቸዋል። የቆሎ ተማሪ ምን ያውቃል፣ ... እንዳይሞቱ እንዳይተርፉ አድርገው ቀጥቅጠው፣ ቀጥቅጠው ሞተዋል ብለው ውሻ ገደል ላይ ጥለዋቸው ሐዱ። እነዚህ ሰዎች (እነ ጽጌ ማለቱ ነው) ታንክ ይዘው መጥተው ይህችን ቤተ ክርስቲያን ቢመቷት ራሱ ይገባቸዋል። ይህን ያህል ወንጀል ነው የተፈጸመባቸው። ቤተ ክርስቲያኗ ይህን አላደረገችም ይህን ያደረገው ማኅበረ ቅዱሳን ነው። ... መመለስም አይቻልም እኮ ችግሩ ይሄ ነው፣ መመለስም መውጣትም አይቻልም። ስለዚህ ይህ ክፉ የሆነ መርዝ አስተሳሰብ ማኅበረ ቅዱሳን ልምድ ውስጥ አለ። በማሳደድ፣ ጀርባ በማጥናት፣ ሰውን ክፉ ስም በማሸከም ... ነው የሚያምኑት። ... እኔ ሰዎቹን ሰይሆን አስተሳሰቡን እጠላዋለሁ። ማኅበረ ቅዱሳናዊ አስተሳሰብ በፍጹም ቤተ ክርስቲያናዊ

አስተሳሰብ ስላልሆነ። (20 ኛው ደቂቃ ጀምሮ)

• ይህ ማኅበር ማጥፋት፣ መግፋት፣ ማበላሸት ነው የሚፈልገው። (27 ኛው ደቂቃ ጀምሮ)

ብሔረ ጽጌም ሒዶ ያደረገው ይህንኑ ነው።

Like . አንተ ታውቃለህ ጌታ ሆይ

የሀራጥቃ እራስ ምታት ማህበረ ቅዱሳን

Like . Abebaw Terefe

እኔ ግን ማህበረ ቅዱሳን እግዚያብሔር ይህን አዉቆ አስቀድሞ ባይመሰርት ኖሮ ይች ቤተክርስትያን ምን ትሆን ነበር ብዬ ሳስብ ከሁለት አንዱ ያጋጥማት ነበር ብዬ አስባለሁ,1 እንደ ህንድ ቤተክርስትያን ከሁለት መከፈል ወይም ስርዓቷ ና ዶግማዋን ያጣች ሉተራዊ ቤተክርስትያን።ነገር ግን ከኛ የበለጠ ለቤቱ እርሱ ይጨነቃልና ይኸ የቤተክርስትያን ችግር እንደሚከሰት ያዉቃልና በ'ባቶቻችንና በወንድሞቻችን ላይ መንፈስ ቅዱስን አሳድሮ ይኸንን ማህበር መሰረተልን።መናፍቃን በያ'ቅጣጫዉ ቢንጫጩ በክርስቶስ ደም የተመሰረተች ቤተክርስትያን ማጥፋት አልቻሉም።

Like . Alem Yakidana Mherat Lij

የእግር እሳታችሁ እንደናንተና እንደሰይጣን ክስማ ቢሆን ገና ድሮ በተበተነ ነበር ነገር ግን ይህን ማህበር እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው ያሰባሰበልን በዚህ ክፉ ዘመን እንደዚህ መናፍቃን እና ተሀድሶ ባበደበት ዘመን እነሱ ባይኖሩ ..... ?????? ድንግል ወላዲተ አምላክ ይህን ማህበር አንቺ በቃል ኪዳንሽ ጠብቂልን

Belay Worku

ካለፈው የቀጠለ

13/ ታኦሎጎስ እንደ የሌሊት ወፍ

የሌሊት ወፍ አቅጣጫ ጠቋሚዋ ድምጿ ከሌላ ነገር ጋር ነጥሮ ሲመለስ በምታገኘው ግብረ መልስ ሲሆን ታኦሎጎስና ታኦሎጎሳውያንም የኑሮ፣የቲፎዞ፣የእንቅስቃ

ሴ አቅጣጫ ዋና መሳሪያቸው ድምፃቸውን ሲያሰሙ በሚሸጠው የካሜት መጠን እና እልልታና ጭብጨባ ሙቀት መጠን በመሆኑ እንደ የሌሊት ወፍ ያልኩት ለዚህ ነው።የሌሊት ወፍ ከሌሎች አእዋፍ የሚለያት በክንፏ ወፍ በጥርሷ እና በጡቷ እንስሳም የምትመስልበት ጠባይ ስላላት ሲሆን ታኦሎጎሳውያንም እንደ ሌሊት ወፍ በልብሳቸው ኦርቶዶክስ በአገልግሎታቸው ፕሮቴስታንት ስለሚመስሉ።የሌሊት ወፍ አይጥ ነሽ ሲሏት ይሄው ክንፊ ወፍነሽ ሲሏት ይሄው ጥርሴ እንድትል መናፍቅ ሲባሉ ዱሮ ስለ ማርያም የዘመሩትን በድጋሚ በካሜት ማሳተም በታኦሎጎስ መዘመር ኦርቶክሳዊ አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ የመደር ስልጠና ማስፍፍት እና ቤተክርስቲያኗን በአስተምህሮ እና ሥርአቷን በመጣስ ልኮነት ማሳየት ሌላው ቀርቶ በቅርቡ ብሄረ ጽጌ በተደረገው ጉባዔ ተናጋሪው በስብከቱ ቦሩ

ሜዳ ይዘጋጅልን ሲል ቀናኢ የቤተክርስቲያን ልጆች የቀዱትን አሰሙኝ እና ገረመኝ ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮህል እንዲሉ ቦሩ ሜዳ ማለቱ ሦሥት ነገር ያመለክተናል

1 ኛ፦ትእቢቱን እነመህምር አካለወልድ በተቀመጡበት ጉበኤ ለመቀመጥ እራስን መምረጥ

2 ኛ፦የቦሩ ሜዳ ጉባዔ የተካሄደው የሀይማኖት ልዩነት ባላቸው ሁለት ክፍሎች የራሳቸውን አስተምህሮ ይዘው ነው።ታዲያ በእኛና በእርሱ መሀል የሃይማኖት ልዩነት መኖሩን ከተረዳ ቦሩ ሜዳ ድረስ ምን ወሰደን ወይ ንስሀ ይግባ ወይ ጠቅሎ እርሱ አዳራሹ ይግባ እንጂ

3 ኛ፦እራሱን በነቢዩ ኤልያስ ሌላውን በአክአብ እና በኤልዛቤል መስሎ ተናግሮአል እንዳይክድ የተቀረጸው በእጃችን አለ ታዲያ ይህን ስብከት እኮ በነጀማነሽ ጉባኤ ላይ እንጂ በቤተክርስቲያን አውደምህረት የሚሰበክ አልነበረም።

ወደቀደመው እንመለስ እና የሌሊት ወፍ እንደ ሌሎቹ አእዋፍ የራሷን ቤት ሰርታ የምትኖር ሳትሆን በሰው ቤት ወይም በዋሻ ተጠልላ ያን የተጠለለችበትን ቦታ አካባቢ ማቆሸሽ ነው ታኦሎጎሳውያንም የራሳቸው የሆነ ነገር ሳይኖራቸው የተጠለሉበትን ቤት ማበላሸት እና የአማኙን ልብ ማቆሸሽ ነው። የሌሊት ወፍ አእዋፍ በሚንቀሳቀሱበት በቀን ሳይሆን በጨለማ ነው የምትንቀሳቀሰው ድምጿም በእረፍት ላይ ያለውን ባለቤቶችን ጥገኛዋ የሌሊት ወፍ ሰላም በመንሳት ትረብሻለች ታኦሎጎሳውያንም በጨለማ በሚመሰል የክህደት አገልግሎት የቤተክርስቲያንን ሰላም በሚያውክ እና የምእመናንን ሰላም በሚነሳ መዝሙር መሰል ዘፈን የቤቱን ባለቤት

አስመርሮ ከቤት ማስወጣት ነው።ስለሆነም እኛ ዝም ብንልም የቤቱ ባለቤት ስለ ቤቱ ዝም አይልም ጅራፍ አለው ማቴ 21፡12 ነገር ግን እኛም ድርሻችንን ልንወጣ ይገባል ቤታችንን ከሌሊት ወፍ እና እርሷ ከፈጠረችው ቆሻሻ እናጽዳ ለዚሁም የቅዱሳን አምላክ የድንግል ማርያም ልጅ እኛንም ይርዳን እነሱንም በጊዜ ወደልባቸው መልሶ ለንስሀና ለይቅርታ ያዘጋጃቸው።

ናቡቴ የተዋሕዶ ድምጽ

Abayneh Kassie

1 hr ·

14/ ሐራጥቃ ተሐድሶን የሚከላከል ብሎም የሚያጸዳ አካል ይኑረን!

ሐራጥቃ የሚለውን ቃል አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ እንዲህ ይተረጉሙታል። "መናፍቅ፣ ጠዋየ ሃይማኖት፣ ባህሉ እና ትርጓሜው ከመጽሐፍ ከንባብ የማይገጥም፤ መጻሕፍት አዎ ያሉትን አልቦ- አልቦ ያሉትን አዎ የሚል፤ የእርሱን ሀሳብ ብቻ የሚከተል፣ የጨዋ የወታደር ዓይነት ነገሩ ከጨዋ የሚስማማ፣ ከሊቃውንት የማይስማማ፣ እንደ አርዮስ እንደ ንስጥሮስ እንደ አውጣኪ ያለ" ይሉታል። ጠዋየ ሃይማኖት ማለታቸው ሃይማኖቱ የተወላገደ ጠማማ ለማለት ነው።

ሰሞኑን አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ይልቁንም እንደ መዥገር ተጣብቀው ከቤታችን ውጡልን ልቀቁልን ብንላቸውም የዝኖን ጆሮ ይስጠን በማለት እምቢ ስላሉት ዘመን አመጣሽ የውጭ ተላላኪዎች በተመለከተ

በሚገልጣቸው እንጂ በማይገልጣቸው አንጥራቸው የሚለውን ሀሳብ በቀና በመቀበል እና በመቀባባል የሃይማኖት ቤተሰቦች ያደረጋችሁትን ርብርብ በማየቴ እጅግ በጣም ደስታ ተሰምቶኛል። አንድ የመኾናችን አንዱ ምልክት እንደኾነ በጣም አድርጎ ይናገራል።

ከእንግዲህ ለእነዚህ ቃል አናበላሽም። ሐራጥቃ ተሐድሶ መባላቸው ያንገበገባቸው አንዳንዶች የሰጡትን ሀሳብም ለመመልከት ሞክሬያለሁ። እነርሱ ይከፋቸዋል ብለን "መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ" ዓይነት አካሄድ አንከተልም። እነዚህ ሐራጥቃ ተሐድሶዎች ዓይነታቸው ሦስት ነው። እነዚህንም በየፈርጃቸው በሌላ ጦማር እንመለከታቸዋለን።

ሐራጥቃ ተሐድሶን ስንዋጋ ከስሜት ነፃ መኾናችንን እናረጋገጥ ዘንድ ይገባል። እነርሱ ከሟ ዓመታት በላይ በተለዋዋጭ ስልት የደከሙበትን መረብ ለመበጣጠስ ጥንቃቄ ይፈልጋል። አረሙን ለመንቀል ሲባል ንጹሕ ዘርም እንዳይነቀል መጠንቀቅ አለብን። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ሐራጥቃ ተሐድሶን እና አማሳኞችን አንድ የሚያደርጋቸው መስመር እየተዘረጋ መኾኑ ፍንትው ብሎ እየታየ ነው። የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚለው ዓለማዊ ፍቅር እፍ ከንፍ እያሉ መኾናቸውን እየታዘብን ነው። ይኽ ደግሞ አበክረን እንድናስብበት ያስገድደናል።

የተዋሕዶ ልጆች በየአጥቢያቸው እያሳዩት ያለው ጥብዐት የተመላበት አገልግሎት ይበል የሚያሰኝ ነው። ርስትን ይዞ እንጂ ለቅቆ መደራደር ያስጠቃል። ታፍነው የነበሩ መረጃዎች በየገጸጦማሩ መለቀቃቸው አስደንጋጭ ሁኔታን በሐራጥቃዎች ዘንድ ፈጥሯል። አሁን በምእመኑ እጅ የተያዙ አስረኞች ናቸው። ከመሳቀቃቸው የተነሣ የቀን እንቅስቃሴያቸውን

እንደ ግብር አባታቸው በጨለማ እያደረጉት ነው። ይኽም አንድ ድል ነው። ሊያነጋግረን የሚገባው እና ሁላችንም ለራሳችን ቃል እንድንገባ የሚያስፈልገው ሰሞኑን በመላ ሰውነታችን እንደ ቋያ እሳት የተቀጣጠለው ኦርቶዶክሳዊ ቁጭት እስከመጨረሻው ሊዘልቅ የሚችልበት ስልት ነው። ሞቅ በረድ የሚለው ስሜታችን ለሐራጥቃ ተሐድሶ እንደ መልካም አጋጣሚ ያገለግላል። ስለዚህ ከስሜት ነፃ እንሁን እላለሁ።

ቅዱስ ሲኖዶስም ይኸንን የመሰለ የሕዝብ እንቅስቃሴ እያየ አጀንዳውን በቀላሉ ዐይቶት ያልፋል ተብሎ አይጠበቅም። እስካሁን ድረስ ማኅበረ ቅዱሳን በአንድ ወገን ሰንበት ትምህርት ቤቶች በሌላ ወገን፣ የፀረ ሐራጥቃ ሰባክያን ጥምረትም እንዲሁ፣ ደግሞም እንደ ሐዋሳ ባሉት አካባቢዎች ደግሞ ምእመኑ እንዲሁም ቅን አገልጋዮች በጥበብ እና በድፍረት በማስተማር በየፊናቸው የበኩላቸውን እያደረጉ መወሰድ ያለባቸውም እርምጃዎች በሚያረካ ደረጃም ባይኾን ሲወሰዱ ቆይቷል።

ጠላቶቻችን አስበው የመሥራታቸውን ያኽል እኛም አስበን መከላከል እና አጥረግርገን የማስወጣት አቋም ወይንም ተክለ ቁመና ልንላበስ ይገባል። አጽራረ በቤተ ክርስቲያንን መከላከል የትርፍ ጊዜ ስራ ሊኾን አይችልም። ጉዳዩን እያጠና፣ መረጃ እየተነተነ፣ ለአባቶች የውሣኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ሐራጥቃ ተሐድሶን የሚከላከል አንድ አካል ሰይሞ ማለፍ ይጠበቅበታል። ስለጉዳዩ መነጋገር ቢያስፈልግ እንኳ አቤቱታ አቅራቢ ሄዶ የሚያነጋግረው ማንን እንደኾነ በግልጥ አይታወቅም። ሐራጥቃ ተሐድሶ ተጠራርጎ እስኪወጣ ድረስ ተኝቶ የማያድር ባለቤት ሊመሠረት ይገባል።

አባቶቻችን በቅንነት የቀረበውን ይኽን ሀሳብ ተወያይተውበት ከእኛ በተሻለ

መልክ ሊያሲዙት ይገባል። ይኽ አካል ሲሰየም መከላከሉ ላይ ብቻ ሳይኾን የማጽዳት ሥራውንም የሚያከናውንበት ሕጋዊ መሠረት ያስፈልገዋል። በአፍም በመጣፍም ለተጣመመ ክህደታቸው ምላሽ መስተትም ይጠበቅበታል። እናም ፀረ ሐራጥቃ ተሐድሶ መምሪያ ወይም ጉባኤ ተሰይሞ ማየት እንፈልጋለን፡

Like . ፍስሃ ጽዬን አየለ

ጠላት ምንግዜም ስልቱን እንደሚቀያይርም ማወቅ ይገባናል (ተሀድሶ)ስለዚ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆችም በዚ ቁርጥ አቋማችንን ማሳየት አለብን።በመቀጠል ተሀድሶ እሚንቁት ነገር የለም ለአላማቸው ማስፈፀሚያ ሲባል ከተራ ግለሰብ አስከ ከፍተኛ ደረጃ እስካለው ሰው ድረስ ስለዚ ግለሰብም ቢሆን ልክ እንደ በጋሻው አይነት በራዥ ስንት ሰው እንደመረዘ ነው ማሰብ ያለብን አንድ የበሰበሰ ፍሬ ንፁሁንም እንደሚያበላሽ መዘንጋት የለብንምና ግለሰብም ላይ ቢሆን ትኩረት መደረጉ አይዘንጋ

Like . Girma Wogaji

አረሙን ለመንቀል ንፁህ ዘር እንዳይነቀል መጠንቀቅ ነው እንጂ መበርታት አለብን ለዚሁ እግዚአብሄር ይርዳን

Like . Dani EL Getachew

ሊያነጋግረን የሚገባው እና ሁላችንም ለራሳችን ቃል እንድንገባ የሚያስፈልገው ሰሞኑን በመላ ሰውነታችን እንደ ቂያ እሳት የተቀጣጠለው ኦርቶዶክሳዊ ቁጭት እስከመጨረሻው ሊዘልቅ የሚችልበት ስልት ነው። ሞቅ በረድ የሚለው ስሜታችን ለሐራጥቃ ተሐድሶ እንደ መልካም አጋጣሚ ያገለግላል። ስለዚህ ከስሜት ነፃ እንሁን እላለሁ።

Mahebere Ledeta

ምስጋና ለስላሴ

15/ ዜና ውግዘት ዘሀራጥቃ በምስራቅ ወለጋ

አርአያነት ባለው በብፁዕ አቡነ ስምዖንና በምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት እና የቤተ ክህነት አገልጋዮች ኮርተናል።

ይህን አርአያነት ያለው ተግባር ለሃገር ውስጥና ከሃገር ውጪ ያሉ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ አገልጋዮችና አማኞች ሊያከብሩና ሊከተሉት ይገባል።

እኒህ አገልጋዮች ይቅርታ ጠይቀን ወደ አገልግሎታችን እንመለስ የሚል ሃሳብ እያነሱ ሲሆን ቤ/ክህነቱ በጥልቀት ሊያየው የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ አስቀድመን ልንጠቁም እንወዳለን።

ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ቅ/ሲኖዶሳችን የሚፈተንበት ቀን ጥቅምት 12/2008 ዓ.ም. ዋዜማ ላይ ነን፤

በከተማችን በነቀምቴና በየወረዳው በመዘዋወር የሐራጥቃ/ የፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ/ ትምህርት በማስተማር፣ በመቀስቀስ በተለይም በጽዋ ማህበርና የዋህ ምዕመናንን እውነተኛ የቅ/ቤ/ክ አገልጋይ በመምሰል የኑፋቄ ትምህርታቸውን በቅ/ቤ አውደ ምህረት ለተልእኮአቸው በተመቻቸላቸው ቦታዎች ሁሉ ከቅ/ቤ/ክ አስተምሮ ውጪ ከቅዱሳን መጽሐፍትና ከአዋልድ መጽሐፍት ጋር የሚጣረሱ ከቅዱሳን አባቶች እና ከመምህራነ ወንጌል ያልተገኙ እውነት የሚመስል ውሸት በምዕመናን ልቦና በመዝራት አጠራጣሪ

ትምህርት በመስጠት ምዕመኑ ለሚወዳት ርትኢት ሃይማኖት ጥርጣሬ እንዲኖረውና አባቶች በዘሩት መልካም የወንጌል ንፁ ዘር ላይ እንክርዳድ ለመዝራት ደፋ ቀና ቢሉም ክፉ ሃሳባቸው በሥላሴ ቸርነት በድንግል ምልጃ በብፁእ አባታችን አቡነ ስምዖን መልካም ፈቃድና በካህናት ጉባኤ በእውነተኛ ምእመናን ጥረት ክፉ ሴራቸው የውሸት ትምህርታቸው ቢጸ ሐሳዊነታቸው ተረጋግጦ በማንኛውም የቅ/ቤ/ክ አገልግሎት እንዳይሳተፉ ክህነት የላቸውም ክህነታቸው እንዲያዝ በመደረጉ እኛ የነቀምቴ ደ/ጽ/ቅ/ማ.ቤ/ክ ማኅበረ ልደታ አገልጋዮች በእጅጉ ደስተኛ ሆነናል።

በአገልግሎት ሕፀፅ ምክንያት መረጃ የተገኘባቸውን የ 8 ቱን ስም ዝርዝርና የአገልግሎት ቦታቸውንና የውግዘት ደብዳቤአቸውን ከዚህ በታች አቅርበናል ይህም ደብዳቤ ለሚመለከታቸው የቤተክርስቲያን አካላትና የመንግስት አካላት በምሥራቅ ወለጋና የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በአባ ስምኦን ቲተር እና በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የምሥራቅ ወለጋ ሀ/ስብከት ጽ/ቤት የራስጌ ማሕተም በቀን 14/01/2008 ዓ.ም. እኒህ ደብዳቤዎች ተበትነዋል።

ተ.ቁ ስም የአገልግሎት ቦታ

1 አባ ሳሙኤል ታከለ ዋማ ገሎ ወረዳ ቤ/ክ ኃላፊ

2 ቄስ ሙሴ ዘሪሁን ነቀምቴ ምስራቀ ጸሐይ ኪ/ም ቤ/ክ

3 መ/ር ስዩም ስንታየሁ ቄ/ወለጋ ደ/ዶሎ

4 ዲ/ን ታረቀኝ ፍቃዱ ነቀምት ዋቻ ደ/ሣ/ቅ/ሚካኤል ቤ/ክ

5 ዲን/አለማየሁ አየልኝ ነቀምት ደርጌ ፈ/ህ/አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤ/ክ

6 ዲ/ን ቶላ በየነ ሲቡ ሲሬ ወረዳ ደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ቤ/ክ

7 ለወጣት ኢታና ዲንቂሳ ነቀምት ዋቻ ደ/ሣ/ቅ/ሚካኤል ቤ/ክ

8 ወጣት ነቢዩ ጀምበሬ አርጆ ጉደቱ ባአታ ማርያም ቤ/ክ

በማናቸውም የቅ/ቤተ/ክ አገልግሎት ላይ እንዳይሳተፉና ምዕመናንንም ነቅተው በመጠንቀቅ ሥርዓተ አምልኮታቸውን እንዲፈጽሙ ይህ ደብዳቤ በሁሉ የነቀምት ከተማ አድባራትና በምሰካበ ቅዱሳን ኡራኤል፤ ወሳሙኤል ገዳም የተነበበና ለምዕመናንን የተገለጸ ሲሆን በዚሁ እለት መስከረም 16 ቀን በመስቀል አደባባይ ደመራው ከመለኮሱ በፊት ጉዳዩን በመግለፅ ሰፊ ትምህርት ተሰጥቶበት ምዕመናን ሁሉን ተረድተው ሥርሆተ ህዝብ ሆኗል።

ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ቅ/ሲኖዶሳችን የሚፈተንበት ቀን ጥቅምት 12/2008 ዓ.ም. ዋዜማ ላይ ነን፤ እንደ ከዚህ በፊቱ ችግሩ እንደ ቀላል ታልፎ /ለሀራጥቃ/ ሌላ ቀጠሮ የምንይዝበት ጊዜ ሊሆን አይገባም።

የምዕመናን ጩኸት በርትቷል የእውነተኛ አገልጋዮች እንድነት ከገደማት እስከ አድባራት ከሃገር ውስጥ እስከ ውጪው አለም በእጅጉኑ አንሰራርቷል። ለዚህም ነው ባለፈው ወር በጥምቀት ተመላሾች..... በ1 ሳምንት ጊዜ ውስጥ ብቻ 100,000 በላይ ፊርማ የተሰበሰበው፤

አባቶቻችንን የተከበራችሁ የሲኖዶስ አባላት ልዑል እግዚአብሔር በሰጣችሁ ስልጣን ሃይማኖታችንንና ምዕመናንን ከተኩላ /ከሐራጥቃ/ጠብቋት። ለዚህ ሁሉ ጩኸት ግን መልሳችሁ ምን ይሆን?

ያጠፋን መምከር፣ መገሰፅ፣ ቀኖና መስጠት በተለይም <<መወገዝ ያለበት መወገዝ አለበት>> ከቅ.መላእክት ወገን ሰይጣን በሥራው ተወግዛል፣ ከቅ/ሐዋርያትም ይሁዳ ተለይቷል፤ ከሊቃውንትም አርዮስ ፣መቅዳንዮስ

....ተወግዘዋል። ‹‹ማውገዝ የነበረ ያለ ወደፊትም የሚኖር ነው።››

አሊያ ሐራጥቃዎች እንደ ሕንድ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን እርስታችንን ለመካፈል (ለመውረስ) የማይዳዳቸው ምንም አይነት ምክንያት የለም።

እናንተ አባቶቻችን ጳጳሳት ‹‹ አሁንም በገዛ ደሙ የዋጀትን የእግዚአብሔር ቤ/ክ ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ››

/ሐዋ ሥራ 20፤28/

ማህበረ ቅድስት ልደታ ዘነቀምቴ ደብረ-ፅዮን

ጥቅምት 11/2008 ዓ.ም.

ይቆየን!

ማራናታ እኔስ የማርያም ነኝ and 49 others

16/ የመናፍቃን ስሕተትና የእኛ የኦርቶዶስ ተዋህዶ አስተምህሮ፣ ክፍል ፪

(በዚህ ርዕስ በዘመናት የተነሱ የመናፍቃን ሃሳቦች እና ቅዱሳን አባቶች ለኑፋቄአቸው የሰጡት ምላሽ ይዳሰስበታል፣ ይህ ኑፋቄ አሁንም በሌሎች ቤተ እምነቶች የሚገኝ ነውና እውቀትን ሸምተን በትህትና የጠፉ በጎችን እናሳውቅ እንመልሳቸውም)

~ አርሲስ የተሰኙ መናፍቃን በነፍስና በሥጋ ወደ ሲኦል ወረደ ይላሉ፣ እኛ ግን መለኮታዊ ቃል ከብቻዋ ከነፍስ ጋር ወደ ሲኦል ወረደ፤ ሥጋን ግን የሴፍና ኒቆዲሞስ ከመስቀል አወረዱት በበፍታም ገንዘው በመቃብር ውስጥ

አኖሩት እርሷም እስከ ትንሣኤ ድረስ ብቻዋን ያለነፍስ ቆየች፥ መለኮት ግን ከነፍሱ ጋር ነበረ ከሥጋውም አልተለየም በአብም ቀኝ ከአለም አስቀድሞ እንደነበረ አኗኗሩ በአካል የተለየ ሆነ በሁሉ ስፍራ በሁሉ ዘንድ መልቶ ይኖራልና! ዮሐ 19፡38-42

~ የሮሜ ሊቀጳጳሳት ልዮን ሥጋ ከመለኮት ያንሳል አለ፥ እኛ ግን ከአንድነት በኋላ የክርስቶስ ሥጋው ከመለኮት አያንስም እንላለን!

~ የኬልቄዶን ማህበርተኞች መለኮትና ሥጋ በሁለት መንገድ በሁለት ሥርዓት ናቸው አሉ። እኛ ግን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው የሆነው አምላክ አንድ አካል አንድ ፈቃድ ነው እንላለን!

አንዳንዶች ደግሞ. . .

~ አምሳሉን ወደ መስቀል አወጣ የተቸነከረ እርሱ አይደለም የሚሉ አሉ፥ እኛ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ለብዙዎች መዳን በሊቀ ካህናት አገልጋይ ፊቱን ተጸፋ፤ በጲላጦስ አደባባይ ተገረፈ በብረቶችም ተቸነከረ በለንጊኖስም ጦር ተወጋ እንላለን! ማቴ 26፡67, ዮሐ 19፡34 (ይህንን የሚሉት ሙስሊሞች ናቸው አልመሲህ ኢሳ አልሞተም አልተሰቀለምም ነገር ግን አምሳያው ተሰቀለ ብለው ያምናሉ፥)

~ አርጌንስ፥ እግዚአብሔር አዳምን እና ሔዋንን ያለበሳቸው ቁርበት እኛ የምንመላለስበት በላያችን ያለ ሥጋ ነው የቁርበት ልብስም አይደለም አለ፥ እኛ ግን ሥጋስ ቀድሞም በተፈጠሩ ጊዜ አላቸው እግዚአብሔር ያለበሳቸው ግን የቁርበት ልብስ ነው ትእዛዙን ስላቃለሉ የነቀፋ ልብስ ነው እንላለን፥ ዘፍ 3፡26

አንዳንዶች ደግሞ. . .

~ ሰማየ ሰማያት የማይወስነው እግዚአብሔር አራት ጎኖቿ ባሉት በሰው ልጆች እጅ በተሰራች ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዴት ያድራል የሚሉ አሉ፣ ሁለተኛም ጎብስት የክርስቶስን ሥጋ የምሥጢርም ወይን ደሙን መሆን ይችላልን? ይላሉ፣ እኛ ግን በጽርሐ አርያም ያለ አኗኗሩ ሳይጎድል ይቀድሳት ዘንድ የመለኮት ኃይል በቤተ ክርስቲያን ያድራል። ጎብስትም በመንፈስ ቅዱስ መውረድ በተቀደሰ ጊዜ ከልማዳዊ ጎብስትነት ሥጋውን ወደመሆን ይለወጣል ወይንም ከልማዳዊ ወይንነት ደሙን ወደመሆን ይለወጣል እንላለን!

~ በወንጌል መምጣት ኦሪት እንደቀረች በሐዋርያትም ስብከት የነቢያት ትንቢት እንደጠፋ ሰንበትም ትንሣኤ በሆነባት በእሁድ እንደተሻረች የሚናገሩ አሉ፣ እኛ ግን ኦሪት በወንጌል ስብከት ከበረች፤ ነቢያትም በሐዋርያት ትምህርት ከፍ ከፍ አሉ፤ አለምን ከመፍጠር የማረፍ ሰንበትም በዓለም አዳኝ ትንሣኤ ዘውድ ተቀዳጇች እንላለን!

~ ዳግመኛም ስለ ማርያምና ስለመስቀል እንደሚክዱ በጆሮአችን የገባ ወሬ አለ፣ እኩሌቶቹ የወለደችው ማርያም ከመስቀሉ ትበልጣለች ይላሉ እኩሌቶቹም በሕማማቱ ደም የተነከረ መስቀሉ ይበልጣል ይላሉ፣ እኛ ግን ማርያም አምላክን የወለደች እንደሆነች እናምናለን! መስቀሉም መለኮት የተዋሐደው ትስብእት ደም የተቀደሰ የብርሀን ማዕተብ መሆኑን እናምናለን!

~ ፍልብያኖስ የመድኃኒታችን የክርስቶስ መለኮቱና ትስብእቱ ሁለት ገጽ ነው አለ፣ እኛ ግን የአምላክችን የመለኮቱና የትስብእቱ ባሕርይ በአንድ ገጽ በአንድ አካል ያለ ነው እንላለን!

~ መቅዶንዮስ መንፈስ ቅዱስ ፍጡር ነው አብና ወልድ ግን የተከከሉ አንድ ናቸው አለ፥ እኛ ግን መንፈስ ቅዱስም ፈጽሞ ያልተፈጠረ ከአብና ከወልድም ያልተለየ ነው አንድ ጎብረ መልክእ ነው እንጅ የአብና የወልድ የመንፈስቅዱስም ባሕርይ አንድ ነው እንላለን!

~ ሰዱቃዊያንና እንደ እነርሱ ያሉ ትንሣኤ ሙታን የለም ይላሉ፥ እኛ ግን ትንሣኤ ሙታንስ አለ ለኃጥአን ፍዳ ለጻድቃንም በጎ ዋጋ አለ እንላለን! ማቴ 22፥23,ዮሐ 5፥25-29, ሐዋ 23፥8

"አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤" (2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3:14፤)

ማራናታ እኔስ የማርያም ነኝ and 48 others

17/ ተሀድሶ - ክፍል ፱

በቀሲስ ደጀኔ ሽፈራው

በእንተ ታቦት፤

1. የበግ ለምድ የለበሱ ካህናት፥- በፕሮቴስታንት ተመልምለው የሰለጠኑ በመሆናቸው፥አብዛኛውን ጊዜ በስውር፥ አልፎ አልፎም በግልጥ የሚሠሩት ለእነርሱ ነው።አንድ የተሀድሶ መሪጌታ የመለመላቸውን ካህናት ይዞ፥በአንድ የፕሮቴስታ ንት መርሐ ግብር ላይ ዝግጅቱን ካቀረበ በኋላ እዚህም አለን፥እዚያም አለን ያለው ለዚህ ነው።ለጊዜው መንበሩን ተደግፈው ፥ጽላቱን እየዳሰሱ ቢቀድሱም፥በታቦቱም በሥጋ ወደሙም

አያምኑም።ታቦቱን ለጊዜው ያከበሩ መስለው ይታያሉ እንጂ፥ እንደ ፈጣሪዎቻቸው እንደ ፕሮቴስታንት “ጣዖት ነው፤” የሚሉ ናቸው።በዚህም እግዚአብሔርን፡-“የጣዖት መገኛ፤” እያሉት ነው።ምክንያቱም ጽላትን ቀርጾ ለሙሴ የሰጠ፥በኋላም ጽላትን እንዲቀርጽ የፈቀደለት እግዝአብሔር ነውና።ዘጸ፡፴፩፥፲፰፣፴፪ ፥፩ - ፳፰።በአዲስ ኪዳንም ሰማይን ከፍቶ፥በሰማይ ቤተ መቅደስ በክብር ያስቀመጠውን ታቦቱን ፥ለወዳጁ ለቅዱስ ዮሐንስ አሳይቶታል።እኛም በክርስቶስ ከእርሱ ጋር አንድ አካል በመሆናችን በእርሱ ዓይን አይተናል።ራዕ፡፲፩፥፲፱።

2. መናፍቃኑ ትናንትም ዛሬም የሚሉት “ታቦተ ሕጉ፥የቃል ኪዳኑ ጽላት በኢየሱስ ክርስቶስ ተሸሯል፤”ነው።ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አስቀድሞ፡-“እኔ ሕግን እና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ልፈ ጽም (ፍጹማን ላደርጋቸው) እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አን ዲት የውጣ (ሥርዓቷ፣ጽሕፈቷ) ወይም አንዲት ነጥብ (አሰራረዟ፣አቀራረጿ) ከቶ አታልፍም፥ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።እን ግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዱቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤(ወደ መንግሥተ ሰማያት አይገባም፤) የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግ ሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል፤(ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል፤) እልችኋለሁና፡-ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም፤) ብሎባቸዋል።”ማቴ፡ ፭፥፲፯ - ፳።በመሆኑም አትግደልን በፈጽሞ አት ቆጣ፥አታመንዝርን ደግሞ

ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያንጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል፥በሚሉት ፍጹማን አድር ጐአቸዋል ወይም አጽንቶአቸዋል።

3. መናፍቃን በጥርጥር ጀምረው በክህደት ለመደምደም ሁልጊዜ የሚጠቅሱት የታላቁን ሐዋርያ የቅዱስ ጳውሎስን መልእክት ነው።ንባቡን እንጂ ትርጓሜውን አይናገሩትም፥ምሥጢሩንም አያስተውሉትም።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥-“እንዲ ህም የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ እንደተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፥በመልእክቱም ሁሉ ደግሞ እንደ ነገረ ስለዚህ ነገር ተናገረ። በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፥ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደ ሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ፤” በማለት የተናገረው ስለ እነዚህ ነው።፪ኛ፡፯ጥ፡፲፮ - ፲፯።የተማሩትም ቢሆኑ ቃሉ በእምነት ስላልተዋሀዳቸው እያወቁ ይክዳሉ።

4. ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ብሉይ ኪዳንን እና አዲስ ኪዳንን እያነጻጸረ፥-“ዳሩ ግን የእስራኤል ልጆች ስለዚያ ስለ ተሻረው ስለ ፊቱ ክብር የሙሴን ፊት ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ፥ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀ ረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ፥የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም? የኩነኔ አገልግሎት ክብር ከሆነ ፥ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት በክብር አብዝቶ ይበልጣልና።ያ የከበረ እንኳ እጅግ በሚበልጥው ክብር ምክንያት በዚህ ነገር ክብሩን አጥቶአልና።ያ ይሻር የነበረው በክብር ከሆነ፥ጸንቶ የሚኖረውማ እጅግ ይልቅ በክብር ሆኖአልና።” ብሎአል።፪ኛ፡ ቆሮ፡፫፥፯ - ፲፩።በዚህ መልእክት ውስጥ የሞት አገልግሎት፥የኩነኔ አገልግሎት፥የተሻረ የሚሉ ኃይለ ቃሎችን

እናገኛለን።የእነ ዚህን ትርጓሜ ከማየታችን በፊት፥ስለ ሙሴ የተነገረውን ዝርዝር ታሪክ እንመለከታለን።

5. መጽሐፍ ቅዱስ፡-ሙሴ ከእግዚአብሔር እጅ ስለተቀበለው ጽላት፥“ሙሴም ተመለሰ፥ሁለቱንም የምስክር ጽላቶች በእጁ ይዞ ከተራራው ወረደ፥ጽላቶቹም በዚህና በዚያ በሁለት ወገን ተጽፎባቸው ነበር።ጽላቶቹም የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ፥ጽሕፈቱም በጽላቶቹ ላይ የተቀረጸባቸው የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበር።”ይላል።ዘጸ፡፴፪፥፲፭ - ፲፮።ከዚህም በተጨማሪ “እግዚአብሔርም ሙሴን፡-በእነዚህ ቃሎች መጠን ከአንተና ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጌአለሁና እነዚህን ቃሎች ጻፍ አለው።በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤እንጀራም አልበላም፥ውኃም አልጠጣም።በጽላቶ ቹም ላይ አሥሩን የቃል ኪዳን ቃሎች ጻፈ።. . . ሙሴ ከሲና ተራራ በወረደ ጊዜ ሁለቱ የምስክር ጽላቶች በሙሴ እጅ ነበሩ፤ ሙሴም ከተራራው በወረደ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ተነጋገረ የፊቱ ቁርበት እንደ አንጸባረቀ አላወቀም ነበር።”ይላል።አሮንና የእስራኤልም ልጆች ባዩት ጊዜ ወደ እርሱ መቅረብ ፈሩ፥በዚህም ምክንያት ፊቱን በጨርቅ እየሸፈነ ያነጋግራቸው ነበር።ዘጸ፡፴፬፥፳፱- ፴፫።

ዐሠርቱ ትእዛዛት፤

6. አስቀድሞ በእግዚአብሔር እጅ በኋላም በሙሴ እጅ በጽላቱ ላይ የተቀረጹት ዐሥሩ ትእዛዛት፡-፩ኛ/ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ፤፪ኛ/

የእግዚአብሔር አምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤፫ኛ/የሰንበትን ቀን

ትቀድሰው ዘንድ አስብ፤ ፱ኛ/አባትህን እና እናትህን አክብር፤፮ኛ/ አትግደል፤፮ኛ/አታመንዝር፤፯ኛ/አትስረቅ፤ ፰ኛ/በባልንጀ ራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፤፱ኛ/

የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤፲ኛ/ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ÷ይላሉ። ዘጸ፡፳÷፭ - ፲፯።ታድያ እነዚህ እንዴት ነው የሚሻሩት? እነዚህን መጠበቅና መፈጸምስ እንዴት ነው የሞትና የኩነኔ አገል ግሎት የሚሆነው?እግዚአብሔርስ ምን ይሁን ብሎ ነው÷እንዲህ ዓይነቱን አገልግሎት ለሕዝቡ የሚሰጠው?ጌታስ በወንጌል ወጣቱ ባዕለ ጸጋ÷"መምህር ሆይ÷የዘለዓለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን ላድርግ?" ባለው ጊዜ÷"ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ትእዛዛትን ጠብቅ፤"ለምን አለው? ማቴ፡፲፱÷፲፯። አንድ ሕግ አዋቂም ተመሳሳይ ጥያቄ በጠየቀው ጊዜ÷"በሕግ የተ ጻፈው ምንድርነው?" ሲል መልሶ ጠይቆታል።ሕግ አዋቂውም፥-"ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም ነፍስህም ውደድ÷ባልንጀራህንም እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ÷ይላል፤" ሲል÷የሚያውቀውን ነገር ግን የማይኖርበትን መልስ ሰጥቶአል። ጌታም፥-"እውነት መለስህ፤ይህን አድርግ÷በሕይወትም ትኖራለህ፤"ብሎታል።ሉቃ፡፲÷፳፰ - ፳፰። "የሞትና የኩነኔ አገልግ ሎት፤" እያለ የጻፈ ቅዱስ ጳውሎስም "ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው÷ትእዛዙም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት፤"ብሎአል። ሮሜ፡፯÷፲፪።ይህ እንዲህ ከሆነ አገልግሎቱን የሞት እና የኩነኔ ያሰኘው ምንድነው?ወደሚለው መሄድ ያስፈልጋል። ምክንያ ቱም ሕግጋቱ ሁሉ የሚፈጸሙት በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ ነውና። "የሞት እና የኩነኔ አገልግሎት፤"

7. በሕገ ልቡና፡-በየተራራው ላይ፥በሕገ ኦሪት ደግሞ በድንኳኑ ውስጥ እና በቤተ መቅደስ ውስጥ፥ይፈጸም የነበረ ውን አገልግሎት የሞት እና የኩነኔ ያሰኘው፡-ኧኛ/በሥጋ ሞት ላይ የነፍስን ሞት፥ወደ መቃብር በመውረድም ላይ ወደ ገሃነመ እሳት መውረድንም ጨምሮ ያመጣ የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ነው።ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ሰዎች ምን ጽድቅ ቢሠሩ፥በአዳም እና በሔዋን ኃጢአት እየተያዙ ወደ ሲኦል ይወርዱ ነበር።ደጋጎቹ ሁሉ የወረዱት ወደ ሲኦል ነበር። ይኸንንም፡-"ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው(በአዳም) ወደ ዓለም ገባ፤በኃጢአትም ሞት፥እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአ ትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤. . . ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ (እስከ ክርስቶስ) ድረስ ሞት ነገሠ፤አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ ምሳሌ ነውና።"በማለት ገልጦ ታል።ሮሜ፡፭፥፲፬ - ፲፬።በቆሮንቶስ መልእክቱም ላይ፥ሁሉ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ይሞቱ ይኰነኑም እንደነበረ ተናግሯል።፩ኛ፡ቆሮ፤፲፭፥፳፪።

8. ፪ኛ/ስለ ሥርየተ ኃጢአት ይታረድ የነበረው በግ አገልግሎቱን የሞትና የኩነኔ አገልግሎት አሰኝቶታል። ምክንያ ቱም የበጉ ደም የዕለት ኃጢአትን ያስተሠርይ ነበር እንጂ፥የአዳምን ኃጢአት አስተሥርዮ ከሞተ ነፍስና ከኩነኔ አያድንም ነበር።አንድም በጉ ሙት፥የሚሠዋለት ሰውም ከሞተ ነፍስ የማይለቀቅ ሙት ስለ ነበሩ፥አገልግሎቱን የሞትና የኩነኔ አሰኝተ ውታል።ይኸንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡-"ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፤ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን

ሊፈጽም(ከአዳም ኃጢአት አንጽቶ ፍጹማን ሊያደርጋቸው፥ከሞትና ከኩነኔ ሊያድናቸው)ከቶ አይችልም።ይህስ ባይሆን ከሚሠዉት መሥዋዕት ባረፉ ነበርና፥ በአንድ ጊዜም ያነጻቸው ነበርና።ነገር ግን በዚያው መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አድርገው የሚያቀርቡት ነበራቸው።የላምና የፍየል ደም ኃጢአትን ሊያስተሠርይ አይችልምና።"ብሏል።ዕብ፤፲፥፩ - ፬።

9. ፫ኛ/ከሞተ ነፍስ የማያድነውን፥ከታረደም በኋላ ሞቶ የሚቀረውን በግ የሚሠዋው የኦሪቱ ሊቀ ካህናትም አገልግሎቱን የሞትና የኩነኔ አሰኝቶታል።ምክንያቱም በጸሎቱና በመሥዋዕቱ የአፍአውን(የውጪውን) ኃጢአት ያስተሠርያል እንጂ፥ የውስጡን(በዘር ይተላለፍ የነበረውን የአዳምን ኃጢአት) አስተሥርዮ ከሞትና ከኩነኔ አያድንም ነበር።እንኳን ሌላውን ሊያ ድን እርሱ ራሱ በሞተ ሥጋ ተይዞ ወደ መቃብር፥በሞተ ነፍስም ተይዞ ወደ ሲዖል ይወርድ ነበር።እርሱ ሙት፥የበጉ መሥዋ ዕት ሙት፥የሚሠዋለት ሰውም ሙት ነበሩ።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥ይኸንንም፥-"እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላ ቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው። . . . በዚህ ላይ፥-መሥዋዕትንና መባን በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕትንም ስለ ኃጢአትም የሚሠዋ መሥዋዕትን አልወደድህም በእርሱም ደስ አላለህም ብሎ፥እነዚህም እንደ ሕግ የሚቀርቡት ናቸው፤ . . . ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን(ሞተ ነፍስን፥ኩነኔን ያመጣ የአዳምን ኃጢአት) ሊያስወግዱ ከቶ የማይች ሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፤" በማለት አስተምሯል። ዕብ፥፯፥፳፫፣፲፥፭ - ፲፩።

10. ነቢዩ ኢሳይያስ፥-"ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ፤(ከሰማይ

ወርደህ፥ከድንግል ማርያም ተወልደህ ምነው ከአዳም ኃጢአት ብታድነን፤)" ካለ በኋላ፥በአዳም ሕይወት ውስጥ ገብቶ፥"አንተ ተቆጣህ፥እኛም ኃጢአትን ሠራን፥ስለዚህም ተሳሳትን።ሁላችን እንደ ርኩስ ሆነናል፥ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው።"በማለት ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል። ኢሳ፡፷፬፥፮ - ፯።ሀብተ ትንቢት የተሰጣቸውን ቅዱሳን ነቢያትን፥እንደ ርኩስ ያደረጋቸው፥ጽድቃቸውንም የመርገም ጨርቅ ያደረገባቸው የአዳም ኃጢአት ነው።ይኸንን ማስተዋል እንጂ፥ከዚህ አልፎ ጽድቅ ሁሉ የመርገም (የደም)ጨርቅ ነው ወደ ሚል መደምደሚያ መድረስ ትልቅ ክህደት ነው።ነቢዩ ኤርምያስም፥-"ለሥጋ ለባሽ ሁሉ ሰላም የለም።ስንዴን ዘሩ፥እሾህንም አጨዱ፤ደከሙ ምንም አልረባቸውም፤"ብሏል።ኤር፡፲፪፥፲፫።ነቢዩ እንደተናገረው ሰላም የነሳቸው፥ጽድቅን እየዘሩ እንዲኖ ነኑ ያደረጋቸው፥ድካማቸውንም ሁሉ ከንቱ ያደረገባቸው የአዳም ኃጢአት ነው።በመሆኑም የሞትና የኩነኔ አገልግሎት የሚ ለው ከታቦቱ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው እናስተውላለን። የተሻረው ምንድነው?

11. ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ የወረደው፥ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍ ሷም ነፍስ ነስቶ የተወለደው፥በመስቀል ላይ ሥጋውን የቆረሰው ደሙንም ያፈሰሰው ታቦቱን ለመሻር አይደለም።ከላይ እንደ ተነገረው፥-የብሉይ ኪዳኑን ዘመን መንፈሳዊ አገልግሎት የሞትና የኩነኔ አገልግሎት ያሰኘውን የአዳምን ኃጢአት ለመሻር ነው።ምክንያቱም ይህች ኃጢአት በሰው ሁሉ ነፍስ ላይ ነግሣ ነበርና ነው።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥-"ሊቀ ካህናትም በየዓ መቱ

የሌላውን(የራሱን ሳይሆን የበጉን) ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ፥ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ (ብዙ ጊዜ ሊሠዋ) አል ገባም፤እንዲህ ቢሆንስ(ቢሆን ኖሮ) ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፤አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ(አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም) ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሸር አንድ ጊዜ ተገልጧል።"ያለው ለዚህ ነው።ዕብ፱÷፳፭ - ፳፮።በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት የአዳም ኃጢአት በመሻሩም፥-"በአንዱም በደል(በአዳም ኃጢአት)ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ÷ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።"ተብሏል።ሮሜ፭÷፲፯።ከዚህ በተጨማሪም፥-"ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው(በተዋህዶ ሰው በሆነው አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ) በኩል ሆኖአልና።ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና።"የሚል አለ።፩ኛ፡ቆሮ፲፭÷፳፩ - ፳፪።

12. በአዲስ ኪዳን የተሻረው÷ዓለምን ማዳን የተሳነው የኦሪቱ የእንስሳት መሥዋዕት ነው።እርሱን የተካው በመስቀል ላይ የተሰዋው የአዲስ ኪዳን በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን ምስክርነት ብንመለከት÷"እነሆ የዓለሙን ኃጢአት የሚያስተሠርይ የእግዚአብሔር በግ፤"ይላል።ዮሐ፩÷፳፱፣፴፮።ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም፥-"ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ፤"ብሏል። ፩ኛ፡ጴጥ፩÷፲፱።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ፥-"እግዚአብሔር በገዛ ደሙ ዋጀን፤" ብሏል።የሐዋ፡፳÷፳፰።ቅዱስ ዮሐን ስም በበኩሉ፥-"አየሁም ÷እነሆም በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ

ነበር፤”ብሏል። ራዕ፡፲፬÷፭።ከዚህ አስቀድሞም፡-“የታረደ በግ፤”ብሎ ታል።ራዕ፡፭÷፮።በትንቢትም ቢሆን ÷ነቢዩ ኢሳይያስ፡- “ተጨነቀ÷ ተሣቀየም÷ አፉንም አልከፈተም፤ለመታረድ እንደሚ ነዳ ጠቦት÷በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ÷እንዲሁ አፉን አልከፈተም።” ብሏል። ኢሳ፡፶፫÷፯። በምሳሌ ኦሪት ደግሞ÷ እስራ ኤል ለነፃነታቸው የሠዉት በግ ለክርስቶስ ምሳሌ ነው።እነዚያ የጠቦቱ ደም ከፈሰሰላቸው በኋላ÷ ከባርነት ቤት ወጥተ ዋል፤እኛ ደግሞ የበጉ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመስቀል ላይ ከፈሰሰልን በኋላ ከሲኦል ወጥተናል።እስራኤል ዘሥጋ የበጉን ሥጋ በእሳት ጠብሰው በልተውታል።እስራኤል ዘነፍስ የምንባል እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ÷ነፍስ የተለየውን እሳተ መለኮት የተዋሀደውን የክርስቶስን ሥጋና ደም እንቆርባለን።ዘጸ፡፲፪÷፩ - ፲፬።ይኸውም ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆነን በመንግሥተ ሰማያት የምንኖርበት ነው። ዮሐ፡ ፮÷፶፫ - ፶፮።

ያለ ድንግል ማርያም አማላጂነት አለም አይድንም

18/ ዘርፌ እየዘመረች ነው እየዘፈነች?

1ኛ ቆሮ 11-13 "በእናንተ በራሳችሁ መካከል ፍረዱ፤ ሴት ራስዋን ሳትሸፍን ወደ እግዚአብሔር ልትጸልይ ይገባታልን?" ይላል

እኔ የገረመኝ አጠገቧ የተቀመጠው ጳጳስ ነው!!!

የኛ አባቶች ሚታወቁት ከመስመር እንዳንወጣ ሲገስፁን ነው...ዜማ ስናበላሽ መቋሚይ አያያዝ ሲዛነፍብን ሌላም ሌላም....ደሞ እዛው ነው

ሚቀጡን! የፍቅር ቅጣት!

በቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖታችን አይደለም ለአገልግሎት ሴት ልጅ በቤተክርስቲያን እራሱዋን ሳትከናነብ መግባት አይፈቀድም። ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

ኧረ እንደውም ተመስገን ነው ቀሚሱ ለጥቂት ከጉልበቷ በታች መሆኑ!

በጣም ያሳዝናል! ተሀድሶዎች ሲኖዶሱን ንቀውታል ጥርስ የሌለው አንበሳ እንደሆነ አውቀውታል!

በተለይ አንዳንድ ጳጳሳት የተሀድሶ የምንፍቅና ችግር እንዳለባቸው ምዕመኑ እየተገነዘበ ነው!

ለዚህም ማረጋገጫው አብዛኛው አባቶች በተሀድሶ ጉባኤ የማይገኙ ሲሆን 2 ጳጳሳት ግን ከበጋሻው እግር ስር እንደማይጠፉና ለእርሱ ከፕሮቴስታንት ድርጅት ከተመደበለት በጀት የተወሰነ ፐርሰንት በየወሩ እንደሚቆረጥላቸው እየተረጋገጠ ነው።

በቅርቡ እንደተለመደው ማስረጃው በድረገፅ ይፋ ይደረጋል። መፀሀፉ ለመንጋው ግድ የሌለው አባት እንደሚፈረድበት ያስቀምጣል። በመሆኑም ዛሬ አንዳንድ አባቶች በፍርፋሪ ተደልለው ከካዱትና ከረከሱት ጋር አብረው ማደግደጋቸው የሚያሳፍረው እነርሱን እንጂ ቤተክርስቲያንን አይደለም።

ስለሆነም ቤተክርስቲያን እየተጠበቀች ያለቸው በየሰንበት ትምህርት ቤቱና ከጥምቀት ተመላሽ በየአካባቢው ባሉ እና በተደራጁ ወጣቶች ነው።

ተሃድሶም የሚሰጋው እነዚህን ወጣቶች ነው በተለይ የተክለሀይማኖት ወጣቶችና የቂርቆስ አካባቢ ወጣቶች የተሃድሶን ቡድን በማሳደድ አንፀባራቂ ታሪክ እየፃፉ ይገኛል። እንደ አራስ ነብር አላስጠጋ ብለዋቸዋል።

ጀግኖች-ግፉበት!!!

የፅጌ ማርያም ወጣቶችም በቀደም የእመቤታችን እለት(መስከረም 21/2008 ዓ.ም) ፖስተር በጋሻውን ኑፋቄህን እኛ ቆመን አትዘራም ብለው አዋርደው እንዳባረሩት መዘገባችንን አይዘነጋም!

ስለሆነም የዱባይ የዳበረ የመድረክ ልምድም ስላላት ነገ ዘርፌ እነደ ቢዮንሴ በታይት በአውደ ምህርት ላይ ልፈንጭበት ማለቷ አይቀርምና ልክ አንድ ጀግና የተዋህዶ ወጣት ናዝሬት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የሰበካ ሃላፊው ስባሪ ሳንቲም ጉቦ ተቀብሎ አውደምህርት ላይ እንድትወጣ በማድረጉና እርሱዋም ከፔንጤ የተሰጣትን ተልኮ ለማስፈፀም አፏን ስትከፍት ማይኩን መንጭቆ ወስዶባት ገፍትሮ እንዳባረራትና ሌሎችም ወጣቶች የእርሱን አራአያ በመከተል ቤተክርስቲያናችን የካሃዲና የአዝማሪ መፈንጫ አትሆንም በማለት በዕለቱ እርምጃ እንደወሰዱት እኛም ይህንን ታሪክ በያለንበት አጥቢያ ቤተክርስትያን መድገም አለብን!!!

ለቤተክርስቲያን ለእናታችን አጥር እንሁናት!!!

የሐዋርያት ጉባኤ ስለሆነች ስለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም እንማልዳለን! (መጽሐፈ ሚስጢር)

ለሌሎች እንዲዳረስ SHARE እና LIKE እንዲያደርጉ በፃድቁ ተክለሀይማኖት ስም እንጠይቃለን።

የዋሻው አንበሳ ተክልዬ ሲነሳ እኔም ልበልህ አባቴ ተክልዬ ግባ ከቤቴ!

ከፃድቁ ረድኤት በረከት አይለየን። አሜን'

Like · Amelework Awoke

እስቲ በመጀመርያ የራሳችንን ሀጥያት እንይ ለሁሉም ፍርድ ሰጪ

እግዚአብሔር ነውና ለርሱ እንተወው ዘርፌን ሚለውጣት ምክር እንጂ ስድብ አይደለም ደግሞም ይህን ያህል ሚጋነን የአለባበስ ስርአት አልጣሰች የጸጉሩዋም አለመሸፈን ቢሆን ከሀጥያተኞች ጎራ አይመድባትም እግዚአብሔር በኦርቶዶክስ እምነታችን ሁላችንንም ያጽናን።

Like · Yonatan Bekele

እናንተ ግን ሁልግዜ ነቀፋ ነቀፋ አይሠለቻችሁም በሥመአም !!!

ዘርፌ በደንብ ዘምሪ

Like · Kidist Tadese

ማናም ማንንም ጃጅ ማረግ አይችልም እስቲ ስለተደረገልን። እናስብ እውነት። ይገባን ነበር። እሱ ቸር ስለ ሆነ ሰላም አውሎ ሰለም የሳድረናል እንደኛ ግን አይገባንም ነገር። ምን ያህል የፍቅር አምላክ እንደሉነ አያችሉት እሱ። ከኛ እሚፈልገው ፍቅርን ብቻ ነው። እርስ በእርስ መዋደድን እግዚያብሄር አብዝቶ የሚጣለው ነገር በሰው ላይ ፍርድ መስጠትን ዘማዊ ቷን እቺ ሴት ሐጥያተኛ ናት ብለው በድንጋይ ሊወግሯት በተነሱም ግዘ እውነት ከናንተ መሐል ሐጥያት ያልሰራ ይውገራት ነገር ግን አንዱ የአንዱን ሐጥያት በግንባራቸው ላይ ተጽፎ ሲያዩት ሉሉም ድንጋዩን ጥሎ ሸሸ። የፍቅር። አምላክ ግን ከወደቀችበት አንስቶ ባረካት እኛንም ያስብን የኛም ሐጣት በግንባራችን ላይ ተጽፎ። ቢሉን ኖር እውነት ማን ማንን ጃጅ ያርግ ነበር። እሱ ግን የኛን ሐጣያት ተሸክሞ እኛን በፍቅር ያኖርናል።

Like . Yonas Endalkachew

ድሮስ ከዘፈን ለመጣ ሰው ምን እጠብቃለን

Like · Maezu Bsrat

የኔእህት ዘሚርልን ግን ፀጉሪሽ ሸፊኒ

ልብስሽም አስረዚሚ እግዛብሄር ልብ ይስጥሽ

Like · Micky Maraky

እ.ር ልቦና ይስጣት ግን የኦርቶዶክስ ውለታ ይሔ አልነበረም የሚጠፍውን ነገር ከምንመኝ የዘላልማዊውን ነገር ብንይዝ ይጠቅመናል

Like · Hana Tebebu

አትፍረድ ይፈረድብሀል ይላል የእግዚያብሔር ቃል

Like · Mekdes Mayva

እኛ ሰዎች ስንባል ለምን ስለራሳችን አናውቅም! በትንሹም በትልቁም አቃቂር ማውጣት

Like · Wasihun Zewdie

ያባቶቼ እርሥት ከሚጠፋ ድንበራቸው ከሚገፋ ሀጥያተኛው እኔ ልሙት በደለኛው እኔ ልጥፋ .ዘርፌ እዚአብሄር ይሥጥሽ ለኦርቶዶክሥ ይህ አልነበረም ዋጋዋ

Ted Lucas Abebe

(ዲያቆን ዳንኤል ክብረትና የፀረ--ተሀድሶ አቋሙ)

※ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ተሀድሶን አስመልክቶ ዛሬ ብዙሀኑን ያነቃነቀ የግንዛቤ ትምህርት በሀገረ አሜሪካ ላሉ ምዕመናን ሰጥቷል፣ የዛሬው ትምህርት እስከዛሬ በጉዳዩ ከሰማኋቸው ትምህርቶች ለየት የሚለው

ምክንያታዊና ለወደፊቱም መፍትሄ ሊያመጣ የሚችል ቁልፍ ነጥቦችን መያዙ ነው። በጥቂቱ ለማየት ያህል፦

※

19/ ተሀድሶን እንጂ ተሀድሶአውያንን ማሳደድ መቆም እንዳለበት ይናገራል። ጉዳዩን በሀይማኖት ወይንም በእወቀት ከመመርመር ይልቅ መዝለፍን፣ ሀይለ ቃልን መጠቀምና ስሜታዊ መሆን ክርስትና የማይፈቅደውና፣ ግለሰብ ላይ ትኩረት ማድረጉ ለውጥን እንደማያመጣ አሳስቧል። በታሪኪም የቄርሎስን እና የንስጥሮስን ታሪክ አንስቶም ማንም በሀይማኖት ቢስት ክህደቱን እንጂ ከሀዲውን ላይ ማተኮሩ ጉዳዩ ለ15 ዓመታት ያህል እድል እንዲከፍት ማድረጉን አሳስቧል።

※ ተሀድሶ የለም፣ ችግር የለም በሚል እና በመሳሰሉት ቃላት ግራ የተጋቡ እና ጉዳዩ ቅናተኞች ፣ ምቀኞች የፈጠሩት ተራ ወሬ ነው ብለው በማመን፣ ባለማወቅ ምክንያት በየዋህነት ከተሀድሶአውያን ወገን የሆኑ ምዕመናንን ስናስረዳ ጉዳዩ ግለሰብ ተኮር ነቀፋ ሳይሆን የቅዱሳን መፅሀፍትን ማስረጃ በማቅረብ እና በሀይማኖት አይን በመመዘን ለየዋሁ ምዕመን ለማስረዳት መሞከር እንዳለብ ነግሮናል።

※ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በአለፉት ዘመናት መናፍቃንን ስታሳፍርና መልስ ስትሰጥ የኖረችው የቅዱሳት መፅሀፍትን(መፅሀፍ ቅዱስን) ዋቢ በማድረግ ነውና በየዘመናችን የቅዱሳት መፅሀፍት ትርጓሜ የተምታታባቸው ሰዎች እንደተነሱ ጠቁመው ቅዱሳን መፅሀፍት ግን ዘመን በተለወጠ ቁጥር የማይለወጡ ጥንታዊነት ያላቸውና ትርጓሜያቸውም የማይታደስ ናትና ምንግዜም እገሌ ምን ይላል? ይሄኛው ሰባኪስ ምን ይላል? በማለት ሰው

መከተልን ትተን የቤተክርስቲያናችንን የቅዱሳን መፃህፍት ምን ይላሉ ብሎ እነርሱን ለማወቅ መሞከር እንዳለብን ነግሮናል። እውቀትን ከእምነት ጋር ማስተባበር ግዴታችን መሆኑን መገንዘብ እንዳለብንና እምነት ያለእውቀት ሞኝነት፤ እውቀትም ያለ እምነት ትምክህትን ወልዶልን ወደ ፍልስፍና እንደሚወስደን በመገንዘብ እያንዳንዱ ሰው የሚያምነውን ማወቅ፣ ያወቀውንም ደግሞ ለሌላው መናገር እና ማሳወቅ፤ አንዱ ለሌላው እያስተማረ ግንዛቤን ማስፋት እንደሚያስፈልግ ነግሮናል።

※ በቀደመው ዘመን ቀዳሚ መናፍቅ የተባለውን አሪዎስን በማንሳት አሪዮስ ከዘመናችን የተሀድሶ አካላት ጋር በባህርያት መመሳሰሉን ለማስረዳት የሞከረው ዳንኤል፣ አሪዎስ በዘመኑ ለተነሳበት የክህደት አላማ ይረዱት ዘንድ በወቅቱ የነበሩ ነገስታትን፣ መንግስታትን፣ ባለስልጣናትን፣ ይባስ ብሎም ጳጳሳትን የራሱ ለማድረግና ይጥር እንደነበር፣ በእነዚህም አካላት ስር ተሸሽጎ የክህደት አጀንዳውን ሲፈስም እንደነበር አውስቶ በዘመናችንም ያሉ ተሀድሶአውያን ይህን ሊያደርጉ እንደሚችሉ በእርግጥም እንደቻሉ ሳይጠቁም አላለፈም።

※ ዲያቆን ዳንኤል በመጨረሻም በአፅንኦት ሲያሳስብ የነበረው ስሜታዊነትን ማስወገድ እንዳለብን ነው። ከዚህ በፊት የአክራሪ እስልምና ወሬ በተወራ ሰሞን የህዝቡ ስሜታዊነት እንጂ ዘላቂ ስራ እንዳልተሰራ በማስታወስ፣ ይህ ሰሞኑን እየተጋጋለ የመጣውን የፀረ-ተሀድሶን እንቅስቃሴ ከስሜት የፀዳና ዘላቂነት ያለው መሆን አለበት ብሏል። ሁሉም አካላት የነጠብጣብ ያህል ድርሻ ማበርከት ብቻ ሳይሆን በአንድነት እና በያገባኛል ስሜት ሊሳተፍ እንደሚገባ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል። ይህ ጉዳይ የጥቂቶች ጉዳይ ሳይሆን

የሁሉም የቤተክርስቲያን አካላት ጉዳይ ነውና እያንዳንዱ ኦርቶዶክሳዊያን በርቱ፣ አይዟችሁ ብሎ በቃል ብቻ ከማበረታታት በዘለለ በተግባርም ሊሳተፍ ይገባናል ብሏል። በዘመናችን ያሉ ሊቃነ ጳጳሱት በፀረ-ተሀድሶ እንቅስቃሴም ሆነ በሌሎች የቤተክርስቲያናችን ወቅታዊ ችግር ላይ ከምዕመኑ ባነሰ መልኩ ለዘብተኛ መሆናቸው ቢያሳዝነውም፤ በዘመነ ሲሲኑዮስ ጊዜ የነበሩት ቆራጥ ሰማዕታትን በማንሳት በዚያን ወቅት ከጳጳሳቱ ይልቅ ለእምነታቸው ቀናኢ በመሆን እስከ ሰማዕትነት የደረሱት ምዕመናኑ እንደነበሩ በማስታወስ ዛሬም የዘመኑ ወጣትም ከዘመነ ሲሲኑዎስ ሰማዕታት ብዙ በመማር ቤተክርስቲያንን ለትውልድ ማስተላለፍ አለብን ብሏል።

※ ዲያቆን ዳንኤል በትምህርቱ መግቢያ ላይ "ሀራጥቃ" የምትለውን ቃል ለመናፍቃን የምተገባ ስትል እርሱም ደግሞታል፣ ቃሉም አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተባሉ ሊቅ በዘመናቸው ለተነሱ መናፍቃን የተጠቀሙበት መሆኑን ነግሮናል።

※ በመረሀግብሩ ማብቂያ ላይ መርሀግብሩን ሲመሩ የነበሩት አባት የዛሬው ትምህርት በዩቲዩብ ተቀድቶ ከሰዓትታ በኋላ ፀረ-ተሀድሶ በተሰኘው የፌስቡክ ገፅ ላይ እንደሚቀርብና ሁሉም ለአልሰሙት እንዲያሰሙ ሼር በማድረግ እንዲተባበሩ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

"በቴድ ሉቃስ"

like Wendemalem Geremew

እውነት ነው ተሃድሶዊያንን ሰው ተሃድሶዊያን ናቸው ስላለን እነርሱን ስናሳድድ ማወቅ ያለብንን የታለቁን መጽሐፍ ቃል ሳናውቅ የማናውቀውንና መፍትሄ የማይሰጠውን ብሎም ቅዱስ እግዚአብሄር የማይወደውን አሳዳጀነት

ከማዝወተር ማወቅ ስለሚገባንና መዋጋት ስላለብን ተሀድሶ ስለሚባለው ፀላኢ ብንታገል መልካም ነው

የቅዱሳን መላዕክት የቅዱሳን ፃድቃን ሰማዕታት አምላክ ቅዱስ እግዚአብሄር በቃሉ በረከት የበረቱትን አብዝቶ ፤የደከሙ አባቶቻችንን አበርትቶ፤ እኛንም በቃሉ አንጸን በስጋዊ ሃሳብ ሳይሆን መንፈሳዊ በሆነ ቃሉ ነገሮችን እንድንመረምር ይርዳን!።

ለወንድማችንም ቃለህይወት ያሰማልን! አሜን!!!

Like · Makiba Estifanos

kesis fekade ansa አንተ አይመለከትህም ይሄ የቤተሰብ ጉዳይ ነው እንደ እስስ መቀያየር አያስፈልግም አንዴ ኦርቶዶክስ አንዴ ተሃድሶ ለራስህ አይደብርህም ትልቅ አይደለህም እንዴ አንዴ ቄስ አንዴ ዲያቆን መሆንስ አይደብርህም የፈለከውን ህምነት ተከተል ግን አቋም ይኑርህ

Like · Lulit Bekle

አሜን እኔም የወንድሜን የወንድአለምን ሃሳብ እጋራለሁ እግዚአብሔር እሱ ይርዳን የጠፉትን ልጆት ወደ ቱ ይስብስብልን ነው የምለው እኔ

Like · Yared Denbu Semeh

እናመሰግናለን ዲ/ዳንሄል! አስር ጊዜ ግሪሳዎቹ ግሪሳዎቹ እያሉ እኛን ከማሰልቸት ውጪ ምንም አልፈየዱም ምንንም አያስተምርም ማንንም አይመልስም

ዘማርያም ዘለቀ

20/ @ ቁርንጭ መናፍቅ አሰግድ ሣህሉ¡ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወልደ እግዚአብሔር ብቻ እንደሚባል እንጂ ወልደ ማርያም ማለት ግድ አለመሆኑ የሚገልጽ ልብ ወለድ ፈጠራ ልፈፋውን ሰማን:: በኦርቶዶክሳዊት የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን አስተምሕሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወልደ እግዚአብሔር ብቻ አሊያም ወልደ ማርያም ብቻ ማለት ክህደት ነው:: ማለት የሚገባው ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ወልደ ማርያም ሥግው ነው:: እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ሲገለጥ ስመ ሥጋዌው አማኑኤል; ኢየሱስ; ክርስቶስ; መድኃኒ ዓለም ተብሎ ተጠራ:: አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ; ረቂቁ ገዘፈ; ግዙፉ ረቀቀ; ምሉዑ ተወሰነ; ዉሱኑ መላ ብለው ለሰው ይነግሩታል:: ረቂቅ ሲሆን ግዙፍ; ግዙፍ ሲሆን ረቂቅ; ምሉዕ ሲሆን ዉሱን; ውሱን ሲሆን ምሉዕ መሆን እንደምን ይቻላል ብሎ ልብ ሊመረምረው ቃል ሊናገረው አይቻልም:: አንድነት ሦስትነት የታወቀ ጌታችን ከእመቤታችን ከተወለደ ወዲህ ነውና:: ወአልቦ መኑሂ ዘአእመሮሙ ለሥሉስ ቅዱስ ዘእንበለ እምድኅረ ተሠገወ ወልድ ዋሕድ እምቅድስት ድንግል እንዲል::

አቶ አሰግድ ምነው ኢየሱስ ክርስቶስን የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ማለትን ደፍረህ የማርያም ልጅም ነው ለማለት አፈርክ? ወንጌልኮ ሲጀምር "የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ::" ማቴ. 1:1 አላስተዋልክምን? ይኼን ንጉሠ ነገስት "የዳዊት ልጅ"; "የአብርሃም ልጅ" የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ በለበሰው ሥጋ አይደለምን? ወልደ ማርያም ብሎ መጥራትስ መቅድመ ወንጌል አይደለምን? እንዳውም

በወንጌል በተደጋጋሚ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን; ራሱ ጌታችንም "የሰው ልጅ" ይላል:: ማቴ.24:36:: አቶ አሰግድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "የሰው ልጅ" የተባለው በባሕርይ አባቱ በአብ ነው? "ሰው" የተባለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አይደለችምን? ከእሷ ስለተወለደ "የሰው ልጅ" ተባለ:: በአምላክነቱ የማይወለድ በሰውነቱ የተወለደ የሱን ሕማሙን እናምናለን:: በሰውነት እንጂ በአምላክነቱ አትወልደውምና:: አኮ ወልደ ማርያም በመለኮቱ ዘእንበለ ዳዕሙ በትስብእቱ እንዲል:: ስለሆነም እኛ ኢየሱስ ክርስቶስን ወልደ እግዚአብሔርም ወልደ ማርያምም ብለን ያው እራሱን አንድ ጌታ እንጠራዋለን::

@ አሰግድ! አንተ የጠቀስከው ማቴ. 16:13 ላይ "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ::" የሚለው ገጸ ንባብኮ' በግልጽ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን "የሰው ልጅ" ብሎ ጠርቷል:: ታዲያ ጌታችን ራሱን የሰው ልጅ ሲል በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም በለበሰው ሥጋ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርይ አባቱ በአብ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንጂ የሰው ልጅ ፈጽሞ አይባልም:: የቅዱስ ጴጥሮስም ምላሽ "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ::" ማቴ. 16:16 ሲል አንተ 5500 ዘመን ሲፈጸም ለኩነተ ሥጋ የመጣህ ቅድመ ዓለም የነበርክ ዓለምንም አሳልፈህ የምትኖር አንተ የሰው ልጅ የተባልክ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ መሠከረ ማለት ነው::

ምነው አቶ አሰግድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን "የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ እያለ አብዝቶ ጮኸ::" ማር. 10:48 የዳዊት ልጅ ብሎ እውሩ መጥራቱ ስሕተት ነው? የዳዊት ልጅ የተባለው በአብ ነው? በድንግል ማርያም?

የዳዊት ልጅ ሲለው የማርያም ልጅ ማለትኮ' ነው:: አይ አሰግድ! እንዲህ ጮርቃ መሆንህ ያሳዝናል:: መናፍቁ አሰግድንና ወንጀልን በጋራ እንከላከል!!!

Niguse Negest

***

21/ ተሐድሷውያኑ የሐበሻን ደም የሚያፈሱት ለሀገር እና ለህዝብ የሚቆረቆሩ የሚጨነቁና የሚደክሙ በመምሰል ሲሆን እጅግ አስቸጋሪ የሆነው እነዚህ ግለሰቦች ባላቸው ረቂቅ ስብዕና እና የማስመሰል ክህሎት ከአደገኛነታቸው እና ከአረመኔነታቸው ይልቅ ተወዳጅ እና መሥዋዕትነት የከፈሉ ወይንም ለሀገራቸው እና ለክርስትና እምነት መሥዋዕትነትን እየከፈሉ ያሉ ትጉታን ተደርገው መወሰዳቸው ሲሆን ማኅበረሰቡ እውነታውን ለመረዳት በዐሥርት የሚቆጠሩ ዓመታት መውሰዱ ሁኔታውን ከአዕምሮ በላይ ያደርገዋል:: አስገራሚውም ጉዳይ እራሳቸው ኢትዮጵያውያኑ በተለይም የኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁኔታውን ሊረዱ አለመቻላቸው እና ፍጹም የአጥፊዎቻቸው ጠበቃ ሁነው መገኘታቸው ጉዳዩን አሁንም ከአዕምሮ በላይ ያደርገዋል:: እንግዲህ ተሐድሷውያኑ ኃይላት በተለያየ ግንባር የከፈቷቸው ጥቃቶች ማኅበረሰቡን ወደ ፍዘት እና መደናገር ውስጥ ከትቶታል:: ማኅበረሰቡን ወላዋይ አድርጐታል; በማኅበረሰቡ መካከል በትንሿቱ ጉዳይ ላይም ቢሆንም መተማመን የማይችል ተጠራጣሪ አድርጐታል; መተሳሰብ እና መረዳዳት

እንዲጠፋ አድርጐአል; ተስፋውን ነጥቆታል; ግድ የለሽ አድርጐታል; ሰው አምላኪ; ባዕድ አምላኪ; የራሱን ተቺ; ረጋሚ አድርጐታል; ማጎበረሰቡን ገንዘብ አምላኪ; ሰው አምላኪ; አድርባይ; አስመሳይ; ሸንጋይ አድርጐታል; ወጣት ሴቶችን እና ወንዶችንም ሴሰኛ እና ሱሰኛ አድርጐአቸዋል:: የተሐድሷውያኑ ጥቃት አላቆመም! አይቆምም:: ዛሬ በሀገራችን አፍጦ ጦር ሰብቆ የመጣ ወራሪ የለም:: ነገር ግን እርስ በርሳችንን የሚያባላ; የሚያናክስ; የሚያጨራርስ; የሚከፋፍል; ታሪክን የሚያጠለሽ; ባሕልን የሚያስንድ; እምነትን የሚያስፈራርስ ምንነቱ እና ማንነቱ ይሄ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የማይችል ኃይል ዜጐቻችንን መልምሎ አሰማርቷል::

+ በጐ ገጽታ እንደየ መስፈሪያው ይለያያል:: ስብከትን እንደ ስታዲየምና እንደ ፓርላማ በደጋፊ ብዛት የምናየው ከሆነ የእኛ ስብከት ውጤታማ ነው:: ሚሊዮኖች እየመጡ ነው:: በጉባኤ ላይ ስንመለከት ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ያላገኙትን ደጋፊ አንድ ቃል ስንናገር የሚያጨበጭብ; እልል የሚል ሕዝብ ግቢውን ሞልቶ አጣቦታል:: ግን የስብከት ውጤቱ ደጋፊ ማብዛት ነው? ብለን ስንጠይቅ ነው ሥራችን እንደሚጠበቀው አለመሆኑን የምናውቀው:: ለምሳሌ በብዙ ጉባኤያት ላይ እስኪ ንስሐ አባት የሌላችሁ አጨብጭቡ ቢባል ከ 80 እስከ 85%ቱ የለኝም ብሎ ነው የሚያጨበጭበው:: ከ 15 እስከ 20%ቱ ንስሐ አባት አለኝ ይላል:: ንስሐ አባት አለኝ የሚለውም ከንስሐ አባቱ ጋር በትክክል መሠረታዊ የሆነ ግንኙነት የለውም:: ስለዚህ ውጤታማ ነውም; አይደለምም ብሎ ለመለካት እንደለኪዎቹ ነው:: ከመንፈሳዊ ይዘቱ አንጻር እንለካው ከተባለ ግን

ውጤቱ አነስተኛ ነው:: ሊቃውንቱ ለምን ከዐውደ ምሕረት ጠፉ ለሚለው በራሳቸውና ከራሳቸው ውጭ በሆነ ምክንያት ነው:: ሊቃውንቱ የነበሩበት ዕውቀት ለሕዝብ ጆሮ ቅርብ አይደለም:: የስብከት ዓላማም ያንተን ዕውቀት ማሳወቅ አይደለም:: በማርቆስ ወንጌል ላይ "መስማት በሚችሉት መጠን ነገራቸው" ነው ያለው:: ክርስቶስም ሲያስተምር በእርሾ; በሰናፍጭ እየመሰለ ነው ያስተማረው:: እንደ እግዚአብሔርነቱ ቢያስተምር አይደለም እኛ መላእክትም አይሰሙትም:: ስለዚህ የሊቃውንቱ የማስተማር ስልትና ዘመኑ አልተገናኘም:: ስለዚህ እነዚህን ሊቃውንት ወደ ዐውደ ምሕረት ለማምጣት ሥልጠና መስጠት; የያዙትን ዕውቀት እንዲመነዝሩት ማድረግ ያስፈልጋል:: ሰዓታቱ; ቅዳሴው; ማኅሌቱ; ትርጓሜው; እስመ ለዓለሙ; መልኩ; ዚቁ; ምልጣኑ እያንዳንዱ ስብከት ነው:: እነዚህን ሊቃውንት ለማቅረብ እስከዛሬ ያጠራቀሙትን ትምህርት አምቀው እንዴት ለሕዝቡ ማቅረብ እንደሚችሉ የሚያሳይ ዘዴ ያስፈልጋል:: እነርሱ የቸገራቸው ዘዴው እንጂ ዕውቀቱ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ሊቃውንት ወደ ዐውደ ምሕረቱ ማቅረብ ካልቻለች ያለፈውን እየረሳች ወደ ፊት ከሔደች ባዶዋን ትቀራለች::

+ አንዳንድ ሰባኪያን በየዐውደ ምሕረት ሲሰብኩ እልል በሉ! አጨብጭቡ ማለት ይቀናቸዋል:: በተጨማሪም ሕዝቡን በማሳቅ ሰዓቱን በቀልድና በተረት ያጠናቅቃሉ:: በአጭሩ ሁለት ነገሮች ይታዩኛል:: አንደኛው በቂ ዕውቀት ከማጣት የተነሣ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የስብከት ሰዓት መርዘሙ ነው:: ማጨብጨብና እልል ማለት በመሠረቱ ወንጀል አይደለም:: እኛ የምንነቅፈው ምክንያቱን ነው:: እልል የሚባልበትንና የሚጨበጨብበትን

ምክንያት ማስተካከል ይኖርብናል:: በአሁኑ ጊዜ የስብከቱ ሰዓት እየረዘመ ስለሆነ ጊዜውን ለመሸፈን በቂ ዕውቀት ለሌለው ሰው ይከብደዋል:: ስለዚህ በቴሌቪዥኑና ኢንተርኔቱ የተመለከተውን; በጋዜጣው ያነበበውን መጠቃቀስ ግድ ሆኗል:: ዛሬ ሰባኪውን የሚረዳው መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ሞንታርቦ ሲሆን እያየን ነው:: በአሁኑ ሰዓት እኮ ስብከትን በንስሐና በሥጋ ወደሙ ማሠር ቀርቷል:: እንደ ፕሮቴስታንቶቹ 'በቃ ተፈውሰሃል! ሞቶልሃል! ተቃንቶልሃል! ተስተካክሎልሃል!' ብሎ ልክ ተፈራርሞ እንደሚያጸድቁት እልል በሉ; አጨብጭቡ ብሎ መለያየት የምዕራባውያን ተጽዕኖ ነው:: በእውነቱ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ የተሰቀለው ንግዳችን እንዲያተርፍ አይደለም:: ከበሽታ እንድንድን; ሀብታም እንድንሆን; ገበሬ ለሚሞላው ሆድም አይደለም:: ይህንንማ ሠርተህ አልያም ግድ ካለ ለምነህ ትሞላዋለህ:: ከጠፋም ትሞታለህ ግልግል ነው:: ስለዚህ ሰውን ቁሳዊ ማድረግ ሥጋዊ ተስፋ ላይ ማንጠልጠል ሃይማኖት እንዲዘነጋ ማድረግ; በሽታውን ከማከም ይልቅ ምልክቶቹን ማጥፋት ማለት ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ እያንዳንዳችን ተሰጥኦአችን ይለያያል:: ዕውቀት እንጂ ተሰጥኦ አይኮረጅም:: አንተ ጥቁርነትህን ወደ ጠይም ማምጣት አትችልም:: ጥቁርነትህን በመታጠብ ንጹሕ ጥቁር መሆን ትችላለህ:: መንፈስ ቅዱስ አጠቃላይ ጥበቃ ያደርግልሃል እንጂ በተሰጥኦህ ውስጥ አይገባም:: ይህን ማወቅ ያስፈልጋል:: ነገር ግን አስቦ አቅዶ በእግዚአብሔር ዐውደ ምሕረት ቴአትር ለመሥራት መውጣት ግን ወንጀል ነው::

Melaku Gebremichael Hirphasa

22/ መሐመድ እና ዝሙት★

እግዚአብሄር በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ የሌላውን ሚስት መመኘትን አውግዟአል (ዘፀአት 20፡17፣ ዘዳግም 5፡21፣ ማቴዎስ 5፡27-28)። ቁርአን ግን አላህ መሐመድን የሌላውን ሰው ሚስት እንዲፈልግ አነሳስቶታል ይለናል። ይህም መሐመድ እንዲያገባት ሲል ያሳደገው ልጁ ሚስቱን እንዲፈታ አድርጎታል። ይሄንንም ክፉ ኃጥያት እንዲፈጽም አላህ ለመሐመድ ያዘዘበትን ምክንያት ሲናገር አባቶች የአሳደጉአቸውን ልጆች ሚስቶችን ማግባት እንደሚችሉ መሐመድ ምሳሌ እንዲሆን ነው ይለናል☞ (ቁርአን ሱራ/ምእራፍ 33፡37)።

★☞ትምህርት ለመስጠት በሚል ሰበብ መሐመድ የተመኛትን ሴት ለማግባት ሰው ሚስቱን እንዲፈታ ማድረጉን መቀበል በጣም የሚከብድ ነገር ነው።

መሐመድ ለራሱና ለተከታዮቹ የጦር ምርኮኛ ከሆኑ ሴቶች ጋር ከጋብቻ ውጭ የሆነ የግብረስጋ ግንኙነት እንዲያደርጉ ፈቅዶአል።

★☞እግዚአብሄር ለእስራኤላውያኖች በጦር ከማረኩአቸው ሴቶች መካከል ማግባት እንደሚችሉ ነገር ግን ሊሸጡአቸው ወይም ሊጫወቱባቸው እንደማይችሉ ተናግሮአቸዋል። እነዚህን ሊያገቡአችው የሚፈልጉትን ምርኮኞች ለ 30 ቀናት ያህል የቤተሰባቸውን ሃዘን እስኪወጡ ድረስ መጠበቅ አለባቸው። ይህም ሴቲቷን ሊያገባት በፈለጋት ሰው እንዳትደፈርና ከእርሱና ከሌሎች እስራኤላውያን ጋር ለመቀላቀል

እንዲያግዛታ ነው (ዘዳግም 21፡10-14)።

መሐመድ ግን በተቃራኒው ተከታዮቹ በእጆቻቸው ከወደቁት ምርኮኞች እና ባሪያዎች ጋር ከጋብቻ ውጭ ግንኙነት እንዲያደርጉ ፈቅዶላቸዋል (ቁርአን ሱራ/ምእራፍ 4:24፣ 23፡5-6፣ 33፡50፣ 70፡29-30)።

★☞መሐመድ ሁለት ቅምጦች ነበሩት። የመጀመሪያዋ የኮፕቲኳ ማሪያ ቢንቱ ሻሙን ኡም ኢብራሂም የአሌክሳንደሪያና የግብጽ ወታደራዊ አዛዥ ከሆነው አል-ሙቃውቂስ ስጦታ ስትሆን,,, ሁለተኛዋን ቅምጥ በተመለከተ ሪሐናህ ቢንቱ አምሩ ወይም ቢንቱ ዘይድ የተባለችው ከባኒ ኳራዲህ ምርኮኞች መካከል የመረጣት ናት,,, (የነብዩ መሐመድ ሲራህ/ህይወት ታሪክ (The Seerah of Prophet Muhammad (S.A.W.))፣ በመሐመድ አሊ አል ሃላቢ አል አታሃሪ በአጭሩ የተዘጋጀ፣ አል ፊርዶስ ኤል ቲ ዲ፣ ሎንደን፣ የመጀመሪያ እትም 2001፣ ክፍል 2 ገጽ 32-33)

★☞አብዱል አዚዝ እንደተረከው፦ አናስ እንዲህ አለ፥ “የአላህ መልእክተኛ ካሃበርን እንደወረረ,,, አሸንፎ ምርኮኞችንና ምርኮን ሰበሰብን። ዲህያም ወደ አላህ መልእክተኛ መጣና ኦ የአላህ መልእክተኛ! ከምርኮኛ ልጃገረዶች ባሪያ ሥጠኝ ብሎ ጠየቀ። ነብዩም ሂድና አንዷን ውሰድ አለው። እርሱም ሳፊያ ቢንት ሁያይን ወሰደ። አንድ ሰው ወደ ነብዩ መጥቶ ኦ የአላህ መልእክተኛ! ሳፊያ ቢንት ሁያይን ለዲሃያ ሰጠኸው እርሷ እኮ የኳራይዛና አን ናዲር ጎሣ ገዥ ለሆነው ባለሟል ነበረች ለአንተ እንጂ ለሌላ አትሆንም አለው። ከዚያ በኋላ ነብዩ ሁለቱንም አምጡልኝ ብሎ አዘዘ። ዲሃያም ከሴትየዋ ጋር በመጣ ጊዜ ነብዩ አያትና ለዲሃያ

እንዲህ አለው የፈለከውን ባሪያ ልጃገረድ ከእርሷ ውጭ ውሰድ አለው።" ,,, (ሳሂህ አል-ቡኋሪ ቅጽ 1 መጽሃፍ 8 ቁጥር 367)

★☞ጃቢር እንደዘገበው፦ አንድ ሰው ወደ አላህ መልእክተኛ (ሠላም በእርሱ ላይ ይሁን) መጣና እንዲህ አለ አንዲት ባሪያ አለችኝ የቤቴ አገልጋይ ነች ውሃ ትቀዳልናለች እናም ከእርሷ ጋር ግንኙነት አደረግሁ እንድታረግዝ ግን አልፈልግም። የአላህ መልእክተኛም እንዲህ አለው ከፈለግህ አዚል አድርግ ግን ለእርሷ የተወሰነው ይሆናል። ሠውየውም ጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ ተመልሶ መጣና እንዲህ አለ ልጅቱ አረገዘች። ለእርሷ የተወሰነው ይሆናል ብየህ የለም አለው። (ሳሂህ ሙስሊም መጽሐፍ 008 ቁጥር 3383)

★☞አቡ ሰይድ አል ኩድሪ እንደዘገበው፦ በሃናይን ውጊያ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሠላም በእርሱ ላይ ይሁን) የጠላትን ጦር እንዲዋጋ ጦር ወደ አውታስ ላከ። ድል አድርገው ምርኮኛ በወሰዱ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሠላም በእርሱ ላይ ይሁን) አጃቢዎች ባሎቻቸው ጣኦት አምላኪ በመሆናቸው ከምርኮኛ ሴቶች ጋር በግብረ ስጋ መገናኘት ከብዶአቸው ነበር። ከዚያም እጅግ ከፍ ያለው አላህ በዚህ ጉዳይ ላይ መልእክት ላከ እንዲህ ሲል ,,, በእጅህ ላይ የወደቀችውን ሴት ለመገናኘት ትችላለህ (4፡ 24),,, (ሳሂህ ሙስሊም መጽሐፍ 008 ቁጥር 3432) (እንዲሁም ሳሂህ ሙስሊም መጽሐፍ 008 ቁጥር 3371)

★☞ስለዚህ የእስልምና አምላክ መልእክተኛው የጎረቤቱን ሚስት እንዲመኝ ፈቅዶለታል (በተለይም ያሳደገውን የልጁን ሚስት)፣ በልቡም ዝሙት አስፈጽሞታል፣ እንዲሁም የልጁን ሚስት አስፈትቶ አጋብቶታል።

ከዚህም በተጨማሪ አላህ መሐመድንና ተከታዮቹን በባርነትና በምርኮኝነት ከያዟቸው ያገቡ ሴቶች ጋር ዝሙት እንዲፈፅሙ ፈቅዶላቸዋል። ታዲያ የስጋ ምኞቱን ለማርካት የእግዚአብሔርን ሕግ የጣሰውን መሐመድን የእግዚአብሔር ነብይ ነው እንዴት እንላለን?

እግዚአብሔር ማስተዋል ይስጥ

Yared Gebremedhin

23/ አውሮፓን ጅብ ያስበላ የሉተር ስብከት

በተዋሕዶ መድረክ

ከሀገር ቤት ከወጣሁ አሥረኛ ዓመቴን እየያዝኩ ነው።በዚያን ጊዜ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ መናፍቃን በቡድን በመደራጀት እንቅስቃሴ ጀምረው ነበር።እኛ ያልዘመርንበት ሰርግ ምኑን ሰርግ ሆነ።እኛ ያልተገኘንበት ጉባኤ እንዴት ጉባኤ ሊባል ይችላል በሚል የሌላውን አገልግሎት ሁሉ ባዶ አድርገው እራሳቸውን ሲያስቀድሙ አስታውሳለሁ።በወቅቱ ከጥቅም አንጻር ብቻ የሚደራጁ የመሰላቸው ጥቂቶች አልነበሩም።አካሄዱ ግን ከጥቅም ባለፈ ሌላ የተለየ ዓላማ ከጀርባው እንደነበረበት ያስታውቃል።ያን ጊዜ በተደጋጋሚ ሲናገሩት የሚሰማ ትልቁ አጀንዳቸው “ጌታ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አልተሰበከምና እርሱን መግለጥ አለብን” የሚል ነው።ይሄ አጀንዳ ደግሞ ምንጩ ማን እንደሆነ እናውቀዋለን።እነዚህ ቀሚሳችንን ለብሰው በድፍረት የሚውረገረጉ ውሉደ መርገም የተሐድሶ ማናፍቃን ተላላኪዎች ናቸው።እንዲህ የሚሯሯጡት የተሰጣቸውን ተናግረው የእለት

ጉርስ ለማግኘት ነው።ዋነኞቹ እና በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ይህ መልእክት እንዲተላለፍ የሚፈልጉት ግን በምዕራቡ ዓለም የዘሩት የሉተር እምነት የጠወለገባቸው ፕሮቴስታንቶቹ ናቸው።ፕሮቴስታንቶቹ የሉተር እምነት በምድር አውሮፓ ጠውልጎና ደርቆ ሲመለከቱ ለጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን "ጌታን ሊገልጡ" ሚሴዎናውያንን ላኩ ሚሴዎናያኑ ደግሞ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አራማጆችን ልከው ሕዝቡን ማደናቆር ያዙ።ለቀባሪ ማርዳት ይሉሃል ይሄ ነው።

በአውሮፓ ተዘርቶ ያልበቀለ፣ሕዝቡን ለእስልምና እና እግዚአብሔር የለም ለሚል ፍልስፍና አሳልፎ የሰጠ ከንቱ እምነት፣ሉተር የመሠረተው የፕሮቴስታንት እምነት እኛ ሃገር ለመዝራት መሞከር ተሳልቆ ወይም ምቀኝነት እንጂ ሌላ ምን ይሉታል።በምድረ አውሮፓ ወደ ሉተራውያን"ቤተ ክርስቲያን"የሚሄድ ሕዝብ ጠፍቷል።ከዚህ ይልቅ ሕዝቡ እግዚአብሔር የለም በሚል ፍልስፍና ኢአማኒ ወደ መሆን ተሸጋግሯል።በሚሺነሪ ታሪክ የምትታወቀው አፍሪካን በፕሮቴስታን እምነት ለማጥለቅለቅ ሌት ተቀን የምትሰራው ስዊድን እንኳን ከሕዝቧ ቁጥር 34 ፐርሰንቱ እግዚአብሔር የለም ብሎ እንደሚያምን ጥናቶች ይጠቁማሉ።የእግዚአብሔር መኖር የሚያምነው ደግሞ 27 ፐርሰንት የሚሆነው ብቻ ነው።በፈረንሳይም 40 ፐርሰንት የሚሆን ሕዝብ የእግዚአብሔርን ሕልውና የማይቀበል ሰሆን የእግዚአብሔር መኖር አምኖ የሚቀበለው ደግሞ 18 ፐርሰንት ብቻ ነው። በመካከል የለም አለ ሳይል የሚኖር ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ እንዳለም ልብ ይበሉ(1)።

ሌላው በ2011 እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር የተደረገ ጥናት

እንደሚያመለክተው በታላቋ ብሪቴን ክርስቲያን ነን ብሎ የሚያምነው 72 ፐርሰንት ሲሆን "ቤተ ክርስቲያን" የሚሄደው ህዝብ ግን 1.4 ፐርሰንቱ ብቻ ነው።ሉተር በተፈጠረባት ሀገር በጀርመን 72 ፐርሰንቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ክርስቲያን ነኝ ብሎ የሚያምን ሲሆን "ቤተ ክርስቲያን" የሚሄደው 1,2 ፐርሰንቱ ብቻ ነው(2)።ከዚህ አንጻር ሁለት ፐርሰንት የሚሞላ ሕዝብ "ቤተ ክርስቲያን"የማሔድባቸው ሃገሮች(እንግሊዝ፣ጀርመንን የመሳሰሉ ሀገሮች)“ዓይናችሁን በወንጌል እናብራ አዲስ ጌታ እንስበካቸሁ”በሚል መነሳታቸው ብቻ ሳይሆን ማሰባቸው በራሱ እጅግ እጅግ የሚያስገርም ነው።ነገሩ የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስላለች ይመስላል።

ጥንታውያኑ አብያተ ክርስቲያናት ከጌታችን እና ከሐዋርያት የተቀበሉትን ክርስትና ይዘው በብዙ ፈተና ሳይፈቱ ዘመናትን ስለመሻገራቸው ዓለም በሙሉ የሚያውቀው እውነታ ነው።ሶሪያ፣ግብፅ፣አርመ

ን፣ኢትዮጵያ ሕንድ፣ኤርትራ ..... ለዚህ ሕያው ምስክሮች ናቸው። ከገጠማቸው ፈተና ከድህነታቸው አንጻር እግዚአብሔር የለም ለማለት የሚቀርቡት እነርሱ ነበሩ።ነገር ግን የያዙት እምነት (ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) በዓለት ላይ የተመሠረተች በመሆና ልጆቿ ችግር ሳይፈታቸው በመከራ ውስጥም እየጸኑ ወልድ ዋሕድ ሲሉ ይኖራሉ።አንዳንድ ጊዜ ሰይጣን ኃይል እና ጉልበት በመጠቀም የእነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ልጆች ሲያርድ እና ሲገድል የምናየውም ለዚህ ነው።አሁን አሁን ዶግማ፣ቀኖና፣ትውፊት ምን እንደሆነ ለማወቅ ዓለሙ ወደ እነዚህ አብያተ ክርስተያናት መገስገስ ጀምሯል።የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለመረዳት ዓለሙ ወደ ጥንታውያኑ

አብያተ ክርስቲያናት እየቀረበ ነው።በነገረ ክርስቶስ ላይ የሚያስተምሩትም ትምህርት ይህ ይጨመርበት ይህ ይጎድለዋል የሚባል አይደለም።

ታዲያ የጥንካሬ ተምሳሌት ለሆኑ፣የጠራ ትምህርተ ሃይማኖት ላላቸው ለእነዚህ አብያተ ክርስተያናት አዲስ ወንጌል መላክ ምን ይሉታል ? እንዴትስ ያለ ድፍረት ነው ? ክርስቶስን አማላጅ የሚል የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ሌሎች ቅዱሳንን ክብር የሚያቃልል አዲስ ወንጌል፣ጾም ጸሎት አያስፈልግም የሚል አዲስ፣ወንጌል ለተዋሕዶ ልጆች ለምን አስፈለገን ? ይህ አዲስ ትምህርት በሉተራውያን ሻንጣ ወደ ሃገር ቤት ገብቶ ውሉደ መርገም በሆኑ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ እምነት አራማጆች በኩል በተዋሕዶ አደባባይ ካልተዘራ የሚል ትንቅንቅ ተይዟል።

ተዋሕዶ ስዊድን እና ጀርመንን እንድትታደግ ድረሺልን የሚል ጥሪ መስማት ሲገባት ሕዝባቸውን አምላክ የለሽ ባደረጉ ፕሮቴስታንቶች ደጃፎቿ እየተንኳኳ ነው።ለማንኛውም እኛ የክርስቶስ ወንጌል ሳይበረዝ እና ሳይከለስ የደረሰን ነን፣የድንግል ማርያም የቃል ኪዳን ልጆች ነን።ስለዚህ አውሮፓን ጅብ ያስበላ የሉተር ስብከታችሁን ይዛችሁ ከመድረካችን ውረዱ።

ቀሲስ ያሬድ ገብረ መድኅን (ኮለምበስ ኦሀዮ)

24/ አውሮፓን ጅብ ያስበላ የሉተር ስብከት በተዋሕዶ መድረክ

200 Like

ቀሲስ ያሬድ ገብረ መድኅን (ኮለምበስ ኦሀዮ)

(አንድ አድርን ጥቅምት 08 2008 ዓ.ም)፦ ከአስር ዓመት በፊት

የፕሮቴስታንት ተሐድሶ መናፍቃን

በቡድን በመደራጀት እንቅስቃሴ ጀምረው ነበር።እኛ

ያልዘመርንበት ሰርግ ምኑን ሰርግ ሆነ።እኛ

ያልተገኘንበት ጉባኤ እንዴት ጉባኤ ሊባል ይችላል

በሚል የሌላውን አገልግሎት ሁሉ ባዶ አድርገው

እራሳቸውን ሲያስቀድሙ አስታውሳለሁ።በወቅቱ

ከጥቅም አንጻር ብቻ የሚደራጁ የመሰላቸው ጥቂቶች

አልነበሩም።አካሄዱ ግን ከጥቅም ባለፈ ሌላ የተለየ

ዓላማ ከጀርባው እንደነበረበት ያስታውቃል።ያን ጊዜ

በተደጋጋሚ ሲናገሩት የሚሰማ ትልቁ አጀንዳቸው “ጌታ በኢትዮጵያ ቤተ

ክርስቲያን አልተሰበከምና

እርሱን መግለጥ አለብን” የሚል ነው።ይሄ አጀንዳ

ደግሞ ምንጩ ማን እንደሆነ እናውቀዋለን።እነዚህ

ቀሚሳችንን ለብሰው በድፍረት የሚውረገረጉ ውሉደ

መርገም የተሐድሶ ማናፍቃን ተላላኪዎች ናቸው።እንዲህ የሚሯሯጡት

የተሰጣቸውን ተናግረው የእለት

ጉርስ ለማግኘት ነው።ዋነኞቹ እና በቤተ ክርስቲያኒቱ

ላይ ይህ መልእክት እንዲተላለፍ የሚፈልጉት ግን

በምዕራቡ ዓለም የዘሩት የሉተር እምነት

የጠወለገባቸው ፕሮቴስታንቶቹ ናቸው።ፕሮቴስታንቶቹ

የሉተር እምነት በምድር አውሮፓ ጠውልጎና ደርቆ

ሲመለከቱ ለጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን “ጌታን
ሊገልጡ” ሚሴዎናውያንን ላኩ ሚሴዎናያኑ ደግሞ
የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አራማጆችን ልከው ሕዝቡን
ማደናቆር ያዙ።ለቀባሪ ማርዳት ይሉሃል ይሄ ነው።
በአውሮፓ ተዘርቶ ያልበቀለ፣ሕዝቡን ለእስልምና እና
እግዚአብሔር የለም ለሚል ፍልስፍና አሳልፎ የሰጠ
ከንቱ እምነት፣ሉተር የመሠረተው የፕሮቴስታንት
እምነት እኛ ሃገር ለመዝራት መሞከር ተሳልቆ ወይም
ምቀኝነት እንጂ ሌላ ምን ይሉታል።በምድረ አውሮፓ
ወደ ሉተራውያን "ቤተ ክርስቲያን" የሚሄድ ሕዝብ
ጠፍቷል።ከዚህ ይልቅ ሕዝቡ እግዚአብሔር የለም
በሚል ፍልስፍና ኢአማኒ ወደ መሆን ተሸጋግሯል።በሚሺነሪ ታሪክ
የምትታወቀው አፍሪካን በፕሮቴስታን
እምነት ለማጥለቅለቅ ሌተ ተቀን የምትሰራው
ስዊድን እንኳን ከሕዝቧ ቁጥር 34 ፐርሰንቱ
እግዚአብሔር የለም ብሎ እንደሚያምን ጥናቶች
ይጠቁማሉ። የእግዚአብሔር መኖር የሚያምነው
ደግሞ 27 ፐርሰንት የሚሆነው ብቻ ነው።በፈረንሳይም 40 ፐርሰንት
የሚሆን ሕዝብ
የእግዚአብሔርን ሕልውና የማይቀበል ሰሆን
የእግዚአብሔር መኖር አምኖ የሚቀበለው ደግሞ 18
ፐርሰንት ብቻ ነው። በመካከል የለም አለ ሳይል

የሚኖር ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ እንዳለም ልብ

ይበሉ(1)።

ሌላው በ 2011 እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር

የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው በታላቋ ብሪቴን

ክርስቲያን ነን ብሎ የሚያምነው 72 ፐርሰንት ሲሆን "ቤተ ክርስቲያን"

የሚሄደው ህዝብ ግን 1.4 ፐርሰንቱ

ብቻ ነው።ሉተር በተፈጠረባት ሀገር በጀርመን 72

ፐርሰንቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ክርስቲያን ነኝ ብሎ

የሚያምን ሲሆን "ቤተ ክርስቲያን" የሚሄደው 1,2

ፐርሰንቱ ብቻ ነው(2)።ከዚህ አንጻር ሁለት ፐርሰንት

የሚሞላ ሕዝብ "ቤተ ክርስቲያን" የማይሄድባቸው

ሃገሮች(እንግሊዝ፣ጀርመንን የመሳሰሉ

ሀገሮች)“ዓይናችሁን በወንጌል እናብራ አዲስ ጌታ

እንስበካቸሁ” በሚል መነሳታቸው ብቻ ሳይሆን

ማሰባቸው በራሱ እጅግ እጅግ የሚያስገርም ነው።ነገሩ የራሷ ሲያርባት

የሰው ታማስላለች ይመስላል።

ጥንታውያኑ አብያተ ክርስቲያናት ከጌታችን እና

ከሐዋርያት የተቀበሉትን ክርስትና ይዘው በብዙ ፈተና

ሳይፈቱ ዘመናትን ስለመሻገራቸው ዓለም በሙሉ

የሚያውቀው እውነታ ነው። ሶሪያ፣ግብፅ፣አርመን፣ኢትዮጵያ

ሕንድ፣ኤርትራ .....

ለዚህ ሕያው ምስክሮች ናቸው። ከገጠማቸው ፈተና

ከድህነታቸው አንጻር እግዚአብሔር የለም ለማለት

የሚቀርቡት እነርሱ ነበሩ።ነገር ግን የያዙት እምነት (ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ)

በዓለት ላይ የተመሠረተች

በመሆና ልጆቿ ችግር ሳይፈታቸው በመከራ ውስጥም

እየጸኑ ወልድ ዋሕድ ሲሉ ይኖራሉ። አንዳንድ ጊዜ

ሰይጣን ኃይል እና ጉልበት በመጠቀም የእነዚህን

አብያተ ክርስቲያናት ልጆች ሲያርድ እና ሲገድል

የምናየውም ለዚህ ነው። አሁን አሁን ዶግማ፣ ቀኖና፣ ትውፊት ምን

እንደሆነ ለማወቅ ዓለሙ ወደ እነዚህ

አብያተ ክርስተያናት መገስገስ ጀምሯል። የቅዱሳት

መጻሕፍትን ትርጓሜ ለመረዳት ዓለሙ ወደ

ጥንታውያኑ አብያተ ክርስቲያናት እየቀረበ ነው። በነገረ

ክርስቶስ ላይ የሚያስተምሩትም ትምህርት ይህ

ይጨመርበት ይህ ይጎድለዋል የሚባል አይደለም።

ታዲያ የጥንካሬ ተምሳሊት ለሆኑ፣የጠራ ትምህርተ

ሃይማኖት ላላቸው ለእነዚህ አብያተ ክርስተያናት

አዲስ ወንጌል መላክ ምን ይሉታል ? እንዴትስ ያለ

ድፍረት ነው ? ክርስቶስን አማላጅ የሚል

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ሌሎች

ቅዱሳንን ክብር የሚያቃልል አዲስ ወንጌል፣ጾም

ጸሎት አያስፈልግም የሚል አዲስ ወንጌል ለተዋሕዶ

ልጆች ለምን አስፈለገን ? ይህ አዲስ ትምህርት

በሉተራውያን ሻንጣ ወደ ሃገር ቤት ገብቶ ውሉደ

መርገም በሆኑ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ እምነት

አራማጆች በኩል በተዋሕዶ አደባባይ ካልተዘራ የሚል

ትንቅንቅ ተይዟል።ተዋሕዶ ስዊድን እና ጀርመንን

እንድትታደግ ድረሺልን የሚል ጥሪ መስማት ሲገባት

ሕዝባቸውን አምላክ የለሽ ባደረጉ ፕሮቴስታንቶች

ደኛፎቿ እየተንኳኳ ነው።ለማንኛውም እኛ የክርስቶስ

ወንጌል ሳይበረዝ እና ሳይከለስ የደረሰን ነን፣የድንግል

ማርያም የቃል ኪዳን ልጆች ነን።ስለዚህ አውሮፓን

ጅብ ያስበላ የሉተር ስብከታችሁን ይዛችሁ

ከመድረካችን ውረዱ።

1-Christy, John (2013)The Decline of European Christianity. Available at < http://www.johnchristy.com/The-Decline-of-European-Christia… >

2-Beshears, Kyle R. (2015) Empty Churches: The Decline of Cultural Christianity in the West.

Notify me

Comment as:

Publish Preview

Create a Link

2 comments:

Anonymous October 18, 2015 at 11:44 PM

ፕሮቴስታንቲዝም ክርስትናን ለሴኩላሪዝም ባሪያ አድርጎ የሚሸጥና እግዚአብሔርን መፍራት እንዲጠወልግና እግዚአብሔርን ማመን እንዲገረና የሚያደርግ የጠላታችን የረዥም ጊዜ እቅድ መኾኑን በአውሮጳና በአሜሪካ በተግባር አይተነዋል።

እኔ ነኝ የሚል ሄዶ ሳውዲ ዐረቢያ “ጌታን ተቀበሉ!” ይበል። በፈሪሐ እግዚአብሔር የሚኖር ጭምት ሕዝብ ላይ ማጓራት ምን የሚሉት ወንጌል ነው። የክርስቶስን ቤዛነት ያመነ፤ በጥምቀትም ወደሞቱ የተቀበረ ሕዝብን ቀይ ጌታን ተቀበል ማለት ከጀርባው የገንዘብ ጥሜትና የሀብት ማግበስበስ ዓላማ ያለው እንጂ እውነት ነፍሳትን አርነት ለማውጣት አይደለም። ይህ ቢኾን ኖሮ በርግጠኝነት የኢየሱስ ክርስቶስ ስሙ እንዲጠራባቸው እንኳን የማይፈልጉ ሚልዮኖች ከዚህ ሕዝብ ቅድሚያ ይሰጣቸው ነበር። ምን ያረጋል! አንገቱን ቆርጠው እንደሚጥሉለት ያቃል። ከነዚህ ውስጥ ወንጌልን በርግጥ የሚያቃት ቢኖር ቀድሞ ለአላውያን ይሰብክላቸው ነበር፤ “በወንጌል አላፍርም!” -- እንደተባለ 1 ቆሮ.9፣23።

Reply

Sasbais Sadbias October 19, 2015 at 2:28 AM

አዎ እውነት ነው ከአውደምህረታችን ይወረዱልን። አሁንማ በግልጽ ነው በየፊስቡክ እየለጠፉና ማንነታቸውን በግልጽ እያሳወቁን ያሉት።በዛሬው እለት በታሪኩ አበራ የፊስ ቡክ ገጽ ላይ የተለጠፈውን ብታነቡት ግልጽ የሆነ ኘሮቴስታንታዊ አስተምሯቸውን ለጥፈው ታገኙታላችሁ። በጋሻው

ያስተላለፈውን መልእክት የሚገርም ግልጽ የሆነ የሉተር ትምህርትን ነው በድፍረት እያሰተላለፉ ያሉት። ሁሉም እንዲገባውና እንዲደርሰው መሰራት አለበት። ተኩላው የተሳካለት እየመሰለ እራሱን እየገለጸ ነውና እናንተም በርቱ እኛም ማድረግ ያለብንን እንድናደርግ መንገዱን አሳውቁን። በርቱ የተዋህዶ ልጆች እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል። ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ነው? ችግር ነው? ወይስ ረሀብ በተዋህዶ

ፀረ-በጋሻው ደሳለኝ ፀረ-ተሃድሶ

የምስራች ከወደ ወለጋ

እልልልልልልልል

25/ የተዋህዶ ልጆችን አንገት ቀና የሚያደርግ መረጃን የያዝከው ፀረ ሀራጥቃ መምህር ዘመድኩን በቀለ እባክህ ቶሎ ና!

※ ※※

ውድ የፊስ ቡክ ጓደኞቼ እንደምን ሰንብታችኋል ? እኔ እጅጉን በጣም ደህና ነኝ ። ያው ለጊዜው ፊስ ቡክ መጠቀም ባልችልም ከፊስ ቡክ በበለጠ መልኩ ተደራሽነቱም በጣም ሰፊ በሆነው መካነ ድር ወይም ዌብ ሳይት በኩል ለመምጣት ከጫፍ እየደረስኩ መሆኑን እያበሰርኩ ፣ ለዚሁም የዌብ ሳይት ዝግጅት መሳካት በብርቱ እየደከማችሁ ያላችሁ ጓደኞቼ ሁላችሁም

በእግዚአብሔር ስም ምስጋናዬ ይድረሳችሁ ።

በተረፈ የእምዬ ቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ልጆች በሙሉ እንኳን ደስ ያላችሁ ።

ዝርዝሩን አጠናክሬ በቀጣይ እመለስበታለሁ ። መረጃዎቹ በሙሉ ተጠቃለው በእጄ የገቡ ቢሆንም ዘርዘር አድርጌ እስካቀርብላችሁ ድረስ በትዕግስት እንድትጠብቁኝ እየጠየቅሁ እስከዚያው ድረስ ግን ከምስራቹ እነሆ ብያችኋለሁና ንሱማ ተቀበሉኝ ።

ነገሩ እንዲህ ነው ። በሀገረ ስብከቱ ምእመናን መረጃ አቅራቢነትና የተጠናከረ ክትትል ከፊታችን በሚመጣው የጥቅምቱ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በፊት በብጹዕ አቡነ ስምዖን የምስራቅ ወለጋ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፊርማና ቲተር እንዲሁም በሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት ማኅተም ተረጋግጦ በወጣ ደብዳቤ በተሃድሶ ግሪሳዎች ላይ እርምጃ ተወስዷል ።

አንድ "መምህር " አንድ " ካህን " 3 "ዲያቆናት" እና አንድ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣት ላይ ስልጣነ ክህነት ያላቸው በሙሉ ስልጣነ ክህነታቸው ተይዞ ከየትኛውም አገልግሎት የታገዱ መሆናቸው ተገልጦ በግልባጭ

※ ለመን/ፓት/ ጠቅላይ ጽ/ቤት

※ ለሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ክፍል

※ " " ስብከተ ወንጌል ክፍል

※ ለነቀምቴ ከተማ አድባራት

※ ለምስራቅ ወለጋ ዞን የአስተዳደር ፀጥታ ዘርፍ ጽ/ቤት

※ ለነቀምቴ ከተማ የአስተዳደር ፀጥታ ዘርፍ ጽ/ቤት

※ ለነቀምቴ ከተማ አድባራት

※ ለ 17 ቱ ወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በሙሉ በየ አድራሻቸው ተጽፏል ።

ደብዳቤው እንደሚገልጸው ከሆነ እነዚህን ሰዎች በማጋለጡ በኩል ምእመናን ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ እንደነበር ደብዳቤው ይገልፃል ።

በዚህም መሠረት

፩ኛ፦ ቄስ ሙሴ ዘሪሁን /ነቀምቴ/

፪ኛ፦ መ/ር ስዩም ስንታየሁ/ነቀምቴ/

፫ኛ፦ ዲን ዓለማየሁ አየልኝ/ነቀምቴ/

፬ኛ፦ ዲን ታረቀኝ ፈቃዱ /ነቀምቴ/

፭ኛ፦ ዲን ነቢዩ ጀምበሬ / አርጆ ጉደቱ /

፮ኛ፦ ወጣት ኢታና ዲንቂሳ / ነቀምቴ/ መሆናቸውን እወቁ ብላለች ቅድስት ቤተክርስቲያን ።

በሌላ በኩል በአዲስ አበባ ደግሞ በግ ዋሻው በፖሊሶች ተከብቦ እንዲያስተምር ሲደረግ በዓይናችን በብረቱ ዐየን ። የሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ግን ይህ ሁሉ ሲደረግ የካህናት ጉባኤውም ይህ ድርጊት ሲፈፀም ዐይተው እንዳላዩ ሰምተውም እንዳልሰሙ ሁሉንም ነገር በዝምታ አልፈውታል ።

ለማንኛውም ብጹዕ አቡነ ስምዖን እና የሀገረ ስብከቱ ካህናት አባቶች በሙሉ የምእመናንን ጩኸት በመስማት ከቤተክርስቲያን ጎን በመቆማችሁ ረጅም ዕድሜ ከተሟላ ጤንነት ጋር ተመኝንላችሁ ። ደስ ሲል በእመቤቴ ። እየመጣሁ ነው ጠብቁኝ ጓደኞቼ እየመጣሁ ነው ። ሙልጭ አድርገው የሚሰድቡኝ ግሪሳዎችም እንዴት እንደናፈቁኝ አትጠይቁኝ ። በሉ ሰላም ሁኑልኝ ።

" ጌታ ሆይ ! ክብርና ምስጋና ይድረስህ "

"ድንግል ሆይ እናቴ አማላጅቱ ሆይ አሁንም እንደትናንቱ ቅደሚ ከፊት ከኋላዬ " አሜን ።

ይህንንም እኔው ራሴ ዘመድኩን በቀለ ጻፍኩት ። እንደተለመደው 0911608054 የእጅ ስልኬ ነው ።

ዘመድኩን በቀለ ነኝ

ጥቅምት 8/2/2008 ዓም

አዲስአበባ - ኢትዮጵያ

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት መልስ አላት

26/ አስገራሚውን ሚስጥር ላካፍላችሁ!

(ትዝታ መዝገቡ ነኝ ከዱባይ!)

በዱባይ የቅዱስ ሚካኤል የተሃድሶ ቤተክርስቲያን ያስተዋልኩትን ልንገራችሁ።

ዱባይ መኖር ከጀመርኩ ጊዜ ወዲህ በሚመቸኝ ቀን አርብ አርብ ማታ በቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ጉባኤ በሚካሄደው እካፈል ነበር። በርግጥ ያው በተከታታይ ባይሆንም አርብ ረፍቴ ከሆነ እያለፍኩም ቢሆን እከታተል ነበር።

ከአንዳንድ ሰዎች የተሃድሶ ቤተክርስቲያን ነው የሚል ጭምጭምታ ብሰማም

ጉዳዩ ከወሬ ያለፈ አልመሰለኝም ነበር። ትንሽ እየቆየ ሲሄድ ነገሮች ሁኔታቸው ምንም አላምር አለኝ። በተለይ ቄስ ተብየው ቀሲስ ተስፋ ሁኔታው ሁላ የመናፍቅ ፀሎቱ በሙሉ ከአዳራሽ የተቀዳ ፖስተር ቢባል የሚስማማው አይነት ነበር። ጉዋደኞቼም የሱ ነገር ግራ ይገባቸዋል ::

አንዳንድ ሰዎች ስንጠይቅ ዝም ብሎ ነው እንጂ እንደውም ቤቱ ብትሄዱ በጣም ትሁት ሰው ነው ይላሉ። ያም ሆነ ይህ አማራጭ በሌለበት ሁኔታ ምንም ማድረግ ስለማይቻል ቃለ እግዚአብሄርን ለተራበ ሰው የፖስተሩን ፀሎት መታገስ ግድ ነበር።

ጭራሽ ሲቆይ የስብከታቸው ጭብጥ ራሱ ምንም አልገባ አለኝ። ከየት እንደመጡ የማይታወቁ መምህራን ተብዬዎች ምን እንደሚሉ ሳይገባኝ ከጉዋደኛዬ ጋር ግራ እየተጋባን እንነጋገራለን። ትንሽም ብትሆን መሰረታዊ የቤተክርስትያን ትምህርቶች ስለማውቅ ቢያንስ የሚናገሩት ነገር ከቤተክርስትያን አስተምህሮ ጋር እንደማይስማማ እናገራለሁ።

በጭራሽ በቤተክርስቲያኑ የእመቤታችን ስም አይጠራም ፥የፃድቃን የሰማእታትማ ነገር የማይታሰብ ነው። እለቱ ሚካኤል ሆኖ እንኩን በስሙ የሚነግዱበትን ቅዱስ ሚካኤል ስም አይጠሩም። አንድ ቀን እንደውም ጉባኤ ቤሪያ ብለው እነዘርፌ ተጋብዘው ከምስኪን የሰው ቤት ከሚሰሩ ልጆች አስጨንቀው ከ260 ድርሀም ከእያንዳንዱ ሰው ተቀብለዋል። በርግጥ እኔ በእለቱ ስራ ስለነበርኩ አልሄድኩም ነበር ጉዋደኛዬ ግን ልመና ባልቀረው ድምፃቸው አፍራ ከፍላ መጥታለች።

በባህር ላይ ልዩ ጉባኤ እናደርጋለን ለዛ የግድ ማዋጣት አለባችሁ ብለው አስጨንቀው ነው የተቀበሉዋቸው። ጉባኤ ቤሪያ የሚሉት ጉባኤ ከለባት

ልበለውና አንድ አርብ በመዝጊያው ቀን ረፍት ስለነበርኩ ተገኘሁ። የግሪሳው ቡድን እዛው ነበሩ። የባህር ላይ ፕሮግራም የተባለውም ቀርቶ ምንም አዲስ ነገር ሳይኖር በተለመደው የአዳራሽ ጉባኤ ተካሄደ።

በእለቱ ከ1pm እስከ 10pm በተደረገው ጉባኤ የእመቤታችን መዝሙር 1 ብቻ ለይምሰል እንደተዘመረ አስታውሳለሁ። አስቡት እንግዲህ ምን ያህል አንደበታቸው የማሪያምን ምስጋና ለማቅረብ እንደተዘጋ።

በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚዘመሩት መዝሙሮች የተወሰኑና የተገደቡ ናቸው። ከ95% በላይ የትዝታው የዘርፌ የምርትነሽ ናቸው:: ገፉ ካለ የቴዲን ያው ስለሚወዱዋቸው ነበር የሚመስለኝ። እኔም እወዳቸው ስለነበር በክፋት አላየሁትም። አሁን ስረዳው የነሱን ብቻ እንድንሰማ የተደረገው አይምሮዋችንን ለመቆጣጠር እንደሆነ አወቅኩ።

በዚህ በተከፈለ እና በመጠራጠር መንፈስ ሆኜ የፋሲካ እለት የአዳር ፕሮግራም ቅዳሴ አለ ሲሉኝ ከጉዋደኞቼ ጋር እንሄዳለን።

የቅዳሴው ፕርግራም የሚመራው ደግሞ ቄስ ተብዬው ፓስተር ነው። እንግዲህ ቅዳሴው ተጀምሮ እያስቀደስን እያለ ፓስተሩ ልበለው ቅዳሴውን እያቁዋረጠ የራሱን የግል ፀሎት ይቀጥላል። ምንም የማላውቀው አይነት የቅዳሴ ስርአት ግራ አጋባኝ።

ቄሱ ፓስተር ቅዳሴውን ይቆርጥና.....

በዱባይ ላይ ኢየሱስ ጌታ ነው አሜን!!!

በቅዱስ ሚካኤል ላይ ኢየሱስ ጌታ ነው አሜን!!!

በኢየሱስ ስም የወደቀ ይሁን

የተመታ ይሁን!

የፈረሰ ይሁን!

አሜን.....ይባላል።

እንዲህ አይነት ፀሎትም ቅዳሴም በቤተክርስቲያን አባቶች ሰምቼ ስላማላውቅ በጣም አስጠላኝ። እስቲ ቅዳሴን እየቆረጠ የራሱን ፀሎት መጨመር ምን አመጣው? ቅዳሴ የራሱ ስርአት አለው። ረዘመ ብሎ ማሳጠር ይህ አያስፈልግም ብሎ መቁረጥ ይህ ያስፈልጋል ብሎ መቀጠል አይቻልም!

ደግሞ እኮ ብታዩት አይኑን ሙሉ ለሙሉ ጨፍኖ በየሰኮንዶ አረፍ እያለ እራሱ እዛው እየፈጠረ ነው የሚፀልየው።

ከሁሉ ደግሞ ግራ ያጋባኝ ወደ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተደረገው ልመና ነው።

ሳስበው መካከለኛ የሚለውን የጴንጤ ዶክትሪን ለማለማመድ ይመስለኛል።

በልጅህ በኢየሱስ ስም እንለምንሀለን!!!

አሜን!!!!.....ይባላል።

እንግዲህ በቤተክርስትያን ካህኑ በቀጥታ አምላካችንና ጌታችን መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የካህናት አለቃ ሀጥያትን የምታስተርይ ይቅር ባይ የኔንም የህዝብህንም ሀጥያት ይቅር በል ሲል ነው የማውቀው።

ትንሽ ቆየት ብሎ ደግሞ የሃይማኖት ፀሎትን ጀመረ።

ከዛ አሸናፊ እግዚአብሄር ሆይ የሚለው ላይ ሲደርስ ቆረጠው የኔም ልብ እዚህ ጋር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቆረጠ።

ምክኒያቱም ቀጥሎ ያለው ክፍል እናታችን ማሪያም ሆይ እንሰግድልሻለን እንማልድሻለን የሚለውን ስለሆነ ላለማለት እንደሆነ አወቅኩ።

በዛ ፈንታ የራሱን ዲስኩር ፀሎት አስገባ

ፀጋውን ስላረሰረስከን.....ስላፈሰስክልን....የሚሉ የማታለያ ቃላቶች እያሰማመረ አይኑን ጨፍኖ ይፀልያል።

ቤተክርስቲያኑን ለቅቄ ልወጣ ብፈልግም ጉዋደኞቼን መጠበቅ ስለነበረብኝ በጣም ብናደድም እንደምንም ለመቆየት ራሴን አረጋጋሁ።

ቁርባን ብለው የሰንበት ተማሪዎቹ በሙሉ በፍፁም ድፍረት የጌታን ስጋና ደም ሲቀበሉ ሳይ በመታሰቢያነት እየወሰዱ ነው የመሰለኝ።

ምክንያቱም በቤተክርስቲያን ምስጢረ ቁርባን ትልቅ ክብር አለው። ከቁርባን በፊት የሚደረገው ንሰሀና ቅድመ ዝግጅት አድርገው ቀኖናቸውን ፈፅመው ከሆነ እሰይ።

"ሳይገባውም ይህን የወሰደ የጌታ ስጋና ደም እዳ አለበት" ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው። አውቀውት ካደረጉትም እግዚአብሄር ይቅር ይበላቸው።

ከዚያም ለመጨረሻ ጊዜ ከድንግል ጠላቶች ጋር ከዋልኩበት ጉባኤ ወጣሁ። ይበልጥ ቀሚሳችንን ለብሰው ወደ ጥፋት ጎዳና ሲመሩን በየዋህነት ማመናችን አመመኝ። የሰው ሀገር መሆኑና አማራጭ አለሞኖሩን አይተው እየቀለዱብን እንደሆነ ተሰማኝ። በዚህ የተነሳ የበአሉ ቀን በጣም አዘንኜ ዋልኩ።

ትንሽ ቆይቶ ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተክርስቲያኑን በግልፅ አወገዘ። የሚሄዱ ምእመናናም የተገዘቱ እንደሆነ አወጀ።

አስቀድሜም ስላልረጋገጥኩ ባይገዘትም አልሄድም ነበር። ወዲያው ደግሞ ጉባኤ ተብሎ እነዘርፌ በጋሻው የግሪሳው ቡድኖች ወደ ዱባይ መጡ።

የአባቶቻችንን ስልጣነ ክህነት አቃለው በተወገዘ ቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ

ርኩሶች ቀንደኛ ተሃድሶዎች ዋና እነሱ መሆናቸውን አረጋገጥኩ።

ወዲያው ከሜሞሪዬ ላይ መዝሙሮቻቸውን በሙሉ ዲሊት አደረግኩ። ከዚያ በሁዋላ ተሀድሶ የሚባል ነገር አለ የለም ለሚሉ እኔ ራሴ ምስክር ነኝ።

የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠበቁ ማቴ. 7:15

ለምድ የተባለው ለምዱ ልብሰ ተክህኖአችን ለምድ የተባለው መስቀላችን ለምድ የተባለው ቆባችን ለምድ የተባለው ስሞቻችን(ዲያቆን፣ቄስ፣መጋቤ ሀዲስ፣ሊቀ ጠበብት፣መጋቤ ብሉይ፣ሊቀሊቃውንት...)

መሆኑን እንወቅ።

እነዚህን ይዘው ወደ እኛ ሲመጡ ካልመረመርን ተኩላዎችን እልልል ብለን እንቀበላለን ምክንያቱም በግ መስለው ከበግ መሀል ተቀላቅለዋልና።

ውስጣቸው ግን ክህደትና ኑፋቄ የተሞሉ ነጣቂ ተኩላዎች ናቸው።

እኔስ ትንሽም ብትሆን የቤተክርስትያን መሰረታዊዋን ነገር ስለያዝኩ ቢያንስ ራሴን ማዳን ቻልኩ። ዛሬም ግን በየዋህነት የሚከተሉዋቸው ምስኪን እህቶቼ ያሳዝኑኛል። የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት እያሉ የገንዘብ ምንጩ ከማይታወቅ source በሚያገኙት ድንማ pick up እና drop off service በመስጠት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ምስኪን ሴቶችን ክህደታቸውን ያስጠናሉ።

ለበለጠ ማረጋገጫ ደግሞ Saint Michael's Ethiopian Orthodox church,dubai ብላችሁ በ FB አድራሻቸው ፓስቶቻቸውን ተመልከቱ።

ግ-ል-ፅ አድርገው መናፍቃን ሰዎችን ለማሳት የሚጠቀሙባቸውን ጥቅሶች

በዋናነት ፓስት ያደርጋሉ። መታለል ይብቃ ያየነውን አይተን ነው የምንጮኸው እባካችሁ ስሙ!!!

ትዝታ መዝገቡ ነኝ ከዱባይ!

እህታችን ለሰጠችው ምስክርነት ቃለህይወት ያሰማልን መንግስተ ሰማያትን ያውርስልን።

እንግዲህ የሚያስተውል ያስተውል!!!

ለሌሎች እንዲዳረስ SHARE እና LIKE እንዲያደርጉ በመድሐኒዓለም ስም እንጠይቃለን!

የመድሐኒዓለም ጥበቃ ፍቅርና ይቅርታ አይለየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር አሜን-ይቆየን።

ሻሎም!!!

Like · Solomon Tibebu

በአሁኑ ሰአት መነኩሴውም ቄሱም ሰባኪውም መናፍቅ ነው አትሸወዱ ምክነያቱም ቤተክርስቲያን አገለገልሁ እያለ ውስጥ ለውስጥ ግን ታድሶ መናፍቅ ነው ስልጣናቸውንም ጥለውታል እነሱ ጸልየው ሰውን ይመልሳሉ ያድናሉ ብላችሁ አትሸወዱ ምክነያቱም መጨረሻው ሰአት ነው ይልቅስ ጡአት ማታ ለአምላካችሁ ጸልዩ በጸሎት ንገሩት በድብቅ የሚደረገውን ያሚአውቅ እሱ ብቻ ነው ቤተክርስቲያን እንሰራለን እያሉ ባንድጎን ታድሶ መናፍቅ ሁነው እንደብድ ውሻ የገንዘብ ሱስ ይዞአቸው ቤተክርስቲያናችንን ግራ እያጋቧት ይገኛሉ ለማን ይነገራል ክርስቲያኖች እሱ ያመጣውን እሱ

እስከሚመልሰው ድረስ ለመዳኔዐለም ጸሎታችንን ልመናችንን ማስተላልፍ ነው የምንጠብቀው ከሱ ብቻ ነው አምላክ ለውነት በል ተሎ ድረስልን በዚሕ በንስቋላው ሰውነታችን ስምሕን እንጠራሐለን እና የጠፉትን መልስ ወደንስሐ የምንመለስበትን መንገድ ፍጠርልን እምነታችን ጠንካራ እንዲሆን መንፈስ ቅዱስን አጽናኝ ላክልን አሜን አሜን በሉ

Like · Birhan Tsige

ቃለ ህይወት ያሰማልን እህታችን።ጆሮ ያለው ቢኖር መስማትን ይስማ፣የማያስተዉል ህዝብ ይገለበጣል።እግዚአብሄር ከመናፍቃን ንክሻ፣ከከለባት ጉባኤ ይጠብቀን አሜን።

Like · Abraham Abrish Yeyesus

ጉረኛ ነገር ነሽ..ቁጭ አድርገው ትምህርተ ድሂንን ቢያስተምሩሽ ኖሮ ከጣኦት አምልኮሽ ትላቀቂ ነበር ከመበርገግ ማስተዋል መረጋጋት ጥሩ ነው ወሬ ይዘሽ ለመሮጥ አትቸኩይ እነ መጋቢ ሀዲስ እነ ትዝታው እነ ዘርፊቱ እነ ምርትነሽ ህያው ጌታን ከናንተ በተሻለና እጅግ በበለጠ ጌታን አላውቅ ብለው ነው..እንደ ክፉ አድራጊወች የሚቆጠሩት???? ከርሳም ቀሳውስቶቻችሁና ጳጳሶቻችሁ የጌታ ቃል የሆነውን ቅዱሱን መፅሀፍ ከማስተማር ይልቅ የዘረ ያእቆብን ተረት ተረት እያነበቡ አሳድገዋችሁ ነው ዛሬ እውነተኛው የጌታ ቃል ኑፋቄ መስሎ ሚታያችሁ...:: እህን ጊዜ የለመድሻትን ያችን የዘረ ያእቆብን የማርያም ታምር ብለው ቢያነቡልሽ ኖሮ ወንጌል የተማርሽ ነበር የሚመስልሽ...አመዳም ሁላ ማርያም እኮ ወንጌላዊት ናት

Like · Kesis Abeb Dires

ከሰማይ የወረደዉ ቃል የተዋሐደው የድንግል ማርያምን ሥጋ መሆኑን አትዘንጉት በቀራንዮ አደባባይ የተሰቀለው ፣ወደመቃብር የወረደው ፣ በ 3 ኛ ቀን የተነሣው፣ ወደሰማይ ያረገው ና በክብር ለፍርድ የሚመጣው ሁሉንም እደየ ሥራው የሚከፍለው አምላክ የድንግል ማርያምን ሥጋ እደተዋሐደ መሆኑን አትዘንጉ ። እሞነቱን ፣ጥምቀቱን ፣ሥጋውና ደሙን መታጠቢያ ንስሐውን የሰጠን የድህነታች መነሻና መድረሻ የድንግል ማርያም ሥጋ መሆኑን አትርሱ አሜን ።

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት መልስ አላት

ከዳንኤል ኪንግ

በአዲስ አበባ ሁለተኛ በሀገር አቀፍ ሶስተኛ የሆነው ይፋዊ ጸረ ተሃድሶ ጉባኤ በቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን 27/ ለተሃድሶ ሚስማማ ስም ይፋ በማድረግ ቀጠለ

"ሐራጥቃ" ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ ማለት ነው "

በመብራት ምክንያት ከመክፈቻ ሰአቱ የዘገየው ፕሮግራም ፀሎተ ሃይማኖት እና ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ በማድረስ ተጀምሮዋል የመጀመርያው ክፍል ትምህርትም መመህረ ወንጌል እና የቤተክርስቲያኗ የህግ ባለሞያ በሆኑት በመምህር አስቻለው ተሰጥቶዋል ።

"ሐራጥቃ" በቲኦሎጂ ትምህርት ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ ማለት ነው።

የቤተክርስቲያኗ ሊቃውንት ይህን ስም እንድጠቀምበት ነግረውኛል" ያሉት

መምህር አስቻለው " ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ" የአባቶቻችንን አምላክ እግዚአብሄር ይመስገን "በሚለው ቃል ጉባኤውን ጀምረዋል።

ይህን ጉባኤ ምናደርገው የሃይማኖት ጉዳይ ስለሆነብን ተገደን ነው ያሉት መምህሩ "ሐራጥቃዎቹ" ተመልሰው ከጉኔ አብረውኝ ቢሰብኩ ደስታዬ ነው ሲሉ ክርስቲያናዊ ቃላቸውን ሰጥተዋል። ካልተመለሱ ግን የቤተክርስቲያኗ ጫንቃ እንሱን መቸከም አይችልም ከዚ በላይ እያነባን ከቤተክርስቲያን ልንለያቸው ግድ ነው ብለዋል። ስለ ቅዱሳን አማላጅነት ሐራጥቃዎቹ ተሳስተዋል ብለው ማስረጃ ከመጸሃፍ ቅዱስ ፍንትው አድርገው የምእመኑን ልብ አረስርሰዋል።

ሁለተኛው ትምህርት የዘመኑ የቤተክርስቲያኗ ጠበቃ የሆኑት ለፕሮቴስታንት ለአህዛብ መልስ በመስጠት ሚታወቁት በቤተክርስቲያን ጉዳይ ማይደራደሩት መምህር ምህረተ አብ ለሐራ ጥቃዎች "ወላዲተ አምላክ "ን በተመለከተ ላነሱት ምንፍቅና የማያዳግም መልስ ሰጥተዋል።

(የመምህራችንን ትምህርት በተከታታይ ለማድረስ እሞክራለው)

መምህር ምህረተ አብ በቱፊት ከአባቶቻችን እንደወረስነው መናፍቃን ሲነሱ የንስሃ የመመለሻ

ቤተክርስቲያን "አረ ሲኖዶስ የለም እንዴ " እሲኪባል ድረስ ግዜ ሰጥታለች ብለው አስረድተዋል ። ክርስትና መጀመር ሳይሆን መጨረስ ነው ያሉት መምህሩ ይሁዳ ሃዋርያ ሣጥናኤል የመላእክት አለቃ ንስጥሮስ ጳጳስ ሆነው ጀምረዋል መጨረሻቸው አላማረም እንጂ ሲሉ ለዘመኑ ሃራጣቃዎች መንቂያ ደውል ደውለዋል።

"በእንተ ስማ ለማርያም " ብለው በስምዋ በልተው በስምዋ ተምረው በስምዋ መምህር ተብለው እመብርሃንን በመሳደብ ለወደቁ ሁሉ "ድንግል ማርያምን ማንም ሊያከብራት አይችልም ሊቀድሳት አይችልም እኛ እስዋን በማክበር እንከብር ዘንድ ነው እንጂ እግዚአብሔር አንዴ አክብሮዋታል ከሱ በላይ አናከብራትም ልናዋርዳትም አንችልም እግዚአብሔር ያከበረው ማንም አያዋርደውም ራሱ ይዋረዳል እንጂ"

ሲሉ አጽኖት ሰጥተው ተናግረዋል።

ጥልቅ የሆነ የሚስጥረ ስጋዌ ትምህርት ከነገረ ማርያም ጋር አያይዘው በስነ መለኮት ትምህርት የሶስት ሴሚስተር ትምህርት ሚሆን አስተምረዋ።

በፕሮግራሙ ቋንቋዬነሽን ጨምሮ የመምህር ምህረተ አብ ወንድም የሆኑት በሚስጥራዊው ቡድን 2 ሲዲ ምክንያት ስለ እምነታቸው በእስር ቤት የተንገላቱት መምህርና ዘማሪ ኤርሚያስ ጨምሮ ዘማርያን ተገኝተዋል ።የአራት ጉባኤ መምህር የሆኑት በማህበረ ቅዱሳን ቲቪ ከሊቃውንት ጋር መልስ በመስጠት ሚታወቁት መጋቢ ሃዲስ ሚስጥረ ሥላሴን ጨምሮ ሌሎች መምህራን በቦታው ተገኝተው ሲያመሰግኑ ሲዘምሩ አምሽተዋል

በተከታታይ የጉባኤውንእንድምታ እስክናስዳስሳቹ በዚ ይብቃን።

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት መልስ አላት

28/ ምንፍቅናና አመጣጡ።

በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

መናፍቅ “ናፈቀ” ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲኾን የቋንቋው ሊቅ ትርጕሙን ሲፈቱት የሚጠራጠር፣ የሚያጠራጥር፣ አጠራጣሪ፣ ሃይማኖቱ ግማሽ የኾነ፤ ምሉእና ፍጹም ትክክል ያይደለ፤ መንፈቁን አምኖ መንፈቁን የሚክድ ማለት ነው። በጽርዕ ቋንቋ ኤሬቲክ፤ በእንግሊዘኛ ሄሬቲክ፤ በግእዝ ደግሞ “ሐራ ጥቃ” ይባላል፤ ትርጕሙን በቋንቋው የተራቀቁት ሊቅ በመዝገበ ቃላታቸው ሲገልጡት መናፍቅ፣ ጠዋየ ሃይማኖት፣ ባህሉና ትርጓሜው ከመጽሐፍ ከንባብ የማይገጥም፤ መጻሕፍት ነው ያሉትን፤ አይደለም፤ አይደለም ያሉትን ነው የሚል የርሱን ሐሳብ ብቻ የሚከተል፤ ነገሩ ካልተማሩት የሚስማማ ከሊቃውንት የማይስማማ ብለውታል።

ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል ምዕ 8፡44 “እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና” እንዳለ፤ የመጀመሪያው መናፍቅ ዲያብሎስ ሲኾን በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ኅልውና በመጠራጠር፤ ሌሎቹን ነገደ መላእክት ለማጠራጠር ሞክሮ፤ በጥቂቶቹ ተሳክቶለታል፤ ዛሬም እንክርዳዱን የዘራበት የርሱ መንፈስ ያደረበት ሰው አስቀድሞ ነገረ እግዚአብሔርን አጠራጥሮ ካስካደው በኋላ፤ ሌሎችን ለማስካድ መሣሪያ ያደርገዋል፤ አዳምንና ሔዋንን ከገነት ለማስወጣት በእባብ ሰውነት እንዳደረና እንደተሳካለት።

በመጨረሻም ዲያብሎስ በሰማይ እያለ ልዑል እግዚአብሔርንና ነገደ መላእክትን ለመስደብ ጀመረ፤ ዛሬም ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያንን

ትምህርት ላስካዳቸው መናፍቃን የስድብ መንፈስ በውስጣቸው ልኮ ሥልጣን ያላቸውን እንዲንቁ እግዚአብሔር ያከበራቸውን እንዲያቃልሉና እንዲሳደቡ የስድብ መንፈስን ይሰጣቸዋል ይህንንም ዮሐንስ በራእዩ በምዕ 13፡4-7 ላይ “ለዘንዶውም ሰገዱለት÷ ለአውሬው ሥልጣንን ሰጥቶታልና፤ ለአውሬውም። አውሬውን ማን ይመስለዋል÷ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል? እያሉ ሰገዱለት፤ ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው÷ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው፤ እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ፤ ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው÷ በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው” ይላል።

ሆኖም ግን ይህ ጠላት ዲያብሎስ ሲሳደብ ቅዱሳን መላእክት ዝም ብለው አላዩትም ይልቁኑ ከቅዱስ ሚካኤል ጋር በመኾን ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው አሳቹን ዘንዶ ተፋልመው፣ ተዋግተው ወደ ጥልቁ እንዲወረወር አደረጉት እንጂ (ራእ 13፡7-9) ይህ ለእኛ አብነት ነው፤ ዛሬም ከእውነተኛው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ትምህርት ፈቀቅ ያለውን፤ ብንችል መምከር፣ መገሠጽ ሲገባ እንቢ ካለ ግን ሌላውን አካል በክሕደቱ መርዞ እንዳይጥል በውግዘት ቄርጦ መጣል ይገባል፤ ጌታችን እንኳ መናፍቁ ዲያብሎስ ሁለቴ ፈትኖት በሦስተኛው ገንዘብ ወርቅ እሰጥኻለኁ ብሎ በአምልኮት ቢመጣበት “ኺድ አንተ ሰይጣን” በማለት ነበር የመጨረሻ ቃል ተናግሮት የለ! (ማቴ 4፡10)። ቅዱስ ጳውሎስም በገላ 1፡7 ላይ “የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ

አንዳንዶች አሉ እንጂ፤ ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን፤ አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" በማለት በአጽንዖት ተናግሯል።

በዘመነ ሊቃውንት የነበረው የጥንቱ መናፍቅነት እና ያሁኑን ስናስተያየው የሰማይና የምድር ያህል ሰፊ ርቀት አለው፤ አበው በብሂላቸው "ቀን አይጥለው፣ ጠጅ አያሰክረው፣ የቀለም ሠረገላ አያሰነካክለው የለም" እንዲሉ የጥንቶቹ መናፍቃን ከስመ ጥር መምህራን የተማሩ፣ ብዙ መጻሕፍት የጻፉ እጅግ ከመማራቸው የተነሣ ከመጠን ከተጻፈው አልፈው በመመራመር ተጠራጥረው የካዱ ሲሆኑ፤ የአሁኑ ግን ከቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ቤት በፍጹም ያልዋሉ፣ ምስጢር ያላደላደሉ፤ አንብበው የማይተረጉሙ፤ በሚገርም መልኩ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ!!! እንዲሉ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን ለማንቋሸሽ የማያውቁትን ግእዝ ሲጠቅሱ እንኳ የማያፍሩ፤ በጥራዝ ነጠቅ ዕውቀት ብቻ የሚመላለሱ፣ የቤተ ክርስቲያን የሴቶችና የወንዶችን መግቢያ እንኳ ያለዩ መሆናቸውን ስናይ እንኳን መናፍቅ ሊባሉ ቀርቶ እንደው ለአቅመ መናፍቅነት (ለመጠራጠር ደረጃ) ራሱ ደርሰዋል ወይ ሲባል፤ በፍጹም አልደረሱም ቢያንስ ለመጠራጠር እኮ ማንበብ፣ መመራመር፣ መፈላሰፍ ያስፈልጋል፤ እኮ!!!

ጌታችን በወንጌል "ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው...በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤ ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም፥ የሌሎችን ድምፅ

አያውቁምና” በማለት እንዳስተማረ፤ በዘመነ ሊቃውንት የነበሩ ምእመናንም እረኞቻቸውን ስለሚያውቁ በድፍረት ሳይማር ላስተምራችሁ የሚላቸው አንድም አልነበረምና ከዚህ ዘመን ጋር ሊነጻጸሩ አይችሉም፤ ምክንያቱም እረኞቻቸውንና የቀናውን ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮን ጠንቅቀው ያውቁ ነበርና በስሜት ዝም ብለው የሚነዱ አልነበሩም፤ ጌታችን እኮ ሐዋርያትን ለስብከተ ወንጌል ከመስደዱ በፊት 3 ዓመት ከ 3 ወር በቃልም በተግባርም ካስተማረ በኋላ ነበር “ሑሩ ወመሐሩ” (ሒዱ አስተምሩ) ያላቸው፤ እንኳን በመንፈሳዊው ዓለም ቀርቶ በዓለማዊው ጥበብ እንኳ ሰው በድፍረት ስለማያቀው ነገር መለፍለፍ አይችልም፤ በሠለጠነው ዓለም አንድ ሰው ሌክቸር ከማድረጉ በፊት የተማረበት ተቋም፤ የትምህርት ደረጃው ከቀረበ በኋላ ነው መልእክቱን (ጥናቱን) በሰዎች ፊት የሚያቀርበው፤ በእኛ ጊዜ ግን ጸጋ በሚል ሽፋን ሰው ስለማያውቀው በድፍረት ሲናገር ብዙዎች ዐውቀው ሳይሆን በስሜት ብቻ ሲያዳምጡ ሲታይ፤ በዘመነ ሊቃውንት የነበሩ በዐፀደ ነፍስ ሕያው የሆኑት አበው እና ክቡራን ምእመናን ለጥቂት ቀናት ከሞት ተነሥተው ዐብረውን ሆነው ቢያዩን ምን ይሉን ይሆን!!! ።

እስቲ የሦስቱን ዓለም ዐቀፍ ጉባኤያትን እንኳ ብንዳስስ በኒቅያ ጉባኤ የተወገዘው ዲያቆኑ አርዮስ በታዋቂዎች ሳይሆን በዐዋቂዎች ሊቃውንት በተመላው በእስክንድርያ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት ከእስክንድሮስ፣ ከአኪላስ ጋር ሆኖ ከተፈጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስ ሥር ሲማር የነበረ ነበረ፤ በኋላ ግን ከምርምር ብዛት መምህሩ ያላስተማረውን፤ መጻሕፍት ያላሉትን ዐዲስ ክሕደት ይዞ ብቅ ሲል፤ መጀመሪያ ጓደኞቹ ገሠጹት፤ በኋላም

መምህሩ ጴጥሮስ አስጠርቶ መከረው፤ እንቢ ቢል ግን አወገዘው፤ በኋላም በ325 ዓ.ም. በኒቅያ 318ቱ ሊቃውንት በተገኙበት በእለእስክንድሮስ አፈ ጉባኤነት፤ በነቅዱስ አትናቴዎስ የነገረ መለኮት ተንታኝነት፤ በቃልም በመጽሐፍም ረትተውት አውግዘው “ጸሎተ ሃይማኖትን” አርቅቀዋል።

በ381 ዓ.ም በተካኼደው ኹለተኛው ዓለም ዐቀፍ ጉባኤ ክሕደቱ ወደ ጳጳስ ደረጃ እያደገ ኼዶ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት የነበረው መቅዶንዮስ “ሎቱ ስብሐት” መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ ነው የሚል ዐዲስ ክሕደትን ቢያስተምርም፤ 150 ሊቃውንት በቍስጥንጥንያ ተሰብስበው መናፍቁን ጳጳስ ረትተው አውግዘው ለይተውታል።

በ431 ዓ.ም ሦስተኛው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ ደግሞ ክሕደቱ እጅጉን አድጎ አነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በተማሩባት በአንጾኪያ የነገረ እግዚአብሔር ትምህርት ቤት ከነድያድርስ ተምሮ በኋላ የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ የነበረው መናፍቁ ፓትርያርክ ንስጥሮስ የኹለት አካልና ባሕርይ የክሕደት ትምህርትንና በእመቤታችን ወላዲተ አምላክነት ላይ ተቃውሞን ቢያመጣ፤ 200ው ሊቃውንት በኤፌሶን ተሰብስበው እነ ቅዱስ ቄርሎስ የተዋሕዶን ነገር በቃል በመጽሐፍ አመስጥረው ንስጥሮስን በ12ት ቃለ ግዝት ለይተውታል።

በ451 ዓ.ም. ላይ ደግሞ የሮሜው ልዮን ንጉሠ መርቅያንንና ንግሥት ብርክልያን ይዞ ከቅዱስ ቄርሎስ አንድ አካል፤ ከመናፍቁ ንስጥሮስ ኹለት ባሕርይ የሚለውን ወስዶ በኬልቄዶን ስድስት መቶ ሠላሳ ስድስት ሰዎችን ይዞ ተሰበሰበ።

የእስክንድርያው ጳጳስ ቅዱስ ዲዮስቆሮስም ይኽ የክሕደት መልእክት

የያዘውን የልዮንን ደብዳቤ በመቅደድ ልዮንን “የአባቶቼን ሃይማኖት ብትከተል በእውነት አባቴ ነህ፤ ከሐዋርያት ጀምራ እስካሁን ድረስ ቀንታ የመጣችውን እምነት ብትለውጥ ግን አባቴ አይደለህም፤ ሳጥናኤል ከመካዱ በፊት ከሊቃነ መላእክት እንደ አንዱ ይከበር ነበር፤ ከካደ በኋላ ግን ክብሩ ሁሉ ተገፍፎ ወደ እንጦርጦስ ወድቋል” በማለት የክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ አምልቶ አስፍቶ ሲናገር፤ ከትምህርቱ ታላቅነት የተነሣ ከተሰበሰቡት ውስጥ ሊከራከረው የደፈረ አንድ ስንኳ አልነበረም።

“ወተምዑ ላእሌሁ ንጉሥ ወንግሥት ወአዘዙ ይዝብጥዎ ወበእንተዝ ዘበጥዎ ወነጸዩ ጽሕሞ ወሰበሩ አስናኒሁ ወከመዝ ገብሩ ቦቱ” ይላል ንጉሡና ንግሥቲቱ ግን በርሱ ተቈጥተው እንዲደበደብ አዝዘው ስለዚኽም ደብድበው ጽሕሙን በመንጨት ጥርሱን ሰብረውታል። ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ግን የተነጨውን ጢሙን የወለቁትን ጥርሶቹን ሰብስቦ “ናሁ ዝንቱ ፍሬ ሃይማኖት ርትዕት” (እነሆ የቀናች ሃይማኖት ፍሬ ይኽ ነው) ብሏቸዋል። ከዚያም አባቶቻችን ሐዋርያት ካስተማሩት ቅዱሳን አበው በሦስቱ ጉባኤያት ከወሰኑት የሚወጡ ኹሉ የተለዩ የተወገዙ እንደኾኑ በደብዳቤው ግርጌ ላይ ጽፎታል።

ሊቁ አርከ ሥሉስም ይኽንን የቅዱስ ዲዮስቆሮስን ተጋድሎ፦-

“ሰላም ለዲዮስቆሮስ ሃይማኖተ ንጉሥ ዘተሣለቀ
ተዋሕዶተ አምላክ ወሰብእ አመ ለክልኤ ነፈቀ
ያስተጻንዕ ህየ እለ ሀለዉ ደቂቀ
ዘተነጽየ እምነ ጽሕሙ ወእምአስናኒሁ ዘወድቀ
ፍሬ ሃይማኖቱ ፈነወ ብሔረ ርጉቀ”

(ሰው የኾነ የአምላክን ተዋሕዶ ለኹለት በከፈለ ጊዜ በንጉሥ ሃይማኖት ላይ የተሣለቀ ለኾነ ለዲዮስቆሮስ ሰላምታ ይገባልኟ በዚያ ያሉትን ልጆች ያጽናና ዘንድ ከወደቁ ጥርሶቹ ከተነጨ ጽሕሙ የሃይማኖት ፍሬ አድርጎ ወደ ሩቅ ሀገር ላከ) በማለት አመስግኖታል።

በመኾኑም ሐዋርያው ይሁዳ በምዕ 1 ላይ “ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝኟ ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልናኟ ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ... እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ደግሞ እያለሙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ ጌትነትንም ይጥላሉ ሥልጣን ያላቸውንም ይሳደባሉኟ...እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ...እነዚህ ከእናንተ ጋር ሲጋበዙ በፍቅር ግብዣችሁ እንደ እድፍ ናቸውኟ እንደ እረኞች ያለ ፍርሃት ራሳቸውን ይጠብቃሉኟ በነፋስ የተወሰዱ ውኃ የሌለባቸው ደመናዎች፥ ፍሬ የማያፈሩ ሁለት ጊዜ የሞቱ ከነሥራቸው የተነቀሉ በበጋ የደረቁ ዛፎች የገዛ ነውራቸውን አረፋ እየደፈቁ ጨካኝ የባሕር ማዕበል፥ ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው” በማለት እንደመከረን ሾልከው ከገቡ ውሃ ከሌለባቸው ባዶ የተራቆቱ ደመናዎች እንድንጠበቅ ያስፈልጋል።

ልዑል እግዚአብሔር በከበረ ደሙ የመሠረታት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ይጠብቅልን።

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት መልስ አላት

28/ "ኦርቶዶክስ መልስ ካላት እኛም ጥያቄ አለን" በሚል ርዕስ በተሐድሶ መናፍቃን በ 2004 ዓ.ም ግንቦት 15 በቅዱስ ሲኖዶስ የተወገዙት እነ ጽጌ ስጦታው CD ማዘጋጀታቸው ይታወሳል። በዚህ CD የጠየቁት አንዱ ጥያቄ በ 81 መጽሐፍ ቅዱስ ላይ "ቃየን አቤልን በሴት ቀንቶ ገደለው" የሚለውን የሚተች ነበርና በውኑ ትችታቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር ሲመዘን ሚዛን ይደፋልን?

+++ "ቃየን አቤልን በሴት ቀንቶ ገደለው" ማለት ትክክል አይደለምን? ነጩን ማጥቆር; ጣፋጩን ማምረር የሚወዱ የተሐድሶ መናፍቃን የሚያጠራጥሩበት ጥቅስ ነው:: "ወንድሙ የሚወድደው መስሎት በየዋህነት የተከተለውን ወንድሙን በገደለው በቃየን መንገድ አትሂድ; እርሱም በሴት ቀንቶ ወንድሙን ገደለው::" |1ኛ.መቃ.23:1-2; የ 2000 ዓ.ም ዕትም| የሚለውን በመጥቀስ ሳይሆን ለእኩይ ግብራቸው በመንቀስ ይተቻሉ:: አርሲሳኑ|መናፍቃኑ| እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡት ሐዋርያው ዮሐንስም ቃየን አቤልን ስለገደለበት ሲናገር "ቃየን ስለምን ወንድሙን ገደለው? የእርሱ ስራ ክፉ የወንድሙ ጽድቅ ስለነበረ ነው::" 1ኛ.ዮሐ.3:12 በማለት በልቡ ክፉትና በአቤል መልካምነት የተነሳ እንጂ እንዴት በሴት ምክንያት ነው የገደለው ይባላል? ይላሉ:: መልስ:- አቤልና ቃየን ከአዳምና ከሔዋን ተለይተው ብቻቸውን ለምን መሥዋዕት አቀረቡ? እግዚአብሔር የሚመለከው በፍጥረት ሁሉ ነው:: ታዲያ አዳምና ሔዋን ስለምን መሥዋዕት አላቀረቡም? እነዚህን ጥያቄዎች የሚመልሱልን መጽሐፈ መቃብያንና መጽሐፈ ኩፋሌ እንዲሁም አዋልድ መጻሕፍት

ናቸው:: ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ምሉዕ ሊሆኑ አይችሉም ማለት ነው:: በዘፍ.4:17 ላይ "ቃየንም ሚስቱን አወቀ; ጸነሰችም ሄኖህንም ወለደች::" ይላል:: ይህች ሴት ከየት መጣች? ቀድሞ አዳምና ሔዋን የወለዱት ቃየንና አቤል ብቻ መሆናቸውን ገልጾ አልነበረምን? ይህች ሴት ከእነርሱ ጋር ከነበረች እንደ አቤልና እንደ ቃየን ለምን መሥዋዕት አላቀረበችም? የሚል ጥያቄ ያስነሳል:: አሁን ለምን ቃየን አቤልን በሴት ቀንቶ ገደለው ተብሎ የተገለጸውን እንመልከት:: መጽሐፈ ኩፋሌ ሲገልጽ አባታቸው አዳም ከቃየንና ከአቤል ጋር ሌሎች ሁለት ሴቶች እንደ ተወለዱ ይናገራል:: "ሔዋንም በአምስተኛው ሱባኤ አዋንን ወለደቻት; አዳምም በስድስተኛው ሱባኤ ልዋን ወለዳት::" |ኩፋ.5:8| ይላል:: እነዚህ ሴቶች ልጆች ከወንዶች ጋር መንትዮች ሆነው እንደተወለዱ የውዳሴና የቅዳሴ ማርያም አንድምታ እንዲሁም ገድለ አዳምም|First Book of Adam and Eve Prologue; P.1| ይገልጻል:: መጽሐፈ ቀሌሜንጦስ ዘሮም እንዲህ ይላል:- "አዳምና ሔዋን ከደብር ቅዱስ ወርደው ከሱ በታች ተቀመጡ:: በዚሁ አዳም ሔዋንን ተገናኘት:: እሷም ፀነሰች:: የመውለጃዋ ጊዜም ደረሰ:: ቃየልንና ሉድንም መንታዎች ወለደች:: ዳግመኛም ሔዋን ፀነሰች:: የመውለጃዋም ጊዜ ደረሰ:: መንታዎቹን አቤልንና አቅሌምያንም ወለደች:: እነዚህ ሁለት ወንዶችና ሁለት ሴቶች የአዳም ልጆች አድገው:: ለጋብቻ ደረሱ:: አዳም ይህን ተመልክቶ ሔዋንን እነሆ እግዚአብሔር እነዚህ ልጆቻችንን አሳደጋቸው:: ስለዚህ ቃየል የአቤልን እህት አቅሌምያን ያግባት:: አቤል ደግሞ የቃየልን እህት ሉድን ያግባት አላት:: አዳምና ሔዋን በዚሁ ተስማሙ::" ይላል::

[መጽሐፈ ቀሌሜንጦስ; ምዕራፍ አንድ]. በዚህም ምክንያት በአንድነት ያደጉት መንትያ የሆኑት ማለት ከቃየን ጋር አብራ የምትውል|የተወለደች| ና ከአቤል ጋር አብራ የምትውል|የተወለደች| በአንድነት እንደማይጋቡ አዳም በልቦናው ስላወቀና እግዚአብሔርም ስለ ገለጸለት ሁለቱም ሴቶች ልጆች ተቀያይረው እንዲጋቡ ፈቀደ:: ገድለ አዳምም ስለዚህ ሁናቴ ሲገልጽ Then Adam said to her|Eve|, "We will join Abel's sister in marriage to Cain, the Cain's sister to Abel."|Second Book of Adam and Eve; Chapter L XXVIII|. ይላል:: ነገር ግን ቃየን በአባቱ ሃሳብ ስላልተስማማና ስላዘነ አዳም ወዲያውኑ ያደረገው አቤልና ቃየን በእግዚአብሔር ፊት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ነገራቸው:: ይህን ያደረገበት ምክንያት ከአቤል ጋር ያልተወለደችውን መንትያ እግዚአብሔር መሥዋዕቱን ከተቀበለው ከእርሷ ጋር እንዲጋባ ነበር:: "But when Adam saw that the older brother hated the younger, he endeavor f to soften their hearts, and said to Cain, "O my son, take of the fruits of your sowing and make an offering to God, so that He might forgive you for your wickedness and sin." He said also to Abel, "Take son of your sowing and make an offering and bring it to God, so that He might forgive you for your wickedness and sin." |

Second Book of Adam and Eve; Chapter LXVII|. ቃየን ግን ቀድሞውንም በዚህ ውሳኔ አዝኖ ነበርና ይበልጥ ክፋት ሠራ:: ይህም ለእግዚአብሔር ከፍሬው እንክርዳድ ያለበትን መሥዋዕት ሊቃጠል ነው እንጂ:: እግዚአብሔር ንስሐ እንዲገባ ምክር መከረው:: "ለምንስ ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ? መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚያበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅዋ ታደባለች; ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው:: አንተ ግን በእርሷ ንገስባት::" |ዘፍ.4:6-7| ያለው:: ይህም ማለት የአባትህ ሃሳብ የእኔ ነውና ተቀበለው በአባትህ ሃሳብ አትናደድ; አትዘን; የአባትህ ሃሳብ የእኔ ነውና:: ለዚህ ነው የአቤልን መሥዋዕት የተቀበልኩት ሲል ነው:: God would accept Abel's offering. Then God looked at Abel and accepted his offering. ... because of his good heart and pure body. |Second Book of Adam and Eve; Chapter LXVII|. ቃየን ወንድሙን ለመግደል ያነሳሳው የመጀመሪያው ምክንያት በሴት መሆኑን እንረዳለን ማለት ነው:: ለዚህም ነው ገድለ አዳም Cain becomes jealous of Abel because of his sisters. |Chapter LXXVI| ያለው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት ከተቀበለ የአባቱ የአዳም ፈቃድ በማራራቅ ሊያጋባቸው እንደወሰነ ስላወቀ ይህችን የሚፈልጋት ሴት ለማግባት ደግሞ ወንድሙን ለመግደል በቅናት ተነሳ:: ገድለ አዳምም Jealousy overcomes Cain|Chapter LXXVIII| ይላል:: |ዘፍ.4:17; ኩፋ.5:8|. በ 1ኛ.ዮሐ.3:12 ላይ የተገለጸውን

ከመቃብያንና ከዘፍጥረት ጋር ሃሳባቸው የተጋጨ አይደለም:: የአቤል ሥራው ወይም ጽድቁ ምን ነበር? የቃየንስ ክፉ ሥራ ምን ነበር? ብለን ብንጠይቅ የመጀመሪያው ምክንያት መሥዋዕት ማቅረባቸው ሊሆን አይችልም:: ነገር ግን ቃየን በአቤል በመቅናቱ ነው:: የቀናበት ምክንያት ስንመለከት ደግሞ የመጀመሪያው የሚወዳት ሴቷን አቤል እንደሚያገባት ሲያውቅና የእርሱ እንደማትሆን ሲረዳ በቅናት ወንድሙን ገድሎታል:: ሐሰት በ 4 ደረጃዎች እንደሚሰራ ማለት ነው:: ይህም በመጀመሪያ ከልብ ይጸነሳል; ከዚያም በገጽታ; ከዚያም በቃላት ወይም በአንደበት በመናገር በመጨረሻም በተግባር እንደምንፈጽመው ማለት ነው:: ልክ እንደዚህ ሁሉ መጽሐፈ መቃብያን የመጀመሪያውን ምክንያት የሆነውን በሴት እንደቀና ገለጸው; ቀጥሎ ያለው ደግሞ በኦሪት እንደተገለጸው በመሥዋዕቱ ምክንያት እንደሆነ ገልጾታል:: ሐዋርያው ዮሐንስ ደግሞ የሦስተኛው የሆነውን የገደለበትን ምክንያትና ውጤቱን ጽፎታል:: ከዚህም የምንረዳው በተለያየ ክፍሎች የአቤልና የቃየንን ጉዳይ ተካፍለው እንደጻፉት ነው:: እንዲህ ካልሆነማ ቃየን አቤልን የገደለበት ምክንያት በመሥዋዕቱ ነው? ወይስ ክፉ ስራ ስለሠራ ነው? ክፉ ሥራ ተብሎ የተገለጸው ምን ይሆን? ታዲያ መጽሐፈ መቃብያን የመጀመሪያው ምክንያት ወስዶ ቢጽፈው ስህተቱ ምኑ ላይ ነው???

29/ ማንቀላፋቱ ይበቃል! !

በቤተ ክርስቲያናችን ላይ

ምን እየተካሔደ ነው? ?

ጥንታዊቷንና ታሪካዊቷን ቤተ ክርስቲያን ለማውደም የተነሳው የሀራ ጥቃ ተሐድሶ ፕሮቴስታንታዊ ቡድን ሰርጎ በመግባት ጥቂት ለጥቅም የተገዙ አገልጋይ መሳይ ተኩላዎችን በማሰማራት በቤተ ክርስቲያን ዶግማ ቀኖናና ትዉፊት ያልጠበቀ የሀሰት ትምህርት በአውደ ምህረትና በሚድያ በማስተላለፍ ህዝበ ክርስቲያንን ከሃይማኖት በማስወጣት ብዙ ነፍሳትን እያጠፉ ይገኛል

ይህ በእንዲህ እንዳለ አስቀድሞ ወንጌልን ከአባቶቹ በሚገባ የተማረው የተዋህዶ ልጅ የመናፍቃን ኮፒ የሆነውን የተሳሳተ አስተምህሮ እጅ እጅ የሚል የተበላሸ ልፈፋና ጩኸት አልሰማም አላደምጥም በማለት ከመቼውም ጊዜ በላይ ለሃይማኖቱ ከአገልጋዩ በተሻለ መልኩ ዘብ ቆሟል ለምድ የለበሱ ተኩላዎች በበረቱ ዘልቀው መግባታቸውን በመረዳት ከአውደ ምህረት እስከ ማስወረድ የአጥፊዎች ሚድያ ቤተ ክርስቲያንን የማይወክሉ መሆናቸውን በመግለጽ ከፍተኛ ተቃውሞ በማንሳት ህዝቡ ቤተ ክትስቲያኑን በመጠበቅ ላይ ይገኛል

ወንጌልን በፖሊስ

ወይስ በህዝብ ፈቃድ ??

ህዝቡ ከመቼውም በላይ አንቅሮ የተፋቸው ጠንቅቆ ያወቃቸው ተኩላዎች የሞት ሞት ፍልሚያ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ለዚህም በሙስናና በብልሹ አስተዳደር የተዘፈቁ የደብር አለቆችን በመጠቀም በአንዳንድ አጥቢያዎች

ላይ ወንጌልን የሚመስል ምንፍቅናቸውን በፖሊስ ወይም በፊደራል ኃይል ለመስበክ መከራ እያደረጉ ይገኛል ለስሙ በአግባቡ የማያውቁትን ኢየሱስን ካላስተዋወቅንህ የሚሉት ጥራዝ ነጠቆች አያስተውሉም ልቦናቸው ተደፍኗል የኛ ጌታ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስማ ወንጌልን በፈቃድ በፍቅር አስተማረ እንጂ መቼ አስገደደን? ታድያ ከየትኛው ኢየሱስ ተምረው ነው በአውደ ምህረት ዙሪያ ፊደራል አሳጥረው ካልሰበክን የሚሉት "ከፍሬያቸው ታውቋቸኋላችሁ " ተብሎ እንደ ተጻፈው

እንደ አይሁድ የሀሰት ትምህርትን ለህዝቡ በግድ ለመጋት ይሮጣሉ ነገር ግን አይሳካላቸውም

የፖሊስ አባላት ንጹሀን አገልጋዮችን ይገፋሉ

ለአጥፊዎች ከለላ ይሰጣሉ

መንጋውን ለመጠበቅ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ የሚወጡ ክህነታቸውን አገልግሎታቸውንና ሃይማኖታቸውን በገንዘብ ያልሸጡ አገልጋዮች ህዝቡ ከሀራ ጥቃ የተሀድሶ መናፍቃን እራሱን እንዲጠብቅ ሃይማኖቱን ፣ታሪኩን ፣ትዉፊቱን እንዲጠብቅ ግንዛቤ ለመስጠት ባዘጋጀው ጉባኤ ላይ ፕሮግራሙ ከግማሽ በላይ በተረጋጋና በዝማሬ ታጅቦ እየተላለፈ ባለበት ሰዓት የጸጥታ ኃይሎች በድገት ገብተው ማስቆማቸው አስገራሚ ክስተት ሲሆን ቤተ ክርስቲያናችን ወዴት እያመራችና በነማን ቁጥጥር ስር እየዋለች እንደሆነ የሚጠቁም ነው

"ንቁ በሃይማኖት ቁሙ "

1ኛ ቆ 16: 13

የተወደዳችሁ የክርስቶስ ቤተሰቦች ይህችን ሐዋርያዊት ክርስቶስ በደሙ

የዋጀት የመሰረታት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን አምላክነት ፈጣሪነት የእመቤታችንን፣ የቅዱሳንን፣የመላእክትን፣የፃድቃን ሰማእታትን አማላጅነት አምናና ተቀብላ የክርስቶስ የሆኑትን ሁሉ ያለጉድለት ይዛ ክርስቶስ የወደዳቸውን ወዳ ያከበራቸውን አክብራ ዝክር ምስክራቸውን እያሰበች ለዓለም ሁሉ ወንጌልን በመስበክ ለዘመናት የማይለወጥና የማይሻረውን እውነት ይዛ በፈተናዎች እያለፈች ዛሬ ላይ ደርሳለች ወደፊትም እስከ ዘለዓለም ትኖራለች

ከኛ ዘንድ ወጡ ዳሩ ግን ከኛ ወገን

አልነበሩም ከኛ ወገን ቢሆኑ ከኛ ጋር

ጸንተው በኖሩ ነበር 1 ኛ ዮ 2:19

በቅዱስ ቃሉ ተጽፎ የምናገኘው ኃለቃል ከበቂ በላይ ሀራ ጥቃዎችን ይገልጻል አገልጋይ መስለው ተደብቀው በቤተ ክርስቲያን ኖሩባት እንጂ ቀድሞም የኛ አይደሉም ነገር ግን ለጥቅማቸው እና ለዝናቸው ሲሉ በማያምኑበት ቤት ቆይተው የስጋዊ ጉልበታቸው የፈረጠመ መስሎ ሲሰማቸው ጡቷን አጥብታ ያሳደገቻቸውን እናት ቤተ ክርስቲያን ለመንከስና ለማርከስ አእምሮአቸው ሲያረጅባቸው ጥቅምና ትእቢት ልቦናቸውን ሲደፍንባቸው እናድስሽ በሚመስል የእናፍርስሽ ደባቸው ሊወጓት ተነሱ ዳሩ ግን የገሀነም ደጆች አይችሏትምና በየዘመኑ የተነሱትን ጠላቶቿን እንደ ዳጎን ሰባብራ በመጣል ዛሬ ላይ ደርሳለች ዛሬም የተነሱት ሀራ ጥቃ ተሀድሶዎችን አጥፍታ ለዘለዓለም ትኖራለች ቤተ ክትስቲያን የመንፈስ ቅዱስ እሳት አጥሯታልና የሚነኳት መናፍስት ሁሉ እንደ ቅጠል ይረግፋሉ !!!!

አምላካችን ሆይ ቤተ ክርስቲያንን "የሚጣሏትና ጠላቶቿን ፈጥነህ

አስገዛሰላት" እመቤታችን በረድኤት በቸርነት አትለየን ለእውነትና ለሃይማኖታቸው የተሰለፉትን አገልጋዮች ጽናትና ብርታት ይስጥል! !

ዲ/ን ይስሐቅ ዓለሙ

Mekrez Ze Tewahdo

ሰላም ለእናንተ ይኹን ውድ የመቅረዝ ተከታታዮች!!! በጥያቄና መልስ ዓምዳችን **30/** ለይሖዋ ምስክሮች የስሕተት ትምህርት ኦርቶዶክሳዊ ምላሽ መስጠት መዠመራችን ይታወቃል። እግዚአብሔር ቢፈቅድ ቀጣዩን ክፍል ነገ (ማግሰኞ) እናቀርብላችኋለን።

በክፍል አንድ (http://www.mekrezetewahdo.org/2014/09/blog-post_30.html) ምላሻችን የይሖዋ ምስክሮች የስሕተት ትምህርቶች ምን ምን እንደኾኑ፥ እንዲኹም መሠረታዊ የምሥጢረ ሥላሴን ትምህርት በመጠኑ ዐይተናል። በክፍል ኹለት ትምህርታችንም ከብሉይ እና ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በማመሳከር ምሥጢረ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እንደኾነ ተመልክተናል (http://www.mekrezetewahdo.org/2014/10/blog-post_15.html)። በክፍል ሦስት ደግሞ እግዚአብሔር በረዳን መጠን ከሐዋርያነ አበው ዝምረን እስከ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ምን ብለው

እንዳስተማሩ እንመለከታለን። ይኽም የምናደርግበት ምክንያት የይሖዋ ምስክሮች የሥላሴ ትምህርት የተወሰነው በ325 ዓ.ም. በጉባኤ ኒቅያ በንጉሥ ቈስጠንጢኖስ አስገዳጅነት ነው ስለሚሉ ነው። ስለዚኽ መልሱን መከታተል ያልዠመራችኁ ዠምራችኁ፤ የዠመራችኁ ደግሞ እየከለሳችኁ ጠብቁን። እግዚአብሔር በምግባር በሃይማኖት ያጽናን። አሜን!!!

መቅረዝ ዘተዋሕዶ

like . Mekrez Ze Tewahdo

“ከሦስት ግብራት የተነሣ ሥራውን ኹሉ ዕወቅ። ግብራትም የተባሉ ስሞች ናቸው። ይኸውም ፍጥረት ስም ዘመድ ነው። ሰው ተገዥ ሹም ይባላል። ሰው መባሉ ስለ ባሕርዩ መገኘት፥ ተገዥ መባሉም ስለ ተገዥነቱ ነው። ሹም (መጋቢ) መባሉም ስለ ተሾመ ነው። አኹን ደግሞ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ እንላለን። ግን አካላት ተቀድመው ተገኝተው እሊኽ ስሞች ኋላ የተጠሩባቸው አይደለም። ሰው ማለት ኋላ የወጣ ስም አይደለም። ባሕርዩ ነው እንጂ። ለሰዎች ኹሉ ከእነርሱ ለእያንዳንዱ የተለየ ስም አላቸውና። እነዚኽም አዳም፣ አብርሃም፣ ይሥሐቅ፣ ያዕቆብ ናቸው። የሰዎቹ ስማቸው ይኽ ነው። የእግዚአብሔር አቃኒም ስሞች ናቸው። ስሞችም አቃኒም ናቸው። አቃኒም ማለት በገጽ፣ በመልክ ፍጹማን የሚኾኑ ባለመለወጥም ጸንተው የሚኖሩ አካላት ማለት ነው። ባሕርዩ አንድ ሲኾን ሦስቱ አካላት ጸንተው በሚኖሩ በእነዚኽ ስሞች ይጠራሉ። ሦስት አካላት አንድ መለኮት ናቸው” ጐርጐርዮስ ገባሬ መንክራት

Like · Mekrez Ze Tewahdo

“ከሥላሴ ውጪ ምንም የማውቀው ነገር የለኝም። ሦስተኛው አካል

መንፈስ ቅዱስ ነው። ኹለተኛው አካል ወልድ ነው። በርሱ ቃልነትም አብ ፍጥረታትን ኹሉ ፈጠረ" ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ

Miko ZE Ethiopia

31/ ልሳን

በተለይ በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዬች እንደ ትልቅ ስጦታ የሚቆጥሩት ልሳንን ነው።

በ 1 ኛ ቆሮ.14 ÷ 12 እንዲህ ይላል፡-

በዓለም ምናልባት ቁጥር የሌለው የቋንቋ ዓይነት ይኖራል ቋንቋም የሌለው ሕዝብ የለም፤

እንግዲህ የቋንቋውን ፍች ባላውቅ ለሚናገረው እንግዳ እሆናለሁ፥ የሚናገረውም ለእኔ እንግዳ ይሆናል።

እንዲሁ ደግሞ እናንተ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ።

ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ።

በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደምንመለከተው ቤተክርስቲያንን ሊያንጽ የሚችል ከእግዚአብሔርም ክብር የሚያሰጥ ፍቅር እንጂ ልሳን አይደለም።

1 ኛ ቆሮ.13 ÷ 1-2 እንዲህ ይላል፡-

በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ።ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።

1ኛ ቆሮ. 13 ÷ 8

ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።

ልሳን ማለት ቋንቋ ማለት ነው።

በልሳን መናገር ማለት የሰው ልጆች በሚሰሙት በሚረዱት ቋንቋ መናገር ማለት ነው።

በአዲስ ልሳን መናገር ማለት በአዲስ ቋንቋ መናገር ማለት ነው።

ሐዋ.2÷4

በሁሉም፣መንፈስ፣ቅዱስ፣ሞላባቸው፥መንፈስም፣ይናገሩ፣ዘንድ፣እንደ፣ሰጣቸው፣

በሌላ፣ልሳኖች፣ይናገሩ፣ጀመር።

ማር.16÷17-18

ያመኑትንም፣እነዚህ፣ምልክቶች፣ይከተሏቸዋል፤በስሜ፣

አጋንንትን፣ያወጣሉ፤በዐዲስ፣ቋንቋ፣ይናገራሉ፤እባቦችን፣ይይዛሉ፥የሚገድልም፣

ነገር፣ቢጠጡ፣አይጐዳቸውም

፤እጃቸውን፣በድውዮች፣ላይ፣ይጭናሉ፣እነርሱም፣ይድና

ሉ።

ልሳን መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጣቸው ስጦታዎች መካከል አንዱ ነው።

1ኛ ቆሮ. 12÷8-10

ለእንዱ፡ጥበብን፡መናገር፡በመንፈስ፡ይሰጠዋልና፥ለእ

ንዱም፡በዚያው፡መንፈስ፡ዕውቀትን፡መናገር፡ይሰጠዋል

፥ለእንዱም፡በዚያው፡መንፈስ፡እምነት፥ለእንዱም፡በእ

ንዱ፡መንፈስ፡የመፈወስ፡ስጦታ፥ለእንዱም፡ተኣምራትን፡ማድረግ፥ለእንዱም፡

ትንቢትን፡መናገር፥ለእንዱም፡መ

ናፍስትን፡መለየት፥ለእንዱም፡በልዩ፡ዐይነት፡ልሳን፡

መናገር፥ለእንዱም፡በልሳኖች፡የተነገረውን፡መተርጐም፡ይሰጠዋል፤

ልሳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው ለሐዋርያት ነው።

ሐዋ.2÷1-17

በዓለ፡ኀምሳ፡የተባለውም፡ቀን፡በደረሰ፡ጊዜ፥ኹሉም፡

ባንድ፡ልብ፡ኾነው፡ዐብረው፡ሳሉ፥

ድንገት፡እንደሚነጥቅ፡ዐውሎ፡ነፋስ፡ከሰማይ፡ድምፅ፡

መጣ፥ተቀምጠው፡የነበሩበትንም፡ቤት፡ኹሉ፡ሞላው።

እንደ፡እሳትም፡የተከፋፈሉ፡ልሳኖች፡ታይዋቸው፤በያን

ዳንዳቸውም፡ላይ፡ተቀመጡባቸው።

በኹሉም፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ሞላባቸው፥መንፈስም፡ይናገሩ፡ዘንድ፡እንደ፡ሰጣቸው፡

በሌላ፡ልሳኖች፡ይናገሩ፡ዠመር።

ከሰማይም፡በታች፡ካሉ፡ሕዝብ፡ኹሉ፡በጸሎት፡የተገ፡እ

ይሁድ፡በኢየሩሳሌም፡ይኖሩ፡ነበር፤ይህም፡ድምፅ፡በኾ

ነ፡ጊዜ፡ሕዝብ፡ኹሉ፡ተሰበሰቡ፥እያንዳንዱም፡በገዛ፡

ቋንቋው፡ሲናገሩ፡ይሰማ፡ስለ፡ነበር፡የሚሉትን፡ዐጡ።

ተገርመውም፡ተደንቀውም፡እንዲህ፡አሉ፦እንሆ፥እነዚህ፡የሚናገሩት፡ኹሉ፡

የገሊላ፣ሰዎች፣አይደሉምን፧እኛም፣እያንዳንዳችን፣የተወለድንበትን፣የገዛ፣

ቋንቋችንን፣እንዴት፣እንሰማለን፧

የጳርቴና፣የሜድ፣የኢላሜጤም፣ሰዎች÷በኹለት፣ወንዝም፣መካከል፣በይሁዳም፣

በቀጳዶቅያም፣በጳንጦስም፣በእስያም÷በፍርግያም፣በጵንፍልያም፣በግብጽም፣

በቀሬናም፣በኩል፣ባሉት፣በሊብያ፣ወረዳዎች፣የምንኖር÷በሮሜም፣

የምንቀመጥ÷አይሁድም፣ወደ፣ይሁዲነትም፣የገባን÷

የቀርጤስና፣የዐረብ፣ሰዎች÷የእግዚአብሔርን፣ታላቅ፣

ሥራ፣በልሳኖቻችን፣ሲናገሩ፣እንሰማቸዋለን።ኹሉም፣ተ

ገረሙና፣አመንትተው፣ርስ፣በርሳቸው፦እንጃ÷ይህ፣ምን፣ይኾን፧አሉ።ሌላዎች፣ግን፣

እያፌዙባቸው፦ጕሽ፣የወይን፣ጠጅ፣ጠግበዋል፣አሉ።

ነገር፣ግን÷ጴጥሮስ፣ከዐሥራ፣አንዱ፣ጋራ፣ቆመ÷ድምፁ

ንም፣ከፍ፣አድርጎ፣እንዲህ፣ሲል፣

ተናገራቸው፦አይሁድ፣በኢየሩሳሌምም፣የምትኖሩ፣ኹላችኹ÷ይህ፣በእናንተ፣

ዘንድ፣የታወቀ፣ይኹን÷ቃሎቼንም፣አድምጡ ለእናንተ፣እንደ፣መሰላችኹ

፣እነዚህ፣የሰከሩ፣አይደሉም÷ከቀኑ፣ሦስተኛ፣ሰዓት፣

ነውና፤ነገር፣ግን÷ይህ፣በነቢዩ፣በኢዮኤል፣የተባለው፣ነው።

እግዚአብሔር፣ይላል፦በመጨረሻው፣ቀን፣እንዲህ፣ይኾናል፤ሥጋ፣በለበሰ፣ኹሉ፣

ላይ፣ከመንፈሴ፣አፈሳለኹ፤ወንዶችና፣ሴቶች፣ልጆቻችኹም፣ትንቢት፣

ይናገራሉ÷ጐበዞቻችኹም፣ራእይ፣ያያሉ÷ሽማግ

ሌዎቻችኹም፣ሕልም፣ያልማሉ፤

ለሰው ልጅ በሚሰሙት ቋንቋ መናገር ለማያምኑት ይጠቅማል።

1ኛ ቆሮ. 14 ÷ 21-30

ሌላዎችን፡ልሳኖች፡በሚናገሩ፡ሰዎችና፡በሌላ፡አንደበት፡ለዚህ፡ሕዝብ፡
እነግራቸዋለኹ÷እንዲህም፡ቢኾን፡አ
ይሰሙኝም፡ይላል፡ጌታ፡ተብሎ፡በሕግ፡ተጽፏል።
እንግዲያስ፡በልሳኖች፡መናገር፡ለማያምኑ፡ምልክት፡ነ
ው፡እንጂ፡ለሚያምኑ፡አይደለም÷ትንቢት፡ግን፡ለሚያም
ኑ፡እንጂ፡ለማያምኑ፡አይደለም።
እንግዲህ፡ማኅበር፡ኹሉ፡ዐብረው፡ቢሰበሰቡ፡ኹሉም፡በ
ልሳኖች፡ቢናገሩና፡ያልተማሩ፡ወይም፡የማያምኑ፡ሰዎች፡ቢገቡ።አብደዋል፡
አይሉምን፧
ኹሉ፡ትንቢት፡ቢናገሩ፡ግን፡የማያምን፡ወይም፡ያልተማ
ረ፡ሰው፡ቢገባ፡በኹሉ፡ይወቀሳል÷በኹሉም፡ይመረመራል፤በልቡም፡የተሰወረ፡
ይገለጣል፡እንዲሁም፦እግዚአብሔር፡በእውነት፡በመካከላቸው፡ነው፡ብሎ፡
እየተናገረ፡በፊቱ፡ወድቆ፡ለእግዚአብሔር፡ይሰግዳል።
እንግዲህ÷ወንድሞች፡ሆይ÷ምንድር፡ነው፧በምትሰበሰቡበት፡ጊዜ፡ለያንዳንዱ፡
መዝሙር፡አለው÷ትምህርት፡አለው÷መግለጥ፡አለው÷በልሳን፡መናገር፡
አለው÷መተርጐም፡አለው፤ኹሉ፡ለማነጽ፡ይኹ
ን።
በልሳን፡የሚናገር፡ቢኖር÷ኹለት፡ወይም፡ቢበዛ፡ሦስት፡ኾነው፡በተራቸው፡
ይናገሩ÷አንዱም፡ይተርጕም፤የሚተ
ረጕም፡ባይኖር፡ግን÷በማኅበር፡መካከል፡ዝም፡ይበልና፡ለራሱና፡ለእግዚአብሔር፡
ይናገር።ነቢያትም፡ኹለት፡
ወይም፡ሦስት፡ኾነው፡ይናገሩ፡ሌላዎችም፡ይለይዋቸው፤

በዚያ፣ለሚቀመጥ፣ለሌላ፣ግን፣አንድ፣ነገር፣ቢገለጥለት፣ፊተኛው፣ዝም፣ይበል።

ልሳን ለመናገር በስርዓትና በአግባብ ይሁን

1ኛ ቆሮ. 14 ÷ 39-40

ስለዚህ፥ወንድሞች፣ሆይ፥ትንቢት፣ለመናገር፣በብርቱ፣

ፈልጉ፥በልሳኖች፣ከመናገርም፣አትከልክሉ፤ነገር፣ግን

፥ኹሉ፣በአገባብና፣በሥርዐት፣ይኹን።

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ልሳን ሲናገር በልሳኖች፣ብናገር፥በመግለጥ፣ወይም፣

በዕውቀት፣

ወይም፣በትንቢት፣ወይም፣በትምህርት፣ካልነገርኋችኹ፣

ምን፣እጠቅማችኋለኹ፡

1ኛ ቆሮ. 14 ÷ 1-6

ፍቅርን፣ተከታተሉ፥መንፈሳዊ፣ስጦታንም፣ይልቁንም፣ት

ንቢት፣መናገርን፣በብርቱ፣ፈልጉ።በልሳን፣የሚናገርስ፣ለእግዚአብሔር፣እንጂ፣

ለሰው፣አይናገርምና፤የሚያስተ

ውለው፣የለምና፥በመንፈስ፣ግን፣ምስጢርን፣ይናገራልና፤

ትንቢትን፣የሚናገር፣ግን፣ለማነጽና፣ለመምከር፣ለማጽ

ናናትም፣ለሰው፣ይናገራል።

በልሳን፣የሚናገር፣ራሱን፣ያንጻልና፤ትንቢትን፣የሚናገር፣ግን፣ማኅበሩን፣ያንጻል።

ኹላችኹ፣በልሳኖች፣ልትናገሩ፣እወድ፣ነበር፥ትንቢትን፣ልትናገሩ፣ግን፣ከዚህ፣ይልቅ፣

እወዳለኹና፤ማኅበሩ፣ይ

ታነጽ፣ዘንድ፣ንግግሩን፣ባይተረጕም፣በልሳኖች፣ከሚና

ገር፣ትንቢትን፣የሚናገር፣ይበልጣል።

አኹን፡ግን፥ወንድሞች፡ሆይ፥ወደ፡እናንተ፡መጥቼ፡በል

ሳኖች፡ብናገር፥በመግለጥ፡ወይም፡በዕውቀት፡ወይም፡በ

ትንቢት፡ወይም፡በትምህርት፡ካልነገርኋችኹ፡ምን፡እጠ

ቅማችኋለኹ፡

አንድ ሰው በጉባኤ መሀል በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገር ከሆነ በጉባኤው ለተሰበሰቡት ሰዎች በሚሰሙት ቋንቋ መተርጎም እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል።

1ኛ ቆሮ. 14 ÷ 13

ስለዚህ፥በልሳን፡የሚናገር፡እንዲተረጕም፡ይጸልይ።

በእውነት ላመኑ ክርስቲያኖች የልሳን ወይም የቋንቋ ጋጋታ ምንም አይጠቅምም።

1ኛ ቆሮ. 14 ÷ 22-25

እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፥ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም።

እንግዲህ ማኅበር ሁሉ አብረው ቢሰበሰቡ ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ። አብደዋል አይሉምን?

ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ በሁሉ ይወቀሳል፥ በሁሉም ይመረመራል፤

በልቡም የተሰወረ ይገለጣል እንዲሁም። እግዚአብሔር በእውነት በመካከላቸው ነው ብሎ እየተናገረ በፊቱ ወድቆ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል።

ስለ ልሳን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር፡-

1ኛ ቆሮ. 14 ÷ 18-19

ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ።

መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው። ጸጋው /ስጦታው/ ብዙ ነው።

በ1ኛ ቆሮ.1 ÷ 4 እንዲህ ይላል፡- በክርስቶስ ኢየሱስ ስላመናችሁ በተሰጣችሁ በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት ሁልጊዜ ስለ እናንተ አምላክን አመሰግናለሁ፤

መንፈስ ቅዱስ ብዙ ከሆነው ጸጋው ለመስጠት አንድ ልብ የሆኑ መለያየት፣ መነቃቀፍ፣ ክርክር በመካከላቸው የሌለ ክርስቲያኖችን ይፈልጋል።

ስጦታዎች የሚሰጡ እንጂ የሚጠየቁ አይደለም።

ሮሜ 12 ÷ 3

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፥ እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ።

ማቴ. 6 ÷ 34

ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።

1ኛ ቆሮ. 14 ÷ 22

እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፥ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም።

Wogderes Fikre

32/ እናት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለተሐድሶ መናፍቃን መልስ መስጠት ቀጥላለች።

ትናንት ምሽት ጥቅምት 3/ 2008 በደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ለተሐድሶ መናፍቃን መልስ ለመስጠት በተዘጋጀው ልዩ ጉባኤ ላይ በሁለት ክፍል ተከፍሎ በሁለት ታላላቅ መምህራን ግቡን በመታ መልኩ የተከናወነው የዚሁ ምላሽ የመስጠት አካል ነው።

በጉባዔው ላይ የተሐድሶ ክህደት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትክክለኛ አስተምህሮ ተገልጣበታል።የመጀመሪያውን ክፍል ት/ት ያስተማሩት የሕግ ባለሙያው መምህር አስቻለው ከበደ ነበሩ።

የሁለተኛውን ከፍለ ጊዜ ያስተማሩት ደግሞ መምህር ምህረተአብ አሰፋ ናቸው። ሀለቱም መምህራን ያሉትን ልዩነቶች አሳይተዋል።

በተለይ መምህር ምህረተአብ በእመቤታችን ላይ ያለውን ክህደት ልቅም አድርገው ምላሽ ሰጥተውበታል።

መምህሩ ትምህርታቸውን ሲጀምሩ ለየት ያለ ምናባዊ ምሳሌ በመመል ነው። "የምድር 3/4 (ሰስት አራረኛ) የሚሆን ትልቅ አዳራሽ ነው።በዚህ አዳራሽ ሎሲፈር የሚመራው ስብሰባ ተካሄደ። የስብሰባው ዋና አጀንዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን እንዴት ማጥፋት እንችላለን የሚል ነው።" እንደ መምህሩ ምስሌ ልዩ ልዩ አስተያየቶች ተሰጡ።ከሁሉም ግን ተመራጭ የሆነው መጨረሻ ላይ የተሰጠው አስተያየ ነው፤ እርሱም

"መፅሐፍ ቅዱሳቸን ይዘን እነርሱን መስለን ከውስጥ በመሆን እያጣመምን በመተርጎም ማጥፋት እንችላለን።" የሚለው ሀሳብ ነው" በማለት ተሐድሶ ከውስጥ ሆኖ የቤተክርስቲያኒቱን እስተምህሮ በመበረዝ ተዋህዶን ለማጥፋት የሚያደርጉትን ድካም አስገንዝበዋል። ተሐድሶዎች ምንፍቅናን ከሚዘሩበት አንዱ የእመቤታችን ነገር ነው። በመሆኑም መምህር ምህረተአብ ትኩረት በማድረግ በደንብ አድርገው በማያዳግም ሁኔታ መልስ ሰጥተዋል። ተሐድሶዎች አሉ መምህር ምህረተአብ "ተሐድሶዎች ክብር ይግባትና እመቤታችን ወላዲተ አምላክ መባል አይገባትም ይላሉ። ይህንን በልዩ ልዩ መልክ ግልፀውታል በዋናነት ግን በመፅሐፍ መልክ አሳትመውታል "መጋቤ ጥበብ" ሰለሞን ነኝ ያለ ሰው "በውኑ በማሪያም ማመን ይገባልን"
ብሎ መፅሐፍ ፅፏል"። ይህ ከሀዲ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ወላዲተ አምላክ መባል እንደማይገባት በግልጽ መግፋን ለማህበረ ምእመናኑ ተናግረዋል። ነገር ግን የእኛ ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ድንግል ማርያም ደግሞ ወላዲተ አምላክ ብለን እንደምናምን በርካታ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ በመስጠት የቤተክርስቲያናችንን አስተምህሮ እና የተሐድሶ መናፍቃንን የለየለት ምንፍቅና ተናግረዋል።
ይህንን ምንፍቅና ከየት አምጥተው እንደሚያቀረሹ ምንጩን፣ መን ሻ ጊዜዉን፣የክህደቱንም የመጀመሪያ አቀንቃኝ ጨምሮ ፍንትው አድርገው እውነቱን ገልፀውታል። መምህር እግዚአብሔር ይስጥልን።
እመቤታችንን የማያከብር ሰው አየሲስ ክርስቶስን አላከበረም ማለት ነው።እርሷን ወላዲት አምላክ መባል አይገባትም ካልን የወለደችው አምላክ አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ያደርሰናል ይህም መፅሐፍ ቅዱሱን

መቃረን ስለሚሆን ግልፅ ክህደት ነው።ስለዚህ እርሱን እምላክ ካልን እርሷ ወልዳዋለችና ወላዲተ አምላክ ማለት ይኖርብናል፤ ማለት ስላለብን ሳይሆን በእውነትም ስለሆነች ነው።

የዛሬን አያድርገውና አሉ መምህር ምህረተአብ "የዛሬን አያድርገውና እነ መርጌታ እንትና እኮ በስሟ ለምነው አኮፋዳቸውን ሞልተዋል" አሉ

እውንነት ነው እነዚህ አሁን አታማልድም ምናምን የሚሉት እኮ በስሟ ለምነው አኮፋዳቸውን ሞልተዋል ስሟ ጠርተው ለምነው ተምረው ከሰው እኩል ሆነዋል። ዛሬ ግን ዛሬ ግን.....ይሁን ብቻ

መምህሩ ስለ እመቤታችን አማላጅነት፣በድህነታችን ውስጥ ያላትን ሚና፣ክብሯን ሁሉ ፍንትው አድርገው በጉልህ አሳይተዋል።

በእመቤታችን በኩል በተሐድሶ መናፍቃን ተነስቶ የነበረው ክህደት እዚሁ ጋር ዘግተዉታል። ተሐድሶ አሁን አንድ ክንፉ ተሰብሯል ማለት ነው። መምህር ምህረተአብ ትምህርቱን ሲጨርሱ እንደተለመደው በዝማሬም አገልግለውናል።እነ ዘማሪ ልዑልሰገድ ዘማሪ ኤርሚያስ ሌሎችም ተገኝተው ነበር።

ይኸው ጉባኤ በቀጣይ ረቡዕ በተመሳሳይ ቦታና ሰዓት ይቀጥላል ልዩ የድምፅ ማስረጃ እንዲያውም ከተቻለ የምስል ማስረጃ ይዘው እንደሚቀርቡ መምህር ምህረተአብ ቃል ገብተዋል። ልዩ ልዩ ዘማርያን እነ ቀሲስ ምንዳዬ ብርሃኑ፣ እነ ሊቀ መዘምራን ዲ.ን ቴዎድስ ዮሴፍ እና ሌሎችም ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

Like · Deacon Moges Asmare

jegnoch memhran bewnet rezhm edman

ystachwu elalehu kale hywot yasemalen emebrhan titebkachw bertulen

Like . Degualem Semagn

ቤተ ክርስቲን ሆይ ምነው ተረበሽ፣አንድነትሽ ጠፍቶ ሰላምን አጣሽ።አንደኛው ሲጠቅምሽ ሌላኛውሲጎዳሽ፣ብዙ ልጆች ወልደሽ የወላድ መካን ሆንሽ።

Like · Mazadasale Dasale

Egziabeher ewnetun yawetawal lesu ymesanew yelem menafekan hulum gudu yewetaaaaaaaal wendemachen kalehiwet yasemalen amen

Dani EL Getachew

Abayneh Kassie

33/ **የግብር ስማቸው "ሀራጥቃ ተሐድሶ" ነው**

በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ የኾነ አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን የመዋጋት እንቅስቃሴ በየአካባቢው እየተካሄደ ነው። ከሀገር ቤት እስከ ምድረ አሜሪካ እየተካሄደ ያለው እንቅስቃሴ ሠናይ ነው። በዚሁ ከቀጠለ ያማረ ውጤት ላይ መድረሳችን አይቀርም። ቀኑም ሩቅ አይኾንም።

እየተቀጣጠለ ያለው ስሜት ለራሳቸው አስፈሪ ኾኖባቸዋል። ግርማችን አስፈሪነታችን ይህ አንድነታችን ነውና። ከፊታችን ለመቆም ወደማይችሉበት ደረጃ እስክናደርሳቸው ድረስ እረፍት ጠይቀን ልንወጣ አይገባም። አሁን በጭንቀት በረት ውስጥ ገብተዋል። መግቢያ መውጫቸው ሁሉ ታጥሮባቸዋል። ግን ስሁታን ናቸውና በዚህም መካከል ስሁት ሰብእናቸው መታየቱ አይቀርም። በዚሁ ስንቀጥል ደግሞ ጠራርገን ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ማስወጣት እንደምንችል በኃያሉ እግዚአብሔር ተስፋ እናደርጋለን።

ልዩነት ያለን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ ጥቃቅኑን ልዩነት ትተን አንድነታችንን አጠንክረን መሄድ ይጠበቅብናል። ለታላቁ ዓላማ ሲባል ጥቃቅኑ ልዩነቶች መሥዋዕት ሊደረጉ ይገባል። እገሌ ይተው ከማለት ስለቤተ ክርስቲያኔ ስል እኔ ትቸዋለሁ እንበል። ትግሉ ከዚህ ይጀምራል።

እጅ ለእጅ ተያይዘን ያለብንን መንፈሳዊ እና ታሪካዊ አደራ እንወጣ።

ሌላው ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ እና መሠረታዊ ለውጥ ልናደርግበት የሚገባው ለሀራጥቃ ተሐድሶ የተሰጠው ስያሜ ነው። በተለምዶ "ተሐድሶ" በሚል መጠሪያ እንጠራቸዋለን። ይህንን ስያሜ የመረጡት እራሳቸው ናቸው። ነገር ግን "ተሐድሶ" የሚለው ቃል በቁሙ አዎንታዊ ትርጉም ያለው ነው። ሃይማኖታዊ ተሐድሶን እንቃወማለን እንጂ አስተዳደራዊ ተሐድሶን አንቃወምም። ስለዚህ ለቃሉ ሁነኛ ቅጽል ልናበጅለት ይገባል። በጭራሽ ለእነርሱ አይመጥንም። "ተሐድሶ" ብለን ከእነርሱ ተቀብለን ማስተጋባት የለብንም።

እነርሱ ሊጠሩ በፈለጉበት መንገድ "ተሐድሶ" እያሉ መጥራት ለእነርሱ

ድል ሲኾን ለእኛ ደግሞ ሽንፈት ነው። ትምህርታቸው የመናፍቅ ነው። መናፍቃን በቤተ ክርስቲያናችን ከሚጠሩባቸው የወል ስሞች አንዱ ሀራጥቃ የሚለው ነው። በአፍርንጅ ቃል "heretics" እንዲሉ። በጅምላ ሀራጥቃ ብለን ከጠራናቸው የትኞቹ የሚለው ጥያቄ ሳይመለስ ሊቀር ነው። ለእርሱ ሲባል ደግሞ "ሀራጥቃ ተሐድሶ" ብንላቸው የተመቸ ነው። ይህም ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ለሚለው የቀረበ አጠራር ነው።

ፕሮቴስታንት የሚለው ቃል አማርኛ ወይንም ግእዝ ባለመኾኑ እንጂ በትርጉም ደረጃ አያስሄድም ማለት አይቻልም። ሀራጥቃ የሚለው ግን የለየላቸው መናፍቃንን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስትጠራበት የኖረ አሁን አሁን ግን እየተረሳ የመጣ ቃል ከመኾኑ በስተቀር ገላጭነቱ አያሻማም። እናም በግብር ስማቸው "ሀራጥቃ ተሐድሶ" እያልን ልንጠራቸው ይገባል።

ጸሐፊያንም፣ ተናጋሪዎችም፣ መምህራንም፣ ማኅበራትም፣ ሰንበት ትምህርት ቤቶችም፣ አበውም የተሻለ አማራጭ እስኪመጣ ድረስ ቢጠቀሙበት ሠናይ ነው እላለሁ። ቃሉን ማስተዋወቅም ይጠበቅብናል። ላልሰሙትም በማካፈል ጉዳዩን የጋራ አድርገነው ለውጥ እናመጣ ዘንድ አደራ እላለሁ። እኔም በማይገባቸው ላልጠራቸው በሚገልጣቸው ልጠራቸው ከእንግዲህ ቃሉን ለመጠቀም ወስኛለሁ። እርስዎስ?

Like . Tewodros Adugna

አውነት ነው ሀራጥቃ ተሀድሶ!

Like ·Yared Gebrehiwot

dani mn yemsel gubaye behertsege mariyam tilant be diyakon begashew tekehedwal

zarem yeketelal kechalk beke bel

Like · Tafete Gedamu Abera

እጅለእጅ ተያይዘን ሙስናን እንከላከል ቢሉ ያምር ነበር

Like · Aman Mengesha Ayele

ሀራጥቃ ተሀድሶ

የለየላቸው መናፍቃን

Like · Andebet Dessiew

እኔም ወስኛለሁ።

የዘመድኩን የዓላማው ደጋፊዎች

34/ የታኦሎጎስን ቲቪን እንደታዘብኩት

ሰሞኑን የማኅበራዊ ሚዲያውም ሆነ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ትልቁ መነጋገሪያና የምእመናን አጀንዳ እኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሃይማኖቱን መልክ ለመለወጥ ለረጅም ዘመናት በብዙ ገንዘብ ፣ የሰው ኃይል ፣ እና ልዩ እስትራቴጂ እየተነንቀሳቀሱ ስላሉት የተሐድሶ መናፍቃን ጉዳይ ነው።

ምን አልባት የተሐድሶ መናፍቃን የሚባሉት በስብከትና በዝማሬ አካባቢ ያሉት ብቻ አለመሆናቸውን ልብ ይሏል ። የተበረዙት ሰባኪያንና ዘማሪያን እንዲሁም ሚዲያው ሚዲያው ላይ የምናያቸው የክፋ ዓላማው የአንድ ቅርንጫፍ ቅጠሎች ናቸው እንጂ ዋናዎቹ አይደሉም ፥ በዚህ ግዙፍ ና ከባድ ፕሮጀክት ጉዳይ ላይ ሰሞኑን የምንመለስበት ይሆንና ዛሬ ላነሳ የፈለግሁት ።

ታዖሎጎስ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ለወጣው የቤተ ክርስቲያን ሚዲያ

ጉዳይ ላይ የታዖሎጎስ የፊስ ቡክ ፔጅ ማስተባበያ መሰል የአቋም መግለጫ ና መልእክት ላይ ይሆናል ።

እውን ታኦሎጎስ ኦርቶዶክሳዊ ሚዲያ ነኝ ብሎ የመናገር በቂ ሞራል አለው? ካለው እስኪ ሚዲያው ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በየ እሁዱ ያስተላለፋቸውን መልእክቶቹን ዞር ብሎ አይቶ መልስ ይስጠን ። መሥራቾቹ በየ ዐውደ ምሓረቱ አሁንም እያሉ ያሉት "እስኪ ማን እንደሚያዘጋው እናያለን " የሚል ዛቻ እንጂ ኦርቶዶክሳውያን ስለመሆናቸው ማረጋገጫ አይደለም ዛቻ የተሰፋ መቁረጥ ምልክት እንጂ ለጥያቄ መልስ አይደለም እኔ አሁን እያልኩ ያለሁት ስለመዘጋት ያለመዘጋት ጉዳይም አይደለም ሥለ ኦርቶዶክሳዊ አይከን ነው

ለምሳሌ እኛ የምንኖርባትና የምናምናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ካሪኩለም (ግጻዌ) አላት ይህንንም ከዓመት እስከ ዓመት አገልግሎቷን ትመራበታለች ። አሁን በዚህ ወቅት የምድርን ተፈጥሮአዊ ለውጥ ማለትም ክረምትን በበጋ ፣ በደመና ተጋርዶ የነበረውን ሰማይ በፀሐይ በጨረቃ ፣በከዋክብት መተካቱንና የአበባ ጊዜ መድረሱን አስባ ትምህርቷ ፣ ጸሎቷ ፣ ቅዳሴዋ ይህን የእግዚአብሔርን ሥራ የምታደንቅበት ጥቅስ መርጣ የምታገለግልበት ወቅት ነው ። ታዖሎጎስ በየትኛው ዓመት ጥቅምት ነው ይህን አስቦ አስቦ አስታውሶ አስተላልፎልን የሚያውቀው? ይህ ብቻ አይደለም በትልቁ ወር በጌታ ዖም እንኳን 8 ቱ ሳምንታት የየራሳቸው ስያሜ አላቸው ዘወረደ ፣ ቅድስት ፣ ምኩራብ ፣ መጻጉ ወ.ዘ.ተ ። ታዲያ በየትኛው ዐቢይ ዖም የየትኛውን እሁድ ትርጉም አብራርቶልን ያውቃል? ሌላውና ትልቁ የኦርቶዶክሳዊነት አይከን በሥላሴ አምኖ ፣ አምላክ ሰው

የሆነበት ትልቁ ምሥጢር የተስተናገደባትን ድንግል ማርያምን ና ሥለ ስሙ በዓለሙ ሁሉ የተንከራተቱለትን ፣ የሞቱለትን ቅዱሳን ዋጋ ሰጥቶ ክብራቸውን በሚገባቸው መጠን መግለጥ ነው ።

ታዲያ ታዖሎጎስ ይህንን ሁሉ መች አሳይቶን ነው ኦርቶዶክሳዊ ሚዲያ ነኝ የሚለን ? እንደውም እኔ የማረሳው በ2006 ዓ ም በታላቁ የትንሣኤ በዓል ቤተ ክርስቲያኒቱ "ወተንሥአ እግዚአብሔር "እያለች በማይለወጥና በማይሰለች የዓመት ቀለም እያወጀች ስትውል ነገር ግን ይህ የተከበረው ሚዲያ በዚህ ዐቢይ ያስተላለፈልን በእውነት ሥለ ምድራዊ ሥራ ጥቅም ነበር ።

ከዚህ የተነሣ ሚዲያው ኦርቶዶክሳዊውን አይከን የማስረሳት ዘመቻ ላይ ያለ ያስመስልበታል ።

ሥለዚህ የዚህ ሚዲያ መሥራች በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሓረት ላይ "እስኪ ቦሩ ሜዳ ይዘጋጅልን" ብሎአል ሹር በእውነት እነ መምህር አካለ ወልድ የቀለም ቀንድ የዋሉበት ታላቁ ቦሩ ሜዳ ለእኛ አይመጥንምና ታዖሎጎሶች ሆይ እስኪ ሩቅ ሳትሄዱ በራሳችሁ ሚዲያ መልስ ስጡን። ከቻላችሁ ሩቅ የሆናችሁት ከቤተ ክርስቲያኒቱ እንጂ ለቤተ ክህነቱ ከእኛ ይልቅ ቅርብ ናችሁና በእናንተው አመቻችነት በአባቶች ፊት እንወያይና ችግራችሁን ነቅሰን ማውጣት አቅቶን እንፈር። ለኛ ቦሩ ሜዳ ይበዛብናልና ።

በመጨረሻም ለምን ተጠየቅን በማለት አሳደዱን አትበሉ ምክንያቱም

1 ኛ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ተብሎ ተጽፏልና ሳንመረምር አናምናችሁም

2 ኛ ሰይጣን የብርሃን መልዐክ መስሎ እንዲመጣ እወቁ ተብሏልና መልዐክ መስሎ የመጣ ሰይጣን ሰባኪና ዘማሪ ሆኖ መምጣት አያቅተውምና በቃል

ብቻ አንቀበላችሁም

3ኛ ኢያሱ እንኳን በምድረ በዳ መልዐክ በተገለጠለት ጊዜ ከመስገዱ በፊት "ከእኛ ወገን ነህ ወይስ ከጠላቶቻችን" ባለው ጊዜ "አንተ ደፋር ለምን ጠየክኸኝ" አላለውም ጥያቄው ተገቢ ስለነበር መልዐኩ እኔ ከእናንተም ከጠላቶቻችሁ ወገን አይደለሁም" በማለት ትክክለኛ አድራሻውን ነው የነገረውና እናንተም ሌላ ግራ መጋባትን ከምትፈጥሩ አድራሻችሁን ከቃል በዘለለ አስታውቁን

4ኛ መጥምቁ ዮሐንስ ክርስቶስን ያወቀው ገና በማኅፀን ሲሆን ያ ጠባብ የእናት ሆድ አምላኩን ለማወቅ መጋረጃ አልሆነበትም በኃላም ኢየሱስን ዓለም ሳያውቀው "የእግዚአብሔር በግ እነሆ" በማለት የመሰከረለት እርሱ ነው ነገር ግን እንዲህ የተረዳው ዮሐንስ በእስር ቤት ሳለ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ጌታ ልኮ "ይመጣል የተባልከው አንተ ነህ ወይስ ሌላ እንጠብቅ" ባለው ጊዜ ጌታም ለዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ሂዱና ያያችሁትን ንገሩት አለ እንጂ ለምን ይጠይቀኛል አላለምና ። እናንተም ከጌታ አትበልጡምና ለምን ተጠየቅን አትበሉ ፥ ለጠየቅናችሁም ጥያቄ መልሳችሁ አሳደዱን ፣ አሰቃዩን ፣ ቀኑብን እያላችሁ እሮሮ በማሰማት ምእመኑን በማደናገር ከመጠመድ የዘለለ ፋይዳ የለውምና ከኦርቶዶክስ ውኃ ልክ ወጣ ብላችሁ መቆማችሁን በቱንቢ ለክታችሁ እዩት ለጽሑፌ ከስድብ የዘለለ የሰለጠነ መልስ ብትሰጡኝ ምኞቴ ነው ካልሆነም እንግዲህ ምን አደርጋለሁ ስድቤን መጠጣት ነው እንጂ ለጥያቄ እንጂ ለስድብ መልስ የለኝምና አልመልስም ።

ጥቅምት የገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕለት 2008 አዲስ አበባ

ለመምህራችን ዲያቆን ተስፋዬ ሞሲሳ እግዚአብሔር አምላክ የአገልግሎት ዘመንህን ያርዝምልን ቃለ ህይወትን ያሰማልን።

ፍሬ ማርያም ዘኦርቶዶክስ

<u>35/ ድል አለ በክርሥቶሥ ዛሬ እየተካሄደ የነበረው ሥብሠባ በተሠድሶ የክፉት ሴራ</u> ተቋረጠ ተሀድሶዎች በርቱ እሥከምጠፉ ዛሬ ያደረጋችሁት ተንኮልና ክፋት ለኦርቶዶክሥ ተዋህዶ የቁርጥ ቀን ልጆች የድል መጀመሪያ የቀራኒዮ የጉዞ መንደርደሪያ ነው "የሚመካ በእግዚአብሄር ይመካ እማምላክ ትጠብቃችሁ።

[የእግዚአብሔርንጉባዔ ማንም ማስቆም አይችልም በርቱ።እውነት ሰለሆነ ክርስቶስ የዚህ አለም ሰዎች የክብር ዙፋን ላይ እንዲቆም አልነበረም የፈቀዱለት በቀራንዮ አደባባይ መስቀል ላይ እንጂ ።አሁንም እናንተ የእውነት(የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ) ልጆች ስለሆናችሁ መስቀሉን ተሸክማችሁ እንደምትከተሉት ነው የሚያሳየን እና አያስደንቀንም።ዲያብሎስ። እንኳን ለፍጥረታዊው ሰው ቀርቶ ለፈጣሪውም አልተኛም ።ግን ድሉ የእውነት ነውና በርቱ የተዋህዶ የቁርጥ ቀን ልጆች!

በመከራ ጽና በፈተና ጽና

ለጊዜው ነውእንጂ ሁሉም ያልፋልና

እዮብ ተፈተነ በጣም ተቸገረ

በመከራው ብዛት ትዕግስትን ተማረ

ልጅ የሌለው ሆነ አጣ ንብረቱንም

በመከራው ጸና አልካደም አምላኩን

መፈተን መልካም ነው ያነጥራል እንደወርቅ

በመጨረሻው ቀንበክብር እንድትደምቅ

አንዱን ሳትወጣ ሌላው ቢያጋጥምህ

በህይወትህ ዘመን ፈተና ቢያጠቃህ

ከ አምላክህ ተስማማ እራስህን አዋርድ

በቃሉም ተመራ እንደ ፈቃዱም ሂድ

ዋጋህ ከ አምላክህ ዘንድ በሰማይ አለና

በርታ ክርስቲያን ሆይ በመከራ ጽና ??✏✏✏✏

??ሮሜ 8፥ 35

ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?

??ሮሜ 8፥36

ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

??ሮሜ 8 ፥37

በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።

??ሮሜ 8 ፥38

ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥

ሮሜ 8 ፥39 ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን

በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

ክብር ሁሉ ለክርስቶስ አይሱስ ይሁን አሜን!!

like . Sarah Bacafto

እግዝያአብሔር አዋቂ ነው ነገር ሁሉ ለበጎነው

Like · Aden Yemariyami Liji

የእግዚአብሔርን ጉባዔ ማንም ማስቆም አይችልም በርቱ እውነት ሰለሆነ ክርስቶስ የዚህ አለም ሰዎች የክብር ዙፋን ላይ እንዲቆም አልነበረም የፈቀዱለት በቀራንዮ አደባባይ መስቀል ላይ እንጂ አሁንም እናንተ የእውነት(የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ) ልጆች ስለሆናችሁ መስቀሉን ተሸክማችሁ እንደምትከተሉት ነው የሚያሳየን እና አያስደንቀንም።

ዲያብሎስእንኳን ለፍጥረታዊው ሰው ቀርቶ ለፈጣሪውም አልተኛም ግን ድሉ የእውነት ነውና በርቱ የተዋህዶ ልጆች እግዚአብሔር ከናተ ጋር ይሁን

Ortodox Lezelealem Tnur with ፍሬ ማርያም ዘኦርቶዶክ

36/ ተሐድሶ መናፍቃን

ምንፍቅና ዛሬ ሳይሆን ገና በፍጥረት መጀመሪያው ዕለት በሳጥናኤል አንድ

ብሎ የጀመረ መርዝ ነው። ከዚያም በኋላ ዲያብሎስ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ሰዎችን በምንፍቅና ሲያሰለጥናቸው ቆይቷል። በየዘመኑ የሚነሡት መናፍቃን የሚያነግቧቸው የኑፋቄ ትምህርቶች እጅግ በርካታዎች ናቸው። በአሁኑ ዘመን የሚገኙ መናፍቃንም ካለፉት በመማር የራሳቸውን የጥፋት ስልት ነድፈው በጨለማ መንገድ ይጓዛሉ። በቅርቡ እየሰማንና እያየን ያለው ነገር ከቀድሞው የተለየ የረቀቀ መንገድ መከተላቸውን ነው። ከምዕመን እስከ ጵጵስና ደረጃ ቁልፍ ቦታዎችን በመያዝ ቤተ ክርስቲያንን ለመከፋፈል ብዙ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው። ስብከቶቻቸውና ዝማሬዎቻቸው ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የጣሱና ለመንፈሳዊ ጥንካሬ ምንም የማይጠቅሙ ዋዛ ፈዛዛ ነገሮች እና ሥጋዊ ፍላጎቶች የሚንጸባረቁባቸው እየሆኑ በመምጣታቸው ሥርዓት የጠበቁት እንዳይደመጡና እንዲጠሉ አድርገዋቸዋል። በዚህ አገልግሎት ሥር የተሰማሩ የተሐድሶ መናፍቃን መሪዎችም በየግላቸው ዘብ የሚቆምላቸውና እነርሱን የሚደግፍ ትውልድ በመፍጠር በአንዲት ቤተክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ሁለት ጎራዎች እንዲፈጠሩና ብጥብጡ እንዲባባስ አድርገውታል። የቀደሙት መናፍቃን ከቤተክርስቲያናችን ተገንጥለው የራሳቸውን የፍልስፍና ትምህርት የሚሰጡበት አዳራሽ እየሰሩ በዚያ ምንፍቅናቸውን ያራምዱ ነበር። የአሁኖቹ መናፍቃን ግን ቤተክርስቲያን ውስጥ ተቀምጠው ቅርሶቿን ለባዕድ አሳልፈው በመሸጥ ሥርዓቷን በመናድ ቤተ ክርስቲያንን ባዶ አዳራሽ በማድረግና ምዕመናንንና ካህናትን ለግላቸው መጠቀሚያ እየደለሉ ከቤተክርስቲያን ለማውጣት ረቂቅ ሥልት ያላቸው ናቸው። ከገጠር እስከ ከተማ የተዳረሰውን ይህ የተሐድሶ ምንፍቅና ሁላችንም ልንታገለው ይገባል። ማንን እየተከተልን፣ ለማን

እያጨበጨብን እንደሆነም ልንረዳ ያስፈልጋል። መስቀል የያዘው ሁሉ ቄስ፣ ቆብ የደፋው ሁሉ መነኩሴ፣ መቁጠሪያ የያዘው ሁሉ ባህታዊ፣ በመንበረ ጵጵስና የተቀመጠው ሁሉ ጳጳስ፣ ድምጽ ያለው ሁሉ ዘማሪ፣ መናገር የሚችለው ሁሉ ሰባኪ፣ የሚቀድሰው ሁሉ ዲያቆን፣ የሚያብረቀርቀው ሁሉ ወርቅ አይምሰላችሁ። ፍሬያቸውን ተመልክተን ከፍሬያቸው ማዎቅ እንችላለን። ለበለጠ ደግሞ በጸሎት፣ በጾም፣ በትሕትና መትጋት ያስፈልጋል። ዛሬ በእነዚህ መናፍቃን የተደናገርን እኔ ክርስቶስ ነኝ እያለ በምትሐት ፀሐይና ጨረቃን በእጁ መዳፍ የያዘ መስሎ ሲመጣ ስንቶቻችን ነን በክርስትናችን ጸንተን የምንገኝ። እባካችሁ ወገኖቼ ኃይልን ከአርያም እስክንለብስ ድረስ በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ጸንተን እንቆይ። ከዚያ በኋላ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲሰጠን መናፍቃንን ድል የምንመታ ኃይለኞች እንሆናለን። ኃይለ መንፈስ ቅዱስ ብርታትና ጽናት ስለሚሆነን ሐዋርያት ባስተማሩት ትምህርት በክርስቶስ መሠረትነት ላይ ታንጸን ለመኖር አይከብደንም። ቤተክርስቲያናችን በምንም አይነት የረቀቀ መንገድ ለሚመጣ መናፍቅ አጉልቶ በሚያሳይ ትምህርቷ ትረታቸዋለች። ስለዚህ የምንከተለው እረኛ አውነተኛ መሆኑን አውቀን የእኛን የበጎቹን ድምፅ መለየት እንደሚችል ተገንዝበን ልንከተል ያስፈልጋል እንጂ ነፋስ በፈለገው አቅጣጫ እንደሚያወዛውዘው ዛፍ ወደዚያ ወደዚህ መወላወል ለክርስትና ሕይወታችን እንቅፋት ነው። አሁን ትኩረት ልንሰጠው የሚያስፈልገው መነቃቀፍን አይደለም ጾም ጸሎትን ነው። እግዚአብሔር አፍኒንና ፊንሐስን በቤተመቅደስ የማይገባ ሥራ በመሥራታቸው ቀስፎ እንዳስወገዳቸው ሁሉ አሁንም የተሐድሶ መናፍቃንን ከሚቀልዱበት መድረክ ጠርጎ

እንደሚያወጣቸው በማመን እንጸልይ።

ተሐድሶ ሁሌም ልቅሶ

ተሐድሶ በዚህ ዘመን ለተነሡ መናፍቃን መጠሪያ ሥም ነው። የቤተክርስቲያናችንን ሥርዓት በማፍረስ እና መሠረቷን ለማጋት የሚንቀሳቀስ ኃይል ነው። ቤተክርስቲያናችን የገሐነም ደጆች እንኳ የሚርዱላት በክርስቶስ ደም የተመሠረተች በመሆኗ ከውጭ የሚወረወረው ቀስትና ከውስጥ ለማፍረስ የሚገፏት ምንም ሊያደርጓት አይችሉም። እነዚህ መናፍቃን በሚያነሧቸው ርዕሰ ጉዳዮች ቤተክርስቲያናችን ስለምትረታቸው "ተሐድሶ ሁሌም ልቅሶ" ሆኖባቸዋል።

ስላልሰማህ ይሆናል

አንድ የተሐድሶ ሰባኪ ከመድረክ ላይ ወጥቶ በመጀመሪያ ስሙን ቀጥሎም የሚማርበትን ኮሌጅ ከገለጠ በኋላ ስብከት አይሉት ስድብ መናገር ጀመረ። "ይህች ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ከ 10 ዓመታት በፊት ወንጌል አልተሰበከባትም ነበር ክብር ምስጋና ይግባው የኔ ጌታ ዛሬ ግን እኔን በፊታችሁ አቁሞ ወንጌልን እንድሰብክ በክብር ሾመኝ። ይኼውላችሁ እኔን አስነሥቶ የተመረጠውን ሕዝብ በእግዚአብሔር ቃል ያረሰርሳል። ለዚህ እልልታ አይገባም? እልል በሉ እባካችሁ! አጨብጭቡ!"

እያለ ከስብከቱ ይልቅ የእልልታው ጊዜ በዝቶ እልል የሚሉት ጉሮሯቸው ደረቀ። ይህን ኑፋቄውን እንደጨረሰ ለመርጎ ግብር መሪው ቦታውን ለቅቆ ከመድረኩ ወርዶ ወንበር ላይ ተቀመጠ። መርሐ ግብር መሪው በጣም አስተዋይና የተማረ ነበርና

"ወንድማችን ተሐድሶዎች የሚያስተምሩትን ትምህርት በግልጥና በሚገባ

ስለነገረን ቃለ ሕይወት ያሰማልን። ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቀድሞ በነቢያት ኋላም በሐዋርያት ትምህርት የጸናች ናት። ወንድማችን ምናልባት ከ 10 ዓመታት በፊት ያለውን ስላልሰማህ ይሆናል እንጅ እነ አትናቴዎስ፣ እነ ዮሐንስ አፈወርቅ በሀገራችንም እነ አቡነ ተክለ ሐይማት፣ እን አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ኧረ ስንቱ! ወንጌልን ዞረው አስተምረዋል። አያችሁ ወገኖቼ የዘመኑ መናፍቃን ወንጌል የተሰበከ እነርሱ ከተወለዱ በኋላ ስለሚመስላቸው ከ 10 ዓመታት በፊት ወንጌል የተሰበከ አይመስላቸውም። ለዚህም ነው እንዲህ አይነቱን ትምህርት የሚያስተምሩት" በማለት የተሐድሶውን ትምህርት ውድቅ አደረገበት።

Ortodox Lezelealem Tnur with ፍሬ ማርያም ዘኦርቶዶክስ and 8 others

sher sher sher

37/ <u>የተሀድሶን የክፍታቸውን ሴራ ሁሉም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች እንድሰሙ</u>

ዛሬ 7:00 ሠአት ላይ ኢትዮ አአ በኦርቶዶክሥ ተዋህዶ የቁርጥ ቀን ልጆቸ መምህራን በፕሮቴሥታንት መለየት ሥብሠባ ላይ እያሉ በፖሊሥ መታገዱን ከቦታው አድርሠውናል እኛም አይዟችሁ ክርሥትና የአበባ ምንጣፍ

ሣይሆን የቀራኒዮ ጉዞ ነው ለወደፊት ገና ብዙ ፈተና ይጠብቀናል የዛሬው ምናልባትም መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ አይደለም ድል አለ በክርሥቶሥ shar eyadergachu የፕሮቴሥታንቱን ሴራ ለአለም የማሣወቅ የሀይማኖት ግዴታ አለባችሁ አለብን “መጋደላችን ከደምና ከስጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።” (ኤፌሶን 6፡ 12)

??ሮሜ 8፥ 35

ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?

??ሮሜ 8፥36

ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

??ሮሜ 8 ፥37

በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።

??ሮሜ 8 ፥38

ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥

ሮሜ 8 ፥39 ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

ክብር ሁሉ ለክርስቶስ አይሱስ ይሁን አሜን!!

15 hrs · Public

More

21 people like this.

Yeshi Konjo

ክርስቲያኖች ወገኖቼ በርቱ ይህ የሆነዉ ለበጎ ነዉ እመቤቴ ማርያም ከፈት ትቁምላችሁ እናንተ የአይሁድ ጅራቶች ደግም ደሰ አይበላችሁ ደስታችሁ በቅርብ ዉደ ሀዘን ስለሜቀየር

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለዘለአለም ትኑር

በአዲስ አበባ ሁለተኛ በሀገር አቀፍ ሶስተኛ የሆነው ይፋዊ ጸረ ተሃድሶ ጉባኤ በቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ለተሃድሶ ሚስማማ ስም ይፋ በማድረግ ቀጠለ

<u>38/ "ሐራጥቃ" ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ ማለት ነው "</u>

በመብራት ምክንያት ከመክፈቻ ሰአቱ የዘገየው ፕሮግራም ፀሎተ ሃይማኖት እና ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ በማድረስ ተጀምሮዋል የመጀመርያው ክፍል ትምህርትም መመህረ ወንጌል እና የቤተክርስቲያኗ የህግ ባለሞያ በሆኑት በመምህር አስቻለው ተሰጥቶዋል።

"ሐራጥቃ" በቲኦሎጂ ትምህርት ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ ማለት ነው።

የቤተክርስቲያኗ ሊቃውንት ይህን ስም እንድጠቀምበት ነግረውኛል" ያሉት

መምህር አስቻለው " ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ" የአባቶቻችንን አምላክ እግዚአብሄር ይመስገን "በሚለው ቃል ጉባኤውን ጀምረዋል።

ይህን ጉባኤ ምናደርገው የሃይማኖት ጉዳይ ስለሆነብን ተገደን ነው ያሉት መምህሩ "ሐራጥቃዎቹ" ተመልሰው ከጉኔ አብረውኝ ቢሰብኩ ደስታዬ ነው ሲሉ ክርስቲያናዊ ቃላቸውን ሰጥተዋል።

ካልተመለሱ ግን የቤተክርስቲያኗ ጫንቃ እንሱን መቸከም አይችልም ከዚ በላይ እያነባን ከቤተክርስቲያን ልንለያቸው ግድ ነው ብለዋል።

ስለ ቅዱሳን አማላጅነት ሐራጥቃዎቹ ተሳስተዋል ብለው ማስረጃ ከመጸሃፍ ቅዱስ ፍንትው አድርገው የምእመኑን ልብ አረስርሰዋል።

ሁለተኛው ትምህርት የዘመኑ የቤተክርስቲያኗ ጠበቃ የሆኑት ለፕሮቴስታንት ለአህዛብ መልስ በመስጠት ሚታወቁት በቤተክርስቲያን ጉዳይ ማይደራደሩት መምህር ምህረተ አብ ለሐራ ጥቃዎች "ወላዲተ አምላክ "ን በተመለከተ ላነሱት ምንፍቅና የማያዳግም መልስ ሰጥተዋል።

(የመምህራችንን ትምህርት በተከታታይ ለማድረስ እሞክራለው)

መምህር ምህረተ አብ በቱፊት ከአባቶቻችን እንደወረስነው መናፍቃን ሲነሱ የንስሃ የመመለሻ ቤተክርስቲያን "አረ ሲኖዶስ የለም እንዴ " እሲኪባል ድረስ ግዜ ሰጥታለች ብለው አስረድተዋል።

ክርስትና መጀመር ሳይሆን መጨረስ ነው ያሉት መምህሩ ይሁዳ ሃዋርያ ሣጥናኤል የመላእክት አለቃ ንስጥሮስ ጳጳስ ሆነው ጀምረዋል መጨረሻቸው አላማረም እንጂ ሲሉ ለዘመኑ ሃራጣቃዎች መንቂያ ደውል ደውለዋል።

"በእንተ ስማ ለማርያም " ብለው በስምዋ በልተው በስምዋ ተምረው

በስምዋ መምህር ተብለው እመብርሃንን በመሳደብ ለወደቁ ሁሉ "ድንግል ማርያምን ማንም ሊያከብራት አይችልም ሊቀድሳት አይችልም እኛ እስዋን በማክበር እንከብር ዘንድ ነው እንጂ እግዚአብሔር አንዴ አክብሮዋታል ከሱ በላይ አናከብራትም ልናዋርዳትም አንችልም እግዚአብሔር ያከበረው ማንም አያዋርደውም ራሱ ይዋረዳል እንጂ"

ሲሉ አጽኖት ሰጥተው ተናግረዋል።

ጥልቅ የሆነ የሚስጥረ ስጋዌ ትምህርት ከነገረ ማርያም ጋር አያይዘው በስነ መለኮት ትምህርት የሶስት ሴሚስተር ትምህርት ሚሆን አስተምረዋ።

በፕሮግራሙ ቋንቋዬነሽን ጨምሮ የመምህር ምህረተ አብ ወንድም የሆኑት በሚስጥራዊው ቡድን 2 ሲዲ ምክንያት ስለ እምነታቸው በእስር ቤት የተንገላቱት መምህርና ዘማሪ ኤርሚያስ ጨምሮ ዘማርያን ተገኝተዋል።

የአራት ጉባኤ መምህር የሆኑት በማህበረ ቅዱሳን ቲቪ ከሊቃውንት ጋር መልስ በመስጠት ሚታወቁት መጋቢ ሃዲስ ሚስጥረ ሥላሴን ጨምሮ ሌሎች መምህራን በቦታው ተገኝተው ሲያመሰግኑ ሲዘምሩ አምሽተዋል

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ

Like . Teddy Assefa Yadeta

አሜን አግዚአብሔር ሃይማኖታችንን ይጠብቅልን።ተዋህዶ ሃይማኖታቺን ማንም ትዉልድ እንደ ፈለጋ የሚቀያይራት እና የሚያድሳት አይደለችም። አመሰራረቷም በጋሻውና ሐርጥቃዎች ለምርምር የሚጠቀሟት የፍልስፍና ሃይማኖት ሳቶን ቃል ከሰዉ ተዋህዶ ስጋ ሁኖ የሰዉን ልጅ ለማዳን ስጋ የሆነው ቃል መከራን ተቀብሎ እስከ ሞት ሆነ ሞቶ ሰዉን ያዳነዉ ፍፁም በእየሱስ ክርስቶስ ደምና አጥንት የተሠሰረተች ሃይማኖት ናት።ታዲያ

በክርስቶስ እየሱስ የተመሰረተቺዉን ኦርቶዶክስ ተዋህዶን መቃወም ምነኛ እርኩሳዊነት ነዉ!እውነት ነዉ የምናገረዉ ታሃድሶ ሐርጥቃዎች ይጠፋሉ። በጋሻዉና ተከታዮቹም በእንብርክክ የተዋህዶ ቤት ፊት ተንበርክከዉ የድንግል ማርያምን ምልጃ ይማፀናሉ።

Like . Frehywot Mar

እኔ የምልው መላኩ ቅዱስ ገብርኤል ፀጋን የትሙላሽ ደስ ይበልሽ ካላት በክብር እኛ ምድራዊ ፍጥሩች ስልምን ልአምላክ እናት ክብር አንሰጥም ክብር እና ውዳስ ድንግል ማርያም ልስምሽ ይሁን

Like · Betelihem Jembere

እግዚአብሄር አምላክ እድሜና ጤናን ከበረከት ጋር ያድላችሁ በእምነታችሁ ያፅናችሁ የእናታችን የድንግል ማሪያም ምልጃ የቅዱሳን መላእክቱ ጥበቃ የሰማእታቱ በረከት የእግዚአብሄር አምላክ ምህረት አይለያችሁ

Like · Kasahun B Tilahun

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትላንትም ፣ዛሬም፣ነገም አንድ ናት ክርስቶስ ስጋውን ቆርሶ ፣ደሙን አፍሶልን የዳንባት እምነታችንን ከ እነዚህ ተኩላዎች የ መጠበቁ ሀላፊነት የ ሁላችንም ነው ።

Like · Temesgen Belachew

ልቤን ሃሴት ተሰማው ። ተዋህዶን ከችግር እያዎጣችኋት በመሆኑ አማኙ በሙሉ ተረጋግቶ እንዲያመልክ ሆኗል ። በርቱ በሁሉም የገጠሪቷ ኢትዮጵያ የዚህ አይነት ዘመቻ ያስፈልጋል አርሶ አደሩን ፣ ዞን እና ወረዳዎችን ሁሉ እውቅና ልንፈጥርላቸው ይገባል። በርቱ ድንግል ማርያም ትከተላችሁ።

Like · Senait Debebe

አቤት እንዴት ድስስ የሚል ፕሮግራም ነበር እንግዲህ እንንቃ የተዋህዶ ልጅ መተኛት ይብቃን አሁን በጣም በዝቶዋል በእመቤቴ እና በተክዬ ቀልድ የለም "ሐራጥቃ" አትርሱ ይሄንን!!

Like · Danu Moges

ሰው እንጂ እምነት አይታደስም እምነታችንን ለነጣቂ ተኩላ እንጠብቅ

Like · Asefa Shibeshi

እኛ የማሪያም ልጆች መቸም አንሸረሸርም ብዙ ምሁራኖች አላት ብዙም ምዕመና አላት ለማሪያም እናታችን የማንከፍለው የለም ልክ በግራኝ ግዜ ቤተክርስቲያንን ሲያቃጥልባቸው አቅም ቢያንሳቸው እራሳቸውን እያቃጠሉ ለኛ አወረሡን ታድያ እንድህ በቀላሉ የምትቀየር ይመሥለዋል ታህድሶ እግዚአብሔር አገራችንን ይባርክ

Like · Zeyede Atlabachew

መምህር ምህረት አብ የማያዳግም መልስ የስጠው ስለ ወላዲት አምላክ ነው ይህ መልስ አይደለም ሲጀመርም ድንግል ትፅንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ነውየሚለው ኢሳ.7፤14 እመ አምላክ ማለት የአምላክ እናት ማለት ነው ታዲያ መምህሩ ይህን ኢ መ/ቅዱሳዊ ት/ት እያስተማሩ በቂ መልስ ሰጥተዋል ያስብላል?ከእርሱ አንድ ያልተማረ ታናሽ ጴንጤ ይበልጠዋል ብዙ መልስ መስጠት ይቻላል ግን አስፈላጊ አይደለም

Matiwos Amare Tewahido

39/ በተሃድሶ መናፍቃን(ሀራ_ጥቃዎች) ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ታላቅ ጉባኤ በአዲሱ ሚካኤል ቤ/ክ ተካሂደ!!

ይኸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ጉባኤ ሳምንት ዕሮብ የሚቀጥል ሲሆን በዚህ ጉባኤ ሀራጥቃዎች ወደ እናት ቤ/ክ እንዲመለሱ ጥሪ ቀርቦላቸዋል። ሀራ ጥቃዎች ከሚዘሩት እንክርዳድ አንዱ የሆነው "ማርያም ወላዲተ አምላክ አትባልም" የሚለው ትምህርታቸውና በመጽሃፍም ካሳተሙት ከተወሰደው ላይ ሰፊ ትምህርት የተሰጠ ሲሆን የማርያምን የአምላክ እናትነትን ያረጋገጠ መልሶች የቀረቡበት ነበር ከዚህም ጋር የተነሳውና እውነትነት ያለው ነገር ቢኖር ማርያም የአምላክ እናት አይደለችም፣ የሚሉ የተወለደው አምላክ አይደለም ብለው ኢየሱስን እንደመካድ ነው ስለዚህም፣"ኢየሱስን የማያውቅ ማርያምን አይረዳትም" የሚለው ሃይለ ቃል ሁሉንም የገዛ ታላቅ ቃል ነው። ይህ የእንክርዳድ ዘር አስቀድሞ በ 428 የተነሳው የንስጥሮስ ሲሆን ማርያም የሰዋዊው ኢየሱስ እናት ብቻ ነች የሚለውን የሁለት አይነት ኢየሱስ ትምህርት ከንቱነት ያጋለጠ ነበር። ጉባኤው "ማርያም ማርያም እንበል" "ተዋህዶ ሃይማኖቴ የጥንት ነሽ የእናትና አባቴ ማህተቤን አልበጥስም " የሚለው መዝሙር ከተዘመረ ብኋላ ዘማሪ ልዑል ሰገድ "ቋንቋዬ ነሽ ድንግል" የሚለውን መዝሙር ካቀረበ ብኋላ ጉባኤው በጸሎት ተፈጽሟል።ሳምንት ሌሎች የሚዘሩ እንክርዳዶች ከማስረጃዎቻቸው ጋር ይቀርባሉ።

እግዚአብሄር የዛ ሰው ይበለን!!

ወስብሃት ለእግዚአብሄር!

Like . በእግዚአብሔር የተወደደ ምስጋና

አሜንን ! ማርያም እማምላክ አይደለችም ማለት ፦ በቀጥታ የጌታችንን የኢየሱስን አምላክነት መካድ ነው ።

እግዚኦ ይቅር በላቸው

Report · Wednesday at 8:03pm

ጥላና አካል

አሁን አሁንስ ፖለቲካ አደረጋችሁት። ስለ እግዚአብሔር ቃል መስበክ ትቶ ይሄ ሺህ ጊዜ በጋሻው ትዝታው ሲሉ መዋል፣ ሲዲ ላይ አንዲት ቃል ቆርጦ መክሰስ መሰለል የአለማውያን ተግባር ነው። ደግሞ እመቤታችን የእየሱስ እናት አይደለችም የሚል ተሃድሶም ሆነ ጴንጤ የለም። ለምን ይዋሻል። ልዩነቱ የምልጃና የስግደት ጉዳይ

ብቻ ነው ። ሁሌ ስለሰው የሚያወሩ ሰወች ተበለጥን ብለው የሚቀኑ ሰዎች ብቻ ናቸው። አንተና ዘመድኩንም የሆነ የአንድ አምባገነን ቡድን ሰላይ እልፍኝ አስከልካይ እንጅ መንፈሳዊ ሰው አትመስሉኝም። መመዘኛውንም አታሟሉም። ለምሳሌ ዛሬ ውይይት ከተደረገ በምስል ደግፈህ አቅርብልን። ከዚህ ውጭ ግን የምታደርጉት ግብግብ ለራሳችሁ ክብር እንጂ ለቤተክርስቲያን አይመስለኝም።

Like . Engidashet Kebede

ጥላና አካል# እስቲ ጥራት በአንደበትክ እንድትከብር ከአይንክ ላይ ቅርፊቱ እንዲነሳልክ የአምላኬ እናት የፈጣሪዬ እናት ብለክ

Like . Ermias Abiy

ሀይማኖት ማለት የፈጣሪን ህግ ጠብቆና ይዞ መገኘት ነው እንጂ ይህ ቃል

አልተመቸኝም ይቀየር እደዘመኑ ይታደስ ማለት አይቻልም እደዚያማ ከሆነ ሰማእትነት የሚባለው ባልነበረ ነበር ቤተክ/ን የምትመራበትኮ የራሷ ከአባቶቻችን የተቀበልነው ህግና ደንብ አላት መታደሱ ለምን አስፈለገ።

Like . Danny Mare

እንኳን ከዘመነ ግሪሳ ወደ ዘመነ ሀራጥቃ በሰላም አሸጋገራችሁ

Like . KT Tsegay

ER ere inezihi menafik menew erasatewni yezew yiwtu ke betekirisitiyan lela bayaweru yisalale durom kene begasaw mini litebek kenegwdegotu ayidenikenim leworo bela e/r yisitilin wenidimatineni

በእንተ ቤተ ክርስትያን ዘሻሸመኔ

ምንተ ንግበር

40/ ይህ ያለንበት ግዜ ለቤተ ክርስትያናችን እጅግ ፈታኝ ግዜ ነው በዛው መጥንም የፈተናዎቿን ምንጮችም በግልጽ ያሳየ ነው ይህም ማለት እንዳጠቃላይ በሃገር አቀፍ ደረጃ ያየን እንደሆነ ዋነኞቹ የፈተና ምንጮች

1. የተሃድሶዋውያን እንቅስቃሴ በያካባቢው በከፍተኛ ደረጃ መበራከት
2. የአባቶቻችን ዝምታ አንድም ችግሩን ካለመገንዘብ አልያም ደሞ በቸልታ ማየትና ጉዳዩን ከቤተ ክርስትያን ህልውና አንጻር ሳይሆን የግለሰቦች ሽኩቻ አድርጎ መመልከት

3. የምዕመኑ ለመረጃዎች ቅርብ ያለመሆን እንዲሁም ትምህርቶችንና መምህራንን አለመለየት

በከተማችንም እየታየ ያለው ችግር ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን አሁን የህዝቡ ግንዛቤ ቢሰፋም በተደራጀ መልኩ እንዳይቃወምና ለቤተ ክርስትያን ሰላምና አንድነት ዘብ እንዳይቆም ይህን ሚና ሊጫወቱ የሚችሉለትን ሰዎች አንድም በጥቅም በመደለል አልያም በማዋከብና በማሰር የህዝቡን ጥያቄ ለማጥፋት ጥረት እየተደረገ ነው። ነገር ግን" አለባብሰው ቢያርሱ..." እንዲል የሃገሬ ሰው ጉዳዩን ሸፋፍኖ ለማለፍ መሞከር ቤተ ክርስትያኒቱን ለባሰ ችግር ይዳርጋት እንደሆን እንጂ የሚፈለገውን ሰላም አያመጣም።

ስለሆነም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን መለየትና በዛ ደረጃ ሃላፊነታቸውን መወጣት ይጠይቃል።

እኒህም:-

1. አባቶች ስህተቱን ስህተት በማለት የእረኝነት አደራቸውን ሊወጡ ይገባል እንዲሁም ቀሚስና ቆቧን ብቻ ይዘው ሥርዓቷን ለማጥፋት የሚተጉትን ለይተው ማወቅና በድፍረት ማውገዝ አለባቸው

2. ምዕመናን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በትኩረት በማጤን በተደራጀ መልኩ መልስ መስጠት አለባቸው ነገር ግን ሁሉን በሥርዓትና በትዕግስት መያዝ ይጠበቅባቸዋል

3. የመንግስት አካላት ሰላም ለማስፈን ሲባል አጥፊውን በዝምታ አልፈው ንጹሁን በማሰር ሳይሆን የገለልተኛነት ሚናቸውን መወጣት አለባቸው ዞሮ ዞሮ ከተማችን ሰላም ብትሆን ጥቅሙ የጋራችን ነውና።

አምላከ ቅዱሳን ቤተ ክርስትያናችንን ከፈተና ይሰውርልን!

ይቆየን።

በእንተ ቤተ ክርስትያን ዘሻሸመኔ

41/ ክፍፍሉን የምንቃወምበት ሌላኛው ምክንያት:

እንደሚታወቀው የሻሸመኔ ህዝበ ክርስትያን ሰላሙ መታወክ ከጀመረ ሰነበተ። ለዚህ ሰላም መደፍረስ በዋናነት ደግሞ የሚከተሉት አካላት በአንድም በሌላም መንገድ ተሳታፊ ናቸው:

1.የተሃድሶ መናፍቃን አራማጆች እነኚህ አካላት ቤተ ክርስትያንን ተጠግተው ከደጇ በሚፈልቅ በረከት አድገው ጎልምሰው በእርሷው ላይ ተረከዛቸውን ያነሱ የእናት ጡት ነካሾች ናቸው። እነዚህም:-

& በሥርዓቷ መኖር ሲሳናቸው ሥርዓቷን ማብጠልጠል መጀመራቸውና ልናድሳት ይገባል ማለታቸው

& ከአባቶች እግር ስር ቁጭ ብለው ሳይማሩ የአባቶችን ትምህርት መናቃቸውና ምስጢሯን ሳይረዱ ነጠላ ጥቅስ እየጠቀሱ ተነጥለው መቅረታቸው ሲሆን ይህ ሸፍጥ ሲታወቅባቸው ደግሞ አላማቸውን ባልተረዱ አባቶች አልያም የእነርሱ ተባባሪ

በሆኑት ፊት ተወዳጅ መስለው ለመታየት መጣራቸው ነው

2. አገልግሎትን ከተራ የቢሮ ሥራ ነጥለው የማያዩና እነርሱ ኪሳቸው ካልጎደለ ቤተ ክርስትያን ብትታወክ መንጋዋም ቢበተን ግድ የማይላቸው

የመንጋው እረኞች(ጥቂት አገልጋይ ካህናት) እነዚህኞቹ ደግሞ የተሃድሶዋውያን ስውር ዓላማ ወይ አልገባቸውም አልያም ለማወቅና ትምህርታቸውን ለመመርመር አይሞክሩም ከፍ ሲልም ቢያውቁትም ግድ አይሰጣቸውም ዛሬ ቤተ ክርስትያንን ያወከ አስተምህሮ ነገ በህልውናዋ ላይ የሚያስከትለው ጠባሳም አይታያቸውም።

3.ለቤተ ክርስትያን "ባይተዋር" የሆኑ ምዕመናን እነዚህኞቹ ደግሞ ለእያንዳንዱ ችግር ሁል ግዜ እንግዳ የሚሆኑና በቤተ ክርስትያን ላይ የተከሰተው ችግር እነሱን እንደማይነካ የሚያስቡ ሲሆን በዚህም ምክንያት ችግሩን ከመሰረቱ አይረዱትም ከዚህ ይልቅ በሰፈር በሚነዛ አሉባላታ ተጽዕኖ ምክንያት ልባቸው ስለሚሸረሸር ሳያውቁት የክፉች ስውር አጀንዳ መፈጸሚያ ይሆናሉ።

ሌሎችም አካላት እንዳሉ ሆኖ ከላይ የጠቀስናቸው ግን በመጀመሪው ረድፍ የሚቀመጡ ናቸው።

&& እኒህን ሃሳቦች በአዕምሯችን ይዘን አሁን ላይ የሚነሳውን የአብያተ ክርስትያናት የአስተዳደር ክፍፍል ጉዳይ እንመልከት መቼም ማነጻጸሪያ ነጥቦቻችን የሚሆኑት:-

ሀ. በአንድ አስተዳደር ስር መሆናችን ያስከተለብን ችግር(በእርግጥም ኖረውም ከሆነ)

ለ. አብያተ ክርስትያናቱ ወደ ክፍፍል ሲገቡም እነዚህን ችግሮች የመፍታት አቅማቸው ምን ያህል እንደሚሆን

ሐ.ወደ ክፍፍሉ ስንመጣ ልናጣ የምንችላቸው የእንድነታችን ጥቅሞች በሚዛናዊነት መታየት መቻላቸው

መ. በተለይ በዚህ ወቅት ወደ ክፍፍል ስንመጣ ሊገጥሙን የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለአብነትም ያህል የተሃድሶ አራማጆችን እንዲህ በአንድነት ቆመን እንኳን ነቅሎ ለማስወጣት ይህን ያህል ፈተና ውስጥ ከገባን ነገ አንድ መናፍቅ ተነስቶ በአንድ ቤ.ክ ተቃውሞ ቢደርስበትና ወደ ሌላ ደብር ቢሄድ እዛ ድረስ ሄደን ለመቃወም የሚያስችል ተሰሚነት ማግኘት መቻላችንን

ይህ ከሆነ ደግሞ አንከፋፈልም የሚል አቋም መያዛችን ይህን ያህል ችግር የሚሆነው ለማንና በምን ምክንያት ነው? ሁላችን የምንተዳደርበት ህገ ቤተ ክርስትያን (ቃለ አዋዲ) የሰበካ ጉባኤ መቋቋሚያ አዋጅን በሚመለከት ባስቀመጠው መሰረት የተቀራረቡ አብያተ ክርስትያናት ከተስማሙ በአንድ ሰበካ ጉባኤ ሊደራጁ ይችላሉ ካለ(ቃለ አዋዲ አንቀጽ ፫) እኛ ደግሞ ለሁሉ ምሳሌ በሚሆን መስማማት ይህን ያህል ዘመን አብረን መዝለቅ ከቻልን ለያውም እጅግ ስኬታማና ዘመናዊ ከሆነ የሰበካ ጉባኤ መዋቅር ጋር(ሻሸመኔ ላይ አንድ ጀማሪ ዲ.ን በየትኛውም ደብር ቢመደብ መነሻ ደሞዙ በዲፕሎማ ደረጃ ሲሆን እንደቆየበት የሥራ ዘመንም የደሞዝ እርከን ይሰራለታል አንድ ጀማሪ ቄስም ቢሆን አሰራሩ ተመሳሳይ ሆኖ መነሻው በመጀመሪያ ድግሪ የደሞዝ እርከን ነው) ይህን ያህል የክፍፍሉ አጀንዳ አንገብጋቢ ለምን ሆነ?

ይህ በእንዲህ እንዳለ መጤን የሚገባቸውም ጉዳዮች ትኩረት ሳያገኙ እንዲሁ በግብታዊነት ተከፋፈሉ ማለት ለማንም ቢሆን ግልጽ ሊሆን አይችልም። ስለዚህም የትኛውንም ሃሳብ ለቤተ ክርስትያን ሰላምና አንድነት እስቀጠቀመ ድረስ ለመቀበል አናመነታም ነገር ግን ጥቂት ግለሰቦችን ላለማስከፋት በሚል ግን ታሪካዊ ስህተት መቼም ቢሆን አንሰራም!!!

የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የመላዕክት ጥበቃቸው የቅዱሳኑ ጸሎት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን!

ይቆየን።

በእንተ ቤተ ክርስትያን ዘሻሸመኔ

42/ እንከፋፈል ከሚለው ጭንብል ጀርባ ያለው እውነታ(Behind the mask of the presumed "decentralization")

ውድ የገጻችን ተሳታፊዎች እንደምን አደራችሁ ለዛሬ ከላይ ባነሳነው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥቂት ሃሳቦችን እናነሳለን እንደተለመደው የተሰማችሁን ጻፉልን ሃሳባችንንም ከወደዳችሁት ለሌሎች እንዲደርስ share በማድረግ አግዙን።

:::::::::::::

ቀደም ባሉ ጽሁፎቻችን በተለይ እንደ ሻሸመኔ ነባራዊ ሁኔታ በአንድ ሰበካ ጉባኤ መመራት የሚያስ ገኘውን ጥቅም ማስነበባችን ይታወሳል ነገር ግን አንዳንድ ወገኖች "እንከፋፈል የሚል ሁሉ ተሃድሶ ነውንዴ?" የሚል ግትር ሙግት ያነሳሉ ። እኛ ይህንን አላልንም ቀድሞ ይህን የ"እንከፋፍላችሁ" ጥያቄ በጽኑ ሲቃወሙ የነበሩ አባቶቻችንም(በህዝብ የተወከሉት) ይህን አላሉም። ዋናው ጥያቄ የነበረው ቤተ ክርስትያንን ሲያምሱ የነበሩና መረጃም የተገኘባቸው የምንፍቅና አራማጆች ጉዳይ ወደ ጎን ተትቶ ይህንን ክፍፍል በቀጭን ትዕዛዝ ተግባራዊ ማድረግ የተፈለገው ለማን ታስቦ ነው። መጀመርያ በአንድ ሰበካ ጉባኤ መተዳደራችን ለብዙዎች ምሳሌ መሆኑ ቀርቶ ድንገት ስጋት ሆኖ የታየው እውነት ከሃይማኖታዊ ችግር ይልቅ

አስተዳደራዊ ጉዳይ በልጦ ነውን?(ተሃድሶነት በቤተ ክርስትያን ላይ ያንዣበበ የሃይማኖት ህጸጽ ነውና) እኛ በአንድ አስተዳደር ሥር መሆናችን የሚያስገኘውን ጥቅም ዘርዝረን ባስረዳነው ልክ እነርሱም መከፋፈሉ የሚያመጣውን ትሩፋት ለምን አይነግሩንም ?

አለያም ጥናት እናደርግበት ዘንድ ለምን ግዜ አልሰጡንም?

ከዚህ ይልቅ ግዜ የማይሰጠውንና ቤተ ክርስትያንን እያመሰ ያለውን የተሃድሶ አራማጆችን ጉዳይ ቸል ማለትን ለምን መረጡ?

እውነታው ህይ ከሆነ ደግሞ ክፍፍሉ የሚያመጣውን ችግር ለማሰብ ነብይ መሆን አያስፈልግም። በዚህ ወቅት እንኳን አንዳንድ ቀንደኛ የተሃድሶ አቀንቃኞች ማልያቸውን ቀይረው የ አባቶች ተቆርቋሪ ሆነው ቀርበዋል።

ይህን ሁሉ ሃሳብ ለመጠቅለል ብንሞክር በዚህ ወቅት እንከፋፈል የሚሉ አካላት አንድም ክፍፍሉን ተከትሎ በሚመጣው አስተዳደራዊ መዋቅር ቁልፍ ቦታ እንዲያገኙ ተስፋ የተሰጣቸውና አልያም አብዛኛው ምዕመንን ስውር ዓላማቸውን ተረድቶ ያገለላቸው የተሃድሶ አራማጆች ብቻ ናቸው "ግርግር ለቀጣፊ ይመቻል "እንዲሉ።

እግዚአብሔር ደግ ዘመን ያምጣልን።

ይቆየን!

Like . Reta Feker

ተሀድሶ ሰው ሰራሽ እና ዘመን አመጣሽ የሆነ መሪሆቻቸው በጋጥወጥ ስነ-ምግባር የተሞሉ መሆናቸው የታወቀ ና ፀሀይ ያሞቀው ነገር ነው : ኢትዩጲያናን ከአለም ለየት የሚያደርጋት ክርስትና ነው

አንድ ሰባኪ መምህር ተወዳጅ እና ተደናቂ የነበረ የሰዎች አድናቆት ከፍ

ባለ ቁጥር እሱ ራሱን ስቶ የፈጠረው ተሃድሶ ፀ-በጋሻው መሆኑን እኛ ውላችንም ምናውቀው ጉዳይ ነው ከሚገርመው ነገር የተሃድሶ አምልኮት በአዋሳ በአለም ጤና

 አ.አ በናዝሬት በተለያዩ የኢትዮጲያ ክፍሎች ተከሰቶ ወጣቶች በሚያስደንቅ ትግል ቤተክርስቲያናቸውን አስከብረዋል በሻሸመኔ ያለውን የአይማኖት ነውጥ የድንግል ማርያም ልጅ ክርስቶስ ፍፃሜውን ያሳምርልን.....

Coment . Dawit Tilahun

እውነት እንጂ ሀስት የት ይደረስላ የክርስቶስ ሥራ ነው ጌታ ከንተጋራ ይሁን ።

Coment . Yehuala Hailu

እመኑኝ ተሃድሶዎች በሀይማኖት መታደስ ይቻላል።ሀይማኖትን ለማደስ መነሳት ግን ፍፁም ስህተት(ኑፋቄ) ነዉ፤ እግዚአብሄንም መሳደብ ነዉ "ስራህ ስህተት አለዉና እኛ እናስተካክልልህ" ማለት ነዉ።ልብ ይስጣችሁ!

Coment . Kenfe Pandulem

Koy ena melw yethadsa teregume mend new begashawes ewne tehadso new ?

ኤፍራታ የድንግል የማርያም ባሪያ reading እኔስ ማርያምን ወዳታለሁ

by Daniel King

43/ *የ 3/2/2008* ቱ ጸረ ሐራጥቃ ይፋዊ ጉባኤ እንድምታ

ክፍል__ሁለት

እንደተለመደው ይህን ተከታታይ ፖስት share በማድረግ እንዲሁም ፖስት በማድረግ እንድታጋሩ ይሁን

By Daniel king

ክርስትናን ለማጥፋት የሰይጣን ማህበርተኞች የተሰበሰቡበትን የዘመነ ሰማእታት ስብሰባ የገለጡበትን መንገድ አይተናል ከዘመነ ሰማእታት በውሃላ ክርስቲያኖች ፈርተው ከተደበቁበት ዋሻ ብቅብቅ ባሉበት ዘመን የሰይጣን ማህበርተኞች ክርስቲያንን ለማጥፋት ቅዱሳን መጻህፍትን ማቃጠልና ማጥፋም የጀመሩበት ዘመንን በምናብ አሳይተውናል መምህርሩ። በዚ ጥፋ ምክንያት እስካሁንም ያልተገኙ መጸሃፍት አሉ መጸሃፈ ሄኖክ በኢትዮጲያ ባይሸሽግ ኖሮ አለም ላይ ጠፍቶ ነበር።ጉባኤውም ክርስትናን በዚ መንገድ ማጥፋት እንደማይቻል ሲገልጡ<< መጸሃፍ ቅዱስን ከአለም ብናጠፋ አለም ላይ ያሉ ክርስቲያኖች በአንድ ቦታ ቢሰበሰቡ አንድ አንድ ጥቅስ ቢያዋጡ ደግመው ይጽፉታል እንዲሁም ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ከነ ትርጓሜው በጉንጫቸው በአምሮአቸው የያዙ ሊቃውንት ብዙ አሉ ስለዚ ደግመው ይጽፉታል>>> ብለዋል

መምህሩ ቀጥለውም የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለማጥፋት የወሰኑበት ዘመንን ታሪካዊ ዳራ አሳይተዋል<<የኢትዮጲያን ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት መጸሃፋቸውን ከማቃጠል እንያዘው ልብሳቸውን እንልበስ መስቀላቸውን እናድርግ ከዛ መጸሃፉን እንበርዝ ፈራጁን አማላጅ እያልን እናስታቸው ከዛም ወደ በዚ ተስማምተን ሃገራቸው እንግባ ብለው ወሰኑ ከዛም

ምእራባዊያን ወደ ሃገራችን ገቡ››› ሲሉ ገልጠውታል

አንድም ሃራጥቃ አሁን አፈጠጠ እንጂ የነበረ በየትውልዱ የተነሱ ሊቃውንት የመከቱት መሆኑን ሲያጠይቅ አንድም ካቶሊኮቹም ሆነ ፕሮቴስታንቶቹ ሁለቱም በየዘመናቱ ወደ ሃገራችን ሚሲዮን መስለው ገብተው የተለያዩ የማጥፋት ዘመቻዎችን በኢትዮጲያ ቤተክርስቲያን ማካሄዳቸውን ነው።

አንድም በሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ውስጥ ገብተው ኦርቶዶክስ መስለው የቤ/ክርስቲያኒቷን አስተምህሮ የለወጡት ፕሮቴስታንቶች “ማር ቶማ” የተባለ ቤተ ክርስቲያን አቋቋሙ። እነዚህ የተገነጠሉትን እምነታቸው ፕሮቴስታንት ስለ ሆነ “ኦሬንታል ፕሮቴስታንት - Oriental Protestant ” ይሏቸዋል፡ሚለውን ሲያበረታ ነው።

አንድም በሱሲኒዮስ ዘመን ንጉሰ ነገስቱን አሳምነው ከ8000 በላይ ኦርቶዶክሳዊያንን ደማቸውን ማፍሰሳቸውን ሲያጠይቅ ነው። አንድም አልፋንዚ ሜንዴዝ የተባው ሚሲዮናዊ የቅባትና የጸጋ ምንፍቅና ትምህርቶችን ለሁለት ኢትዬጲያን አስተምሮ አሳምኖ ሲሄድ ‹‹በኢትዬጲያ ሁለት እሾክ ሰክቼባታለው ለዘመናት ይወጋታል ›› ሲል የተናገረውን ሲያጠይቅ ነው።

ሲቀጥሉም ‹‹ሰይጣን ከውጪ ሆኖ ቤተክርስቲያናችንን ማሸነፍ ስላልቻለ ፕሮቴስታንታዊ የተሃድሶ ጀሃድ (ሃራጥቃ) በቤተክርስቲያን ላይ አውጀዋል። ይህ መመርያ እየተሰራበት ዛሬ በየክፍለ ከተማው በየቀበሌው እያያቹ ነው የማ መፈንጫ እንደሆንን ቁጥራችን በምን ያህል እንደቀነሰ የኛው ህዝብ ነው እየሄደ ያለው ሌላ አይደለም። እየወሰዱ እያታለሉ ጌታን የተቀበለውን

ህዝብ እንደ አዲስ ጌታን ተቀበል እያሉ አውሬ እንኳን የራስዋን ልጅ አድና በማትበላበት ምድር እነሱ የራሳቸውን ወገን አድነው እየበሉ ክርስቶስን ያመኑ እያስመሰሉዋቸው ከክርስቶስ መንገድ እያወጡዋቸው ነው።››› ሲሉ የውጪ ውጊያን ገልጸዋል ከምራብያን በወረሱት ወፍ ዘራሽ ትምህርት የራሳቸውን ወገን እያደኑ ከክርስቶስ እቅፍ እያወጡ ለዘመናት የኖሩት የሃገር ልጆች ነበሩ ና ወገን ነበሩና። እነዚ የሉተሪዝም ተላላኪዎች ናቸው ማጣቀሻቸው የውጪ መጸሃፍት ማስረጃቸው ሉተር የሆኑ ቅጥረኞች።

መምህሩ ቀጠሉ ‹‹አሁን ይህም አላዋጣ ሲላቸው ውስጣቸው እንግባ ብለው ቤተክርስቲያን ውስጥ ገቡ።እንዴት አድርገው ቤተክርስቲያን ውስጥ ገቡ?? በኛው ሰዎች እኔ እጄ ላይ ባለ ማስረጃ ነው ምናገረው በካህናት ማሰልጠኛ በየ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቱ በየኮሌጁ በየ ሰንበት ትምህርት ቤቱ ውስጥ ሰርገው በመግባት ከደብር አለቆች ጀምረው ውስጥ ለውስጥ ሆነው ቤተክርስቲያኒትዋን ‹‹ምን አለበት›› እያሉ የማታምነውን እንደምታምን የምታምነውን ደግሞ እንደምታምን አድርገው ጥላሸት በመቀባት ቤተክርስቲያንዋን ሰው እንዲጠላና ህዝቡ እንዲመነፍቅ አመለካከቱ ኦርቶዶክሳዊነቱ እንዲጠፋ ይህን ሸርበዋል ዘራም እኔ እነግራቹሃለው መቼም አያቆሙም።››

ከደብር አለቆች ጋር ሸርበው ምንፍቅናን ሚያስተምሩ በዮሴፍ ቤተክርስቲያን የደብሩ አለቃ እና የሃራጥቃ ወታደሮች ሚያደርጉትን በማስረጃ ስለሚታወቅ በማስረጃ ማቅረብ እችላው ለንግግሩ

እንዲሁም በብሄረ ጽጌ ማርያም ቤተክርስቲያን ነአኩቶ እንኩቶ በመባል ሚጣወቁት የደብር አለቃን እንደማስረጃ ማየት ይቻላል በሥላሴ መንፈሳዊ

ኮሌጅ የተደራጁ የሃራጥቃ ሰራዊት አሁንም አሉ ከዛ ወጥተው ስብከተ ወንጌልሃላፊ እንዲሁም ሰባኪ ሆነው ወረቀት ስላላቸው ብቻ ህዝቡን ምንፍቅና እያጠጡት ነው። በየሰንበት ትምህርት ቤቱ በመግባት መንፈሳዊ አገልግሎትን ማዳከም በክርክርና በሁከት ምእመኑን መሸበብ እንዲሁም በውስጥ ማህበር በመስራ ለብቻ እየተገኛኙ ምንፍቅናን መማማር ሚጠቀስ ነው። እንቀጥላለን

ይትባረክ እግዚአብሄር አምላከ አበዊነ

የባ/ዳር ካቴድራል መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ሰ/ት/ቤት ገጽ ፔጁን ላይክ በማድረግ መንፈሳዊ እውቀትዎን ያጎልብቱ

<u>44/ ማን ይታደስ?</u>

(የትነበርክ ታደለ)

አዳሾች ምንድነው የምታድሱት?

* አምስቱ አእማደ ሚስጢራት የቤተክርስቲያናችን የእምነት

መሰረቶች ናቸው! አይጨመርባቸውም! አይቀነስባቸውም!

* ሰባቱ ሚስጢራተ ቤተክርስትያን የእምነታችን

መመርያዎች ናቸው! ምንም አይጨመርባቸውም!
አይቀነስባቸውም!
* የጸሎትና የምስጋና ልሳኖቻችን የሆኑት የቅዱስ ያሬድ ሶስቱ
ዜማዎች (ግእዝ፣ እዝል፣ አራራይ) እንዲሁ በፍጹም አለማዊ
ቀለም አይነካቸውም። አይቀየጡም!
* አባቶቻችን በተለያዩ ወቅቶች በቅዱስ በሲኖዱስ
የሚወስኑልን ማናቸውም ውሳኔዎች መርሀዎቻችን ናቸው!
አይበረዙም! አይከለሱም!
* ሀይማኖታችንን የምንሰብክባቸው የአነጋገር ለዛና የቋንቋ
ቃና እንዲሁ በዘመናዊነት ፋሽን የማይቃኙ የራሳችን
መለያዎች ናቸውና አይታደሱም!
(((እንግዲህ ምኑን ታድሱታላችሁ? አዎ የሚታደስ
አይጠፋም!!!
~ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ተሰግስገው የስጋ ስራ የሚሰሩ
ሙሰኛ፣ ሌባ፣ ቃላባይ አገልጋዮች!
~ በጥንቆላ፣ በዛርና በአጋንንት መልእክተኝነት የሚመላለሱ
ምእምናን!
~ በሰበካ ጉባኤ እና በቤተክህነት ውስጥ የተጎሰጎሱና
ስለእምነቱ ምንም እውቀት የሌላቸው ፖለቲከኞች!
~ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ተጎልተው ሀሜትና ዝሙት
የሚያስፋፉ ወጣቶች!.....እነዚህ ናቸው መታደስ
ያለባቸው!...ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰው አላወቀብንም ብለው

የሌላውን እምነት ለማስፋፋት ቤተክርስትያን ውስጥ
የሚሸሎከለኩ አስመሳዮች ናቸው መታደስ ያለባቸው! በተረፈ
ቤተክርስትያን ዶግማዋም ሆነ ቀኖናዋ እንዲሁ በሂያጅ መጪ
የማይታደስ የማይቀለበስ በጽኑ መሰረት ላይ የቆመ መሆኑን
እንመሰክራለን! እናንተው ታደሱ!

የባ/ዳር ካቴድራል መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ሰ/ት/ቤት ገጽ ፔጁን
ላይክ በማድረግ መንፈሳዊ እውቀትዎን ያጎልብቱ
<u>45/ ለ ተሐድሶዎችና ጭፍሮቻቸው</u>
የማቴዎስ ወንጌል 16፥18
እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ
ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።
የሉቃስ ወንጌል 12፥8
እላችሁማለሁ፥ በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ሁሉ፥ የሰው ልጅ
ደግሞ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል፤
ቅድስት ቤተክርሰቲያናችን አውደ ምህረት ዘርግታ ኑ ልጆቼ
ብላ አምላካዊና ፍቅር በተሞላበት ጥሪ ጠርታን ሳለ ማዕጁን
ረግጠን በየአዳራሹ መሰብሰብ ለምን እፈለግ? ለምንስ በስሟ
ለመሸሸግ ተፈለገ? ቤተክርስቲያናችን ክርስቶስ በደሙ
የመሰረታት ነች ማንም እየተነሳ የፈለገበት ቦታ ሊያደርጋት

አይችልም። ማንም ሲፈልግ በድንጋይ፣ በጣዖታ ያምልክ በኋላ
በስራው ይጠየቅበታል ግን የእውነተኛይቱን ሐይማኖት ስም
ከለላ እያረጉ መጠቀም ለምን አስፈለገ? ራሳቸውን ለምን
አይችሉም? ታዖሎጎስም ሆነ ቃለ ዓዋዲ የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ስር ለምን ይደበቃሉ? እኛስ የሰው ተከታይ
ለምን እንሆናለን? እውነት የእውነተኛይቱ ሐይማኖት ተከታይ
ከሆንን ስለ ተሐድሶና ተከታዮቹ ሲነሳ ለምን እንጨረጨራለን
የተለየ ጥቅምና ግንኙነት ከሌለን በስተቀር? የተሰማንን
ስሜት መግለጽ እንችላለን ግን ጥቅስ ስላወቅን ብቻ
ያለቦታው እያስገባን ለማደናገር አንሞክር ። መሰል መልስና
አስተያየት ለምትሰጡ ራሳችሁን መርምሩ።
የዮሐንስ ወንጌል
9÷22
ወላጆቹ አይሁድን ስለ ፈሩ ይህን አሉ፤ እርሱ ክርስቶስ ነው
ብሎ የሚመሰክር ቢኖር ከምኩራብ እንዲያወጡት አይሁድ
ከዚህ በፊት ተስማምተው ነበርና።
እናንተም እውነተኛውን ነገር ብትመሰክሩ
ጥቅማችን፣ምቾታችን ይቀርብናል ካላላችሁ በስተቀር
ቤተክርስትያንን ተመሳስለው ከሚመጡ ተኩላዎች የመጠበቅ
ሃላፊነት አለባችሁ። እያንዳንዳችንስ ቤተክርሰትያን
አውደምሕረት አዘጋጅታ ኑ ልጆቼ እውነተኛውን ወንጌል
ተማሩ ስትለን ለምን ወደ አዳራሽ መፈርጠጥ አስፈለገ?

ወደ ሮሜ ሰዎች 13፥14

ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም

እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።

መጽሐፈ ምሳሌ 18፥1

መለየት የሚወድድ ምኞቱን ይከተላል፥ መልካሙንም ጥበብ

ሁሉ ይቃወማል።

ለሠዎች ጥብቅና ከምንቆም ይልቅ ለቤተክርስቲያን ብንቆም

ይሻላል።

መጽሐፈ ምሳሌ 21፥25

ታካችን ምኞቱ ትገድለዋለች፥ እጆቹ ይሠሩ ዘንድ

አይፈቅዱምና።

በመጨረሻ በወንጌሉ እንደተጠቀሰው ፦-

የማቴዎስ ወንጌል

10፥26

እንግዲህ አትፍሩአቸው፤ የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም

የተሰወረ ምንም የለምና።

10፥28

ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን

አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ

የሚቻለውን ፍሩ።

10፥31

እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ።

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ አስራት ሀገርሽን

ቤተክርስቲያናችንን ከተኩላዎች ጠብቂልን።

46/ ዮዲት (ጉዲት) ማን ነበረች ?

ዮዲት (ጉዲት) የቤተ እስራኤሎች ንጉሥ የነበረው የጌዴዎን ልጅ ነበረች። የተወለደችው በጎንደር ክፍለ ሀገር ፥ በስሜን አውራጃ፥ በበየዳ ወረዳ ልዩ ስሙ ማጀ ከተባለ ቀበሌ ነበር። አባትዋ ጌዴዎን በ 858 ዓ.ም ከአኩስሙ ክርስቲያን ንጉሥ ከአንበሳ ሰገድ (ሕዝብ ናኝ) ጋር ተዋግቶ ድል ሁኖ ተማረከ። ከዚያም ሞት ተፈርዶበት ሰቅለው ገደሉት። ልጁ ዮዲት ይህን እንደሰማች ወደ ቡግና (ላስታ) ሂዳ የዛጊዌ ልጅ ከሆነችው ከመራሪ ልጅ ከእንቆጳዝዮን በግርድና ሥራ ተቀጠረች። ከዚያም በሂደት በቅልጥፍናዋና በጀግነቷ የእንቆጳዝዮን ጦር አዛዥ ሆነች። ይህን ዕድገቷንና ዝናዋን የሰሙ የስሜን፥ የጠለምት፥ የወገራ፥ የወልቃይትና ጠገዴ ቤተ እስራኤላውያን ወገኖቿዋ እየሄዱ ጦሯን ተቀላቀሉላት። ይህን የሰማው የአኩስሙ አፄ አንበሳ ሰገድ ጦሩን ይዞ ዮዲትን ለመውጋት ወደ ላስታ ዘመተ። ዮዲትም የራሷን ጦር ይዛ ላስታ ከመደረሱ በፊት በለሣ ላይ ልትገጥመው ወደ በለሣ ተጓዘች። የአፄውን ጦር ድል የምታደርግበት መላ ወይም ዘዴ ዘየደች። መላውም ይህ ነበር። የላይ በለሣ ሕዝብ በየቤቱ ጠጅ እንዲጥል አዘዘች። የአፄው ሠራዊት ከዚያ አካባቢ እንደደረሰ በየቤቱ ሲገባ ጠጅ በጋን ሞልቶ ሲያገኝ ጠጁን በብዛት ጠጣና ሰክሮ ተኛ። ወድያውም ዮዲት ሠክሮ የተኛውን ጦር በቀላሉ በቁጥጥር ሥር አደረገችው። አፄው ጥቂት

የሠራዊቱን አባላት ይዞ ወደ ዳሞት ሸሸ። በዚህ ምክንያት ያ ቦታ ''መልዛ/መላ ይዛ'' እየተባለ እንዲጠራ ሆነ።

ዮዲትም ወደ አኩስም ሂዳ ካሃናቱን ገደለች፣ ቤተ ክርስቲያናቱን አቃጠለች። የካህናቱን መገደልና የቤተ ክርስቲያናቱን መቃጠል ስትሰማ ክርስቲያኒቱ የላስታዋ አለቃዋ ÷ እንቆጳዝዮን÷ ወደላስታ እንድትመጣና ለፍርድ እንድትቀርብ መልክት ለዮዲት ላከች። ዮዲት ግን በየዳ ላይ ወጥታ አሻፈረኝ አለች። እንቆጳዝዮንም የላስታንና የዋግን ጦር ይዛ ወደበየዳ ዘመተች። በጣልያን ወረራ ጊዜ የበየዳው ደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ ጦር የላስታውን የልጅ ወሰን ከበደን ጦር ድል ባዳደረጉበት ሁኔታ ፤ ዮዲትም በየዳ ላይ 2 ቀን የፈጀ ጦርነት ተደርጎ ዮዲት የእንቆጳዝዮንን ጦር ድል አድርጋ እንቆጳዝዮንን ራሷንም ማረከቻት። ከዚያም ዮዲት የእንቆጳዝዮንን ልጅ መራ ተክለሃይማኖትን አገባች። 41 ዓመት ኢትዮጵያን ጠቅልላ ከገዛች በኋላ ሞት አይቀርምና በ919 ዓም. ሞተች። ባልዋ መራ ተክለሃይማኖት ''አፄ ዛጉዌ ንጉሠ ነገሥት '' ተብሎ በ1919 ዓ.ም አኩስም ላይ ነግሦ የዛጉዌን ዳይናስቲ ወይም ሥርዎ መንግሥት መሠረተ። ይህ ዳይናስቲም ወይም ሥርዎ መግሥት እስከ 1270 ዓ. እ ድረስ ቆይቶ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት አደራዳሪነት በሰላም ወደይኩኖ አምላክ ተላለፈ።

አንዳንድ ሰዎች ዮዲት ሲዳማ ናት ÷ ሐድያ ናት የሚሉ አሉ። እናንተስ ምን ትላላችሁ ? ስለዮዲት ያነበባችሁትን ወይም ከአፈ ታሪክ የሰማችሁትን ጣፋ እስቲ እናመሳክረው።

ከበደ አ. ቦግ አለ !

47/ የእግዚአብሄርን ቃል በዘመናዊ አመክንዮ ማብጠልጠል የጀመረ እግዚአብሄርን ቢክድ አይገርምም!!!

የራስ ምስክርነት ከምንም በላይ ነው ስለዚህ

መናፍቃን የሚያመልኩት ኢየሱስ መፅሃፍት የሚመሰክሩለት ሳይሆን እራሳቸው በአእምሯቸው የፈጠሩት ወይም ሃሰተኛው በስሙ የመጣው እንደ የግል አዳኝ የተባለው መሆኑን ተረዱ!! እንደነዚህ ያሉ ሰዎች በመፅሃፍ ቅዱስ ሃይለ ቃል ከመመስረት ይልቅ በራሳቸው መረዳት ፣በማሰብ ችሎታቸው ስለሚተማመኑ ለቅዱስ ቃሉ ከመገዛት ፈንታ ፤ ቅዱስ ቃሉን እንዲህ ለራሳቸው አስገዝተውታል።

ወገኖቼ!!

ቃል(አምላክ) ስጋ እንዴት ሆነ??

ኢየሱስ ከሁለት ባህሪ ባለመለወጥ ፣ ያለ ህድረት ፤ያለ መመለስ(እንደ ሙሴ በትር) ፤ ያለመቀላቀል ፤ያለ መደረብ ፤ያለ መለያየት በተዋህዶ አንድ ባህሪ አይደለምን??

ሰው የምንለውስ ከሰው ዘር የገባ ትውልድ የሚቆጠርለት ማለት አይደለምን?? ኢየሱስ ሰውነቱ እንዴት ነው??ዮሴፍ አባቱ ሳይሆን እንዴት የዳዊት ልጅ ተብሎ ዘር ተቆጠረለት??

ይህንን አጥርተህ ያላወክ ኢየሱስን በእውነት እያመለክ አይደለም!!!! ለነዚህ ግን በመፅሃፍ እንደተፃፈ እላለሁ ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች፥

እያሳቱና እየሳቱ፥ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ።2 ጢሞ 3፡13

Dec 19, 2014 · Public · in Timeline Photos

View Full Size · Send as Message · Report

6 people like this.

Matiwos Amare Tewahido

ቃል የነሳው ስጋን ብቻ ነውን? የህ 1፤1 ቃል ስጋ ሆነ ሲል ጌታ ከእመቤታችን የነሳው ስጋን ብቻ ነውን? በቤተ ክርስቲያናችን መሰረት ከሶስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ አካላዊ ቃል ከእመቤታችን የተወለደው ከስጋዋ ስጋ ከነፍሷ

ነፍስ ነስቶ ነው። አማናዊው የክርስትና ትምህርት በቃለ እግዚአብሄር ላይ የተመሰረተ እንጅ ልቦለድ ወይም ፍልስፍና

አይደለም። ማስረጃ 1 ኛ እመቤታችን በስደት እያለች ሄሮድስ በሞተ ጊዜ የጌታ መልአክ ለዮሴፍ የህፃኑን ነፍስ

የሚፈልጉት ሞተዋልና ተነስ ማቴ 2 ይህ ማለት ጌታችን ከእመቤታችን ነፍስን ነስቷል ማለት ነው 2 ኛ ጌታችን ድህነተ

አለምን በመስቀል ላይ ሲፈፅም ያን ጊዜ ነፍሱ ከስጋው ተለየች ይላል ማቴ 27፤50 ይህም ጌታችን ከእመቤታችን

ከስጋዋ ስጋ እንደነሳ ከነፍሷም ነፍስ እንደነሳ ያረጋግጥልናል። እዚህ ላይ አንድ ማስተዋል ያለብን

ነገር አለ ይህውም ወንጌላዊው ዮሀንስ ቃል ስጋ ሆነ ሲል የስጋንና የነፍስን ተዋህዶ በስጋ ስም መጥራቱ እንጅ

ነፍስን አልነሳም ማለቱ አይደለም። ምክንያቱም የስጋና የነፍስ ተዋህዶ በስጋ ስም ወይም በነፍስ ስም የሚጠራበት ጊዜ
አለና። ማስረጃ 1ኛ ያእቆብ ሰባ አምስት ነፍስ ሆኖ ወደ ግብፅ ወረደ ይላል። ይህ ማለት የስጋንና የነፍስን
ተዋህዶ በነፍስ ስም መጥራቱ እንጅ ስጋቸው ከነአን ቀረ ማለት አይደለም። 2ኛ ነቢዩ ዳዊት የስጋንና የነፍስን
ተዋህዶ በነፍስ ስም ሲጠራ፦ የሰው ሁሉ ነፍስ አንተን ተስፋ ታደርጋለች መዝ 144፤15 መጨረሻም ይህን የስጋንና
የነፍስን ተዋህዶ በስጋ ስም ሲጠራ ወደ አንተ የመጣውን የስጋ ፀሎት ሁሉ ተቀበል መዝ 64፤2 ይህ ጥቅስ ስጋን
እንጅ ነፍስን አያመለክትም ቢባል ፈፅሞ አያስኬድም ምክንያቱም ነፍስ የሌለው ስጋ በድን ስለሆነ መፀለይ አይችልም።

48/ *የተሀድሶዎች ስራ ክፍል 1* ዲያብሎስ በዚች ቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ፈተና እነ አርዮስን አስነሳ እነ አትናቴዎስን የመሰሉ ሊቃውንት ተነሱ አርዮስንም አወገዙ ።ቤተክርስቲያን አሸነፈች ስለዚህ ዲያብሎስ ሁለተኛውን ፈተና አመጣ። ጨካኝ መንግስታትን አስነሳ ዘመነ ሰማዕታት ሆነ ። በመግደል ሳይሆን በመሞት አሸነፉት ። ዲያብሎስም ሶስተኛውን ፈተና ተሀድሶን አመጣ። በ5ቱ ቤተክርስቲያናት ማለትም ህንድ፣ አርመን፣ ግብፅ፣ ሶርያና ኢትዮጵያ ላይ ጥቃቱን ጀመረ።ተሀድሶዎች

መጀመሪያ ጥቃታቸውንየጀመሩት ሶሪያ ላይ ነው።ገዳማትን ዘጉ ፣ ሴት መነኩሴዎችን ደፈሩ፣ ካህናትንም ለሁለት ከፈሉ ።የቤተክርስቲያንዋን ንብረት ወርቅና ብር ሁሉ ዘረፉ ።ታላቁ ሊቅ ዮሐንስ አፈወርቅ ያስተማረባትን የሶፊያን ቤተክርስቲያን ቅርስ ዘረፉ መንበሩ አያለ ቤተክርስቲያንዋን ወደ መስጊድነት ቀየሩ። ነገር ግን ምዕመኑና ካህኑ አንድ በመሆን የተዘጉትን ቤተክርስቲያንና ገዳማት ማስከፈት ጀመሩ።ለሁለት ተከፍለው የነበሩትንም አንድ አደረጉ።እግዚአብሔር ከሶሪያውያኖች ጋር ነበርና የተሀድሶ ሴራ በሶርያ ከሸፈ።ዲያብሎስ ቀጥሎ የህንድን ቤተክርስቲያን መዋጋት ጀመረ።የህንድ ቤተክርስቲያን ከውጪ በጣኦት አምላኪያን ከውስጥ በተሀድሶዎች ትፈተን ጀመር።ህንድ ላይ ተሀድሶዎች ከባድ ጥፋት አድርሰዋል ካህናቱ ለሁለት ከተከፈሉ ቡሃላ ፍርድ ቤት ክስ ጀመሩ ዳኛውም እናንተ መግባባት ካልቻላቹ ቤተክርስቲያንዋን ለ 2 ተካፈሉ አለና ገዳሙን ቤተክርስቲያኑን ኮሌጁን ቆጥሮ እኩል አካፈላቸው።እንዲሁም ነገስታቱ ጣኦት አምላኪዎች በመሆናቸው ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ሀገሪቱ የክርስቲያን ስላልሆነች ክርስቲያን በመሆኑ ብቻ ግብር እንዲከፍል ተባለ ። ካህን የሆነ ደሞ ለክህነቱ ብቻ እንዲከፍልና ማግባትና ጫማ ማድረግም እንዳይችል ከነገስታቱ ጋር ተማክረው አስደረጉ። ካህንም ኗሪ በመሆኑ ፣ ክርስቲያን በመሆኑና ካህን በመሆኑ ማለትም ከሌላው ሶስት እጥፍ ስለሚከፍል የካህን ቁጥር ቀነሰ። ብዙ ገዳማትና ቤተ ክርስቲያናትም ተዘጉ ።በዛ ጊዜ የህንዶች ቅዳሴ 1:45 ደቂቃ ነበር ሚፈጀው ተሀድሶዎች ደሞ ይሄ ረዝሟል ብለው 15 ደቂቃ አደረጉት ስለማርያም ስለቅዱሳን ስለመላዕክት የሚናገረውን ክፍል ቆርጠው

አወጡት።የህንድን ቤተ ክርስቲያን የታደጉዋት የህንድ እናቶች ናቸው ሁሉም በቀን ከሚቀቅሉት እሩዝ ላይ አንድ እጅ እየቀነሱ ያጠራቅሙና የሳምንቱን እሁድ ይዘው ይመጡና ለቤተክርስቲያን ይሰጡ ጀመር። እሱም ተሸጦ ለካህናት ደሞዝና የተዘጉ ቤተክርስቲያናትና ገዳማትን ያስከፍቱ ጀመር ።እግዚአብሔርም ከህንዶች ጋር ነበረና የህንድ ቤተክርስቲያን አገግማ ተቋቋመች የተሀድሶዎችም ሴራ ከሸፈ። ቀጣይ የተሀድሶ ታርጌት ደሞ አርመን ሆነች ይቀጥላል....

49/ *የተሀድሶዎች ስራ (ክፍል 2)*

በባለፈው ክፍላችን ተሀድሶዎች ሶሪያና ህንድን ምን እንዳደረጉና እግዚአብሔር ደሞ እንዳከሸፈባቸው ከዛም ፊታቸውን ወደ አርመን እንዳዞሩ አይተን ቆመናል። እነሆ ካቆምንበት እንቀጥላለን ። አርመን ገቡ።አርመንም በሰዐቱ ኮሚኒዝም የሚል ለውጥ ላይ ነበረች ይሄን ተገን አርገው ቤተክርስቲያኒቱም ለውጥ ያስፈልጋታል አርጅታለች ተሀድሶ ያስፈልጋታል ህዝቡም ወንጌል አልተሰበከምና ወንጌል ሊሰበክ ይገባዋል ብለው ተነሱ አርመንንም ለ3 ከፈልዋት።ነገር ግን እግዚአብሔር የሲኦል ደጆች አይችሏትም ብሏልና ምዕመናኑ ቤተ ክርስቲያናችን ስትከፈል ለምን ዝም እንላለን ። አባቶቻችን ሲጣሉ ማስታረቅ አለብን ብለው ከኘሬዝዳንቱ እስከ ምዕመኑ አንድ ሆነው ከኛም ሀገር አባቶች ተወክለው ሄደው ለ3 የተከፈሉትን አስማምተውና አስታርቀዉ አንድ አደረጓቸው።የተሀድሶዎችም ሴራ በአርመን ከሸፈ። ዲያብሎስም ይህን ሲያይ ቀጣይ ታርጌቱን ግብፅን

አደረገ።ግብፅም በሰዓቱ በእንግሊዝ ቅኝ ትገዛ ነበር። ስለዚህ ባንድ በኩል እንግሊዞች ባንድ መልኩ ተሀድሶዎች ባንድ መልኩ እስማኤላውያን መከራ አፀኑባቸው። ካህን የሆነ በበቅሎ መጓዝ አይችልም እና ሌሎች ብዙ ትዕዛዛትን አወጡ።ካህን እንዲጠፋ ብለው ።በዚህም ም/ት የካህናት እጥረት መጣ ብዙ ቤተክርስቲያኖችም ተዘጉ።ተሀድሶዎቹም ለህዝቡ በሚገባው ቋንቋ መዝሙር እናስጠናለን ብለው ገቡ ።በየአዳራሹም የሚዘመረው መዝሙር የፕሮቴስታንቶች ብቻ ሆነ።ቤተክርስቲያኒቱም ተናወጠች። ይሄኔ እግዚአብሔር 1 ሰዉ አስነሳ ይህ ሰው ቤተሰቦቹ ሀብት ያወረሱት ሀቢብ የሚባል የባለፀጋ ልጅ ነበር።ሀቢብ ጊዮርጊስም ከአቡነ ቄርሎስ ጋር በመሆን ቤተሰቦቹ ያወረሱትን ቤት የካህናት ማሰልጠኛ አደረገው። በየአዳራሹም በመዞር ከቤተክርስቲያን የኮበለሉትን እየመለሰ መዝሙር እየፃፈ እራሱ ማስተማር ጀመረ።ወደቤተክርስቲያን የመጡት ምዕመናን ሀይማኖቱ ሲገባቸው ወደ ገዳም እንዲሄዱና ምናኔውንና ምንኩስናውን እንዲኖሩት አደረገ።በየኮሌጁና በየ ዩንቨርስቲው የነበሩ ወጣቶችን ማታ ማታ እያስተማረ ወደ ቤተክርስቲያን አመጣቸው።ያኔ እነ አቡነ ሽኖዳን እነ አቡነ ሙሴን የመሰሉ አባቶች ፈሩ።የግብፅ ቤተክርስቲያን ችግር የተፈታዉ እነ አቡነ ሺኖዳ መንበረ ፕትርክናውን ሲይዙ ነው ።እነሱም ቤተክርስቲያን በህግ በስርዓት የምትመራ እንጂ ማንም እንዳሻው አይመራትም ሲሉ ነው።ግብፆች ተሀድሶን ለማሸነፍ 50 ዓመት ታግለዋል አቡነ ሺኖዳ ከ 100 በላይ መፃህፍት ከፃፉበት ም/ት አንዱ ተሀድሶዎች አንስተው ለነበረው ጥያቄ ለመመለስነው። እግዚአብሔርም በዚህ ሁኔታ የግብፅን ቤተ ክርስቲያን ታደጋት።የተሀድሶዎችም ሴራ በግብፅ ከሸፈ።

ቀጣይ ታርጌታቸው ደግሞ ኢትዮጵያ ሆነች።

ይቀጥላል...

Philimon Tafere

50/ *የተሀድሶዎች ስራ (ክፍል 3)

ከባለፈው የቀጠለ ከህንድ ቡሃላ ታርጌት ያደረጉት ኢትዮጵያን ነበር። በ 1983 ዓ.ም መንግስት ሲለወጥ እድሉን የተጠቀሙ መስሏቸው የተወሰኑ ጳጳሳት ኢትዮጵያን ጥለው ኮበለሉ አሜሪካ ገቡ።በ 1986 ዓ.ም ሜሪላንድ ግዛት ውስጥ ተሰበሰቡና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ያለው ኢትዮጵያ ሳይሆን አሜሪካ ነው አሉ።ሲኖዶሱም እኛ ነን አሉ ።የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን የምንመራት ከዚ ሆነን እኛ ነን አሉ።ከዛም ስርዓት ማሻሻል ጀመሩ ቅዳሴዉ ረዝሟልና ህዝቡ እየከበደው ነው ብለው ቅዳሴውን 15 ደቂቃ አደረጉት።ከበሮ ፣ፅናፅል፣ መቋሚያ ይቅርና ጊታርና ኪቦርድ መግባት አለበት ብለው ወሰኑ።14 ቱ ቅዳሴ ይበዛል ስለዚህ 3 ቅዳሴ ይበቃል።ቅዳሴ እግዚ፣ ቅዳሴ ሀዋሪያትና ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ ይበቃል ብለው ወሰኑ።እንደውም ቅዳሴ ማርያምን መቀደስ በቀን 4 ቅዳሴ እንደ መቀደስ ነው አሉ።አዳዲስ ጳጳሳት ለአሜሪካ እንሾማለን ብለው ጳጳሳትን ሾሙ።እዛ ሄደው ቤተክርስቲያንን ለማሻሻል የሞከሩትበት ም/ት እዚ ያሉት አባቶች መፅሀፍ እናሻሽል ፣ስርዐት እንለውጥ ሲሏቸው አይ እናንተ ተለወጡ እንጂ

ቤተክርስቲያን አትለወጥም ስላልዋቸው ነው።ይህንም አስመልክተው በቦርድ የምትመራ ቤተክርስቲያን መሰረቱ። እዚ ደሞ የሴቶች ገዳም ውስጥ ወንዶችን የወንዶች ገዳም ውስጥ ደሞ ሴቶችን በማስገባት ምንኩስናን ለማቃለል ሞከሩ ወዲያው ተነቃባቸው ።ከዛ ደሞ በገዳም ገብተው የብራናን መፅሀፍ እየፋቁ መቀየር ጀመሩ ። ይሄም ተነቃባቸው።ስለዚህ ስልታቸውን ቀይረው መጡ ።አሁን እየተጠቀሙት ያሉት ስልት የራሳችንን ሰባኪዎችና ዘማሪዎች መጠቀም ነው።ይህም በሁለት መንገድ እየተጠቀሙበት ነው። አንደኛዉ ስልት ማስረሳት ነው። ይህም ስለቅዱሳን ስለመላዕክት የሰማንበትን ጊዜ ማርዘም ነው። ማለትም መፅሀፍ ቅዱሳዊ ስብከት ሆኖ ግን ወልድ ዋህድ የማይል፣ ስለ መላዕክት ስለ ፃድቃን ሰማዕታት የማይናገር፣ ስለ ፆም ፀሎት ስለ መንፈሳዊ ተጋድሎ የማይናገር ማለት ነው። ሁለተኛው ደሞ ማቃለል ነው። ህዝቡ ካህን እንዲጠላ ምንኩስናን እንዲጠላ የቅዱሳን ገዳማትን ክብር እንዲያቃልል ማድረግ ነው።ስለዚህ ልንጠነቀቅና ልናውቅባቸው ይገባል።ሚካኤል የአመቱ ሆኖ ስለሚካኤል ማርያምም የአመትዋ ሆኖ ስለማርያም ካልሰበከና ካልዘመረ ልንጠረጥር ይገባል። እግዚአብሔር አምላክ ቤተ ክርስቲያናችንን ይጠብቅልን። በርግጥ የሲኦል ደጆች፣ የገሀነም ደጆች አይችሏትም ተብሏልና አልቻሏትም አይችሏትምም። ይቺ ቤተክርስቲያን እኛ በሀጥያት ስናረጅ እስዋ በፀጋ መንፈስ ቅዱስ ፣ በንስሀና በስጋ ወደሙ እኛን ታድሳለች እንጂ እስዋ አትታደስም።

ምንጭ ፡የዲ/ን ዳንኤል ክብረት ስብከተ

51/ የብዙ ሙስሊም ዘመዶቼ ጥያቄ ነው

ኡየሱስ ጌታ ነው የሚል አምላክ ነው የሚል በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ ካለ አሁኑኑ እጠመቃለሁ በማለት ይናገራሉ እኔ በግሌ ቤተ ሰቦቼም ከእስልምና ወገኖች መሀል ስለሆኑ ይህን ፅሁፍ ፖስት ላደርግ ተገደድኩ....

መልካም ንባብ

ሙስሊም ወገኖች ከሚያነሷቸው ጥያቄዎች መካከል "ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እኔ አምላክ ነኝና አምልኩኝ በማለት የተናገረበትን ቦታ አሳዩን" የሚለው አንዱና ዋነኛው ነው። ይህ አግባብ የሆነ ጥያቄ ቢመስልም ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስን ተልዕኮ በትክክል ካለመረዳት እና የመጽሐፍ ቅዱስን ቋንቋ በትክክል ካለማወቅ የመነጨ ጥያቄ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ለመሆን የግድ እኔ አምላክ ነኝና አምልኩኝ በማለት መናገር ያስፈልገዋል የሚለው እሳቤ ምክንያታዊ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ስለመሆኑ፤ ስለስቅለቱ፤ ስለሞቱና ስለትንሳኤው የተናገረባቸው በርካታ ቦታዎች አሉ። ሙስሊም ወገኖች እነዚህን እውነታዎች አለመቀበላቸው ኢየሱስ አምላክ ነኝና አምልኩኝ ያለበትን ቦታ ብናሳያቸው ሊቀበሉ እንደማይችሉ ያሳያል። ታድያ የጥያቄቸው ትክክለኛው ነጥብ ምንድነው? ሙስሊም ወገኖች በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር እርሱ እውነተኛ አምላክ መሆኑን የተናገረባቸውን ቦታዎች በመጥቀስ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በተመሳሳይ መንገድ መናገር ነበረበት ይሉናል። ነገር ግን የብሉይ ኪዳን እና የአዲስ ኪዳን ዘመናት ልዩነት እንዳላቸው አይገነዘቡም። እግዚአብሔር በሁሉም ዘመናት

በተመሳሳይ መንገድና ሁኔታ ራሱን መግለጥ የግድ አያስፈልገውም። ጥያቄያችን ሊሆን የሚገባው ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን በምን አይነት መንገድ ነው የገለጠው? የሚል እንጂ እኛ በምንፈልገው መንገድ ስላልተናገረ አምላክ አይደለም በማለት መደምደም ትክክል አይደለም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ገልጧል። ነገር ግን ይህ መንገድ "አምላክ ነኝና አምልኩኝ" የሚሉትን እነዚህን ቃላት በመናገር ላይሆን ይችላል። ስለዚህ እኔ ባልኩት መንገድ ካልተናገረ በስተቀር አምላክነቱን አልቀበልም በማለት ሌሎች ማስረጃዎችን መካድ ጠያቂው መልስ ፈላጊ ሳይሆን ክርክር ፈላጊ መሆኑን ያሳያል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረበት ዘመን "አምላክ ነኝና አምልኩኝ" የሚሉትን እነዚህን ቃላት መናገር ያላስፈለገበትን የተወሰኑ ምክንያቶች መጥቀስ እንችላለን። ይህንን ስንል ግን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን ክዷል፣ ሸሽጓል ወይንም ደግሞ በምንም አይነት መንገድ አልተናገረም ማለታችን አይደለም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው አምላክነቱንና ጌትነቱን ለማወጅ አልነበረም። የኢየሱስ ተልዕኮ ራሱን በማዋረድ ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ መስጠት እንጂ መለኮታዊ ክብሩን በማወጅ ሰዎች እንዲያውቁት ባለመሆኑ በየስፍራው እየዞረ አምላክነቱን ቢያውጅ ከተል ዕኮው ጋር የሚጣጣም አይሆም። ጌታ ኢየሱስ የራሱን ክብር ፍለጋ እንዳልመጣ በተደጋጋሚ ተናግሯል:-

"እኔ ግን የራሴን ክብር አልፈልግም፤ የሚፈልግ
የሚፈርድም አለ።" ዮሐ 8:50

“እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም
ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት
አልመጣም።” ማቴ 20:28

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህንን ሐሳብ ልብን በሚነካ መንገድ ያስቀምጠዋል።

“በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ
ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር
ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት
እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥ ነገር ግን የባሪያን
መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥
በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም
ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ። በዚህ
ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ
አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤
ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት
ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ
ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ
እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።” ፊልጵስዩስ 2፡5-10

ኢየሱስ በእርሱና በአብ መካከል ያለውን የአካል ልዩነት ግልፅ ሳያደርግ ‹አምላክ ነኝና አምልኩኝ› የሚሉትን ቃላት ቢናገር አይሁዶች ግራ ይጋቡ ነበር። አይሁዶች ስለ እግዚአብሔር ሦስቱ አካላት፣ ማለትም ስለ ሥላሴ ሙሉ ግንዛቤ ስላልነበራቸው ኢየሱስ ‹አምላክ ነኝና አምልኩኝ› የሚሉትን

ቃላት ቢናገር ‹አብ ነኝ› የሚል ስለሚመስላቸው እንዲህ ብሎ መናገሩ ግርታን ከመፍጠርና በእርሱ ላይም ተቃውሞን ከማስነሳት የዘለለ ጠቀሜታ ሊኖረው አይችልም ነበር። ስለዚህ ሁልጊዜ አምላክነቱን የሚያሳዩ ስራዎችን እየሰራ እና በትምህርቶቹም ውስጥ ጥበብን በተሞላ መንገድ እየነገራቸው ሰዎች አምላክ መሆኑን ወደማወቅ ደረጃ እንዲመጡ መርቷቸዋል። ነገር ግን ይህንን ሲያደርግ ሁል ጊዜ ከአብ ጋር ያለውን የአካል ልዩነት ግልፅ በማድረግ ነበር።

ኢየሱስ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረበት ዘመን ከሌሎች ሰዎች የተለየ መልክ አልነበረውም። ዛሬ አንድ ሰው ወደ እኛ መጥቶ ‹አምላክ ነኝና አምልኩኝ› ቢለን እንደማንቀበለው ሁሉ ኢየሱስም በዘመኑ ይህንን ቢል ኖሮ ተቃውሞን ከማትረፍ ውጪ ምንም ጠቀሜታ አይኖረውም ነበር። አምላክ ነኝና አምልኩኝ ከሚለው መንገድ ይልቅ በተግባር አምላክ መሆኑን መግለጥ የተሻለ በመሆኑ ይህንኑ አድርጓል። ሰዎች ደግሞ ሥራውን በማየት አምላክነቱን ወደ ማወቅ ሲመጡ እና ለአምላክ የሚገባውን ክብር ሲሰጡት በመስማማት ሲያረጋግጥላቸው እንጂ አንድም ጊዜ ሲቃወማቸው አልታየም። ለዚህ ትልቅ ማስረጃ የሚሆነን በዮሃንስ ወንጌል 21:24-29 ላይ የሚገኘው ታሪክ ነው።

“ነገር ግን ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ዲዲሞስ የሚሉት

ቶማስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከእነርሱ ጋር አልነበረም።

ሌሎቹም ደቀ መዛሙርቱ። ጌታን አይተነዋል አሉት።

እርሱ ግን፦ የችንካሩን ምልክትበ እጆቹ ካላየሁ

ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ

ካላገባሁ አላምንም አላቸው። ከስምንት ቀን በኋላም
ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፥ ቶማስም
ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ
መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ። ሰላም ለእናንተ ይሁን
አላቸው።ከዚያም በኋላ ቶማስን። ጣትህን ወደዚህ
አምጣና እጆቼንእይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ
አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው።
ቶማስም። ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ
አምነሃልና፤ ሳያዩ የሚያምኑ
ብፁዓን ናቸው አለው።" ዮሃ 21፡24-29
ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ባይሆን ኖሮ ቶማስ <ጌታዬ
አምላኬም> በማለት ሲጠራው በተቃወመው ነበር። ነገር ግን ይህንን
ከማድረግ ይልቅ "ስላየኸኝ
አምነህል ሳያዩ የሚውትያምኑ ብፁአን ናቸው"
በማለት እምነቱን አረጋግጦለታል። ከዚህ በማስከተል ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ አምላክነቱን የተናገረባቸውና በተግባር የገለጠባቸውን መንገዶች
እንመለከታለን። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ አምላክነቱ የሚሰጧቸውን ሌሎች
ምስክርነቶችንም እንመለከታለን።
ኢየሱስ አምላክ መሆኑን የገለጠባቸው መንገዶችና
ንግግሮች
(1) መሲህ መሆኑን (ክርስቶስ መሆኑን) በመናገር:-
ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ትንቢት የተነገረለት መሲህ መሆኑን በተደጋጋሚ

ተናግሯል። ለምሳሌ:-

“ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ

ደቀ መዛሙርቱን ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ

ይሉታል? ብሎ ጠየቀ። እነርሱም፦ አንዳንዱ

መጥምቁ ዮሃንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም

ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት።

እርሱም፦ እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?

አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፦ አንተ ክርስቶስ

የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ኢየሱስም

መልሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥

በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን

አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።” የማቴዎስ ወንጌል 16፡13-17

“ሴቲቱ ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ

አውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችው።

ኢየሱስ፦ የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት።” የዮሃንስ ወንጌል 4፡25-26

(በተጨማሪም ዮሃንስ 26:1-3 ማርቆስ 14:1-2; 12:35-37; 13:26-27 ሉቃስ 24:13:15; 2425-27; 24:44-49 ያንብቡ)

የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መሲሁ አምላክ መሆኑን ይናገራሉ:-

“ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና

አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ

መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ

ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ
በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት
ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥
ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት
ይህን ያደርጋል።" ትንቢተ ኢሳይያስ 9፥6-7
"የጭፍሮች ሴት ልጅ ሆይ፥ ጭፍሮችሽን አሁን
ሰብስቢ ከብቦ አስጨንቆናል የእስራኤልን ፈራጅ
ጕንጩን በበትር ይመታሉ። አንቺም ቤተ ልሔም
ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ
ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ
ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን
ይወጣልኛል።" ትንቢተ ሚክያስ 5፥1-2
"እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ
ያስተካክላል እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት
ወደ መቅደሱ ይመጣል የምትወዱትም የቃል ኪዳን
መልእክተኛ፥ እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ
እግዚአብሔር፦ ነገር ግን እርሱ እንደ አንጥረኛ እሳትና
እንደ አጣቢ ሳሙና ነውና የሚመጣበትን ቀን
መታገሥ የሚችል ማን ነው? እርሱስ በተገለጠ ጊዜ
የሚቆም ማን ነው? እርሱም ብርን እንደሚያነጥርና
እንደሚያጠራ ሰው ይቀመጣል፥ የሌዊንም ልጆች
ያጠራል፥ እንደ ወርቅና እንደ ብርም ያነጥራቸዋል

እነርሱም ለእግዚአብሔር በጽድቅ ቍርባንን
የሚያቀርቡ ይሆናሉ።" ትንቢተ ሚልክያስ 3፡1-3
47 "አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ ለዘላለም ነው የመንግሥትህ
በትር የቅንነት በትር ነው። ጽድቅን ወደድህ ዓመፃንም
ጠላህ ስለዚህ ከባልንጀሮችህ ይልቅ እግዚአብሔር
አምላክህ የደስታ ዘይትን ቀባህ።" መዝሙረ ዳዊት 45
ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ነጥቦች አመክንዮአዊ በሆነ መንገድ
ስናስቀምጣቸው እንደሚከተለው ይሆናል:-
1 ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ትንቢት የተነገረለት መሲህ መሆኑን ተናግሯል
2 በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መሰረት መሲሁ አምላክ ነው
3 ስለዚህ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ተናግሯል።
ይህ ሲሎጂዝም ለመረዳት በጣም ቀላል የሆነና ኢየሱስ አምላክ መሆኑን
እንደተናገረ በግልፅ የሚያሳይ ነው።
(2) "የሰው ልጅ" የሚለውን ማዕርግ በመጠቀም:-
ኢየሱስ ክርስቶስ በተደጋጋሚ "የሰው ልጅ" የሚለውን ማዕርግ ሲጠቀም
እናያለን። ለምሳሌ:-
"እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ፥ አስቀድሜ ሁሉን
ነገርኋችሁ። በዚያን ወራት ግን ከዚያ መከራ በኋላ
ፀሐይ ይጨልማል ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥
ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት
ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በብዙ ኃይልና
ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል። በዚያን ጊዜም

መላእክትን ይልካል ከአራቱ ነፋሳትም ከምድር ዳርቻ
እስከ ሰማይ ዳርቻ የተመረጡትን ይሰበስባቸዋል።” የማርቆስ ወንጌል 1323-27

“ሊቀ ካህናቱም በመካከላቸው ተነሥቶ። አንዳች
አትመልስምን? እነዚህስ በአንተ ላይ የሚመሰክሩብህ
ምንድር ነው? ብሎ ኢየሱስን ጠየቀው። እርሱ ግን
ዝም አለ አንዳችም አልመለሰም። ደግሞ ሊቀ
ካህናቱ ጠየቀውና። የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ
ነህን? አለው። ኢየሱስም፦ እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም
በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ
ታያላችሁ አለ። ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደና።
ከእንግዲህ ወዲህ ምስክሮችን ምን ያስፈልገናል?
ስድቡን ሰማችሁ፤ ምን ይመስላችኋል? አለ።
እነርሱም ሁሉ ሞት ይገባዋል ብለው ፈረዱበት።” የማርቆስ ወንጌል 14፡ 60-64

“የሰው ልጅ” የሚለውን ስያሜ ሚስጥር የምናገኘው በትንቢተ ዳንኤል 7:13-14 ላይ ነው:-

“በሌሊት ራእይ አየሁ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል
ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ
ሸመገለውም ደረሰ ወደ ፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና
አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት
ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ግዛቱም

የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም
የማይጠፋ ነው።"

በዚህ ጥቅስ መሰረት ይህ የሰው ልጅ የተባለው አካል ህዝቦችን ሁሉ የሚገዛ፤ የማያልፍ የዘላለም ግዛት ያለው እና የማይጠፋ መንግስት ያለው ነው። ከአምላክ በስተቀር ህዝቦች ሁሉ ሊገዙት የሚገባ እና ዘላለማዊ ግዛትና መንግስት ሊኖረው የሚችል ማነው? ኢየሱስ "የሰው ልጅ" የሚለውን ማዕርግ መጠቀሙ ስጋ ለብሶ የመጣ አምላክ መሆኑን ለማሳየት እንደነበር ከዚህ ትንቢት እንረዳለን።

(3) አምላክ ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ነገሮች በማድረግ:-

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ኢየሱስ ታጢዓትን ይቅር የማለት ችሎታ እንዳለው ማሳየቱ ነው:-

"ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ደግሞ ገብቶ
በቤት እንደ ሆነ ተሰማ። በደጅ ያለው ስፍራም
እስኪጠባቸው ድረስ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ቃሉንም
ይነግራቸው ነበር። አራት ሰዎችም የተሸከሙትን ሽባ
አመጡለት። ስለ ሕዝቡም ብዛት ወደ እርሱ ማቅረብ
ቢያቅታቸው እርሱ ያለበትን የቤቱን ጣራ አነሡ፥
ነድለውም ሽባው የተኛበትን አልጋ አወረዱ።
ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን። አንተ ልጅ፥
ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው። ከጻፎችም አንዳንዶቹ
በዚያ ተቀምጠው ነበር በልባቸውም። ይህ ሰው ስለ

ምን እንደዚህ ያለ ስድብ ይናገራል? ከአንዱ
ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ሊያስተሰርይ ማን
ይችላል? ብለው አሰቡ። ወዲያውም ኢየሱስ
በልባቸው እንዲህ እንዳሰቡ በመንፈስ አውቆ እንዲህ
አላቸው፦ በልባችሁ ይህን ስለ ምን ታስባላችሁ?
ሽባውን። ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ።
ተነሣ አልጋህንም ተሸከምና ሂድ ከማለት ማናቸው
ይቀላል? ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ
ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው
እንድታውቁ፤ ሽባውን። አንተን እልሃለሁ፥ ተነሣ፥
አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው።
ተነሥቶም ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት
ወጣ፥ ስለዚህም ሰዎች ሁሉ ተገረሙና። እንዲህ ያለ
ከቶ አላየንም ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ።" የማርቆስ ወንጌል 2፡1-
12
ከአምላክ በስተቀር ኃጢዓትን ይቅር ሊል የሚችል ማነው?
(4) ለአብ የሚገባው ክብር ሁሉ ለእርሱም
እንደሚገባ በመናገር:-
"ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን
ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ
አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን
የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።" የዮሃንስ ወንጌል 5፡22-23

አብን የምናከብረው እርሱን በማምለክ ነው። ኢየሱስንም አብን እንደምናከብረው ማክበር የምንችለው ለአብ የምንሰጠውን ክብር ሁሉ ስንሰጠው ነው።

(4) ወደ እርሱ እንድንፀልይ እና እርሱም ደግሞ የምንለምነውን በሙሉ እንደሚያደርግልን በመናገር:-

“እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።” የዮሃንስ ወንጌል 14

ኢየሱስ የሁሉን ሰው ፀሎት ለመስማት በሁሉም ስፍራ መገኘት እና ሁሉን ማወቅ መቻል አለበት፤ የምንለምነውን ሁሉ ለማድረግ ደግሞ ሁሉን ቻይ መሆን አለበት። ከአንዱ አምላክ በስተቀር ፀሎታችንን ሰምቶ የምንለምነውን ሁሉ ማድረግ የሚችል ማነው? ኢየሱስ ግን ይህንን ማድረግ እንደሚችል ነግሮናል ስለዚህ አምላክ መሆኑን ተናግሯል።

(5) በሁሉም ስፍራ መገኘት እንደሚችል በመናገር:-

“ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።” የማቴዎስ ወንጌል 18፡19-20

“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና
በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥
ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው
ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም
ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።” የማቴዎስ ወንጌል 28፡19-20

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምንሰበሰብበት ስፍራ ሁሉ በመካከላችን መገኘት የሚችለው እና እስከዓለም ፍፃሜ ድረስ ከእኛ ጋር መሆን የሚችለው በሁሉም ስፍራ የመገኘት ችሎታ ካለው ብቻ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ይህን ማድረግ እንደሚችል መናገሩ በሌላ ቋንቋ አምላክ መሆኑን መናገሩ ነው።

(6) ሰዎች በስሙ የኃጢዓት ይቅርታን እንደሚያገኙ
በመናገር

“በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ
አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፦
ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን
ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት
ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ
እንዲሁ ተጽፎአል። እናንተም ለዚህ ምስክሮች
ናችሁ።” የሉቃስ ወንጌል 24፡45-48

ከአምላክ ስም በስተቀር የኃጢዓት ይቅርታን የሚያስገኝ ስም የማን ስም ነው?

(7) በስሙ በሽተኞች እንደሚፈወሱና አጋንንት

እንደሚወጡ በመናገር እና በእርሱ የሚያምኑ ሰዎች

ይህንን ማድረግ እንዲችሉ ስልጣን በመስጠት

“ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤

በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤

እባቦችን ይይዛሉ፥ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ

አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ

እነርሱም ይድናሉ። ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር

ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም

ቀኝ ተቀመጠ። እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ

ሰበኩ፥ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፥

በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር።” የማርቆስ ወንጌል 16፡17-20

“ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው ጌታ ሆይ፥ አጋንንት

ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት። እንዲህም

አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ

አየሁ። እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥

በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥

የሚጐዳችሁም ምንም የለም። ነገር ግን መናፍስት

ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን

በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።” የሉቃስ ወንጌል 10፡17-20

አጋንንትን ማስወጣት የሚችልና በሽተኞችን መፈወስ የሚችል ከአምላክ

ስም በስተቀር የማን ስም ሊሆን ይችላል? ሰዎች ይህንን ማድረግ እንዲችሉ

ስልጣን መስጠት የሚችል ከአምላክ በስተቀር ማነው?

(8) መላዕክትን ማዘዝ እንደሚችል እና የእርሱ እንደሆኑ በመናገር

“ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ።” የማቴዎስ ወንጌል 24፡29-30

ከአምላክ በስተቀር ቅዱሳን መላዕክትን እንደራሱ አገልጋዮች ማዘዝና መላክ የሚችል ማነው?

(9) በመጨረሻው ቀን ሙታንን የሚያስነሳው እርሱ እንደሆነ በመናገር

“ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና። ከሰጠኝም ሁሉ አንድንስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው። ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።” የዮሐንስ ወንጌል 6፡38-40

ከአምላክ በስተቀር በፍርድ ቀን ሙታንን ማስነሳት የሚችል ማነው?

(10) በመጨረሻው ቀን በሁሉም ላይ የመፍረድ
ስልጣን ያለው እርሱ መሆኑን በመናገር
“የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም
ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ
ዙፋን ይቀመጣል፤ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤
እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው
ይለያቸዋል፥ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው
ያቆማቸዋል። ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ
ይላቸዋል። እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም
ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት
ውረሱ። ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ
አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥
ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥
ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና። ጻድቃንም መልሰው
ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ?
ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? እንግዳ
ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ
አይተንመቼ አለበስንህ? ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ
አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን? ንጉሡም መልሶ፦
እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ
ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ
አደረጋችሁት ይላቸዋል። በዚያንጊዜ በግራው ያሉትን

ደግሞ ይላቸዋል። እናንተርጉማን፥ ለሰይጣንና

ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ

ሂዱ። ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ

አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥

ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታስሬም

አልጠየቃችሁኝምና [...]" የማቴዎስ ወንጌል 25፡31-43

"ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት

ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ

በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር

የላከውን አብን አያከብርም።" የዮሐንስ ወንጌል 5፡22-23

ከአምላክ በስተቀር በመጨረሻም ቀን በህያዋንና በሙታን የመፍረድ

ስልጣን ያለው ማነው?

(11) የዘላለምን ህይወት መስጠት እንደሚችል

በመናገር

"በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ

ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን

እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም

ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ

ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም

አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን። አይሁድ ሊወግሩት

ደግመው ድንጋይ አነሡ።" የዮሐንስ ወንጌል 10፡27-31

ከአምላክ በስተቀር የዘላለምን ህይወት መስጠት የሚችል የለም!

(12) ለዓምላክ ብቻ የሚገባውን ስግደትና አምልኮን

በመቀበል

“እነሆም፥ ሲሄዱ ነጹ። ከእነርሱም አንዱ እንደ

ተፈወሰባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን

እያከበረ ተመለሰ፥ እያመሰገነውም በእግሩ ፊት

በግንባሩ ወደቀ፤ እርሱም ሳምራዊ ነበረ። ኢየሱስም

መልሶ፦ አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ?

ከዚህ ከልዩ ወገን በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብሩ

የተመለሱ አልተገኙም አለ። እርሱንም ተነሣና ሂድ፤

እምነትህ አድኖሃል አለው።” የሉቃስ ወንጌል 17፥15-19

“ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች ያደረገውን ድንቃ

ድንቅ በመቅደስም ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ እያሉ

የሚጮኹትን ልጆች ባዩ ጊዜ፥ ተቈጥተው እነዚህ

የሚሉትን አትሰማምን? አሉት። ኢየሱስም፦

እሰማለሁ፤ ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋናን

ለራስህ አዘጋጀህ የሚለውን ቃል ከቶ

አላነበባችሁምን? አላቸው።” የማቴዎስ ወንጌል 21፥15-16

መጽሐፍ ቅዱስ ስግደትና አምልኮ የሚገባው ለአምላክ ብቻ እንደሆነ ይናገራል። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሰዎችን ስግደትና ምስጋና ተቀብሏል። በመጨረሻው ጥቅስ ውስጥ እንደምናነበው ኢየሱስ ክርስቶስ ዳዊት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለያሕዌ የተናገረውን ጥቅስ ለእርሱ የተነገረ መሆኑን ሲያረጋግጥ እናያለን። ኢየሱስ ለአምላክ ብቻ የሚገባውን ክብር በመውሰድ

አምላክ መሆኑን አሳይቷል።

(13) ጌታ መሆኑን በመናገር

የሰዎች ጌታ መሆኑን

“እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና
መልካም ትላላችሁ። እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር
ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ
በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል።
እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ
ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።” የዮሐንስ ወንጌል 13፡13-15

የሰንበት ጌታ መሆኑን

“እንዲሁም የሰው ልጅ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነው
አላቸው።” የማርቆስ ወንጌል 2፡28

ኢየሱስ በዮሃንስ ወንጌል ላይ የሰዎች ጌታ መሆኑን ተናግሯል። ይህ ደግሞ ጌታ መሆኑን አልተናገረም በማለት በተደጋጋሚ ለሚናገሩት ሙስሊሞች በቂ መልስ ነው። ብዙዎቹ ግን ኢየሱስ ጌትነቱን በግልፅ መናገሩን ስለማያውቁ ጌታ ነኝ ያለበትን ቦታ አሳዩን በማለት ይጠይቃሉ። ነገር ግን ይህንን ቦታ ስናሳያቸው ትንሽ ደንገጥ በማለት ይቆዩና ሌላ ዘዴ ይፈጥራሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎችም ጌታ ተብለዋል ይላሉ። ነገር ግን ኢየሱስ በዚህ ቦታ ላይ ጌትነቱ ልክ ሐዋርያቱ የሚሉት ዓይነት ጌትነት መሆኑን ስለተናገረ ሐዋርያት በሚሉት ዓይነት መንገድ እንጂ በራሳችን መንገድ ልንተረጉመው አንችልም። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በቀጣይነት እንደምንመለከተው ሐዋርያት የኢየሱስን አምላክነት ያምኑ ስለነበር ጌታ ነህ ሲሉት አምላክነቱን

ለማመልከት እንጂ ከፍ ያለ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ጌታ በሚባሉበት መንገድ እየጠሩት አይደለም። ኢየሱስ ጌታ መሆኑን የተናገረበት ሌላው አጋጣሚ የሰንበት ጌታ መሆኑን መናገሩ ነው። ይህ ደግሞ በማያሻማ ሁኔታ አምላክነቱን ያሳያል ምክንያቱም ሰንበት ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ቀን መሆኑ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተነግሯልና (ዘጸአት 31:12-17)። እግዚአብሔር ለራሱ በቀደሰው ቀን ላይ ጌታ መሆን የሚችል ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ የሚገኙ ማስረጃዎች

በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የሚገኙት የኢየሱስ ንግግሮች ወደሰማይ ካረገ በኋላ የተናገራቸው ናቸው

(1) ፊተኛውና ኋለኛው

“አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።” የዮሐንስ ራእይ 22፡13

“ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩበታች 48 ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።” የዮሐንስ ራእይ 1፡ 17-18

የሚከተለው የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ይህንን ንግግር መናገር የሚችለው አምላክ ብቻ መሆኑን ያሳያል:-

“የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዠም

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ
ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ
የለም። እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ይነሣና ይጥራ
ይናገርም፤ ከጥንት የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅልኝ፥
የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ።" ትንቢተ ኢሳይያስ 44፡6-7

(2) ኩላሊትንና ልብን የሚመረምር

"አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ኩላሊትንና ልብን
የምመረምር እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ፥" የዮሐንስ ራእይ 2፡23

የሰዎችን የተሰወረ የውስጥ ሐሳብ መርምሮ ማወቅ የሚችለው ከአምላክ በስተቀር ማን ሊሆን ይችላል? የሚከተለው የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ይህንን ንግግር መናገር የሚችለው አምላክ ብቻ መሆኑን ያሳያል:-

"እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፥ እንደ
ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ
ኩላሊትንም እፈትናለሁ።" ትንቢተ ኤርምያስ 17፡10

(3) ለሁሉም እንደየስራው የሚከፍል

"እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ
ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።" የዮሐንስ ራእይ 22፡12

"ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ።" የዮሐንስ ራእይ 2፡23

በመጨረሻው የፍርድ ቀን ለሁሉም ሰው እንደየስራው መክፈል የሚችል ከአምላክ በስተቀር ማን ሊሆን ይችላል?

(4) አምላክ ነኝ ብሏል

“በዙፋንም የተቀመጠው። እነሆ፥ ሁሉን አዲስ

አደርጋለሁ አለ። ለእኔም። እነዚህ ቃሎች የታመኑና

እውነተኞች ናቸውና ጻፍ አለኝ። አለኝም ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፥

መጀመሪያውና

መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ

እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን

ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ

ይሆነኛል።” የዮሐንስ ራእይ 21፡5-7

በዚህ ጥቅስ መሰረት አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና መጨረሻ የሆነው እርሱ አምላክ መሆኑን ይናገራል። በዮሐንስ ራዕይ 22:12-13 ላይ ይህ አልፋና ኦሜጋ መጀመርያና መጨረሻ የሆነው በቶሎ እንደሚመጣ ይናገራል። እዝያው ምዕራፍ ቁጥር 20 ላይ ይህ በቶሎ የሚመጣው ራሱ ኢየሱስ እንደሆነ ተነግሮናል። ስለዚህ አልፋና ኦሜጋ የሆነው በቶሎ እንደሚመጣ የተናገረው በም ዕራፍ 21:7-8 ላይ አምላክ መሆኑን የተናገረው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ግልፅ ነው።

እግዚአብሔር አብ ስለ እርሱ ምን አለ?

ሙስሊም ወገኖች በቁርአን ውስጥ የሚገኙትን የአላህ ንግግሮች እንደሆኑ የሚያምኗቸውን ቃላት ያለምንም ቅድመሁኔታ ይቀበላሉ። ለምሳሌ ዒሳ ከድንግል ነው የተወለደው የሚለውን ትልቅ እምነት የሚጠይቀውን ንግግር የተቀበሉት ዒሳ በቁርአን ውስጥ እኔ ከድንግል ነው የተወለድኩ በማለት ስለተናገረ ሳይሆን አላህ ራሱ ዒሳ ከድንግል ነው የተወለደው በማለት

ስለተናገረ ነው። ዒሳ ከድንግል መወለዱን ለማመን ለእነርሱ በቁርአን ውስጥ የተጻፈው የአላህ ንግግር ብቻ በቂ ከሆነ ለኛም ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ለመቀበል የእግዚአብሔር አብ ንግግር ብቻ በቂ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም። ስለዚህ እግዚአብሔር አብ ስለልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ምን ብሎ እንደተናገረ የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ መዝሙረ ዳዊት ውስጥ የተጻፈውን ትንቢት በመጥቀስ የተናገረውን እንመልከት።

“ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን በወረሰ
መጠን እንዲሁ ከእነርሱ አብዝቶ ይበልጣል።
ከመላእክትስ። አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፥
ደግሞም፦ እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ
ይሆነኛል ያለው ከቶ ለማን ነው? ደግሞም በኩርን
ወደ ዓለም ሲያገባ። የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም
ለእርሱ ይስገዱ ይላል። ስለ መላእክትም። መላእክቱን
መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ
ይላል፤ ስለ ልጁ ግን። አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ እስከ
ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት
በትር ነው። ጽድቅን ወደድህ ዓመፅንም ጠላህ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ
በደስታ ዘይት ቀባህ ይላል። ደግሞ ጌታ ሆይ፥ አንተ
ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማዮችም የእጆችህ
ሥራ ናቸው፤ እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ

ትኖራለህ፤ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፥ እንደ
መጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል፤ አንተ
ግን አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም ይላል።
ነገር ግን ከመላእክት ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ
እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ ከቶ ለማን
ብሎአል? ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው
ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት
አይደሉምን?” ወደ ዕብራውያን 1፡4-14
በዚህ ጥቅስ መሰረት እግዚአብሔር አብ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን መላእክት የሚሰግዱለት፣ ጌታ፣ አምላክ፣ ዘላለማዊ ዙፋን ያለው፣ የሰማያት ፈጣሪ፣ ወዘተ በማለት ይጠራዋል። ይህ ለክርስቲያኖች ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ለመቀበል ብቻውን በቂ ማስረጃ ነው።
ሐዋርያት ምን አሉ?
የኢየሱስ ሐዋርያት ከእርሱ ጋር አብረው ስለነበሩ ስለማንነቱ ከማንም በላይ ያውቃሉ ስለዚህ የእነርሱ ምስክርነት ለኢየሱስ አምላክነት ትልቅ ማስረጃ ነው። ቀጥሎ እነዚህ ቅዱሳን ሰዎች ስለ እርሱ አምላክነት የተናገሯቸውን እንመለከታለን።
ስምዖን ጴጥሮስ
“የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ ስምዖን
ጴጥሮስ፥ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር
እምነትን ላገኙ፤ የመለኮቱ ኃይል፥ በገዛ ክብሩና

በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና

እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ

ሰጠን፥ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት

ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።” 2 ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1፥1-3

የዘብዴዎስ ልጅ ዮሃንስ

“በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር

ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ

በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ

በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ

አልሆነም።” የዮሐንስ ወንጌል 1፥1-3

“የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም

የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን

እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥

እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ

አምላክና የዘላለም ሕይወትነው።” 1 ኛ የዮሐንስ መልእክት 5፥20

ቶማስ

“ቶማስም ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት።

ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ

ብፁዓን ናቸው አለው።” የዮሐንስ ወንጌል 20፥28-29

ጌታ ኢየሱስን ፊትለፊት በማየቱ ምክንያት እና ከሐዋርያት ጋር

እንደማገልገሉ መጠን የሐዋርያው

ቅዱስ ጳውሎስ ምስክርነት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

እርሱስ ስለ ኢየሱስ አምላክነት ምን አለ?

“አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ

በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም

የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን።” ወደ ሮሜ ሰዎች 9፡5

“ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ

ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን

ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም

የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ

ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን

በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል

በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል።” ወደ ሮሜ ሰዎች 9፡11-13

ከላይ የተመለከቱትን ማስረጃዎች ካጤነ በኋላ ኢየሱስ ስለ አምላክነቱ አልተናገረም በማለት የሚሞግት ለህሊናው ያደረ ሰው ይኖራል የሚል ግምት የለንም።

ኢየሱስ እንዲህ አለ

ያለውና የነበረው ወደፊትም የሚኖረው የሚመጣውንም የሚመገዛ አልፋ

ኦሜጋ ጌታ አምላክ እኔ ነኝ ራዕ 1፡8

ኢየሱስ ጌታ ነው 1 ኛ ቆሮ 12፡3

ኢየሱስ ጌታ ነው ብለህ በአፍህ ብትመሰክር ትድናለህ ሮሜ 10፡9

ብዙ ግዜ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ አላረኩም ለምን አለ ለምን አለ? አምላክና አባት አለው በማለት ይሟገታሉ

እኔ የምለው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ የማርያም ልጅ ማለት ሳንረዳ ከሆነ ይህን ያልነው ትልቅ ኪሳራ ውስጥ ነን

ኢየሱስ ፍፁም ሰው ነው

ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ነው

በምድር ላይ ሲመላለስ በተዋህዶ ነው ፍፁም ሰውነቱና ፍፁም አምላክነቱ አንድ በመሆን በመዋህድ ስለዚህም ኢየሱስ ለለበሰው ስጋ እግዚአብሔር አብ አምላክ ነው

እደግመዋለሁ ኢየሱስ ለለበሰው ስጋ ፣ ሰውነቱ እግዚአብሔር አምላክ ነው

ኡየሱስ ፍፁም አምላክ ነው ብለናል ከሶስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚአብሔር አብ የወጣ ቃል ነው

ስለሆነም እግዚአብሔር ወልድ አግዚአብሔር አብን አባቴ እያለ ይጠራዋል

እግዚአብሔር አብም እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስን ልጄ እያለ ይጠራዋል

እንግዲህ ምኑ ጋር ነው ስህተቱ መለኮትና ስጋ አንድ በሆኑበት ተዋህዶ

በስጋው አምላኬ በመለኮቱ አባቴ ማለቱ???

አሁን የተግባባን መሰለኝ ሌላው ደግሞ..

አምላክ ነኝ ያለውን ከላይ ካያችሁ አሁን ከናንተ የሚጠበቀው ማመን ነው እምነት ከመስማት ነው መስማትም የእግዚአብሔርን ቃል ነው ተብሎ ተፅፏልና እግዚአብሔር ሆይ በማስተዋል እንዲያነቡት አግዛቸው ።

52/ ከመከራና ከክፉ ሰው አትሸሽ

ከመከራ የምትሸሽ ከሆነ መንፈሳዊም ይሁን ስጋዊ ጥንካሬህ ፊላ ሆኗል

ማለት ነው

መንፈሳዊ ድፍረትህ ሊከዳህ ሲል መከራን መሸሽ ትመኛለህ ምልክቱ ደግሞ እንቶ ፈንቶ ወይም እሰጣ ገባ ባህር ውስጥ ገብተኽ በልደር ባይነት ተጠምቀኽ ስለፍቅር የሚል ስም ይዘህ ትወጣና ሐጢአትን በፍቅር ስም እየሳምክ ጽድቅን በመንከስ የአስመሳይነት ጦር እቃ ጥርስህን ታጠነክራለህ ።ነፍስህ እያረረች ስጋህ ትበስላለች

ከክፉ ሰው አትሸሽ

ከክፉ ሰውም አትሸሽ ግን ተጠንቀቅ ምክንያቱም የክፉትን መልክ ካላየህ የደግነት መልክ መልካምነትን አታደንቅም ከመልክ ጥፉ ጋር ካልተወዳደርክ አትመረጥም የራስህን የተሻለ መልካምነትን ለማድነቅ ክፉትን ማየት ይኖርብሐል ክፉውን መሆንና ማድረግ ግን መሸነፍ ነው ።

መንፈሳዊ?

ከሁሉ አስቀድመህ ንስሐ ግባ

በጾምና በጸሎት ትጋ

ለጸሎትህ ኃይልና ብርታት እንድትሆንህ የእመቤታችንን አማላጅነት ጠይቅ

ከዚህ በኋላ ቅድስናህን ሰይጣን እንዳይቀማህ ጠብቅ

መንፈሳዊ ህይወትህ እድገቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ከቤተክርስቲያን አትራቅ

ለማስቀደስ ለሰርክ ጸሎት ትጋ

ወንጌልን እንደ ቅዱስ መንፈሱ ተረዳ እንጂ እንደራስክ ስሜት አትተርጉም

በዚህ መስመር ለመጓዝ ትእግስት ይኑርህ

ቁጡ አትሁን

53/ † † † ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አትታደስም!!

ምድራችን እስከ ዕለተ ምጽአት ከመልካም ስንዴው ጋር እንክርዳዱን ማብቀሏ፤ ከየዋሁ በግ ጋር ተኩላውን ማሰለፏ፤ ከንጹሐን ሐዋርያት መካከል ይሁዳን ማስገኘቷ አይቀርም። እንክርዳዱ እንዳይነቀል ከስንዴው ጋር አብሮ በቅሎ ፣ ተኩላው እንዳይጋለጥ በግ ይመስል ዘንድ ለምድ ለብሶ ከስንዴው ጋር ልዘናፈል ፣ ከበጉም ጋር ሊመሳሰል ብለው ያልሆኑትን ለመሆን እየታገሉ ለዓላማቸው መስለው የሚሠሩ ተቀርቋሪም ሆነው የሚቀርቡ በማባበል ቃል የሚጎዱ ከፍጥረት ጅማሬ እስከ ዘመን ፍጻሜ፤ ከመላእክት ከተማ እስከ ደብረ ዘይት ተራራ ጌታችን እስከሚገለጥበት ቦታ ከገነት እስከ ዛሬዋ መቅደስ ስተው እያሳቱ ክደው እያስካዱ ከዚህ ዘመን ደርሰዋል።ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን በዚህ ሁሉ መከራ የምትሰጥም ለሚመስላቸው ደጆቿን ለመስበር ለሚታገሉ በዙሪያዋ እንደ አንበሳ ለሚዘሩ &ከሠሪው ጋር ለሚታገል ወዮለት& /ኢሳ. 45/ ከማለትስ ሌላ ምን እንላለን ? መሠረቷ ዐለት ነውና ብትወድቁበት ትሰበራላችሁ ቢወድቅባችሁ ትፈጫላችሁ ከማለት ሌላስ ምን እንናገራለን ? / ኢሳ.8/። ኦርቶዶክሳውያን ፦ ተሃድሶ የለም ብሎ የሚያስብ ከእኛ መካከል ይኖራል ብለን አላስብም ፤ ፀሙ በዛ ፥ ይቀነስ ፤ ቅዳሴው ረዘመ ፥ ይጠር ፤ እምነት

እንጂ ምግባር ምንም አይሰራም ፤ ቅዱሳን የሁሉን ፀሎት መስማት አይችሉም ፤ ገድላት ድርሳናት ይወገዱ ፤ ወዘተ የሚሉ የምንፍቅና ሃሳቦችን ይዘው በቤተክርስቲያን ጉያ ተሰግስገው ፥ የቤተክርስቲያንን ስም አንጠልጥለው የሚባዝኑ የትየለሌ ናቸውና።

ዛሬ ተሃድሶወች ተዋህዶን ለማጥቃት ተሰልፈዋል ፥ ባህርዳር ውስጥ ቅዳሴ ቀዳሽ ዲያቆናትና መርጌቶች መናፍቃን አዳራሽ ደግሞ ዘማሪወች ሆነው አይተናል ፥ ማርያም ቤተክርስቲያን ካህን ፥ ከፕሮቴስታንት ግን ደመወዝ የሚከፈላቸው አሉ ፤ በየገዳማቱ ገንዘብ ተመድቦላቸው መነኮሳትን ከባእታቸው የሚያስኮበልሉ ፥ ገዳማትን የሚያራክሱ ፥ ብህትውናን የሚያስነቅፉ አሉ ፤ ቅዱሳን አያማልዱም ፥ ክርስቶስ አማላጅ ነው እያሉ እኛ ግን ኦርቶዶክሳውያን ነን የሚሉ የፅጌ ስጦታው ፍሬወች አሉ።

ኦርቶዶክሳውያን ፦ ሁሉም ግን ከበስተጀርባ ያነገቡት አላማቸው አንድ ነው ፥ ይሄውም አለማዊ ንዋይ ማካበት ፤ የቤተክርስቲያኗን ዶም ፀሎት ስግደት መራቅ ፥ ማናናቅ ፤ ትህትናን አርቆ ትእቢትን መልበስ ፤ ስለገንዘብ ሲሉም የትኛውንም ክህደት መፈፀም።

እኛ ግን በተረዳንበት ፥ በቃልም ብቻ ያልሆነ በህይወት ቀምሰን አጣጥመን በምንኖርበት እምነት ይሄውም በክርስቶስ አለትነት በነብያት ትንቢት በሃዋርያት ትምህርት ላይ ፀንተን ቆመናል።

ይህን እምነታችንን ስለመጠበቅ እንትጋ ፥ ነገር ግን ዲያቢሎስ በእኛ እንዳይከብር ስድብና ክፉ ቃላትን በፍፁም ከአንደበታችን አይውጣ።

እግዚአብሄር አምላካችን ሃይማኖታችንን ይጠብቅልን። አሜን።

54/ ዓይኔን ጨፍኜ ብጸልይስ?

"አሳቤ ተሰብስቦ ረጋ ብዬ መጸለይ የምችለው አይኖቼን ስጨፍን ነው። ሰዎች ደግሞ ዓይን ከድኖ መጸለይ የመናፍቃን ስለሆነ ልክ አይደለም" ይሉኛል። በዚህ ላይ ምን ትመክሩኛላችሁ።

<ምሳሌ 16:30 ዓይኑን የሚዘጋ ጠማማ አሳብን ያስባል>

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የምንጸልየው ዓይኖቻችንን ከፍተን ወደ ላይ ወደ ሰማይ አቅንተን ነው። ምክንያቱም እንዲህ መጸለይ የቅዱሳን አበው ሥርዓት ነውና። ይህንን በተመለከተ ልበ አምላክ ዳዊት "ዓይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ" ብሏል። (መዝ 120÷1) በተጨማሪም "በሰማይ የምትኖር ሆይ አይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ። እነሆ የባሪዎች ዓይኖች ወደ ጌታቸው እንዲሆኑ የባሪያይቱም ዓይን ወደ እመቤቷ እጅ እንደሆነ እንዲሁ እስኪምረን ድረስ ዓይናችን ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ነው።" ብሏል። (መዝ 122÷1-2)

+ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በወንጌል ያስተማረን ዓይንን ከፍቶ ወደ ሰማይ አቅንቶ መጸለይ ነው።

"ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ። አባት ሆይ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ።"

(የዮሐንስ ወንጌል 11:41)

" ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ወደ ሰማይ ዓይኖቹን አነሣና እንዲህ አለ። አባት ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአል፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ፥ በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደ ሰጠኸው፥ ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ

ልጅህን አክብረው።"

(የዮሐንስ ወንጌል 17:1-2)

ከዚህም የተነሣ የሐዲስ ኪዳን ምእመናን ሁሉ የሚከተሉት ይህንኑ የጸሎት ሥርዓት ነው። ለምሳሌ ቅዱስ እስጢፋኖስ በአይሁድ እጅ በድንጋይ እየተወገረ እርሱ ግን ዓይኑን ከፍቶ: ወደ ሰማይ አቅንቶ "ጌታ ሆይ ነፍሴን ተቀበል" እያለ ይጸልይ "ይህንን ኃጢአት አትቁጠርባቸው" እያለም ያማልድ ነበር። (የሐዋ 7÷54-58)።

ከላይ በአጭሩ ለመግለጥ እንደሞከርነው መሠረታዊው ነገር ይህ ሲሆን የጠያቂያችን አሳብ ግን ከዚህ ወጣ ያለ ነው። ከጥያቄው እንደተረዳነው ዓይንን ጨፍኖ ለመጸለይ የቀረበው ሰበብ "አሳብ ይሰበስብልኛል: ልቦናዬም ይረጋጋልኛል" የሚል ነው። ነገር ግን ዓይን ስለተጨፈነ አሳብ አይሰበሰብም: ልቦናም አይረጋጋም። ምክንያቱም ዓይንን በመጨፈን አሳብ የሚሰበሰብ ቢሆን ኖሮ ዓይኖቻቸው የጠፋባቸው ወገኖቻችን ሁሉ ለጸሎት በሚነሡበት ጊዜ ልቡናቸው አይበተንባቸውም ያሰኛል። ምናልባት "ነገር በዓይን ስለሚገባ ነው" ይባልም ይሆናል። ይሁን እንጂ ነገር በጆሮም ይገባል: ታዲያ ስንጸልይ ጆሮዎቻችንን በጥጥ ልንወትፍ ነው?

የተወደዳችሁ አንባቢያን እኛ በስሜታዊነት በአንድ ጊዜ ከመንፈሳዊ ሕይወት ጫፍ ላይ ለመውጣት: አንድ ጊዜ ከፍጽምነት ማዕረግ ለመድረስ ስለምንፈልግ እንጂ አሳብን ሰብስቦ በተረጋጋ ልቦና መጸለይ በአንድ ጊዜ የሚደረስበት ጸጋ አይደለም። ምክንያቱም መንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ አለው። በመሆኑም በብዙ ገድል ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላኛው ደረጃ በእግዚአብሔር ቸርነት እያደጉ ይደርሱበታል እንጂ ቁጭ ተብሎ ስለተፈለገ ብቻ የሚገኝ

አይደለም። ስለዚህ በምንጸልይበት ጊዜ የሚረብሹ ብዙ የአሳብ ውጣ ውረዶች ቢኖሩም ከእነርሱ ጋር በእምነት እየተጋደልን እስከመጨረሻው መጽናት አለብን። በዚህን ጊዜም እነዚያ የሚያስቸግሩን ነገሮች ሁሉ ቀስ በቀስ በእግዚአብሔር ፈቃድ እየጠፉልን ይሄዳሉ። ስለሆነም የክርስትና ሕይወት የገድል ሕይወት እንደሆነ ማወቅ አለብን። ቅዱስ ጳውሎስም " መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤" (2 ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 4:7) ያለው በከንቱ አይደለምና

(ምንጭ:ከ"ቃለ ተዋሥኦ" መጽሐፍ ላይ ከገጽ 17-18 የተወሰደ በዲያቆን ጎሩይ ባየ)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፎቶዎች / Ethiopian Orthodox Tewahido Photos

55/ የጸረ ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ጥምረት ጠንካራ መግለጫ አወጣ

ቅዱስ ሲኖዶስና የሚመለከታቸው አካላት አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ እየተጠየቀ ነው

ሌሎችም በርካታ ማኅበራትና የቤተ ክርስቲያኗ አካላት ተቃውሟቸውን እያሰሙ ነው

እቢኤስ ቴሌቪዥን በኦርቶዶክስ ስም የሚቀርቡ ስርጭቶች የኦርቶዶስ ለመሆናቸው ማረጋገጫ እንዲጠይቅ ተጠይቋል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ስም የተሰየሙ : ነገር ግን ፍጹም የቤተ ክርስትያን ያልሆነ እና ኢ ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት የሚሰጥባቸው ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ ቤተ ክርስትያኗ አፋጣኝ እርምጃ እንድትወስድ የጸረ ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ጥምረት አሳስቧል::

ማንም የፈለገውን እምነት በነጻ ማራመድ እንደሚችል ነገር ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስም እየተጠሩ ከቤተ ክርስትያኗ አስተምህሮ የሚጻረር ትምህርት በአስቸኳይ መቆም እንዳለበትና ቤተ ክርስትያኗም በስሟ የሚነግዱ ጣብያዎችን በሕግ መጠየቅ የምትችልበት ሁኔታ እንዲመቻች ተጠይቋል::

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን ላይ ሰፊና ረቂቅ ዘመቻ እንደተከፈተና ይህም ዘመቻ ቤተ ክርስትያኗ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ቤተ ክርስትያኗን ገዝግዞ ለመረከበ አላማ ያለው በመሆኑ እያንዳንዱ ምዕመን ቤተ ክርስትያኑን ነቅቶ እንዲጠብቅ አሳስቧል::

በተለይም "ታዖሎንስና" "ቃለ አዋዲ" የተባሉ ; በኦርቶዶክስ ስም የሚጠሩ ነገር ግን ፍጹም ኦርቶዶክሳዊ ላህይና መልዕክት የሌላቸው ዜማዎች ትምህርቶችና ስብከቶች እየተላለፉ መሆኑንና ; እነዚህም ጣብያዎች በኦርቶዶክስ ስም ቤተ ክርስቲያኒቱን የማይወክል ትምህርት ማስተላለፍ ስለማይችሉ ቤተ ክርስትያኗ ይህንን በህግ እንድታስቆምና በቤተክርስትያን

ስም የሚተላለፉና ለሕዝብ የሚቀርቡ የሬዲዎና የቴሌቭዥን ስርጭት በቤተ ክርስትያኒቱ የበላይ አካል የተፈቀደ መሆን እንደሚኖርበት ተጠቅሷል::

ሌሎችም በርካታ የቤተ ክርስትያን አካላት በዚህ ጉዳይ ላይ በመምከር ላይ ሲሆኑ በቅርቡ አቋማቸውን ይፋ እንድሚያደርጉ ይጠበቃል:: የኢቢኤስ ቴሌቪዝንም በኦርቶዶክስ ስም የሚተላለፉት እነዚህ ጣብያዎች የቤተ ክርስትያን ለመሆናቸው ህጋዊ ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ካልሆነ ግን በኦርቶዶክስ ስም መነግዳቸውን እንዲያስቆም እየተጠየቀ ነው:: በየደረጃው ያሉ የቤተ ክርስትያን አካላት አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ ተጠይቋል::

ዝርዝር ውይይቶችን በተከታታይ ክፍል እንለጥፋለን

youtu.be

YOUTUBE.COM

September 19 at 11:24am · Public

Unlike Page · More

Bini Zelideta and 214 others like this.

Write a comment...

Comment

Mention Friends

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፎቶዎች / Ethiopian Orthodox Tewahido Photos

https://www.youtube.com/watch?v=t6iQ63-pNoY

የጸረ ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ጥምረት መግለጫ

youtube.com ·

Like · 11 · Reply · Report · Sep 19

Wongel Yashenifal Afework Alaro

እኔን በጣም የምገርመኝ የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን በመፅሀፍ ቅዱስ አታምንም እንዴ በ EBS TV የሚሰበከው እኮ የእግዚአብሄር ቃል ነው፤እናንተ እንደ ሰዱቃዊያንና ፈርሳዊያን ሰው ሰራሽ ህግ እንዲሰበክ ትፈልጋላችሁ፤የእግዚአብሄርን እውነት አፍናችሁ ልታስቀሩ አትችልም፤ይህንን ደግሞ እወቁ፤ጨለማ ብርሃንን አያሸንፍም።

Like · 11 · Reply · Report · Sep 20

10 replies

Solomon Abate

ቀጥሉበት "ሽል ከሆነ ይገፋል ዱባ ከሆነ ይጠፋል"

Like · 10 · Reply · Report · Sep 20

Mulne Ze Mmgw

እግዚአብሄር የትንቢት መፈፀምያ አያድርገን። በዚህኛው መንግስት ዘመን ፍቅር በቤተ መቅደስ ትቀዘቅዛለች የተባለበት ወቅት ነው።ሁላችንም ልናስተውል እንጂ ልንካሰስ አይገባም። እባካችሁ ሁሉን መግለፅና ፣ማድረግ ወደሚችለው አምላክ እንለምን። አለም ላይ የቀረች ብቸኛ የእግዚአብሄር የስሙ መገኛ የሆነች ሀገራችንን ማስተዋል አጥተን እርስ በራሳችን ስንወነጃጀል ከሰማያዊ በረከት አናርቃት። ይህን ችግር ደግሞ በፆምና በፀሎት ነው ልናሸንፍ የምንችለው። እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ።አሜን

Like · 6 · Reply · Report · Sep 20

Meseret Haile

በእዉነት እግዚአብሄር አምላክ የእያንዳንዱን አባቶች እንዲሁም ምዕመን ልብ ያብራ በጣም የሚገርመኝ የኦርቶዶክስ አስተምሮ ያልሆነ ስብከት ቁጭ ብለው የሚያዳምጡ አባቶችና ምዕመናንን በአዳ፟ራሽ ማየታችን ልብ ይስጠን.

Like · 4 · Reply · Report · Sep 19

2 replies

Aklilu Solomon

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስብከቷም ቅዳሴዋም በእውነት ስለክርስቶስ ነው፤ ክብር ለሚገባው ክብርን ትሰጣለች በእውነት የኛ ከሆኑ እንደወንድሞቻቸው ለምን በቤቱ አይሰብኩም ስለዚህ ቤተክርስቲያን ዝም ልትል አይገባም እነዚህ የበግ ለምድ የለበሱ ናቸው በመጨረሻ ሰዓት ዋኖቹም ይስታሉ፤

Like · 3 · Reply · Report · Sep 21

Ab Yemariyam Lije

ዘገያችሁ ግን ደስ የሚል ዜና ነው እግዚአብሔር ይመስገን በረቱ ድንግል እመቤቴ ትርዳችሁ!!!

Like · 1 · Reply · Report · Sep 20

Yerom Desalgne

አቤት የሰው ክፋት አሁን እውንነት ለቤተ ክርስቲያን ለአይማኖት ተቆርቁራችሁ ነው

አይመስለኝም እንደኔ እንደኔ

ወንጌል ለምን ተሰበከ ካልሆነ በስተቀር

ለሁሉም እግዚያህቤር ይፍረድ እሱ የያንዳንችንን ስራ ያያል

34 Like · 1 · Reply · Report · Sep 21

Tola Gurba

ገማልያል የተባለ የሙሴ ሕግ ምሑር ሐዋርያትን የሚያሳድዱትን ሊቀ ካህናቱንና የእስራኤልን ሰዎች ሁሉ ያላቸው ነገር ትዝ አለኝ።

" እንዲህም አላቸው የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ስለ እነዚህ ሰዎች ምን እንደምታደርጉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳስ እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ ተነሥቶ ነበርና፥ አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበተኑ እንደ ምናምንም ሆኑ። ከዚህ በኋላ ሰዎች በተጻፋበት ዘመን የገሊላው ይሁዳ ተነሣ ብዙ ሰዎችንም አሸፍቶ አስከተለ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበታተኑ። አሁንም እላችኋለሁ ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ ተዉአቸውም፤ ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደ ሆነ ይጠፋልና፤ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም፥ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ። ... " ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር።

" (የሐዋርያት ሥራ 5:35-42)

Edited · Like · 1 · Reply · Report · Sep 20

Tola Gurba

አሁን እዉነትን የተራበ ትውልድ ነው ያለው ፤ ተረት ተረት የሰለቸው ።

እግዚአብሔር ይመስገንና መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል ብሎ የሚመራመር ትውልድ ተነሥቷል ፤ ቄስ እገሌ ወይ መምህር እገሌ ወይ ደግሞ ፓስተር እገሌ ምን አለ ብሎ የማይወሰን ። ይሄ የተሃድሶ ሰደድ እሳት ፈጽሞ የሚጠፋ አይደለም። የሃይማኖት ተቆርቋሪ የምትመስሉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ።

56/ ሙስሊሙን ዓለም ለውድቀት የዳረጉት ዋና ዋና ክስተቶች (2)

ኮሎኒያሊዝም

በዚህ የታሪካችን ምእራፍ ሙስሊሞች በቅኝ ገዢዎችና በገዛ መሪዎቻቸው ለከፋ ባርነት የተጋለጡበትን የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን እንመለከታለን። ቅኝ ገዥዎች የሕዝቦችን ሰብአዊ፣ ኃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃነት ገፈዋል። የተፈጥሮ ሃብታቸውን ዘርፈዋል። ከሁሉም የከፋው ግን ኢስላማዊውን የሥርዓተ ትምህርት በማፋለስ ሞራል አልባ የሆኑ ባእድ እሴቶች የታጨቀባቸው ትምህርቶች መፈብረካቸው ነበር።

ይህ ሴራ በጥናትና በምርምር በጥንቃቄ የታቀደና መጪው ሙስሊም ትውልድ ወርቃማ ታሪኩን እንዲረሳ፣ እንዲጠላ፣ በራሱና በሐይማኖቱ እንዲያፍር፣ ኢስላም ለዘመናዊ አኗኗር የማይሆን ኋላቀር ስርዓት መሆኑን ለማሳመን የተቀነባበረ ነበር። የቅኝ ገዢዎች አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ በሙስሊሞች አእምሮ ምእራባዊ አስተሳሰቦችንና እሴቶችን በማጨቅ ላይ

ያተኮረ ነበር። ኮሎኒያሊስቶች እውነተኛና ለዓለም ጠቃሚ እውቀት የምእራባውያን ብቻ መሆኑን፣ የሰው ልጆች ስልጣኔም መሠረት በነርሱ አስተሳሰቦች ላይ ሊቀረጽ እንደሚገባና የሌሎች ሕዝቦችና ሐይማኖቶች ስልጣኔዎች የማይረቡ መሆናቸውን ለማሳመን ብዙ ጥረዋል። ይህ በሙስሊሞችና በሌሎችም የዓለም ሕዝቦች ላይ የተፈጸመ ታላቅ ወንጀል ነው። ሕዝቦችን ከታሪካቸው፣ ከባህላቸውና ከእሴቶቻቸው ለመነጠል የተደረገ ጥረት ነው።

በሌላ በኩል የቀድሞ ኢስላማዊ ሥርዓተ ትምህርት ሙስሊሞችን ከሐይማኖታቸው ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ ነበር። ራሱን የቻለ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ የፈጠረ ነበር። ቅኝ አገዛዝ ይህንን ነበር ያወደመው። ታላላቅ ሙስሊም አሊሞችንና ምሁራንን፣ ሙስሊም ሳይንቲስቶችን፣ የሕክምና ጠበብትን ያፈሩ መድረሳዎችና ዝነኛ ኢስላማዊ የትምህርት ተቋማት ተዘግተው አልያም ተዘንግተው በምትካቸው ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች ተፈለፈሉ። ዓለማዊ ጥቅሞችንና ስኬቶችን የፈለጉ ሙስሊሞች ሁሉ ወደነዚሁ የትምህርት ተቋማት ለመግባት ተገደዱ። ይህ ሁኔታ ቆይቶ በሙስሊሙ ዓለም ዘላቂ ችግር አስከትሏል። በተለይ ብሩህ አእምሮ ያላቸው ሙስሊም ልጆች በነዚህ ተቋማት ሕሊናቸው ተበርዞ ሲወጡ ራሳቸውን ከኢስላም እንዲያርቁ፣ ኢስላማዊ ባህላቸውን እርግፍ አድርገው እንዲተው ከማድረጉም በላይ በኢስላም ላይ ጥላቻ እንዲያሳድሩና የበታችነት ስሜት እንዲሰማቸው ሆኗል።

በአዳዲስ መሪዎች መፈጠር፣ ሙስሊሞችን በተለይ ወጣቱን ትውልድ ከሐይማኖታቸውና ከባህላቸው ለመነጠል የተወጠነው ሴራ ወዲያው ግቡን መታ። ሙስሊም ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በምእራባውያን ቅኝ ገዢዎች ወደ ተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ለመላክ በመገደዳቸው አዲሱ ትውልድ ከኢስላም እየራቀ ሄደ። በተለይ በመንግስት መዋቅር ውስጥ የተሻለ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ለመጎናጸፍ ከኢስላም ራስን ማራቅ ለእድገት እንደ መመዘኛ በመወሰዱ ለሃይማኖታቸው ደንታ የሌላቸው አያሌ ሙስሊሞች ተመረቱ። በርግጥ ይህ ፖሊሲ የተተገበረው በመግስት አዋጅ አልነበረም። ቅኝ ገዢዋች፣ ሙሰሊሞች ልጆቻቸውን ወደ ተቋማቱ እንዲልኩ የተለያዩ የማታለያ መንገዶችን ተጠቅመዋል። በዚህ ሂደት በአጭር ጊዜ ውስጥ የስልጣን እርከኖችና ወሳኝ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቦታዎች በዚህ ብልሹ ትውልድ ተሞሉ። በመጨረሻም ከኢስላምና ከሙስሊሞች ይልቅ ለምእራባዊው ስልጣኔና እሴቶቹ ታማኝና ተከታይ የሆኑ መሪዎች ተፈጠሩ።

የነፃነት እንቅስቃሴዎች

ዘመናዊውን ትምህርት የተከታተለው አዲስ ትውልድ አባላት የምእራቡን ዓለም ስልጣኔና ታሪክ በቅርበትና በጥልቀት ለመረዳት ቻሉ። ይህ ሁኔታ በውስጣቸው የፖለቲካዊ ነፃነትን ስሜት አነሳሳ። ራሳቸውንም በተለያዩ ፖለቲካዊ ቡድኖችና እንቅስቃሴዎች በማደራጀት ሙስሊም ሃገራት ከቅኝ አገዛዝ እንዲላቀቁ ትግል ጀመሩ። እነዚህ የፖለቲካ ፊታውራሪዎች የምእራቡን አለም ጠልቀው መረዳታቸው ፖለቲካዊ አካሄዳቸውን አመቻችቶላቸዋል።

የወጣቱ ትውልድ መሪዎች ለኢስላምና ለሙስሊሞች ታማኝ ባይሆኑም ሕዝቡን ለራሳቸው ፖለቲካዊ መጠቀሚያነት ለማዋል አልሰነፉም። በፕሮፓጋንዳቸው ሃይማኖታዊ ነጥቦችን በማንሳት የሙስሊሙን ስሜት በመኮርኮር ከጎናቸው ለማሰለፍ ችለዋል። ትግላቸው ከኩፍር ጋር እንደሆነ በማስመሰል ሙስሊሞች ለሃይማኖታቸውና ለነፃነታቸው ሲሉ የሕይወት መስዋእትነት መክፈል ሃይማሃታዊ ግዴታቸው እንደሆነ በመስበክ ሕዝቦች ቅኝ ገዥዎችን አምርረው እንዲዋጉ ቀስቅሰዋል። በየሃገሩ የሚኖሩ ሙስሊሞችም በዚህ መንገድ ተታለዋል። የአሳዛኙ የአልጀሪያ የነፃነት ትግል ሊጠቀስ ይችላል። አልጀሪያ ውስጥ ኢስላማዊ መንግስት በመመስረት ስም የተካሄደው ትግል በመጨረሻ ለጥቂት ግለሰቦችና ድኖች የስልጣን ማስገኛ ሆኗል። የነፃነት እንቅስቃሴው መሪዎች ሕዝቡን በጂሃድ ካልቀሰቀሱት እንደማይከተላቸው አወቁ። በዚህ መልኩ የሕዝቡን የዋሕነትና ለኢስላም ያለውን ፍቅር ለግል የስልጣን ጥቅማቸው አዋሉት።

በቱርክም ተመሳሳይ የፖለቲካ አሻጥር ተፈጽሟል። በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት ግሪኮች የቱርክ አካል የሆነችውን ኤሺያ ማይነርን ሲወሩ የቱርክ የነፃነት መሪ ሙስጠፋ ከማል ሕዝቡን ለትግልና ለጦርነት የቀሰቀሰው በኢስላም ስም ነበር። በየሙስሊም ሰራዊቱ መሃከል እየዞረ ቁርአንን ከፍ አድርጎ ሕዝቡ ለነፃነቱ በርትቶ እንዲዋጋ፣ አለበለዚያ ወራሪዎቹ ቁርአንን ከቱርክ ምድር እንደሚያጠፉት ይሰብክ ነበር። በኢስላም መጠቃት የበገነው ሕዝብም ተከተለው። ያለ በቂ ጦር መሳሪያ በአውሮፓ ይደገፍ የነበረውን የግሪክ ወራሪ ጦር ወግቶ አስወጣ። በነፃነቱ

ማግስት ግን ሙስጦፋ ከማልና አምባገነናዊ መንግስቱ የሚታወቁት በጸረ-ኢስላም ዘመቻቸው ሆነ።

በሌሎች ሙስሊም አገራትና አካባቢዎችም ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር። በአብዛኞቹ ሙስሊም አገራት የነበሩት የነፃነት እንቅስቃሴ መሪዎች በግላዊ እምነታቸው በምእራባዊ የአስተሳሰብ ተጽእኖ ስር የወደቁ ነበሩ። ኢስላማዊ እውቀት በእጅጉ ይጎድላቸዋል። ሕዝቡ ደግሞ በተጻራሪው ነው። ለኢስላም ታማኝ፤ ማንኛውንም አይነት መስዋእትነት ለመክፈል የተዘጋጀ ነበር። መሪዎቹ ከነፃነት ትግሉ በኋላ ግባቸው የስልጣን ጥማታቸውን ከማርካት፣ ከሚለቁት ቅኝ ገዥዎች እግር ተተክተው ጭቆናውን በአዲስ መልክ ከመቀጠል ውጭ ሕዝቡ የታገለላቸውን መብቶች አንዱንም አላስከበሩለትም።

Miko ZE Ethiopia

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን!

57/ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐይማኖት እና የፕሮቴስታንት እምነት ልዩነት ክፍል አንድ

ሳሚ ዘቂርቆስ 01/04/07

የምትናፍቁኝ እና የምናፍቃችሁ ወዳጆቼ በወደደን እስከ ሞት ድረስ በአፈቀረን በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ፍቅር እንደምን ቆያችሁ? ለዘላለማዊ

ሕይወት እና ለሰማያዊ ክብር ብቻ የመረጠን ብናመሰግነው የማይሰለቸን አምላካችን እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው። ለወላዲተ አምላክ ለድንግል ማርያምም ምስጋና ይድረሳት ለመላእክቱ ቅዱሳኑ ለሰማእታቱ ለጻድቃኑ እንዳከበራቸው መጠን ምስጋና ይሁን።

የትምህርቱ አላማ "ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ" ማቴ 24፡4 እንዳለን ጌታችን ሐይማኖታችንን እንድናውቅና መስለው ከሚኖሩት እንድንጠነቀቅ ነው።

ወዳጆቼ እንደጌታ ፍቃድ ተከታታይ ትምህርት ስለሆነ በጥሞና እንድትከታተሉኝ እያሳሰብኳችሁ ደግሞ በእውነት አቅሙን እና ጥበቡንም እንዲሰጠኝ በጸሎታችሁ ታስቡኝ ዘንድ አደራ እላችኋለው።

1. ክርስቶስን በተመለከተ

- ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ከተዋሕዶ በኋላ አንድ ባሕሪ ብላ ታምናለች(One nature)

- ፕሮቴስታንት ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት ባሕሪ ብላ ታምናለች (Two nature)

ግልጽ ለማድረግ

- ንስጥሮስ በ 431 ዓ.ም በኤፌሶን ጉባኤ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕሪ አለው።ይህ ሁለት ባሕሪ አንዱ የሥጋ አንዱ የመለኮት ሲሆን ምንም አልተዋሃዱም ብሎ ተነሳ

- ቅዱስ ቄርሎስ በዚሁ ጉባኤ አንድ ብረት ቀጥቃጭ ከብረት መሳሪያን ሲሰራ ብረቱን እሳት ውስጥ ይከተዋል ከዚያም ብረት የእሳቱን ባሕሪ እሳቱም የብረት ባሕሪን ይዋሃዳል። ስሙ ተቀይሮ የጋለ ብረት እንለዋለን።

- እንዲሁ ከተዋሕዶ በኋላም በእሳት የተመሰለው መለኮት በብረት የተመሰለውን የስጋ ባሕሪ ገንዘቡ አድርጓል። አምላክ ሰው ሁኗል፤ሰውም አምላክ ሆኗል።በመሆኑም ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት ባሕሪ አንልም። ይህ አሳማኝና እውነተኛ ትምህርት ነው።

2. ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያንን

- ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሁሉንም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አምና ትፈጽማለች

- ፕሮቴስታንት ምንም ዓይነት የቤተክርስቲያንን ምስጢራት አትቀበልም።

ግልጽ ለማድረግ

- ፕሮቴስታንት ጥምቀትን እንደ በጎ ተግባር እንጂ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ልጅነት ይገኝበታል ብለው አያምኑም።

- ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ግን ምሳ 9፡1ን መሰረት በማድረግ ሰባቱንም ምስጢራት ቤተክርስቲያን በሚታይ ነገር የማይታይ ጸጋ የምናገኝ በት እንደሆነ ታምናለች።

- "ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ ሰው መንግስተ ሰማይ አይገባም "(ዮሐ 3፡5)

ሜሮን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የምናገኝበት ምስጢር መሆኑን ታምናለች። (1 ዮሐ 2፡20-27)፤(2 ኛቆሮ 1፡22)፤(2 ቆሮ 1፡31)

ቅ.ቁርባን ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንደምናደርግበት ታምናለች። (ዮሐ 6፡56) "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ"

- የዘላለም ሕይወት ይሰጣል (ዩሐ 6፡53)

- የእርሱን መከራ የምናስብበት ነው (1 ቆሮ 11፡25)

- የጌታ ሥጋ ተብሎ ተገልጧል (1 ኛ ቆሮ 11፡29)

ንሰሐ፡- መናዘዝ መመለስ መጸጸት ማለት ነው።

- ለአባቶች ተናዝዘን ንሰሐ መግባት እንዳለብን ታምናለች።

- ኃጢአታችን ይደመስሳል (ዮሐ 93፡19)

- የመፍታትም የማሰርም ስልጣን ለካህናት ተሰጥቷል (ማቴ 16፡20)

- ማንም ራሱን ለካህን ብቻ ነው ማሳየት ያለበት (ማቴ 8፡14)

ቀንዲል፡- ለሕሙማን በሚጸለይ ጸሎት አማካኝነት የሚቀባ ዘይትን ቀንዲል እንለዋለን። ይህን ኦርቶዶክስ ትቀበላለች

- ሐዋርያት በዘይት ፈውሰዋል (ማር 6፡13)

- በትህዛዝ ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት እንዳለ(ያዕ 5፡14-5)

ምስጢረ ተክሊል ፡-አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት በመንፈስ ቅዱስ አንድ የሚሆኑበት ምስጢር ነው።(ማቴ 19፡14)

- ጋብቻ ቅዱስ ነው (ዕብ 13፡14)

ፕሮቴስታንት ጋብቻን በሁለት ጥንዶች መካከል የሚደረግ ኮንትራት እንጂ ምስጢሩን አያውቁትምም አይቀበሉትምም።

ምስጢር ክህነት፡- ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ካህናት ምስጢራትን የሚፈጽሙበት ሥልጣን ነው።

- በሰማይም በምድርም ስልጣን አላቸው (ዮሐ 20፡22)

- በእግዚአብሔር ተጠርቶ የተመረጠ ብቻ ነው በዚህ አገልግሎት የሚያገለግለው (ዕብ 4፡5)

- በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኛቸው ሶስቱ ዋና ዋና መሳርያት።

1 ጳጳስ (1 ጢሞ 3፡1-17)

2 ካህን (1 ጢሞ 5፡17)

3 ዲያቆን (ፍል 4፡2-3)

- ከእነዚህ መዕረጋት ውጪ የለም ሌሎቹ የሥልጣን፣የአመራር ስሞች ናቸው።
- ሐዋርያት ሾመዋል (ቲቶ 1፡5)

ይቆየን

Yehabesha.com

58/ የሆሊውድ ሴሊብሪቲዎችና እምነታቸው ምን ይሆን?

ብዙዎቹን በሙዚቃና በፊልሞቻቸው እናውቃቸዋለን፣ እንወዳቸዋለን። ወደ ግል ህይወታቸው ገባ ብለን ግን ስለ ዕምነታቸው ላናውቅ እንችላለን። ልክ የጋብቻ ኑሯቸው እንደሚያስገርም ሁሉ እምነታቸውም ሊያስገርም ይችላል፦ እስቲ የእንዳንዶቹ ሃይማኖት ምን እንደሆነ እንንገራችሁ፦

1- ማርሊን ሞንሮ፦ በሞት የተለየችው ታዋቂዋና ውቧ ማርሊን ሞንሮ የክርስቲያን ሳይንስ ተከታይ ነች። እምነቷ ክርስትና እና ሳይንስን አጣምሮ የያዘ ክርስቲያን ሳይንስ የተሰኘ ሃይማኖት ነው።

2- ጀኒፈር ሎፔዝ፦ ጀኒፈር ያደገችው በካቶሊክ ቤተሰብ ካቶሊክ ሆና ቢሆንም አሁን ቀይራ የሳይንቶሎጂ ዕምነት ተከታይ ሆናለች፣ ከማርክ አንቶኒ ጋር አንዱ ያላግባባቸውም ይኸው ነው ይባላል።

3- ብሪትኒ ስፒርስ፣ ታዋቂ ሙዚቀኛና ዳንሰኛ ናት .. ብሪትኒ ደግሞ የባብቲስት ዕምነት ተከታይ ነች፣ መሃል ላይ ግን ካባላህ የተሰኘና ማዶና እንደፈጠረችው የሚገመት ዕምነት መከተል ጀምራ ነበር፣ የመጀመሪያ ልጇን ከወለደች በኋላ ደግሞ ካባላህ በቃኝ ብላ ዕምነቴ ልጄ ነው ማለት ጀምራ ነበር፣ አሁን በቅርቡ እንደገና ባብቲስት ነኝ ብላለች ...

4- አንጀሊና ጆሊ፣ አንጀሊና ጆሊ ኢትዮጵያዊቷን ዘሃራ በማደጎነት ታሳድጋለች፣ የብራድ ፒትም ሚስት ናት .. አንጀሊና ጆሊ እምነቷ ምን ይመስላችኋል? .. ሞክሩ .. አንጀሊና እምነት የላትም ፣ “እግዜር አለ ብለው ለሚያምኑት ይኑርላቸው .. ፣ ለኔ ግን ግዴለም ነው የምትለው .. እግዜር የለሽ [ኤቲስት] ነች .. አንጀሊና ..፣

5- ጃክሰን ቫይቭ፦ የማይክል ጃክሰን ቤተሰብ ጃክሰን ቫይቮች ደግሞ የጆቫ ዊትነት ተከታዮች ሆነው ነው ያደጉት፣ ትልቅ ከሆኑ በኋላ ግን ሁሉም የየራሳቸውን ምርጫ ይዘዋል፣ ማይክል ወደ ህይወቱ መጨረሻ አካባቢ ጆቫ ዊትነስ መሆኑን በአደባባይ መናገሩ ይታወሳል።

6- ጀሲካ ሲምሰን፣ ውቧ ድምጻዊት ጀሲካ ሲምሰን አባቷ የባፕቲስት ሚሽን ፓስተር ነበር፣ እሷም ከዚያው ቀጥላ አሁንም ድረስ ባብቲስት መሆኗን ትናገራለች፣ በነገራችን ላይ ጀሲካ ሳላገባ ወሲብ አልፈጽምም ብላ ቆይታለች፣ ከዚያም “ኒክ ላቺን” አገባች፣ ያን ጊዜም “ጣፋጩ ሃጢአት” የሚል ዘፈን ለቃለች፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ከኒክ ጋር ያደረገችውን ወሲብ ለመጥቀስ ይመስላል።

7- ቶም ክሩዝ፦ ቶም ክሩዝ ከ 1990 ጀምሮ በመጀመሪያ ሚስቱ በሚሚ ሮጀርስ አማካኝነት የሳይንቶሎጂ ዕምነት ተከታይ ሆነ። አሁንም በሳይንቶሎጂ

እምነት ዋና ተሳታፊ ነው፡

8- ሪቻርድ ጊር፦ ሪቻርድ ጊር ታዋቂው የፊልም ተዋናይ፣ በ 1978 ዓም ቲቤት የሄደ ጊዜ በቲቤቶች ዕምነት ተማርኬያለሁ አለና ከዚያ ጊዜ ወዲህ የቡዲዝም እምነት ተከታይ ሆነ፣ ደላይ ላማ ራሳቸው አስተምረውታልም ይባላል፣ ሪቻርድ ጊር ቡዲስት ነው ማለት ነው ...

9- ማዶና፦ ማዶና የካባላህ እምነት ተከታይ ነች። ካባላህ ከጁዲዝም የወጣ የ ዕምነት አይነት ነው፣ ራሷ ማዶና ዋና ፈጣሪውም ናት ይባላል፣ ከዘጠናዎቹ ግማሽ ጀምሮ የተፈጠረ እምነት ነው።

10- ኬቪን ቤከን ፦ ታዋቂው የፊልም አክተር ኬቪን ቤከን እምነት የለውም ፣ እግዜር የሚባል የለም ባይ ፣ ኤቲስት ነው ማለት ነው፡

11- ሉፕ ፊያስኮ፦ ታዋቂው ራፐር ሉፕ ፊያስኮ ሙስሊም ነው፣ ያደገውም በሙስሊም ቤተሰብ መካከል መሆኑን ይናገራል።

12- ዘ ቢትልስ ፦ ዘ ቢትልስ የታወቁ ሙዚቀኞች እንደነበሩ ይታወቃል። ከነሱ መካከል አንዱ ጆርጅ ሃሪሰን ነው፣ ጆርጅ ከቢትልስ ጋር ህንድ አገር ሙዚቃ ለማቅረብ ከሄዱበት ጊዜ ጀምሮ ሃሬ ክሪሽና የሚባል የህንድ ዕምነት ተከታይ ሆኗል። ሃሬ ክሪሽናዎች በተለይ የሚታወቁት ሥጋና የሥጋ ዘር ባለመብላታቸው ነው፣ ቬጂቴሪያን ሆነ ማለት ነው።

13- ሲልቨር ስታሎን፦ ታዋቂውና ራምቦ በሚለው የፊልም ስሙ የሚታወቀው ሲልቨር ስታሎን፣ ድሮም አሁንም ካቶሊክ ነኝ ብሏል፣ በወጣትነቱ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን መሄድ አቁሞ የነበረ ቢሆንም ባለፉት አስር ዓመታት እንደገና እሁድ እሁድ መሄጅ ጀምሬያለሁ ነው የሚለው።

14- ኤልሳቤጥ ቴይለር፦ ኤልሳቤጥ ቴይለር በህይወት የለችም፣ ሆኖም

ኤልሳቤጥ በፊት ክርስቲያን ነበረች፣ ሁለተኛውን ባለቤቷን ኤዲ ፊሸር ስታገባ ግን ወደ ጁዲዝም ተቀየረች፣ እስክትሞት ድረስም የጁዲዝም እምነት ተከታይ ሆና ነው የኖረችው።

15- ላንስ አርምስትሮንግ፦ ላንስ አርምስትሮንግ በብስክሌት ውድድር በተለይ በፈረንሳዩ ቱር ደ ፍራንስ በተደጋጋሚ አንደኛ በመሆን ያሸነፈ ቢሆንም ሃይል ሰጪ መድሃኒት መውሰዱ በመረጋገጡ ዝናውን ያጣ ብስክሌተኛ ነው። ላንስ አርምስትሮንግ ታዲያ ሃይማኖት የለውም፣ እግዜር የለም ባይ [ኤቲስት] ነው።

16- ቬነስ ዊሊያምስ እና ሴሪና ዊሊያምስ፦ እነዚህ ሁለት ታዋቂ አሜሪካውያን የሜዳ ቴኒስ ሻምፒዮን እህትማማቾች፣ ከ እናታችን የወረስነው ነው ብለው የጆቫ ዊትነስ እምነት ተከታይነታችው በአደባባይ ይናገራሉ። ሴሪና በ 2008 ዓ.ም ለባራክ ኦባማ ድምጽሽን ትሰጪያለሽ? ተብላ ስትጠየቅ “እኛ ጆቫ ዊትነስ ነን፣ በፖሊቲካ ጉዳይ ላይ ድምጽ አንሰጥም ስለዚህ ማንንም አልመርጥም” ነበር ያለችው።

17- ኦርላንዶ ብሉም፦ ኦርላንዶ ብሉም የታወቀ የፊልም አክተር ነው፣ ከብራድ ፒት ጋር የሰራው ፊልም ዛሬም ድረስ ይታይለታል፣ ታዲያ ኦርላንዶ የቡዲዝም ተከታይ መሆኑን በቅርቡ ተናግሯል።

18- ዶ/ር ኦዝ፦ በሚያቀርባቸው የተለያዩ የህክምና ዝግጅቶች ቲቪ ላይ ይታወቃል . ዶክተር ኦዝ፣ ታዲያ ዶክተሩ የቱርክ ተወላጅ ሲሆን ድሮም ዛሬም የ እስልምና እምነት ተከታይ እንደሆነ ተናግሯል።

19- ጁሊያ ሮበርትስ፦ ጁሊያ ሮበርትስን ሁላችሁም ታውቋታላችሁ፣ ታዋቂ የፊልም አክተር ናት፣ ጁሊያ ሮበርት .. እምነቷ ታዲያ ሂንዱይዝም መሆኑን

ታውቁ ነበር? ጁሊያ ሮበርት ህንድ ሄዳ አንድ ፊልም ከቀረጸች በኋላ ጸጥታቸው ደስ አለኝ ብላ ወደ ሂንዱይዝም የተቀየረችው . .. እናም የሂንዱ እምነት ተከታይ ሆና ቀርታለች፣

20- ሌዲ ጋጋ፦ ሌዲ ጋጋ .. ድሮም ዛሬም ካቶሊክ መሆኗን በአደባባይ ተናግራለች። በሁሉም ትምህርታቸው ባልስማማም ግን ካቶሊክ ነኝ ነው ያለችው ... [አይ ጋጋ፣ የምትለውና የምታደርገው አታጣም]

21- ጀስቲን ቢበር፦ ጀስቲን ቢበር ወጣቱ ካናዳዊ ድምጻዊ ክርስቲያን ነኝ ይላል፣ እናቱ ዳግም የተወለደች ክርስቲያን ነች፣ እሱም የ እናቴን ነው የምደግፈው .. ዳግም የተወለድኩ ክርስቲያን ነኝ ብሏል ... ፣

22- በቅርቡ ከካንዬ ዌስት ጋር የተጣመረችው ኪም ካርዳሻን እና ቤተሰቦቿ ፣ እኛ ደግሞ የአርመን ኦርቶዶክስ ክርስቲያንን ነን ይላሉ፣ ኪም ከሃብቱ 10 በመቶ ለቤተክርስቲያን እሰጣለሁ ስትልም ትናገራለች።

23- በመጨረሻም የሩሴል ሳይመንን እንንገራችሁና እናብቃ ... ሩሴል ሳይመን የሂፖፕ ሙዚቃን ከፈጠሩት አንዱ ነው ይባላል፣ በሂፖፕ ሙዚቃ አካባቢ ሶስተኛው ሃብታም እንደሆነም ይነገርለታል፣ ታዲያ የሩሴል ሳይመን እምነት ምን መሰላችሁ .. ራሱም አያውቀውም .. ግን የሂንዱና የቡድሂስት ድብልቅ ነው ብሏል .. እና ደባልቆ የሚጠቀምበት የራሱ መመሪያ አለው። ለጊዜው ድብልቅ ብለነዋል . ስም ገና አልተሰጠውም።

(source Admas radio atlanta)

Miko ZE Ethiopia

59/ የመናፍቃን የሮሜ 8፡34 የማታለያ ጥቅስ ሲጋለጥ

ከመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ (የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ መምህር)

የኢየሱስን የባሕርይ አምላክነትና ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ መኾኑን ለማመን የተቸገሩና ፈራጅነቱን የካዱ ተጠራጣሪዎች ከሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች አንደኛው በሮሜ 8፡34 ላይ ያለው ጎይለ ቃል ነው። ይኸ “እስመ ለሊሁ ያጸድቅ መኑ ዘይኴንን ክርስቶስ ሞተ ወተንሥአ እሙታን ወሀሎ ይነብር በየማነ እግዚአብሔር ወይትዋቀስ በእንቲኣነ” (ርሱ ሲያጸድቅ የሚፈርድ ማነው ክርስቶስ ሙቶ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ በአብ ቀኝ ተቀምጧል ስለእኛም ይፈርዳል) የሚለው የጠራው የግእዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጎይለ ቃል በተለየ መልኩ በዘመናት ኹሉ ለዚኽች ቤተ ክርስቲያን መቼም ቢኾን መልካም ዐስበው በማያውቁ ይልቁኑ ፈራርሳ ቢያይዋት ደስ በሚሰኙ የክርስቶስን ፈራጅነት በካዱ በባሕር ማዶ ቀሳጮች ብዙ ጊዜ ተሰርዞ (ይማልዳል) በሚል ተቀይሮ እናነብባለን።

ለምስክርነት እስቲ እንይ፡-

በ 1938 ዓ.ም ታትሞ የነበረው መጽሐፍ ቅዱስ “ክርስቶስ ኢየሱስ ሞተ ከሙታንም ተለይቶ ተነሣ፤ በአብ ቀኝ ተቀምጧል፤ ስለእኛም ይፈርዳል” ይላል

በ 1975 ዓ.ም ታትሞ ከግእዙ ወደ ዐማርኛው የተመለሰው “ርሱ ሲያጸድቅ የሚፈርድ ማነው ክርስቶስ ሙቶ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ በአብ ቀኝ ተቀምጧል ስለእኛም ይፈርዳል” ይላል።

በ1980 ዓ.ም ግእዙን የሚያውቁ ዐይናማ ሊቃውንት ሳያዩት በጥቂቶች አስተባባሪነት የክርስቶስን ፈራጅነት በማያምኑ በምዕራባውያን የዶላር ድጋፍ የታተመው ደግሞ “እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኰንንስ ማን ነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” ይላል።

ይኽ ዕትም ችግሩ ይኼ ብቻ ሳይኾን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ የተጻፈበትን የግሪክን ቋንቋ እና ቀደምት የተተረጎመትን የግእዝ፣ የሶርያ፣ የአርመን፣ የቅብጥ ቅጅ በተለይ በግሪክ የተጻፈውን የ1900 ዓመት እድሜ ያለውን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ከማየት ይልቅ እንግሊዞች እንዲመቻቸው አድርገው ቃላቱን በድፍረት እየጨመሩና እየቀነሱ በ1611 ዓ.ም ያሳተሙትን የ400 ዓመት ዕድሜ ያለውን የኪንግ ጀምስ ቅጂን ወደ ዐማርኛ ተርጒመው ለማቅረብ ሞክረዋል፤

በዚኹ በሮሜ 8፡27 ላይ “ወባሕቱ መንፈስ ለሊሁ ይትዋቀስ ለነ በእንተ ሕማምነ ወምንዳቤነ ወውእቱ የሐትቶ ለልብነ ወየአምር ዘይኄሊ መንፈስ ወይትዋቀስ በጎበ እግዚአብሔር በእንተ ቅዱሳን” (ርሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ይመልስልናል፤ ርሱ ልቡናችንን ይመረምረዋል፤ ልብ ያሰበውን ርሱ መንፈስ ቅዱስ ያውቃል፤ በእግዚአብሔር ዘንድም ለቅዱሳን ጸሎት መልስ ይሰጣል) የሚለውን ገጸ ንባብ ለውጦ በድፍረት “ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ ዐሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና” በሚል በድፍረት ቃሉን በመለወጥ መንፈስ ቅዱስንም አማላጅ አድርገው መንፈስ

ቅዱስን በመናቅ አሳትመውት እናነብባለን።

ይኽ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ የተጻፈውን ቅዱስ ቃል ሰዎች እንደገዛ ፈቃዳቸው አጣምመው ለማቅረብ የሚሞክሩ ቢኾንም እስቲ ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 8፡33-34 ላይ “እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኰንንስ ማን ነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ ..... ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” የሚለውን ጎይለ ቃል በዝርዝር ዐይተን ሰዎች በተለያየ ጊዜ የጨመሩበት በባዶ ቦታው ላይ ያለው በእውነት ስለምን እንደሚያስገነዝብ መረዳት እንችላለን እስቲ ከዚኽ በታች እንየው፡-

“እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?”

ቅዱስ ጳውሎስ በዚኽ ምዕራፉ ላይ በትክክል እንዳስቀመጠው እግዚአብሔር መራጭ እንደኾነ ነው፤ ከላይ በትክክል እንዳየነው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደሰፈረው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ በእውነት እግዚአብሔር እንደኾነ የታወቀ የታመነ የተረጋገጠ ነውና ስለዚኽ “እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?” በማለት የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት አረጋግጦ ጻፈ፤ የመረጣቸውስ ማንን ነው ቢሉ “ንዑ ትልዉኒ” (ኑ ተከተሉኝ) ብሎ የጠራቸው ብሎ ሐዋርያትን፤ ዳግመኛም 72 ቱ አርድዕትን፣ 36 ቱ ቅዱሳት አንስትን ነው፤ ይኽነንም ወንጌላዊዉ ማቴዎስ “በሥራ ኼለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ ርሱ ጠርቶ እንዲያወጡአቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ኼሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው” በማለት ፲፪ቱ ሐዋያትን እንደጠራና

ሥልጣንን እንደሰጣቸው በትክክል አስቀመጠ።

ራሱ ቅዱስ ጳውሎስም በዚኹ ምዕራፍ ቍ፴፩ ላይ “አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው” በማለት ሐዋርያት ሰብአ አርድዕት እያለ የሾማቸው ስምዖን የተባለውን ጴጥሮስ ልብድዮስ የተባለው ታዴዎስ፤ ዲዲሞስ የተባለውን ቶማስ እየለ የጠራ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መኾኑን መሰከረ።

“የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው” በማለት የጠራቸውን የሐዋርያት ነገራቸው ወንጌልን በተአምራት እያስረዳ እያጸደቀ እውነት መኾኑን ሰዎች እንዲያውቁት ያደረገው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መኾኑን አስረዳ። ከዚያም “ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው” የጠራቸው ሐዋርያቱን በዚኽም ዓለም በተአምራት በወዲያኛውም ዓለም “እውነት እላችኋለሁ፥ እናንተስ የተከተላችሁኝ፥ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ፥ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ” (ማቴ 19፡28) በማለት ያከበረው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን በትክክል እንዳስተማረ በቍ 32 ላይ ላይም “እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?” በማለት ማንም ሊወቅሳቸው የማይችለውን ቅዱሳን ሐዋርያትን የመረጠው ፍጹም እግዚአብሔር የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን ገለጸ።

የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው?

ቅዱስ ጳውሎስ በትክክል በዚኽ ላይም ማጽደቅ እና መኰነን የሚችል ርሱ

ልዑል እግዚአብሔር እንደኾነ በትክክል አስቀምጧል፤ እውነት ነው ዓለምን በታላቅ ግርማ አሳልፎ መላእክቱን አስከትሎ በዙፋኑ ተቀምጦ ለኹሉም እንደ የሥራው የሚከፍለው፤ ጻድቃንን በቀኙ አቁሞ “እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ” ብሎ የሚያጸድቅ፤ በግራው የቆሙትን ኃጥኣንን ደግሞ “እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ” በማለት የሚኰንነው ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም እግዚአብሔር መኾኑን በትክክል ገለጸ። ራሱ ጌታ “የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል” በማለት እንዳስተማረን (ማቴ 25፡31-46)። ታዲያ ማጽደቅና እና መኰነን የፍርድ ሥራ እንጂ የማማለድ ሥራ ነውን በፍጹም አይደለም።

“የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው”

ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያትን የጠራው፣ የሚያጸድቀው የሚኰንነው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር መኾኑን በትክክል ካስረዳ በኋላ በመቀጠልም ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቶ ባባቱ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ መቀመጡን “የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው” በትክክል አስተማረ፤ ሞትን ድል አድርጎ ስለመነሣቱም ፊተኛው እና ኋለኛው ርሱ ስለመኾኑ ራሱ ጌታ “ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም

በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ” በማለት ይኽነን እውነት እንዲጽፍ ለዮሐንስ እንዳዘዘው ቅዱስ ጳውሎስም እውነቱን መሰከረ።

ወንጌላዊ ማርቆስም ስለዚኽ ነገር “ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ” (ማር 16፡19) በማለት ባባቱ ዕሪና መቀመጡን እንደነገረን ቅዱስ ጳውሎስም በድጋሚ ይኽነን አስተማረ።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት አስቀድሞ፦ “እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ጠላቶችኽን በእግርኽ መረገጫ እስካደርግልኽ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው” ብሎ እንደተነበየ /መዝ.፻፱(፻፩)፡፩/ በአብ ቀኝ ተቀምጧል። ቅዱስ ጳውሎስም ይኽ ትንቢት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈጸመ አስተምሯል /ዕብ.፩፡፲፪/።

ዓምደ ሃይማኖት የተባለው ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ የሉቃስ ወንጌልን በተረጐመበት ፳፬ኛው ምዕራፍ ላይ ይኽን በተመለከተ ሲናገር እንዲኽ ይላል፦ “ደቀ መዛሙርቱን ከባረካቸው በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ። በአባቱ ቀኝ (ዕሪናም) ተቀመጠ። የተቀመጠውም በባሕርየ መለኮቱ ብቻ አይደለም፤ በተዋሐደው ሰውነቱም ጭምር እንጂ። አካላዊ ቃል ባሕርያችንን ሲዋሐድ እኛን ወደዚኽ ክብር ለመመለስ ነበርና። ... እግዚአብሔር ሲኾን ስለ እኛ ሰው ኾነ። በፍቃዱ መከራ መስቀልን በተዋሐደው ሰውነቱ ተቀበለ። በተዋሐደው ሰውነቱ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በተዋሐደው ሰውነቱም ዐረገ። በሕያዋንና በሙታን ላይ ይፈርድ ዘንድም ዳግመኛ በክበበ ትስብእት ይመጣል” /Commentary on Luke, Chap.24/።

አኹን ለመለኮት የተገደበ የተወሰነ ቀኝ ግራ ፊት ኋላ አለው ማለትም አይደለም ቀኝ ማለት ኀይል ምልአትን በዕሪና መተካከልን የሚያመለክት ብቻ ነው ሊቁ “እስመ ብሂለ የማን ይመርሕ ኀበ ተዋሕዶቶሙ ወዕሪናሆሙ በክብር” (ቀኝ ማለት በክብር መተካከላቸውን ተዋሕዶቸውን ያመለክታል) እንዳለ፤ እንግዳን “ንበር” (ተቀመጥ)፤ ይሉታል እንጂ እንደ ባለቤት “ነበረ” (ተቀመጠ) እንዳይሉት ለዐይን ጥቅሻ እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ ከክብሩ አልተለየምና “ነበረ” ይለዋል፤ ለዚኽ ነው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ 1፡3 ላይ “በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ” በማለት የጻፈው።

እስኪ እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ቀኝ የሚለውን ኀሊናን በመሰብሰብ እንየው።

“እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል በጠላቶችህም መካከል ግዛ” (መዝ 109፡1)

“እኔ ነኝ እኔ ፊተኛው ነኝ እኔም ኋለኛው ነኝ እጄም ምድርን መሥርታለች ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች በጠራኋቸው ጊዜ በአንድነት ይቆማሉ (መዝ 48፡12-13)

እንኪያስ ዳዊት፦ ጌታ ጌታዬን። ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው ሲል እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል? ማቴ 22፡43-44

“አቤቱ፥ ቀኝህ በኃይል ከበረ” (ዘፀ 15፡6)

“አቤቱ፥ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው? ቀኝህን ዘረጋህ፥ ምድርም ዋጠቻቸው” (ዘፀ 15፡11-12)

“የእልልታና የመድኃኒት ድምፅ በጻድቃን ድንኳን ነው የእግዚአብሔር ቀኝ

ኃይልን አደረገች የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች” መዝ 117፡15-16)

“ኢየሱስም፦ እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ” ማር 14፡62 ይላል።

በመኾኑም ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱሳን ሐዋርያቱን የጠራው የሚያጸድቀው የሚከሰንነው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ስለመኾኑና ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቶ በአብ ቀኝ (ዕሪና) እንዳለ ከገለጸ በኋላ በዕለተ ዐርብ ባደረገው የድኅነት ምስጢር ዓለምን አድኖ ዋጋችንን የሰጠን ዳግመኛም በታላቅ ጌትነት ለፍርድ ተመልሶ የሚመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና “ደግሞ ስለ እኛ የሚፈርደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” በማለት በትክክል ተናገረ እንጂ፤ ምክንያቱም ከላይ ዝምሮ የጥቅሱን ሐሳብ እንዳየነው ሙሉ ነገሩ የክርስቶስን እግዚአብሔርነት፣ መራጭነት፣ አጽዳቂነት፣ ኰናኝነት፣ ሞትን ድል አድርጎ መነሣት፣ በአብ ዕሪና መቀመጥ ብቻ ነው፤ ታዲያ ራሱ ክርስቶስ ፍጹም እግዚአብሔር ከኾነና በአባቱ ዕሪና ከተቀመጠ በኋላ እንሶ ወደ ማን ሊማልድ ነው ይባላል? ወደ አብ ወደ መንፈስ ቅዱስ እንዳንል በአምላክነት፣ በፈጣሪነት፣ በቅድምና፣ በእግዚአብሔርነት፣ በዕበይ፣ በመንግሥት፣ በሥልጣን፣ በመመለክ፣ በመመስገን፣ በገናንነት፣ በክብር፣ በኀይል፣ በክሂል፣ በፈቃድ፣ በትእዛዝ አንድ ናቸው።

ስለዚኽ ከጊዜ በኋላ እነዚኽ ቀሳጮች ምስጢረ ሥላሴን አፋልሰው የማይለየውን አንድነት ለመበታተን እንዲመቻቸው በማድረግ አስገብተውበታል እንጂ ክብር ይግባውና ጌታስ በዘመነ ሥጋዌዉ በዕለተ ዐርብ ባደረገው ተልእኮ ዓለምን ከራሱ፣ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር

አስታረቀ ዳግመኛም ታረቀ ከዚያም የማስታረቅን ቃል ለሐዋርያት ሰጥቶ በክብሩ ተቀመጠ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ በጌትነት ይመጣል እንጂ አኹንም እንደገና ያደነውን ዓለም እንደገና እንዳልዳነ አኹንም መልሶ ይማልዳል ማለት ሎቱ ስብሐት ጠላት ዲያብሎስ የዘራው መርዝ ኑፋቄ ክሕደት ነው።

ለዚኽ ነው ቅዱስ ጳውሎስ በ 2 ቆሮ 5፡18-20 “ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን” በማለት የማስታረቅ አገልግሎት ለቅዱሳን ሐዋርያት ለቤተ ክርስቲያን አበው የተሰጠ መኾኑን ትክክለኛውን ትምህርት ያስተማረው።

እግዚአብሔር ቢፈቅድ ሌሎችም በተጠራጣሪዎች የሚነሱ ጥቅሶችንም ወደፊት ተንትነን እናያለን።

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

ነገረ ክርስቶስ ከሚለው መጽሐፌ የተወሰደ

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የቀናውን እውነት የኾነውን የሐዋርያትን ትምህርት ሳትበርዝ ሳትከልስ ሳትቈራርጥ ያስተማረችውን በደምህ የመሠረትካትን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንን ጠብቅልን።

60/ በፕሮቴስታንቱ ዓለም ደግሞ ከካቶሊካውያኑ ፍጹም ተቃራኒ በመኾን ቅዱስ ትውፊትን አንቀበልም ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን በቂ እንደኾነ ያስተምራሉ። ነገር ግን ይኽም ቢኾን ፍጹም የተሳሳተ ትምህርት ነው። አንድ ቀላል ምሳሌ እናንሣና ትምህርታቸው ምን ያኽል ስሕተት እንደኾነ እናሳይ። እሑድን እንደ ጌታ ቀን አድርገው ያከብራሉ። በብሉይ ኪዳን እንዲከበር የታዘዘው ግን ቅዳሜ ነው /ዘጸ.20፡8/። ቅዳሜን ትተው እሑድን ማክበር ከየት አገኙት? ዳግመኛም የጌታችንን ልደት፣ ጥምቀት፣ ትንሣኤ እንዲኹም በዓለ ኃምሳ አብረዉን ያከብራሉ። ነገር ግን ይኽን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም አናገኝም። ሌላ ጥያቄ እንጨምር። ወደ ዓለም ኹሉ የተሰማሩት ሐዋርያት 12 መኾናቸውን ወንጌል ይነግረናል። ነገር ግን ኹሉም ጽሑፍ አልጻፉም። አላስተማሩም ማለት ግን አይደለም። ታድያ ትምህርታቸው የት አለ? ትምህርታቸውን የምናገኘው በአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ኹለንተናዊ ሕይወት ውስጥ ብቻ ነው።

"የምናስተውል ካለን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል"፤

 በሚሞት ስጋችሁ ሐጢያት አይንገስ

ብልቶቻችሁን የፅድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ (ሮሜ 6፥12-14)

 ከሴት ጋር አለመገናኘት መልካም ነው ካልተቻለ ዝሙትን ለመከላከል በአንድ ይፅና ከዚህ ውጭ ጉዞ ወደ እሳት ነው (1 ኛ ቆሮ 7፥1)

 ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱ ያፈርሰዋል ቤተ መቅደሱም እናንተው ናችሁ (1 ኛ ቆሮ 3፥17)

 ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእረፍትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸፍኑ (1 ኛ ጢሞ 2፥9)

 የወንድ ልብስ የለበሰች ሴት በእምላክ ዘንድ የተጠላች ናት (ዘዳ 22፥5; ዘፀ 39፥28)

 ፀጉሯን ሳትሸፍን የምትፀልይ ሴት እራሷን ያዋረደች ናት(1 ኛ ቆሮ 11፥5)

 የወይን ጠጅ ከሚጠጣ ጋር አትቀመጥ (ምሳ 23፥20)

 ዘፈን የሰነፎች ዜማ ነው (መክ 7፥5)

 በዛም አጋንንት ይዘፍናሉ (ኢሳ 13፥21)

61/ ተሐድሶ እንዴት ይታያል?

አያቶች፥-...

አባቶች... ጥበብ ዕድሜያቸውን ገብረው፣

የጎጆ ንድፍ ሲያበጁ፣

አረጁ... ዘመናቸውን ፈጁ...

ልጆች!

ጎጆውን ለመውረስ ሳይከጅሉ፣

እንዲህ አሉ....

‹ያባቶቻችን ጎጆ

ይሁን ባዶ ይሁን ኦና

በኛ መጠን አልተቀለሰምና።..›

(በዕውቀቱ ሥዩም)

ከቅርብ ጊዜያት ጀምሮ የተሐድሶ ጉዳይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አነታራኪ ሆኗል። ንትርኩም ባፍ በመጣፍ እንደሚባለው ሆኗል ማለት ይቻላል። ይህም በተለለያዩ ድራተ ገጽ፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ መጽሐፎችና ቴሌቪዥን ጣቢያዎችም እየተገለጸ ቆይቷል። ጭቅጭቁ ደግሞ ተሐድሶ የሚባለው እንቅስቃሴ አለ ወይስ የለም ከማለት ይጀምራል። እኔም ከዚህ ‹እውን የተባለው የተሐድሶ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እየተካሔደ ነው? ወይም አለ?› ብዬ በመጠየቅ ልነሳ ፈለኩ።

የዚህ ጥያቄ መልስ ‹የለም› የሚል ቢሆን ኖሮ የተባለው ሁሉ ስህተት ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ መነታረክ አያስፈልግም ነበር። በ‹ሌለ› ጉዳይ ላይ መነታረኩ ምን ጥቅም ይኖረዋል? በሌለ ነገር ያለው ‹የለም› የሚለው ስም ብቻ ነው። ባይሆን አንድ ነገር በአግባቡ መታየት ይኖርበታል ‹እና በእንቅስቃሴው ዙሪያ የተዘጋጁ መጽሐፎች፣ መጽሔቶች፣... ከየት አምጥተውት ነው መነጋገሪያ ያደረጉት?›

እኔ በግሌ፦

1) ይህንን እንቅስቃሴ ከሚያካሒዱ ሰዎች ጋር በካል ተገናኝቻለሁ

2) ቤተክርስቲያን ለማደስ በሚል የተዘጋጁ ከ 10 ያላሰነሱ መጻሕፍትንና የተወሰኑ መጽሔቶችን አግኝቼ ተመልክቻቸለሁ፤ በግብረ መልስ የተጻፉ ጽሑፎችንም እንደዚሁ

3) የተሐድሶን እንቅስቃሴ ለማጋለጥ በሚል ወይም እንቅስቃሴውን በመደገፍ የተለቀቁ ማስረጃዎችን በተለያዩ ድራተ ገጻትን አይቻለሁ

እነዚህን ማስረጃዎች ተመልክቼ መኖሩን ማረጋገጥ ችያለሁ። ስለዚህ ተሐድሶ የሚባለው እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የለም ብሎ የሚከራከረኝን በጥርጣሬ ለማየት እገደዳለሁ። በዚህ የተነሣ የሚከራከረኝ ሰው ከሚከተሉት ሦስት ቡድኖች በአንደኛው ውስጥ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።

1) ምናልባት በቤተ ክርስቲያኒቱ ያለውን ነበራዊ እንቅስቃሴ አያውቅም፤ የተሐድሶ እንቅስቃሴንም ባለማወቁ በድፍኑ ‹የለም› ሲባል ሰምቶ ያንን በመያዝ በጭፍን ያወራል፤

2) እንቅስቃሴው መኖሩን ቢያውቅም የቤተ ክርስቲያኒቱ ስምና ክብር እንዳይጎድፍ እንቅስቃሴውን ሸፍኖ በመያዝ በምሥጢርነት ማቆየት ፈልጓል፤ ስለዚህ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ‹የለም› የሚለውን ሐሣብ ያራምዳል፤

3) ‹የለም› በሚል ሽፋን እንቅስቃሴው ውስጥ ለውስጥ እንዲከናወን የሚያደርግ ሰው ነው።

ከነዚህ የቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመናን ክፍሎች መካከልም የመጀመሪያዎቹ ችግራቸው የመረጃ እጥረት ነው ማለት ይቻላል፤ ስለዚህ የተሐድሶ

እንቅስቃሴ መኖሩን በትክክል የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካገኙ አቋማቸውን በመቀየር ‹የተሐድሶ እንቅስቃሴ መኖሩን› አምነው ለመቀበል አይቸገሩም። ችግራቸው ባለማወቅ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ በማወቅ መፍትሔ ያገኛል። ሁለተኛው ጎራ የሚገኙት አጉል ቀናነትና የዋህነት አለባቸው። እሳትንም በጭድ በመሸፈን ሊያጠፉ ይሞክራሉ። ስለዚህ የችግሩ ዕድሜ ማራዘሚያ ለመሆን ይገደዳሉ። የሐድሶ እንቅስቃሴ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር መሆኑን ካመኑ ችግሩን ሳያስወግዱ ማቆየት ውስብስብ ችግርን መጋበዝ እንጂ መፍትሔ አያስገኝም። ሦስተኛው የተሐድሶ እንቅስቃሴ አካል ነው። ስለዚህ የማታለል ሥራ ነው የሚያከናውነው፤ የተሐድሶ እንቅስቃሴም ስውር አካሔድ ማሳያ ነው ማለት ይቻላል። በተለይም የቤተ ክርስቲያኒቱን መድረክ ለማስተማሪያነት የሚጠቀም ሰው የተሐሶ እንቅስቃሴ መኖሩን አያውቅም ለማለት ያስቸግራል።

እሺ! ተሐድሶ የለም በማለት የሚከራከሩት በዚህ መልክ በሦስት ከፈልናቸው ታዲያ በምን እንለያቸው? ትልቁ ጥያቄ እዚህ ላይ ነው። ይህም ራሱን የቻለ የመፍትሔ አቅጣጫ መቀየስ እንዳለበት ይነግረናል። ይህ ከሆነም መፍትሔውን ለሌሎች አካላት (ለአባቶች) ወይም ለቤተ ክርስቲያን ልጆች ጥረትና መረጃን በአግባቡ የመያዝና የማሳወቅ ሥራ፤ እንዲሁም ትብብርና ቤተ ክርስቲያኒቱን የመጠበቅ ኃላፊነት እንተወውና ወደ ሌላ ነጥብ እንሸጋገር።

‹የተሐድሶ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያኒቱ መኖሩ እርግጥ ከሆነ ምንጩ ከየት ነው? ከውስጥ ወይስ ከውጭ? ከውስጥ ነው የሚባል ከሆነ የትኛውን የቤተ ክርስቲያኒቱን መሠረታዊ መርህ ነው አድሳለሁ የሚለው? ለማደስ

ያነሳሳው ምክንያትስ ምንድን ነው? ምክንያቱስ አግባብንት ያለውና በቂ ነው? እሺ ይሁን ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማደስም በቂና አግባባዊ ምክንያትም ይኑረው አካሔዱስ ትክክል ነው ወይ?...› እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች አጥጋቢና አዎንታዊ መልስ ሊያገኙ ይገባል። ያለበለዚያ የተሐድሶው እንቅስቃሴ ችግር አለበት።

በተቃራኒው ከውጭ ከሆነም ከየትኛው ቤተ እምነት እንደፈለቀና ይህንን ሊያደርግ የቻለበት ምክንያትና አካሔዱ ተለይቶ መታወቅ ይኖርበታል። አይ! ሁለቱም (ከውስጥና ከውጭ) በመተባበር የሚያከናውኑት እንቅስቀሴ ነው ከተባለም እንዴት? የሃይማኖት ልዩነት የለም ማለት ነው? ይህ ከሆነስ በጥንት ጊዜ የተደረጉ ጉባኤያት ስህተት ናቸው ማለት ይሆን? ይህንንስ ለማድረግ የሚያስችል አሳማኝ ነገር ከምን ተገኘ? ... › እነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ገባቸው ተመርምሮ መታየት አለበት።

ወደ መጀመሪያው ተመልሰን ‹ይህ የተሐድሶ እንቅስቃሴ የተነሣው ከቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ከውስጥ ሊሆን ይችላል› በሚል ግምት ላይ እንነሣ። እሺ ከሆነ እንቅስቃሴ የሚያደርገው ምኑን ለማደስ ነው? ዶግማዎቿን? የቀኖና ሥርዓታቷን? ወይስ በታሪክ አመጣጧ ችግር ተፈጥሮ? ነው ከዚህ ከተባሉት አማራጮች ሌላ ምክንያት ይኖራል?› የሚሉ ጥያቄዎችን ለማንስት እንገደዳለን።

ምክንያቱም እንቅስቃሴ የሚደረገው የሃይማኖት ዶግማዎቿን ለመቀር ከሆነ ግቡ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በሌላ ለመቀየር ነው ማለት ነው። የአንድ የሃይማኖት ዶግማ ለዘላለም አይቀየርም፤ ዶግማው ከተቀየረ ሃይማኖትነቱ ተለወጠ ማለት ነው። የኢ/ኦ/ተ/ቤ የምትመራባቸው አምስት አዕማደ

ምሥጢራት (ምሥጢረ-ሥላሴ፣ ምሥጢረ-ሥጋዌ፣ ምሥጢረ-ጥምቀት፣ ምሥጢረ-ቁርባን እና ምሥጢረ-ትንሣኤ ሙታን) አሏት። ከእነዚህ አንዱ ከተቀየረ እሷነቷን ታጣለች። ስለዚህ የሚካሔደው የተሐድሶ እንቅስቃሴ የቤተ ክርስቱን ዶግማዎች ለመቀየር ከሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማጥፋት ያለመ ነው ማለት ይቻላል። ደግሞስ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዶግማ ለማስቀየር የሚያስችል ሌላ ዶግማ ከየት ተገኘ? ለምንስ መቀየር አስፈለገ? እንቅስቃሴው የቤተ ክርስቲያንቱን ዶግማዎች ለመቀየር ከሆነስ ለምን ተሐድሶ ይባላል?.... በዚህ ዙሪያ ብዙ ጥያቄዎችን በማንሳት መተንተንና አንድምታቸውንም ማሳየት ይቻላል። ይሁንና በጥቅሉ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዶግማዎች (አዕማደ ምሥጢራት፣ መሠረታዊ እምነቶች) መቀየር ቤተ ክርስቲያኒቱን ማጥፋት ነው። የተሐድሶ እንቅስቃሴም ‹ዶግማ ተኮር› ከሆነ ለማደስ ሳይሆን ለመቀየር ያለመ ነው ለማለት እንገደዳለን። ሥርዓትዎቿን ለማሻሻል ያለመ ከሆነስ?

የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓታት የዶግማ ማስፈጸሚያ ሥልቶች ናቸው። ለምሳሌ መጠመቅ የግድ ነው፡- ዶግማ ነው፤ የአጠማመቅ ሁኔታ ግን ሥርዓት ነው። ቁርባን ዶግማ ነው፤ ‹እንዴት መቁረብ ይኖርብናል?› በሥርዓት መልስ ያገኛል። በዚህ ዓይነት ከሐዋሪያት ጀምሮ ያሉ አባቶች ከጎብረተሰቡ የአኗኗር ሁኔታ ጋር የሚስማሙና ለጽድቅ ሥራ የሚያበቁ የእምነት መተግበሪያ ስለቶችን ነድፈዋል፤ እንደሁኔታውና እንደጎብረተሰቡ እያዩም ሊያስተካክሉት ይችላሉ። ለዚህም ልክ እንደ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ ቤተ ክርስቲያኒቱ የምታሻሽልበት የራሷ ሥርዓት አላት። የተሐድሶም እንቅስቃሴ በዚህ ዙሪያ ከሆነ በሥርዓቱ መሠረት ተቀባይነት ሊኖረው

ይችላል። ባይሆን ‹የትኛውን ሥርዓት ነው እንዲሻሻል የተፈለገው? እንዲሻሻል የተፈለገበት ምክንያትስ ምንድን ነው? እስከዛሬ ትክክል በመሆን ሲሠራበት ኖሮ አሁን ስህተት መሆኑ በምን ታወቀ? ይሻሻል የተባለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓት የተሻለና ትክክለኛው ቢሆንስ?...› የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። እንዲሁም ‹የሚሻሻለው የቤ/ቱ ሥርዓት የዶግማዎቹን አይነኬነት ያረጋገጠ ነው ወይ?› የሚለው ጥያቄም መሠረታዊና ሊታለፍ የማይችል መልስ ፈላጊ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች ተነስተው አግባባዊ መልስ ካገኙ ሥርዓትን ማሻሻሉ ስህተት አይሆንም። ‹እውን የተሐድሶ እንቅስቃሴ በዚህ መልክ ነው ወይ?› የሚለውን ጥያቄ ወደ ኋላ እናየዋለን።

በሌላ በኩል በሦስተኛው አማራጭ መሠረት ቤተ ክርስቲያኒቱን ማደስ ያስፈለገው በታሪክ ስህተት የሆኑ አስተምሆሮዎች ቀይራ ወይም ጨምሯ በመገኘቷ ነው የሚል መከራከሪያ በተሐድሶዎች ሊነሣ ይችላል። ይህም ቢሆን አንደኛ ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ነው፤ ሁለተኛም በታሪክ የተፈጠረ ስህተትን ማሻሻልና ማስተካከል የሚቻለው ስምምነት ላይ ሲደረስበት ነው እንጂ በአቋራጭና በቅሰጣ እስትራቴጂ አይደለም። ለምሳሌም ‹በቤተ ክርስቲያኒቱ የተፈጠረው ትውፊታዊና ታሪካዊ ስህተት ምንድን ነው? ከመቼ ጀምሮ? ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ምንድን ነው? ትውፊታዊና ታሪካዊ ስህተት ስለመፈጠሩ ማረጋገጫችን ምንድን ነው? እስከዛሬ ተደብቆ ኖሮ ዛሬ እንዴት ሊታወቅ ቻለ? ምናልባት ስህተቱ የአሁኑ ቢሆንስ?...› እነዚህና መሰል ጥያቄዎች ተነሥተው መልስ ማግኘት አለባቸው። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባቶች የአስተምህሮ የዘር ሀረግ

አላቸው። እና ቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርቷ በጊዜ ሒደት መሣሣቱን የሚያሣውቀውን ማስረጃ ተሐድሶ በነማን የዘር ሐረግ አገኘው? እነሱ እንደ ትክክለኛ ወስደው እናድስበት የሚሉት ትምህርት በክህደታቸው አውግዛ ከቤቷ የለየቻቸው መናፍቃን አስተምህሮ ቢሆንስ? እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ተነስተው መልስ የሚፈልጉትም የተሐድሶ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ተነሳሽነት የውስጥ አስተምህሮትዋን መሠረት አድርገው የተነሱ ከሆነ ነው። የተሐድሶ እንቅስቃሴ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ውጪ ባሉ ኃይሎች ቀስቃሽነት የራስዋን አስተምህሮ መሠረት ሳያደርግ የተነሳ ከሆነ ክርክሩ በሌላ አንግል ይሆናል።

‹የተሐድሶ እንቅስቃሴ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ውጭ ባሉ ኃይሎች አነሣሽነት ተመሥርቶ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመለወጥ የሚንቀሳቀስ ወይም ከውስጥና ከውጭ ባሉ አካላት ስምምነት የተፈጠረ እንቅስቃሴ ቢሆንስ ምን ዓይነት የክርክር አቋም ይኖራል? አሁን የሚካሔደው የተሐድሶ እንቅስቃሴስ ምንጩ ከየትኛው እንደሆነ እንዴት እናውቃለን?› የሚሉ መከራከሪያዎችን እንመርመርቻው። ከሁሉም በፊት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ውጭ ባሉ የዕምነት ተቋማት የተመሠረተ ድርጅት ነው ካልን በየትኛው ተቋም አነሣሽነት እንደተመሠረተ በዶግማ አሥተምህሮውና በእንቅስቃሴ ግንኙነቱ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ከኦ/ተ/ቤ/ክ ውጭ ያሉት ሁሉም የዕምነት ተቋማት በጎበረት ተስማምተው ተሐድሶን አቋቁመው በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አስርፀው አስገቡት ብሎ ለማመን ይከብዳል። በተለይም እርስ በራሳቸው የማይስማሙ የእምነት ተቋማት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ለማደስ ጎበረት ፈጠሩ ማለት የማያስከድ ዕይታ ይሆናል። ደግሞስ የኢ/ኦ/ቤ/ክን ሃይማኖት

ለማደስ የሚስማሙበት ምክንያት ምንድን ነው? ቢሆንስ ለምን በስውርና ምዕምናና አገልጋይ ካህናት ሳይውቁት ይህንን ያደርጋሉ? መንፈሳዊና ክርስቲያናዊ አካሔድ ነው? የሕግ አግባብስ ይኖረዋል? ነው ከቤተ ክስርስቲያኒቱ አባቶች ጋር ተስማምተው ነው ይህንን የሚያከናውኑት? ምክንያቱም ‹ተሐድሶ ከላይ ካሉ ‹አባቶች› ጀምሮ የተቀናጀ እንቅስቃሴ ለማካሔድ እየጣረ ነው› የሚባል ሐሜት ስላለ ስምምነት ያደረጉ ‹አባቶች› ካሉ ብዬ ነው። ይህ ከሆነም ‹ምን ማለት ነው?› ከመንፈሳዊነት አንጻር ስናየው የሃይማኖት ልዩነት የለም ለማለት ነው? አዎ ከተባለም ኢየሱስ ክርስቶስን ፍጡር ማለትም ሆነ ፈጣሪ ማለት ትክክል ነው ማለት ነው? አሁንም አዎ ከተባለ እንደዚህ ከሆነ ለምን በሃይማኖት ማመን ያስፈልጋል? የሁሉም እምነት ትክክል ከሆነ አለማመንም ትክክል የማይሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? በሃይማኖትም አለመመራት ትክክል ነው ከተባለ ነገሩ ከመንፈሳዊነት ወጥቷል። ሃይማኖት አልባነት ትክክል ከሆነም ተሐድሶ ስሑት ሊሆን ይችላል? አይችልም፡- ሃይማኖትን የማጥፋት ወይም የማርገብ ዓላማ አካል ነውና።

ከዚህ በላይ የቀረበውን መከራከሪያ በማጥበብ ‹የተመረጡና ተቀራራቢ አስተምህሮ ያላቸው የሃይማኖት ተቋማት በጋራ የመሠረቱት ነው፤ ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚመሩ የእምነት ተቋማት ልዩነታቸው የተረጓጎም ነው፤ ስለዚህ ተቀራርበው በመነጋገር ወጥ የሆነ የሚያግባባ አስተምህሮ ለመቅረፅ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው።› የሚል የመከራከሪያ ግምት ሊቀርብ ይችላል። ይሁንና ይህም ቢኾን አያስኬድም።

ምክንያቱም፡-

አንደኛ የተሐድሶ እንቅስቃሴ የሚካሔደው በኦርቶዶክስ ቤ/ክን እንጂ በሌሎቹም ጭምር እየተካሔደ መሆኑን የሚጠቁም ማስረጃም ሆነ መረጃ የለም። ‹ተሐድሶ ነኝ› የሚለው ቡድንም እንቅስቃሴውን የሚያደረገው በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ውስጥ መሆኑን ነው በጽሑፎቹ ያረጋገጠው።

ሁለተኛም አንድምታው እስከዛሬ የተካሔዱ የአባቶች ጉባኤያትን ሁሉ ይቃወማል። ለምሳሌ የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንት (መካነ ኢየሱስ፣ የወንጌላዊያን አቤያተ ክረርስቲያን ጎብረት፣...) ሁሉም የእምነት ተቋማት ተስማምተው አንድ አስተምህሮ ሊኖራቸው ከቻለ ከኒቂያ (ሠለስቱ ምዕት) ጀምሮ የተደረገ ጉባኤያትና በጉባኤያቱ የተደረጉት ውግዘቶች የተሣሣቱ ለመሆን ይገደዳሉ። ይህ ደግሞ አጠቃላይ የክርስትና ታሪክን ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል። በሌላ አንግል ካየነውም በመጀመሪያ እስከ 4ኛው መ/ክ/ዘ ያሉ ጉባኤትን ኹሉም አቤያተ ክርስቲያናት በትክክልነት የሚቀበሉ ከሆነም የኦርቶዶክስን አስተምህሮ (ዶግማ) መቀበል ይኖርባቸዋል። ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትመራበት ዶግማ እስከዚያ ጊዜ ድረስ የተወሰኑ ውሳኔዎችን መሠረት ያደረገ ነውና። ለዚህም የአባቶችን አስተምህሮ ሰብስቦ የያዘውን ሃይማኖተ አበው የሚለውን መጽሐፍና የቤተ ክርስቲያኒቱን ቅዳሴያት ማየት ጥሩ ምስክር ይኾናል።

ሦስተኛም እንቅስቃሴው የሚካሔደው በስውር ስለሆነ የየእምነት ተቋሟቱን ምዕመናንና ካህናት የሃይማኖት ነፃነት የሚጋፋ ነው። ለምሳሌ እኔ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በዶግማዋና በሥርዓቷ ስንዱ እመቤት እንደሆነች አምናለሁ፤ እና ይህንን የማምንበትን ቀይረው ለምን እምነት አልባ ሊያደርጉኝ ይፈልጋሉ?

አራተኛም ‹ሁሉም ልክ ነው› ወይም ‹ሁሉም ስህተት ነው› የሚል መርህን የተከተለ ይመስላል። ይህ ከሆነም መሠረት አልባነት ነው፤ ምክንያቱም ሁሉም ትክክል ከሆነ ስህተት የሚባል የለም ማለት ነው፤ ሁሉም የተሳሳተ ከሆነም ትክክል የሚባል መሠረት አይኖርም። ይህ ደግሞ ከሃይማኖት ያለፈም አደጋ አለው። ሃይማኖትን የተወሰኑ ግለሰቦች የጉባኤ ስምምነትና ፍላጎት ማንፀባረቂያ በማድረግ ግቡን የሳተ ያደርጉታል። ይህ ምዕመናንን ለኢ-አማንያን አሳልፎ መስጣት ነው።

እነዚህ የእምነት ተቋማት በስምምነት ተሐድሶን ማቋቋማቸው የማያስኬድ ከሆነም ይህንን ቡድን በስውርና በምሥጢር የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን ለማፍረስ የሚፈልግ ድርጅት ወይም የሃይማኖት ተቋም ያቋቋመው ነው የሚል ጥርጣሬ መያዝ የግድ ይሆናል። ምክንያቱም አሁን በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከውስጥ ሊነሣ የሚችልበት አግባብ ከሌለ፤ ከውጭ ያሉ የእምነት ተቋማትም በመስማማት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን ለማደስና ለማረም የማይችሉ ከሆነ፣ የተሐድሶ እንቅስቃሴ መኖሩ ደግሞ እርግጥ ከሆነና ይህንንም የሚያከናውነው በስውር ከሆነ ይህንን እንቅስቃሴ በእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ይዞ የሚያሽከረክረው ድርጅት አለ ብለን መገመታችን አግባብ ይሆናል። አሁን እንብርቱ ጋር ደርሰናል፤ የተሐድሶ የሚያስወናጭፋቸው (ይታደሱልኝ በማለት) ያቃላት ድንጋዮች ከየት እንደሆኑ እያነጻጸሩ ማየት ምንጫቸውን በሚገባ ያስረዳሉ። ይህ ሲሆን ነው ክርክሩን ከቤተ ክርስቲያኒቱ አውጥቶ ሜዳ ላይ የሚያደርገው።

እንዲሁም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመቀየር (በሌሎች የእምነት ተቋማት ከተመሠረተ ተሐድሶ አዳሽ ሳይሆን ለዋጭ ነው የሚባለው)

ምክንያትና አግባብነትስ አለው ወይ? አግባብበነት ከሌለው እንዴት በማያገባቸው ቤ/ክን ላይ ተደራጅተው ለማደስ ይንቀሳቀሳሉ? በሕግስ ሊጠየቁ አይችሉም? ነው የኢትዮጵያ ሕግ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን የመጠበቅ ኃላፊነት የለበትም? እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ እንኳን የኢትዮጵያ ማንነት አስኳል የሆነቸውን ቤ/ክን እያንዳንዱ ዜጋም ቢሆን የሕግ ከለላ አለው? እና እንዴት ይህንን ያህል የታሪክና የባህል ማዕከል የሆነች ተቋም ሌሎች ኃይሎች መፈንጫ ሰትሆን ዝም ይባላል? ልብ ይበለሉኝ የተሐድሶው እንቅስቃሴ ከውጭ ወደ ውስጥ ከሆነ መቀየር እንጂ ማሻሻል አይደለም።

ምናልባት የቤተ ክርስቲያኒቱም አባቶች ተስማምተውበታል ሊባል ይችላል። ይህም ቢሆን የበለጠ ችግርን ጎልጉሎ የሚያወጣ ይሆናል እንጂ የመፍትሔ መልስ የሚሰጥ አይደለም። አንደኛ እነዚህ የተመረጡ ‹የሃይማት ተቋማት አባቶችና ወንድሞች› የሃይማኖት ልዩነትን ለማጥፋት በመጣር እስከዛሬ ድረስ የተኖረበትን የክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮ ገደል ይከቱታል። እንደገናም አስመሳይነትና አታላይነት የተጠናዎታቸው ናቸው፤ በተሐድሶ እንቅስቃሴ የሚከናውኑት በሥውርና በሐሰት በመሸፈን ነውና። ክርስትና ደግሞ መንገዱ እውነት የሆነ የእውነት ጉልላት ክርስቶስን አካሉ ያደረገ ሃይማኖት ነው። እሱም በሐሰትና በማታላል አስተምሩልኝ ያለ አይመስለኝም። ‹ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቀረጣል› ብለው ነው እንጂ!

ወለተ ሀና

**** የሀራጥቃ ተሐድሶ ጉባዔ ነው። ዘንድሮም በኦርቶዶክስ ተዋህዶ

መነገድ ይፈልጋሉ ። ብዙ ሰው የተሸወደው ወይም የሚሸወደው በቅዱስ ሚካኤል ሥም ስለተሰየመ ነው።በቅዱስ ሚካኤል ሥም ተሸፍነው የተሐድሶ እንክርዳድ ስብከት የሚሰበክበት ባዶ አዳራሽ ነው። ለሥሙ የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ይባላል ነገር ግን አንድም ቀን ስለ ቅዱስ ሚካኤል ተዘምሮበት አያውቅም።ቅዱስ ሲኖዶሱ በተደጋጋሚ አውግዞታል።በቅዱስ ሲኖዶሱም እውቅና የለውም።ፓስተር አሰግድና ጓደኞቹ ለቢዝነስ ብለው የከፈቱት የተሐድሶ መራቢያ ባዶ አዳራሽ እንጂ ቤተክርስቲያን አይደለም።በ 34 ኛው የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ ተደጋጋሚ ተነስቶ እንዲዘጋ የተወሰነበት አዳራሽ ነው።ልብ ያለው ልብ ያድርግ።ጆሮ ያለው ይስማ። ለማያውቁ ሰዎች በማሳወቅ ወገኖቻችንን ከተኩላዎች እንጠብቅ።please share it

“ገርፎ የመጮኽ”፦ የተሐድሶዎች የማደናገሪያ ስልት

ጥቅምት 26 ቀን 2008 ዓ.ም

ክፍል ሁለት

የተሐድሶዎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ በክፍል አንድ ዝግጅታችን በማጎበረ ቅዱሳን ጎትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ክፍል በስምዐ ጽድቅ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጋዜጣ በተከታታይ እየወጣ ያለውን ጽሑፍ አቅርበንላችሁ እንደነበር ይታወሳል። ክፍል ሁለትን ደግሞ እነሆ፦

አማናዊቷ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም ተመሥርታ በሐዋርያት ስብከት ከሰፋችበት ጊዜ ጀምሮ ያለ ፈተና አልጋ በአልጋ የሆነ ሕይወት

የመራችበት ጊዜ የለም፣ ወደፊትም አይኖርምም። በሐዋርያት ዘመን ይሁዳና ቢጽሐሳውያን፣ በሐዋርያውያን አበው ዘመን ግኖስቲኮች፣ በሊቃውንት ዘመን አርዮስ፣ መቅዶንዮስ፣ ንስጥሮስና ልዮን ቤተ ክርስቲያንን ለመፈተን የተነሡ ነበሩ። ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ እንደ ተጻራሪዎች አሳብ አሉታዊ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ለምእመናን መንፈሳዊ ዕድገት አዎንታዊ አስተዋጽኦ የነበራቸው ብዙ መከራዎችን አሳልፋለች። እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ የሚለው የጌታችንና የአምላካችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ማረጋገጫ በዚህ ሁሉ በማያቋርጥ ማዕበል ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ድል አድራጊ ሆና ወጀቡን ማለፍ መቻሏ ነው።

ባለንበት ዘመን ቤተ ክርስቲያንን የማዳከምና ምእመናንን የመንጠቅ ተግባር ለይቶላቸው በሌላ የእምነት ጎራ የተሰለፉ አካላት ተልእኮ መሆኑ ቀርቷል። ይህ ተግባር ዛሬ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን እሷ እንደ ሻማ እየቀለጠች ባበራችላቸው፣ በሥጋዊ ፈቃዳቸው የእንጀራ ማብሰያ ያደረጉትን ሙያ ባስተማረቻቸው፣ በጉያዋ ባደጉ፣ የእናት ጡት ነካሽ በሆኑ በራሷ ልጆች የሚፈጸም ሆኗል። እነዚህ ሰዎች በአለባበሳቸው፣ በአነጋገራቸው (ግእዝ ስለሚጠቅሱ)፣ በአካሔዳቸው (ቤተ ክርስቲያን ስለሚመላለሱ) እና በአገልግሎታቸው (ተአማኒነት ለመፍጠር ስለሚተጉ) ክርስቲያኖች ሊመስሉን ይችላሉ። ይህ ሁሉ ቀን እስኪወጣ ለማደናገሪያነት የተጠቀሙበት ማስመሰያ ጭምብል እንጂ በእውነት ፊት ሚዛን የሚደፋ መንፈሳዊነት ያለበት ሕይወት አይደለም። ይህ ድርጊታቸው የሚያስቀርብን ነገር ግላዊ ጥቅም ቢሆን ሁሉን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ ማለፍ ይቻል ነበር። ነገር ግን

ከውስጥ እስከ ውጪ በተዘረጋ መዋቅር፣ ቤተ ክርስቲያንን እስከ መረከብ፣ ካልተቻለ እስከ መክፈል በሚያደርስ የተቀናጀ ስልት፣ በፕሮቴስታንታዊ በጀት በታገዘ ድጋፍ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከምድረ ገጽ ላይ ለማጥፋት የኤልዛቤልን ዕቅድ የሚያስፈጽሙ አካላትን መታገሥ አግባብ ባለመሆኑ ማንነታቸውን ገልጾ ሕዝብ እንዲያውቀው ማድረግ መንፈሳዊ ግዴታችን ይሆናል።

እነርሱ መዋቅር ዘርግተው፣ ስልት ነድፈው፣ በጀት መድበው ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት እየሠሩ ያሉት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ነው። ከዚህ በፊት በቀረቡ ጥናቶች እንደተገለጸው ተሐድሶዎች ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እስከ መክፈል፣ ከተቻለም እስከ መረከብ ያደርሱናል ብለው የዘረጓቸው ስልቶች አሉ። እነዚህን ስልቶች እውን ለማድረግ ደግሞ የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ። ከእነዚህ ተሐድሶዎች ከሚጠቀሟቸው መንገዶች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

፩.በሚያውቋቸው ሰዎች በኩል መቅረብ፡- ዛሬ ላይ ተሐድሶ ነን በማለት ቤተ ክርስቲያንን እናድሳለን የሚሉ አካላት የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ስለነበሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሰዎችን ያውቃሉ። በቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ውስጥ፣ በአብነት ትምህርት ቤት ወንበር ዘርግተው የሚያስተምሩ የአብነት መምህራንን፣ በልዩ ልዩ ገዳማት የሚገኙ መናንያንን እና አስተዳዳሪዎችን፣ የመንፈሳዊ ትምህርት ተቋማት አስተዳዳሪዎችን፣ መምህራንን እንዲሁም የሰንበት ትምህርት ቤት አመራሮችንና አባላትን ማወቃቸውና መቅረባቸው በእነርሱ በኩል ተልእኳቸውን የማስፈጸም ዕድል ፈጥሮላቸዋል።

ለምሳሌ በ፲፱፻፯ ዓ.ም ቀኖና ተሰጥቶት ተጸጽቶ በመመለስ ፋንታ በኑፋቄው በመግፋቱ ምክንያት በ፳፻ወ፬ ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዐተ ጉባዔ ከተወገዙት ፲፮ የተሐድሶ አራማጅ ግለሰቦች መካከል አንዱ የሆነው፣ አሁንም ኦርቶዶክስ ነኝ በማለት የሚያደናግረው እና በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የሚካሔደውን የተሐድሶ እንቅስቃሴ የሚመራው ጽጌ ሥጦታው ብዙ የአብነት መምህራንን ለመቀሰጥ ዕድል ያገኘው በአብነት ትምህ ርት ቤት የሚያውቃቸውን ሰዎች በመጠቀም ነው። መሠረተ ክርስቶስ ቸርችም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ በሚደረገው እንቅስቃሴ ለአገልግሎት የምፈልጋቸው በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ካህናትን ብቻ ነው Â ማለቷ የአብነት መምህራንን ለማጥመድ የቤተ ክርስቲያንን ቋንቋ የሚያውቅ አካል አስፈላጊ እንደሆነ በመረዳቷ ነው። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ተሐድሶዎች ከቤተ ክርስቲያኒቷ ቋንቋና ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር መተዋወቃቸው በምእመናን ዘንድ ተቀባይ ነትን በማግኘት ተልእኳቸውን ለማሳካት ምን ያህል ያገዛቸው መሆኑን ነው።

፪.በገንዘብ ማታለል፡- ተሐድሶዎች ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ከምንጨ ላይ መሥራት አለብን ብለው ትኩረት የሰጧቸው አብዛኛዎቹ ቦታዎች ላይ የሚገኙት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የገንዘብ ችግር ያለባቸው ናቸው። አብነት ትምህርት ቤቶችን ብንወስድ በቤተ ክርስቲያን መዋቅር የተረሱ የቤተ ክርስቲያን የደም ሥሮች ናቸው ። የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ ከመቀየሩ ጋር ተያይዞ በአሁኑ ዘመን ከዚህ በፊት እንደነበረው ቁራሽ እየለመኑ መማር የማይታሰብ እየሆነ መጥቷል። በዚህ ምክንያት የአብነት ተማሪዎች ሌሎች

የገንዘብ ማግኛ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ ትምህርታቸውን መቀጠል ይፈልጋሉ። በዚህ መካከል ከአሜሪካና ከአውሮፓ የፕሮቴስታንት ድርጅቶች በሚላክላቸው ገንዘብ ኪሳቸውን ያደለቡት ተሐድሶዎች አንድ አማራጭ ሆነው አብነት ተማሪዎችን ቀረቧቸው። ተሐድሶዎቹ ለገዳማት፣ ለመንፈሳዊ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎችና ለገጠሪቷ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ዲያቆናትም ተመሳሳይ ድጋፍ እናደርጋለን በሚል ሰበብ እየበረዟቸው ይገኛሉ። ባለፈው ዓመት አዲስ አበባ ኮተቤ አካባቢ ባካሔዱት ስብሰባ ላይ ማኅበረ ቅዱሳን ያልደረሰባቸውን አብነት ትምህርት ቤቶችን ቀድመን በድንማ መልክ መቅረብና መያዝ አለብን Â የሚል አቅጣጫ መንደፋቸውን ተናግረዋል።

፫.□□ አሠልጥኖ □□/አሰይጥኖ መመለስ፡- በትውውቅም ሆነ በማታለያ የቀረቧቸውን ሰዎች የጥፋት ዓላማቸውን ለመፈጸም የሚችሉበትን

አቅም Â በሥልጠና ካስታጠቋቸው በኋላ ተልእኳቸውን ሳይረሱ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ተመልሰው ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጓቸዋል። የተሐድሶ ሥልጠናዎችን ወስደው ወይም ሃይማኖታቸውን ትተው ወደ ሌላ በረት ሔደው ከቆዩ በኋላ የጣሉትን ቆብና መስቀል ይዘው ኦርቶዶክሳዊ መስለው የተመለሱ ሰዎች ቁጥር ብዙ ነው። በዚህ መንገድ ውጪ ድረስ ሔደው ተምረው የመጡ አሁንም

አባ Â እገሌ፣ ቄስ Â እገሌ፣ ዲያቆን Â እገሌ እየተባሉ የሚጠሩ በልብሳቸውና በምላሳቸው ኦርቶዶክሳውያን፣ በልባቸው ግን ፕሮቴስታንት የሆኑ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች Â አሉ።

፬.ሚዲያዎችን መጠቀም፡- ተሐድሶዎች እንቅስቃሴያቸውን ከግብ

ለማድረስ የጎትመት፣ የኤሌክትሮኒክስና የብሮድካስት ሚዲያዎችን ይጠቀማሉ። ማን እንዳዘጋጃቸው የማይታወቁ ባለቤት አልባ በራሪ ወረቀቶችን፣ ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችንና መጻሕፍትን እንዲሁም የተለያዩ የምስል ወድምጽ ውጤቶችን በማሠራጨት መርዛቸውን ይረጫሉ። ድረ ገጾችን፣ የጡመራ መድረኮችን፣ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን መርሐ ግብራትን በመጠቀም ኑፋቄያቸውቸውን እያስፋፉ ይገኛሉ።

፬.፩.ጋዜጦች

ተሐድሶዎች እያሳተሙ ከሚያሠራጯቸውና መርዛቸውን ከሚረጩባቸው ጋዜጦቻቸው መካከል መጥቅዕ፣ በሃይማኖት ቁሙ፣ መርከብ፣ መና ተዋሕዶ፣ እውነት፣ ኖኅተ ብርሃን፣ ከሣቴ ብርሃን፣ ርግብ፣ ንቁ፣ ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው።

፬.፪.መጽሔቶች

ሌሎች ተሐድሶዎች ኑፋቄያቸውን የሚያሠራጩባቸው የጎትመት ውጤቶች መጽሔቶች ናቸው። ከእነዚህ መጽሔቶች መካከል ጥቂቶቹ አንቀጸ ብርሃን፣ ብሔራዊ ተሐድሶ፣ ከሣቴ ብርሃን ዘኢትዮጵያ፣ ሰላማ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ ጮራ፣ ቤተ ፍቅር፣ ወዘተ ሲሆኑ ከእነዚህ ባልተናነሰ ሁኔታ ለተሐድሶ እንቅስቃሴው ድጋፍ ሰጪ የሆኑ ጽሑፎችን የሚያቀርቡ ጌሠም፣ ትሪኒቲ፣ ማቴቴስ፣ ካሪዝማ፣ ወዘተ የሚባሉ የፕሮቴስታንት መጽሔቶች አሉ።

፬.፫.መጻሕፍት

ተሐድሶዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ከአንድ መቶ ሰማንያ (፻፹) በላይ መጻሕፍት ጽፈዋል። መጽሐፎቻቸው የክርስቶስን

አምላክነትና የእመቤታችንን አማላጅነት ክደው የሚያስክዱ፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚነቅፉ፣ ቅዱሳንን የሚሳደቡ፣ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን የሚያጥላሉ ናቸው። ተሐድሶዎች የግብር አባታቸው የሉተር ልጆች እንጂ ኦርቶዶክሳውያን አለመሆናቸውን መጽሐፎቻቸው ይናገራሉ። ከቁጥራቸው ብዛት የተነሣ ሁሉንም የተሐድሶ መጻሕፍት መዘርዘር ከባድ ቢሆንም በ፲፱፻፹ ዓ.ም ከእነ ጽጌ ሥጦታው ጋር የተወገዘው አሸናፊ መኮንን ብቻ ከሃያ አምስት በላይ መጻሕፍትን ጽፏል። የተለያዩ የብዕር ስሞችን በመጠቀም ቤተ ክርስቲያንን መሳደብ የእንጀራ ማብሰያው ያደረገው ሠረቀ ብርሃን ዘወንጌል መስተብቁዕ ዘሙታን፣ የዘመናት እንቆቅልሽ ሲፈታ፣ ማሳቀልና ሎፌ የሚሉ በመርዝ የተሞሉ መጻሕፍትን ጽፏል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ምእመናንን በስውር መንጠቁ አላጠግባቸው ብሎ ቤተ ክርስቲያንን በግልጽ እየተዋጉት ያሉት ፕሮቴስታንቶችም የተሐድሶ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዳለ እና እንቅስቃሴውም ለእነርሱ ድጋፍ ሰጪ መሆኑን በመጽሐፎቻቸው ገልጸዋል። ለምሳሌ፦ ጸጋአብ በቀለ የተባለ የፕሮቴስታንት ፓስተር

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ - ሳታድግ ያረጀች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን Â በሚለው መጽሐፉ፣ ዳንኤል ተሾመ የሚባል የመካነ ኢየሱስ ቸርች አባል የሆነ ፕሮቴስታንት የቅርብ ዘመኑ (፲፱፻፹፱-፲፱፻፺፱) የተሐድሶ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን Â በሚል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባዘጋጀው ጽሑፍ እንዲሁም በቀለ ወልደ ኪዳን የተባለ

ከሌሊቱ ስንት ሰዓት ነው?በሚለው መጽሐፉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ

ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላለው የተሐድሶ እንቅስቃሴ ገልጸዋል። እነዚህ መጻሕፍት የተሐድሶ እንቅስቃሴን ግብና ከፕሮቴስታንት ጋር ያለውን ድርና ማግነት ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው።

፬.፬.ድረ ገጾችና የጡመራ መድረኮች

በዚህ ዘመን ሁሉም ነገር በኤሌክትሮኒክስ መቅረብ የሚችል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተሐድሶዎች ኑፋቄያቸውን ለመዝራት ከተጠቀሙባቸው ስልቶች መካከል አንዱ ድረ ገጾችንና የጡመራ መድረኮችን መጠቀም ነው። ቁጥራቸ ውን በትክክል ማወቅ ባይቻልም በዛ ያሉ የተሐድሶ የጡመራ መድረኮችና ድረ ገጾች አሉ። ከእነዚህ ድረ ገጾችና የጡመራ መድረኮች መካከል አባ ሰላማ፣ ጮራ፣ ደጀ ብርሃን፣ የዲያ ቆን አሸናፊ መኮንን ገጽ፣ ተሐድሶ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ ዐውደ ምሕረት፣ ማራናታ፣ ቤተ ፍቅርና የዲያቆን አቤኔ ዘር ተክሉ ገጽ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

፭.ተገፋን ብሎ መጮህ፡- ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል Â እንደሚባለው፣ ተሐድሶዎች አጥፊዎቹ፣ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ የሚተጉት ራሳቸው ሆነው ሳለ በራሳቸው ድረ ገጾች፣ የጡመራ መድረኮችና በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በኩል ተገፋን እያሉ ይጮሃሉ። በ፷፱ወ፯ ዓ.ም የተወሰኑ ዘማርያን Â አሜሪካ ሔደው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በማኅበረ ቅዱሳን ለተገፉ ሰባክያንና ዘማርያን በሚል ገንዘብ ሲሰበስቡ ነበር። በ፷፱ወ፱ ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዐተ ጉባዔ የተወገዘው ማኅበረ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተባለው የተሐድሶ ድርጅት ደግሞ የካቲት ፯ ቀን ፷፱ወ፯ ዓ.ም በቁ ጥር አ/ሰ/ማ/18/262/06 በማኅበረ ቅዱሳን አቀነባባሪነት የተወሰነብን የውግዘት ውሳኔ እንዲነሣልን ስለመጠየቅ

ይመለከታል Â የሚል ደብዳቤ በአድራሻ ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ አስገብቶ ነበር። ደብዳቤው ርእሱ እንደሚናገረው ማኅበረ ቅዱሳንን የሚያወግዝና ውግዘታችን ይነሣልን የሚል ነው። ድርጅቱ በደብዳቤው፡-

ክልላዊ ማኅበር መመሥረት የለባችሁም፣ በአገር አቀፍ የተፈቀደለት ማኅበረ ቅዱሳን ብቻ ስለሆነ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሁኑ፣ ካልሆናችሁ ግን መናፍቃን ናችሁ፣ ትለያላችሁ Â በማለት ሲዝትብን የነበረ ማኅበረ ቅዱሳን ከእኔ በቀር ሌላ ማኅበር መኖር የለበትም የሚል አቋም ይዞ በከፍተኛ ሁኔታ በመንቀሳቀስ ራሱን እንደ ልጅ በመቁጠር እኛን ደግሞ እንደ እንጀራ ልጅ እንድንታይና እንድንወገዝ ካለው ጽኑ አቋሙ የተነሣ ምንም ዐይነት የክህደት ትምህርት ሳንማርም ሆነ ሳናስተምር ያለ ምንም መረጃ ይሁን ማስረጃ በአሉቧልታና በትምክህት መናፍቃን ናቸው እያለ በገንዘብ ጎይል በሁሉም ዘንድ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖር በማድረግ ሳንጠየቅ፣ ሳንመከር፣ ሳንገሠጽ፣ እውነት ይሁን አይሁን ሳይጣራ፣ ቀርበን በወቅቱም ምንም ዕድል ሳይሰጠን በማኅበረ ቅዱሳን ከፍተኛ ተዋናይነት የውግዘት ውሳኔ መተላለፉ አሳዝኖናል ይላል።

ከዚህም በተጨማሪ አባ ሰላማና ተሐድሶ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በሚባሉት ድረ ገጾቻቸው በ፳፻ወ፱ ዓ.ም ተሐድሶዎች ሲወገዙ፣ ከዚያም በኋላ እነሱን ለማስቆም ቤተ ክርስቲያኒቱ በምታደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ አገልጋዮቿን የምታሳድድ ቤተ ክርስቲያን Â እያሉ ስሟን ሲያጠፉ ይሰማሉ። ለምሳሌ ተሐድሶ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኑ! እንዋቀስ Â በሚል ርእስ ባወጣው ጽሑፍ እንደ አለመታደል ሆኖ ሲኖዶሳችን መናፍቃንን በመደገፍ ጻድቃንን ያሳድዳል፤ ቀን ሲደርስ የእግዚአብሔርን ፍርድ እናያለን፤ እስከዚያው

እንክርዳዱ ከስንዴው ጋር ተናንቆ ያድጋል። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በቃሉና በመንፈሱ ተሐድሶ ይጎብኝልን።በማለት ጽፈዋል። ሊያ የሚባል መጽሔት ላይ ደግሞ የወንድሞች ከሣሽ ማኅበረ ቅዱሳን Â በሚል ርእስ ሰፊ ሐተታ ያለው ጽሑፍ ጽፈው ነበር።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ቁጥር በሰባት ሚሊዮን መቀነሱን በይፋ አምናለች። ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ስትል በአንድ ወገን መንጋው አለመጠበቁንና በዚህ ምክንያት መሰረቁን አምናለች። በሌላ በኩል ግን ሌሎች ሰረቁኝ፣ ወሰዱብኝ ከማለት ያለፈ ምክንያቱን በሚገባ ያጤነችው አትመስልም። ሌሎች በውጪ አግኝተው ከወሰዷቸው በላይ እንደ ማኅበረ ቅዱሳን ያለ የወንድሞች ከሳሽና አክራሪ ቡድን እኔን አልመሰላችሁምና መናፍቃን ሆናችኋል በሚል ሕገ ወጥ መንገድ ያሳደዳቸው ጥቂቶች አይደሉም። ምናልባት ለቁጥሩ መቀነስ የማኅበረ ቅዱሳን እጅም እንዳለበት መታመን አለበት ይላል። (ሊያ መጽሔት ቅጽ ፪ ቁጥር ፭፯ ሚያዝያ ፭፻ወ፭ ዓ.ም)

እስካሁን ያየነው የአገር ውስጡን ጩኸት ነው። ተሐድሶዎች ከፕሮቴስታንቶች ጋር በመተባበር ይህንን ጩኸት ዐለም አቀፋዊ አድርገውታል። ዓላማዬ የክርስቲያኖችን ጭቆና ለዓለም ማሳወቅ ነው Â የሚል ክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር Â የሚባል አንድ የዜና አውታር አለ። በቀን ከዐሥር በላይ ከሃይማኖት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ዜናዎች ያወጣል። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን በደል አውጥቶ አያውቅም። በሶርያ በየዕለቱ ከሞት ጋር ስለሚታገሉት ኦርቶዶክሳውያን፣ ስለ ፓትርያርኩ ለዐሥራ አምስት ቀናት የሔዱበት አድራሻ አለመታወቅ የዘገበው ነገር

አልነበረም። ያልዘገበው ግን ባለማወቅ ሳይሆን በዓላማ ነው። ለዚህ ድርጅት ክርስቲያን ማለት ፕሮቴስታንት ነው። የሚያሰማውም የእነሱን ጩኸት ነው። ተቀማጭነቱን አሜሪካ ያደረገ ኦፕን ዶርስ የሚባል ድርጅት አለ። ድርጅቱ አንድሪው ቫን ደር ቢጅል በሚባል ግለሰብ በ፲፱፻፺፭ የተመሠረተ መንግሥታዊ ያልሆነ የክርስቲያን ድርጅት ነው። እንደ ራሳቸው አገላለጽ በግለሰቦች መዋጮ የሚተዳደር ነው። ከ፲፱፻፺፯ ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ በክርስቲያኖች ላይ ከፍተኛ ጭቆና የሚያደርሱ የአምሳ አገራትን ዝርዝር ያወጣል። በዚህ ድርጅት ዘገባ መሠረት አገራችን ኢትዮጵያ ክርስቲያኖችን ከሚጨቁኑት አምሳ አገራት መካከል ባለፉት አምስት ዓመታት ማለትም በ2011 ፴፫ኛ፣ በ2012 ፴፭ኛ፣ በ2013 □□፲፭ኛ፣ በ2014□□ ፲፯ኛ እና በ2015□□ ፳፪ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። ድርጅቱ ባለፉት ሁለት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የክርስቲያኖች ጭቆና ከዓመት ወደ ዓመት እየቀነሰ ነው Â ይላል። ይህ አገላለጽ ሲብራራ ተሐድሶዎች ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ የተሻለ ዕድል እያገኙ ነው ማለት ነው።

ተቋሙ በ2013 ባወጣው ዘገባው ስለ ኢትዮጵያ እንዲህ የሚል ቃል አስቀምጧል፦

Ethiopia has a complex mix of persecution dynamics.Ecclesiastical arrogance is the country historical persecution dynamic. For years, the Ethiopian Orthodox Church (EOC) has been seriously persecuting believers who

have left their ranks or joined the renewal movements within the EOC. (World Watch List 2013)

ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ የሆነ ጭቆና የሚካሔድባት አገር ናት። ቤተ ክህነታዊ እብሪትየአገሪቱ ታሪካዊ የጭቆና መታወቂያ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ወጥተው አዲስ የመጣውን የፕሮቴስታንት እምነት እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያሉ የተሐድሶውን ጎራ የተቀላቀሉትን አማኞች ክፉኛ ትጨቁናለች። ካለ በኋላ ቀጥሎ፦

The fanatic group inside the EOC (˜Mahibere Kidusan) is a growing threat for non-traditional Protestants and renewal movements within the EOC. The group allegedly wants to control the government policies to restrict the activities of other religions. Mahibere Kidusan is currently riding high. (World Watch List 2013)

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር የሚገኘው ማኅበረ ቅዱሳን የሚባለው አክራሪ ቡድን ለፕሮቴስታንቶች እና በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ላሉ ተሐድሶዎች ታላቅ ሥጋት ነው። ቡድኑ ሌሎች የእምነት ቤቶች የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ለመገደብ የመንግሥትን ፖሊሲዎች በጥብቅ መቆጣጠር በጥብቅ ይፈልጋል። Â **በአሁኑ ጊዜ ማኅበሩ በፍጥነት**

እያንሠራራ ነው።

2013 ማለት በኢትዮጵያ ተሐድሶ ዎች የተወገዙበት ዓመት ማግስት ማለት ነው። ለዚህም ነው እየተጨቆንን ነው የሚለው ጉዳይ ዓለም አቀፋዊ አጀንዳ እንዲሆን እና ፖለቲካዊ አቅጣጫ እንዲይዝ ለማድረግ የሞከሩት። ተሐድሶዎች የዘረጉት መስመር የት እንደሚደርስ ወይም ተሐድሶው በማን ግፊት እየተመራ እንደሆነ ይህ አገላለጽ ሁነኛ ማሳያ ነው። ኦርቶዶክስ ሳይሆኑ ኦርቶዶክስ ነን Â በማለት የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለመቀየር ብሎም ቤተ ክርስቲያንን ለመክፈል የሚሠሩ ወገኖች ቁጥራቸው በርከት ባሉባቸው ቦታዎች ኦርቶዶክሶችን በማሸማቀቅ፣ በማስፈራራትና በመዝለፍ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት የተነሡት እነርሱ ሆነው ሳለ ራሳቸው የሠሩትን ግፍና በደል ለቤተ ክርስቲያን አድርገው ተሳደድን ብለው ይጮሃሉ። ብዙዎቻችንም ዐውቀንም ይሁን ሳናውቅ የእነርሱ ጩኸት ደጋፊዎችና ጠበቆች እየሆን ነው። የራስን አጥብቆ መያዝና ለሌላ ወገን አላስደፍርም ማለት ማስወቀስና ማስተቸት ከጀመረ ቆይቷል።

እነርሱ እነዚህን መንገዶች ተጠቅመው ቤተ ክርስቲያንን የማዳከም፣ ዶግማና ቀኖናዋን የመቆነጻጸል ተግባራቸውን ቀጥለውበታል። እኛ ይህ ሁሉ ሲፈጸም ምን ያከናወንነው ተግባር አለ ተብለን ራሳችንን ብንጠየቅ መልሳችን ምንም የሚል ነው። ስለዚህ ቢያንስ የችግሩን አሳሳቢነትና የአደጋውን አስከፊነት ጠንቅቀን ማወቅና መንገዶቻቸውን ለመዝጋት የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት ይገባናል። እነርሱ በገንዘብ ለማታለል ምቹ ሁኔታ ያገኙት እኛ አብነት ትምህርት ቤቶችን እና ገዳማትን ባለመደገፋችን መሆኑን መረዳት አለብን።

ዝንቱ ሰብአ ዜና

62/ የተሐድሶ መረብ አድማስና የትኩረት አቅጣጫዎች

ኅዳር 2 ቀን 2008 ዓ.ም

ክፍል ሦስት

ባለፉት ሁለት ተከታታይ ጽሑፎች ተሐድሶ መናፍቃን በምን ዐይነት መንገድ ምእመናንን እየነጠቁ እንደሆነ ተመልክተናል። ከዚህ ቀጥለን በምናወጣቸው ተከታታይ ጽሑፎች ደግሞ የተሐድሶ አድማሱ የት ድረስ እንደሆነ ለአንባቢያን ግንዛቤ የሚሰጥ መረጃ የምናቀርብ ይሆናል።

የተሐድሶ እንቅስቃሴ ዓለም አቀፋዊ መልክ ያለውና በዓለም ላይ ባሉ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ላይ በፕሮቴስታንት የእምነት ተቋማት የተቃጣ ስውር ሴራ ነው። እንቅስቃሴው ከውጪ ወደ አገር ውስጥ የመጣ ስለሆነ የተሐድሶው አቀንቃኞች በአሳብ፣ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ ወዘተ ከሚያግዟቸው በልማት ስም ከተቋቋሙ ድርጅቶች ጋር ከፍተኛ ቁርኝት አላቸው። ከእነዚህ ድርጅቶች እና ከፕሮቴስታንት ቸርቾች በሚበጀት በጀት፣ ከአገር ውስጥ እስከ ውጪ አገር በተዘረጋ መዋቅር፣ ቤተ ክርስቲያንን ከተቻለ ሙሉ በሙሉ ለመረከብ ፕሮቴስታንት ለማድረግ ካልሆነም ለሁለት ለመክፈል በሚያስችል ስልት እየሠሩ እንደሆነም

ተመልክተናል።

በአገር ውስጥ ያሉት ሠላሳ የሚደርሱ የተሐድሶ ማኅበራት የቤተ ክርስቲያን ምንጮች በሆኑት የአብነት ትምህርት ቤቶች፣ ገዳማት፣ መንፈሳዊ ኮሌጆች፣ ሰንበት ትምህርት ቤቶችና ማኅበራት ላይ እንዲሁም መዋቅራዊ ድጋፍ ለማግኘት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ላይ ይሠራሉ። የተለያዩ መመዘኛዎችን በመጠቀም ትኩረት አድርገው የሚሠሩባቸው ቦታዎች አሉ። መነሻቸውን አዲስ አበባ ላይ አድርገው በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ሰፋ ያለ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ። ከዚህ ዕትም ጀምሮ በተከታታይ ጽሑፎች ከመነሻቸው ከአዲስ አበባ ጀምረን ትኩረት ሰጥተው በሚሠሩባቸው አካባቢዎች ያለውን እንቅስቃሴ እንመለከታለን።

አዲስ አበባን ማእከል ያደረገው የተሐድሶ መረብ

አዲስ አበባ የተሐድሶ እንቅስቃሴው ማእከል ነው። ታሪክ የሚነግረን ተሐድሶዎች እንቅስቀሴው ሲጀመር ጀምሮ ማእከላቸውን አዲስ አበባ አድርገው ወደ ሌሎቹ የአገራችን ክፍሎች ኑፋቄያቸውን ያስፋፉት መሆኑን ነው። አዲስ አበባ ተሐድሶዎች በየአጥቢያው ተወካዮችን አስገብተው ብዙ ሥራ የሚሠሩበት፣ የተለያዩ የሥልጠና መስጫ ተቋማትን እና ኮሌጆችን ያቋቋሙበት፣ የቤት ለቤት ሥራዎችን በሰፊው የሚሠሩበት፣ የጽዋ ማኅበራትን በብዛት የፈጠሩበት፣ ከክፍለ ሀገር ለሚያመጧቸው ካህናትና ዲያቆናት ሥልጠና የሚሰጡበት ነው። የቴሌቪዥን መርሐ ግብር የሚያስተላልፉት፣ አብዛኛው የተሐድሶ መናፍቃን መጻሕፍት የሚታተሙት፣ የገንዘብ ልገሳ የሚያደርጉላ ቸው የመናፍቃን ድርጅቶች የሚገኙት አዲስ አበባ ነው። ፕሮቴስታንታዊ የአምልኮ ሥርዓት የሚፈጸምባቸው የተሐድሶ

አዳራሾች በስፋት የሚገኙትም እዚሁ ነው።

ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ የሚያስችላቸውን መዋቅራቸውን የዘረጉትና ስልታቸውን የነደፉት አዲስ አበባን ማእከል አደርገው ነው። በአሁኑ ሰዓት ከአዲስ አበባ እየተነሡ ያልደረሱበት የአገራችን ክፍል የለም ማለት ይቻላል። አዲስ አበባ ላይ ያላቸው መረብም ጠንካራና ሁሉንም አጥቢያዎች የሚያቅፍ ለማድረግ እንቅልፍ አጥተው በመሥራት ላይ ናቸው። መሐል አዲስ አበባ አካባቢ ካሉት አጥቢያዎች ተነቅቶባቸው ሲባረሩ በአዲስ አበባ ዙሪያ ወደሚገኙ አጥቢያዎች በመሔድ ተመሳስለው ገብተው የቅሰጣ ሥራቸውን ይሠራሉ። ቤተ ክርስቲያን ተልእኳቸውን ተረድታ በውግዘት የለየቻቸውና አጋልጣ ምእመናን እንዲያውቋቸው ያደረገቻቸው ተሐድሶዎች ከጀርባ ሆነው በየአጥቢያው የሰገሰጓቸው ተሐድሶ መናፍቃን ተልእኳቸውን ያፋጥኑላቸዋል።

እንቅስቃሴው በግልም በቡድንም እንዲሁም በድርጅት ስም የሚካሔድ ነው። በግለሰብ ደረጃ የተሐድሶ አቀንቃኞችን እገሌ ወእገሌ ማለቱ ባያቅትም ለአንባቢም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ጥቅም ካለመኖሩና እነርሱንም የበለጠ እንዲደበቁ ዕድል መስጠት ስለሚሆን ይህንን መጠበቅ የለብንም። ነገር ግን በብዙ ቦታዎች እንደሚታየው በዓላማ እንቅስቃሴውን የሚመራው አካል አንድ ወይም ጥቂት ነው። ሌላው ግን ምን እየተሠራ እንደሆነ እንኳን ሳያውቅ ሌሎቹ ስለሔዱ ብቻ የሚከተል ነው።

በተደጋጋሚ ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ካህናትን እያመጡ አዲስ አበባ ላይ ያሠለጥናሉ። በተለይ ከገጠር ለሥልጠና የሚያመጧቸው ካህናት ከጥቂቶቹ በስተቀር በየዋህነት ጉዳዩ ምን እንደሆነ ሳይረዱ የሚመጡ

ናቸው። እነዚህ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን የማፍረስ ሴራዎች ያውም የቤተ ክርስቲያን ምንጮች ያልናቸው አብነት ትምህርት ቤቶችና ገዳማት ላይ ሐላፊነት ላላቸው ሰዎች ተሰጥቶ የፈለጉት ነገር አለመሳካቱን ስናይ የእግዚአብሔርን ጠብቆት እናደንቃለን። ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ የሚሰጡት ሥልጠና Â ውጤት ማምጣት ያልቻለው በአንድ በኩል ከሠልጣኞች አቅም ማነስ የተነሣ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሚከተሉት ዓላማ የጥፋት በመሆኑ እግዚአብሔር እንዳይሳካላቸው ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን በረድኤት ስለሚጠብቃቸው ነው ብለን እናምናለን። ተሐድሶዎችም ምዕራባውያን ቤተ ክርስቲያንን የማፍረስ ስውር ተልእኳቸውን ለማሳካት የበጀቱት ዳጎስ ያለ ገንዘብ እንዳይቀርባቸው እንጂ ለጽድቅ ስለ ማይሠሩ ለሪፖርት ብቻ ሥልጠና ሰጥተው የሚልኳቸው ብዙዎችን ነው።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መቦርቦርን እንጀራ ማብሰያ አድርገው የያዙት ብዙ የተሐድሶ ድርጅት አንቀሳቃሾች መናሃሪያቸው አዲስ አበባ ነው። በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዐተ ጉባዔ የተወገዙና ከሥልጣነ ክህነታቸው የተሻሩ ግለሰቦች ሳይቀሩ የክህነት ስማቸውን ተጠቅመው ዲያቆን ፣ መሪ ጌታ Â እያሉ መጻሕፍት ያሳትማሉ። ሥልጠና የሚሰጡባቸው፣ ኑፋቄያቸውን የሚዘሩባቸው፣ በእነርሱ አነጋገር አምልኮት የሚፈጽሙባቸው፣ በሥውር ቤተ ክርስቲያንን የማፍረስ ሴራ የሚጠነስሱባቸው፣ የቴሌቭዥን መርሐ ግብራትን የሚቀርጹባቸው፣ የግልና የኪራይ አዳራሾች አሏቸው። በእነዚህ አዳራሾች ሲያሻቸው ያስጨፍራሉ፣ ሲያሻቸው እንፈውሳለን ይላሉ፣ ሲያሻቸው ደግሞ እነርሱ ሳይማሩና የያዙት ወንጌል ሳይገባቸው ያስተምራሉ።

የቤት ለቤት ቅሰጣ አልበቃ ብሏቸው በመገናኛ ብዙኀን ወደ ሕዝብ መድረስ ጀምረዋል። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ምእመናን ስለ ተሐድሶ ያላቸው ግንዛቤ እየጨመረ መምጣቱ፣ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ከተሐድሶዎች ጋር እያደረጉት ያለው ትንቅንቅ መጎልበቱና ለምእመናን የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብራት እየበረከቱ መምጣታቸው ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም፤ አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ ከተሐድሶዎች እጅ ነፃ ለማድረግ ግን ሰፋ ያለና የተቀናጀ ሥራ የሚጠይቅ ነው።

አጥቢያቸው የሚገኘውን ሰንበት ትምህርት ቤት አፍርሰው ሌላ ሰንበት ትምህርት ቤት ለማቋቋም፣ አባላቱን ለሁለት ከፍለው አገልግሎቱ እንዳይካሔድ ለማድረግ የሚጥሩ ከተሐድሶ በሚገኝ ገንዘብ የሚደለሉ አንዳንድ አስተዳዳሪዎችና የስብከተ ወንጌል ሓላፊዎች መኖራቸው የሚታወቅ ነው። ዓላማችንን ያስፈጽሙልናል ያሏቸውን የሰንበት ተማሪዎች ሰብስበው የተለየ ትምህርት Â ካስተማሩ በኋላ ተልእኮ ሰጥተው ተመልሰው ሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጉ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሌላ ተልእኮ ይዘው ተመሳስለው የገቡትን የጥፋት መልእክተኞች አካሔድ አጢነው ሲያግዷቸው ለምን ታገዱ ብለው ሰንበት ትምህርት ቤቱን ለመዝጋት የሚነሡ የስብከተ ወንጌል ሓላፊዎች እየበዙ መጥተዋል። ይህ የሚያሳየው ምን ያህል ተመሳስለው ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደገቡ ነው። ምእመናንም ሆኑ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች እንዲህ ዓይነት የጥፋት ተልእኮ አንግበው የሚንቀሳቀሱትን ወገኖች ሲመለከቱ ማንነታቸውን የሚያሳይ መረጃ መሰብሰብ፣ ከማን ጋር እንደሚውሉ፣ ምን እንደሚሠሩ፣ አነጋገራቸው፣ አካሔዳቸው፣

ኦርቶዶክሳዊነታቸው ምን እንደሚመስል ማጣራት ይኖርባቸዋል።

በአንዳንድ አጥቢያዎች ገድላትና ድርሳናት፣ ተአምረ ማርያምና ስንክሳር እንዳይነበቡ የሚከለክሉ አስተዳዳሪዎች አሉ። የጠበል ቦታ አያስፈልግም ብለው ለጋራዥ በማከራየት ገንዘብ ከመመዝበር አልፈው ምእመናንን ከድኅነት የሚለዩና የተሐድሶ አጋርነታቸውን የሚገልጡ ወገኖች አሉ። ተሐድሶዎቹ ከእንደዚህ ያሉ የጫኑዋቸውን ተሸክመው ለማስፈጸም ከሚደክሙ አካላት ጋር በመመሳጠር ዐውደ ምሕረትን ለመቆጣጠር ጥረት እያደረጉ ነው። ነገር ግን በሰንበት ት/ቤት ወጣቶችና በጠንካራ ምእመናን ተጋድሎ ዓላማቸው አልተሳካም። ሰባክያነ ወንጌልን የሚመድቡትና የማስተማር ሐላፊነት የተሰጣቸው አንዳንድ የስብከተ ወንጌል ሐላፊዎች በዐውደ ምሕረት ላይ ወጥተው ሲያስተምሩ ስለ ቅዱሳን ማስተማር የኢየሱስን ማዳን ይሸፍናል ሲሉ ይሰማሉ። የሚጋብዟቸው መምህራን ደግሞ ኢየሱስን ብቻ እንሰብካለን የሚል መፈክር አንግበው ይንቀሳቀሳሉ። እነዚህ ወገኖች ያልገባቸው ወይም አውቀው ለማደናገር የሚጥሩት ስለ ቅዱሳን መስበክ ስለኢየሱስ ክርስቶስ መስበክ መሆኑን ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ አጥቢያዎች አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ተጀምረው ሳይጠናቀቁ ገና በመቃኞ እያሉ እና አጸዱ እንኳን ቅጥር ሳይኖረው ሁሉም ቁሳቁስ የተሟላለት ዘመናዊ አዳራሽ የሚሠሩም አሉ። ለምን ተብለው ሲጠየቁ

ለወንጌል ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ስለሆነ Â የሚል መልስ ያቀርባሉ። በእውነቱ የሰው ልጅ ድኅነት ማግኘት ገድጂቸው ይህን ቢያደርጉ መልካም ነበር። የእነሱ ዓላማ ግን ሌላ ነው። ሰዎች ከመንግሥተ ሰማያት በአፍአ

እንዲቀሩ ማድረግ። ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን አሳንሶ አዳራሾችን ዘመናዊ አድርጐ መገንባት የተሐድሶዎች አንድ ስልት ተደርጎ እየተሠራበት ነው። ይህንን አካሔድ የሚቃወሙትን የወንጌል ጸሮች እያሉ ይሳደባሉ፤ ምእመናን እንዲጠሏቸው ያደርጋሉ። ለአካሔዳቸው እንቅፋት ይሆናሉ ያሉዋቸውን በሐላፊነት የሚገኙ አገልጋዮች ማባረር፣ ያላጠፉትን ይህን ጥፋት ፈጸሙ በማለት የሀሰት ስም መስጠት፣ ማብልጠልና ከምእመናን ጋር ማጋጨት በአዲስ አበባ የተለመደ እየሆነ መጥቷል። በዚህ ምክንያትም በየፖሊስ ጣቢያውና በየፍርድ ቤቱ ሲጓተቱ የሚውሉ አገልጋዮች ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ መጥቷል።

ይህ አካሔድ በቶሎ መፍትሔ ካልተሰጠው ከቅዳሴ በኋላ ዐውደ ምሕረት ላይ ተአምረ ማርያም ሳይነበብ ምእመናን ወደ አዳራሽ እንዲገቡ መደረጉ የማይቀር ነው። እነዚህ እና የመሳሰሉት አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሽፋን ተደርገው የሚሠሩ የተሐድሶ ቅሰጣዎች ናቸው።

ሌላው ደግሞ በግልጽ የሚሠራው የተሐድሶ እንቅስቃሴ ነው። ለምሳሌ፦ ፍል ውኃ አካባቢ የሚገኝ ተስፋ ተሐድሶ የሚባል ድርጅት አለ። ይህ ድርጅት ላለፉት ሦስትና ዐራት ዓመታት ከተለያዩ ቦታዎች ለተውጣጡ የገዳማት አበምኔቶች፣ የአብነት ትምህርት ቤት መምህራን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚያገለግሉ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሥልጠና እየሰጠ በሰርተፊኬት አስመርቋል። ከ፳፻ወ፮ ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ፍኖተ ሕይወት ማኅበረ መድኀኔዓለም የተስፋ ተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የሚባል ተቋም ከፍቶ በዲፕሎማ ማስመረቅ ጀምሯል። ድርጅቱ ነሐሴ ፲፰ ቀን ፳፻ወ፮ ዓ.ም ደግሞ Integrated Theological

Training and Skill Development for Africa

ከሚባል ኮሌጅ ጋር በመተባበር የመጀመሪያ ዙር ዐሥር ተማሪዎችን በዲፕሎማ አስመርቋል።

በአጠቃላይ የአዲስ አበባ እና ዙሪያውን እንቅስቃሴ ስንመለከት በገንዘብ ጥማት ልቡናቸው በታወረ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች፣ በተሐድሶ እንቅስቀሴ መረብ ውስጥ ባሉ ስብከተ ወንጌል ሓላፊዎች እና በፕሮቴስታንት ድርጅቶች ጥምረት የሚካሔድ ነው። ገንዘብ እስካገኙ ድረስ ለቤተ ክርስቲያን ዶግማና ቀኖና ደንታ የሌላቸው የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ባሉባቸው አጥቢያዎች እና ከተሐድሶዎች ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው የስብከተ ወንጌል ሓላፊዎች ባሉባቸው አጥቢያዎች ዐውደ ምሕረቱ የሚፈቀደው ለኦርቶዶክሳውያን ሳይሆን ለተሐድሶ መናፍቃን ነው። በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለው እንቅስቃሴ በዚህ መልክ የሚቀጥል ከሆነ ከጊዜ በኋላ የተወሰኑ አጥቢያዎች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አይደለንም ማለታቸው የማይቀር ነው።

ሰሜኑን ማእከል ያደረገ የተሐድሶ እንቅስቃሴ

ይህ እንቅስቃሴ የክርስትና መሠረት የተጣለበትን ሰሜኑን የአገራችንን ክፍል ለማጥፋት ታቅዶ የሚካሔድ ነው። እንቅስቃሴው ጥንታውያን ገዳማትና አብነት ትምህርት ቤቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በትምህርት ስም፣ በማኅበራዊ ልማቶች ስም፣ በእርቅና ሰላም ስም፣ ማረሚያ ቤቶችን እናግዛለን በሚል ስም ምእመናን እና ሕፃናት ላይ ትኩረት አድርገው ይሠራሉ። የዚህ እንቅስቃሴ ፊታውራሪዎች ከሣቴ

ብርሃን የተሐድሶ ድርጅት፣ መሠረተ ክርስቶስ ቸርችና የኢትዮጵያ አዲስ ኪዳን መጥምቃዊት ቸርች ሲሆኑ በግለሰብ ደረጃ እንቅስቃሴው ውስጥ ታላቅ ሱታፌ ያላቸው ግለሰቦች አሉ።

ከሣቴ ብርሃን ከመወገዙ በፊትም የትኩረት አቅጣጫው የነበረው ሰሜኑ የአገራችን ክፍል ነበር። የከሣቴ ብርሃን ቅጥረኞቹ ጽጌ ሥጦታው፣ ሠረቀ ብርሃን ዘወንጌል፣ ጌታቸው ምትኩ፣ ባዩ ታደሰና ሙሴ መንበሩ ከአዲስ አበባ ተነሥተው በጎጃም በር ወጥተው ሥልጠና ሰጥተው፣ ቅኝት አድርገውና አዳዲስ ተከታዮች አፍርተው በሸዋ በር ይመለሳሉ። በ፷፱ወ፯ ዓ.ም ብቻ ሸኖ፣ አንጾኪያ፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ባሕር ዳር ሁለት ጊዜ እና አዲስ አበባ ላይ ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትና አብነት ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ በአጠቃላይ ከሁለት መቶ በላይ ለሚሆኑ ካህናትና የአብነት መምህራን ሥልጠና ሰጥተዋል። ሥልጠናውን የሚወስዱት ሰዎች የሚመለመሉት በከሣቴ ብርሃን ቢሆንም ሥልጠናው የሚሰጠው በፕሮቴስታንት አዳራሾችና በፕሮቴስታንት ፓስተሮችም ነው።

ከ፷፱ወ፭ ዓ.ም ጀምሮ ብሔራዊ ተሐድሶን አመጣለሁ እያለ ሌሎችን የተሐድሶ ድርጅቶች ሲቀሰቅስና ሲያስተባብር የነበረው ይኸው ድርጅት ባለፈው ዓመት የወንጌል አገልግሎት ማኅበራት ጎብረት የሚባለው እናት የተሐድሶ ድርጅት እንዲቋቋም አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው። ስሙን በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ስም ሠይሞ ስለሚንቀሳቀስ የቤተ ክርስቲያን አካል መስሎ የሚታያቸው ብዙዎች ናቸው። ያለ ቤተ ክርስቲያን ዕውቅናና ፈቃድ ከተከፈቱት የቴሌቪዥን መርሐ ግብሮች በተጨማሪ ፷፱ወ፬ ዓ.ም ላይ የተወገዘው ከሣቴ ብርሃን የተሐድሶ ድርጅትም

መጥቅዕ የተባለ የቴሌቪዥን መርሐ ግብር ሊጀምር ዝግጅቱን አጠናቋል።

ሁለተኛው የሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተሐድሶ እንቅስቃሴ ፊታውራሪ የሆነችው መሠረተ ክርስቶስ ቸርች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሰሜኑን በወንጌል እንወርሳለን የሚል ፕሮጀክት ነድፋ እየሠራች ሲሆን ፕሮጀክቱ በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ፈሰስ እየተደረገ የሚሠራ ነው። መሠረተ ክርስቶስ እንደሸፋን ተጠቅማ ሰሜኑ ላይ ትኩረት አድርጋ የምትሠራው ሁለት ፕሮጀክቶችን ነው። እነዚህ ፕሮጀክቶች ሰሜኑን በወንጌልና የማረሚያ ቤቶች አገልግሎት የሚባሉ ናቸው። የእነዚህ ፕሮጀክቶች ዋና የትኩረት አቅጣጫ ሰሜኑ የአገራችን ክፍል ቢሆንም በሌሎች አካባቢዎችም ተመሳሳይ እንቅስቀሴዎችን ታደርጋለች።

ሰሜኑን በወንጌል የሚባለው ፕሮጀክት በትግራይ፣ ጎንደር፣ ወሎ፣ ጎጃምና ሸዋ አካባቢ በከፍተኛ ሁኔታ እንቅስቃሴ እያደረገች ነው። በእነዚህ አካባቢዎች የተለያዩ አጥቢዎች፣ የአብነት ትምህርት ቤቶችና ማረሚያ ቤቶች ላይ ትኩረት አድርጋ እየሠራች ነው። ለዚህ ዓላማ ማስፈጸሚያ የሚሆን ገንዘብ የምታገኘው ከተለያዩ የውጪ ድርጅቶች (የፕሮቴስታንት) ከሚላክ ገንዘብ፣ በሚያውቋቸው ሰዎች ከውጪ ከሚሰበሰብ እርዳታ እና ያሠለጠኗቸውን ሰዎች በቪሲዲ በመቅረፅና እርሱን በማሳየት ከደጋፊ ዎች በሚገኝ ገንዘብ ነው። የመሠረተ ክርስቶስ የልማት ድርጅት (Meserete Kirstos Church Relief Development) የታላቁ ተልእኮ አገልግሎት አጋር ስለሆነ ከዚህ ድርጅትም የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ይደረግላታል።

የዚህ እንቅስቃሴ ዓላማ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ካህናት፣ ዲያቆናትና

መሪጌቶች በገንዘብ በማታለል፣ የተለያዩ ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት፣ ማንነታቸውን መለወጣቸው እንኳን ሳይታወቃቸው የተሐድሶ እንቅስቃሴው አጋርና ቀኝ እጅ እንዲሆኑ በማድረግ በውስጥ ሆነው የተሐድሶ ሥራ እንዲሠሩ ተልእኮ መስጠት ነው። ሥልጠና የሚሰጡላቸው ደግሞ የተሐድሶውን እንቅስቃሴ ዓላማ ብለው የያዙት እነ ሠረቀ ብርሃን ዘወንጌል፣ ጽጌ ሥጦታው፣ አግዛቸው ተፈራ፣ የዕድል ፈንታ፣ ታምራት፣ ፓ/ር ሰሎሞን ከበደ፣ ወዘተ ናቸው።

በ፳፻፯ ዓ.ም ብቻ ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ለመጡ ከሃምሳ በላይ ለሚሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወረዳ ቤተ ክህነት፣ ሊቃነ ካህናት፣ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሥልጠና ሰጥታለች። ሥልጠናው በተለያዩ ዙሮች መሐል ሜዳ፣ አዲስ አበባና ደብረ ዘይት ላይ የተካሔደ ነበር። ስለ እርቅና ሰላም አስተምራለሁ በሚል ሰበብ የማሠልጠኛ ሰነድ አዘጋጅታ የራሷን ዶክትሪን እያስተማረች ነው። ለዚሁ ዓላማ በ፳፻ወ፯ ዓ.ም የብርሃን ፍሬ የሚባል የበጎ አድራጎት ድርጅት አቋቁማለች። የበጎ አድራጎቱ መመሥረት ዋና ዓላማ በልማት ስም ምንፍቅናን ማስፋፋት ሲሆን â ወንጌልን ማስፋፋት ዋና ዓላማችን ቢሆንም በውስጠ ታዋቂነት የሚሠራ እንጂ ከመተዳደሪያ ደንቡ ላይ አይቀመጥም â በማለት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተቀመጡት የበጎ አድራጎት ማኅበሩ â የማስመሰያ â ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

1.የቂም በቀል፣ ደም የመመለስ ወይም የጥቁር ደም፣ የነፍስ ግድያ ባህልና ግጭትን እንደ ጀግንነት የመቁጠር ልማድን ለኅብረተሰቡ በማስተማር ማስወገድ፣

2.ኋላ ቀር የሥራ ባህልን፣ ከአቅም በላይ መደገስንና አባካኝነትን፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻን፣ የትዳር መፍረስንና የቤተሰብ መበተንን፣ ለዕድገትና ለሰላም ጠንቅ የሆኑ አስተሳሰብ አመለካከትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ጎብረተሰቡን በማስተማርና በማማከር ማስወገድ፣

3.በልዩ ልዩ ሱሶችና መጥፎ ልማዶች ተጠምደው ጎጂ ልማደኛ ሆነው ጎዳና ውስጥ ያሉ ወጣቶችን ካሉበት ሱስና መጥፎ ልማድ እንዲወጡ መርዳት፣

4.የአቅም ግንባታ የመልካም ሥራ ሠርቶ ማሳያ ልማቶችን መሥራት ናቸው።

በማረሚያ ቤቶች ውስጥ በእርዳታ ሰበብ በመግባት በሃምሳ ስድስት (፶፮) ማረሚያ ቤቶች ላይ የእምነት ማስፋፋት ሥራ እየሠራች ሲሆን ታራሚዎቹ ሲወጡ በሚሔዱበት ቦታ የራሳቸው â ቸርች â እንዲያቋቁሙ ተልእኮ ትሰጣለች። በሃያ አንዱ (፳፩) ማረሚያ ቤቶች ደግሞ መደበኛ ሠራተኞች ተቀጥረው ይሠራሉ። አብዛኛዎቹ ተቀጣሪዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዲቁናና በሰንበት ትምህርት ቤት ሲያገለግሉ የነበሩ ተሐድሶዎች ናቸው። ስውሩ የእምነት ማስፋፋት ሥራቸው እንዳይጋለጥ የተወሰኑ ማረሚያ ቤቶች ላይ የልማት ሥራዎችን ይሠራሉ። የተወሰኑ ማረሚያ ቤቶች ላይ ቤተ መጻሕፍትና ካፍቴሪያ ሠርተው ሰጥተዋል። ለታራሚዎች የልብስና የሳሙና እርዳታ ያደርጋሉ።

መሠረተ ክርስቶስ ከእነዚህ ሁለት ዋና ዋና ፕሮጀክቶች በተጨማሪ በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በትምህርትና አቅም ግንባታ፣ በምግብ ዋስትና፣ በልማት፣ የተፈጥሮ አደጋን እና ኤች አይ ቪ ኤድስን በመከላከል ስም በመግባት ምእመናንን የመቀሰጥ ሥራ ትሠራለች። አዲስ አበባ፣ ናዝሬት፣

ደብረ ዘይት፣ ሆለታ፣ ማርቆስ፣ ሜታ ሮቢ፣ መሐል ሜዳ፣ ጀልዱ፣ ቀዋ ገርባ፣ ወዘተ እነዚህ ፕሮጀክቶች ተፈጻሚ የሆኑባቸውና ውጤት ያመጡባቸው ቦታዎች ናቸው። የልማት ሥራዎች መሠራታቸውን ማንም ኢትዮጵያዊ አይቃወምም፣ ነገር ግን በልማት ስም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናንን በመንጠቅ፣ ከማንነቱ መለየትና ከርስት መንግሥተ ሰማያት በኣፍአ እንዲቀር ማድረግ ተገቢ እንዳልሆነ ለመግለጽ እንወዳለን። እኛ የምንቃወመውም ርዳታውን እና ልማቱን ሳይሆን ከልማቱ በስተጀርባ ያለውንና ሰውን ከሃይማኖት መለየቱን ነው።

የኢትዮጵያ አዲስ ኪዳን መጥምቃዊት ቸርች ደግሞ በትምህርት ዘርፍ ላይ ተሰማርታ ሕፃናት ላይ ትኩረት አድርጋ የምትሠራ ናት። በተለያዩ አካባቢዎች ትምህርት ቤት በመክፈት በቅናሽ ዋጋ እና ለወላጆች በሚደረግ ድጋፍ ስም የራሷን የእምነት ማስፋፋት ሥራ እየሠራች ነው። እስካሁን የእንቅስቃሴው አድማስ በሰሜን ሸዋ ዞን ዓለም ከተማ ወረዳ ላይ ቢሆንም ከተነደፈው ፕሮጀክትና ይዘውት ከተነሡት ግብ አንጻር በዚህ እንደማያቆም ግልጽ ነው።

ሌላው መነሣት ያለበት ጉዳይ ባለፉት ቅርብ ዓመታት ትግራይ አካባቢ እየተካሔደ ያለው የተሐድሶ እንቅስቃሴ ነው። ማኅበረ ሰላማ መወገዙ የሚፈልገውን የቅሰጣ ተግባር ከመሥራት አልከለከለውም። እንዲያውም አድማሱን አስፍቶ ከምእመናን ወጥቶ በየዩኒቨርሲቲው የሚማሩ ተማሪዎችን እና የቅዱስ ፍሬምናጦስ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀ መዛሙርትን በመሰብሰብ በሥውር ማሠልጠንና ማስተማር ጀምሯል። ከማኅበረ ሰላማ በተጨማሪ ባለፈው ዓመት ትግራይ ተሐድሶ መንፈሳዊ

ማኅበር (ቤተ ክርስቲያን) የሚባል የተሐድሶ ማኅበር ተመሥርቷል። ይህ ማኅበር ደንብ ቀርጾ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ እየተንቀሳቀሰ ነው። ይህ ሁሉ የሚያሳየን እየተካሔደ ያለው የተሐድሶ እንቅስቃሴ አድማሱ ምን ያህል ሰፊ እንደ ሆነና አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ሰሜኑን የአገራችንን ክፍል ምን ያህል ትኩረት እንዳደረጉበት ነው።

የአንድ አገር ልማትና ዕድገት ወደ ላቀ ደረጃ የሚደርሰው የሃይማኖት፣ የዘር፣ የቀለም ገደብ ሳይገድበው በተባበረ ክንድ ሲሠራ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው ሁሉ የአገሩን ልማትና የጎበረተሰቡን ዕድገት የሚጠላ አይሆንም። ሆኖም የልማቱ ተባባሪዎች ነን የሚሉ አካላት ፊት ለፊት ሰውን የሚያሳሱና መልካም የሚመስሉ ነገሮችን እያሳዩ ውስጣቸው ግን በማር የተለወሱ መርዞች ይዘውና ሌላ ተልእኮ አንግበው የሚንቀሳቀሱ ከሆነ ልማቱም ልማት፣ ዕድገቱም የተሟላ አይሆንም። ምክንያቱም አንድ ሕዝብ ለአገሩ ክብር፣ ለሃይማኖቱ ፍቅር፣ ለማኅበራዊ እሴቱ ዋጋ ከሌለው ማልማትም ማደግም አይችልምና።

እስካሁን ያየናቸው በልማት ስም የተሠሩት ሥራዎች ደግሞ ውስጣቸው ቤተ ክርስቲያንን የማፍረስ ሴራ ያነገቡ የራስን አስተሳሰብና እምነት በሌሎች ላይ ለመጫን ዓላማ ያደረጉ ናቸው። ይህ ዓይነቱ አካሔድ ግን ፍትሐዊም ሃይማኖታዊም አይደለም። ልማትን እንደ መሸፈኛ ተጠቅመው የቀረቡት ከላይ የጠቀስናቸው ተግባራትም በቤተ ክርስቲያን ላይ የተነጣጠሩ የጥፋት ተልእኮዎች እንጂ አማናዊ ልማቶች ስላልሆኑ ዝም ተብለው መታየት የለባቸውም።

ምንጭ፡- ስምዐ ጽድቅ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጋዜጣ፣ 23ኛ ዓመት ቁጥር 3፣ ቅጽ 23 ቁጥር 331፣ ከጥቅምት 16-30 ቀን 2008 ዓ.ም.

Miko ZE Ethiopia

ከሚዛኑ ሳይሆን ከመዛኙ

ከከሣቴ ብርሃን ገ/ኢየሱስ

63/ ሰሞኑን መናፍቁ ‹‹ሄቨን›› ‹‹መጽሐፈ ኑፋቄ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን ›› በሚለው ‹‹page ›› ላይ እመቤታችንን በተመለከተ የጻፈችውን ጽሑፍ እንደብዙዎች እኔም አንብቤዋለሁ።

እንደተለመደው የጥላቻ ስድብና የክህደት አባባል ሞልቶበታል። እኔም የማምነውንና የምታመንለትን ነገር የመመስከርና ለሚሰነዘሩ ጥያቄዎች መልስ የመስጠት ክርስቲያናዊ ግዴታዬን ለመወጣት የሚከተለውን ምላሽ አቅቤያለሁ። ይህ ጽሑፍ ‹‹ሄቨንን›› ለመገሰጽና ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀ ብቻ ሳይሆን ተደጋግሞ የሚለፈፍ ነገር እውነት እየመሰላቸው በድቡሽታዊ መሬት የተገነባ እምነታቸው በጥርጥር ነፋስ እየዘመመ ያለ ምዕመናንን በአንጻረ ‹‹ ሄቨን›› አስተምሮ በማይነቃነቅ ዓለት የቆመ ማትናወጥ እምነት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው።

ሄቨንበጽሁፏ ኹለት መሰረታዊ የክህደት አባባሎችን ተናግራለች።

1ኛው -ድንግል ማርያምን የመላዕክት እህት በማለት ኦርቶዶክሳዊያን ሃይለ አርያማዊ መልአካዊ መልክዕ ይሰጧታል። የሚልና

2 ኛው-እመቤታችን ለዮሴፍ የተሰጠችው በሚስትነት ነው። ክርስቶስን ከወለደችም በኋላ ሌሎች ልጆች አሏት (ላቲ ስብሐት) የሚሉት ናቸው። እያንዳንዳቸውን ከቤተክርስቲያን ትምህርት አንጻር እንዴት እንደሚታዩ አንድ በአንድ ለመዘርዘር እሞክራለሁ።

፩. እመቤታችን የመላእክት እህት (እህተ መልዕክት) ለምን ተባለች?

እመቤታችን እህተ መላዕክት የመባሏን ምስጢር ከመናገራችን በፊት ወንድምነትና እህትነት በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ምን እንደሚመስል ማየቱ ተገቢ ነው። የሄቨን ክህደት ስር ይህ ነውና። እንደሷ አመለካከት እመቤታችንን እህተ መላዕክት ማለት በዘር ወይም በተፈጥሮ ከመላእክት ጋር በመዛመድ የመላእክት አካል ለብሳለች ብሎ እንደመናገር ነው። ይህ አላዋቂ አነጋገር ተሸክማው ለምትዘረው፤ ለይስሙላ ለምትጠቀሰው ለምትዘረዘረው መ/ቅዱስ ባይተዋር መሆኗን በግልጥ ያሳያል። ምክኒያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ የእህትነትና ወንድምነት ጽንሰ ሐሳብ በዘርና በተፈጥሮ ዝምድና የተወሰነ ብቻ ስላልሆነ ነው። እንዲያውም ራሱ መጽሐፉ ወንድም፤ እህት ብሎ የሚጠራቸው ብዙዎቹ በዘር ዝምድና ወንድም ወይም እህት ያልሆኑ ናቸው። ጥቂት ምሳሌዎችን ልጥቀስ።

1. ከአርዕስተ አበው አንዱ አብርሃም ከካራን ሲወጣ አብሮት የወጣው ሎጥ ወንድሙ ተብሏል።(ዘፍ ፲፪፤፲፪) በሥጋ ዝምድና ከሄድን ርግጥ ነው ሎጥ ወንድሙ ልጅ፤ አብርሃምም ለሎጥ አጎቱ እንጂ ወንድሙ አልነበረም ዘፍ ፲፩፤፲፯ (ዘፍ ፲፪፤፲፯)። ዳሩ ግን በግብር ሥጋዊ አንድ ላይ የኖሩ የወንድም ያህል የሚፋቀሩ፤ በግብር መንፈሳዊ በህገ እግዚአብሄር የኖሩ ብፁዓን ማቴ ፭፤፲)ስለሆኑ ቅዱሳን ተባሉ::

2. ዐማዒው ከለዳውያን ንጉሥ ብልጣሶር የናቡከደነፆር ልጅ ተብሎ ተጠርቷል። ራሱም ንጉሥ ናቡከደነፆርን አባቴ ብሎ ጠርቶታል። (ዳን ፭÷፰) በጭካኔና በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ የሚመስለው ናቡከደነፆርን አባቴ ብሌ ቢጠራውም ራሱ መ/ቅዱሱም ልጅ ቢለውም በመንግስትና በእግዚአብሔር ንዋያት ላይ በፈጸሙት ግፍም የተተካኩ ነገስታት ስለሆኑ በአባትና ልጅ ተፈረጁ እንጂ ትክክለኛ ዝምድናቸው የአያትነትና የልጅ ልጅነት ነው። (መጽሐፍ ቅዱስ የግብር መስማማትን ለመግለፅ ያለቀጥታ ዝምድና እህት፣ወንድም፣ አባት ፣ልጅ ----- እያለ እንደሚጠራ ልብ በል!)

3. በዘመነ አዲስ ኪያሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን 120 ቤተሰቦቹን ወንድሞቼ እያለ ይጠራቸው ነበር። በዋለበት የዋሉ ባደረበት ያደሩ ተከታዮች ስለሆኑ። ከእርሱ ጋር መብል ስጋዊን ከእሱም መብል መንፈሳዊ የበሉ የጠጡ ናቸውና።

4. ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ በክርስቶስ የተባሉ ምእመናን ሁሉ በክርስቶስ ወንድሞችና እህቶች እንደሆኑ ግሪካዊ፣አይሁዳዊ፣ህዝብ፣ አህዛብ፣የገዘረ ያልተገዘረ የሚል ልዩነት ሳይኖር ከማህፀነ ዮርዳኖስ የወጣ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ የተወለደ ተጠምቆ የስላሴን ልጅነት ያገኘ ሁሉ ወንድምና እህት እንደሆነ ገልፀናል። ( ) ይህ አራተኛው ማስረጃ በመንፈስና በእምነት በሃይማኖት የሚገኝ ወንድምነትና እህትነት ከስጋ ወንድምና እህትነት በመንፈሳዊ ህይወት ጎልቶ እንደሚታይ ያሳያል። በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ሌሎች ቅዱሳት መጽሐፍት እንደ ሃይማኖታዊ መጽሐፍትነታቸው ትኩረት የሚሰጡት ለሃይማኖታዊ ዝምድና እንደሆነ ልብ

ልንል ያስፈልጋል።

እንግዲህ ይህን ያህል ስለ ወንድምነት እና እህትነት የመጽሐፍ ቅዱስን እይታ ከተመለከትን ወደ ፍሬ ሐሳቡ እንመለስ።

እመቤታችን እህተ መላእክት ተብላ ትጠራለች። ሊቁ አባ ሀርያቆስ ‹‹እህተ መላእክት፤ እመ ሰማዕታት ፤ወእግዝዕተ ፃድቃን እያለ ሲጠራት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ‹‹ደግሞ እህተ መላእክት ወእመ ኩሉ ሕዝብ ... የመላእክት እህት የህዝቡ ሁሉ እናት›› ብለዋታል። አባ ሀርያቆስም ሆነ አባ ጊዮርጊስ እመቤታችን የሰማዕታት፤የፃድቃን የህዝቡ ሁሉ እናት ብለው ሲጠሯት እንደው በራሳቸው ሳይሆን ‹‹እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ (ሰው ሁሉ እናታችን ጽዮን ይላል) መዝ (፹፯÷፭) የሚለውን ፍፃሜው ለድንግል ማርያም የሆነውን ቃለ ትንቢት በማስታወስና ‹‹እነኋት እናትህ›› ዮሐ (፲፱÷፳፯) በማለት ጌታችን ድንግልን በዮሐንስ ወኪልነት ከዕፀ መስቀሉ ስር ለተገኙ ክርስትያኖች በእናትነት የሰጠበትን ቃል ኪዳን በማሰብ ነው።

እህተ መላዕክት ሲሏትም በም/ክ ነው

ከንጽህና አንፃር

Ø ቅዱሳን መላእክት በባህርያቸው ንፁሐን ንኡዳን ክቡራን ናቸው። የረከሱ ፍጥረታትን በምልጃቸው ያስምራሉ እንጂ እነሱ ራሳቸው አይረክሱም። ከሃጢአት ያልተመለሱ ልበ ደንዳኖችን ሊገስጹ አሊያም እንደሰዶምና ገሞራ ሊቀጡ ይላካሉ እንጂ እነሱ ሀጥያት አይሰሩም። በአምልኮ እግዚአብሔር ፀንተው በምስጋና ተግተው በተሰጣቸው ስፍራ (በኢዮር፤በራማ፤በኤረር፤ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት፣በመንበረ መንግስት) በንፅህና በቅድስና ዘለአለም እስከ ዘለአለም ይኖራሉ።

Ø እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደ መላዕክት በንፅህና በቅድስና ኖራለች። ንፅሕናዋም በሁለት መንገድ ይገለፃል። አንደኛው << ሞት በአንድ ሰው በአዳም ም/ክ ወደ ዓለም ገባ እንዳለ ቅ/ጳውሎስ ሁሉ በአዳምና በልጆቹ ላይ በወረደ መርገመ ሃጥያት(ጥንተ አብሶ) ሲረክስ እመቤታችን ግን ይህ የቀደመ መርገም ያልነካት ንፅህት መሆኗ ነው። ኢሳ ፯÷፲፬ (የዚህን ምሳሌ በዘመነ ጌዲዮን መ/መሳ ፮÷፴፮-፴፱መለከቷል።) 2 ተኛው ከሃልዮ ከነቢብ ከገቢር ሀጥያት የነፃች በስጋም በነፍስ ሀጥያት ያላወቃት (ማርያም ድንግል ንፅህተ ስጋ ወነፍስ እንዳለ ደራሲው በመልክአ ማርያም) መሆኗ ነው ። ይህንንም ቅ/ገብርኤል (ቡርክት አንቲ እም አንስት... ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ) በማለት መስክሮላታል ። ይህ ፍፁም ንጽህናዋን አምላክ ተመለከተና በማህፀኗ አደረ በስጋም ወለደችው። እንግዲህ የድንግል ማርያም ንጽህና እንደ መላዕክቱ የባህርይና ለሁሉም ወገን በመሆኑ በንጽህና ለምትመስላቸው የመላዕክት እህት ተባለች ይህ ታዲያ ምን ይደንቃል?

2 ከግብር አንጻር

የእግዚአብሔርን የክብር ዙፋን የሚሸከሙ ኪሩብ (በብዙ ኪሩቤል)መላዕክት ናቸው። እነዚህ መላዕክት እግዚአብሔር በዘፈቀደ ለቅዱሳን እንደታያቸው እሳታዊውን ዙፋን በደመና ይሸከማሉ።፯ የእሳት መጋረጃዎች በዙፋኑ ዙሪያ ተከልለዋል። እመቤታችን በማኅጸኗ ዙፋንነት በሆዷ ያስቀመጠችው ያን ኪሩቤል የሚሸከሙትን እሳተ መለኮት ነው። በሰማያዊው ዙፋን ፯ የእሳት መጋረጃዎች ጌታን እንደከለሉት በድንግል ማህጸን ዙፋን በተቀመጠ ጊዜ በ፯ቱ ባህርያተ ሰብእ (፫ቱ ባህርያተ ነፍስና

፱ቱ ባህርያተ ሥጋ አምላክነቱን ሰወረ። በመሆኑም በሰማይ ዙፋኑን ለሚሸከሙ መላዕክት (ኪሩብ)አምላክን ፱ወር ከ፯ቀን በማህጸኗ ዙፋንነት ያስተናገደች እመቤታችን እህታቸው ተባለች። አንድም መላእክት ዘወትር በዙፋኑ ፊት ቆመው በፍርሐትና በመንቀጥቀጥ ቅዱስ፣ ቅዱስ ፣ቅዱስ እያሉ ያመሰግኑታል። ይማጸኑታል እመቤታችንም በአማላጅነት በንጉሱ ቀኝ ትቆማለችና እህታቸው ተባለች። <<ወትቀውም ንግሥት በየማንከ... ንግስቲቱ በቀኝህ ትቆማለች እንዲል >>መዝ.፵፬፥፱

3. ከምልጃና ከመዳን ሰራ አንፃር

መዳን በእግዚአብሔር በማመን እና ህጉን ትዛዛቱን በመፈፀም ነው ። እግዚአብሔርም እንዳንጠፋ ስለሚፈልግ በእርሱ ለምናምን ለእኛ ብዙ የድህነት መንገዶችን ሰጥቶናል ። ከነዚህ ውስጥ ምልጃ በዋነኝነት ሚጠቀስ ነው። ድህነት እና ንስሐን በተመለከተ መላእክትንና ድንግልን የሚያመሳስላቸው ነገር አለ። ሁለቱም የሰው ልጅ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ አጥብቀው ይሻሉ። ተመልሶ ወደ ህፅነ እግዚአብሔር ሲገባም ደስ ይሰኛሉ። በአንዲት ነፍስ መዳን በሰማይ መላእክት ዘንድ ታላቅ ደስታ እንደሚሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ድንግል ማርያምም የሰው ልጅ ብቻም ሳይሆን ፍጥረት ሁሉ ቢፅድቅላት ደስ የምትሰኝ ርህርህት እናት ናት። ስለዚህ ድንግል ማርያምም ሆኑ መላእክት ፍጡራን እንዲድኑ ካላቸው ጽኑዕ መሻት የተነሳ ዘወትር በጌታ ፊት ምልጃን ያቀርባሉ። ጸሎታቸውም መና የሚቀር ሳይሆን በቅድስናቸው ብዛት ካገኙት ሞገስ የተነሳ እግዚአብሔር የሚሹትን ስለሚፈፅምላቸው ሀይል ያለው ነው። ያዕ ፭፥፲፮ ስለሆነም ስለዚህ የምልጃና የድህነት ስራ ድንግል ማርያም

የመላእክት እህት ተባለች ።

ባጠቃላይ ድንግል ማርያም እህተ መላእክት ስትባል ከላይ ባነሳናቸው ምክንያቶች እንጂ ሄሸንና መሰሎቿ እንደሚያስቡት መላካዊ አካል ተጋርታ አይደለም ። መላዕክት እንደማያገቡ እንደማይጋቡ በዘርዓ-ብእሲ እንደማይራቡ በማቴ.፳፪፡፴- ፴፪ ተገልጿል ። ስለዚህ በህገ መላእክት የሚኖር ወይም የኖረ ጻድቅ ሰው (እንደ ድንግል ማርያም)ይኖራል እንጂ የመልአክ አካል ያለው ሰው አልኖረም አይኖርምም ።

<< የአብዬን ለእምዬ >> ሆነ እንጂ ነገሩ መላእክት እንደ ተጋቡ አድርገው ወገኖቻቸውን የሚሰብኩትስ ያው የነሱ ዘሮች (የዮሐዋ ምስክሮች) ናቸው። ድንግል ማርያምም ሀይለ አርያማዊት ፤ሰማያዊት ባህርይ እንዳላት ከምድር እንዳልተገኘች የሚያምኑትም አባቶቻቸው ካቶሊኮች ናቸው። እኛ ግን ከላይ እንደገለፅነው መላእክት አያገቡም አይጋቡም፤እመቤታችንም ከአባትዋ ከኢያቄም ከእናትዋ ከሐና የተወለደች የዳዊት ዘር ሆና ሳለ በንፅህናዋ ፤በትህትናዋ አምላክን ለመውለድ ተመረጠች በዚህም ከፍጡራን በላይ ተባለች ብለን እናምናለን ።

ወስብሃት ለእግዚአብሔር

የባ/ዳር ካቴድራል መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ሰ/ት/ቤት ገጽ ፔጁን ላይክ በማድረግ መንፈሳዊ እውቀትዎን ያጎልብቱ

እውነተኛው ድኅነት በመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

እባክዎ የብዙ ሰዎች የድነት ጥያቄ ስለሆነ ሼር ያድርጉ

64/ ድኅነት ማለት በዚህ ፅሁፍ ትርጉም ዘላለማዊ ህይወት ማግኘት መንግስተ ሰማያትን መውረስ ማለትነው

- “ መዳን በእምነት ብቻ ነው ” የሚለው የፕሮቴስታንቶች የድኅነት መፈክር ነው።ይህም አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ለብቻ ነጥሎ የመጠቀምን አደገኛነት የሚያመለክት ነው።

እምነት ለመዳን የመጀመሪያው ደረጃ ነው

- ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ “እንግዲህ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ።” ዮሐ 8፡24። “ያመነ የተጠመቀም ይድናል።” ብሏል። ማር 16፡16።

- እምነት ለመዳን የመጀመሪያው ደረጃ ቢሆንም ብቸኛው ጉዳይ ግን አይደለም።

ምሳሌ 1

- አረጋዊው ስምኦን ሕፃኑን ጌታችንን ታቅፎ “ጌታ ሆይ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና” ሉቃ 2፡29-30። ቢልም ከሠላሳ ሦስት ዓመት በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከበረ ደሙ ፈሳሽነት

የፈጸመውን ማዳን ግን አላየም ነበር።

- አረጋዊው ስምኦን ያየው የጌታችንን ልደት ነበር። ነገር ግን

ሰው መሆኑ ወደ መዳን

የሚያደርስ የመጀመሪያ ደረጃ በመሆኑ የተነሳ ያለመጠራጠር

“ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት

ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋል።” አለ።

- ሰውን በማዳን ጉዞ የመጀመሪያ የሆነው የጌታችን

መወለድም በዚህ ክፍል ሁሉንም ሂደት

የሚገልጽ ሆኖ ተቀምጧል። ታዲያ ይህ ማለት በመወለዱ

ብቻ ድነናል ማለት ነው?

አይደለም ምክንያቱም “ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም።”

ተብሎ ተጽፎልናልና። ዕብ 9፡22።

ምሳሌ 2

- ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ሲላስ ለእስር ቤት ጠባቂው “በጌታ

በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና

ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።” የሐዋ ሥራ 16፡31።

አሉት።

- ታዲያ በርሱ እምነት ብቻ ቤተሰቡ ሁሉ እንዴት ሊድን

ይችላል? የአንዱ ሰው እምነት

ሌላውን ሰው ሊያድነው ይችላል?

- ትክክለኛው ትርጉሙ የወህኒ ቤት ጠባቂው እምነት ለራሱ

መዳን የመጀመሪያ ደረጃ

እንደሆነ የሚያስረዳ ነው።

- የመጀመሪያ ደረጃ የሆነው የእርሱ ማመን ቤተሰቡ በሙሉ ወደ እምነቱ እንዲገቡ የሚጠቅም ቤተሰቡንም ሁሉ ወደ ድኅነት የሚመራ መልካም ጅማሬ ነበር።

- ይህም በሚከተለው ጥቅስ ተገልጿል። “ለእርሱና በቤቱም ላሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩአቸው። በሌሊትም በዚያች ሰዓት ወስዶ ቍስላቸውን አጠበላቸው፥ ያን ጊዜውንም እርሱ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ተጠመቀ።” የሐዋ ሥራ 16፡ 32-33።

- የወህኒ ቤት ጠባቂው እምነት ለቤተሰቡ ሁሉ መዳን ምክንያት የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ ሌላውንም (የቤተሰቡን እምነትና ጥምቀት) ደረጃ ሳይቀንስና ሳያጠፋ ሁሉን ሂደት የሚገልጽ አድርጎ ተጠቅሞበታል።

ምሳሌ 3

- ጌታችን ዘኬዎስን “ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል።” አለው። ሉቃስ 19፡9።

- ጌታችን ለዘኬዎስ ይህን የተናገረው ዘኬዎስ ያለአግባብ ከሌሎች የወሰደውን ሁሉ አራት እጥፍ አድርጎ ሊከፍል ቃል ሲገባ ነው። ጌታችን የተናገረው

ቃል የሚያስገነዝበን

የዘኬዎስ ንሥሐ ለቤተሰቡ ሁሉ መዳን የመጀመሪያ ደረጃ

እንደሆነ ነው። ነገር ግን ንስሐ

ብቸኛው ደረጃ አይደለም።

- ቤተሰቡ በሙሉ ንስሐ መግባትና ማመን አለበት። ከሁሉም

በላይ በመስቀል ላይ

በሚፈሰው ደሙ ስለሚፈጸመው ማዳኑ የገባው ቃል

ያረጋገጠው ይህን ነውና።

ምሳሌ 4

- ቅዱስ ጳውሎስ “እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን

በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ

ሰላምን እንያዝ።” ሮሜ 5፡1። ቅዱስ ያዕቆብም “ሰው

በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ

እንዲጸድቅ ታያላችሁ።” ያዕ 2፡24። በማለት ጽፈዋል።

- ቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያውን ደረጃ እምነትን ሁሉንም

ሂደት ለማመልከት

የተጠቀመበት ሲሆን ቅዱስ ያዕቆብ ደግሞ እምነት ብቻውን

እንደማያጸድቅ ገልጦልናል።

ምሳሌ 5

- ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችን ተገልጦለት “የኃጢአትንም ስርየት

በእኔም በማመን በተቀደሱት

መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን

ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር

ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ፥ ከሕዝቡና ወደ

እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ

አድንሃለሁ።" እንዳለው ነግሮናል። የሐዋ ሥራ 26፡18።

- በሌላ ክፍል "... ንስሐ ይገቡ ዘንድና ለንስሐ የሚገባ ነገር

እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር

ይሉ ዘንድ ተናገርሁ።" አለ። የሐዋ ሥራ 26፡19-20።

- በመጀመሪያ እምነት ቀዳሚው ደረጃ ሆኖ የተጠቀሰ ሲሆን

በሁለተኛው ክፍል ደግሞ

እምነት ብቻውን ሳይሆን ሌሎችም (ንስሐ/ ወደ

እግዚአብሔር መመለስ/ መልካም ሥራ)

ደረጃዎች ለመዳን አስፈላጊነታቸው ተገልጿል።

ምሳሌ 6

- ቅዱስ ጳውሎስ "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።"

ብሏል። ሮሜ 10፡13። ይህንን

ያነበበ ሰውም ያመነ ሁሉ የሚድን ሊመስለው ይችላል። ነገር

ግን ጌታችን "በሰማያት

ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ

ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ

ሰማያት የሚገባ አይደለም።" በማለት የሥራንም አስፈላጊነት

ነግሮናል። ማቴ 7፡21።

- ስለዚህ እምነት የመጀመሪያው ደረጃ ሆኖ ሕግጋቱን

መጠበቅ ተከታዮቹ ደረጃዎች

እንደሆኑም ተጽፎልናል። ማር 10፡18-27፤ ሉቃስ 18፡

18-27።

ምሳሌ 7

- ጌታችን ስለ ልባሞቹና ሰነፎቹ ደናግል ምሳሌ ከተናገረ በኋላ

“ቀኒቱንና ሰዓቲቱን

አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።” አለ። ማቴ 25፡13።

- ይህንን ከሰነፎቹ ደናግል አንጻር እስኪ እንመልከት።

መንቃት በጌታችን የተጠቀሰ

ብቸኛው ቁምነገርና ለመዳን የመጀመሪያው ደረጃ ቢሆንም

የመጨረሻው ግን አይደለም።

1 ኛ ደረጃ፡- መንቃት

2 ኛ ደረጃ፡- ዘይት የሌለን መሆኑን ማስተዋል

3 ኛ ደረጃ፡- ልባሞቹን ደናግል እንዲረዱን መጠየቅ

4 ኛ ደረጃ፡- ምክራቸውን በመቀበል በፍጥነት ዘይቱን

ለመግዛት መሄድ

5 ኛ ደረጃ፡- ሙሽራው መጥቶ በሩን ከመዝጋቱ በፊት ተመልሶ

መድረስ

- እነዚህ ሰነፎቹ ደናግል የመጀመሪያው ደረጃ መንቃትን

ለመዳን የሚያስፈልግ ብቸኛው

ደረጃ እንደሆነ በመቁጠር ሌላውን ሁሉ ትተው በንቃት

ቢጠብቁ ሰነፎች ተብለው

አይጠሩም ይሆን? እንደዚሁ ለመዳን የሚያስፈልግ ብቸኛ
ደረጃ እምነት ብቻ ነው የሚልም
ሰው ሰነፍ ይባላል። “አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ
ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ
ትወዳለህን?” እንደተባለ። ያዕቆብ 2፡20
- እምነትን ከሥራ መለየት ነፍስን ከሥጋ እንደ መለየት ነው።
ውጤቱም ሞት ነው።
“ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ
የተለየ እምነት የሞተ ነው።”
ያዕ 2፡26።
- ቅዱስ ያዕቆብ መልካም ሥራን ከነፍስ፤ እምነትንም ከሥጋ
ጋር ያለማዘዋወር ማገናኘቱስ
ምን ያህል ድንቅ ነው!!!
ፕሮቴስታንቶች ንስሐ አንዱ የጸጋ ሥራ አድርገው ሲቆጥሩት
ሰው ባይሻውም
በኢየሱስ እግር ሥር ራሱን ከጣለ ከኃጢአቱ ነጻ ይወጣል
ይላሉ።
- በኦርቶዶክሳዊ እምነት የሰው መንፈሳዊ ሕይወት ሁሉ
ከመንፈስቅዱስ ጋር ኅብረት ያለው
ነው። መንፈስቅዱስ በጎን እንድናደርግ ቢረዳንም መሻት ግን
ያስፈልገናል። መሻት
የሌላቸውንም ሐዋርያው “ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና

ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ
አልተቃወማችሁም” በማለት ይወቅሳቸዋል። ዕብ 12፡4።
- ቅዱስ መጽሐፍ መንፈሳዊ ሕይወትን የእግዚአብሔር የጦር
እ
ቃ የሚያስፈልገው ትግልእንደሆነ “መጋደላችን ከደምና ከሥጋ
ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም
ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት
መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው
እንጂ። ስለዚህ በክፋው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም
ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦር ሁሉ Aንሡ።” በማለት
ያስረዳናል። ኤፌሶን 6፡12።
- ሰው ይህንን ጦርነት ያለ ጥርጥር ተዋግቶ ማሸነፍ
ይጠበቅበታል። እርሱም ሥራ ነው።
- ይህም ውጊያ ጌታችን ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት
መላእክት/አለቆች በላከው መልእክቱ
“ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፥ ነጭ ድንጋይንም
እሰጠዋለሁ” ራዕ 2፡17። እንዳለው
የራሳችንን መወጣት ይጠበቅብናል። “ወደ እኔ ተመለሱ፥
ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥
እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ
እግዚአብሔር” ያለንም ለዚሁ ነው።

ዘካ 1፡3።

- ከሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ይገለፃሉ።

1. እምነት

2. ጥምቀት

3. የቤተክርስቲያን ምስጢራት

4. መልካም ሥራ

1. እምነት

- “እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።”

ዕብ 11፡1።

- “እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል። አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን?” ያዕ 2፡19-20።

- “ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።” 1ኛ ቆሮ 13፡2።

2. ጥምቀት

- ምስጢረ ጥምቀት ከጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ እስከ

ዛሬ ድረስ በኦርቶዶክሳዊት

ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸም ነው። ይህም “እንግዲህ

ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ

በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥

ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ

እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም

እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ

ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። ” በሚለው ቃሉ የተደገፈ ነው።

ማቴ 28፡19-20።

3. የቤተክርስቲያን ምስጢራት

- የተጠመቁ ከጥምቀታቸው፤ ንስሐ የገቡ ከቀኖናቸው በኋላ ፤

የጋብቻ ምስጢር

የተፈጸመላቸውም... ቅዱስ ቁርባን መቀበል ይኖርባቸዋል።

የቅዱስ ቁርባን ጥቅሞች

1. የኃጢአት ሥርየትና ድኅነት

ሁላችንም ዘወትር እንበድላለን፤ ዘወትርም በጌታችን ደም

ከኃጢአታችን መታጠብ

ይኖርብናል። “የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት

ሁሉ ያነጻናል። ... ኃጢአትን

አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ

ውስጥ የለም።” 1 ኛ ዮሐ 1፤8-10።

2. በቃልኪዳኑ መሠረት በርሱ ለመኖር መቻል

“ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም
በእርሱ እኖራለሁ። ”
ዮሐ 6፤53-58።
3. ዘላለማዊ ሕይወት
“ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት
አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን
አስነሣዋለሁ።” ዮሐ 6፤54 እና 58።
4. በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ፤ መንፈሳዊ ብቃት ማግኘትና
በርሱ ሕያው መሆን
“ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና።
ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም
ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ
ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል። ”
ዮሐ 6፤55 እና 57።
5. በቅዳሴ እንደተገለጸው ለነፍሳችን፤ ለሥጋችንና
ለመንፈሳችን መታደስን ይሰጣል
ቅዱስ ቁርባን ከመቀበላችን በፊት የሚያስፈልጉ ጥቂት
ቅድመ ሁኔታዎች
- ኦርቶዶክሳዊ መሆንና ጎብስቱ ወደ እውነተኛ ሥጋነት
ወይኑም ወደ እውነተኛ ደምነት
እንደሚለወጥ ማመን። “ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት
በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ

አመሰገነ፥ ቆርሶም። እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን
ሥጋዬ ነው” 1ኛ ቆሮ 11፡24።
- ዘወትር የሚናዘዝና ንስሐ በመግባት ኃጢአትን በመተው
የሚኖርና ለዚሁም የንስሐ አባት
ያለው መሆን።
- የተጣለውን የታረቀ መሆን “እንግዲህ መባህን
በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች
በአንተ
ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን
ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም
መጥተህ
መባህን አቅርብ። አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር
ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም
ለሎሌው፥
ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤ እውነት እልሃለሁ፥ የመጨረሻዋን
ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም።”ማቴ 5፡
23-24።
- ቅዳሴ የሚያስቀድስና ቃለ እግዚአብሔርንም የሚማር
መሆን
- ኦርቶዶክሳውያን ሰው ጌታችን “ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ
አትችሉም” በማለት ዮሐ 15፡5
እንዳስተማረን መልካም ሥራን መሥራት እንድንችል

የመንፈስቅዱስ እርዳታ

እንደሚያስፈልገን መረዳት ይኖርብናል።

- “እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም

ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ

ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል። አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ

ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ

ትወዳለህን?” ያዕ 2፡19-20።

- በእኛ ላይ የሚሆነው ፍርድ እንደ ሥራችን ይሆናል። ማቴ

25

- ልበ አምላክ ዳዊት “አቤቱ፥ ምሕረትም ያንተ ነው አንተ

ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን

ትሰጣለህና።” ብሎአል። መዝ 62፡12።

- “እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ፥

መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን፥ ወደ

ፍርድ ያመጣዋል።” መክ 12፡14።

- “የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ

አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ

ሥራው ያስረክበዋል።” ማቴ 16፡27።

- “ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ድካማችሁ በጌታ

ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና

የምትደላደሉ፥ የማትነቃነቁም፥ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ

የሚበዛላችሁ ሁኑ።” 1 ኛ ቆሮ 15፡58።

- “ቃሉ የታመነ ነው። እግዚአብሔርንም የሚያምኑት
በመልካም ሥራ በጥንቃቄ
እንዲጸኑ፥ እነዚህን አስረግጠህ እንድትናገር እፈቅዳለሁ። ይህ
መልካምና ለሰዎች
የሚጠቅም ነው፤ ከወገናችንም ያሉት ደግሞ ፍሬ ቢሶች
ሆነው እንዳይቀሩ፥ የግድ
ስለሚያስፈልገው ነገር በመልካም ሥራ እንዲጸኑ ይማሩ።”
ቲቶ 3፡8 እና 3፡14።
- “አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ
ጊዜ በሥራ የጸደቀ
አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ
ነበረ፥ በሥራም እምነት
እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን” ያዕ 2፡21-22።
- “መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን
አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ
እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።” ማቴ 5፡16።
- “ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር
ሰላምም ይሆንላቸዋል” ሮሜ 2፡10።
- “እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት
ነው።” ያዕ 4፡17።
- መዳን የእድሜ ልክ ሂደት ሲሆን በጾም፤ በጸሎት፤
በምስጋና፤ በንስሐ... መታጠር

አለበት። ዘወትር በጦርነት ውስጥ ነን ውጤቱም
እይታወቅምና ሰው
የመጀመሪያውን ውጊያ አሸንፎ በአሥራ ሁለተኛው ሊሸነፍ
ይችላል። ማንም
እስኪፈጽም ድረስ ስለ ውጤቱ እርግጠኛ ሊሆን አይችልም።
ማቴ 24፡13።
- ቅዱስ ጳውሎስ “በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን
መዳን ፈጽሙ።” እንዳለ ፊል 2፡12
- ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንደነገረው ጳጳሳትም እንኳ
ቢሆኑ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል።
“ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ ይህን
ብታደርግ፥ ራስህንም
የሚሰሙህንም ታድናለህና።” እንዳለ። 1ኛ ጢሞ 4፡16
- ቅዱስ ጴጥሮስም “ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ
ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ
ዘንድ አለው? ” ብሎናል። 1ኛ ጴጥ 4፤18።
- ቅዱስ ጳውሎስም “... የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን
ኢየሱስን ተመልከቱን፥ በፊታችን
ያለውን ሩጫ በትእግሥት እንሩጥ።” እብ 12፡1።
- “እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል” ማቴ 24፡
13።
- ማንኛውም እምነትን ከሥራ ነጥሎ የሚሰብክ ሰነፍና

ሞትንም የሚሰብክ ነው።

“ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ ነውና ” ያዕ 2፡20።

- በርግጥም “እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው

ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ

ሊያድነው ይችላልን? ” ብሎናል። ያዕ 2፡14።

- እምነት ሥራ ካለው እምነቱም ሥራ ያሆናል። በእምነትም

የምንሠራው እግዚአብሔር

ያዘዘንን የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ዮሐ 6፡28-29፤ ዮሐ

5፡36።

እምነትና ሥራ

- የንስሐ ሕይወት ነው

- መንፈሳዊ ትግል ነው

- የቅድስና ሕይወት ነው

- እምነት የሚሠራው በፍቅር ሲሆን ነው

- አገልግሎት ነው

ይቆየን

ወስብሀት ለእግዚአብሔር

Dani EL Getachew

ሰበር ዜና፦

65/ ትንቅንቅ ከተሐድሶ መናፍቃን ጋር

www.atrons.com/2015/11/blog-post_21.html

አትሮንስ ኅዳር 12 ቀን 2008 ይህን ሁለት ቀን በጎንደር ከተማ ተሐድሶ

መናፍቃን መስመራቸውን ዘርግተው ባልታሰበ ጊዜ እና ወቅት ጠብቀው ኑፋቄአቸውን ለመዝራት ሲዘጋጁ ሰንብተዋል። አዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት እንድንሰብክ ፈቃድ ሰጥ□ናል የሚል የፎርጅድ ደብዳቤ ለተሐድሶ አራማጆች አካል ፋክስ በማድረግ አቶ መናፍቁ በጋሻው እና አሰግድ ሳህሉ ጎንደርን በወንጌል እንጎበኛታለን በሚል ድብቅ ሴራ ሲንቀሳቀሱ በወጣት ሰንበት ትምህርት ቤት ማህበረ ቅዱሳን እና ማህበራት አንድ በመሆን ሃሳባቸው ሊገታ ችሏል። የነዚህ መናፍቃን ስራ ቤተ ክህነት ድረስ በመሄድ እና አባቶቻችንን በማስጨነቅ ፈቃድ አግኝተው ቢሆንም ቅዱስ ገብር ኤል ቤተክርስቲያን ጉባኤውን ለማዘጋጀት ጉዳዩን ወደ ሰበካ ጉባኤው ሲተላለፍ ም ዕመናን ይህን ሲሰሙ በሕብረት ወደ ቤተ ክህነት በመሄድ ጉባኤው ሊታገድ ችሏል። ብጹእ አባታችን አቡነ ኤልሳ እንዳሉት እኔ ፈቃድ መስጠት አልፈለኩም ነበር ነገር ግን ጠቅላይ ቤተ ክህነት እንዲሰብክ ደብዳቤ ተጽፎለታል የሚል ደብዳቤ በመመልከቴ ነበር የፈረምኩት ነገር ግን ይህ ስህተት እንደሆነ ተረድቻለሁ እና ጉባኤው እንዲታገድ ሲሉ አስረድተዋል። ይህ በ እንዲህ እንዳለ አሰግድ ሳህሉ ወደ ግምጃ ቤት ማርያም የሐዲስ ኪዳን ጉባኤ ቤት በመዝለቅ ብር እሰጣችኋለሁ አትቸገሩም፤ አትራቡም፤ ልርዳችሁ በማለት ጉባኤ አዘጋጅተውለት ነበር፤ እኛም እንደአጋጣሚ ሆኖ ግምጃ ቤት ማርያም የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ አዘጋጅተን ነበር የጉባኤውም መንፈስ ጸረ ተሐድሶን በተመለከተ ነበር። ጉባኤው እየተካሔደ በነበረበት ወቅት እነዚህ ተሐድ□አዊያን ወደ ቤተክርስቲያኒቱ በመግባት ይሰብካል ያስተምራል እያሉ ጸብ ለመጫር ሞክረው ነበር። የጉባኤ ተማሪዎችም ባለማወቅ ገንዘብ

ስለረዳን ጉባኤ ቤታችን እንዳያድግ ለምን እንደዚህ ትሆናላችሁ አሉን። ከስንት ጭቅጭቅ በኋላ በስብሰባ ጉዳዩ እንዲገባቸው ከሆነ በኋላ የአሰግድ ሴራ እንዲከሽፍ ሆኗል። በመቀጠልም እኔ በማገለግልበት ደብር እኛ ሳናውቅ አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን መጥቶ እንደሚያስተምር ፕሮግራም ተይዞለት የነበረ ቢሆንም የ እኛ አባቶች ይህን መናፍቅ ባለማወቃቸው ይቅርታ ጠይቀው ጉባኤው ሊታገድ ችሏል። በአሁኑ ሰዓት የዛሬ ፲ አመት መናፍቃን ናቸው ተብለው ከቤተ ክርስቲያን ከተባረሩት ግለሰቦቻ ጋር በመሆን ኤጂ ሆቴል እየተዝናና ይገኛል። አሁንም ያለው ጎንደር ነውን እኛ የተዋሕዶ ልጆች እስከመቼ ድረስ ተኝተን እንኖራለን። አንድ ነገር ማድረግ ይጠበቅብናል። ሲኖዶሱ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው አለበለዚያ ግን እነዚህ ሰዎች አልተኙልንም ሰውን በተለያየ ጊዜና ወቅት እየጠበቁ ማጋጨት ስልታቸው ነውና እልባት ይሰጠን። እነዚህ መናፍቃን ም ዕመናኑን ማህበረ ቅዱሳን ነው ይህን የሚያደርግ እያሉ ያስወራሉ ያላስተዋለው ሰው እነሱን ተከትሎ ባለማወቅ ቤተ ክርስቲያንን ሲያቆስል ይኖራል። ስለዚህ ይህ ጉዳይ የማህበረ ቅዱሳን ብቻ ሳይሆን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ የሆነ ሁሉ ይምለከተዋል። እንደኔ ማኅበረ ቅዱሳን የተዋሕዶ ልጆች ስለሆኑ የቤተክርስቲያን ጉዳይ ያገባኛል ስለሚሉ መናፍቃን ይጠሏቸዋል። ማህበረ ቅዱሳን አባል ያልሆኑ ነገር ግን ተሐድሶን የሚያሳድድ አካል ካለ ማህበረ ቅዱሳን ነው እያሉ ማጭበርበራቸው የሚታወቅ ነው። ልናውቅ የሚገባን ቢኖር ማህበረ ቅዱሳንን በ እውቀት፤ በጉልበት፤ በሃሳብ በተለያየ መልኩ ልንረዳቸው ይገባል ምክንያቱም ዘብ የቆሙት ለቅድስት ቤተክርስቲያን ነውና። የ እኔ አቋምም እንዲህ ነው እኔ

የማህበሩ አባል አይደለሁም ነገር ግን በገንዘብ፤ በሃሳብ በማንኛውም ነገር እደግፋቸዋለሁ። ቤተክርስቲያንን እስከረዷት ድረስ። ለማንኛው የተሐድሶ መናፍቃንን ሃሳብ በጣጥሰን መጣል አለብን እንጂ እነዚህን ግለሰቦች ብቻ አይደለም። እሰከ መጨረሻው የተሐድሶ እንቅስቃሴን ልንበጣጥሰው ይገባል። በዚህ ሳምንት ጎንደር መጡ ነገስ» እንሰብበት ይህ ጉዳይ የሁላችንም ጉዳይ ነው።

Miko ZE Ethiopia

66/ የሮሜ 8፡34 የማታለያ ጥቅስ ሲጋለጥ

የኢየሱስን የባሕርይ አምላክነትና ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ መኾኑን ለማመን የተቸገሩና ፈራጅነቱን የካዱ ተጠራጣሪዎች ከሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች አንደኛው በሮሜ 8፡34 ላይ ያለው ጎይለ ቃል ነው። ይኸ “እስመ ለሊሁ ያጸድቅ መኑ ዘይኴንን ክርስቶስ ሞተ ወተንሥአ እሙታን ወሀሎ ይነብር በየማነ እግዚአብሔር ወይትዋቀስ በእንቲኣነ” (ርሱ ሲያጸድቅ የሚፈርድ ማነው ክርስቶስ ሙቶ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ በአብ ቀኝ ተቀምጧል ስለእኛም ይፈርዳል) የሚለው የጠራው የግእዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጎይለ ቃል በተለየ መልኩ በዘመናት ኹሉ ለዚኽች ቤተ ክርስቲያን መቼም ቢኾን መልካም ዐሰበው በማያውቁ ይልቁኑ ፈራርሳ ቢያይዋት ደስ

በሚሰኙ የክርስቶስን ፈራጅነት በካዱ በባሕር ማዶ ቀሳጮች ብዙ ጊዜ ተሰርዞ (ይማልዳል) በሚል ተቀይሮ እናነብባለን።

ለምስክርነት እስቲ እንይ፦

በ 1938 ዓ.ም ታትሞ የነበረው መጽሐፍ ቅዱስ “ክርስቶስ ኢየሱስ ሞተ ከሙታንም ተለይቶ ተነሣ፤ በአብ ቀኝ ተቀምጧል፤ ስለእኛም ይፈርዳል” ይላል

በ 1975 ዓ.ም ታትሞ ከግእዙ ወደ ዐማርኛው የተመለሰው “ርሱ ሲያጸድቅ የሚፈርድ ማነው ክርስቶስ ሙቶ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ በአብ ቀኝ ተቀምጧል ስለእኛም ይፈርዳል” ይላል።

በ 1980 ዓ.ም ግእዙን የሚያውቁ ዐይናማ ሊቃውንት ሳያዩት በጥቂቶች አስተባባሪነት የክርስቶስን ፈራጅነት በማያምኑ በምዕራባውያን የዶላር ድጋፍ የታተመው ደግሞ “እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኰንንስ ማን ነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” ይላል።

ይኽ ዕትም ችግሩ ይኼ ብቻ ሳይኾን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ የተጻፈበትን የግሪክን ቋንቋ እና ቀደምት የተተረጎመትን የግእዝ፣ የሶርያ፣ የአርመን፣ የቅብጥ ቅጅ በተለይ በግሪክ የተጻፈውን የ 1900 ዓመት እድሜ ያለውን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ከማየት ይልቅ እንግሊዞች እንዲመቻቸው አድርገው ቃላቱን በድፍረት እየጨመሩና እየቀነሱ በ 1611 ዓ.ም ያሳተሙትን የ 400 ዓመት ዕድሜ ያለውን የኪንግ ጀምስ ቅጂን ወደ ዐማርኛ ተርጕመው ለማቅረብ ሞክረዋል፤

በዚኹ በሮሜ 8፡27 ላይ “ወባሕቱ መንፈስ ለሊሁ ይትዋቀስ ለነ በእንተ ሕማምነ ወምንዳቤነ ወውእቱ የሐትቶ ለልብነ ወየአምር ዘይኄሊ መንፈስ ወይትዋቀስ በጎበ እግዚአብሔር በእንተ ቅዱሳን” (ርሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ይመልስልናል፤ ርሱ ልቡናችንን ይመረምረዋል፤ ልብ ያሰበውን ርሱ መንፈስ ቅዱስ ያውቃል፤ በእግዚአብሔር ዘንድም ለቅዱሳን ጸሎት መልስ ይሰጣል) የሚለውን ገጸ ንባብ ለውጦ በድፍረት “ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ ዐሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና” በሚል በድፍረት ቃሉን በመለወጥ መንፈስ ቀዱስንም አማላጅ አድርገው መንፈስ ቅዱስን በመናቅ አሳትመውት እናነብባለን።

ይኽ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ የተጻፈውን ቅዱስ ቃል ሰዎች እንደገዛ ፈቃዳቸው አጣምመው ለማቅረብ የሚሞክሩ ቢኾንም እስቲ ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 8፡33-34 ላይ “እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኰንንስ ማን ነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ ..... ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” የሚለውን ኀይለ ቃል በዝርዝር ዐይተን ሰዎች በተለያየ ጊዜ የጨመሩበት በባዶ ቦታው ላይ ያለው በእውነት ስለምን እንደሚያስገነዝብ መረዳት እንችላለን እስቲ ከዚኽ በታች እንየው፡-

“እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?”

ቅዱስ ጳውሎስ በዚኽ ምዕራፉ ላይ በትክክል እንዳስቀመጠው እግዚአብሔር መራጭ እንደኾነ ነው፤ ከላይ በትክክል እንዳየነው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ

እንደሰፈረው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ በእውነት እግዚአብሔር እንደኾነ የታወቀ የታመነ የተረጋገጠ ነውና ስለዚኽ “እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?” በማለት የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት አረጋግጦ ጻፈ፤ የመረጣቸውስ ማንን ነው ቢሉ “ንዑ ትልዉኒ” (ኑ ተከተሉኝ) ብሎ የጠራቸው ብሎ ሐዋርያትን፤ ዳግመኛም 72 ቱ አርድዕትን፣ 36 ቱ ቅዱሳት አንስትን ነው፤ ይኽንንም ወንጌላዊዉ ማቴዎስ “ዐሥራ ኹለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ ርሱ ጠርቶ እንዲያወጡአቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ኹሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው” በማለት ፲፪ቱ ሐዋያትን እንደጠራና ሥልጣንን እንደሰጣቸው በትክክል አስቀመጠ።

ራሱ ቅዱስ ጳውሎስም በዚኹ ምዕራፍ ቍ፴፩ ላይ “አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው” በማለት ሐዋርያት ሰብአ አርድዕት እያለ የሾማቸው ስምዖን የተባለውን ጴጥሮስ ልብድዮስ የተባለው ታዴዎስ፤ ዲዲሞስ የተባለውን ቶማስ እየለ የጠራ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መኾኑን መሰከረ።

“የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው” በማለት የጠራቸውን የሐዋርያት ነገራቸው ወንጌልን በተአምራት እያስረዳ እያጸደቀ እውነት መኾኑን ሰዎች እንዲያውቁት ያደረገው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መኾኑን አስረዳ። ከዚያም “ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው” የጠራቸው ሐዋርያቱን በዚኽም ዓለም በተአምራት በወዲያኛውም ዓለም “እውነት እላችኋለሁ፥ እናንተስ የተከተላችሁኝ፥ በዳግመኛ ልደት የሰው

ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ፥ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ" (ማቴ 19፡28) በማለት ያከበረው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን በትክክል እንዳስተማረ በቁ 32 ላይ ላይም "እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?" በማለት ማንም ሊወቅሳቸው የማይችለውን ቅዱሳን ሐዋርያትን የመረጠው ፍጹም እግዚአብሔር የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን ገለጸ።

የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው?

ቅዱስ ጳውሎስ በትክክል በዚኽ ላይም ማጽደቅ እና መኰነን የሚችል ርሱ ልዑል እግዚአብሔር እንደኾነ በትክክል አስቀምጧል፤ እውነት ነው ዓለምን በታላቅ ግርማ አሳልፎ መላእክቱን አስከትሎ በዙፋኑ ተቀምጦ ለኹሉም እንደ የሥራው የሚከፍለው፤ ጻድቃንን በቀኙ አቁሞ "እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ" ብሎ የሚያጸድቅ፤ በግራው የቆሙትን ኃጥኣንን ደግሞ "እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ" በማለት የሚኰንነው ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም እግዚአብሔር መኾኑን በትክክል ገለጸ። ራሱ ጌታ "የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል" በማለት እንዳስተማረን (ማቴ 25፡31-46)። ታዲያ ማጽደቅና እና መኰነን የፍርድ ሥራ እንጂ የማማለድ ሥራ ነውን በፍጹም አይደለም።

“የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው”

ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያትን የጠራው፣ የሚያጸድቀው የሚኰንነው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር መኾኑን በትክክል ካስረዳ በኋላ በመቀጠልም ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቶ ባባቱ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ መቀመጡን “የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው” በትክክል አስተማረ፤ ሞትን ድል አድርጎ ስለመነሣቱም ፊተኛው እና ኋለኛው ርሱ ስለመኾኑ ራሱ ጌታ “ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ” በማለት ይኽንን እውነት እንዲጽፍ ለዮሐንስ እንዳዘዘው ቅዱስ ጳውሎስም እውነቱን መሰከረ።

ወንጌላዊ ማርቆስም ስለዚኽ ነገር “ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ” (ማር 16፡19) በማለት ባባቱ ዕሪና መቀመጡን እንደነገረን ቅዱስ ጳውሎስም በድጋሚ ይኽንን አስተማረ።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት አስቀድሞ፥- “እግዚአብሔር ጌታዬን፥- ጠላቶችኽን በእግርኽ መረገጫ እስካደርግልኽ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው” ብሎ እንደተነበየ /መዝ.፻፱ (፻፲)፡፩/ በአብ ቀኝ ተቀምጧል። ቅዱስ ጳውሎስም ይኽ ትንቢት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈጸመ አስተምሯል /ዕብ.፲፡፲፪/

የመናፍቃን የሮሜ 8፡34 የማታለያ ጥቅስ ሲጋለጥ

part 2

ዓምደ ሃይማኖት የተባለው ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ የሉቃስ ወንጌልን በተረጐመበት ፳፬ኛው ምዕራፍ ላይ ይኽን በተመለከተ ሲናገር እንዲኽ ይላል፡- “ደቀ መዛሙርቱን ከባረካቸው በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ። በአባቱ ቀኝ (ዕሪናም) ተቀመጠ። የተቀመጠውም በባሕርየ መለኮቱ ብቻ አይደለም፤ በተዋሐደው ሰውነቱም ጭምር እንጂ። አካላዊ ቃል ባሕርያችንን ሲዋሐድ እኛን ወደዚኽ ክብር ለመመለስ ነበርና። ... እግዚአብሔር ሲኾን ስለ እኛ ሰው ኾነ። በፍቃዱ መከራ መስቀልን በተዋሐደው ሰውነቱ ተቀበለ። በተዋሐደው ሰውነቱ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በተዋሐደው ሰውነቱም ዐረገ። በሕያዋንና በሙታን ላይ ይፈርድ ዘንድም ዳግመኛ በክበበ ትስብእት ይመጣል” /Commentary on Luke, Chap.24/።

አኹን ለመለኮት የተገደበ የተወሰነ ቀኝ ግራ ፊት ኋላ አለው ማለትም አይደለም ቀኝ ማለት ጎይል ምልአትን በዕሪና መተካከልን የሚያመለክት ብቻ ነው ሊቁ “እስመ ብሂለ የማን ይመርሕ ጎበ ተዋሕዶቶሙ ወዕሪናሆሙ በክብር” (ቀኝ ማለት በክብር መተካከላቸውን ተዋሕዶቸውን ያመለክታል) እንዳለ፤ እንግዳን “ንበር” (ተቀመጥ)፤ ይሉታል እንጂ እንደ ባለቤት “ነበረ” (ተቀመጠ) እንዳይሉት ለዐይን ጥቅሻ እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ ከክብሩ አልተለየምና “ነበረ” ይለዋል፤ ለዚኽ ነው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ 1፡3 ላይ “በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ” በማለት የጻፈው።

እስኪ እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ቀኝ የሚለውን ጎሊናን በመሰብሰብ እንየው።

“እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን

ይልክልሃል በጠላቶችህም መካከል ግዛ” (መዝ 109፡1)

“እኔ ነኝ እኔ ፊተኛው ነኝ እኔም ኋለኛው ነኝ እጄም ምድርን መሥርታለች ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች በጠራኋቸው ጊዜ በአንድነት ይቆማሉ (መዝ 48፡12-13)

እንኪያስ ዳዊት፦ ጌታ ጌታዬን። ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው ሲል እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል? ማቴ 22፡43-44

“አቤቱ፥ ቀኝህ በኃይል ከበረ” (ዘፀ 15፡6)

“አቤቱ፥ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው? ቀኝህን ዘረጋህ፥ ምድርም ዋጠቻቸው” (ዘፀ 15፡11-12)

“የእልልታና የመድኃኒት ድምፅ በጻድቃን ድንኳን ነው የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች” መዝ 117፡15-16)

“ኢየሱስም፦ እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ” ማር 14፡62 ይላል።

በመኾኑም ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱሳን ሐዋርያቱን የጠራው የሚያጸድቀው የሚኾንነው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ስለመኾኑና ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቶ በአብ ቀኝ (ዕሪና) እንዳለ ከገለጸ በኋላ በዕለተ ዐርብ ባደረገው የድኅነት ምስጢር ዓለምን አድኖ ዋጋችንን የሰጠን ዳግመኛም በታላቅ ጌትነት ለፍርድ ተመልሶ የሚመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና “ደግሞ ስለ እኛ የሚፈርደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” በማለት በትክክል ተናገረ እንጂ፤ ምክንያቱም ከላይ ዝምሮ የጥቅሱን ሐሳብ እንዳየነው ሙሉ

ነገሩ የክርስቶስን እግዚአብሔርነት፣ መራጭነት፣ አጽዳቂነት፣ ኰናኝነት፣ ሞትን ድል አድርጎ መነሣት፣ በአብ ዕሪና መቀመጥ ብቻ ነው፤ ታዲያ ራሱ ክርስቶስ ፍጹም እግዚአብሔር ከኾነና በአባቱ ዕሪና ከተቀመጠ በኋላ እንሶ ወደ ማን ሊማልድ ነው ይባላል? ወደ አብ ወደ መንፈስ ቅዱስ እንዳንል በአምላክነት፣ በፈጣሪነት፣ በቅድምና፣ በእግዚአብሔርነት፣ በዕበይ፣ በመንግሥት፣ በሥልጣን፣ በመመለክ፣ በመመስገን፣ በገናንነት፣ በክብር፣ በኀይል፣ በክሂል፣ በፈቃድ፣ በትእዛዝ አንድ ናቸው።

ስለዚኽ ከጊዜ በኋላ እነዚኽ ቀሳጮች ምስጢረ ሥላሴን አፋልሰው የማይለየውን አንድነት ለመበታተን እንዲመቻቸው በማድረግ አስገብተውበታል እንጂ ክብር ይግባውና ጌታስ በዘመነ ሥጋዌዉ በዕለተ ዐርብ ባደረገው ተልእኮ ዓለምን ከራሱ፣ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አስታረቀ ዳግመኛም ታረቀ ከዚያም የማስታረቅን ቃል ለሐዋርያት ሰጥቶ በክብሩ ተቀመጠ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ በጌትነት ይመጣል እንጂ አኹንም እንደገና ያደነውን ዓለም እንደገና እንዳልዳነ አኹንም መልሶ ይማልዳል ማለት ሎቱ ስብሐት ጠላት ዲያብሎስ የዘራው መርዝ ኑፋቄ ክሕደት ነው።

ለዚኽ ነው ቅዱስ ጳውሎስ በ 2 ቆሮ 5፡18-20 “ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ

እንለምናለን" በማለት የማስታረቅ አገልግሎት ለቅዱሳን ሐዋርያት ለቤተ ክርስቲያን አበው የተሰጠ መኾኑን ትክክለኛውን ትምህርት ያስተማረው። እግዚአብሔር ቢፈቅድ ሌሎችም በተጠራጣሪዎች የሚነሱ ጥቅሶችንም ወደፊት ተንትነን እናያለን።

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

ነገረ ክርስቶስ ከሚለው መጽሐፌ የተወሰደ

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የቀናውን እውነት የኾነውን የሐዋርያትን ትምህርት ሳትበርዝ ሳትከልስ ሳትቈራርጥ ያስተማረችውን በደምህ የመሠረትካትን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንን ጠብቅልን።

Miko ZE Ethiopia

እነሆ ዛሬ አንድ ታላቅ መልዕክትን ላካፍላችሁ ወደድሁ። የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ለጢሞቴዎስ የጻፈው በ 2 ኛው መልዕክቱ ምዕራፍ 3 ን ባነበብኩ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ዘመን ያለውን ነገር አይቶና ተረድቶ በሚገባ የጻፈልን እንደሆነ እረዳለው

67- የዘመናችንን ፕሮቴስታንት የገለጸበት መንገድ ይደንቀኛል

- አሳቾች ቢበዙም በእውነተኛይቱና በቀደመችው መንገድ ጸንተን እንድንኖር ይመክረናል

- ስለ ቅዱሳን መጻሕፍት ጥቅምና አስፈላጊነት በአጭርና ግልጽ በሆነ

መንገድ ይገልጻል

እንግዲህ ምን እንላለን ቃሉን ለማብራራት መሞከር ራሱ ማበላሸት ይመስለኛል ቅዱስ ጳውሎስ በግሩም ሁኔታ፤ በጣፋጭ ቃላት፤ ደግሞም በጥበብና በአጭሩ ሁሉን ገልጾታልና ሙሉውን ምዕራፍ እነሆ እናንተ ደግሞ አንብቡትና የተረዳችሁትን ጻፉልን፡-

2 ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3

1 ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ።

2 ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥

3 ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥

4 ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤

5 የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ።

6-7 ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ፥ ኃጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞትም የሚወሰዱትን ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ፥ ከእነዚህ ዘንድ ናቸውና።

8 ኢያኔስና ኢያንበሪስም ሙሴን እንደ ተቃወሙት፥ እንዲሁ እነዚህ ደግሞ አእምሮአቸው የጠፋባቸው ስለ እምነትም የተጣሉ ሰዎች ሆነው፥ እውነትን ይቃወማሉ።

9 ዳሩ ግን የእነዚያ ሞኝነት ደግሞ ግልጥ እንደ ሆነ፥ ሞኝነታቸው ለሁሉ ይገለጣልና ከፊት ይልቅ አይቀናላቸውም።

10 አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግሥቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ፤

11 በአንጾኪያና በኢቆንዮን በልስጥራንም የሆነብኝን የታገሥሁትንም ስደት ታውቃለህ፤ ጌታም ከሁሉ አዳነኝ።

12 በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።

13 ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች፥ እያሳቱና እየሳቱ፥ በክፉት እየባሱ ይሄዳሉ።

14 አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤

15 ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል።

16-17 የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።

በቀደመችው መንገድ በተዋህዶ ጸንተን እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!!!

Miko ZE Ethiopia

ተከታታይ ትምህርት (ክፍል 3)

68/ የፕሮቴስታንት አመለካከት በጥምቀት ላይ

ጥምቀት በፕሮቴስታንት ዘንድ አንድ ሰው በእግዚአብሔር ለማመኑ ምልክት ነው ማለትም የሚዳነው በጥምቀቱ ሳይሆን በማመኑ ነው ለማመኑ ምልክት ይሆነው ዘንድ ተጠመቀ ይላሉ ። ጌታ በ 30 ዓመቱ ነውና ሰው አድጎ ሃይማኖቱን አውቆ መጠመቅ አለበት ይላሉ።

የኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ጥምቀት የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን በር መግቢያ መሆኑን ትገልጻለች። መጽሐፍ ቅዱስም በዮሐ.3÷5 " እውነት እውነት እላችኋለሁ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለዳችሁ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት አትችሉም" ይላል። ብዙ ጊዜ ፕሮቴስታንቶች ለዚህ እንደ ማረጋገጫ የሚሰጡት " ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" ይላል በ ማር.16÷16 ስለዚህም ፍርድ የሚያመጣበት አለማመኑ እንጂ አለመጠመቁ አይደለም ይላል። ነገር ግን የዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚነግረን አምኖ የመጠመቅን ምሥጢር እንጂ ጥምቀት አያስፈልግም ወይም ወሳኝ አይደለም አያሰኝም ይህ ቃል ይበልጡኑ ልንረዳ የሚገባው ወደ አላመኑትና ገና ቃሉ ወዳልደረሰቻው ነው ይኽም ሐዋርያት ለማስተማር ስለሚጓዙ የተሰጣቸው መመሪያ ነው። ዓለም አላመነም ነበርና ለዚህም ነው ከፍ ብለን ከቁጥር 13 ጀምሮ ስናነብ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያለው። ይህም ዓለም ያመነ ስላልነበረ ቀድሞ ማመን ስለሚገባው እንጂ ጥምቀትን ዋጋ ቢስ የሚያደርግ አይደለም። ያለ ጥምቀት ልጅነት የለምና። ሌላው ከዚህ ጥቅስ ጋር በተያያዘ

የ 40 ቀንና የ 80 ቀን ጥምቀት አያስፈልግም ሰው ካወቀና በእድሜው ከበሰለ በኋላ መጠመቅ ይኖርበታል ይላሉ በእርግጥ አምላካችን በ 30 ዓመቱ ተጠምቋል ይህም ምክንያቶች ነበሩት " ጽድቅን እፈጽም ዘንድ ይገባኛል። " እንዳለ በ 30 ዓመቱ የተጠመቀባቸው ምክንያቶች እንደ ቤተክርስቲያናችን ትምህርት

የአዳምን ልጅነት ለመመለስ፣

ሊቀ ካህናት ተብሎ ሊሾም የሚችለው በዚህ እድሜ ስለሆነ፣

ለመልካም ሥራ ሁሉ ስትነሱ በዚህ ዕድሜ ማስተዋል ታገኛላችሁ ለማለት ነው።

በሐዋ.16÷31-34 ....." ..... እርሱና ቤተሰቦቹ ተጠመቁ" ይላል። ቤተሰብ ሲባል ከትልቅ አንስቶ እስከ ትንሽ ያሉትን ሕፃናትን በሙሉ የያዘ ነው ስለዚህም ሕፃናት አይጠመቁም የሚያሰኝ አይደለም። ሐዋ. 16÷15 ላይ ያለው የሊዲያ ታሪክ ይህንኑ ያሳያል።

የ 40 ቀንና የ 80 ቀን ጥምቀት ከየት መጣ

ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ሲሆን ጥምቀት " ዳግም ልደት " ነው። ጥምቀቱ የሞትና የትንሣኤ ምልክት ነው። ወደ ማጥመቂያው ውስጥ ሲነከር ወደ መቃብር ከጌታ ጋር መውረድ ፣ ወደ ላይ ብቅ ሲል ከክርስቶስ ጋር መነሣቱ ምሳሌ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠንን መረጃ እንመልከት " ..... ወይም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እነሆን ዘንድ በጥምቀት ከእረሱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት

ከእርሱ ጋር ተቀበርን" ሮሜ.6÷3-4.

ለሕፃናት በሚደረግ ጥምቀት መጽሐፍ ቅዱስ አይቃወምም እንደውም ይደግፋል እንጂ። ለዚሁም ማረጋገጫ ጌታችን " ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው" ይላል። እንደዚህ ሕፃን የእግዚአብሔርን መንግሥት የማይቀበላት አይገባባትም ብሏል።(ማቴ.19÷14)።

ታዲያ ይህን እውነት ይዘን ስንጓዝ ወደ ብሉይ ኪዳን መለስ ብለን እናስተውለዋለን። ይህም በዘሌ.12÷1-8 ስናነብ ይህንኑ የወንድና ልጅና የሴት ልጅ ወደ እግዚአብሔር ቤት መሄድ የሚገባቸውን ጊዜ እንዲህ በማለት ገልፆታል። " ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅ ብትወልድ 7 ቀን ያህል የረከሰች ናት። በ 8ኛው ቀን ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ ከደምዋም እስክትነፃ 33 ቀን ትቀመጥ " ይላል 7 + 33 = 40 ለወንድ ልጅ የሚደረገው ይህ ነው ብሏል። ቀጥሎም " ለሴት ልጅ ደግሞ ሴት ብታረግዝ ሴት ልጅ ብትወልድ ሁለት ሳምንት የረከሰች ናት ከደምዋም እስክትነፃ ድረስ 66 ቀን ትቀመጥ " ይላል 14 + 66 =80 ይሆናል። ነገር ግን በአጋጣሚ ከ 40 ቀን በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ቢያልፍ በሌላ ጊዜ መጠመቅ አይችልም ማለት አይደለም ከዛም ቀን በፊት ልጁ ችግር ቢደርስበት ከዛ ቀደም ብሎ በሞግዚት ሄዶ መጠመቅ እንደሚችል ፍትሐ ነገሥት ያዛል።

እጅግ ልናስተውለው የሚገባው ደግሞ አምላካችን ይህንኑ ሥርዐት መፈፀሙ ነው። ሉቃ. 2÷22-24 "21፤ሊገርዙትም፡ስምንት፡ቀን፡በሞላ፡ ጊዜ፥በማሕፀን፡ሳይረገዝ፡በመልአኩ፡እንደ፡ተባለ፥ስሙ፡ ኢየሱስ፡ተብሎ፡ተጠራ። 22-24፤እንደ፡ሙሴም፡ሕግ፡የመንጻታቸው፡ወራት፡በ

ተፈጸመ፣ጊዜ፣በጌታ፣ሕግ፦የእናቱን፣ማሕፀን፣የሚከፍ

ት፣ወንድ፣ኹሉ፣ለጌታ፣የተቀደሰ፣ይባላል፣ተብሎ፣እንደ፣ተጻፈ፣በጌታ፣ፊት፣

ሊያቆሙት፣በጌታም፣ሕግ።ኹለት፣ዋሊያ፣ወይም፣ኹለት፣የርግብ፣ጫጨቶች፣

እንደ፣ተባለ

፣መሥዋዕት፣ሊያቀርቡ፣ወደ፣ኢየሩሳሌም፣ወሰዱት።"...

.....ስለ ጥምቀት .ይቆየን (ይቀጥላል).

በቀጣይ

1. የአጠማመቅ ሥርዐታችንና ፍቺው
2. በጥምቀት የምናገኛቸው ነገሮች
3. ሕፃኑ ከመነከሩ የሚፈጸሙ
4. በጥምቀት ላይ የሚነሱ የፕሮቴስታንት ጥያቄዎች

Miko ZE Ethiopia

POSTED BY MICHAEL ABEBE

69/ ላያቸው ተዋህዶ ፤ ውስጣቸው ተሐድሶ የሆኑ መጻህፍት

ባሳለፍነው ዓመት በወርሀ ግንቦት የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ላይ አንድ ወሳኝ ውሳኔ መወሰኑን ይታወቃል ፤ በውሳኔውም በርካቶች የተወገዙበት ቀሪዎቹ ደግሞ መዝገባቸው በይደር እንደቆየ የምናስታውሰው ነው ፤ በጊዜው በፕሮቴስታንቶች እየተደገፉ የቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ

ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነት፣ ክርስቲያናዊ ትውፊትና ታሪክ በጎቡእና በገሃድ ተደራጅተው ለማፍረስና ለማፋለስ እየተንቀሳቀሱ ድርጅቶች ፍጹም ውግዘት የሚገባቸውን የፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ እንቅስቃሴ አራማጅ ማኅበራትና ግለሰቦች በመለየት ማኅበረ ሰላማ፣ ማኅበረ በኩር፣ የምሥራች አገልግሎት፣ አንቀጸ ብርሃን፣ የቅድስት ልደታ ለማርያም መንፈሳዊ ማኅበር፣ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ተሐድሶ ጎብረት፣ አሸናፊ መኰንን፣ አግዛቸው ተፈራ፣ ጽጌ ስጦታው እና ግርማ በቀለ የመሰሉት ሰዎችና ላያቸው ማር የተቀቡ ውስጣቸው ግን ነጣቂ የሆኑ ተቋማት ተለይተው መለየታቸው ይታወቃል።

በጊዜው የተወገዙት ሰባቱ ድርጅቶች ውስጥ ከሣቴ ብርሃን ፤ ማኅበረ ሰላማ ፤ የምሥራች አገልግሎት ፤ የቅድስት ልደታ ለማርያም መንፈሳዊ ማኅበር ፤ አንቀጸ ብርሃን (ከድርጅቱ ጋራ አሸናፊ መኰንንና ዳንኤል ተሾመ) ፤ የእውነት ቃል አገልግሎት ፤ ማኅበር በኩርና የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ተሐድሶ ጎብረት ይገኙበታል ። ከእነዚህ በተጨማሪ ከተወገዙት 16 ሰዎች የክህነትና የክብር ማዕርጋቸው ተሽሮ የበፊቱ አቶ የሚለው ስም ከተመለሰላቸው ውስጥ በግንባር ቀደምነት አቶ አሸናፊ መኰንን ይገኝበታል።

ይህ ሰው ለዘመናት ኦርቶዶክሳዊ በመምሰል የእኛ ያልሆነ ትምህርት ኑፋቄ የተቀላቀለበት መጽሃፍቶችን በመጻፍ በርካታ ብሮችን መሰብሰብ ከመቻሉም በተጨማሪ ምንፍቅናውን በበርካታ መጽሃፍቶች መዝራት ችሏል ፤ አሁን ግን ይህ ሰው ስራው ታውቆበት ከቤተክርስትያን ከተባረረም በኋላ የመጽሀፍት ነጋዴዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ መጽሀፍቶቹ ከትክክለኛ

መጽሀፋቶች ጋር በመደባለቅ በገበያ ላይ ይዘዋቸው ይገኛሉ ፤ ስለዚህ ምዕመናን የዚህን ሰው ትምህርት እና መንገድ ቤተክርስትያን ስላወገዘች መጽሀፋቶቹን እና ትምህርቱን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከመጠቀም ወደ ኋላ እንዲሉ “አንድ አድርገን” መልዕክቷን ታተላልፋለች። ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ መጽሀፎቹን ላያቸው ተዋህዶ ፤ ውስጣቸው ተሐድሶ የሆኑ መጻህፍት የፊት ሽፋን በመውሰድ በቀላሉ መለየት እንድትችሉ በዚህ መልክ አቅርበንላችኋል።”የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።” የማቴዎስ ወንጌል 7፤15

እነዚህ ሁሉ መጻህፍት በአቶ አሸናፊ የተጻፉ ናቸው ፤ ስለዚህ የምንሰማው ስብከት እና የምናነባቸው መንፈሳዊ መጻህፍት የእነማን እንደሆኑ ለይተን ማወቅ መቻል አለብን ።

እነዚህ በጣም ጥቂቶች ናቸው..ሌሎቹን በሌላ ጊዜ እናቀርባለን

Miko ZE Ethiopia

70/ የፕሮቴስታንት አመለካከት በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ

ፕሮቴስታንት (ጴንጤዎች) በተለይ በራዕይ 22÷18-19 በዚህ የትንቢት መጽሐፍ የጨመረ የቀነሰ ማንም ቢኖር በዚህ መጽሐፍ ያሉት መርገሞች

ይደርሱበታል ይላልና ሌላ መጽሐፍ የለም ይላሉ። ይህ ቃል ግን ራእይ ዮሐንስን የሚወክል እንጂ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን አይደለም። ምክንያቱም መጽሐፍቶቹ በሙሉ የተፃፉት በተለያየ ቦታ ነበር በአንድ ላይ አሰባስበው በአሁኑ መልክ ያደረጉት 318ቱ ሊቃውንት ናቸው። እነዚህ በየቦታው ከተጻፉት አንዱ ደግሞ ራእይ ዮሐንስ ነው። ይህም በፍጥሞ ደሴት ላይ ነበር። እነዚሁ ሊቃውንት ያሰባሰቧቸውን መጻሕፍት በአንድ ሲያደርጓቸው ራእይ በአፃፃፉ ከ95 እስከ 100 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በመጻፉ በመጨረሻ ላይ አደረጉት።ምክንያቱም ሌሎቹ ከዚህ በፊት ቀድመው የተጻፉ ስለነበሩ። ያለው እቅነት ይህ ነው። ቃሉንም ብናይ በዚህ ትንቢት መጽሐፍ አለ እንጂ በወንጌል መልዕክታት አላለም። ወንጌል ትንቢት አይደለም ማለት የተፈፀመ ነው በብዙ የተገለጸበት። ታዲያ እውነቱ ይህ ከሆነ እንዴት ሁሉን ሊወክል ይችላል።ይህማ ባይሆን ኖሮ በዚህ መጽሐፍ ያልተፃፈ ሌላ አለ ባላልን ነበር ዮሐ.20÷31 ፣ 21÷25 ስለዚህም ሌሎቹ መጻሕፍት ከጌታ ጋር የሚያጣሉ አይደሉም ። ጳውሎስ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ብሎ የተናገረው ለዚህ ነው። 2ጢሞ.3÷16። ምክንያቱም እዚሁ ወንጌል ላይ ሌላ ያልተጻፈ አለ ብሎ እንደገና ደግሞ ራዕዩ ላይ የለም ካለ በጣም ይቃረናል። ስለዚህ አሁን ማንን ልንወቅስ ልንኮንን ነው። ዮሐንስን እንዳንል በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ እንደጻፈው ገልጸል። ራእይ 1÷9 ታዲያ እኛ ወይስ ፕሮቴስታንቶቹ የተሳሳትነው? ነገር ግን እኛ አይደለንም እነርሱ እንጂ። ማስተዋል ከኃጢያት መራቅ ነውና እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው። ኢዮ.28÷28። በፕሮቴስታንት አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ እንደፈለገው መተርጎም ይችላል

ለዚህም ነው ዛሬ እጅግ ተከፋፍለውና ተበራክተው የምናገኛቸው ።

በኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ማንም እንደፈለገው ሊተረጉም አልተፈቀደም ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን " ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" 2 ኛጴጥ.1÷21 ይለናል። መጽሐፍትን እንደፈለጉ እንደ ራስ ሀሳብ መተርጎም መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ይቃወማል። በእምነት አባቶቻችንን እንድንመስል መጽሐፍ ያስተምረናልና። ዕብ.13÷7.....ይቆየን (ይቀጥላል)

Wogderes Fikre

71/ እናት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለተሐድሶ መናፍቃን መልስ መስጠት ቀጥላለች።

ትናንት ምሽት ጥቅምት 3/ 2008 በደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ለተሐድሶ መናፍቃን መልስ ለመስጠት በተዘጋጀው ልዩ ጉባኤ ላይ በሁለት ክፍል ተከፍሎ በሁለት ታላላቅ መምህራን ግቡን በመታ መልኩ የተከናወነው የዚሁ ምላሽ የመስጠት አካል ነው።

በጉባዔው ላይ የተሐድሶ ክህደት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትክክለኛ አስተምህሮ

ተገልጦበታል።የመጀመሪያውን ክፍል ት/ት ያስተማሩት የሕግ ባለሙያው መምህር አስቻለው ከበደ ነበሩ።

የሁለተኛውን ከፍለ ጊዜ ያስተማሩት ደግሞ መምህር ምህረተአብ አሰፋ ናቸው። ሀለቱም መምህራን ያሉትን ልዩነቶች አሳይተዋል።

በተለይ መምህር ምህረተአብ በእመቤታችን ላይ ያለውን ክህደት ልቅም አድርገው ምላሽ ሰጥተውበታል።

መምህሩ ትምህርታቸውን ሲጀምሩ ለየት ያለ ምናባዊ ምሳሌ በመመል ነው። "የምድር 3/4 (ሶስት አራረኛ) የሚሆን ትልቅ አዳራሽ ነው።በዚህ አዳራሽ ሎሲፈር የሚመራው ስብሰባ ተካሄደ። የስብሰባው ዋና አጀንዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን እንዴት ማጥፋት እንችላለን የሚል ነው።" እንደ መምህሩ ምስሌ ልዩ ልዩ አስተያየቶች ተሰጡ።ከሁሉም ግን ተመራጭ የሆነው መጨረሻ ላይ የተሰጠው አስተያየ ነው፤ እርሱም "መፅሐፍ ቅዱሳቸን ይዘን እነርሱን መስለን ከውስጥ በመሆን እያጣመምን በመተርጎም ማጥፋት እንችላለን።" የሚለው ሀሳብ ነው" በማለት ተሐድሶ ከውስጥ ሆኖ የቤተክርስቲያኒቱን እስተምህሮ በመበረዝ ተዋህዶን ለማጥፋት የሚያደርጉትን ድካም አስገንዝበዋል። ተሐድሶዎች ምንፍቅናን ከሚዘሩበት አንዱ የእመቤታችን ነገር ነው። በመሆኑም መምህር ምህረተአብ ትኩረት በማድረግ በደንብ አድርገው በማያዳግም ሁኔታ መልስ ሰጥተዋል። ተሐድሶዎች አሉ መምህር ምህረተአብ "ተሐድሶዎች ክብር ይግባትና እመቤታችን ወላዲተ አምላክ መባል አይገባትም ይላሉ። ይህንን በልዩ ልዩ መልክ ግልፀውታል በዋናነት ግን በመፅሐፍ መልክ አሳትመውታል "መጋቤ ጥበብ" ሰለሞን ነኝ ያለ ሰው "በውኑ በማሪያም ማመን ይገባልን"

ብሎ መፅሐፍ ፅፏል"። ይህ ከሀዲ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ወላዲተ አምላክ መባል እንደማይገባት በግልጽ መፃፉን ለማህበረ ምእመናኑ ተናግረዋል። ነገር ግን የእኛ ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ድንግል ማርያም ደግሞ ወላዲተ አምላክ ብለን እንደምናምን በርካታ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ በመስጠት የቤተክርስቲያናችንን አስተምህሮ እና የተሐድሶ መናፍቃንን የለየለት ምንፍቅና ተናግረዋል።

ይህንን ምንፍቅና ከየት አምጥተው እንደሚያቀረቡ ምንጩን፣ መን ሻ ጊዜዉን፣የክህደቱንም የመጀመሪያ አቀንቃኝ ጨምሮ ፍንትው አድርገው እውነቱን ገልፀውታል። መምህር እግዚአብሔር ይስጥልን።

እመቤታችንን የማያከብር ሰው አየሲስ ክርስቶስን አላከበረም ማለት ነው።እርሷን ወላዲት አምላክ መባል አይገባትም ካልን የወለደችው አምላክ አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ያደርሰናል ይህም መፅሐፍ ቅዱሱን መቃረን ስለሚሆን ግልፅ ክህደት ነው።ስለዚህ እርሱን እምላክ ካልን እርሷ ወልዳዋለችና ወላዲተ አምላክ ማለት ይኖርብናል፤ ማለት ስላለብን ሳይሆን በእውነትም ስለሆነች ነው።

የዛሬን አያድርገውና አሉ መምህር ምህረተአብ "የዛሬን አያድርገውና እነ መርጌታ እንትና እኮ በስሚ ለምነው አኮፋዳቸውን ሞልተዋል" አሉ

እውንነት ነው እነዚህ አሁን አታማልድም ምናምን የሚሉት እኮ በስሚ ለምነው አኮፋዳቸውን ሞልተዋል ስሚ ጠርተው ለምነው ተምረው ከሰው እኩል ሆነዋል። ዛሬ ግን ዛሬ ግን.....ይሁን ብቻ

መምህሩ ስለ እመቤታችን አማላጅነት፣በድህነታችን ውስጥ ያላትን ሚና፣ክብሯን ሁሉ ፍንትው አድርገው በጉልህ አሳይተዋል።

በእመቤታችን በኩል በተሐድሶ መናፍቃን ተነስቶ የነበረው ክህደት እዚሁ ጋር ዘግተዉታል። ተሐድሶ አሁን አንድ ክንፉ ተሰብሯል ማለት ነው። መምህር ምህረተአብ ትምህርቱን ሲጨርሱ እንደተለመደው በዝማሬም አገልግለውናል።እነ ዘማሪ ልዑልሰገድ ዘማሪ ኤርሚያስ ሌሎችም ተገኝተው ነበር።

ይኸው ጉባኤ በቀጣይ ረቡዕ በተመሳሳይ ቦታና ሰዓት ይቀጥላል ልዩ የድምፅ ማስረጃ እንዲያውም ከተቻለ የምስል ማስረጃ ይዘው እንደሚቀርቡ መምህር ምህረተአብ ቃል ገብተዋል። ልዩ ልዩ ዘማርያን እነ ቀሲስ ምንዳዬ ብርሃኑ፣ እነ ሊቀ መዘምራን ዲ.ን ቴዎድስ የሴፍ እና ሌሎችም ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

Like · Deacon Moges Asmare

jegnoch memhran bewnet rezhm edman ystachwu elalehu kale hywot yasemalen emebrhan titebkachw bertulen

Like . Degualem Semagn

ቤተ ክርስቲን ሆይ ምነው ተረበሽ፣አንድነትሽ ጠፍቶ ሰላምን አጣሽ።አንደኛው ሲጠቅምሽ ሌላኛውሲጎዳሽ፣ብዙ ልጆች ወልደሽ የወላድ መካን ሆንሽ።

Like · Mazadasale Dasale

Egziabeher ewnetun yawetawal lesu ymesanew yelem menafekan hulum gudu yewetaaaaaaaal wendemachen kalehiwet

yasemalen amen

Dani EL Getachew

Abayneh Kassie

72/ የግብር ስማቸው "ሀራጥቃ ተሐድሶ" ነው

በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ የኾነ አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን የመዋጋት እንቅስቃሴ በየአካባቢው እየተካሄደ ነው። ከሀገር ቤት እስከ ምድረ አሜሪካ እየተካሄደ ያለው እንቅስቃሴ ሠናይ ነው። በዚሁ ከቀጠለ ያማረ ውጤት ላይ መድረሳችን አይቀርም። ቀኑም ሩቅ አይኾንም።

እየተቀጣጠለ ያለው ስሜት ለራሳቸው አስፈሪ ኾኖባቸዋል። ግርማችን አስፈሪነታችን ይህ አንድነታችን ነውና። ከፊታችን ለመቆም ወደማይችሉበት ደረጃ እስክናደርሳቸው ድረስ እረፍት ጠይቀን ልንወጣ አይገባም። አሁን በጭንቀት በረት ውስጥ ገብተዋል። መግቢያ መውጫቸው ሁሉ ታጥሮባቸዋል። ግን ስሁታን ናቸውና በዚህም መካከል ስሁት ሰብእናቸው መታየቱ አይቀርም። በዚሁ ስንቀጥል ደግሞ ጠራርገን ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ማስወጣት እንደምንችል በኃያሉ እግዚአብሔር ተስፋ እናደርጋለን።

ልዩነት ያለን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ ጥቃቅኑን ልዩነት ትተን አንድነታችንን አጠንክረን መሄድ ይጠበቅብናል። ለታላቁ ዓላማ ሲባል ጥቃቅኑ ልዩነቶች መሥዋዕት ሊደረጉ ይገባል። እገሌ ይተው ከማለት ስለቤተ ክርስቲያኔ ስል እኔ ትቸዋለሁ እንበል። ትግሉ ከዚህ ይጀምራል።

እጅ ለእጅ ተያይዘን ያለብንን መንፈሳዊ እና ታሪካዊ አደራ እንወጣ።

ሌላው ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ እና መሠረታዊ ለውጥ ልናደርግበት የሚገባው ለሀራጥቃ ተሐድሶ የተሰጠው ስያሜ ነው። በተለምዶ "ተሐድሶ" በሚል መጠሪያ እንጠራቸዋለን። ይህንን ስያሜ የመረጡት እራሳቸው ናቸው። ነገር ግን "ተሐድሶ" የሚለው ቃል በቁሙ አዎንታዊ ትርጉም ያለው ነው። ሃይማኖታዊ ተሐድሶን እንቃወማለን እንጂ አስተዳደራዊ ተሐድሶን አንቃወምም። ስለዚህ ለቃሉ ሁነኛ ቅጽል ልናበጅለት ይገባል። በጭራሽ ለእነርሱ አይመጥንም። "ተሐድሶ" ብለን ከእነርሱ ተቀብለን ማስተጋባት የለብንም።

እነርሱ ሊጠሩ በፈለጉበት መንገድ "ተሐድሶ" እያሉ መጥራት ለእነርሱ ድል ሲኾን ለእኛ ደግሞ ሽንፈት ነው። ትምህርታቸው የመናፍቅ ነው። መናፍቃን በቤተ ክርስቲያናችን ከሚጠሩባቸው የወል ስሞች አንዱ ሀራጥቃ የሚለው ነው። በአፍርንጅ ቃል "heretics" እንዲሉ። በጅምላ ሀራጥቃ ብለን ከጠራናቸው የትኞቹ የሚለው ጥያቄ ሳይመለስ ሊቀር ነው። ለእርሱ ሲባል ደግሞ "ሀራጥቃ ተሐድሶ" ብንላቸው የተመቸ ነው። ይህም ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ለሚለው የቀረበ አጠራር ነው።

ፕሮቴስታንት የሚለው ቃል አማርኛ ወይንም ግእዝ ባለመኾኑ እንጂ በትርጉም ደረጃ አያስሄድም ማለት አይቻልም። ሀራጥቃ የሚለው ግን

የለየላቸው መናፍቃንን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስትጠራበት የኖረ አሁን አሁን ግን እየተረሳ የመጣ ቃል ከመኾኑ በስተቀር ገላጭነቱ አያሻማም። እናም በግብር ስማቸው "ሀራጥቃ ተሐድሶ" እያልን ልንጠራቸው ይገባል። ጸሐፊያንም፣ ተናጋሪዎችም፣ መምህራንም፣ ማኅበራትም፣ ሰንበት ትምህርት ቤቶችም፣ አበውም የተሻለ አማራጭ እስኪመጣ ድረስ ቢጠቀሙበት ሠናይ ነው እላለሁ። ቃሉን ማስተዋወቅም ይጠበቅብናል። ላልሰሙትም በማካፈል ጉዳዩን የጋራ አድርገነው ለውጥ እናመጣ ዘንድ አደራ እላለሁ። እኔም በማይገባቸው ላልጠራቸው በሚገልጣቸው ልጠራቸው ከእንግዲህ ቃሉን ለመጠቀም ወስኛለሁ። እርስዎስ?

Like . Tewodros Adugna

አውነት ነው ሀራጥቃ ተሀድሶ!

Like ·Yared Gebrehiwot

dani mn yemsel gubaye behertsege mariyam tilant be diyakon begashew tekehedwal zarem yeketelal kechalk beke bel

Like · Tafete Gedamu Abera

እጅለእጅ ተያይዘን ሙስናን እንከላከል ቢሉ ያምር ነበር

Like · Aman Mengesha Ayele

ሀራጥቃ ተሀድሶ

የለየላቸው መናፍቃን

Like · Andebet Dessiew

እኔም ወስኛለሁ።

ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

<u>ይገርማል ሠው ግን እንዴት ሰውን ለማታለል እሄን ያህል ጉርጓድ ይምሣል??</u>

ዛሬ አዲሥ የተከፈተ Zemedkun Bekele የሚል አካውንት የድሮው የመምህር ዘመድኩን መሥሎኝ አድ አድርጌ ነበር ግን ከጥቂት ሠአታት በኋላ ሥሙ ከመቅፅት ግሪሣው ነኝ በሚል ተለወጠ ከዛም የምናቀውን የቤተክርሥትያን ትምህርት ሣይሆን የአዳራሽ ኑፋቄን መዝራት ጀመረ...!! ወገን ነቃ ልንል ይገባል ሠይጣን በብዙ መልኩ እናት ቤተክርሥትያናችንን ለማናወጥ እኛ መሀል ይገባል አላማውም በኛ መሀል ፀብንና ጥላቻን በመጣል እናት ቤተክርሥያናችንን ማደሥ ነው የኛ ቤተክርሥትያን ደሞ እኛን የምታድሥ እንጂ እሷ የምትታደሥ አይደለችምና እኛን መሥለው በኛ መሀል ፀብንና ጥላቻን ከሚጥሉ ነጣቂ ተኩላዎች ልንጠበቅ ይገባል ።

እግዚአብሄር ቤተክርሥትያናችንን ይጠብቅልን አሜን

።።። እናት ቤተ ክርሥትያን አትታደሥም ።።።

Matiwos Amare Tewahido

<u>*73/* በተሃድሶ መናፍቃን(ሀራ ጥቃዎች) ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ታላቅ</u>

ጉባኤ በአዲሱ ሚካኤል ቤ/ክ ተካሄደ!!

ይኸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ጉባኤ ሳምንት ዕሮብ የሚቀጥል ሲሆን በዚህ ጉባኤ ሀራጥቃዎች ወደ እናት ቤ/ክ እንዲመለሱ ጥሪ ቀርቦላቸዋል። ሀራ ጥቃዎች ከሚዘሩት እንክርዳድ አንዱ የሆነው "ማርያም ወላዲተ አምላክ አትባልም" የሚለው ትምህርታቸውና በመጽሃፍም ካሳተሙት ከተወሰደው ላይ ሰፊ ትምህርት የተሰጠ ሲሆን የማርያምን የአምላክ እናትነትን ያረጋገጠ መልሶች የቀረቡበት ነበር ከዚህም ጋር የተነሳውና እውነትነት ያለው ነገር ቢኖር ማርያም የአምላክ እናት አይደለችም፣ የሚሉ የተወለደው አምላክ አይደለም ብለው ኢየሱስን እንደመካድ ነው ስለዚህም፣"ኢየሱስን የማያውቅ ማርያምን አይረዳትም" የሚለው ሃይለ ቃል ሁሉንም የገዛ ታላቅ ቃል ነው። ይህ የእንክርዳድ ዘር አስቀድሞ በ 428 የተነሳው የንስጥሮስ ሲሆን ማርያም የሰዋዊው ኢየሱስ እናት ብቻ ነች የሚለውን የሁለት አይነት ኢየሱስ ትምህርት ከንቱነት ያጋለጠ ነበር። ጉባኤው "ማርያም ማርያም እንበል" "ተዋህዶ ሃይማኖቴ የጥንት ነሽ የእናትና አባቴ ማህተቤን አልበጥስም " የሚለው መዝሙር ከተዘመረ ብኋላ ዘማሪ ልዑል ሰገድ "ቋንቋዬ ነሽ ድንግል" የሚለውን መዝሙር ካቀረበ ብኋላ ጉባኤው በጸሎት ተፈጽሟል።ሳምንት ሌሎች የሚዘሩ እንክርዳዶች ከማስረጃዎቻቸው ጋር ይቀርባሉ።

እግዚአብሄር የዛ ሰው ይበለን!!

ወስብሃት ለእግዚአብሄር!

Like . በእግዚአብሔር የተወደደ ምስጋና

አሜንን ! ማርያም እማምላክ አይደለችም ማለት ፦ በቀጥታ የጌታችንን

የኢየሱስን አምላክነት መካድ ነው ።

እግዚኦ ይቅር በላቸው

Report · Wednesday at 8:03pm

ጥላና አካል

አሁን አሁንስ ፖለቲካ አደረጋችሁት። ስለ እግዚአብሔር ቃል መስበክ ትቶ ይሄ ሺህ ጊዜ በጋሻው ትዝታው ሲሉ መዋል፣ ሲዲ ላይ አንዲት ቃል ቆርጦ መክሰስ መሰለል የአለማውያን ተግባር ነው። ደግሞ እመቤታችን የእየሱስ እናት አይደለችም የሚል ተሃድሶም ሆነ ጴንጤ የለም። ለምን ይዋሻል። ልዩነቱ የምልጃና የስግደት ጉዳይ

ብቻ ነው ። ሁሌ ስለሰው የሚያወሩ ሰወች ተበለጥን ብለው የሚቀኑ ሰዎች ብቻ ናቸው። አንተና ዘመድኩንም የሆነ የአንድ አምባገነን ቡድን ሰላይ እልፍኝ አስከልካይ እንጅ መንፈሳዊ ሰው አትመስሉኝም። መመዘኛውንም አታሟሉም። ለምሳሌ ዛሬ ውይይት ከተደረገ በምስል ደግፈህ አቅርብልን። ከዚህ ውጭ ግን የምታደርጉት ግብግብ ለራሳችሁ ክብር እንጂ ለቤተክርስቲያን አይመስለኝም።

Like . Engidashet Kebede

ጥላና አካል# እስቲ ጥራት በአንደበትክ እንድትከብር ከአይንክ ላይ ቅርፊቱ እንዲነሳልክ የአምላኬ እናት የፈጣሪዬ እናት ብለክ

Like . Ermias Abiy

ሀይማኖት ማለት የፈጣሪን ህግ ጠብቆና ይዞ መገኘት ነው እንጂ ይህ ቃል አልተመቸኝም ይቀየር እደዘመኑ ይታደስ ማለት አይቻልም እደዚያማ ከሆነ ሰማእትነት የሚባለው ባልነበረ ነበር ቤተክ/ን የምትመራበትኮ የራሷ

ከአባቶቻችን የተቀበልነው ህግና ደንብ አላት መታደሱ ለምን አስፈለገ።

Like . Danny Mare

እንኳን ከዘመነ ግሪሳ ወደ ዘመነ ሀራጥቃ በሰላም አሸጋገራችሁ

Like . KT Tsegay

ER ere inezihi menafik menew erasatewni yezew yiwtu ke betekirisitiyan lela bayaweru yisalale durom kene begasaw mini litebek kenegwdegotu ayidenikenim leworo bela e/r yisitilin wenidimatineni

በእንተ ቤተ ክርስትያን ዘሻሸመኔ

74/ እንከፋፈል ከሚለው ጭንብል ጀርባ ያለው እውነታ(Behind the mask of the presumed "decentralization")

ውድ የገጻችን ተሳታፊዎች እንደምን አደራችሁ ለዛሬ ከላይ ባነሳነው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥቂት ሃሳቦችን እናነሳለን እንደተለመደው የተሰማችሁን ጻፉልን ሃሳባችንንም ከወደዳችሁት ለሌሎች እንዲደርስ share በማድረግ አግዙን።

:::::::::::::

ቀደም ባሉ ጽሁፎቻችን በተለይ እንደ ሻሸመኔ ነባራዊ ሁኔታ በአንድ ሰበካ ጉባኤ መመራት የሚያስ ገኘውን ጥቅም ማስነበባችን ይታወሳል ነገር ግን

አንዳንድ ወገኖች "እንከፋፈል የሚል ሁሉ ተሃድሶ ነውንዴ?" የሚል ግትር ሙግት ያነሳሉ ። እኛ ይህንን አላልንም ቀድሞ ይህን የ"እንከፋፍላችሁ" ጥያቄ በጽኑ ሲቃወሙ የነበሩ አባቶቻችንም(በህዝብ የተወከሉት) ይህን አላሉም። ዋናው ጥያቄ የነበረው ቤተ ክርስትያንን ሲያምሱ የነበሩና መረጃም የተገኘባቸው የምንፍቅና አራማጆች ጉዳይ ወደ ጎን ተትቶ ይህንን ክፍፍል በቀጭን ትዕዛዝ ተግባራዊ ማድረግ የተፈለገው ለማን ታስቦ ነው። መጀመርያ በአንድ ሰበካ ጉባኤ መተዳደራችን ለብዙዎች ምሳሌ መሆኑ ቀርቶ ድንገት ስጋት ሆኖ የታየው እውነት ከሃይማኖታዊ ችግር ይልቅ አስተዳደራዊ ጉዳይ በልጦ ነውን?(ተሃድሶነት በቤተ ክርስትያን ላይ ያንዣበበ የሃይማኖት ህጸጽ ነውና) እኛ በአንድ አስተዳደር ሥር መሆናችን የሚያስገኘውን ጥቅም ዘርዝረን ባስረዳነው ልክ እነርሱም መከፋፈሉ የሚያመጣውን ትሩፋት ለምን አይነግሩንም ?

አለያም ጥናት እናደርግበት ዘንድ ለምን ግዜ አልሰጡንም?

ከዚህ ይልቅ ግዜ የማይሰጠውንና ቤተ ክርስትያንን እያመሰ ያለውን የተሃድሶ አራማጆችን ጉዳይ ቸል ማለትን ለምን መረጡ?

እውነታው ህይ ከሆነ ደግሞ ክፍፍሉ የሚያመጣውን ችግር ለማሰብ ነብይ መሆን አያስፈልግም። በዚህ ወቅት እንኳን አንዳንድ ቀንደኛ የተሃድሶ አቀንቃኞች ማልያቸውን ቀይረው የ አባቶች ተቆርቋሪ ሆነው ቀርበዋል።

ይህን ሁሉ ሃሳብ ለመጠቅለል ብንሞክር በዚህ ወቅት እንከፋፈል የሚሉ አካላት አንድም ክፍፍሉን ተከትሎ በሚመጣው አስተዳደራዊ መዋቅር ቁልፍ ቦታ እንዲያገኙ ተስፋ የተሰጣቸውና አልያም አብዛኛው ምዕመንን ስውር ዓላማቸውን ተረድቶ ያገለላቸው የተሃድሶ አራማጆች ብቻ ናቸው

"ግርግር ለቀጣፊ ይመቻል "እንዲሉ።

እግዚአብሔር ደግ ዘመን ያምጣልን።

ይቆየን!

Like . Reta Feker

ተሀድሶ ሰው ሰራሽ እና ዘመን አመጣሽ የሆነ መሪሀቻቸው በጋጥወጥ ስነ-ምግባር የተሞሉ መሆናቸው የታወቀ ና ፀሀይ ያሞቀው ነገር ነው : ኢትዩጲያናን ከአለም ለየት የሚያደርጋት ክርስትና ነው

አንድ ሰባኪ መምህር ተወዳጅ እና ተደናቂ የነበረ የሰዎች አድናቆት ከፍ ባለ ቁጥር እሱ ራሱን ስቶ የፈጠረው ተሃድሶ ፀ-በጋሻው መሆኑን እኛ ውላችንም ምናውቀው ጉዳይ ነው ከሚገርመው ነገር የተሃድሶ አምልኮት በአዋሳ በአለም ጤና

 አ.አ በናዝሬት በተለያዩ የኢትዮጲያ ክፍሎች ተከሰቶ ወጣቶች በሚያስደንቅ ትግል ቤተክርስቲያናቸውን አስከብረዋል በሻሸመኔ ያለውን የአይማኖት ነውጥ የድንግል ማርያም ልጅ ክርስቶስ ፍፃሜውን ያሳምርልን.....

Coment . Dawit Tilahun

እውነት እንጂ ሀስት የት ይደረስላ የክርስቶስ ሥራ ነው ጌታ ከንተጋራ ይሁን ።

Coment . Yehuala Hailu

እመኑኝ ተሃድሶዎች በሀይማኖት መታደስ ይቻላል።ሀይማኖትን ለማደስ መነሳት ግን ፍፁም ስህተት(ኑፋቄ) ነዉ፤ እግዚአብሄንም መሳደብ ነዉ "ስራህ ስህተት አለዉና እኛ እናስተካክልልህ" ማለት ነዉ።ልብ ይስጣችሁ!

Coment . Kenfe Pandulem

Koy ena melw yethadsa teregume mend new begashawes ewne tehadso new ?

በእንተ ቤተ ክርስትያን ዘሻሸመኔ

75/ ክፍፍሉን የምንቃወምበት ሌላኛው ምክንያት:

እንደሚታወቀው የሻሸመኔ ህዝበ ክርስትያን ሰላሙ መታወክ ከጀመረ ሰነበተ። ለዚህ ሰላም መደፍረስ በዋናነት ደግሞ የሚከተሉት አካላት በአንድም በሌላም መንገድ ተሳታፊ ናቸው:

1.የተሃድሶ መናፍቃን አራማጆች እነኚህ አካላት ቤተ ክርስትያንን ተጠግተው ከደጇ በሚፈልቅ በረከት አድገው ጎልምሰው በእርሷው ላይ ተረከዛቸውን ያነሱ የእናት ጡት ነካሾች ናቸው። እነዚህም:-

& በሥርዓቷ መኖር ሲሳናቸው ሥርዓቷን ማብጠልጠል መጀመራቸውና ልናድሳት ይገባል ማለታቸው

& ከአባቶች እግር ስር ቁጭ ብለው ሳይማሩ የአባቶችን ትምህርት መናቃቸውና ምስጢሯን ሳይረዱ ነጠላ ጥቅስ እየጠቀሱ ተነጥለው

መቅረታቸው ሲሆን ይህ ሸፍጥ ሲታወቅባቸው ደግሞ አላማቸውን ባልተረዱ አባቶች አልያም የእነርሱ ተባባሪ

በሆኑት ፊት ተወዳጅ መስለው ለመታየት መጣራቸው ነው

2. አገልግሎትን ከተራ የቢሮ ሥራ ነጥለው የማያዩና እነርሱ ኪሳቸው ካልጎደለ ቤተ ክርስትያን ብትታወክ መንጋዋም ቢበተን ግድ የማይላቸው የመንጋው እረኞች(ጥቂት አገልጋይ ካህናት) እነዚህኞቹ ደግሞ የተሃድሶዋውያን ስውር ዓላማ ወይ አልገባቸውም አልያም ለማወቅና ትምህርታቸውን ለመመርመር አይሞክሩም ከፍ ሲልም ቢያውቁትም ግድ አይሰጣቸውም ዛሬ ቤተ ክርስትያንን ያወከ አስተምህሮ ነገ በህልውናዋ ላይ የሚያስከትለው ጠባሳም አይታያቸውም።

3.ለቤተ ክርስትያን "ባይተዋር" የሆኑ ምዕመናን እነዚህኞቹ ደግሞ ለእያንዳንዱ ችግር ሁል ግዜ እንግዳ የሚሆኑና በቤተ ክርስትያን ላይ የተከሰተው ችግር እነሱን እንደማይነካ የሚያስቡ ሲሆን በዚህም ምክንያት ችግሩን ከመሰረቱ አይረዱትም ከዚህ ይልቅ በሰፊር በሚነዛ አሉባላታ ተጽዕኖ ምክንያት ልባቸው ስለሚሸረሸር ሳያውቁት የክፉች ስውር አጀንዳ መፈጸሚያ ይሆናሉ።

ሌሎችም አካላት እንዳሉ ሆኖ ከላይ የጠቀስናቸው ግን በመጀመሪው ረድፍ የሚቀመጡ ናቸው።

&& እኒህን ሃሳቦች በአዕምሯችን ይዘን አሁን ላይ የሚነሳውን የአብያተ ክርስትያናት የአስተዳደር ክፍፍል ጉዳይ እንመልከት መቼም ማነጻጸሪያ ነጥቦቻችን የሚሆኑት:-

ሀ. በአንድ አስተዳደር ስር መሆናችን ያስከተለብን ችግር(በእርግጥም

ኖረውም ከሆነ)

ለ. አብያተ ክርስትያናቱ ወደ ክፍፍል ሲገቡም እነዚህን ችግሮች የመፍታት አቅማቸው ምን ያህል እንደሚሆን

ሐ.ወደ ክፍፍሉ ስንመጣ ልናጣ የምንችላቸው የአንድነታችን ጥቅሞች በሚዛናዊነት መታየት መቻላቸው

መ. በተለይ በዚህ ወቅት ወደ ክፍፍል ስንመጣ ሊገጥሙን የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለአብነትም ያህል የተሃድሶ አራማጆችን እንዲህ በአንድነት ቆመን እንኳን ነቅሎ ለማስወጣት ይህን ያህል ፈተና ውስጥ ከገባን ነገ አንድ መናፍቅ ተነስቶ በአንድ ቤ.ክ ተቃውሞ ቢደርስበትና ወደ ሌላ ደብር ቢሄድ እዛ ድረስ ሄደን ለመቃወም የሚያስችል ተሰሚነት ማግኘት መቻላችንን

ይህ ከሆነ ደግሞ አንከፋፈልም የሚል አቋም መያዛችን ይህን ያህል ችግር የሚሆነው ለማንና በምን ምክንያት ነው? ሁላችን የምንተዳደርበት ህገ ቤተ ክርስትያን (ቃለ አዋዲ) የሰበካ ጉባኤ መቋቋሚያ አዋጅን በሚመለከት ባስቀመጠው መሰረት የተቀራረቡ አብያተ ክርስትያናት ከተስማሙ በአንድ ሰበካ ጉባኤ ሊደራጁ ይችላሉ ካለ(ቃለ አዋዲ አንቀጽ ፫) እኛ ደግሞ ለሁሉ ምሳሌ በሚሆን መስማማት ይህን ያህል ዘመን አብረን መዝለቅ ከቻልን ለያውም እጅግ ስኬታማና ዘመናዊ ከሆነ የሰበካ ጉባኤ መዋቅር ጋር(ሻሸመኔ ላይ አንድ ጀማሪ ዲ.ን በየትኛውም ደብር ቢመደብ መነሻ ደሞዙ በዲፕሎማ ደረጃ ሲሆን እንደቆየበት የሥራ ዘመንም የደሞዝ እርከን ይሰራለታል አንድ ጀማሪ ቄስም ቢሆን አሰራሩ ተመሳሳይ ሆኖ መነሻው በመጀመሪያ ድግሪ የደሞዝ እርከን ነው) ይህን ያህል የክፍፍሉ አጀንዳ አንገብጋቢ ለምን ሆነ?

ይህ በእንዲህ እንዳለ መጤን የሚገባቸውም ጉዳዮች ትኩረት ሳያገኙ እንዲሁ በግብታዊነት ተከፋፈሉ ማለት ለማንም ቢሆን ግልጽ ሊሆን አይችልም። ስለዚህም የትኛውንም ሃሳብ ለቤተ ክርስትያን ሰላምና አንድነት እስቀጠቀመ ድረስ ለመቀበል አናመነታም ነገር ግን ጥቂት ግለሰቦችን ላለማስከፋት በሚል ግን ታሪካዊ ስህተት መቼም ቢሆን አንሰራም!!!

የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የመላዕክት ጥበቃቸው የቅዱሳኑ ጸሎት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን!

ይቆየን።

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለዘለአለም ትኑር

በአዲስ አበባ ሁለተኛ በሀገር አቀፍ ሶስተኛ የሆነው ይፋዊ ጸረ ተሃድሶ ጉባኤ በቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ለተሃድሶ ሚስማማ ስም ይፋ በማድረግ ቀጠለ

<u>76/ "ሐራጥቃ" ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ ማለት ነው "</u>

በመብራት ምክንያት ከመክፈቻ ሰአቱ የዘገየው ፕሮግራም ፀሎተ ሃይማኖት እና ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ በማድረስ ተጀምሮዋል የመጀመርያው ክፍል ትምህርትም መመህረ ወንጌል እና የቤተክርስቲያኗ የህግ ባለሞያ በሆኑት በመምህር አስቻለው ተሰጥቶዋል።

"ሐራጥቃ" በቲኦሎጂ ትምህርት ፕሮቴስታንታዊ ተሃድሶ ማለት ነው።

የቤተክርስቲያኗ ሊቃውንት ይህን ስም እንድጠቀምበት ነግረውኛል" ያሉት መምህር አስቻለው " ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ" የአባቶቻችንን አምላክ እግዚአብሄር ይመስገን "በሚለው ቃል ጉባኤውን ጀምረዋል።

ይህን ጉባኤ ምናደርገው የሃይማኖት ጉዳይ ስለሆነብን ተገደን ነው ያሉት መምህሩ "ሐራጥቃዎቹ" ተመልሰው ከጉኔ አብረውኝ ቢሰብኩ ደስታዬ ነው ሲሉ ክርስቲያናዊ ቃላቸውን ሰጥተዋል።

ካልተመለሱ ግን የቤተክርስቲያኗ ጫንቃ እንሱን መቸከም አይችልም ከዚ በላይ እያነባን ከቤተክርስቲያን ልንለያቸው ግድ ነው ብለዋል።

ስለ ቅዱሳን አማላጅነት ሐራጥቃዎቹ ተሳስተዋል ብለው ማስረጃ ከመጸሃፍ ቅዱስ ፍንትው አድርገው የምእመኑን ልብ አረስርሰዋል።

ሁለተኛው ትምህርት የዘመኑ የቤተክርስቲያኗ ጠበቃ የሆኑት ለፕሮቴስታንት ለአህዛብ መልስ በመስጠት ሚታወቁት በቤተክርስቲያን ጉዳይ ማይደራደሩት መምህር ምህረተ አብ ለሐራ ጥቃዎች "ወላዲተ አምላክ "ን በተመለከተ ላነሱት ምንፍቅና የማያዳግም መልስ ሰጥተዋል።

(የመምህራችንን ትምህርት በተከታታይ ለማድረስ እሞክራለው)

መምህር ምህረተ አብ በቱፊት ከአባቶቻችን እንደወረስነው መናፍቃን ሲነሱ የንስሃ የመመለሻ ቤተክርስቲያን "አረ ሲኖዶስ የለም እንዴ " እሲኪባል ድረስ ግዜ ሰጥታለች ብለው አስረድተዋል።

ክርስትና መጀመር ሳይሆን መጨረስ ነው ያሉት መምህሩ ይሁዳ ሃዋርያ ሣጥናኤል የመላእክት አለቃ ንስጥሮስ ጳጳስ ሆነው ጀምረዋል መጨረሻቸው

አላማረም እንጂ ሲሉ ለዘመኑ ሃራጣቃዎች መንቂያ ደውል ደውለዋል።

"በእንተ ስማ ለማርያም " ብለው በስምዋ በልተው በስምዋ ተምረው በስምዋ መምህር ተብለው እመብርሃንን በመሳደብ ለወደቁ ሁሉ "ድንግል ማርያምን ማንም ሊያከብራት አይችልም ሊቀድሳት አይችልም እኛ እስዋን በማክበር እንከብር ዘንድ ነው እንጂ እግዚአብሔር አንዴ አክብሮዋታል ከሱ በላይ አናከብራትም ልናዋርዳትም አንችልም እግዚአብሔር ያከበረው ማንም አያዋርደውም ራሱ ይዋረዳል እንጂ"

ሲሉ አጽኖት ሰጥተው ተናግረዋል።

ጥልቅ የሆነ የሚስጥረ ስጋዌ ትምህርት ከነገረ ማርያም ጋር አያይዘው በስነ መለኮት ትምህርት የሶስት ሴሚስተር ትምህርት ሚሆን አስተምረዋ።

በፕሮግራሙ ቋንቋዬነሽን ጨምሮ የመምህር ምህረተ አብ ወንድም የሆኑት በሚስጥራዊው ቡድን 2 ሲዲ ምክንያት ስለ እምነታቸው በእስር ቤት የተንገላቱት መምህርና ዘማሪ ኤርሚያስ ጨምሮ ዘማርያን ተገኝተዋል።

የአራት ጉባኤ መምህር የሆኑት በማህበረ ቅዱሳን ቲቪ ከሊቃውንት ጋር መልስ በመስጠት ሚታወቁት መጋቢ ሃዲስ ሚስጥረ ሥላሴን ጨምሮ ሌሎች መምህራን በቦታው ተገኝተው ሲያመሰግኑ ሲዘምሩ አምሽተዋል

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ

Like . Teddy Assefa Yadeta

አሜን አግዚአብሔር ሃይማኖታችንን ይጠብቅልን።ተዋህዶ ሃይማኖታቺን ማንም ትዉልድ እንደ ፈለጋ የሚቀያይራት እና የሚያድሳት አይደለችም። አመሰራረቷም በጋሻውና ሐርጥቃዎች ለምርምር የሚጠቀሟት የፍልስፍና ሃይማኖት ሳቶን ቃል ከሰዉ ተዋህዶ ስጋ ሁኖ የሰዉን ልጅ ለማዳን ስጋ

የሆነው ቃል መከራን ተቀብሎ እስከ ሞት ሆነ ሞቶ ሰዉን ያዳነዉ ፍፁም በእየሱስ ክርስቶስ ደምና አጥንት የተሠሰረተች ሃይማኖት ናት።።ታዲያ በክርስቶስ እየሱስ የተመሰረተቺዉን ኦርቶዶክስ ተዋህዶን መቃወም ምነኛ እርኩሳዊነት ነዉ!እውነት ነዉ የምናገረዉ ታሃድሶ ሐርጥቃዎች ይጠፉሉ።። በጋሻዉና ተከታዮቹም በእንብርክክ የተዋህዶ ቤት ፊት ተንበርክከዉ የድንግል ማርያምን ምልጃ ይማፀናሉ።።

Like . Frehywot Mar

እኔ የምልው መላኩ ቅዱስ ገብርኤል ፀጋን የትሙላሽ ደስ ይበልሽ ካላት በክብር እኛ ምድራዊ ፍጥሩች ስልምን ልአምላክ እናት ክብር አንሰጥም ክብር እና ውዳስ ድንግል ማርያም ልስምሽ ይሁን

Like · Betelihem Jembere

እግዚአብሄር አምላክ እድሜና ጤናን ከበረከት ጋር ያድላችሁ በእምነታችሁ ያፅናችሁ የእናታችን የድንግል ማሪያም ምልጃ የቅዱሳን መላእክቱ ጥበቃ የሰማእታቱ በረከት የእግዚአብሄር አምላክ ምህረት አይለያችሁ

Miko ZE Ethiopia

77/ ምን ነካቸው የዘመኑ ሰዎች የእኛ አጀንዳ ይህ አደለም ድንግል ማርያም በየትኛውም የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል ስማ አልተነገረም ይሉናል እውነት ድንግል ማርየም በመፅሀፍ ቅዱስ አልተሰበከችም ይሆን እንመልከት

---------->

---------- ‹‹ማርያም›› የሚለው ስም ምንም በራሱ ክቡር፣ ብቁና ምሥጢረ ብዙ ቢሆንም ስሟን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቀው ሐዋርያው ሉቃስ እንኳን በተለያየ አንቀጽ ደጋግሞ ሲጠቅሳት ስሟን በሌጣ ማርያም እያለ አልጠራትም። ለምሳሌ፦ በጸራቅሊጦስ ዕለት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ለመቶ ሃያው ቤተሰብ ከመውረዱ አስቀድሞ ሁሉም በአንድነት ተሰብስበው ይጸልዩ እንደነበር ሲመሰክር የሐዋርያትን ስም አንድ በአንድ ከዘረዘረ በኋላ ‹‹እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።›› ይለናል።

የሐዋርያት ሥራን የጻፈው ቅዱስ ሉቃስ መሆኑ የታወቀ ነው። (የሐዋ 1.14) በዚህ አንቀጽ ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት አብረው የነበሩ ቢሆንም እንደ ሐዋርያት በስም አልተጠቀሱም። ‹‹ሴቶች›› ብቻ ብሎ አልፎአቸዋል። ከሴቶቹ በስም የተጠቀሰችው ድንግል ማርያም ብቻ ናት።

የሚያስደንቀው በስም መጠቀሷ ብቻ አይደለም። ቅዱስ ሉቃስ አምላክን ከመጽነሷ በፊት ‹‹የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ›› በማለት ያስተዋወቀን ቢሆንም አሁን ግን በክብረ ድንግልና ላይ ክብረ ወሊድ እንደተደረበላት ስላወቀ ‹‹የኢየሱስ እናት ማርያም›› ሲል ጠቀሳት።

ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ ነው። የኢየሱስ እናት ማለት የአምላክ እናት ማለት እንደሆነ አያከራክርም። ስለዚህ በነጠላው ‹‹ማርያም›› በማለት ፋንታ ወላዲተ አምላክ ማርያም ወይም ‹‹የኢየሱስ እናት ማርያም›› ማለትን የተማርነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

የአገራችን ትውፊትም ይህን የተከተለ ነው። አንዲት ሴት ከመጠሪያ ስሟ

በተጨማሪ ወይዘሪት እገሊት ስትባል ትኖርና ስታገባ የጋብቻ ክብር ስለሚጨመርላት ወይዘሮ እገሊት ትባላለች። ልጅ ስትወልድ ደግሞ የእገሌ/የእገሊት እናት ትባላለች። መውለድ ራሱ ታላቅ ክብር ነውና፤ ምስጋናንም ያበዛል። ዘለፋ ስለ ልያ ወንድ ልጅ በወለደች ጊዜ ልያ ያውም እርሷ ራሷ ላልወለደችው ልጅ ‹‹ደስታ ሆነልኝ ሴቶች ያመሰግኑኛል›› ያለችው ስለዚህ ነው። ንጉሥ ጳጳስ የወለደች ሴት ደግሞ ክብሯ እጥፍ ይሆናል። ጻድቅ፣ ቅዱስ የወለዱ እናቶች እንዴት የተከበሩ ናቸው? አምላክን የወለደች የድንግል ማርያምን ክብር መግለጫ ምን ቋንቋ ምን እንደበት ይኖራል? ኤልሳቤጥ ለድንግል ማርያም እጅግ የቅርብ ዘመዷ አክስቷ ናት። ባገኘቻት አጋጣሚ ስሟን ስትጠራ ኖራለች።

አምላክን ጸንሳ ወደ እርሷ በሄደች ጊዜ የተቀበለቻት በሚያስደንቅ መንገድ ነበር። በአክብሮት ቃል ‹‹የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?›› አለች። (ሉቃ 1.43) ይኸውም መንፈስ ቅዱስ አምላክን ጸንሳ ወደ እርሷ መምጣቷን ስለገለጠላት ነው። መውለድ ብቻ ሳይሆን መጽነስም እናት ለመሰኘት በቂ ነው።

ተጸንሰው ለመወለድ የማይደርሱ ቢኖሩም የኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መወለድ እንኳን ተጸንሶ ከዚያም በፊት ቢሆን የማይጠረጠር ስለነበር ‹‹የጌታዬ እናት›› ብላ ኤልሳቤጥ ምስክርነቷን ሰጠች። ‹‹የጌታዬ እናት›› ያለችው አዲስ ምሥጢር ተገልጦላት እንጂ ‹‹ማርያም›› የሚለው ቀድሞ የምታውቀው ስም ጠፍቷት አይደለም። ኤልሳቤጥ ኢየሱስ ክርስቶስ የአማልክት አምላክ የጌቶች ጌታ መሆኑን የምታምን ታላቅ ሴት ናት።

ሐዋርያው ቶማስ የእጁን ተአምራት የቃሉን ትምህርት እየተመለከተ

ቢቆይም በጥርጥር ይፈተን ነበር። ‹‹ጌታዬ አምላኬም›› ለማለት የቻለው እጁን በጎኑ ካስገባ በኋላ የመለኮት እሳት እጁን ሲፈጀው ነበር። ኤልሳቤጥ ግን የአምላክን እናት ተመልክታ በማኅፀን ያለውን ሕጻን ‹‹ጌታዬ›› ለማለት በቃች። ‹‹የጌታዬ እናት›› ማለቷ የአምላኬ እናት ማለቷ ነው። የጌታ እናት እመቤት እንደምትባል ለማንም ግልጽ ነው። ልጇን ‹‹ጌታዬ›› የሚል ሰው እናቱን ‹‹እመቤቴ›› ማለት አይከብደውምና። ስለዚህ ድንግል ማርያምን እመቤታችን እንላታለን። ቅድስት ኤልሳቤጥ በነጠላው ‹‹ማርያም›› በማለት ፋንታ ‹‹የጌታዬ እናት›› በማለት አክብራ መጥራቷን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

እንደ ሐዋርያው ሉቃስና ዮሐንስ ‹‹የኢየሱስ እናት›› ብላ እንዳትጠራት ገና ሕፃኑ በማኅፀን ነውና ስላልተወለደ ስም አልወጣለትም። በመልአኩ ትንቢትና የምሥራች ቃል መሠረት ከተወለደ በኋላ ‹‹ኢየሱስ›› ተባለ። ሐዋርያትና ሌሎችም ቅዱሳን ‹‹የኢየሱስ እናት›› በማለት ጎብረታቸውን ያሳዩት ሕጻኑ ከተወለደ በኋላ ነው። ሕዝቡን ከኃጢአታቸው የሚያድናቸው ስለሆነ ነው።

ድንግል ማርያምን አክብሮ መጥራት በእርሷ የተደረገውን ታላቅ አምላካዊ ሥራ መረዳትና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን ይጠይቃል።

ቀጥለን የምንመለከተው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊውን ነው። ዮሐንስ ከመስቀል ስር ቆሞ ሳለ ድንግል ማርያም በአደራ የተረከበ ከእርሷም ጋር ለአሥራ አምስት አመታት የኖረ ሐዋርያ ነው። ካለው መንፈሳዊ ጸጋ ባሻገር አብሮ በመኖርም ስለ እመቤታችን ብዙ ለማወቅ ታድሎአል። ይህ ሐዋርያ ስለ እመቤታችን ሰፋ አድርጎ በመጻፍ ይታወቃል። በጻፈው ወንጌል ውስጥ

በቃና ዘገሊላ የአማላጅነቷን ነገር፤ በራእይ መጽሐፉ ደግሞ የስደቷን ነገር በስፋት ጽፏል። ይሁን እንጂ በአንድም ስፍራ ስሟን በነጠላ ‹‹ማርያም›› ብሎ አልጠራትም። ለአብነት ያህል በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት የሆነውን ሲናገር ‹‹የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች።›› ብሏል። ደጋግሞ የጠቀሳትም በዚሁ መንገድ ነው። (ዮሐ 2.1፤ ዮሐ 2.3) አስቀድመን እንደተመለከትነው ‹‹የኢየሱስ እናት›› ማለት ወላዲተ አምላክ ማለት መሆኑ ግልጥ ነው። እመቤታችን በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራ የተጠቀሰች ስለሆነ በእያንዳንዱ ቦታ የተጠቀሰችበት አግባብ ራሱን የቻለ መልእክት እንዳለው ማስተዋል ያስፈልጋል።

ማስተዋሉን ያድልልን

Sara Ye Mariam Lij

78/ የተሃድሶዎቹ ዱባይ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ፓስተር ቀሲስ ነኝ ባዩ ቀንደኛው ተሃድሶ "ተስፈ እንዳለ" ከአውሮፓውያን (ከ only Jesus) በተመደበለት በጀት ያላወቁ ሚስኪን ልጆችን እያሰለጠነ ለፕሮቴስታንት የሚያቀብል ተኩላ ነው እናም ከማስመሰሉ ከጥምጣሙ ከቀሚሱ ከትወናው በስከ ጀርባ በመዝናናት ላይ ይህን ይመስላሉ!!!

ስለዚህ የተወደዳችሁ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች የት እንዳላችሁ ምን ላይ

እንደቆማችሁ ራሳችሁን ትመረምሩ ዘንድ ይህን ፎቶ አውጥተነዋል!!

ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጀቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሸልከው ያገባሉ፤

ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል።(2 ኛ ጴጥ 2፥1-2)

Tsere Tehadiso added 8 new photos — with Yisak Gese and 9 others.

✔✔✔ ሁለተኛው የፀረ ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ጥምረት የአገልጋዮች ውይይት ተጀመረ✔✔✔

በሚኒሶታ ጽርሐ አርያም ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን በመካሄድ ላይ የሚገኘው ይህ ጉባኤ ለሦስት ተከታታይ ቀናት የሚዘልቅ እና ዋና አላማው በቤተክርስቲያናችን ላይ የተሰነዘረውን የተሐድሶ መናፍቃንን እንቅስቃሴ ለመግታት በተለያዩ የሰሜን አሜርካ ግዛቶች የሚገኙ አገልጋዮች በጥልቀት ለመወያየት የተሰባሰቡበት ጉባኤ ነው።

አበው መነኮሳት፣ ካህናት፣ መምህራነ ወንጌልና ዲያቆናት በጉባኤው ላይ ከተለያየ ቦታ ተገኝተው በጥልቀትና በታላቅ ቁጭት በፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ጉዳይ ላይ በመወያየት ላይ ይገኛሉ።

በዚህ ታሪካዊ ጉባኤ ላይ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎችና ዕቅዶች ይቀርባሉ፣ ጠቃሚ ውሳኔዎች ይተላለፋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የቅዱሳን ሐዋርያትን ጉባኤ የባረከ አምላክ የአባቶቻችንንም ጉባኤ ይባርክልን።

ዘማርያም ዘለቀ

«እግዚአብሔርን ልባርከው፤ ጌታን ልባርከው» ይባላልን?

አርሲሳን(መናፍቃን)ና የተሐድሶ መናፍቃንም በጸሎታቸውና በየመዝሙራቸው ሁሉ እግዚአብሔርን፤ ጌታዬን ልባርከው ሲሉ ይሰማሉ። ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን?

በመዝ.33፡1 «እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ።» ግእዙ «እባርኮ ለእግዚአብሔር በኩሉ ጊዜ» ይላል። በርግጥ ልበ አምላክ ዳዊት ይኼን ያለው ስለ ሕዝቅያስ የተናገረው ነው። ይህም ማለቱ እግዚአብሔርን በ፯፣ በ፲፪፣ በ፳፬ቱ ጊዜያት አመሰግነዋለኁ ሲል ነው። ስለሆነም መጻሕፍት እግዚአብሔርን እባርከዋለው ሲሉ አመሰግነዋለሁ ማለት እንጂ መባል ስላለበት አይደለም። መጻሕፍት ምሥጢር እንጂ ዘይቤ አይጠነቀቁምና። ለዚህም ነው በመዝ. 33፡3 ላይ «እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት፤» ግዕዙም «አዕብይዎ ለእግዚአብሔር ምስሌየ።» ሲል እግዚአብሔርን ከኔ ጋራ እንደኔ አመስግኑት፤ አክብሩት ማለቱ ነው።

ዳግመኛም «ወናልዕል ስሞ ኀቡረ፤ በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ፤» የሚለውን ገጸ ንባብ ሊቃውንቱ ሲተረጉሙ እኔም እናንተም አንድ ሁነን፤ እንዳንድ ልብ መካሪ እንዳንድ ቃል ተናጋሪ ሁነን ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ ማለቱ ነው።(ዳዊት 33፡3 አንድምታ ተመልከት)

«ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ፤» የሚለውን አሁን ፍጡር ፈጣሪውን የሚያከብረው የሚያገነው ሁኖ አይደለም። ክቡር፤ ልዑል እያልን እናመሰግነው ሲል ነው፤ በማለት ተርጉመውታል።ሉቃ.1፡65።

ስለሆነም ዳዊት በመዝ.33፡1 «እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ።» ስላለ ቃሉን በቁሙ ወስደን እግዚአብሔርን፤ ጌታዬን ልባርከው ማለት አይገባንም። መጻሕፍት ምሥጢር እንጂ ዘይቤ አይጠነቀቁምና። ለአብነት ሮሜ.3፡5 «ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን።» ይላል። ይኼን አሁን በማስተዋል ብንመለከተው እግዚአብሔር እውነተኛ ነው መባል ያለበት ወይስ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን ነው መባል ያለበት? መተርጉማኑ ግን ይህን ገጸ ንባብ «እስመ እግዚአብሔር ጻድቅ።» እግዚአብሔር እውነተኛ ነው በማለት ነው የተረጎሙት። ስለሆነም ወኩሉ ሰብእ ሐሳዊ(ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ቢሆን) እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው ማለት ነው። ስለሆነም ከዚህ የምንማረው መጻሕፍት ምሥጢር እንጂ ዘይቤ አይጠነቀቁምና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈውን ቃል በቃል ገንጠል ዘንጠል አድርጎ መውሰድ መዘባረቅን ከማስከተሉም በላይ ካላሰቡበት የኑፋቄ አዘቅት ይጥላል።

1. መንፈሳዊ ኮሌጆችና “ደቀ መዛሙርቱ”
2. ምን እና ምን ናቸው?
3. የተሃድሶዎቹ ዱባይ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ፓስተር ቀሲስ ነኝ ባዩ
4. ሁለተኛው የፀረ ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ጥምረት የአገልጋዮች ውይይት ተጀመረ
5. &እግዚአብሔርን ልባርከው፤ ጌታን ልባርከው& ይባላልን?

ሚካኤል ዘየካ

79/ " እርቃናችሁን ሆናችሁ ጸልዩ "

ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም አለ ያገሬ ሰው ፤ ወዳጄ ከወደ

ሲዉዘርላንድ የተሰማውን ጉድ ልንገርህ ። አንዱ ፖስተር አማኞቹ እርቃነ ሥጋቸውን ሆነው ካልጸለዩ በቀር እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደማይሰማቸው ፣ ለጸሎታቸው መልስ ከፈለጉ ግን እርቃነ ሥጋቸዉን ሆነው መጸለይ እንደሚገባቸው አዞ ከልጅ እስከ አዛውን በአደባባይ እርቃናቸውን ሆነው ሲጸልዩ ዋሉ ። የሚገርመው ግን ከዛ ሁሉ ሕዝብ ልብስ ለብሶ የሚጸልየው ፖስተሩ ብቻ መሆኑ ነው ፣ ሕጉ ለሌላው ይሰራል ለእሱ ግን አይሰራም !

መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ እንድናረግ ያዛል ?

ወዳጄ እግዚአብሔር ገና ከጥንት የሰውን ልጅ ሲፈጥረው ግሩምና ድንቅ አርጎ የብርሃን ልብስ አጎናጽፎ ነው የፈጠረው ፣

ሕጉን አፍርሶ ጸጋውን ተገፎ እርቃኑን በሆነ ጊዜ ደግሞ " የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም። " ዘፍ 3:21 እንደተባለ እርቃኑን ይሆን ዘንድ አልወደደም አልፈቀደም ።

የተጻፈ ሕግ በሌለበት በሕገ ልቦና ይኖር የነበረው ካም ልጁንና የልጅ ልጆቹን ፦

" ከነዓን ርጉም ይሁን፤ ለወንድሞቹም የባሪያዎች ባሪያ ይሁን። " ዘፍ 9 : 25 አስብሎ ያስረገማቸው ለምንድን ነው ? አባቱ ኖህ ሰክሮ እርቃኑን በወደቀ ጊዜ የአባቱን አፍረተ ሥጋ በማየቱ አይደለምን?

በሕገ ኦሪቱም የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ፊት እርቃኑን እንዳይሆንና ኃፍረቱ እንዳይገለጥ " ኃፍረተ ሥጋህ በእርሱ እንዳይገለጥ ወደ መሠዊያዬ በደረጃ አትውጣ። " ሲል አስጠንቅቋል ።

ዘጸ 20 : 26

አጋንንት ፣ እርኩስ መንፈስ ፣ ክፉ ጋኔን ያደረበት ሰው እንጂ መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው በፍጹም እርቃኑን በአደባባይ አይቆምም ። ከክርስቶስ ወንጌል የተማርነው ይህንን ነው ፦" ወደ ምድርም በወጣ ጊዜ አጋንንት ያደሩበት አንድ ሰው ከከተማ ወጥቶ ተገናኘው፥ ከብዙ ዘመንም ጀምሮ ልብስ ሳይለብስ በመቃብር እንጂ በቤት አይኖርም ነበር።" ይላል ቃሉ ።

ጌታ ይህንን ሰው በፈወሰው ጊዜ ደግሞ ሕዝቡ " የሆነውን ነገር ሊያዩ ወጥተውም ወደ ኢየሱስ መጡ፥ አጋንንትም የወጡለትን ሰው ለብሶ ፣ ልቡም ተመልሶ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጦ አገኙት" ይላል ። ሉቃ 8 : 26 - 35

ወዳጄ እርቃነ ሥጋችሁን ሆናችሁ ካልጸለያችሁ በቀር እግዚአብሔር ለጸሎታችሁ መልስ አይሰጣችሁም የሚለው አውሮፓንና አብዛኛውን የአፍሪካ አገሮችን ለጅብ ያስበላው የሉተር ስብከት እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ አይደለም ።

ስለዚህ በዚህ በኢየሱስ ስም በሚነገድበት በፕሮቴስታንቱ ካምፕ ምን እየተደረገ ምን እየሆነ እንዳለ አውቀን ከዚህ ራሳችንን እንድንጠብቅ ፤ ለነዚህም ወገኖች እግዚአብሔር ልቦናቸውን እንዲመልስላቸውና ወደ ቀናችው ወደ ተዋሕዶ እንዲመለሱ ልንጸልይላቸው ይገባል ።

ሊንኩን ተጭነው ዜናውን ይመልከቱ

በቃ በቃ

80/ ዶር ዛኪር ለህዝቡ ትምህርት ከሰጡ በሓላ በጥያቄና መልስ ፕሮግራም ላይ አንዱ በመነሳት እንዲህ ሲል ይጠይቃል “ዶር.ዛኪር ይህን ማወቅ እፈልጋለሁ፤ ቁርአን በመልዕክተኛው ሙሐመድ እንድናምን ይናገራል፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ በእኢየሱስ ያመነ የዘላለም ህይወት እንደሚኖር ይናገራል። በቁርዐን መሰረት ሁለቱም የፈጣሪ መልዕክተኛ መሆናቸውን ነው ሚናገረው፤ ታዲያ ይህ እውነት ከሆነ እየሱስ የቱጋር ነው ስህትት የሰራው፤ ማለቴ ይህ ሁሉ ሰው ስህተት ውስጥ እንዲገባ ያረገው በየትኛው ስህተቱ ነው ?” ዶር ዛኪረም የሰውዬውን ጥያቄ ለህዝቡ ከደገሙት በሓላ አብራርተው መለሱለት።

“ወንድሜ የጠየከው ጥያቄ እጅጉን ጠቃሚ ነው ነገር ግን እየሱስ(ዐ.ሰ) ፈጽሞ ስህተትን አልሰሩም፤ ስህተቱን የሰራው እሱ ሳይሆን ቸርች ነው።በኛ መሰረት እየሱስ (ዐ.ሰ) ከተከበሩት የአላህ መልዕክተኛ አንዱ ነው።እየሱስ በዩሐንስ ወንጌል 14፡6 መሰረት “እኔ ህይወትም፣እውነትም፣ መንገድም ነኝ ወደ አባቴ ማንም አይመጣም በኔ ቢሆን እንጂ” ያለው እውነቱን ነው። ይህ ማለት መልዕክተኝነቱን ነው ሚነግረን፤ ሙህመድ(ሰ.ዐ.ወ) ካሉት ጋርም እጅጉን ይመሳሰላል።በጊዜው የእየሱስን ትምህርት በትክክል ከተከተልክ ገነት ትገባለህ ማለት ነው የዘላለም ህይወት ማለት ገነት ነው። በሙሴ(ኢ.ሰ) ጊዜ ወደ ፈጣሪ ሊያቀርብህ ሚችለው ሙሴ ብቻ ነው፤ እንዲሁም በእየሱስ ጊዜ ወደ ፈጣሪ ሊያቀርብህ ሚችለው እየሱስ ብቻ ነው በተመሳሳይ በሙህመድ ጊዜ ወደ ፈጣሪ ሊያቀርብህ ሚችለው

ሙሀመድ(ሰ.ዐ.ወ) ብቻ ነው።

በተመሳሳይ እየሱስ በዩሀንስ ወንጌል 16፡7 ላይ “ብዙ ምነግራቹ ነገሮች ነበሩኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም እውነተኛው መንፈስ የመጣ ጊዜ ወደ እውነት ይመራችሓል” ሰለ ሙሀመድ(ሰ.ዐ.ወ) መምጣት ይናገራል፤ እውነተኛ የእየሱስ ወዳጅ ነኝ ካልክ ሙሀመድን(ሰ.ዐ.ወ) መከተል ግድ ነው።ስለዚህ “ፈጣሪ ነው” እያሉ ስህተቱን እየሰሩ ያሉት ከቸርች ነው፤ እየሱስ ፈጽሞ አልተሳሳተም።አንድም ቦታ እየሱስ(ዐ.ሰ) በራሱ ጊዜ “ጌታ ነኝ” አላለም።አሁንም በድጋሚ ነው ምነግራቹ ማንኛውም ክርስቲያን ከመጽሃፍ ቅዱስ እየሱስ ራሱ በማያሻማ መልኩ “እኔ ጌታ ነኝ ወይም እኔን ተገዙኝ” የሚል ካመጣልኝ ዛሬውኑ ክርስትናን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ።ቸርች ነው ስህተቱን የሰራው፤ፈጽሞ እየሱስ አይደለም።

እየሱስ በርግጥም ያለው በዩሀንስ ወንጌል 14፡28 “ከኔ አባቴ ይበልጣል”፤ በዩሀንስ ወንጌል 10፡29 “አባቴ ከሁሉም ይበልጣል”፤ በማቲዎስ ወንጌል 12፡38 “በፈጣሪ ፍቃድ አጋኔንትን የማወጣ ስሆን..”፤ በሉቃስ ወንጌል 11፡20 “በፈጣሪ እጅ አጋኔንትን የማወጣ ስሆን”፤በዩሀንስ ወንጌል 5፡30 “አንዳችም ነገር በራሴ ማድረግ አይቻለኝም፤ የሰማሁትን እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፤ያባቴን ፍቃድ ቢሆን እንጂ የራሴን አልፈጽምም ” ማንኛውም ሰው “የኔን ሳይሆን የፈጣሪን ፍቃድ ፈጻሚ ነኝ”ካለ ሙስሊም ነው ማለት ነው።ሙስሊም ብሎ ማለት ራስን ለፈጣሪ ፍቃድ በማስገዛት የሚገኝ ሰላም ማለት ነው።

እኛ ሙስሊሞች እየሱስ ክርስቶስን እንወደዋለን እናከብረዋለን እንከተለዋለንም ነገር ግን አናመልከውም።ምክኒያቱም እሱ መልዕክተኛ ነው

እንጂ ፈጣሪ አይደለም።ጥያቄህን እንደመለስኩልህ ተስፋ አደርጋለሁ፤ እሺ አሁን እየሱስ(ዐ.ሰ) መልዕክተኛ መሆኑን ታምናለህ ?" ሰውዬውም "አዎ አምናለሁ" ሙሀመድስ(ሰ.ዐ.ወ) የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን ታምናለህ ? "አ አ አይ አላምንም... ም ም ምክኒያቱም በመጽሀፍ ቅዱስ አምናለሁ" ሲል መለሰ ዶር.ዛኪር በመቀጠል "ታዲያ በጽሀፍ ቅዱስ በዩሀንስ ወንጌል 16፡12-14 'ብዙ ምነግራቹ ነገሮች ነበሩኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም እውነተኛው መንፈስ የመጣ ጊዜ ወደ እውነት ይመራችሓል፤ የሰማውን ቢሆን እንጂ በራሱ አይናገርም፤ እኔንም ያልቀኛል' ይላል።ወንድሜ እዚጋ እየሱስ ስለማን ነው እያወራ ያለው ፤ልታስረዳኝ ትችላለህ ? መጽሃፍ ቅዱስ አንብበሃል ?" ሲል ጠየቀው ሰውዬውም "አዎ ስለ መንፈስ ቅዱስ ነው እያወራ ያለው" ዶር ዛኪር "በጣም ጥሩ መጽሃፍ ቅዱስን አጥንተሃል ማለት ነው፤ እሺ ስለ መንፈስ ቅዱስ ነው ሚያወራው ብለሃል ትንሽ አንቀጾችን ከፍ በልና አንብብ ዩሃንስ ወንጌል 16፡7 "የኔ መሄድ ግዴታ ነው፤ እኔ ካልሄድኩ እውነተኛው መንፈስ አይመጣም" ይላል ስለዚህ ይህ ሰው እንዲመጣ መስፈርቱ ግዴታ እየሱስ መሄድ አለበት።መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እየሱስ ከመምጣቱ በፊት ነበር፤ እየሱስም እያለ ነበር፤ የኤልሳቤት ማህጸን ውስጥም ነበር፤እየሱስ ሲጠመቅም ነበር። ታዲያ እንዴት ብሎ ነው ለመንፈስ ቅዱስ ሚሆነው ? ይህ ማለት መጽሀፍ ቅዱስን ባግባቡ አልተረዳኸውም ማለት ነው።መንፈስ ቅዱስን ሳይሆን ሙሀመድን(ሰ.ዐ.ወ) ለማመልከት ነው።

በአዲስ ኪዳን በዩሀንስ ወንጌል 14፡16፤ በዩሀንስ ወንጌል 15፡26 በዩሀንስ ወንጌል 16፡7 በዩሀንስ ወንጌል 16፡12-14 ሁሉ ሚያወሩት

ስለ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነው።እኔ ልጠይቅህ ምፈልገው በመጽሀፍ ቅዱስ አማኝ ነኝ ካልክ እየሱስ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ስለ ሙሀመድ መምጣት ይናገራል።ታዲያ ለምንድነው በሙሀመድ(ሰ.ዐ.ወ) ማታምነው፤ የእየሱስን ግማሹን አስተምህሮ ነው ምትከተለው ማለት ነው ?" ሰውዬውም አሰብ ካረገ በሓላ "አስተምህሮቱ ሚለው እውነተኛ ተናጋሪ አስጠንቃቂ እልካለሁ ይላል እንጂ ይህ ሰው ነው ተብሎ በስም አልተጠቀሰም" ዶር ዛኪር "በኦርጅናል ሂብሩ መጽሐፍ ቅዱስ መዝሙረ ሰለሞን 5፡16 'ሂኮ መሞተኪም ፊኩሊ ሙሀመዲም ዛይዱ ዚወይ ዛይራይ ባይነጁሬ ሰለም' በስም ተጠቅሶዋል 'ፊኩሊ ሙሀመዲም' ሙሀመድ ስሙ ሲሆን 'ኢም' ደግሞ በኢብራይስጥኛ ለክብር የሚገባ ቃል ነው።አሁንስ ታምናለህ ? " ሰውዬው እጅጉን ሚሉት አጡ " አየዋለሁ " ሲሉም መለሱ ዶር ዛኪርም "መጀመሪያ ቸርች ልትጠይቅ ነው? " ሰውዬውም "አይ በራሴ አየዋለሁ" ዶር.ዛኪር "እስከመች?" "እሺ ዛሬ ማታ " ዶር.ዛኪር "እኔም ከነገ ወዲያ ነው ምሄደው፤ ከዛ በፊት ልታገኝ ከፈለክ ነገ ጠዋት አስተባባሪዎችን ጠይቃቸው" ሰውዬውም "እሺ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።"

ክርስቲያን ወንድምና እህቶች ምን ትጠብቃላችሁ የሙሀመድ(ሰ.ዐ.ወ) መምጣት በግልጽ መጽሀፋቹ ላይ ተቀምጦ ሳለ በተሳሳተ እምነት ጊዜያቹን ለምን ትገድላላቹ ?

81/ የተሐድሶ መናፍቃን ሕላዌ - የዘመናችን ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ጥያቄ

ተሐድሶ መናፍቃን ከዛሬ ሰማንያ ዓመት በፊት ወደ አገራችን ሲገቡ፣ ትምህርት ቤት ከፍተው ሲያስተምሩ፣ ያስተማሯቸውን ተማሪዎች በማሳበር አደራጅተው "ሠራዊተ ክርስቶስ" በሚል ሥያሜ የአንግሊካን ፕሮቴስታንት ቸርች ቅርንጫፍ አድርው ሲያሠራቸው ተሐድሶ መናፍቃን አይታወቁም ነበር። በ፲፱፻፹ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ናዝሬት ላይ ተጀምሮ የነበረውን የሠራተኞች ጉባኤ ጠምዝዘው "የአማኑኤል ጎብረት" የሚባል የመናፍቃን ድርጅት ሲያደርጉት ተሐድሶ የሚባል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለ ወይስ የለም የሚለው ገና ያከራክር ነበር። በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ቅዱስ ሲኖዶስ ስድስት መነኮሳት ነን ባዮችን አውግዞም የተሐድሶ መናፍቃን መኖር አለመኖር አከራካሪነቱ አላቆመም ነበር። እንዲሁ በ፳፻ወ፬ ዓ.ም ቅዱስ ሲኖዶስ የተሐድሶ መናፍቃን ፊታውራሪዎች የሆኑ ስምንት ማኅበራትንና አሥራ ስድስት ግለሰቦችን አውግዞም ሕዝበ ክርስቲያኑ የተሐድሶ መናፍቃንን ሕላዌ ገና አላመነም። ይህን የተረዱት ተሐድሶ መናፍቃን በቤተ ክርስቲያን ላይ ሊያመጡት ላሉት የምጥ ጣዕር መንገድ ጠራጊ አድርገው በሚጠቀሙባቸው የቴሌቪዥን መርሐ ግብራት ብቅ ይሉና "እንደ ተቋም ተሐድሶ የሚባል አለ ብለን አናምንም፤ ካለ ቦታውንና ቢሮውን ብትነግሩን" ብለውን ይመለሳሉ።

ተሐድሶ መናፍቃን ኢትዮጵያ ውስጥ የአንድ አረጋዊ ዕድሜ ያህል ቆይተው፣ በቃል የጀመሩትን ተምኔት እውን ለማደረግ ከግለሰብነት ወጥተው

ወደ ተቋም መጥተው፣ ኮሌጅ ከፍተው፣ የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር የተከተለ የራሳቸው መዋቅር ዘርግተው፣ የእምነት መግለጫ አውጥተው፣ ከተናጥል አሠራር ወደ ጎብረት አድገው፣ የቤተ ክርስቲያንን ዶግማ፣ ቀኖና፣ ሥርዐትና ትውፊት የሚንዱ ሁለት መቶ የሚደርሱ መጻሕፍትን ጽፈው፣ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ ስልት ነድፈውና የሃያ አምስት ዐመት ዕቅድ አቅደው እኛ ግን ዛሬም ተሐድሶ መናፍቃን የሚባል አለ ወይስ የለም የሚል ክርክር ላይ ነን። የተሐድሶ መናፍቃን ሕላዌ ጉዳይ ዛሬም ጥያቄ መሆኑ ትርጉሙ አንድ ብቻ አይሆንም። አንድም በዓላማ የውስጥ አርበኛ ሆነው የሚሠሩት አካላት የሚያስወሩት ወሬ ነው። አንድም የተሐድሶ መናፍቃን ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተጋረጠ ፈተና መሆኑን ተገንዝቦና ቤተ ክርስቲያንን በመጠበቅ አንጻር ራስን ለችግሩ የመፍትሔ አካል አድርጎ አለመቁጠር አለ ማለት ነው። አንድም ለራስ ክብርና ዝና ቅድሚያ በመስጠት ግለሰባዊ ግጭትን እንደ ሃይማኖት ልዩነት በመቁጠርና በማኩረፍ ቤተ ክርስቲያንን ለተሐድሶ መናፍቃን አሳልፎ ለመስጠት የሚሠራ አካል አለ ማለት ነው። በማንኛውም መንገድ ቢሆን ተሐድሶ መናፍቃን ሠርተው ካመጡት ይልቅ እኛ በመተኛታችን ያገኙት ለውጥ ይበልጣል።

ምን ዐይነት አዚም እንደተጣለብንና በምን ዐይነት ቋንቋ ቢነገረን ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ እንደምንነሣ ለመግለጽ የሚያስቸግር ዘመን ነው። እነርሱ እንጸድቅበታለን ብለው ለማያምኑበት ጉዳይ እየደከሙ እኛ እስከ ሞት ድረስ ለመታመን ቃል ለገባንላት አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለቅዱሳን ስለ ተሰጠች ሃይማኖታችን መከራ ለመቀበል ፈራ ተባ እንላለን። መንግሥተ እግዚአብሔር ያለ መከራ እንደማትገኝ ቅዱሳን ሐዋርያት “በብዙ ድካም

በብዙ መከራ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንገባ ዘንድ ይገባናል” በማለት አስረግጠው ነግረውናል። “እኔ የዋህና በልቤም ትሑት ነኝ” ብሎ ያስተማረን ጌታችን በቤተ መቅደስ ውስጥ ሸቀጥ ይዘው የተገኙ ለዋጮችን ጅራፍ አዘጋጅቶ አስወጥቷቸዋል። ጌታችን ይህን ያደረገው ቤተ ክርስቲያን እምነታቸውን በካዱና ገንዘብን በእግዚአብሔር ቦታ ባስቀመጡ ለዋጮች ስትረክስ ዝም ማለት ተገቢ አይደለም ሲለን ነው። ዐላውያን ነገሥታትን ሳይፈሩ የገሠጹትን ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ኤልያስን፣ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን “መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ” ብለን እየሰበክን ትችት የምንፈራ ከሆነ ድጋፋችን ለሚገሥጹት ሳይሆን ለሚገሠጹት ነው ማለት ነው። ከጥንት ጀምሮ ብዙ መናፍቃን ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ መነሣታቸውንና በውግዘት መለየታቸውን ጠቅሰን ታሪክ እያስተማርን ተሐድሶ መናፍቅ የሚባል በእኔ ተቋም ውስጥ ፈጽሞ የለም የምንል ከሆነ ለተሐድሶ መናፍቃን ድጋፍ በመስጠት ተባባሪ እየሆንናቸው ነው። ፕሮቴስታንቶች ራሳቸው የተሐድሶ መናፍቃን እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተካሔደ እንደሆነና እነርሱም ለዚህ ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው በድፍረት እየተናገሩ ሳሉ እኛ የለም ማለታችን ራስን ማሞኘት እንጂ ትርፍ አያመጣም።

ከአንድ ከሉተር ምንጭ የተቀዱት ፕሮቴስታንቶችና ተሐድሶ መናፍቃን ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መስካሪ ሆነው በጋራ እየሠሩ ነው። እኛ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሐድሶ መናፍቃን ሠርገው ገብተዋል የሚለው አካልና በፍጹም ተሐድሶ የሚባል ነገር የለም የሚለው አካል ጎራ ለይቶ የእርስ በእርስ ንትርክ ውስጥ

በመግባት ለተሐድሶ መናፍቃን የተሻለ የማስላሰያ ጊዜ እየሰጠናቸው ነው። ትናንት ተሐድሶ መናፍቃን ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት እየተጉ እንደሆነና በተሐድሶ መናፍቃን ትኩረት የተደረገባቸው የቤተ ክርስቲያን ተቋማት እንዳሉ የተናገረ አንደበት፣ የፊረመ ጣት ዛሬ አዲስ "እውነት" ይዞ ብቅ ይላል። ትናንት ተሐድሶ መናፍቃን ናችሁ ራሳችሁን አርሙ፣ አስተካክሉ ካላቸው ሰዎች ጋር ወግኖ ቤተ ክርስቲያንን የሚያሳዝን፣ ምእመናንን የሚበትን ንግግር ሲያደርግ ይገኛል። ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን የመጠበቅ ሐላፊነት ሰጥታ ያስቀመጠችው ኖላዊ ለቤተ ክርስቲያን ካልወገነ የቤተ ክርስቲያንን ችግር ለማን ይነግሯል? አበው ሲተርቱ "ከባል የታመነ ከማን ጋር ይሔዷል?" ይላሉ። በተሐድሶ መናፍቃንና በፕሮቴስታንቶች ሕገ ወጥ ጋብቻ ስንገረም በተሐድሶ መናፍቃንና በሙሰኞች ጥምረት ስንደምመ አሁን ደግሞ ተሐድሶ መናፍቃንና የቤተ ክርስቲያን ተቋማት ግንባር ፈጥረው ቤተ ክርስቲያንን መዋጋት ጀመሩ።

ተሐድሶ መናፍቃን ኑፋቄያቸውን ለማስተላለፍ፣ ቤተ ክርስቲያንን ለመሳደብ እና ብዑዓን ሊቃነ ጳጳሳትን ለማቃለል የሚጠቀሙት ሚዲያዎችን ነው። ከእነዚህ ሚዲያዎች መካከል ድረ ገጾችና የጡመራ መድረኮች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ። ተሐድሶ መናፍቃን ከአሥር በላይ ድረ ገጾችና የጡመራ መድረኮች ያሏቸው ሲሆን ሁሉም በአንድነት የሚሳተፉበት ድረ ገጻቸው ግን አባ ሰላማ የሚባለው ነው። ይህ ድረ ገጽ ቤተ ክስቲያንን የሚሳደብ፣ ቅዱሳንን የሚያንቋሽሽ፣ ብጹዓን ሊቃነ ጳጳሳትን የሚያቃልል ድረ ገጽ ነው። ድረ ገጹ እንዲህ ሆኖ ሳለ የራሳቸው ድረ ገጽ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን የትምህርት ተቋማት የሚያወጧቸው ደብዳቤዎች ለሚመለከታቸው አካላት

ከመድረሳቸው በፊት በዚህ ድረ ገጽ ይወጣሉ። አባ ሰላማ አሁን የተሐድሶ መናፍቃን ብቻ ሳይሆን የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅም ልሳን ሆኗል። ኮሌጁ የራሱ ድረ ገጽ አለው፤ መጻፍ የሚፈልገውን ሁሉ በራሱ ድረ ገጽ ማስተላለፍ ይችላል። ከኮሌጁ የተባረሩ የሦስት ሠራተኞች ደብዳቤና ዝርዝር ሁኔታ፣ ኮሌጁ ለማኅበረ ቅዱሳን የጻፈው ደብዳቤ፣ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ያስገቡት አሥራ ሦስት ገጽ የአቋም መግለጫ ማብራሪያ የወጣው በአባ ሰላማ ድረ ገጽ ነው። የዶክተር ሐዲስ የሻነው ስንብት ግን በድረ ገጹ አልተዘገበም።

Derese Lema

82/ የሐራ ጥቃን መናፍቃንን ለመከላከል ምን እናድርግ?

በቤተክርስቲያናችን ትምህርት መሰረት መናፍቅ ማለት ተጠራጣሪ ከሐዲ ማለት ሲሆን የክርስቶስን አምላክነት የቅዱሳኑን ሁሉ ክብርና አማላጅነት የሚጠራጠር የሚክድ ማለት ነው።

በክርስትና ታሪክ መናፍቃን የተነሱት ገና ከመጀመርያው አምላካችን ሰው ሆኖ ሊያድነን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ቅ. ዮሐንስ በአንደኛ መልእክቱ እንዳስተማረው " ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው

መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ።"

1 ዮሐ. 4፥3 ብሏል። እናም ምንም አዲስ ነገር የለም ያኔም በሐዋርያት ዘመን ነበር።

አይነታቸውና አቀራረባቸው በአገላለጽና በጊዜ ቢለያይም መናፍቃን ግን ያው መናፍቃን ናቸው። አምላክን አማላጅ የሚሉ አምላክነቱን የማያምኑ ማለት ነው።

የመጀመሪያ አላማቸውና የመጨረሻ ግባቸውም በየደረጃቸው የምናምንባቸውን አምላካችንን እና መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን እና የእግዚአብሔር ባለሟል የሆኑትን ቅዱሳንን እና መላእክትን ማስካድ ነው።

ማንኛችንም ብንሆን ይህ የእምነት ሙላት በልባችን ከሌለ የክርስቶስን አምላክነት እና የቅዱሳኑን አማላጅነት ብንጠራጠር የምንፍቅና መንፈስ በልባችን እንደገባ ልንረዳ ያስፈልገናል።

ብዙ ሰዎች መናፍቅ ማለት ለይቶለት ቤተክርስቲያንን ርግፍ አድርጎ ትቶ በመናፍቃን አዳራሽ የሚጨፍር በግልጽም ሳያፍር እኔ ጴንጤ ነኝ ጆሆባ ዊትነስ ነኝ... ወዘተ ያለ ሰው ብቻ ይመስላቸዋል።

ነገር ግን ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል እያሉ መጠራጠር እና አለማመን ምንፍቅና ነው።

ስለዚህ ይህን የምንፍቅና መንፈስ ለመዋጋት ምን እናድርግ?

1. በቤተክርስቲያናችን ሥርአት በጸሎት ጊዜያት ሁሉ ይህን የምንፍቅና መንፈስ ከእኛ የምናርቅበት እና እምነታችንን የምንገልጽበት የጸሎት ክፍል

ጸሎተ ሃይማኖት ነው። ይህ ጸሎት አንድ ሰው በቃሉ እምነቱን የሚመሰክርበት እና መናፍቅ አለመሆኑንም የሚምልበት አእማደ ምስጢራትን ወይንም ዶግማን አጠቃሎ የያዘ ታላቅ ጸሎት ነው። በግልም ሆነ በጉባኤ ወይንም በተለያዩ የጸሎት ሥርአቶች ወቅት ይህን ጸሎት ማድረስ ያስፈልጋል ሃይማኖታዊ ግዴታም ነው።

አሁን አሁን ግን በቅዳሴ ጸሎት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ይህ ጸሎት እየተተወ ነው። ስለሆነም ይህ ጸሎት ከአባታችን ሆይ እና ከእመቤታችን ጸሎት ቀጥሎ ሊዘወተር የሚገባው ጸሎት መሆን ይገባዋል። ሁላችንም ልክ እንደ አባታችን ሆይ በቃል ልንይዘው የሚገባ ጸሎት ነው።

ይህ ጸሎት የተጻፈበት ዋናው ምክንያት ልክ እንደዛሬው ዘመን መናፍቃን በዝተው የክህደት ትምህርት ሲያስፋፉ ለዛ አጸፋዊ ምላሽ እንዲሆን የተዘጋጀ ነው። እምነታችን በትክክል ምን እንደሆነ ሰልስቱ ምእት እና በእነርሱ ፈለግ ከነርሱ በኋላ የተነሱ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አባቶች በኒቂያ በቁስጥንጥንያ እና በኤፌሴን ጉባኤያት ያስተላለፉት የሃይማኖት ውሳኔ ነው። ስለዚህ ይህን ጸሎት በማዘውተር ክህደትን ልንከደው ይገባናል።

2. ከክህደት ሥራ እና ሰራተኞች እንዲሁም የክህደትን ሥራ ከሚደግፉና ከሚያስፋፉ የቤተክርስቲያንን መብትና ልእልና ከሚደፍሩ ሰዎች፣ ድርጅቶች፣ አባቶች እና ሌሎችም ተቋማት መንግሥትንም ጨምሮ እምነታችንን ለመበረዝ ሃይማኖታችንን ለማፍረስ የሚያደርጉትን ማንኛውንም አይነት እንቅስቃሴ ያለምንም ይሉኝታና ፍርሃት መቃወም፤ ይህን ከሚያደርጉ ጋርም ሕብረት አለመፍጠር ያስፈልጋል። ጣዖት ከታቦት ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን ሕብረት አላቸው ያለው ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህ

ነውና። 2 ቆሮ. 6፥15

በአሁኑ ጊዜ ግን የብዙዎቻችን ትልቁ ችግር ይህ ነው።

አንድ እግራችን እዚህ አንደኛው እዛ! ለቤተክርስቲያን ትክክለኛ ሕግና አስተምህሮ እንቆማለን እያልን በተቃራኒው ሕግንና ቀኖናን ካፈረሱና ካስፈረሱ ጋር እንሞዳሞዳለን። መናፍቃኑን ወግነው ለእነርሱ ሽንጣቸውን ይዘው ሲከራከሩ መልሰን አቤቱታችንን ለእነርሱ እናቀርባለን። እርስ በርሱ የተጣረዘ /paradoxical/ አቋማችንን ልናርም ይገባናል። ይህ አይነቱ አካሔድ በተለይ በእኛ በኢትዮጵያውያን በይበልጥም ደግሞ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማንያን ላይ በሁሉም ዘርፍ በሃይማኖትም በሃገርም ደረጃ እየደረሰብን ላለው ውስብስብ ችግር ከእግዚአብሔር መፍትሔ እንዳናገኝ ያደረገን በራሳችን መከራችንን እያበዛንና እያጸናን ያለንበት አካሔድ ነው። እግዚአብሔር እውነት ነው፤ የእውነትም አምላክ ነውና ከሃሰት ጋር ስንወግን ምህረቱን ያዘገየዋል።

ሁልጊዜ ለወገኔ ይድላው ሳንል ለእውነትና ለእምነት ብቻ ከቆምን እግዚአብሔር የከበደና የማይቻል የሚመስለውን ባልጠበቅነው ሁኔታ ሊያስወግደው ይችላል። እኛ ግን የሃይል ሚዛን እያየን በፍርሃት በዘርና በጥቅም ላይ ተመርኩዘን የሚያዋጣ የመሰለንን በመከተላችን መከራችንን እየጨመርን እንገኛለን። ይህን ማረምና ማስተካከል ይገባናል።

" እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው፤ እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው፤ ከቊጣው የተነሣ ምድር ትንቀጠቀጣለች፤ አሕዛብም መዓቱን አይችሉም።" ኤር.10፥10

3. በተቻለ አቅም የእኛን እምነት/ቤተክርስቲያን መሰረታዊ

አስተምህሮዎች ማወቅ መማር መረዳት ይገባል። በርግጥ ሁሉ ሰው ጥቅስ አዋቂ መሆን ወይም እንደ መምህራን ማወቅ አይጠበቅበትም። "ወንድሞች ሆይ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አትሁኑ የባሰውን ፍርድ እንዳንቀበል" ተብለናልና።

ያዕ. 3፥1።

ሰው ሁሉ ጥቅስ ካላወቀም አያውቅም ሊባል አይቻልም። ማወቃችንም ከመናፍቃን ጋር ለመከራከር ሳይሆን ለራስ ለሕይወት ማወቅ ይገባናል። ይህ እውቀት የሚያስፈልገን "ህዝቤ እውቀት ከማጣት የተነሳ ጠፍቷል" የተባሉትን እንዳንሆን ማለት ነው። ሆሴ.4፥6

ድሮ ድሮ ብዙ ሰው ዳዊት እስከ መድገም ድረስ ይማር ስለነበር እንደ ዛሬው አይነት ጥቅስና ቁጥር ባይጠቅስም እምነቱን ግን አጽንቶ ለሃይማኖቱ እስከሞት ድረስ የታመነ ነበር። ዛሬ ግን ብዙ ጥቅስ አዋቂ ወደ ክህደት እየሔደ ነው። ስለዚህ ለክርክር ሳይሆን ለሕይወት እና ለእምነት ጽናት ያህል ብቻ እንወቅ። ይህም እውቀት በሦት መንገድ ለሰዎች ይሰጣል።

በስፋት የተለመደውና የክርስትናም ይትብሐል የሆነው ከመምህራን ዘንድ መማር ነው። ይህም በግል ወይንም በጉባኤ አዘውትሮ በመገኘት በፊስ ቡክ በዩቲዩብ በስልክ ወዘተ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ደግሞ በቤተክርስቲያን ሊቃውንትና መምህራን የተጻፉ መጽሐፍትን በማንበብ ነው። ይህም በስፋት ይገኛል። ሦስተኛው ግን በስፋት የሚደረግ ሳይሆን ለተወሰኑ ሰዎች እግዚአብሔር ለወደዳቸው ብቻ የሚያደርገው ነው። ይህም በልባቸው እውቀትን ይገልጽላቸዋል። አንድም እንዲሁ በጸጋው አንድም ከጥረታቸው በቅንነት ካላቸው ፍላጎት ከጾምና ጸሎት የተነሳ እውቀትና ጥበብ

ይገለጽላቸዋል። የእኛ ድርሻ በስፋት ሁለቱ የመጀመርያዎቹ ስለሆኑ በዚያ ላይ መበርታት ይገባናል።

4. መናፍቃን እየተጠቀሙባቸው ያለውን የኑፋቄ ማስፋፊያ ዋና ዋና መንገዶችን እና ክፍተቶችን መዝጋት ያስፈልጋል።

ለምሳሌ መናፍቃን አባቻቸው አርዮስ እንዳደረገው አንዱና ዋነኛው ኑፋቄን የሚሰራጫው መንገድ መዝሙርና ግጥም ነው።

የህዝቡን የመዝሙር ፍላጎት ለማርካት ከመናፍቃኑ በላይና ቀድሞ ሥርአት ያላቸው ዜማ ሚስጢርና ትርጉም የማያዛቡ መዝሙራት በስፋት ማቅረብ ያስፈልጋል።ለመዘመር የሚፈልጉትን ግጥምና ዜማ በመስጠት ሌሎችም ጥሩ ጥሩ ድምጽ ያላቸውን ሰዎች ወደ ዝማሬ አገልግሎት እንዲገቡ መገፋፋት ያስፈልጋል።

ይህ ማለት ግን ሁሉም ሰው ወይንም ዘማርያን ድፋቱን ቅናቱን ጭረቱን ወዘተ ሳያዛንፉ መዘመር አለባቸው ሳይሆን ለዛ ያለው የታረሙና ኢትዮጵያዊ ቅላጼ ያላቸው መዝሙሮች በስፋት እንዲዳረሱ ማድረግ ይገባል።

በየንግሡ በአል በየቤቱ በየመርሐግብሩ በየጋራውና ሸንተረሩ በየመኪናው ውስጥ...ወዘተ ሊዘመሩ የሚገባቸውን የቤተክርስቲያን አስተምህሮ ያለቀቁ መዝሙራትን ማስፋፋት ይገባል።

እንደ ማህበረ ቅዱሳን የማኅበሩ አባል የሆነ በግል መዘመር አይችልም የሚሉ ስንኩል ህጎችም ሊታረሙ ያስፈልጋቸዋል። ስንቱን ምርጥ ምርጥ ዘማሪያን ሊሆኑ የሚችሉ ወንድም እህቶችን አምክኗል!

5. ማኅበረ ቅዱሳን ከማይታማባቸው አንደኛው ሥራው በርግጥም

የቤተክርስቲያንን ትምህርት ለመበረዝ የሚንቀሳቀሱትን መናፍቃን በማጋለጥ የሰራው ሥራ ነው። ይህ ማለት ግን በሌሎች ዘርፎች የሰራው ሁሉ ልክ ነው እያልኩ አይደለም።

የአደረጃጀት ሁኔታው ለቤተክርስቲያን እድገት ያመጣል ብዬ አላምንም። በዛ ዙሪያ ያለኝ ትችትና ተቃውሞ እንደተጠበቀ ነው።

በዘላቂነት ቤተክርስቲያንን ከመናፍቃን ለመከላከል በተለይም በቤተክህነቱ ውስጥ ያሉትን እና ሰርገው የሚገቡትን እንዲሁም የቤተክርስቲያንን ልእልና እና መብት ለማስከበር መንግሥት የሆነ ሁሉ ቤተክርስቲያንን ለፈቃዱ ማስፈጸሚያ እንዳያውላት በተናጠል ከጎን ያለ ማጎበር ሳይሆን ውስጥ ያለና በየመምሪያውና በየመዋቅሩ በመግባት፤ አባቶችን ለመግፋትና የሰው ሃይል ለመቀነስ ሳይሆን፤ ጠንካራ አሰራርና የስራ አፈጻጸም እንዲኖር ማእከላዊነቱ ውስጥ መጠቃለል እንደሚገባው ያለኝ እምነት ጽኑ ነው።

ወደ ርእሱ ስመለስ ግን እነኝህ ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ የወጡ ናቸው ተብለው በተለያየ ጊዜ የተገለጹ ሰዎች በትክክልም ናቸው።

ስለሆነም እንደነዚህ አይነት ቀሳጮች ጉባኤያት ላይ አለመገኘት ስብከታቸውን አለመስማትና መዝሙር መሰል ዘፈና ዘፈን የሆኑ ሥራዎቻቸውን አለማዳመጥና አለመግዛት ያስፈልጋል። ሰው ማንን ይመስላል ቢሉ ኑሮውን እንደተባለው እንዳይሆንብን ማለት ነው። ደግሞም ከአህያ የዋለች ጊደር እንትን ተምራ መጣች እንዲሉ ከእንደ እነዚህ አይነት ሰዎች ጋር መጎዳኘትና መዋል አያስፈልግም።

6. እነኝህ ሃራ ጥቃዎች በምንገኝበት ደብራትና ገዳማት ክህደታቸውን እንዳይዘሩ የማስተማር እድል እንዳያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል። እንደነዚህ

ያሉት የግድ ካላስተማሩ ወንጌል አይሰበክም ያለው ማነው? እንደውም በግድ ካላስተማርን ማለታቸው በራሱ የምንፍቅናቸው አንዱ ማረጋገጫ ነው። ወንጌላውያን በውዴታ እንጂ በግድ እናስተምር ከእኛ ወዲያ አዋቂና መምህር የለም አይሉምና።

7. ሰዎች ግራ እንዳይጋቡና መናፍቃኑም እንዳያጭበረብሩ ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ ትውፊትና ይትባሕል እንዴት እንደወጡ የዛ ክህደትና አካሔም መጨረሻው ምን እንደሆነ በግልጽ ለህዝ ማስረዳት መረጃዎችንም አለመደበቅ ያስፈልጋል።

ሃራ ጥቃ ማለት ራሱን በውሃ ውስጥ ቀብሮ ሰላማዊ መስሎ ያልታየ መስሎ በመደበቅ እንስሳትን የሚያጠቃ የሚመርዝ የእባብ ዝርያ ሲሆን እነዚህም እንዲሁ ራሳቸውን ደብቀው ነገር ግን ስለ ክርስቶስ አምላክነት ስለቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ድንግል ማርያም ስለ ቅዱሳን እና መላእክት አማላጅነት የማያስተምሩ ጌታ ጌታ በማለት ብቻ የሚጮሁ መሆናቸውን እየገለጡ ማሳየት ይገባል።

ይቆየን።

ሚካኤል ዘየካ

83/ የፕሮቴስታንት " ሃይማኖት " መስራች የሆነው የማርቲን ሉተር

እውነተኛ ማንነት[ክፍል አንድ]

ooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooo

በተለያየ የትምህርት የኑሮ እና የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ የተለያዩ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ስለ ማርቲን ሉተርና ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ታሪክ ሲጠየቁ በሚገርም ሁኔታ ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆኑት እዚህ ግባ የሚባል እውቀት የላቸውም ፣ ሃያ በመቶ የሚሆኑት ፕሮቴስታንቶች ደግሞ ስለ ሉተር በጥንቃቄ የተመረጡ እውነቶችን ብቻ የያዘ እውቀት አላቸው ፣ ይሁንና የመረጃ ምንጫቸው ድብቅ አጀንዳ ያለውና እንዲያውቁ የተፈለገውን ውሱን መረጃዎች ብቻ የሰጣቸው በመሆኑ እውቀታቸው አድሏዊና አደገኛ ነው ። እነዚህ ወገኖች ዛሬ " የእኔ " የሚሉትን እምነት የተቀበሉት በራሳቸው በጥንቃቄ ከተካሄደ ጥናትና ምርምር ከተገኘ እውቀት ሳይሆን መንፈሳዊ ባዶነታቸውን አይተው በጠባብ መረጃ ምዕራባውያን የፕሮቴስታንት ጽንፈኞች በሞሏቸው ውስን እውቀት ነው ።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ፦

☞ እውነትን ፈልገው ነገር ግን በተቃራኒ አቅጣጫ እየተጓዙ ያሉ ወገኖች ስለ እምነታቸው መስራች ስለ ማርቲን ሉተር እውነተኛ ማንነት እንዲያቁ ማረግ ።

☞ ዓለም አቀፍ የሆኑ ተጨባጭ ማስረጃዎችን መሰረት በማረግ ፕሮቴስታንቲዝም በዓለም ላይ ያስከተለውንና በማስከተል ላይ ያለውን ጥፋት መግለጽ ።

☞ የሚቃወሙንን ዉጤታማ በሆነ መንገድ መቃወምና መመከት የምንችለው ተቃዋሚዎቻችንን ወይም ጠላቶቻችንን በሚገባ ስናውቃቸው

ብቻ ነው አለበለዚያ ግን " በጨለማ መተኮስ " ይሆንብናል ፣ ስለዚህ ጠላታችን ዲያቢሎስ መሳሪያው አርጎ ስላስነሳቸው ተቃዋሚዎቻችን በሚገባ እናውቃቸው ዘንድ በቂ መረጃ መስጠት ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት መረጃዎች ፦

፨ ሉተር ራሱ ከጻፋቸውና ከተናገራቸው ፣

፨ የቅርብ ደቀ መዛሙርቶቹ እረዳቶቹ ስለሱ ከጻፉትና ከተናገሩት ፣

፨ ስለ ሉተር ያጠኑ የታሪክ ፀሐፊዎችና ተመራማሪዎች ከጻፉትና ከተናገሩት የተወሰዱ ሲሆን እነዚህ ዓለም አቀፍ መረጃዎች የሉተርን እውነተኛ ማንነት ለመረዳት እጅግ ጠቃሚ ናቸው ።

ዛሬ በፕሮቴስታንቱ ዓለም የሚታዩት ችግሮች ሁሉ ምንጫቸው ከእምነቱ መስራች ከማርቲን ሉተር ስብዕና የተቀዱና የተወረሱ ናቸው ። የችግሮቹ ምንጭ ከሉተር እውነተኛ ማንነትና ስብዕና የተቀዱና የተወረሱ ናቸው ከተባለ ደግሞ የእምነቱን መስራች የሉተርን እውነተኛ ማንነትና ስብዕና ማወቅ ደግሞ ግድ ይላል ።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና የሰራውን ሥራ ሳያቁ ክርስቲያን መሆን ወይም ስለ ክርስትና ማወቅ ፈጽሞ አይቻልም ፤ ስለ ማርክሲዝም ማወቅ የሚሻ የካርል ማርክስን ሕይወት ፣ ትግልና ትምህርት ለማወቅ ይገደዳል አለዚያ ማርክሲዝምን ማወቅ የማይሞከር ነው ፤ በዓለም ላይ የተፈጠሩ ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊ ወዘተ... እንቅስቃሴዎች ሁሉ ካለ ፈጣሪዎቻቸው (መሥራቾቻቸው) ሕይወት የላቸውም ።

በየዘመኑ ብቅ የሚሉ መሪዎች በጎብረተሰቡ ውስጥ የሚያመጡት ለውጥ እጅግ ጠቃሚና ገንቢ ወይም እጅግ አፍራሽ ውጤት ማስከተሉ በአያሌው

የእነዚህ መሪዎች አስተዳደግ አኗኗር የአካልና የአዕምሮ ጤና እና የሕይወት ልምድ ማወቅን ወሳኝ ያረገዋል ።

ስለ ማርቲን ሉተር እውነተኛ ማንነት ምን ያህል ያቃሉ ? እስቲ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ለዛሬ ጥቂቶቹን ለማየት እንሞክር ፦

1. ሉተር በአዕምሮ አለመረጋጋት ችግር የተዋጠ ግለሰብ ነበር ።

ooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooo ሉተር

ከልጅነት እስከ እውቀቱ በአእምሮ አለመረጋጋት ችግር ሲሰቃይ የኖረ ሰው ነው ። የፈረሳይኛና የጀርመንኛ ቋንቋዎች መምህር ፕሮፌሰር ፒተር ዋይነር ስለ ማርቲን ሉተር የተጻፉ ሁለተኛ ምንጮችን በመጥቀስ Martin Luther, Hitlers Spiritual Ancestor. በሚል ርዕስ ለብዙ ዘመናት በጥቂት ሊቃውንት/Scholars ብቻ ይታወቅ የነበረውን የማርቲን ሉተር እውነተኛ ማንነት

(ጸረ - ክርስትና እና ጸረ - ክርስቶስ

ተልዕኮ) የሁሉም ሰው እውቀት ይሆን ዘንድ ባበረከቱት መጽሐፋቸው ላይ ሉተር በልጅነቱ ዘመን በእናቱና በመምህራኖቹ እየተደበደበ ነበር ያደገው ይሉናል ።

ሉተር ፦ " አንድ ቅንጣት ለውዝ ሰረክ ብላ እናቴ ደሜ እስኪፈስ ገረፈችን " ማለቱንና ትምህርት ቤትም በቀን እስከ አሥራ አምስት ጊዜ ይገረፍ እንደ ነበር ፕሮፌሰር ዋይነር ጠቅሰዋል ።

ይህም አግባብ ያልሆነ ከባድ ቅጣት በዚህ ሕጻን ልጅ ባሕርሪ ላይ ጥቁር ነጥብ ጣለ ። ድንጉጥ ወፍ ዘራሽና ተጠራጣሪ ሆኖ እንዲቀር አደረገው ። የራሱ ጓደኞቹም የመንፈስ ጭንቀት እነደሚያሰቃየውና አዕምሮው ልክ

እንዳልሆነ መስክረዋል ። ሉተር ጠቅላላ ነርቫዊ ቅንባሮው (nervous system) ውጥረት እንደ ነበረበት የሚያጠያይቅ አይደለም ይላሉ ።

ሉተር ገና በልጅነቱ ምንኩስናን የመረጠው ቤተሰቦቹን ጠይቆ ሲመለስ ድንገት በኃይለኛ አውሎ ንፋስ በመያዙና ከአጠገቡ የወደቀ መብረቅም በፈጠረበት ድንጋጤ የተነሳ ከወደቀበት ቦታ ሆኖ ፦

" አውጭኝ አውጭኝ ቅድስት አኒ ከዚህ መዓት ካወጣሽኝ መነኩሴ እሆናለሁ " ብሎ ሳያስበው በጭንቅ July 2, 1505 እ.ኤ.አ መሃላ በመግባቱ ነበር ። ለዚህ ለፈራ ለተደናገጠ ስሜታዊና ያልተረጋጋ ወጣት ምንኩስና እጅግ ከባድ ነበር ብለዋል ፕሮፌሰር ዋይነር ።

ሉተር መነኩሴ ከሆነ በኃላ ከሌሎች መነኩሴዎች ጋር ሆኖ በመጸለይ ላይ እያለ መሬት ላይ ወድቆ " ሰይጣን አልያዘኝም ሰይጣን አልያዘኝም " እያለ ይጮኽ ነበር ፣ ይህን ክፉ የልጅነት ሕይወቱን በሰይጣን ከመጠቃት ጋር አያይዞትና ከእግዚአብሔር የተሰጠ ምላሽ አድርጎ አስቦት ሊሆን ይችላል ። በምንኩስና ዘመኑ ወጣት መነኩሳት ሉተርን በሰይጣን የተጠቃ አድርገው ያዩት ነበር ።

ሉተር ሕይወቱን በሙሉ የአዕምሮ አለመረጋጋት በሽታ ያሰቃየው እንደ ነበር ራሱ ከተላላካቸው ደብዳቤዎች ከጻፋቸው መጽሐፍት ከተናገራቸውና የቅርብ ረዳቶቹ ስለዚህ ሰውዬ ባሕሪ ከተናገሩት ማወቅ ይቻላል ።

ሉተር የነበረበትን የአእምሮ ጭንቀት ራሱን በሥራ በመጥመድ ወይም ከሚገባው በላይ ጊዜውን በጸሎት በማሳለፍ ሁል ጊዜ ነገሮችን ከልክ በላይ በመስራት ሊረሳ መሞከሩ የባሰውን የአእምሮ ህመሙን አባብሶታል ።

ሉተር በሥራው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን መጻረር ብቻ ሳይሆን ፣ ይህን ተጻራሪ

ሐሳቡን በእርሱ ውስጥ ያደረ እግዚአብሔር የሚናገረው እንደሆነ አድርጎ ሰብኳል ። ዛሬ ሀገራችን ውስጥ የፈሉት ተቆጥረው የማያልቁ እርስ በርሳቸው የሚጻረሩ የፕሮቴስታንት ውላጅ ክፍልፋይ አንጃዎች ለሚፈጽሙት ግፍ ሁሉ " ኢየሱስ ነገረኝ " ወዘተ... የሚሏትን ፈሊጥ ከዚህ የፕሮቴስታንት እምነት መሥራች ንግግሮችና ጹሑፎች ቀጥታ የተቀዱ ፣ የተወረሱ ፣ ወይም እርሱን መሠረት ያደረጉ ናቸው ።

ሉተር የአዕምሮ ጤንነቱ እጅግ የተዛነፈ ስለ ነበር ያስተላለፈው መልእክትና ውጤቱም እንዲሁ የተዛነፈ ሆነ ።

ሉተር እድሜውን በሙሉ በተጻራሪና በሁሉም አቅጣጫ በሚስቡት ፣ ሕይወቱን በሚያጥለቀልቁት የሥጋ ፍላጎቶችና በማይፈልጋቸው ስሜቶች መዋጡ ፣ ከእግዚአብሔር መራቁ በሚፈጥርበት ጸጸት የተዋጠ የውጊያ አውድማ ነበር ።

በ 1521 እ.ኤ.አ ይህንን የውስጥ መረበሽ በሚመለከት ሉተር ፦

" በቃ ጸሎትን ችላ ከማለቴም በላይ አንዴ እንኳን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን አልናፈቅሁም ፤ ከቁጥጥር ውጭ በሆነው ሁሉም አይነት ወሲባዊ አምሮት እየጋየሁ ነው ። በመንፈስ ኃይል መሞላት ሲገባኝ በወሲባዊ አምሮት ፣ በጉምጀታ ፣ በስንፍና በሥራ ፈትነትና በእንቅልፋምነት ተውጫለሁ " ብሎ ነበር ። [page 20]

የሉተርን የአእምሮ ህመም ፦ የሉተር የሕይወት ታሪክ ጸሐፊው ፈንክ ብሪንታኖ

" የሚያደርጉትን የሚያሳጣ ቅዠት " ብለውታል ። ፕሮፌሰር በስኮህን ደግሞ ሉተርን " አዕምሮውን የሳተ " ይሉታል ።

[as quated from Luther 's Letters , Enders edition V.3 p.189]

2. ሉተር ሰይጣንን እንደ ማምለጫ ተጠቅሞበታል ።

ooooooooooooooooooooooooooooooooooooooo

የሉተር የአዕምሮ መበጥበጥና ራስን የመሳት ምልክቶች በዚህ የተገቱ አልነበሩም ። ሉተር ከእርሱ ጋር ያልተስማማ በእርሱ አዲስ " ሃይማኖት " ያላመነን ሰው ወይም ማንኛውም ደስ ያላለውን ነገር ሁሉ ለመግለጽ የሚጠቀምበት ቃል " ከሰይጣን ነው " የሚል ነበር ።

ዛሬ የፕሮቴስታንቲዝም ፍልስፍና አብዮት የተቀበሉ ኢትዮጵያውያን ጥቁር ፕሮቴስታንቶች ፕሮፓጋንዲስቶች የማያውቁትንና የማይፈልጉትን ሁሉ " ከሰይጣን ነው " የማለትን ጣጣ የተማሩት ከዚህ ሰውዬ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ ስብከት ነው ።

በማነበራዊ ግንኙነቱ ፣ በንግግሩ ፣ በጽሑፉና በሰበካው ዘወትር ዲያቢሎስን ማንሳት ከሉተር ባሕሪዎቹ ውስጥ አንዱና ዋንኛው ነበር ። በመጽሐፍ ቅዱስ ከተፈቀደው ፣ ከሚገባው በላይ ለሰይጣን ኃይልና ዋጋ የሰጠ ሰው ነበር ።

ሉተር በሰይጣን መንፈስ የተመራ ሰው እንደ ነበር የበለጠ ግልጽ የሚያደርገው እንዲህ ማለቱ ነው ፦ Satan sleeps with me much more than my wife does / ከሚስቴ ይልቅ ሰይጣን አብዛኛውን ጊዜ አብሮኝ ይተኛል ። Martin Luther, Hitlers Spiritual Ancestor. [page 22]

3. ሉተር ጠላቶቼ የሚላቸውን ለመቃወም ጸያፍና ወሲባዊ የሆኑ ቃላትን በሰፊው ተጠቅሟል ።

ooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooo

ትልቅ " የእግዚአብሔር " ሰው ነኝ ከሚል የማይጠበቅ ጸያፍ ቃላትን እንደ አባት ገዳይ የሚጠላውን የካቶሊክ ሮማዊ ቤተ ክርስቲያን ለመስደብና ሕዝብንም በዚች ቤተክርስቲያን ላይ በጥላቻ ለማነሳሳት በገፍ ተጠቅሟል ። ሌላው ቀርቶ የሉተር የራሱን ሀሳብ ፣ ሕግ ወዘተ...ተጠቅመው የተቃወሙትን አድናቂ ተከታዮቹን አልማረም ። በራሳቸው አይሁዳዊ ሃይማኖት መጽናት የፈለጉትንና ፕሮቴስታንቲዝምን ለመቀበል ፍቃደኛ ያልሆኑ የጀርመን ቤተ እስራኤላውያን ለማመን በሚያስቸግሩ አሰቃቂ ቆሻሻ ቃላት ዘልፏል ። ሉተር ለእሱ አዲስ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም የማይመቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ነብያትን እና ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይቀር ለመቃወምና ለማዋረድ አጸያፊ ቃላትን የተጠቀመ ሰው ነው ።

አድናቂውና ተከታዩ የነበሩት ሚቡሊንገር ሉተር በተከታዮቹ ላይ ያሳደረውን ክፉ ተጽዕኖ ሲናገሩ ፦ " በጣም ብዙ ሰባኪያን ከሉተር መጽሐፍት ላይ የሰበሰቡትን ጸያፍ የስድብ መዝገበ ቃላት በየቤተክርስቲያኑ መቅደስ ቆመው ይነዙታል ... በአሁኑ ጊዜ ጥሩ የኢቫንጀሊካል ሰባኪ መሆን የሚፈልጉ ሁሉ ሰበካቸው በጸያፍ ስድብና ዘለፋ የታጨቀ መሆኑ አግባብ ይመስላቸዋል " በማለት ገልጸውታል ።

Janssen Johannes , History of German people. 1910, V.3 p.211

ዘረኛው ሉተር ቤተ እስራኤላዊያንን በጓደኝነት መቅረብ የሚፈልግ ጀርመናዊ ፕሮቴስታንት መዘረፍ ፣ መዋረድ ፣ መጎዳት የሚፈልግ ብቻ

መሆን አለበት ብሏል ። ቀጥሎም ጉዳቴ አነሰኝ የሚል ፕሮቴስታንት የሚከተለውን እንዲያደርግ ፕሮቴስታንታዊ ምክሩን ሰጥቷል ፦ " ይህ በቂ ካልሆነ የቤተ እስራኤሎችን አፍ እንደ ሸንት ቤት እንዲጠቀምበት ይጠይቃቸው ወይም ወደ ቤተ እስራኤሎች ፊንጢጣ ውስጥ ይግባና ያን ቅዱስ ነገር ያምልክ " በማለት አሳፋሪና አስነዋሪ ንግግሮችን ተናግሯል ።

ዛሬ በየፕሮቴስታንቱ የጸሎት ቤቱ የሚወርደውን የዘረኝነትና ጸረ ኢትዮጵያዊ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የጥላቻ ስብከት ከየት የመጣና የተቀዳ ይመስልሃል ?

የሉተርን ጸያፍ ፣ ዘረኛ ፣ በጥላቻ የተመረዘና ሀላፊነት የጎደለው ጽሑፎቹንና ሕዝባዊ ንግግሮቹን ያጠኑት ደራሲ ማርቲን እንዲህ ሲሉ ቃላቸውን ሰጥተዋል " ሉተር በጸያፍና ወሲብ ነክ በሆኑ ቃላት የተለከፈ ይመስላል ፤ በል ሲለው በጣም ይናደዳል ፣ ሲናደድም በጥሩ እንግሊዘኛ ሊገለጹ የማይችሉ ጸያፍ ቃላትን ያስታውክ ነበር " ብለዋል ። Peter F. Wiener.

[page 20]

ሉተር ከውጭ ወደ ውስጥ ከመጠን በላይ የሚወስደው መጠጥ ብቻ አልነበረም የሚያረክሰው ከውስጥ ወደ ውጭ የሚያወጣው እጅግ መራራና እጅግ

ኢ- ክርስቲያናዊ የቃላት አመራረጡ ጭምር እንጂ ፣ ሉተር የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን " የዲያብሎስ ሸርሙጣ ቤተ ክርስቲያን " ሲል አስከፊ በሆነ መልኩ ይገልጻታል ።

Grisar Hartmann , Luther translated. 1917

ሉተር ከ 5 መቶ አመት በፊት የነበሩትን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስን ፦

" ዋሾ ፣ እብድ ውሻ ፣ ሕይወት አጥፊ ፣ ነፍሰ ገዳይ ፣ የለየለት አጭበርባሪ ፣ ቆሻሻ አሳማ ፣ የዲያብሎስ ልጅ ፣ ምን ይህ ብቻ ሰይጣን ራሱ ነው እንጂ " በማለት ነበር የዘለፋቸው ። " [page 302]

የ " ገድል ወይስ ገደል " ደራሲ ፋሽስታዊና ሉተራዊ በሆነ ስልቱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እያበሻቀጠ የሸፍታዎችና የነፍሰ ገዳዮች ዋሻ ወዘተ... እያለ መስደቡን ታስታውሳለህ ?

ቅድስት ቤተክርስቲያንን ደንቆሮ ፣

ጸረ - ሕዝብ ፣ ኃላ ቀር ፣ ጣኦት አምላኪ ፣ ኦሪታዊ ፣ ኮተታም ወዘተ ... እያሉ የሚሳደቡ ሰዎች የማን ልጆች መሰሉህ ? ስድቡ አልበቃ ብሎ የእመቤታችንን ፣ የቅዱሳንን ስዕል አንዴ እየዘቀዘቁ ፣ አንዴ በእግራቸው እየረገጡ የሌላውን ሃይማኖት መብት የሚነኩ እኩይ ተግባራትን የሚፈጽሙ ፣ የሚያንቋሽሹና የሚያዋረዱ እነዚህ ሰዎች ይህንን ድፍረት ከማን የተማሩት በማንስ መንፈስ የሚንቀሳቀሱ ይመስልሃል ?

ዛሬ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በጸያፍ አንደበታቸው የሚያረክሷት ፣ በክርስትና ብቻ የ 2 ሺ ዘመን ልምዷን ፣ እውቀቷን ፣ ጥበቧን ፣ ሥነ ጽሑፏን ፣ ዜማዋን ፣ የጊዜ ቀመሯን ፣ ሳይንሳዊ መንፈሳዊና ሀገራዊ ዉለታዋን ክደው በድንቁርና የሚከሷት ያልተረጋጋ መንፈስ ያላቸው እነዚህ ጥቁር ጀሀደኞች በሉተር መንፈስና ኃይል እንደሚንቀሳቀሱ ሥራቸው ምስክር ነው ።

ማቴ 5 : 22 እንዲህ ይላል ፦

" በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል .... ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነም እሳት ፍርድ ይገባዋል ። "

4. ሉተርና ደም ፍላት

ooooooooooooooooooooooooooooooooooooooooo

ሉተር ለደም ፍላት ያለውን ፍቅር በቴብል ቶክ / Table Talk የንግግር ስብስቦቹ ላይ እንደተዘገበው በኩራት እንዲህ ይላል " ደም ፍላት ጠቅላላ እኔነቴን እንደማነቃቂያ ሆኖ ያገለግለኛል ፣ ችሎታዬን ይስለዋል ፣ ሰይጣን እንዳይጠናወተኝ ይረዳኛል ፣ በተጨማሪም ፍርሃትን ያባርርልኛል ፣ ከሌላው ጊዜ ይልቅ በደም ፍላት ጊዜ የምጽፈውና የምናገረው በጣም ውጤታማ ነው ። መግጠም ፣ መጻፍና መጸለይ ከፈለኩኝ ደም ፍላት ውስጥ መሆን አለብኝ ።" [page 22]

በመሰረቱ በክርስትና እምነት ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሃይማኖት ውስጥ ደም ፍላትና ብስጩነት የተከለከለ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ " የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ይሁን ፣ የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሰራምና" ይላል ። ያዕ 1 : 19 - 20

በደም ፍላት ጊዜ የሚታሰቡና የሚፈጸሙ ነገሮች ሁሉ ውጤታቸው አስከፊ ነው ፤ የሉተር ሃይማኖት (አብዮት) ፕሮቴስታንቲዝም በደም ፍላት ሰዓት ታስቦና ተጸንሶ የተወለደ ሲሆን አስከፊ ውጤቱና ያስከተለው ማህበራዊ ቀውስ ለዚህ ምስክር ነው ። አሜሪካኖች " ቁጣ " በእብደት ጀምሮ በጸጸት ያልቃል የሚል አባባል አላቸው ነገር ግን ሉተር በስህተቶቹ ብዙም የሚጸጸት

ሰው አልነበረም ።

5. ሉተር አመክንዮ / reason / የሚጠላ ሰው ነበር ።

ooooooooooooooooooooooooooooooooooooooo

ሉተር ስሜታዊ የሆነ ሰው እንጂ ምክንያት ያለው የሰከነ ግንዛቤ የሌለውና ይህንንም የማይወድ ሰው ነበር ። ስለ መረጋጋት ፣ ስለ ግንዛቤ ስለ ምክንያታዊነት ፣ በተለይም ስለ አመክንዮ ያለውን ንቀት በራሱ አንደበት ሲናገር ፦

" አመክንዮ የሰይጣን ታላቅ ሴተኛ አዳሪ ናት ፣ በተፈጥሮዋና በአኳኋኗ አስከፊ ሴተኛ አዳሪ ናት ፣ ሸርሙጣ ናት በዲያቢሎስ የተሾመች ሴተ አዳሪ ። አዎ በቁስልና በቁምጥና የተወረሰች ፣ ከእግር ስር ተጥላ መረገጥና መክሰም ያለባት ሴት አዳሪ ... አስቀያሚ ትሆን ዘንድም ፊቷ ላይ ፋንድያ ለጥፉባት ፣ በምትጠመቅበት ውኃ ውስጥ ሰምጣ መሞት አለባት ። .... መከራ ይገባታል ፣ በቤት ውስጥ በሚገኘው እጅግ ቆሻሻ ወደ ሆነው ቦታ ወደ ሽንት ቤት ልትገፋ ይገባታል " ብሏል ። Peter F. Wiener [page 23 - 24] / as quated from Erlangen v. 16 p. 142 - 148

የታወቁት ፈላስፋ ሚስተር ማርቲን የሉተርን ጸረ - አመክንዮ / ጸረ-ምክንያታዊ

ባሕሪ ሲገልጹ ፦ ጸረ - ምክንያታዊ የሆነው የሃይማኖት አስተሳሰቡ የብዙዎችን ጭንቅላት የመረዘ ነው ... ሉተር አሰልቺና አስቸጋሪ ከሆነው የአዕምሮን የማስብ ችሎታ ከመጠቀምና ሁሌም ተገቢ በሆነ መንገድ ነገሮችን ከማገናዘብ ሀላፊነት ' የተገላገለ ' ሰው ነው ይሉታል ።

ጆነስ ዲሸሊዮ ቲ ፦ ሁሉም ነገር ከራሱ የግል የማይጨበጥ ሃሳብ ጋር ከተጋጨ አይቀበለውም ይሄ ደግሞ ምክንያታዊነት የሚጎለውና የክርስትናን አንድነት የሚበትን ነው " በማለት የሉተር ሃይማኖት ያደረሰውን ቀውስ The History of Philosophy. በሚለው መጽሐፋቸው በትክክል ገልጸውታል ።

ሉተር በቀላል ምርምር ሊደረስበት የሚቻለውንና የሚገባውን አመክንዮን መካዱና ሰው ዝም ብሎ በደመ ነፍስ ብቻ የመሰለውን እንዲያምንና እንዲከተል ማስተማሩና መፍቀዱ ጸረ - አንድነትና ጸረ - ክርስትና የሆኑ ሃይማኖቶች እንደ አሸን እንዲፈሉ መንገዱን ከፍቷል ።

ፕሮቴስታንቲዝም / ሉተሪዝም / እውቀትንና ምክናያታማነትን ይቃወማል ።

ነገር ግን ክርስቶስም ሆነ ሐዋርያት ሁሉን መርምረን ፈትነን መልካም የሆነውን እንድንይዝ እንጂ እውር ድንብሩን ሁሉ በጭፍን ዝም ብለን እንድናምን አላስተማሩም ።

" በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው።" ሐዋ 1:3

እንደሚል " በብዙ ማስረጃ " እንጂ

" በጭፍን እምነት " የተሰበከ ክርስትና የለም ።

6. ሉተር የወጣለት የሃይማኖት ትምክህተኛ ነበር ።

ooooooooooooooooooooooooooooooooooooo

ይቀጥላል .....

ያለሱ ሌላ አምላክ ለሌለ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።

ሰውን ወዳጅ የምህረት አማላጅ ቅዱስ ሚካኤል አይለየን ።

✝ ሚካኤል ዘየካ ✝

ምንጭ ☞ የገሃነም ደጆች ፕሮቴስታንታዊ ጅሀድ በኢትዮጵያዊነት - ተዋሕዶነት ላይ ሲፋፋም

✍ በእሱባለው በለጠ

1 ኛ. መጽሐፍ በ 1997 ዓ.ም የታተመ

ምስጋና ፦ ይሄንን መጽሐፍ አንብቤ ለወንድሞቼ እንዳካፍላቸው ከክፍለ ሀገር ድረስ መጥተህ መጽሐፉን በመስጠት ለተባበርከኝ ወንድሜ ከፍ ያለ ምስጋና ላቀርብልህ እረልጋለሁ እግዚአብሔር ይስጥልኝ በጣም አመሰግናለሁ ።

Enat Mulatu

:::::Share share በማረግ ግደታዎን ይወጡ:::::::

84/ “ያዳነኝ ኢየሱስ ነው፤ማርያም አላዳነችኝም፤”ለሚሉ፡- ቤተ ክርስቲያን፡-ማንንም ቢሆን “ኢየሱስ አላዳነህም፤” ያለችበት ጊዜ

የለም።ያልተጻፈ ማንበብ ፥ያልተነገረ ማስተጋ ባት የተሀድሶ መናፍቃን ቋሚ ሥራ ነው።መነሻቸውም መድረሻቸውም ሐሰት ነው። በቤተ ክርስቲያን፡-የኢየሱስን አዳኝነት መስበክ አዲስ ግኝት አይደለም።በቤተ ክር ስቲያን የኢየሱስ አዳኝነት፡-ከንባብ አልፎ የትርጓሜ ትምህርት ነው፤በኦሪቱ የነበረው ምሳሌ፥በነ ቢያቱ የተነገረ ትንቢት እየተተረጐመ የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በምልዓት ሲሰበክባት የኖረች የምትኖርም ቤተ ክርስቲያን ናት።መዝሙሩ፥ቅዳሴው፥ማህሌቱ፥ከዕጣነ ሞገር ጀምሮ ቅኔው የሚሰብከው የኢየሱስን አዳኝ ነት ነው።በነገረ ማርያምና በነገረ ቅዱሳንም ውስጥ የምናገኘው የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ነው።ገድላቱና ተአምራቱ የሚ ነግሩን፥ቅዱሳኑ ወንጌልን እንዴት ሕይወት እንዳደረጉት ነው።አዳኛቸውን ኢየሱስ ክርስቶስን፡-ሁሉን ትተው እንዴት እንደ ተከ ተሉት፥በስሙ እንዴት ከዓለም ፈጽመው እንደተለዩ፥ስለ ስሙ እንዴት እንደተጋደሉና ለአክ ሊለ ሕይወት እንደበቁ ይነግሩናል።የወንጌልን ቃል ስናይ በሰው አቅም የሚፈጸም አይመስ ልም፥ገድለ ቅዱሳንን ስናነብ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉ እንደሚቻል ይሰብኩናል።“ኢየሱስ አዳኝ ነው፤”ብለው የሰበኩት በቃል ብቻ ሳይሆን በሕይወትም ጭምር እንደሆነ ይነግሩናል ።ከውዳሴ ማርያም ጀምሮ ያሉት የጸሎት መጻሕፍትም፡-ሁሉም የሚሰብኩት ኢየሱስ ክርስቶ ስን ነው።ለምሳሌ፡-የሰኞ ውዳሴ ማርያም ገና ሲጀ ምር፡-“ጌታ ልቡ ያዘነና የተከዘ አዳምን ወደ ቀድሞ ቦታው ይመልሰው ዘንድ ወደደ፤ቅድስት ሆይ፥ ለምኝልን።ከድንግል ያለ ወንድ ዘር በሥጋ ተወለደና አዳነን።”ይላል። -የተሀድሶ መናፍቃን ትልቁ የክህደት መጀመሪያቸው፥እንደ አባቶችቸው ሉተራውያን ለምን? የቅድስት ድንግል ማርያም ስም ይነሣል የሚለው

ነው።መጨረሻቸው ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስን የባህርይ አምላክነት መካድ ነው።(ማኅበረ ቅዱሳን የመውደድና የመጥላት ወይም በሃይማኖት አንድ ሆኖ በሥርዓት የመለየት ጉዳይ አይደለም፤ጉዳዩ፦እነርሱ፦-ኦርቶዶ ክሳዊ ሃይማኖታቸውንና ሥርዓታቸውን ክደው ፍጹም ፕሮቴስታንት የመሆናቸው ጉዳይ ነው።ይኸ ሁሉ ጫጫታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳይሰበክ ቀርቶ ሳይሆን÷ለምን እንደ ፕሮቴስታንቱ አማላጅ አላልነውም ነው።)በመሠረቱ የእመቤታችን ስም የማይጠራበት ክርስ ትና ወይም ጌታን ከእመቤታችን÷እመቤታችንንም ከጌታ የሚለይ የክርስትና ት/ት የለም።ታላቁ የቤተክርስቲያን አባት÷ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ በነገረ ማርያም ትምህርታቸው፦-“ለማንኛ ውም ክርስቲያን ይልቁንም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለሚከታተል የሃይማኖት ሰው÷የድንግል ማርያም ሕይወትና የቤተ ክርስቲያን አመሠራ ረት እንግዳ አይሆንበትም።ይህም ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ፦ከሷ መወለዱና መወለዱም እኛን ለማዳን ብቻ መሆኑ ከታ ወቀ÷የሰውን ልጅ የመዳን ቀን ከሰው ልጆች በቅድሚያ ያወቀች÷ለእግዚአብሔር የማዳን ሥራ መሣሪያ በመሆን አዳኙን መሲሕ የወለደች÷ለእግዚአብሔር ታማኝ የምሥጢር መዝገብ ናትና ነው።በመዳን ት/ት (setereology) የእመቤታችን ሕይወት ከእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ጋር የተዋሐደ ነው።(ነገረ ማርያምን ከነገረ ክርስቶስ ፈጽሞ መለየት አይቻልም)።ስለዚህ በቤተ ክርስቲያናችን፦-ድንግል ማርያም ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ሆና ትከበራለች።በመዝሙራ ችንም ሆነ በቅዳሴያችን ከስመ ሥላሴ ቀጥለን የምንዘምረው የድንግል ማርያምን ውዳሴ ነው። አምላክ ሰው በመሆኑ ለሰው ልጆች የዋለውን ውለታ፦-ስደቱን÷መንከራተቱን÷ስቅለቱንና

ሞቱን በምናስታውስበት ጊዜ ድንግል ማርያምን ለመለየት አይ ቻልም።ወልዳ ያስገኘች ናት፥ አዝላ የተሰደደች ናት፥በማስተማር ጊዜው አብራ ተንከራትታለች፥በተሰቀለበት ዕለት ከመስቀሉ ሥር አልተለየችም።ይህ ሁሉ የሚያሳየው እመቤታችን የሰውን ልጆች ለማዳን ከተደረገው ጉዞ አለመለየቷን ነው ።"ብለዋል።ይህ የማይነቃነቅ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ት/ት ነው።ይህን የያዘ ኦርቶዶክሳዊ ነው፥ያልያዘ ደግሞ ፈጽሞ አይደለም። -"ያዳነኝ ኢየሱስ ነው፥ ስለዚህ የድንግል ማርያም ስም አይነሣብኝ፥ቢነሣም ሕዝቡ ጴንጤ እን ዳይለን ትንሽ ለሽ ፋን ያህል ብቻ ይሁን፤" ማለት አይቻልም።ሰይጣን የምዕራቡን ዓለም፥- በመጀመሪያ፥-"ኢየሱስ ብቻ፤" አሰኝቶ፥ከድንግል ማርያምና ከቅዱሳን ለያቸው።ቀጥሎም "ኢየ ሱስ አማላጅ ነው፤" አሰኛቸው፥በመጨረሻም፥- በእነርሱና በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል ያለውን የፈጣሪና የፍጡር ልዩነት አጥፍቶ፥"ጓደ ኢየሱስ፤" አሰኝቶ፥ከርሱም ለያቸው።እነርሱንም አዳራ ሾቻቸውንም ባዶአቸውን አስቀራቸው።ይህን እውነት ማንም ማስተባበል አይችልም።ምናል ባት ለጊዜውም ቢሆን ሰይጣን እንዴት የኢየሱ ስን ስም ሊያስጠራ ይችላል? ይባል ይሆናል። ነገር ግን በማቴዎስ ወንጌል ላይ፥- ሰይጣንን፥-"ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ፤" ሲል እናገኘዋለን።ማቴ፥ ፰፥፳፱።ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም፥-"አጋንንት ደግሞ ያምናሉ፥ይንቀጠቀ ጡማል፤"ብሎአል።ያዕ፥፪፥ ፲፱።ስለዚህ እኛ የምናየው የኢየሱስ ስም መጠራቱን ወይም "በኢየ ሱስ እናምናለን፤"መባሉን ብቻ ሳይሆን "ማነው የጠራው? እንዴትስ ነው የሚያምነው?"የሚለ ውን ጭምር ነው። -የድኅነት ነገር ከተነሣ፥"እንዴት ነው ያዳነን?" የሚለው ነገርም የግድ አብሮ

ይነሣል።የመጀመሪ ያው፡-“ከሰማይ ወርዶ፥ያለ ዘርዓ ብእሲ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፥ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ አዳነን፤” የሚለው ነው።የተወለደውም ከድንግል ማርያም የነሳውን ሥጋና ነፍስ ተዋ ህዶ ፍጹም ሰው በመሆን ነው።በመሆኑም፡-ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፡-የዕለት ፅንስ ሆኖ በማኅፀነ ድንግል ማርያም የጀመረውን የማዳን ሥራ በመስቀል ላይ በመፈ ጸም አድኖናል ፥ብለን እናምናለን።“ድኅነታችን በመስቀል ላይ እንዴት ተፈጸመ?” የሚለው ደግሞ፥ቅንነቱ ካልጠፋ ወይም ኅሊና ካልታወረ በስተቀር ለማንም ግልጥ ነው።በመስቀል ላይ ፡-ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ፥ክቡር ደሙን አፍስሶ፥ቅድስት ነፍሱንም አሳልፎ በመስጠት ነው።ይህ የዳንበት፥መለኰት የተዋሀደው ሥጋ፣ደምና ነፍስ የተገኘው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ነው። ታድያ፡-“በድኅነታችን ውስጥ የእመቤታችን ድርሻ የለም፤” እንዴት ይባላል? “ያዳነኝ ኢየሱስ ነው፥የማርያምን ስም አትጥሩ ብኝ፤”የሚለው ከየት የመጣ ነው? የማርያምን ስም እኮ ቅዱስ ገብርኤል ጠርቶታል፥ከሁሉም በላይ የጌቶች ጌታ፥ የነገሥታት ንጉሥ፥የአማል ክት አምላክ፥የፍጥረታት ፈጣሪ የሆነ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ጠርቶታል።ብፁዕ አባታችን አቡነ ጎር ጎርዮስ ካልዕ እንዳሉት፡-“እግዚአብሔር ለማዳን ሥራው መሣሪያ አድርጓታል፥የእመ ቤታችን ሕይወት ከእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ጋር የተ ዋሀደ ነው።” - አንዳንዶች “በመስቀል ላይ የተቆረሰው የኢየሱስ ሥጋ እንጂ የማርያም ሥጋ አይባልም፤” ብለው ጅል ክርክር ለመ ከራከር ይሞክራሉ።ይህም ድንግል ማርያምን ያሳነሱ እየመሰላቸው ነው።መናፍቃንም ዙሪያውን እያጨበጨቡላቸው ነው። ነገር ግን ከንቱ ድካም ነው።ምክንያ ቱም ኢየሱስ

ክርስቶስ ድንግል ማርያምን ከፍ አድርጐ አንድ ጊዜ እናቱ አድርጐአታል፥ ወርቅ አልብሶ፥ወርቅ አጐናጽፎ በቀኙ አቁሞአታል።በመሆኑም ማንም ድኩም ተነሥቶ ዝቅ ሊያደር ጋት አይችልም። መዝ፡፵፭ ፥፱።ኧረ ለመሆኑ፡- እንዴት ነው? የእሱ ሥጋ፡-የእሷ፥የእሷ ሥጋ ደግሞ የእሱ የማይባለው? የእናትና የልጅ ዝምድና ከልደት በኋላ ይቋረጣል እያሉን ነው?ወይስ ምን ለማለት ነው? ለምሳሌ፡-የሔዋን ከአዳም ጐን መወለድ ለክርስቶስ ከድንግል ማር ያም መወለድ ምሳሌ ነው።ታድያ አዳም ሔዋንን፡- ከጐኑ ከተወለደች በኋላ ለምን ሥጋዬ አላት? ዘፍ፡፪፥፳፫። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስን፡-“ልጄ ሆይ፤” ትለው የነበረው እኮ ፍጹም ሥጋዋ በመሆኑ ነው። ሉቃ፡፪፥፶፭።እነዚህ ሰዎች እርሱን ከርሷ ለመለየት ይኸንን ያህል መከራ ማየታቸው በሥጋም ሆነ በነፍስ ሚዛን ሲታይ የጤና አይደለም ።ለእነርሱ ከጌታ እናት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ይልቅ የሚበልጥባቸው ኦር ጋን ነው። እነዚህ ለኦርጋን የተንጫጩ ሰዎች፥እመቤታችን በየብሎጉ እና በየፊስ ቡኩ ስትሰደብ አንድም ቀን መልስ ሰጥተው አያው ቁም።ነገር ግን “ቅዱስ ኦርጋን” ተነካ ብለው ሰሞኑን ጩር ቃቸውን ጥለው ሊያብዱ ነው።እመቤታችን ስትሰደብ መልስ የማይሰጡበት ምክንያት ግን ለጥ ቂቶች ካልሆነ በቀር ለብዙዎች ግልጥ ነው።ፎኛ/ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ስላልሆኑ ነው፤ ፎኛ/በብ እር ስም ተሸፍነው እመቤታችንን እየሰደቡ የሚጽፉት እነርሱ ራሳቸው ስለሆኑ ነው። -ቤተ ክርስቲያን፡-እመቤታቸችንን ምክንያተ ድኀን(የመዳኛ ምክንያት) ብላ እንጂ በመስቀል ተሰቅላ አዳነችን ያለች በት ጊዜ የለም።እግዚአብሔር፡-የኖኅን መርከብ ምክንያተ ድኀን አድ ርጐ ኖኅን እና ቤተሰቹን እንዳዳነ

እመቤታችንን ምክን ያት አድርጐ ዓለምን አድኖአል።ብፁዕ አባታችን እንዳሉት፡-“በመዳን ት/ት (setereology) የእመቤታችን ሕይወት ከእግዚአ ብሔር የማዳን ሥራ ጋር የተዋሀደ ነው።”በመሆኑም እመቤታችንን ከሕይወቱ ያስወጣ ሰው፡- “ኢየሱስ አድኖኛል፤”ማለት አይችልም።ለመሆኑ፡- እናቱን ሲያቀሉበት፥ከቤት ልቡናቸው በጥ ላቻ ሲያስወጧት፥ስሟን እንኳ ለመጥራት እየተጸየፉ፥ጌታን ማስደሰት ይቻል ይሆን? ክርስት ናን ለመስበክ ከቤተ ልሔም የከብቶች በረት ተነሥተን እስከ ቀራንዮ ብንጓዝ፥ከዚያም አልፈን ወደ ሰማይ ብንወጣ እመቤታችን የሌለችበት ይኖር ይሆን?“በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋ ፍና(በንጽሐ ሥጋ፥በንጽሐ ነፍስ፥ በን ጽሐ ልቡና ጸንታ) ንግሥቲቱ (የሰማይና የምድር ንግ ሥት ድንግል ማርያም) በቀኝህ ትቆማለች፤”ይላል።መዝ፡፺፬፥፱ ።

እግዚአብሔር አምላክ እረጂም እድሜን ከሙሉ ጤና ጋር ለነዚህ ድንቅ አባቶች ይስጥልን።

Internet added 3 new photos .

85/ ዮዲት ጉዲት (Yodit Gudit) ማን ናት?

ከክርስቶስ ልደት በኋላ ፡ በአንደኛው ክፍለ ዘመን

መጀመሪያ በንግሥት ህንደኬ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ
የገባው የጥምቀት ዜና በአራት ኛው ክፍለ ዘመን
በአብርሃና አጽብሐ ዘመነ መንግሥት በአባ ሰላማ
ከሣቴ ብርሃን ስብከት ተስፋፍቶ አብዛኛው
የኢትዮጵያ ሕዝብ ስብከተ ወንጌልን አምኖ
ጥምቀትንና ክርስትናን ተቀበለ። እጅግ በጣም
ጥቂት የሆኑ የአይሁድ (ጁዳይዝም) ሃይማኖት
አማኞች በወንጌል አናምንም ክርስቲያን አንሆንም ፣
ሕገ ኦሪትን አንለቅም በማለት በ፱፻፹፪ (982) ዓ.
ዓለም ግደማ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን የመጣውን
እምነተ እሥራኤል መከተልን ቀጠሉ።
የክርስትና ሃይማኖት አንቀበልም ብለው በአይሁድ
(የኦሪት) እምነታቸው የፀኑት ሕዝቦች በነገሥታቱ
ትእዛዝ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከሆነችው
ከአክሱምና ከዙሪያዋ አየለቀቁ በመውጣት
በወልቃይት፣ በሰሜንና ፥ በወገራ ፣ በደምቢያ ፥
ዛአገው ፥ በላስታ ፥ በሰቆጣና በመሳሰሉት ሊኖሩ
እንደሚችሉ ስለ ተገለጸላቸው አክሱምንና
አካባቢዋን እየለቀቁ በመሔድ ተበታትነው ይኖሩ
ጀመረ ። በዚህ ምክንያት ፈላሻ ተባሉ ። ፈላሻዎች
እምነታቸው ሕገ ኦሪት ቢሆንም ኢትዮጵያዊነታቸው
የተረጋገጠ ስለሆነ ፥ በመንግሥት ትእዛዝ

በተፈቀደላቸውና በሚኖሩባቸው በሰሜንና በላስታ

እንዲሁም በተለያዩ ሥፍራዎች ለረዥም ጊዜ

በመኖር ቁጥራቸው እየበዛ ሔደ ። የሕዝቡ ቁጥር

አየበዛ ሲሄድም ለአክሱም መንግሥት ግብር

እየከፈለ በሰላም ይኖር ጀመር።

ዮዲት ጉዲት

በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ፹፱፺፪ (852) ዓ.ም

ገደማ ዮዲት የተባለችው የጌዴዎን ልጅ ንግሥት

ዘሯ ከፈላሻ ውስጥ በመሆኑ ፈላሾችን ይዛ ተነሣች።

በላስታ የሚኖር የክርስትያን ሃይማኖት ተከታይና

የቡግና ባላባት በዮዲት ውበትና ኃይለኛነት

ስለተማረከ ሃያማኖቱን ለውጦ አገባት። በዚህም

ምክንያት ተጨማሪ ኃይል ለማግኘት ቻለች ።

በዚህ ዘመን በአክሱም ዙፋን ላይ የተቀመጠው

የንጉሥ ድግናዣን ልጅ አንበሳ ውድም ነበር ።

አንበሳ ውድም አባቱ ሲሞት ገና የዐሥራ ሁለት

ዓመት ልጅ ቢሆንም የንግሥና ሥልጣኑን ያዘ።

ዮዲትም ንጉሡ ገና ሕፃን ስለሆነ የሚን ጥቃት

የሚቋቋም ኃይል ሊያሰባስብ እንደማይችል

በመገመት አጋጣሚውን ተጠቅማ ልትወጋው

አሰበች ።

በዚያን ጊዜ አክሱም የእስልምናን ሃይማኖት

ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት የተነሣ ጠረፎቿ
በመወረራቸው በቀይ ባሕር የነበራትን የበላይነት
ያጣችበት ወቅት ነበር ። ይህች የክርስቲያን ባላጋራ
የሆነች ንግሥት ፈላሾች የሆኑትን ሁሉ በአንድነት
አስባስባና አሥተባብራ የአክሱም ንጉሥ አንበሳ
ውድምን ለመውጋት ተነሣች ። ከላስታ ፣ ስሜንና
ወልቃይት የተሰበሰቡትን ፈላሾችና ሌሎችም
ቀሥቅሣና አስፈራርታ በማሥነሣት ብዙ ሠራዊት
እየመራች ወደ አክሱም ዘመተች ። ወደ አክሱም
በምትጓዝበት ጊዜ ያለፈችበትን ሥፍራ ሁሉ ሠራዊቷ
ይመዘብርና ያጠፋ ነበር ። አብዛኛዎቹ አብያተ
ክርስቲያናትና ሌሎችም ውድ የሆኑ የባህል ቅርሶች
የተቃጠሉትና የወደሙት በዮዲት ጭካኔ የተሞላበት
ወረራ ነበር ። ብዙ ጊዜ አምረውና ደምቀው ግርማ
ሞገስ የነበራቸው አብያተ ክርስትያናትና ሐውልቶች፣
ጭራሽ ከወደሙት ሌላ ለታሪክ ምሥክርነት በእሳት
ጋይተው ፍርስራሻቸው ብቻ የሚታየው ብዙ ናቸው።
በዮዲት ጉዲት ወድሞ በ□ላ በንግስት እሌኒ ታድሶ
የነበረው የአብረሃ ወ ዓጽብሃ ቤተክርስትያን፣ መር
ጡለ ማርያም፣ ጎጃም
ብዙ ክርስትያኖች ሲጨፈጨፉና የቀሩትንም
በታላቅ አደጋና ሥጋት ተውጠው የመከራ ዘመናት

አሳልፈዋል። የዮዲት ፍላጉት የክርስትና
ሃያማኖትንን አጥፍታ የአይሁድን እምነት ለማስፈን
ነበር። ይህን በስፋት ይካሂድ የነበረውን ጭፍጨፋ
ለመቋቋም የተሳናቸውና በሥጋት ላያ ወድቀው
የነበሩት የአክሱም መሳፍንትና መኳንንት ፋታና ጊዜ
አግኝተው መልሰው ለማጥቃት እስኪችሉ ድረስ
ሕፃኑን ንጉስ ይዘው ሸዋ ውስጥ ወደሚገኘው ወደ
መንዝ ሸሹ ። መንዝ የተመረጠበትም ዋናው
ምክንያት የመልክዓ ምድሩ አቀማመጥ ገደላማና
ዋሻ በመሆኑ ጠላት ስለማይደፍረው ፥ ገፍቶም
ቢመጣ ለመከላከል አመቺ በመመሆኑ ነበር ።
ዮዲት የክርስትናን ሃይማኖት አጥፍታ የፈላሻን
ሃይማኖት በሰፊው እንዲሰበክና እንዲስፋፋ
ስለፈለገች በአክሱም ሕዝቦች የተገነባውንና ሁለት
ሺህ ዓመታት ያህል አብቦ የቆየውን ሥልጣኔና
የሥልጣኔ ውጤት የሆኑትን ታሪካውያን ሥራዎች
ማፈራረሷን ተያያዘችው ። አብያተ ክርስቲያናትን
ማቃጠልና ካህናትን መግደል የዕለት ሥራዋ ሆነ።
በተለያዩ አጋጣሚዎች ከተረፉትና እስካሁን ድረስ
ካሉት ጥቂቶች በስተቀር ሐውልቶችን ውብ የሆኑ
የሥነ ጥበብ ቅርሶችንሞ አፈራርሳለች፤ አብያተ
ክርስትያናትን አቃጥላለች ። የክርስትና ሃይማኖት

ተከታይ ተራው ሕዝብና ቄሶች ተሰየፉ ።
የመንግሥት ዘርነት የነበራቸው የመሳፍንት ልጆችም
መንግሥቱን አንዳይቀናቀኑና አንዳይሸፍቱ
ሕዝቡንም እንዳያነሣሡ ተብሎ ወደ ደብረ ዳሞ
ተራራ አየተወሰዱ በእስር እንዲቀመጡ ይደረግ
ነበር ።
በቆየው ሥርዓት በዚህ ገዳም ውስጥ የመሳፍንት
ልጆች በቁም አስረኛነት አየተጠበቁ ይቆዩና ንጉሡ
ሲሞት ከመሳፍንቱ ውስጥ ሕዝቡ የመረጠው
ይነግሥ ነበር ። በዚሁ ምክንያት የተሰበሰቡበትን ፬፻
(400) የሚሆኑ የመሳፍንት ልጆች በጅምላ
አሳረደቻቸው። ዮዲት በፈጸመችው ጭካኔ ሥራና
ከፍተኛ ጥረት የተነሣ ተግባሯንና ክፋትዋን
የሚገልጹ የተለያዩ ቅጥያ ስሞች ተስጥቷታል።
በትግራይ ሕዝብ ጉዲት (ጉደኛ) በአፋር ሕዝብ
ጋፅዋ (አስፈሪ አውሬ) በመባል ስትታወቅ በአማራ
ሕዝብም እሳቶ (የምታቃጥል) ብለዋታል። ጉዲት
ሕፃኑን ንጉሥ አንበሳ ውድምን በመንዝ የመደበቁን
ዜና በሰማች ጊዜ ኃይሉን ሰብሮ እሱን ማርኮ
እንዲያመጣ ጦር ልካ ነበር ነገር ግን የላከችው
ሠራዊት በመሸነፉ ሐሳቧ ሳይሰምር ቀረ ። ስለዚህ
አንበሳ ውድምንና ተከታዮቹን አጥፍታ እርካታ

ለማግኘት በማሰብ ራሷ ሠራዊቷን እየመራች ወደ መንዝ ዘመተች። አንበሳ ውድምና ተከታዮቹ ግን ለማጥቃት ይበልጥ አስቸጋሪ ወደ ሆነውና እዚያው ሸዋ ውስጥ ወደሚገኘው ወደ መርሐቤቴ ሸሹ። ዮዲትም በዚሁ ሳትገታ ልትከታተለው ሞክራ ነበር። ይሁን እንጂ ከመሬቱ አቀማመጥ አስቸጋሪነት ሌላ የንጉሡ ወታደሮች የመንዝና የመርሐቤቴ ሕዝብ በየጊዜው ያደርሱባት የነበረው ጥቃት አንድ ላይ ተዳምረው ሰሳደክሚት ዓላማዋ ሳይሳካላት ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ እንደገና እንድትመለስ ተገደደች ።
ከዚህ በ□ላ ለ፲፫ (13) ዓመታት ስትገዛ ቆየች ።
ይህች ጨካኝ ንግሥት አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ቅርሶች ያጠፋችበትን የ፵ (40) ዓመታት ዕድሜ ገዝታ ማክተሚያ ላይ የእብርሃ ወአጽብሐን ቤተክርስቲያን አቃጥላ በምትመለስበት ጊዜ እግዚአብሔር መንገዷን አሳስቶ አዲንፋስ ከሚባለው ቦታ ከፍተኛና አስፈሪ አውሎ ነፋስ አስነሥቶ ወርውሮ አደካውህ ከሚባለው ቦታ ላይ አንደ ጣላትና በዚሁ ምክንያት አንደ ሞተች ብዙ ሊቃውንት ይናገራሉ። መቃብሯም ከውቅሮ ከተማ በታች በሚገኘው አደካውህ አጠገብ የድንጋይ ምልክት ተቀምጦበት ይገኛል ።

ምንጭ:-

1. "የኢትዮጵያ ሥልጣኔ" ፣ በላይ ግደይ፣

መጋቢት ፲፱፻፹፫

2. "ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ"፣ ዘመድኩን በቀ

ለ፣ የካቲት ፲፱፻፺፪

3. "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን

ታሪክ"፣ አቡነ ጎርጎርዮስ፣ ሴኔ ፲፱፻፷፱